# >> የወንጌላት ስምምነትና ንጽጽር <<

በ1954 ዓ. ም. በታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ

መግለጫዎችና መጣጥፎች:-


በሮበርት ኤል ቶማስ እና በስታንሊ ኤን ጉንድሪ

Robert L. Thomas and Stanley N. Gundry



አሳታሚ

የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን

አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

1992 ዓ.ም.

Lapsley/Brooks Foundation

Dallas Texas

2000 A. D.

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

የዚህ መጽሐፍ ምንባቦች የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን፥ ይህም የተደረገው በኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ፈቃድ ነው። ይህ መጽሐፍ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ምርምር ሊውል ይችላል፤ ሆኖም መጽሐፉን ያለ ደራሲው ፈቃድ ኮፒ አድርጎ ለንግድ መጠቀም አይፈቀድም።

የግርጌ ማስታወሻዎቹና አባሪዎቹ የተወሰዱት "The NIV Harmony of the Gospels" copyrighted 1988 by Robert L. Thomas and Stanley N. Gundry ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን የታተመውም በደራሲው ፈቃድ ነው።

አሳታሚ

የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን

ስልክ 201464 ፥ ፖስታ 41221

አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ

1992

Publisher

Lapsley/Brooks Foundation

Dallas, Texas, U.S.A.

2000

# ከአሳታሚው ማስታወሻ

## (የሚነበብ)

ይህን ጠቃሚ መጽሐፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ለሚያደርጉ ኢትዮጵያውያን ስናቀርብ በደስታ ነው።

የጌታን ሕይወትና ሥራዎቹን በታሪካዊ ሂደት ቅደም ተከተል ማቅረብ ዘመናዊ ፈጠራ አይደለም። ወንጌላትን የማስማማት ሥራ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካሄደው በ170 ዓ.ም. ታቲያን በተባለ ንጉሥ አማካይነት ነበር። ይህ ሰው አራቱንም ወንጌላት በመቀላቀል አንድ ታሪክ አወጣ።

በሦስተኛው ክፍለ ዘመን የእስክንድርያው አሞኒየስ የማቴዎስ ወንጌልን እንዳለ በመውሰድ ማርቆስ፥ ሉቃስ፥ እና ዮሐንስ ውስጥ የሚገኙትን ተመሳሳይ ጥቅሶች በማቴዎስ ወንጌል ጥቅሶች ትይዩ አስቀመጣቸው። በእነዚህ ወንጌላት ውስጥ በማቴዎስ ወንጌል ያልተጠቀሱ ነገሮች ባጋጠሙት ጊዜ ጥቅሶቹን ዘሏቸዋል።

በአራተኛው ክፍለ ዘመን የቂሣርያው ዩሲቢየስ አራቱንም ወንጌላት እርስ በርሳቸው በማመሳከር ወንጌላትን የማስማማት ሥራ አካሂዷል።

ከፕሮቴስታንት ተሐድሶ በኋላ በተለያዩ ቋንቋዎች ወንጌላትን የማስማማት ሥራዎች አውሮፓ ውስጥ ቀርበዋል። በ1776 ዓ.ም. ግራይስባክ የተባለ ጀርመናዊ እያንዳንዱን ወንጌል ጎን ለጎን በማስቀመጥ የወንጌላትን ማስማማት ሥራ ለማካሄድ የመጀመሪያው ሰው ሆነ። ይህ መጽሐፍ የተጻፈውም በዚህ መንገድ ነው።

ሁኔታዎችን በትክክለኛው ቅደም ተከተላቸው የማስቀመጡ ችግር ከመጀመሪያ የነበረ ነበር። አንዳንድ ሁኔታዎች በማናቸውም አኳኋን በጌታ ሕይወት ውስጥ ተከስተው ይሆናል። እንዲሁም ጌታ ተመሳሳይ ድርጊቶችን በተለያዩ ጊዜያት አከናውኖ ሊሆን ይችላል።

በዚህ የወንጌላት ማስማማት ሥራ ውስጥ ኤ.ቲ. ሮበርትሰን በመባል የሚታወቀው የግሪክኛ ምሑር ባቀረበው አሳብ መሠረት ለታሪካዊ ሁኔታዎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ቁጥር ሰጥተናቸዋል። ሮበርትሰን በ1893 ዓ.ም. በጆ. ኤ. ብሮደስ የቀረበውን የወንጌላት ማስማማት ሥራ በማደስ፥ የመጀመሪያ ሥራውን በ1922 ዓ.ም. አሳትሟል።

በመጨረሻም፥ ይህን መጽሐፍ በጥንቃቄ ያጠኑት ዘንድ እናበረታታዎታለን። ከጸሎትና ከልብ ከመነጨ እምነት ጋር የጌታን ሕይወት በሚያጠኑበት ጊዜ፥ የራስዎንም ሆነ ትምህርቱን የሚያስተላልፉለትን ሰው ሕይወት እንደሚቀይሩ እምነታችን ነው።

## ምስጋና

ይህ መጽሐፍ ለሕትመት እንዲበቃ ሞያዊ እርዳታ በመስጠት ረገድ የተሳተፉትን ኢትዮጵያውያን በሙሉ፥ በተለይም ገበየሁ አየለ፥ እንግዳሸ ማርቆስ፥ ትፍስህት ለማ፥ ታሕሳስ ክበበው፥ ማስረሻ አባተ ላደረጉት አስተዋጽዎ ከልብ እናመሰግናለን።

# መቅድም

የወንጌላት ተዛምዶ አራቱን ወንጌላት በአንድ ጊዜ ለማጥናት ያስችላል። ምንም እንኳን አራቱ ወንጌላት በተናጠል የሚጠኑበትን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የሚተካ ባይሆን፥ የኢየሱስን ሕይወት በሁሉም አቅጣጫ በሚገባ ለማጥናት ምትክ የማይገኝለት መሣሪያ ነው። የዚህ ጽሑፍ አዘጋጆችም፥ ጽሑፉ ለከፍተኛ የሥነ-መለኮት ተማሪዎች ጠቀሜታ እንዲኖረው በማድረግ አስማምተው አቅር በውታል። ይህም ቢባል የግሪክኛው አዲስ ኪዳን እውቀት የሌለውና በግሉ የሚያጠና ጥንቁቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሚቀርበውን አሳብ በቀላሉ ሊገነዘብ ይችላል። ለከፍተኛ ትምህርት የሚሆኑ ዝርዝርና ረቂቅ ጉዳዮች በዚህ ሥራ ውስጥ አልታከሉም።

በተዛምዶ ጽሑፉ በተጨማሪም ሌሎች ገለጣዎች ታክለዋል። ከክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ቀደም ተከተል የሚቀጥለው የተዛምዶው ንድፍም ይህን መቅድም ይከተላል። ይኸው ንድፍ ከተዛምዶው ጋር ተጣምሯል። ይህን ንድፍ ለአንድ አፍታ መመልከቱ ሁነቶች ከሌላው ጋር በተዛመደ አኳኋን የተከናወኑት መቼ መሆኑን ያስገነዝባል። ማድረጉ በተቻለ ጊዜም እያንዳንዱ ሁነት የተከናወነበት ሥፍራ በተዛምዶው ተገልጧል። የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ምንጭም የተወሰዱበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እየተገለጠ ቀርቧል።

አንድ ሰው የወንጌላትን ተዛምዶ በሚያጠናበት ጊዜ፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በበለጠ እየተረዳ ይሄዳል። የዚህ ዓይነቱ እውቀት ለርሱ የሚኖረንን ፍቅር ያሳድገዋል። ይበልጥ ስንወደው፥ በታማኝነት ይበልጥ እናገለግለዋለን፤ ሁሌም እናከብረዋለን። እግዚአብሔር ይህን አገልግሎት ለሌሎች ፍሬያማ አድርጎ ይቀበለው።

# የተዛምዶው አቀራረብ እና ገጽታ ማብራሪያ

1. የወንጌላት ጽሑፍ። በአንዱ፥ በሁለቱ፥ በሦስቱ ወይም በአራቱም ወንጌላት የተገለጠ ድርጊት ቢሆን፥ በወንጌላቱ ተዛምዶ እያንዳንዱ ገጽ ውስጥ ይገኛል። በዚህ መጽሐፍ የወንጌል ጽሑፍ በአምዶች የተቀናበረ ሲሆን፥ በእያንዳንዱ አምድ ውስጥ ያለው ጉዳይ ተመሳሳይ ከሆኑና ሌላ አምድ ውስጥ ካሉ ጉዳዮች ጋር በመጎራበት ቀርቧል። የአምዶቹ ስፋት በዚያ የንባብ ክፍል ውስጥ ያለውን ድርጊት እንደመዘገቡት ወንጌላት ብዛት ይለያያል። የወንጌላቱ አቀማመጥ ቅደም ተከተል ከግራ ወደ ቀኝ በመሆኑ የአዲስ ኪዳንን አቀማመጥ የተከተለ ነው።

2. የክፍል ቁጥሮች። የወንጌላት ጽሑፍ በክፍሎች የተከፋፈለና ምናልባትም በድርጊቱ ቅደም ተከተል የተቀናበረ ነው። እያንዳንዱ ክፍልም በአርእስቱ መነሻው ላይ ቁጥር ተሰጥቶታል።

3. የክፍል አርእስት። እያንዳንዱ ክፍል አንድ ርእስ ተሰጥቶታል። አርእስቱ ለትንታኔና ለዝርዝር ገለጣ ያመቹ ዘንድ ተጽፏል።

4. መልክዓ ምድራዊ ምልክቶች። ከብዙዎቹ የክፍል አርእስት ግርጌ በሰረዝ ገባ ብሎ የተቀመጠ ቃል ወይም አንቀጽ ይገኛል። ይህ የሚያመለክተው በዚያ ክፍል የተገለጠው ሁነት የተደረገበትን ስፍራ ነው።

5. የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍና ቁጥሮች። በእያንዳንዱ የተዛምዶ ጽሑፍ አምድ አናት ላይ የመጽሐፉ ስም፥ ምዕራፎቹ እና ቁጥሮቹ ሰፍረዋል። እነዚህ የሚያመለክቱት በአምዱ ውስጥ የሚገኘውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ነው።

6. የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች። የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ምንጮች ከእያንዳንዱ ጥቅስ ቀጥሎ በቅንፍ ተመልክተዋል። ቅንፎቹ የሚያመለክቱት እነዚህ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች በተዛምዶው አዘጋጆች የታከሉና የነርሱን አስተያየት የሚገልጡ መሆናቸውን ነው።

7. የተጠቀሱት ጊዜያት የተመለከቱት በአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ነው።

8. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንዳንድ የመጽሐፍ ጥቅሶች ተጨማሪ ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል። እነዚህ ጥቅሶች በግርጌ ማስታወሻዎቹ መጀመሪያ ላይ በቅንፍ ተመልክተዋል።

9. የወንጌላት ጥቅሶች በቅደም ተከተላቸው መሠረት ከሚገኙባቸው ገጾች ጋር በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ በማውጫ ላይ ቀርበዋል።

# ማውጫ

## የኢየሱስ የሕይወት ታሪክ ከልጅነት እስከ እውቀት


| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ምዕራፍ 1፡- ኢየሱስ ማን እንደነበር አጭር መግለጫ** | | | | | |
| 1. ሉቃስ ወንጌልን ለመጻፍ የነበረው ዓላማ | | | 1:1-4 | | 23 |
| 2. የዮሐንስ መቅድም፡- ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ የነበረ ሥጋ የለበሰ ቃል | | | | 1:1-18 | 23 |
| 3. ኢየሱስ በሕጋዊ ረገድ የዮሴፍ፥ በተፈጥሮ ደግሞ የማርያም ዘር መሆኑ | 1:1-17 | | 3:23ለ-38 | | 24 |
| **ምዕራፍ 2፡- የመጥምቁ ዮሐንስ የልጅነት ዓመታት** | | | | | |
| 4. ስለ ዮሐንስ መወለድ ለዘካርያስ የተነገረው ትንቢት | | | 1:5-25 | | 26 |
| 5. ስለ ኢየሱስ መወለድ ለማርያም የተነገራት ትንቢት | | | 1:26-38 | | 27 |
| 6. የማርያም ኤልሳቤጥን መጎብኘት እና የኤልሳቤጥ መዝሙር | | | 1:39-45 | | 27 |
| 7. የማርያም የደስታ መዝሙር | | | 1:46-56 | | 28 |
| 8ሀ. የዮሐንስ መወለድ | | | 1:57-66 | | 28 |
| 8ለ. የዘካርያስ የነቢይነት መዝሙር | | | 1:67-79 | | 29 |
| 8ሐ. የዮሐንስ እድገትና የልጅነት ሕይወት | | | 1:80 | | 29 |
| **ምዕራፍ 3፡- የኢየሱስ ክርስቶስ የልጅነት ዓመታት** | | | | | |
| 9. ስለ ኢየሱስ የመወለድ ሁኔታ ለዮሴፍ እንደተገለጠው | 1:18-25 | | | | 30 |
| 10. የኢየሱስ መወለድ | | | 2:1-7 | | 30 |
| 11. የመላእክት ምስጋና እና የእረኞች ምስክርነት | | | 2:8-20 | | 31 |
| 12. የኢየሱስ መገረዝ | | | 2:21 | | 31 |
| 13. ኢየሱስን ወላጆቹ ቤተ መቅደስ ይዘውት ሲገቡ ስምዖንና ሐና እንዳከበሩት | | | 2:22-38 | | 31 |
| 14. የሰብአ ሰገል ጉብኝት | 2:1-12 | | | | 32 |
| 15. ወደ ግብፅ ሽሽት እና በቤተልሔም የወንድ ልጆች መገደል | 2:13-18 | | | | 33 |
| 16. ወደ ናዝሬት መመለስ | 2:19-23 | | 2:39 | | 34 |
| 17. ኢየሱስ እድገትና የልጅነት ሕይወት | | | 2:40 | | 34 |
| 18. የኢየሱስ የመጀመሪያው የፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም | | | 2:41-50 | | 34 |
| 19. የኢየሱስ ወደ አዋቂነት ማደግ | | | 2:51-52 | | 35 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|

## ምዕራፍ 4፡- የመጥምቁ ዮሐንስ ሐዝባዊ አገልግሎት

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 20. የአገልግሎት መጀመር | | 1:1 | 3:1-2 | | 36 |
| 21. አካሉ፥ አዋጁ፥ እና ጥምቀቱ | 3:1-6 | 1:2-6 | 3:3-6 | | 36 |
| 22. ለፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያን፥ ለተሰበሰቡ ሰዎች፥ ለቀራጮች፥ እና ለወታደሮች ያስተላለፋቸው መልእክቶች | 3:7-10 | | 3:7-14 | | 37 |
| 23. ስለ ክርስቶስ የሰጠው መግለጫ | 3:11-12 | 1:7-8 | 3:15-18 | | 38 |

## ምዕራፍ 5፡- የዮሐንስ አገልግሎት ማብቃትና የክርስቶስ ሕዝባዊአገልግሎት መጀመር

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 24. የኢየሱስ በዮሐንስ መጠመቅ | 3:13-17 | 1:9-11 | 3:21-23ሀ | | 39 |
| 25. የኢየሱስ በበረሃ መፈተን | 4:1-11 | 1:12-13 | 4:1-13 | | 40 |
| 26. ዮሐንስ ለካህናትና ሌዋውያን ስለ ራሱ የሰጠው ምስክርነት | | | | 1:19-28 | 41 |
| 27. ዮሐንስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ የሰጠው ምስክርነት | | | | 1:29-34 | 42 |
| 28. የኢየሱስ የመጀመሪያዎቹ ተከታዮች | | | | 1:35-52 | 43 |
| 29. የኢየሱስ የመጀመሪያ ተአምር፡- ውኃ ወደ ወይንጠጅ መለወጡ | | | | 2:1-11 | 44 |
| 30. ኢየሱስ ከዘመዶቹና ከመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ጋር በቅፍርናሆም ያደረገው ቆይታ | | | | 2:12 | 44 |
| 31. በፋሲካ በዓል የቤተ መቅደሱ የመጀመሪያ ጽዳት | | | | 2:13-22 | 44 |
| 32ሀ. ስለ ኢየሱስ የመጀመሪያ ተአምራት ሕዝቡ የነበረው አስተሳሰብ | | | | 2:23-25 | 45 |
| 32ለ. ኒቆዲሞስ ከኢየሱስ ጋር ያደረገው የአሳብ ልውውጥ | | | | 3:1-21 | 45 |
| 33. የዮሐንስ በኢየሱስ መተካት | | | | 3:22-36 | 46 |
| 34. የኢየሱስ ይሁዳን ለቆ መሄድ | 4:12 | 1:14ሀ | 3:19-20፥ 4:14ሀ | 4:1-4 | 47 |
| 35ሀ. ኢየሱስ ከአንዲት የሰማሪያ ሴት ጋር ያደረገው ውይይት | | | | 4:5-26 | 47 |
| 35ለ. የመንፈሳዊ ፍሬ ፈተና | | | | 4:27-38 | 49 |
| 35ሐ ለሲካር ወንጌል ማድረሱ | | | | 4:39-42 | 49 |
| 36. ገሊላ መድረስ | | | | 4:43-45 | 49 |

## ምዕራፍ 6፡- የክርስቶስ የገሊላ አገልግሎት

> በይሁዳ አካባቢ ተቃውሞ የተነሣ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ <

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 37. የገሊላ አገልግሎት ባሕርይ | 4:17 | 1:14ለ-15 | 4:14ለ-15 | | 50 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 38. በገሊላ ቃና በነበረበት ጊዜ አንድ የቅፍርናሆም ልጅ በኢየሱስ መፈወስ | | | | 4:46-54 | 50 |
| 39. የናዝሬት አገልግሎቱና ተቀባይነት አለማግኘቱ | | | 4:16-31ሀ | | 51 |
| 40. ወደ ቅፍርናሆም መሄዱ | 4:13-16 | | | | 52 |
| > የሐዋርያት መጠራትና በመላው ገሊላ ያደረጉት አገልግሎት < | | | | | |
| 41. የአራቱ መጠራት | 4:18-22 | 1:16-20 | 5:1-11 | | 52 |
| 42. በቅፍርናሆም በምኩራብ ውስጥማስተማሩና ርኩስ መንፈስ ያለባቸውን በመፈወስ ሥልጣንነቱን ማሳየቱ | | 1:21-28 | 4:31ለ-37 | | ባለ 53 |
| 43. የጴጥሮስ አማትና ሌሎች መፈወሳቸው | 8:14-17 | 1:29-34 | 4:38-41 | | 54 |
| 44. ከስምዖንና ከሌሎች ጋር በገሊላ ያደረገው ጉብኝት | 4:23-25 | 1:35-39 | 4:42-44 | | 55 |
| 45. የለምጻሙ ሰው መንጻት ለሕዝቡ ይፋ ሆኖ መወራቱ | 8:2-4 | 1:40-45 | 5:12-16 | | 56 |
| 46. ሽባው ይቅር መባሉና መፈወሱ | 9:1-8 | 2:1-12 | 5:17-26 | | 57 |
| 47ሀ. የማቴዎስ መጠራት | 9:9 | 2:13-14 | 5:27-28 | | 59 |
| 47ለ በማቴዎስ ቤት የተደረገው ግብዣ | 9:10-13 | 2:15-17 | 5:29-32 | | 59 |
| 48. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ከመጾም ፋንታ ለምን ድግስ እንደሚበሉ ለማስረዳት ሦስት ምሳሌዎች ማቅረቡ | 9:14-17 | 2:18-22 | 5:33-39 | | 60 |
| > ስለ ሰንበት አከባበር የተነሣ ውዝግብ እና የኢየሱስ ከአካባቢው ፈቀቅ ማለት < | | | | | |
| 49ሀ. ኢየሱስ በሰንበት ዕለት አንድ ድውይ ፈወሰ | | | | 5:1-9 | 62 |
| 49ለ. ኢየሱስ ሰንበትን በመሻሩና ከአብ ጋር አንድ ነኝ በማለቱ እርሱን ለመግደል የተደረገ ጥረት | | | | 5:10-18 | 62 |
| 49ሐ. የወልድን ከአብ ጋር እኩል መሆን ያመለከተ ገለጣ | | | | 5:19-47 | 63 |
| 50. ደቀ መዛሙርት በሰንበት ዕለት እሸት በመቅጠፋቸው የተፈጠረ ውዝግብ | 12:1-8 | 2:23-28 | 6:1-5 | | 64 |
| 51. እጁ የሰለለችበትን ሰው በሰንበት መፈወስ | 12:9-14 | 3:1-6 | 6:6-11 | | 65 |
| 52. ኢየሱስ ከተለያየ ሥፍራ ከመጡ ብዙ ሰዎች ጋር ወደ ገሊላ ባሕር እልፍ ማለቱ | 12:15-21 | 3:7-12 | | | 66 |
| > የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መመረጥና የተራራው ስብከት < | | | | | |
| 53. አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ተመረጡ | | 3:13-19 | 6:12-16 | | 67 |
| 54ሀ. የተራራው ስብከት መጀመር | 5:1-2 | | 6:17-19 | | 67 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 54ለ. የመንግሥቱ ወራሾች ለሆኑት በረከት፥ ለዚያ ለማይበቁት ደግሞ ወዮታ | 5:3-12 | | 6:20-26 | | 68 |
| 54ሐ. መንግሥቱን በመጠበቅ ወቅት የአኗኗር ኃላፊነት | 5:13-16 | | | | 69 |
| 54መ. ሕግ፥ ጽድቅና መንግሥት | 5:17-20 | | | | 69 |
| 54ሠ. ሕግን በመተርጎም ረገድ ስድስት ማነጻጸሪያዎች | 5:21-48 | | 6:27-30፥ 32-36 | | 69 |
| 54ረ. ሊወገዱ የሚገባቸውና ግብዝነት ያለባቸው ሦስት "የጽድቅ ሥራዎች" | 6:1-18 | | | | 71 |
| 54ሰ. ንፉግነትን፥ የከፋ ፍርድን እና ብልህነት በጎደለው አኳኋን ቅዱስ የሆኑ ነገሮችን ማቃለልን በተመለከተ የቀረቡ ሦስት ክልከላዎች | 6:19-7:6 | | 6:37-42 | | 72 |
| 54ሸ. ተግባርና ድምዳሜው | 7:7-27 | | 6:31፥43-49 | | 73 |
| 54ቀ. የሕዝቡ አጸፋ | 7:28-8:1 | | | | 75 |
| > በማደግ ላይ ያለ ዝናና ለንስሐ የተሰጠው ትኩረት < | | | | | |
| 55. የመቶ አለቃው እምነትና የአገልጋዩ መፈወስ | 8:5-13 | | 7:1-10 | | 75 |
| 56. ናይን በተባለው ሥፍራ የአንዲት መበለት ልጅ ከሞት ተነሣ | | | 7:11-17 | | 76 |
| 57. መጥምቁ ዮሐንስ ከመንግሥት ጋር ያለው ግንኙነት | 11:2-19 | | 7:18-35 | | 77 |
| 58. የኮራዚ እና የቤተ ሳይዳ ከተማዎች ንስሐ ባለመግባታቸው ወየውላችሁ መባላቸው | 11:20-30 | | | | 78 |
| 59. በኃጢአቷ የተጸጸተች ሴት የክርስቶስን እግሮች ሽቶ ቀባቻቸው | | | 7:36-50 | | 79 |
| > የአይሁድ መሪዎች የመጀመሪያ ግልጥ ተቃውሞ < | | | | | |
| 60. ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርትና ከሌሎች ጋር የተደረገ ጉዞ | | | 8:1-3 | | 80 |
| 61. ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን በክርስቶስ ላይ ያቀረቡት ስድብ አዘል ክስ | 12:22-37 | 3:20-30 | | | 81 |
| 62. ክርስቶስ ምልክት እንዲያሳይ ተጠይቆ እምቢ አለ | 12:38-45 | | | | 82 |
| 63. የአዲሱ መንፈሳዊ ዝምድና መገለጥ | 12:46-50 | 3:31-35 | 8:19-21 | | 83 |
| > የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢራት በምሳሌ ተገለጡ < -- ባሕሩ ዳር ለተሰበሰቡ ሕዝቦች -- | | | | | |
| 64ሀ. የምሳሌዎቹ አጀማመር | 13:1-3ሀ | 4:1-2 | 8:4 | | 84 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 64ለ. የአፈሮቹ ምሳሌ | 13:3ለ-23 | 4:3-25 | 8:5-18 | | 84 |
| 64ሐ. የዘሩ ፈጣን እድገት ምሳሌ | | 4:26-29 | | | 87 |
| 64መ. የእንክርዳዱ ምሳሌ | 13:24-30 | | | | 87 |
| 64ሠ. የሰናፍጭ ዛፍ ምሳሌ | 13:31-32 | 4:30-32 | | | 88 |
| 64ረ. ዱቄት ውስጥ ስለተሸሸገ እርሾ የተነገረ ምሳሌ | 13:33-35 | 4:33-34 | | | 88 |
| -- ቤት ውስጥ ለነበሩ ሐዋርያት -- | | | | | |
| 64ሰ. የእንክርዳዱ ምሳሌ ተብራራ | 13:36-43 | | | | 88 |
| 64ሸ. የተሰወረው መዝገብ ምሳሌ | 13:44 | | | | 89 |
| 64ቀ. ዋጋዋ የበዛ እንቁ ምሳሌ | 13:45-46 | | | | 89 |
| 64በ. የመረቡ ምሳሌ | 13:47-50 | | | | 89 |
| 64ተ. የባለቤቱ ምሳሌ | 13:51-53 | | | | 89 |
| > ያልተቋረጠ ተቃውሞ < | | | | | |
| 65. ባሕሩን ማቋረጥና ማዕበሉን መገሰጽ | 8:18፥ 23-27 | 4:35-41 | 8:22-25 | | 90 |
| 66. አጋንንት ያደሩባቸውን የጌርጌሴኖን ሰዎች መፈወስና ከዚያ የተከተለው ተቃውሞ | 8:28-34 | 5:1-20 | 8:26-39 | | 91 |
| 67. ወደ ገሊላ መልስ፥ የኢየሱስን ልብስ የነካች ሴት መፈወስና የኢያሲሮስ ልጅ ከሞት መነሣት | 9:18-26 | 5:21-43 | 8:40-56 | | 93 |
| 68. ሦስት የፈውስ ተአምራትና ሌላው ስድብ አዘል ክስ | 9:27-34 | | | | 96 |
| 69. እምነት የለሿን ናዝሬትን ለመጨረሻ ጊዜ መጎብኘት | 13:54-58 | 6:1-6ሀ | | | 97 |
| > በገሊላ የተደረገ የመጨረሻ ጥረት (ዘመቻ) < | | | | | |
| 70ሀ. የሠራተኞች ጥቂት መሆን | 9:35-38 | 6:6ለ | | | 97 |
| 70ለ. ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሥልጣን መስጠት | 10:1-42 | 6:7-11 | 9:1-5 | | 98 |
| 70ሐ. ሠራተኞች ተላኩ | 11:1 | 6:12-13 | 9:6 | | 101 |
| 71ሀ. ሄሮድስ የኢየሱስን ማንነት ማወቅ ተሳነው | 14:1-2 | 6:14-16 | 9:7-9 | | 101 |
| 71ለ. የመጥምቁ ዮሐንስ መታሠርና የራሱ መቆረጥ | 14:3-12 | 6:17-29 | | | 102 |


## ምዕራፍ 7፡- በገሊላ ዙሪያ የክርስቶስ አገልግሎት


| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| > ስለ ሕይወት እንጀራ የተሰጠ ትምህርት < | | | | | |
| 72ሀ. የሠራተኞች መመለስ | | 6:30 | 9:10ሀ | | 104 |
| 72ለ. ከገሊላ መውጣት | 14:13-14 | 6:31-34 | 9:10ለ-11 | 6:1-3 | 104 |
| 72ሐ. አምስት ሺዎችን መመገብ | 14:15-21 | 6:35-44 | 9:12-17 | 6:4-13 | 105 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 73. ኢየሱስን ለማንገሥ ያለ ጊዜው የተደረገ ሙከራ ተገታ | 14:22-23 | 6:45-46 | | 6:14-15 | 108 |
| 74. በማዕበል በተናወጠ ባሕር ላይ መራመድ | 14:24-33 | 6:47-52 | | 6:16-21 | 108 |
| 75. ጌንሴሬጥ በተባለ ሥፍራ የተከናወነ ፈውስ | 14:34-36 | 6:53-56 | | | 110 |
| 76ሀ. ስለ እውነተኛው የሕይወት እንጀራ የተደረገ ገለጣ | | | | 6:22-59 | 110 |
| 76ለ. ከደቀ መዛሙርት ብዙዎቹ ወደ ኋላ መመለሳቸው | | | | 6:60-71 | 112 |
| > የፈሪሳውያንን፥ የሰዱቃውያንና የሄሮዳውያንን እርሾ አስመልክቶ የተሰጠ ትምህርት < | | | | | |
| 77. ሥርዓታዊ ንጽሕናን ባለመጠበቅ የተፈጠረ ውዝግብ | 15:1-3ሀ፥ 7-9፥ 3ለ-6፥ 10-20 | 7:1-23 | | 7:1 | 113 |
| 78. ለአማኟ ከነናዊት ጢሮስ እና ሲዶና ውስጥ የተደረገላት አገልግሎት | 15:21-28 | 7:24-30 | | | 115 |
| 79ሀ. "አሥር ከተማ" በተባለው ሥፍራ የተከናወነ ፈውስ | 15:29-31 | 7:31-37 | | | 116 |
| 79ለ. "አሥር ከተማ" ውስጥ አራት ሺዎችን መመገብ | 15:32-38 | 8:1-9ሀ | | | 117 |
| 80. ወደ ገሊላ መመለስ እና ከፈሪሳውያን፥ እንዲሁም ከሰዱቃውያን ጋር መጋጨት | 15:39-16:4 | 8:9ለ-12 | | | 118 |
| 81ሀ. ስለ ፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያንና ሄሮዳውያን ስሕተት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | 16:5-12 | 8:13-21 | | | 118 |
| 81ለ. ቤተሳይዳ ውስጥ አንድ ዓይነ ስውር መፈወሱ | | 8:22-26 | | | 119 |
| > መሢሐዊነት በትምህርት ተሰጠ፥ ተረጋገጠ < | | | | | |
| 82. ጴጥሮስ የኢየሱስን መሢሕነት ተናገረ፤ ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገረ የመጀመሪያ ትንቢት | 16:13-20 | 8:27-30 | 9:18-21 | | 120 |
| 83. የክርስቶስ ተቀባይነት ማጣት፥ መሰቀሉ እና ትንሣኤው ለመጀመሪያ ጊዜ በቅድሚያ ስለመነገሩ | 16:21-26 | 8:31-37 | 9:22-25 | | 122 |
| 84. የሰው ልጅ ምጽአትና ፍርድ | 16:27-28 | 8:38-9:1 | 9:26-27 | | 123 |
| 85. የኢየሱስ በተራራ ላይ መለወጥ | 17:1-8 | 9:2-8 | 9:28-36ሀ | | 123 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 86. ስለ ትንሣኤ፥ ስለ ኤልያስ እና ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የተደረገ ውይይት | 17:9-13 | 9:9-13 | 9:36ለ | | 125 |
| > ለሌሎች ስለማሰብ የተሰጡ ትምህርቶች < | | | | | |
| 87. ጋኔን ያደረበት ልጅ መፈወስ እና የእምነት የለሽነት መገሰፅ | 17:14-21 | 9:14-29 | 9:37-43ሀ | | 126 |
| 88. የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለሁለተኛ ጊዜ በቅድሚያ መነገሩ | 17:22-23 | 9:30-32 | 9:43ለ-45 | | 128 |
| 89. የቤተ መቅደስ ግብር ክፍያ | 17:24-27 | | | | 129 |
| 90. በመንግሥት ከሁሉ ስለሚበልጠው ሰው ማንነት የተነሣ ጥያቄና ቶክክር | 18:1-5 | 9:33-37 | 9:46-48 | | 129 |
| 91. አማኞችን ወደ ኃጢአት መገፋፋትን በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | 18:6-14 | 9:38-50 | 9:49-50 | | 130 |
| 92. በደለኛ ወንድምን በይቅርታ ስለመቅረብ | 18:15-35 | | | | 133 |
| > የዳስ በዓልን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የተደረገ ጉዞ < | | | | | |
| 93. ከተከታዮች ፍጹም የሆነ መሰጠት ተጠየቀ | 8:19-22 | | 9:57-62 | | 134 |
| 94. የኢየሱስ የሥጋ ወንድሞች ስላቅ | | | | 7:2-9 | 134 |
| 95. በሰማሪያ ምድር የተደረገ ጉዞ | | | 9:51-56 | 7:10 | 135 |

## ምዕራፍ 8፡- ኢየሱስ ይሁዳ ውስጥ ያደረገው የኋላ አገልግሎቱ

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| > በዳስ በዓል የተጀመረው አገልግሎት < | | | | | |
| 96ሀ. የኢየሱስን አስተምህሮና ተአምራት በተመለከተ የተከሰቱ ልዩ ልዩ አጸፋዎች | | | | 7:11-31 | 136 |
| 96ለ. ኢየሱስን ለመያዝ የተደረገው ሙከራ መክሸፉ | | | | 7:32-52 | 137 |
| 97. በአመንዝራ ለተያዘችው ሴት የኢየሱስ ይቅርታ | | | | 7:53-8:11 | 138 |
| 98. ኢየሱስ የዓለም ብርሃን ነኝ በማለቱ የተፈጠረ ግጭት | | | | 8:12-20 | 139 |
| 99ሀ. ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለው ግንኙነት | | | | 8:21-30 | 139 |
| 99ለ. የኢየሱስ ከአብርሃም ጋር ያለው ግንኙነትና ይህን በመግለጡ የተቃጣበት የድንጋይ ወገራ | | | | 8:31-59 | 140 |
| 100ሀ. ዓይነ ሥውር ሆኖ የተወለደው ሰው መፈወስ | | | | 9:1-7 | 141 |
| 100ለ. የዓይነ ሥውሩ ሰውዬ ጎረቤቶች አጸፋ (አስተያየት) | | | | 9:8-12 | 142 |
| 100ሐ. የዓይነ ሥውሩ በፈሪሳውያን መመርመርና መወገድ | | | | 9:13-34 | 142 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 100መ. ኢየሱስ ራሱን ለዓይነ ሥውሩ መግለጡ | | | | 9:35-38 | 144 |
| 100ሠ. የፈሪሳውያን መንፈሳዊ ዕውርነት | | | | 9:39-41 | 144 |
| 101ሀ. የመልካሙ እረኛና የሌባው ምሳሌ | | | | 10:1-18 | 144 |
| 101ለ. በአይሁድ መካከል የተባባሰው መከፋፈል | | | | 10:19-21 | 145 |
| > ፍቅር ስለተሞላበት አገልግሎትና ስለ ጸሎት የግል ትምህርቶች < | | | | | |
| 102ሀ. የሰባዎቹ መሾም | | | 10:1-16 | | 146 |
| 102ለ. የሰባዎቹ መመለስ | | | 10:17-24 | | 147 |
| 103. የመልካሙ ሳምራዊ ታሪክ | | | 10:25-37 | | 147 |
| 104. የኢየሱስ ማርያምንና ማርታን መጎብኘት | | | 10:38-42 | | 148 |
| 105. ስለ ጸሎት የተሰጠ ትምህርትና ስለ ደፋሩ ወዳጅ የተነገረ ምሳሌ | | | 11:1-13 | | 149 |
| > ከሕግ መምህራንና ከፈሪሳውያን ጋር የተደረገ ሁለተኛ ክርክር < | | | | | |
| 106. ሦስተኛው ስድብ አዘል ክስ እና ሁለተኛው ክርክር | | | 11:14-36 | | 150 |
| 107. ኢየሱስ አንድ ፈሪሳዊ ቤት ምሳ ተጋብዞ ለፈሪሳውያንና ለሕግ መምህራን ያሰማው ወየውላችሁ | | | 11:37-54 | | 151 |
| 108ሀ. ደቀ መዛሙርቱን ስለ ግብዝነት ማስጠንቀቅ | | | 12:1-12 | | 152 |
| 108ለ. ንፉግነትንና በሀብት መተማመንን በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | | | 12:13-34 | | 153 |
| 108ሐ. ለሰው ልጅ መምጣት ዝግጁ ባለመሆን ላይ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | | | 12:35-48 | | 154 |
| 108መ. ሊመጣ ስላለው መለያየት የተነገረ ማስጠንቀቂያ | | | 12:49-53 | | 155 |
| 108ሠ. የአሁኑን ዘመን ከመመርመር መዘናጋትን በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ | | | 12:54-59 | | 155 |
| 109. ሁለት አማራጮች፡- በንስሐ መመለስ ወይም መሞት | | | 13:1-9 | | 156 |
| 110. አንዲት ሕመምተኛ በሰንበት በመፈወሷ የአንድ የምኩራብ አለቃ ተቃውሞ | | | 13:10-21 | | 156 |
| 111. ተሳደበ በማለት ኢየሱስን በመቅደስ መታደስ ዕለት እንደገና ለማሠር ወይም ለመውገር የተደረገ ሙከራ | | | | 10:22-39 | 157 |


## ምዕራፍ 9፡- በፖርያ (በዮርዳኖስ ማዶ) የኢየሱስ አገልግሎት


| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| > የደቀ መዛሙርትነት መሠረት (ደንብ) < | | | | | |
| 112. ከኢየሩሳሌም ወደ ዮርዳኖስ ማዶ | | | | 10:40-42 | 159 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 113ሀ. ስለ ደኅንነትና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለመግባት የተነሣ ጥያቄ | | | 13:22-30 | | 159 |
| 113ለ. ስለ ኢየሱስ ሞት የተደረገ ቅድመ ገለጣ እና ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ማዘኑ | | | 13:31-35 | | 160 |
| 114. ኢየሱስ በሰንበት ዕለት ከአንድ የፈሪሳውያን አለቃ ቤት ለምሳ ተጋብዞ በተገኘበት ሆዱ የተነፋ አንድ ሰው መፈወሱ፥ እና በሥነ ሥርዓቱ ላይ የቀረቡ ሦስት ምሳሌዎች | | | 14:1-24 | | 160 |
| 115. ደቀ መዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ | | | 14:25-35 | | 162 |
| 116. ከኃጢአተኞች ጋር የተደረገ ግንኙነትን በመቀበል ላይ የተነገሩ ምሳሌዎች | | | 15:1-32 | | 162 |
| 117ሀ. የገንዘብን ትክክለኛ አጠቃቀም ለማስተማር የተነገረ ምሳሌ | | | 16:1-13 | | 164 |
| 117ለ. የሀብትን አደገኛነት ለማስተማር የተነገረ ታሪክ | | | 16:14-31 | | 165 |
| 117ሐ. ደቀ መዝሙርትነትን የሚመለከቱ አራት ትምህርቶች | | | 17:1-10 | | 166 |
| 118ሀ. የአልዓዛር ሕመምና ሞት | | | | 11:1-16 | 166 |
| 118ለ. አልዓዛርን ከሞት ማስነሣት | | | | 11:17-44 | 167 |
| 119. ኢየሱስ ይገደል ዘንድ የአይሁድ መሪዎች ውሳኔ | | | | 11:45-54 | 169 |
| > ወደ ኢየሩሳሌም በተደረገ የመጨረሻ ጉዞ ላይ የተቀረቡ ትምህርቶች < | | | | | |
| 120ሀ. ጌታ በሰማርያና በገሊላ በማለፍ ላይ ሳለ አሥር ለምጻሞችን መፈወሱ | | | 17:11-21 | | 170 |
| 120ለ. ስለ ሰው ልጅ ምጽአት የተሰጡ መግለጫዎች | | | 17:22-37 | | 170 |
| 121. ጸሎትን አስመልክቶ የተነገሩ ሁለት ምሳሌዎች:- የማትታክተው መበለት፥ ፈሪሳዊውና ቀራጩ | | | 18:1-14 | | 171 |
| 122. በፍቺ ጉዳይ ላይ ከፈሪሳውያን አስተምህሮ ጋር የተፈጠረ ግጭት | 19:1-12 | 10:1-12 | | | 172 |
| 123. ከመንግሥተ ሰማያት ጋር በተዛመደ ሁኔታ በምሳሌነት የቀረቡ ትንንሽ ልጆች | 19:13-15 | 10:13-16 | 18:15-17 | | 173 |
| 124ሀ. ብልጽግናና መንግሥት | 19:16-30 | 10:17-31 | 18:18-30 | | 174 |
| 124ለ. የባለሀብቱን መብት አስመልክቶ የተነገረ ምሳሌ | 20:1-16 | | | | 177 |
| 125ሀ. ስለ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ለሦስተኛ ጊዜ በቅድሚያ መነገሩ | 20:17-19 | 10:32-34 | 18:31-34 | | 178 |
| 125ለ. በምኞት ስለተሞላ ኩራት የተነገረ ማስጠንቀቂያ | 20:20-28 | 10:35-45 | | | 179 |
| 126. የዓይነ ሥውሩ በርጠሜዎስና የጓደኛው መፈወስ | 20:29-34 | 10:46-52 | 18:35-43 | | 180 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 127ሀ. የዘኪዮስ ደኅንነት ማግኘት | | | 19:1-10 | | 181 |
| 127ለ. የእግዚአብሔር መንግሥት ቢዘገይ እንኳን አማኞች የሚኖርባቸውን ኃላፊነት ለማስተማር የተነገረ ምሳሌ | | | 19:11-28 | | 181 |
| **ምዕራፍ 10፡- የኢየሱስ በግልጥ ለእስራኤል መቅረብና ያስከተለው ግጭት** | | | | | |
| > በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባትና አንዲት የበለስ ዛፍ < | | | | | |
| 128ሀ. ቢታኒያ መድረስ | | | | 11:55-12:1፥ 9-11 | 183 |
| 128ለ. ወደ ኢየሩሳሌም በክብር መግባት | 21:1-3፥ 6-7፥ 4-5፥ 8-11፥ 14-17 | 11:1-11 | 19:29-44 | 12:12-19 | 184 |
| 129ሀ. የበለስ ዛፍ ቅጠል እንጂ ፍሬ ስለታጣባት መረገሟ | 21:18-19ሀ | 11:12-14 | | | 188 |
| 129ለ. ቤተ መቅደሱን ለሁለተኛ ጊዜ ማጥራት | 21:12-13 | 11:15-18 | 19:45-48 | | 189 |
| 130ሀ. አንዳንድ ግሪካውያን ኢየሱስን ለማግኘት መሻታቸው እና የሰው ልጅ ከፍ ከፍ የማለቱ አስፈላጊነት | | | | 12:20-36ሀ | 190 |
| 130ለ. ከተሰበሰበው ሕዝብ ለኢየሱስ የተደረጉ አቀባበሎችና እርሱ ለሕዝቡ የሰጠው መልስ | | | | 12:36ለ-50 | 191 |
| 131. የደረቀችው የበለስ ዛፍ እና ስለ እምነት የተሰጠ ትምህርት | 21:19ለ-22 | 11:19-26 | 21:37-38 | | 191 |
| > በኢየሱስ ሥልጣን ላይ የተነሣ ግልጥ መገዳደር < | | | | | |
| 132ሀ. ሊቀ ካህናት፥ የሕግ መምህራንና የሕዝብ ሽማግሌዎች ስለ ኢየሱስ ሥልጣን መጠየቃቸው | 21:23-27 | 11:27-33 | 20:1-8 | | 193 |
| 132ለ. የኢየሱስ መልሶች ከራሱ ጥያቄዎች ጋር እና ሦስት ምሳሌዎች | 21:28-22:14 | 12:1-12 | 20:9-19 | | 194 |
| 133. ፈሪሳውያን እና የሄሮድስ ወገን የሆኑ ሰዎች ለቄሣር ግብር ስለ መክፈል ኢየሱስን በመጠየቅ ሊያጠምዱት ያደረጉት ሙከራ | 22:15-22 | 12:13-17 | 20:20-26 | | 197 |
| 134. ሰዱቃውያን ስለ ትንሣኤ ያነሡት አደናጋሪ ጥያቄ | 22:23-33 | 12:18-27 | 20:27-40 | | 199 |
| 135. የአንድ ፈሪሳዊ ሕግ ነክ ጥያቄ | 22:34-40 | 12:28-34 | | | 200 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| > ከጠላቶቹ ለተሰነዘሩ መገዳደሮች የኢየሱስ መልስ < | | | | | |
| 136. ክርስቶስ ከዳዊት ጋር እንደ ልጅ እና እንደ ጌታ ያለው ግንኙነት | 22:41-46 | 12:35-37 | 20:41-44 | | 201 |
| 137ሀ. ስለ ፈሪሳውያን እና የሕግ መምህራን የተነገሩ ሰባት ወዮታዎች | 23:1-36 | 12:38-40 | 20:45-47 | | 202 |
| 137ለ. ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ማዘኑ | 23:37-39 | | | | 205 |
| 138. አንዲት መበለት የነበራትን ሁሉ መስጠቷ | | 12:41-44 | 21:1-4 | | 205 |


## ምዕራፍ 11፡- በክርስቶስ የሞት ዝግጅት ላይ የተነገሩ ትንቢቶች


| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| > የደብረዘይት ስብከት፡- ኢየሱስ ስለ ቤተመቅደስና ስለ ዳግም ምጽአቱ በትንቢት ተናገረ < | | | | | |
| 139ሀ. የስብከቱ አጀማመር | 24:1-3 | 13:1-4 | 21:5-7 | | 206 |
| 139ለ. የምጥ መጀመሪያ | 24:4-14 | 13:5-13 | 21:8-19 | | 207 |
| 139ሐ. የጥፋት ርኩሰትና ተከታዩ ሥቃይ | 24:15-28 | 13:14-23 | 21:20-24 | | 209 |
| 139መ. የሰው ልጅ መምጣት | 24:29-31 | 13:24-27 | 21:25-27 | | 211 |
| 139ሠ. ቅርብ፥ ነገር ግን መቼ መሆኑ ያልታወቀው ጊዜ ምልክቶች | 24:32-41 | 13:28-32 | 21:28-33 | | 212 |
| 139ረ. ተግቶ መጠበቅንና ታማኝነትን የሚያስተምሩ አምስት ምሳሌዎች | 24:42-25:30 | 13:33-37 | 21:34-36 | | 213 |
| 139ሰ. በሰው ልጅ መምጫ ጊዜ የሚኖር ፍርድ | 25:31-46 | | | | 215 |
| > አሳልፎ የመስጠት ዝግጅቶች < | | | | | |
| 140. የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን ለማሠርና ለመግደል ያቀዱት ሤራ | 26:1-5 | 14:1-2 | 22:1-2 | | 216 |
| 141. ማርያም ኢየሱስን ለቀብሩ ሽቶ መቀባቷ | 26:6-13 | 14:3-9 | | 12:2-8 | 217 |
| 142. ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት መስማማቱ | 26:14-16 | 14:10-11 | 22:3-6 | | 218 |
| > የመጨረሻው ማዕድ < | | | | | |
| 143. የፋሲካ ማዕድ መሰናዶ | 26:17-19 | 14:12-16 | 22:7-13 | | 218 |
| 144. የፋሲካ ማዕድ መጀመርና፥ ታላቅ ሆኖ ስለመቆጠር በደቀ መዛሙርቱ መሐል የተፈጠረ ክርክር | 26:20 | 14:17 | 22:14-16፥ 24-30 | | 219 |
| 145. የደቀ መዛሙርትን እግር ማጠብ | | | | 13:1-20 | 220 |
| 146. አሳልፎ ሰጪው መታወቁ | 26:21-25 | 14:18-21 | 22:21-23 | 13:21-30 | 221 |
| 147. የጴጥሮስ ክህደት በቅድሚያ መነገሩ | 26:31-35 | 14:27-31 | 22:31-38 | 13:31-38 | 223 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 148. የማዕዱ ማብቃት እና የጌታ እራት ሥርዓት መደንገግ (1ኛ ቆሮ. 11፡23-26) | 26:26-29 | 14:22-25 | 22:17-20 | | 225 |
| > ከደርቡ እስከ ጌቴሴማኒ የተደረገ ጸሎትና ስብከት < | | | | | |
| 149. ስለ ጌታ መድረሻ፥ ስለ አብ፥ እንዲሁም ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነሡ ጥያቄዎች መልስ አገኙ | | | | 14:1-31 | 226 |
| 150ሀ. የወይኑ ግንድና ቅርንጫፎቹ | | | | 15:1-17 | 228 |
| 150ለ. ከዓለም የሚነሣ ተቃውሞ | | | | 15:18-16:4 | 228 |
| 150ሐ. የመንፈስ ቅዱስ መምጣትና አገልግሎቱ | | | | 16:5-15 | 229 |
| 150መ. ስለ ጌታ ትንሣኤ ደስታ በቅድሚያ መነገሩ | | | | 16:16-22 | 230 |
| 150ሠ. የጸሎት መልስ ማግኘትና የሰላም ተስፋ | | | | 16:23-33 | 230 |
| 151. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱና ለሚያምኑ ሁሉ መጸለዩ | | | | 17:1-26 | 231 |
| 152. ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የጸለያቸው ሦስት አስጨናቂ ጸሎቶች | 26:30፥ 36-46 | 14:26፥ 32-42 | 22:39-46 | 18:1 | 232 |


## ምዕራፍ 12፡- የክርስቶስ ሞት


| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| > አልፎ መሰጠትና እስራት < | | | | | |
| 153. ኢየሱስ አልፎ ተሰጠ፥ ታሠረ፥ ብቻውን ተተወ | 26:47-56 | 14:43-52 | 22:47-53 | 18:2-12 | 235 |
| > ፍርድ < | | | | | |
| 154. በአይሁድ ዘንድ የመጀመሪያው ምዕራፍ፤ ኢየሱስ ሐና ፊት መቅረቡ | | | | 18:13-14፥ 19-23 | 238 |
| 155. ሁለተኛው ምዕራፍ በአይሁድ ዘንድ፥ ኢየሱስ ቀያፋ እና ሸንጎ ፊት መቅረቡ | 26:57፥ 59-68 | 14:53፥ 55-65 | 22:54ሀ፥ 63-65 | 18:24 | 239 |
| 156. የጴጥሮስ ክህደቶች | 26:58፥ 69-75 | 14:54፥ 66-72 | 22:54ለ-62 | 18:15-18፥ 25-27 | 241 |
| 157. ሦስተኛው ምዕራፍ በአይሁድ ዘንድ፤ ኢየሱስ በሽማግሌዎች (በሸንጎው) ፊት | 27:1 | 15:1ሀ | 22:66-71 | | 243 |
| 158. የአስቆሮቱ ይሁዳ ጸጸትና ታንቆ መሞት (ሐዋ. ሥራ 1፡18-19) | 27:3-10 | | | | 244 |
| 159. የመጀመሪያው ምዕራፍ በሮማውያን ፊት፥ ጲላጦስ ፊት | 27:2፥ 11-14 | 15:1ለ-5 | 23:1-5 | 18:28-38 | 244 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 160. ሁለተኛው ምዕራፍ በሮማውያን ፊት፥ በሄሮድስ ፊት | | | 23:6-12 | | 247 |
| 161. ሦስተኛው ምዕራፍ በሮማውያን ፊት፥ ጲላጦስ ፊት | 27:15-26 | 15:6-15 | 23:13-25 | 18:39-19:16 | 248 |
| > ስቅለት < | | | | | |
| 162. የሮማውያን ወታደሮች ፌዝ | 27:27-30 | 15:16-19 | | | 252 |
| 163. ወደ ጎልጎታ ጉዞ | 27:31-34 | 15:20-23 | 23:26-33ሀ | 19:17 | 253 |
| 164. የመጀመሪያዎቹ ሦስት የስቅላት ሰዓታት | 27:35-44 | 15:24-32 | 23:33ለ-43 | 19:18፥ 23-24፥ 19-22፥ 25-27 | 255 |
| 165. የመጨረሻዎቹ ሦስት የስቅለት ሰዓታት | 27:45-50 | 15:33-37 | 23:44፥46 | 19:28-30 | 259 |
| 166. የኢየሱስ ሞት ምስክሮች | 27:51-56 | 15:38-41 | 23:45ለ፥ 47-49 | | 260 |
| > ቀብር < | | | | | |
| 167ሀ. የኢየሱስ ሞት መረጋገጥና አስከሬኑን መረካከብ | 27:57-58 | 15:42-45 | 23:50-52 | 19:31-38 | 261 |
| 167ለ. የኢየሱስ አስከሬን መቃብር ውስጥ አረፈ | 27:59-60 | 15:46 | 23:53-54 | 19:39-42 | 263 |
| 168. መቃብሩን ሴቶች ተመለከቱት፥ በወታደሮችም ተጠበቀ. . . | 27:61-66 | 15:47 | 23:55-56 | | 263 |


## ምዕራፍ 13፡- የክርስቶስ ትንሣኤና እርገት


| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| > ባዶው መቃብር < | | | | | |
| 169. መቃብሩ በሴቶች ተጎበኘ | 28:1 | 16:1 | | | 265 |
| 170. ድንጋዩ ተንከባለለ | 28:2-4 | | | | 265 |
| 171. ሴቶቹ ያገኙት ባዶ መቃብር ነው | 28:5-8 | 16:2-8 | 24:1-8 | 20:1 | 265 |
| 172. ጴጥሮስና ዮሐንስ ያገኙት ባዶ መቃብር ነው | | | 24:9-12 | 20:2-10 | 267 |
| > ከእርገት በኋላው መገለጥ < | | | | | |
| 173. ለመግደላዊት ማርያም መታየት | | 16:9-11 | | 20:11-18 | 268 |
| 174. ለሌሎች ሴቶች መታየት | 28:9-10 | | | | 269 |
| 175. ወታደሮች ለአይሁድ ባለሥልጣናት ያቀረቡት ዘገባ | 28:11-15 | | | | 269 |
| 176. ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ለነበሩት ሁለት ደቀ መዛሙርት መታየት | | 16:12-13 | 24:13-32 | | 270 |

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 177. ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ያዩትን ለሌሎቹ መንገራቸው (1ኛ ቆሮ. 15፡5ሀ) | | | 24:33-35 | | 271 |
| 178. ተሰብስበው ለነበሩ አሥር ደቀ መዛሙርት መታየት | | 16:14 | 24:36-43 | 20:19-25 | 271 |
| 179. ለአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት መታየት (1ኛ ቆሮ. 15፡5ለ) | | | | 20:26-31 | 272 |
| 180. ዓሣ በማጥመድ ላይ ለነበሩ ሰባት ደቀ መዛሙርት መታየት | | | | 21:1-25 | 273 |
| 181. በገሊላ ለአሥራ አንዱ መታየት (1ኛ ቆሮ. 15፡6) | 28:16-20 | 16:15-18 | | | 274 |
| 182. የኢየሱስ ወንድም ለሆነው ያዕቆብ መታየት (1ኛ ቆሮ. 15፡7) | | | | | 275 |
| 183. ኢየሩሳሌም ውስጥ ለደቀ መዛሙርቱ መታየት (ሐዋ. ሥራ 1፡3-8) | | | 24:44-49 | | 275 |
| > እርገቱ < | | | | | |
| 184. የክርስቶስ የመጨረሻ በረከትና መለየት (ሐዋ. ሥራ 1፡9-12) | | 16:19-20 | 24:50-53 | | 276 |


## መጣጥፎች


1. ወንጌላትን የማዛመድ ሥራ መርሖችና ችግሮች 279
2. ኢየሱስ የተናገረባቸው ቋንቋዎች 286
3. የክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ቅደም ተከተል 290
4. ኢየሱስ የተሰቀለበት ቀንና ዓመት 295
5. የኢየሱስ ለምርመራ መቅረብ 299
6. የሄሮድስ ቤተሰብ 301

♦ የጥቅሶች ማውጫ በቅደም ተከተል 305

# >> የወንጌላት ስምምነትና ንጽጽር <<

# 1

# ኢየሱስ ማን እንደነበር አጭር መግለጫ

## ♦ ክፍል 1. ሉቃስ ወንጌልን ለመጻፍ የነበረው ዓላማ

<u>ሉቃስ 1፡ 1-4</u>

1-4 የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፥ ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች
የሆኑት እንዳስተላለፉልን፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው
ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ፥ እኔ[1] ደግሞ ስለ ተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ
በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ።

## ♦ ክፍል 2. የዮሐንስ መቅድም፡- ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ የነበረ ሥጋ የለበሰ ቃል

<u>ዮሐንስ 1፡ 1-18</u>

1 በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም
እግዚአብሔር ነበረ። 2 ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።

3 ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። 4 በእርሱ
ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች። 5 ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥
ጨለማም አላሸነፈውም።

6 ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ 7 ሁሉ በእርሱ
በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ። 8 ስለ ብርሃን
ሊመሰክር መጣ እንጂ፥ እርሱ ብርሃን አልነበረም። 9 ለሰው ሁሉ የሚያበራው
እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር።

10 በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥ ዓለሙም አላወቀውም። 11 የእርሱ ወደ
ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። 12 ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ
ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ 13
እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ
ፈቃድ አልተወለዱም።

14 ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም
ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።

15 ዮሐንስ ስለ እርሱ መሰከረ እንዲህም ብሎ ጮኸ፡- ከእኔ በኋላ የሚመጣው
እርሱ ከእኔ በፊት ነበረና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል፤ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነበረ።
16 እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ
ነበርና፤ 17 ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ። 18 መቼም ቢሆን
እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ
ተረከው።

---

[1] [ሉቃስ 1፡3] የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል በመጻፍ ረገድ ምናልባት ብቸኛው አሕዛብ ሳይሆን አይቀርም የሚባለው ሉቃስ (ቈላ. 4፡11፥ 14)፥ ሁለቱን መጻሕፍት፥ ማለት የሉቃስ ወንጌልንና የሐዋርያት ሥራን ጽፏል። እነዚህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለቱ ረጃጅም መጻሕፍት ናቸው። ምንም እንኳ ጳውሎስና ዮሐንስ እያንዳንዳቸው ብዙ መጻሕፍት ቢጽፉም፥ የዳጎሰ ጽሑፍ ከመጻፍ አንጻር፥ ሉቃስ በከህሎቱ የላቀ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ ነው።

## ♦ ክፍል 3. ኢየሱስ በሕጋዊ ረገድ የዮሴፍ፥ በተፈጥሮ ደግሞ የማርያም ዘር መሆኑ

<u>ማቴዎስ 1፡1-17</u>

1 የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ
የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ።
2 አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅም
ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ይሁዳንና
ወንድሞቹን ወለደ፤ 3 ይሁዳም
ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፤
ፋሬስም ኤስሮምን ወለደ፤ 4 ኤስሮምም
አራምን ወለደ፤ አራምም አሚናዳብን
ወለደ፤ አሚናዳብም ነአሶንን ወለደ፤
ነአሶንም ሰልሞንን ወለደ፤ 5 ሰልሞንም
ከራኬብ ቦኤዝን ወለደ፤ ቦኤዝም ከሩት
ኢዮቤድን ወለደ፤ ኢዮቤድም እሴይን
ወለደ፤ 6 እሴይም ንጉሥ ዳዊትን
ወለደ። 7 ሰሎሞንም ሮብዓምን ወለደ፤
ሮብዓምም አቢያን ወለደ፤ አቢያም
አሣፍን ወለደ፤ 8 አሣፍም ኢዮሣፍጥን
ወለደ፤ ኢዮሣፍጥም ኢዮራምን ወለደ፤
ኢዮራምም ዖዝያንን ወለደ፤ 9 ዖዝያንም
ኢዮአታምን ወለደ፤ ኢዮአታምም
አካዝን ወለደ፤ 10 አካዝም ሕዝቅያስን
ወለደ፤ ሕዝቅያስም ምናሴን ወለደ፤
ምናሴም አሞፅን ወለደ፤ 11 አሞፅም
ኢዮስያስን ወለደ፤ ኢዮስያስም በባቢሎን
ምርኮ ጊዜ ኢኮንያንንና ወንድሞቹን
ወለደ። 12 ከባቢሎንም ምርኮ በኋላ
ኢኮንያን ሰላትያልን ወለደ፤ ሰላትያልም
ዘሩባቤልን ወለደ፤ 13 ዘሩባቤልም
አብዩድን ወለደ፤ አብዩድም ኤልያቄምን
ወለደ፤ ኤልያቄምም አዛርን ወለደ፤ 14
አዛርም ሳዶቅን ወለደ፤ ሳዶቅም አኪምን
ወለደ፤ አኪምም ኤልዩድን ወለደ፤ 15
ኤልዩድም አልዓዛርን ወለደ፤
አልዓዛርም ማታንን ወለደ፤ ማታንም
ያዕቆብን ወለደ፤ 16 ያዕቆብም ክርስቶስ
የተባለውን ኢየሱስን የወለደች
የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ።

<u>ሉቃስ 3፡23ለ-38</u>

እንደመሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ፥
የኤሊ ልጅ፥

24 የማቲ ልጅ፥ የሌዊ ልጅ፥ የሚልኪ
ልጅ፥ 25 የዮና ልጅ፥ የዮሴፍ ልጅ፥
የማታትዩ ልጅ፥ የአሞጽ ልጅ፥ የናሆም
ልጅ፥ የኤሲሊም ልጅ 26 የናጌ ልጅ፥
የማአት ልጅ፥ የማታትዩ ልጅ የሴሜይ
ልጅ፥ የዮሴፍ ልጅ፥ 27 የዮዳ ልጅ፥
የዮናን ልጅ፥ የሬስ ልጅ፥ የዘሩባቤል
ልጅ፥ የሰላትያል ልጅ፥ የኔሪ ልጅ፥ 28
የሚልኪ ልጅ፥ የሐዲ ልጅ፥ የዮሳስ ልጅ፥
የቆሳም ልጅ፥ የኤልሞዳም ልጅ፥ የኤር
ልጅ፥ 29 የዮሴዕ ልጅ፥ የኤልዓዘር ልጅ
የዮራም ልጅ፥ የማጣት ልጅ፥ የሌዊ
ልጅ፥ 30 የስምዖን ልጅ፥ የይሁዳ ልጅ፥
የዮሴፍ ልጅ፥ 31 የዮናን ልጅ፥
የኤልያቄም ልጅ፥ የሜልያ ልጅ፥
የማይናን ልጅ፥ የማጣት ልጅ፥ የናታን
ልጅ 32 የዳዊት ልጅ፥ የእሴይ ልጅ፥
የኢዮቤድ ልጅ፥ የቦዔዝ ልጅ፥ የሰልሞን
ልጅ፥ 33 የነአሶን ልጅ፥ የአሚናዳብ
ልጅ፥ የአራም ልጅ፥ የአሮኒ ልጅ፥
የኤስሮም ልጅ፥ 34 የፋሬስ ልጅ፥ የይሁዳ
ልጅ፥ የያዕቆብ ልጅ፥ የይስሐቅ ልጅ፥
የአብርሃም ልጅ፥ የታራ ልጅ፥ 35 የናኮር
ልጅ፥ የሴሮህ ልጅ፥ የራጋው ልጅ፥
የፋሌቅ ልጅ፥ የአቤር ልጅ፥ የሳላ ልጅ፥
36 የቃይንም ልጅ፥ የአርፋክስድ ልጅ፥
የሴም ልጅ፥ የኖኅ ልጅ፥ የላሜህ ልጅ፥
37 የማቱሳላ ልጅ፥ የሄኖክ ልጅ፥ የያሬድ
ልጅ፥ 38 የመላልኤል ልጅ፥ የቃይናን
ልጅ፥ የሄኖስ ልጅ፥ የሴት ልጅ፥ የአዳም
ልጅ፥ የእግዚአብሔር ልጅ።

(ማቴዎስ 1፡ 1-17 የቀጠለ)

17 እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አሥራ አራት ትውልድ፥ ከዳዊትም እስከ ባቢሎን ምርኮ አሥራ አራት ትውልድ፥ ከባቢሎንም ምርኮ እስከ ክርስቶስ[2] አሥራ አራት ትውልድ ነው።

[2] በግሪክኛ "ክርስቶስ" እና በዕብራይስጥ "መሢሕ"፡- የሁለቱም ትርጉም "የተቀባው" ማለት ነው።

# 2

# የመጥምቁ ዮሐንስ የልጅነት ዓመታት

## ♦ ክፍል 4. ስለ ዮሐንስ መወለድ ለዘካርያስ የተነገረው ትንቢት

[ክፍል 5ና 9ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም፡- በመቅደሱ ውስጥ -

<u>ሉቃስ 1፡5-25</u>

5 በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን
ነበረ፤ ሚስቱም ከአሮን ልጆች ነበረች፥ ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ። 6 ሁለቱም በጌታ
ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ። 7
ኤልሳቤጥም መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜያቸው አርጅተው
ነበር።

8 እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል፥ 9 እንደ ካህናት ሥርዓት
ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ[3] ደረሰበት። 10 በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ
በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር።

11 የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው። 12 ዘካርያስም ባየው ጊዜ
ደነገጠ፥ ፍርሃትም ወደቀበት። 13 መልአኩም እንዲህ አለው፡- ዘካርያስ ሆይ፥ ጸሎትህ
ተሰምቶልሃልና አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፥ ስሙንም
ዮሐንስ ትለዋለህ። 14 ደስታና ተድላም ይሆንልሃል፥ በመወለዱም ብዙዎች ደስ
ይላቸዋል። 15 በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፥ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ
አይጠጣም፤ ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፤ 16 ከእስራኤልም
ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል። 17 እርሱም የተዘጋጁትን
ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ፥ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን
ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል።

18 ዘካርያስም መልአኩን፡- እኔ ሽማግሌ ነኝ ምስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን
በምን አውቃለሁ? አለው።

19 መልአኩም መልሶ፡- እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፥
እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር፤ 20 እነሆም፥
በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ፥ ይህ ነገር እስከሚሆን ቀን ድረስ ዲዳ
ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው።

21 ሕዝቡም ዘካርያስን ይጠብቁት ነበር፤ በቤተ መቅደስም ውስጥ ስለ ዘገየ ይደነቁ
ነበር። 22 በወጣም ጊዜ ሊነግራቸው አልቻለም፥ በቤተ መቅደስም ራእይ እንዳየ
አስተዋሉ፤ እርሱም ይጠቅሳቸው ነበር፤ ድዳም ሆኖ ኖረ።

23 የማገልገሉም ወራት ሲፈጸም ወደ ቤቱ ሄደ። 24-25 ከዚህም ወራት በኋላ ሚስቱ
ኤልሳቤጥ ፀነሰችና፡- ነቀፌታዬን ከሰው መካከል ያስወግድልኝ ዘንድ ጌታ
በተመለከተበት ወራት እንዲህ አድርጎልኛል ስትል ራስዋን አምስት ወር ሰወረች።

---

[3] [ሉቃስ 1፡9] እርሱን የመሰሉ ካህናት ብዙ ከመሆናቸው የተነሣ ዘካርያስ ይህን ዕለታዊ አገልግሎት እንዲያከናውን ምናልባት በዕድሜው አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል የተጠየቀው። ይህን በመሰለው ያልተለመደ ሁኔታ እስራኤልን የመወከል ግዴታ ያለጥርጥር ለዚህ ጻድቅ ሰው እጅግ ከብዶት ነበር።

## ♦ ክፍል 5. ስለ ኢየሱስ መወለድ ለማርያም የተነገራት ትንቢት
[ክፍል 4ና 9ን ይመልከቱ]
*- ናዝሬት -*

ሉቃስ 1፡26-38

26 በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፥
27 ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል
ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፥ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። 28 መልአኩም ወደ
እርስዋ ገብቶ፡- ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ
ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት።

29 እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና፡- ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ
ነው? ብላ አሰበች። 30 መልአኩም እንዲህ አላት፡- ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብሔር
ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። 31 እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥
ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። 32 እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ
አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን[4] ይሰጠዋል፤ 33 በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም
ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።

34 ማርያምም መልአኩን፡- ወንድ ስለማላውቅ[5] ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው።

35 መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥
የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ
የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። 36 እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ፥ እርስዋ ደግሞ
በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፥ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ
ወር ነው፤ 37 ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።

38 ማርያምም፡- እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች። መልአኩም
ከእርስዋ ሄደ።

## ♦ ክፍል 6. የማርያም ኤልሳቤጥን መጎብኘት እና የኤልሳቤጥ መዝሙር [ክፍል 7፥ 8ለና 13ን ይመልከቱ]
*- የይሁዳ ተራራዎች -*

ሉቃስ 1፡39-45

39 ማርያምም በዚያ ወራት ተነሥታ ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና
ወጣች፥ 40 ወደ ዘካርያስም ቤት ገብታ ኤልሳቤጥን ተሳለመቻት። 41 ኤልሳቤጥም
የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ፤ በኤልሳቤጥም
መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፥ 42 በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች፡- አንቺ ከሴቶች
መካከል የተባረክሽ ነሽ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። 43 የጌታዬ እናት ወደ እኔ
ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? 44 እነሆ፥ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ
ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና። 45 ከጌታ፤ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች
ብፅዕት ናት።

---

[4] [ሉቃስ 1፡32] ገብርኤል የተጠቀመበት ቋንቋ ያለጥርጥር የሚያመለክተው፥ የእዚህን የእስራኤል መሢሕ ምድራዊ አመራር አስመልክቶ የነበረውን የብሉይ ኪዳን እምነት ነው። ማርያም ከትውልዱ የተገኘችበት ዳዊት፥ ምድራዊ ዙፋን እንደነበረው ሁሉ፥ ተአምራዊ ልደቱ ለማርያም የተተነበየለት የጌታ ዙፋንም እንዲሁ ይሆናል። የኢየሱስ መንግሥት ግን ፍጻሜ የለውም (ሉቃስ 1፡33)።

## ♦ ክፍል 7. የማርያም የደስታ መዝሙር

[ክፍል 6፥ 8ለና 13ን ይመልከቱ]

*- የይሁዳ ተራራዎች -*

<u>ሉቃስ 1፥46-56</u>

46 ማርያምም እንዲህ አለች፡-

47 “ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት
ታደርጋለች፤ 48 የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ
ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ 49 ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ
አድርጎአልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው። 50 ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና
ትውልድ ይኖራል። [መዝ. 103፥17] 51 በክንዱ ኃይል አድርጎአል፤
ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል፤ 52 ገዥዎችን ከዙፋናቸው
አዋርዶአል፤ ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል፤ 53 የተራቡትን በበጎ ነገር
አጥግቦአል፤ ባለ ጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል። [መዝ. 107፥9] 54-55
ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ፥ ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱ ትዝ እያለው
እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶአል።”

56 ማርያምም ሦስት ወር የሚያህል በእርስዋ ዘንድ ተቀመጠች ወደ ቤትዋም
ተመለሰች።

## ♦ ክፍል 8ሀ. የዮሐንስ መወለድ

*- የይሁዳ ተራራዎች -*

<u>ሉቃስ 1፥57-66</u>

57 የኤልሳቤጥም የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ፥ ወንድ ልጅም ወለደች። 58
ጎረቤቶችዋም ዘመዶችዋም ጌታ ምሕረቱን እንዳገነነላት ሰምተው ከእርስዋ ጋር ደስ
አላቸው።

59 በስምንተኛውም ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት መጡ፥ በአባቱም ስም ዘካርያስ ሊሉት
ወደዱ። 60 እናቱ ግን መልሳ፡- አይሆንም፥ ዮሐንስ ይባል እንጂ አለች።

61 እነርሱም፡- ከወገንሽ ማንም በዚህ ስም የተጠራ የለም አሉአት።

62 አባቱንም ማን ሊባል እንዲወድ ጠቀሱት። 63 ብራናም ለምኖ፡- ስሙ ዮሐንስ
ነው ብሎ ጻፈ። ሁሉም አደነቁ። 64 ያንጊዜም አፉ ተከፈተ መላሱም ተፈታ
እግዚአብሔርንም እየባረከ ተናገረ። 65 ለጎረቤቶቻቸውም ሁሉ ፍርሃት ሆነ፤ ይህም
ሁሉ ነገር በይሁዳ በተራራማው አገር ሁሉ ተወራ፤ 66 የሰሙትም ሁሉ፡- እንኪያ
ይህ ሕፃን ምን ይሆን? እያሉ በልባቸው አኖሩት፤ የጌታ እጅ ከእርሱ ጋር ነበረችና።

---

[5] [ሉቃስ 1፥34] ከአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች፥ ሉቃስ ብቻ (በዚህ ክፍል) እና ማቴዎስ፥ ክፍል ዘጠኝ ውስጥ የኢየሱስን ከድንግል መወለድ በግልጥ ያስተምራሉ። ገላትያ 4፡4 ምናልባት ይህን የተለየ ትምህርት የሚመለከት አይደለም። ዮሐንስ 1፥13 ከድንግል መውለድ ጋር የተዛመደ ቋንቋ ተጠቅሞ የክርስቲያኖችን አዲስ ልደት ሲገልጥ፥ በተዘዋዋሪ ይህን እምነት የሚጠቅስ ይመስላል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከጥንት ጀምሮ፥ አስተምህሮው የቀጥተኛ ክርስትና ዋና ክፍል ነበር።

## ♦ ክፍል 8ለ. የዘካርያስ የነቢይነት መዝሙር

[ክፍል 6፥ 7ና 13ን ይመልከቱ]

- የይሁዳ ተራራዎች -

<u>ሉቃስ 1፡67-79</u>

67 አባቱ ዘካርያስም መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና ትንቢት ተናገረ እንዲህም አለ፡-

68 "የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ፥ ጐብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአልና፤
69-70 ከጥንት ጀምሮ በነበሩት በቅዱሳን ነቢያት አፍ እንደ ተናገረ፥ በብላቴናው
በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድን አስነስቶልናል፤ 71 ማዳኑም ከወደረኞቻችንና
ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው፤ [መዝሙር 106፡10] 72-73 እንደዚህ ለአባቶቻችን
ምሕረት አደረገ፤ ለአባታችን ለአብርሃምም የማለውን መሐላውን ቅዱሱን ኪዳን
አሰበ፤ 74-75 በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለ ፍርሃት
በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን። 76 ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፥
የልዑል ነቢይ ትባላለህ፥ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና፤ [ሚልክያስ
3፡1] 77 እንደዚህም የኃጢአታቸው ስርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ
ትሰጣለህ፤ 78 ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጐበኘበት በአምላካችን ምሕረትና
ርኅራኄ ምክንያት ነው፤ 79 ብርሃኑም በጨለማና በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት
ያበራል እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል።" [ኢሳይያስ 9፡1-2]

## ♦ ክፍል 8ሐ. የዮሐንስ እድገትና የልጅነት ሕይወት

- የይሁዳ ምድረ በዳ -

<u>ሉቃስ 1፡80</u>

80 ሕፃኑም አደገ በመንፈስም ጠነከረ፥ ለእስራኤልም እስከ ታየበት ቀን ድረስ በምድረ በዳ ኖረ።

# 3

# የኢየሱስ ክርስቶስ የልጅነት ዓመታት

## ♦ ክፍል 9. ስለ ኢየሱስ የመወለድ ሁኔታ ለዮሴፍ እንደተገለጠው

[ክፍል 4ና 5ን ይመልከቱ]

- ናዝሬት -

<u>ማቴዎስ 1፡ 18-25</u>

18 የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ
ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች።[6] 19 እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት
ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ።

20 እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም
አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን
ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። 21 ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን
ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።

22 በነቢይ ከጌታ ዘንድ፦ 23 እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥
ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው [ኢሳይያስ 7፡ 14] ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ
ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፦ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።

24 ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፤ እጮኛውንም
ወሰደ፤ 25 የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ
አለው።

## ♦ ክፍል 10. የኢየሱስ መወለድ

- ቤተልሔም -

<u>ሉቃስ 2፡ 1-7</u>

1 በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች። 2
ቄሬኔዎስ በሶርያ አገር ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ጽሕፈት ሆነ። 3 ሁሉም
እያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደ ከተማው ሄደ።

4-5 ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ
ቤተ ልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ፥ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው
ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ። 6 በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፥ 7 የበኵር
ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ
ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።

---

[6] [ማቴ. 1፡ 18] ምናልባት ማርያም ዮሐንስ እስኪወለድ ድረስ (ሉቃስ 1፡ 56) ኤልሣቤጥ ዘንድ ስለቆየች ለአራት ወራት ያህል ዮሴፍ አላያትም። ተመልሳ በመጣች ጊዜ እርግዝናዋ ይታወቅ ነበር። በዚህም ሳቢያ ዮሴፍ ከሁለት ነገሮች አንዱን ማድረግ ነበረበት፦ በድንጋይ እንድትወገር ማድረግ (ዘዳግም 22፡ 23-27) ወይም በምሥጢር መፍታት። ይህን ልዩ ሁኔታ ሊገልጥለት መልአክ እስከመጣ ድረስ ዮሴፍ ሁለተኛውን አማራጭ ወስኖ (ሊፈታት) ነበር። ዮሴፍ መልአኩ የነገረውን ማለት በጋብቻው አሳብ መግፋቱን እንደ ጻድቅ ሰው አላሰበውም ነበር። የጽንሱን መሠረታዊ ሁኔታ በተረዳ ጊዜ ግን የፍቺውን አሳብ ተወው።

## ♦ ክፍል 11. የመላእክት ምስጋና እና የእረኞች ምስክርነት

- በቤተልሔም አጠገብ ባለ ሜዳ -

ሉቃስ 2፡8-20

8 በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ። 9
እነሆም፥ የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ፥ ታላቅ
ፍርሃትም ፈሩ። 10 መልአኩም እንዲህ አላቸው፦ እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን
ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ 11 ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት
እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና። 12 ይህም ምልክት ይሆንላችኋል፤
ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግምም ተኝቶ ታገኛላችሁ።

13 ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ። እግዚአብሔርንም
እያመሰገኑ፦

> 14 "ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ
> ፈቃድ" አሉ።

15 መላእክትም ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ በወጡ ጊዜ፥ እረኞቹ እርስ
በርሳቸው፦ እንግዴህ እስከ ቤተ ልሔም ድረስ እንሂድ እግዚአብሔርም የገለጠልንን
ይህን የሆነውን ነገር እንይ ተባባሉ።

16 ፈጥነውም መጡ ማርያምንና ዮሴፍን ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ። 17
አይተውም ስለዚህ ሕፃን የተነገረላቸውን ነገር ገለጡ። 18 የሰሙትን ሁሉ እረኞቹ
በነገሩአቸው ነገር አደነቁ፤ 19 ማርያም[7] ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች
ትጠብቀው ነበር። 20 እረኞችም እንደ ተባለላቸው ስለ ሰሙትና ስላዩት ሁሉ
እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ተመለሱ።

## ♦ ክፍል 12. የኢየሱስ መገረዝ

- ቤተልሔም -

ሉቃስ 2፡21

21 ሊገርዙት ስምንት ቀን በሞላ ጊዜ፥ በማኅፀን ሳይረገዝ በመልአኩ እንደ ተባለ፥
ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ።

## ♦ ክፍል 13. ኢየሱስን ወላጆቹ ቤተ መቅደስ ይዘውት ሲገቡ ስምዖንና ሐና እንዳከበሩት [ክፍል 6፥ 7ና 8ለን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም -

ሉቃስ 2፡22-38

22-24 እንደ ሙሴም ሕግ የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ፥ በጌታ ሕግ፦
የእናቱን ማኅፀን የሚከፍት ወንድ ሁሉ ለጌታ የተቀደሰ ይባላል ተብሎ እንደ ተጻፈ
[ዘጸአት 13፡1፥ 12] በጌታ ፊት ሊያቆሙት፥ በጌታም ሕግ፦ ሁለት ዋሊያ ወይም
ሁለት የርግብ ጫጩቶች እንደ ተባለ፥ መሥዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ኢየሩሳሌም
ወሰዱት። [ዘሌዋውያን 5፡11፥ 12፡8]

---

7 የኢየሱስ እናት ማርያም በሉቃስ ወንጌል መጀመሪያ ክፍል ለሠፈረው ታሪክ ዋና ምንጭ ለመሆኗ ከሚጠቁሙት አመልካቾች አንዱ ሉቃስ 2፡19 ላይ የተጻፈው ቃል ነው።

(ሉቃስ 2፡22-38 የቀጠለ)

25 እነሆም፥ በኢየሩሳሌም ስምዖን የሚባል ሰው ነበር፥ ይህም ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበረ፤ ጻድቅና ትጉህም ነበረ፥ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ። 26 በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር። 27 በመንፈስም ወደ መቅደስ ወጣ፤ ወላጆቹም እንደ ሕጉ ልማድ ያደርጉለት ዘንድ ሕፃኑን ኢየሱስን በአስገቡት ጊዜ፥ 28 እርሱ ደግሞ ተቀብሎ አቀፈው እግዚአብሔርንም እየባረከ እንዲህ አለ፦

29 "ጌታ ሆይ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤

30-31 ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይተዋልና፤

32 ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን [ኢሳይያስ 42፡6፥ 49፡6] ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው።"

33 ዮሴፍና እናቱም ስለ እርሱ በተባለው ነገር ይደነቁ ነበር። 34-35 ስምዖንም ባረካቸው እናቱን ማርያምንም፦ እነሆ፥ የብዙዎች ልብ አሳብ ይገለጥ ዘንድ፥ ይህ በእስራኤል ላሉት ለብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሣታቸው ለሚቃወሙትም ምልክት ተሾሞአል፥ በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል አላት።

36 ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች፤ እርስዋም ከድንግልናዋ ጀምራ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ኖረች፤ 37 እርስዋም ሰማኒያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም አርጅታ ነበር፤ በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር። 38 በዚያችም ሰዓት ቀርባ እግዚአብሔርን አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ስለ እርሱ ትናገር ነበር።

## ♦ ክፍል 14. የሰብአ ሰገል ጉብኝት

- ኢየሩሳሌምና ቤተልሔም -

ማቴዎስ 2፡1-12

1-2 ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በንጉሡ በሄሮድስ[8] ዘመን በተወለደ ጊዜ፥ እነሆ፥ ሰብአ ሰገል፦ የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ።

3 ንጉሡ ሄሮድስም ሰምቶ ደነገጠ፥ ኢየሩሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር፤ 4 የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው። 5-6 እነርሱም፦

"አንቺ ቤተ ልሔም፥ የይሁዳ ምድር፥ ከይሁዳ ገዢዎች ከቶ አታንሺም፤ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንቺ ይወጣልና"

[8] [ማቴ. 2፡1] ይህ ታላቁ ሄሮድስ የሮም መንግሥት ባለሥልጣን ሆኖ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ37-40 ዓመት ዓለም ድረስ እስራኤልን ገዝቷል። ራሱን እንደ "አይሁድ ንጉሥ" ይቆጥር ነበር። ሰብዓሰገል የጠየቁት ጥያቄ በቅናት የታወከ አዕምሮውን ወደከፋ ሁኔታ ቀየረውና እንደለመደው ሌላ ግፍ እንዲፈጽም አደረገው። የሕፃናቱ ጭፍጨፋ (ማቴ. 2፡16፥ ክፍል 15) ሌላ የዙፋን ተቀናቃኝ ለማስወገድ ያደረገው ሙከራ ነበር። የተሰዉት ሕፃናት ግን አንዳንዶች እንደሚያስቡት ብዙ አልነበሩም። ለምሳሌ በዚህ በተለምዶ፥ የንጹሐን ጭፍጨፋ በሚባለው ግድያ ቤተልሄምን በምታክል መንደር ውስጥ ምናልባት ከሃያ ሕፃናት በላይ አልተሰዉም። (መጣጥፍ 63 ይመልከቱ።)

(ማቴዎስ 2፡ 1-12 የቀጠለ)

ተብሎ በነቢይ እንዲህ ተጽፎአልና በይሁዳ ቤተ ልሔም ነው አሉት። [ምክያስ 5፡2]

7 ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን ዘመን ከእነርሱ በጥንቃቄ ተረዳ፥ 8 ወደ ቤተ ልሔምም እነርሱን ሰድዶ፦ ሂዱ፥ ስለ ሕፃኑ በጥንቃቄ መርምሩ፤ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ አላቸው።

9 እነርሱም ንጉሡን ሰምተው ሄዱ፤ እነሆም፥ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር። 10 ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው። 11 ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፥ ወድቀውም ሰገዱለት፥ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት። 12 ወደ ሄሮድስም እንዳይመለሱ በሕልም ተረድተው በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ሄዱ።

## ♦ ክፍል 15. ወደ ግብፅ ሽሽት እና በቤተልሔም የወንድ ልጆች መገደል

- ቤተልሔምና ግብፅ -

ማቴዎስ 2፡ 13-18

13 እነርሱም ከሄዱ በኋላ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ፦ ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ፥ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው።

14-15 እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን በሌሊት ያዘና ከጌታ ዘንድ በነቢይ፦ ልጄን ከግብፅ ጠራሁት የተባለው እንዲፈጸም [ሆሴዕ 11፡1] ወደ ግብፅ ሄደ፥ ሄሮድስም እስኪሞት ድረስ በዚያ ኖረ።

16 ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገል እንደ ተሣለቁበት ባየ ጊዜ እጅግ ተቆጣና ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን በቤተ ልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን፥ ሁለት ዓመት የሆናቸውን ከዚያም የሚያንሱትን ሕፃናት ሁሉ አስገደለ። 17-18 ያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ፥

> "ድምፅ በራማ ተሰማ፥ ልቅሶና ብዙ ዋይታ፤ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች፥ መጽናናትም አልወደደችም፥ የሉምና"

የተባለው ተፈጸመ። [ኤርምያስ 31፡15]

## ♦ ክፍል 16. ወደ ናዝሬት መመለስ

- ግብፅና ናዝሬት -

<u>ማቴዎስ 2፡ 19-23</u>

19 ሄሮድስም ከሞተ በኋላ፥ እነሆ፥ የጌታ
መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ፡-
20 የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና
ተነሣ፥ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ
እስራኤል አገር ሂድ አለ።

21 እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን ያዘና
ወደ እስራኤል አገር ገባ። 22 በአባቱም
በሄሮድስ ፈንታ አርኬላዎስ በይሁዳ እንደ
ነገሠ በሰማ ጊዜ፥ ወደዚያ መሄድን ፈራ፤
በሕልምም ተረድቶ ወደ ገሊላ አገር ሄደ፤
23 በነቢያት፡-[9] ናዝራዊ ይባላል የተባለው
ይፈጸም ዘንድ፥ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ
መጥቶ ኖረ።

<u>ሉቃስ 2:39</u>

39 ሁሉንም እንደ ጌታ ሕግ
ከፈጸሙ በኋላ፥ ወደ ገሊላ ወደ
ከተማቸው ወደ ናዝሬት ተመለሱ።

## ♦ ክፍል 17. የኢየሱስ እድገትና የልጅነት ሕይወት

- ናዝሬት -

<u>ሉቃስ 2፡ 40</u>

40 ሕፃኑም አደገ፥ ጥበብምሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ
በእርሱ ላይ ነበረ።

## ♦ ክፍል 18. የኢየሱስ የመጀመሪያው የፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም

- ኢየሩሳሌም -

<u>ሉቃስ 2፡ 41-50</u>

41 ወላጆቹም በያመቱ በፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ነበር። 42 የአሥራ
ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ፥ እንደ በዓሉ ሥርዓት ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ፤ 43
ቀኖቹንም ከፈጸሙ በኋላ፥ ሲመለሱ ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር፥
ዮሴፍም እናቱም አላወቁም ነበር። 44 ከመንገደኞች ጋር የነበረ ስለ መሰላቸው
የአንድ ቀን መንገድ ሄዱ፥ ከዘመዶቻቸውም ከሚያውቋቸውም ዘንድ ፈለጉት፤ 45

---

[9] [ማቴ. 2፡23] ተለይቶ የሚጠቀስና የዚህ ቃል መነሻ ነው የሚባል የብሉይ ኪዳን ትንቢት የለም። ቃሉ የሚያመለክተው ምናልባት መሢሑን ዝቅ የማድረግና ያለመቀበል ሁኔታን የሚያመለክቱ ትንቢቶችን ይሆናል (እነዚህን ቁጥሮች ያነጻጽሩ፡- መዝ. 22-6-8፥ 13፤ 69፡8፥ 20-21፤ ኢሳ. 11፡1፤ 49፡7፤ 53፡2፥ 5፥ 8፤ ዳን. 9፡26)። በተለይ የሚታወቀው ኢሳ. 11 ላይ የሚገኘው ቃል ሲሆን፥ እሱም "ቅርንጫፍ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተመሠረተበትና "ናዝራዊ" ከሚለው ቃል ጋር የሚስማማው ነው።

<u>(ሉቃስ 2፡41-50 የቀጠለ)</u>

ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። 46 ከሦስት ቀንም በኋላ
በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውም ሲጠይቃቸውም በመቅደስ አገኙት፤ 47
የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና በመልሱ ተገረሙ። 48 ባዩትም ጊዜ ተገረሙ፥
እናቱም፡- ልጄ ሆይ፥ ለምን እንዲህ አደረግህብን? እነሆ፥ አባትህና እኔ እየተጨነቅን
ስንፈልግህ ነበርን አለችው።

49 እርሱም፡- ስለ ምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ
አላወቃችሁምን? አላቸው።[10] 50 እነርሱም የተናገራቸውን ነገር አላስተዋሉም።

## ♦ ክፍል 19. የኢየሱስ ወደ አዋቂነት ማደግ

- ናዝሬት -

<u>ሉቃስ 2፡51-52</u>

51 ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ፥ ይታዘዝላቸውም ነበር። እናቱም ይህን
ነገር ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር። 52 ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም
በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።[11]

---

10 [ሉቃስ 2፡49] እነዚህ በጽሑፍ የሠፈሩ የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ቃላት ናቸው። እግዚአብሔርን “አባቴ” ብሎ ሲጠራ፥ ምናልባት እናቱ፥ “አባትህና እኔ” ብላ ለተናገረችው መልስ መስጠቱ ይሆናል። የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ መሆኑና መለኮትነቱ፥ እንዲሁም ከድንግል መወለዱ፥ ከቃላቱ ጀርባ ተገልጧል (ሉቃስ 10፡21-22፥ ክፍል 102ለ ላይ ያለውን ገለጣ ያነጻጽሩ)።

11 [ሉቃስ 2፡52] ሉቃስ 2፡40 እስከ አሥራ ሁለት ዓመት ድረስ ያለውን የኢየሱስ የልጅነት ዕድሜ በአጭሩ ሲገልጥ፥ ሉቃስ 2፡52 ደግሞ፥ በግምት ከአሥራ ስምንት እስከ ሠላሳ ዓመቱ ያለውን ወደ ጎልማሳነት ማደግ ያቀርባል (ክፍል 24 ውስጥ ሉቃስ 3፡23ን ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)። ስለኋለኛው ጊዜ፥ በዚህ ቁጥር ከተጠቀሰው ባሻገር ዝርዝር መረጃ የለንም። ቢሆንም ስለአሥራ ስምንቱ ዓመታት አንዳንድ ጠቅላላ ዘገባ ሊቀርብ ይችላል። ኢየሱስ ያደገው፥ አንድ ሰፊ ቤተሰብ ውስጥ ባሉ ልጆች መካከል እንዳለ አንጋፋ ሆኖ ነው (ማር. 6፡3፥ ክፍል 69ን ይመልከቱ)። ዮሴፍ ቤተሰቡን ያስተዳድር የነበረው ኢየሱስ ይረዳው በነበረ የአናጺነት ሥራ ነው። ዮሴፍ የሞተው ምናልባት ኢየሱስ ማንነቱን ለሕዝብ ከመግለጡ በፊት ሳይሆን አይቀርም። ከወንጌላትና ከቀደሙት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጥቆማ በመነሣት እናቱ፥ ታናናሽ ወንድሞቹና እህቶቹ የሚያስፈልጋቸውን የሚያቀርብላቸው ኢየሱስ ነበር ለማለት እንችላለን (ማር. 6፡3)። ስለሆነም በሕዝብ ፊት ማገልገሉን እስኪጀምር ድረስ በአናጺነቱ ተግባር የቀጠለ ይመስላል። ቁሳቁሶች፥ ቤት፥ ማረሻ፥ ቀንበር እና የመሳሰሉትን አዘውትሮ በትምህርቱ መጥቀሱ፥ በአናጺ ከሚሠሩት ቁሳቁሶች ጋር የነበረውን ቅርበት ያመለክታል።

# 4

# የመጥምቁ ዮሐንስ ሕዝባዊ አገልግሎት

## ♦ ክፍል 20. የአገልግሎቱ መጀመር

- በይሁዳ ምድረ በዳ -

| ማርቆስ 1፡1 | ሉቃስ 3፡1-2 |
| --- | --- |
| 1 የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ። | 1 ጢባርዮስ[12] ቄሣርም በነገሠ በአሥራ አምስተኛይቱ ዓመት፥ ጴንጤናዊው ጲላጦስም በይሁዳ ሲገዛ፥ ሄሮድስም በገሊላ የአራተኛው ክፍል ገዥ፥ ወንድሙ ፊልጶስም በኢጡርያስ በጥራኮኒዶስም አገር የአራተኛው ክፍል ገዥ፥ ሊሳኒዮስም በሳቢላኒስ የአራተኛው ክፍል ገዥ ሆነው ሳሉ፥ 2 ሐናና ቀያፋም ሊቃነ ካህናት ሳሉ፥ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ። |

## ♦ ክፍል 21. አካሉ፥ አዋጁ፥ እና ጥምቀቱ

[ክፍል 26ን ይመልከቱ]

- በይሁዳ ምድረ በዳና በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ ባለ አገር -

| ማቴዎስ 3፡1-6 | ማርቆስ 1፡2-6 | ሉቃስ 3፡3-6 |
| --- | --- | --- |
| 1-2 በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ፡-[13] መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ። 3 በነቢዩ በኢሳይያስ፡-<br>''የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው | 2-3 እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ [ሚልክያስ 3፡1]<br>''የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ'' [ኢሳይያስ 40፡3]<br>ተብሎ በነቢዩ | 3-6 በነቢዩ በኢሳይያስ ቃል መጽሐፍ፡- [ኢሳይያስ 40፡3-5]<br>''የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ፤ ዐዘቅቱ ሁሉ ይሙላ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉ ዝቅ ይበል፥ ጠማማውም |

---

12 [ሉቃስ 3፡1] የዮሐንስን የአገልግሎት ጊዜ በሚመለከት፥ ሉቃስ አምስት የፖለቲካ መሪዎችና ሁለት የሃይማኖት መሪዎችን መዝግቧል። በቅደም ተከተል ሲቀመጥ፥ የሮም ንጉሠ ነገሥት፥ የሦስቱ የአይሁድ ገዥዎች፥ በስተሰሜን ያለው ግዛት ገዥና የአባትና ልጅ ጥምር የአምልኮ አገዛዞች ናቸው። አቢላ በተባለው ሥፍራ ከተደረገው የከርሠ ምድር ቁፋሮ የተገኘው መረጃ እንደሚያረጋግጠው፥ በጢባሪዮስ ቄሣር አገዛዝ ዘመን (ከ14-37 ዓ.ም.) ሊሳኒዮስ የተባለ ገዥ እንደነበረ ማረጋገጫ ተገኝቷል (መጣጥፍ 3ን ይመልከቱ)።

13 [ማቴ. 3፡1፤ ሉቃስ 3፡3] የመጥምቁ ዮሐንስ ተልእኮ፥ በምሥራቃዊው ሥርዓት መሠረት፥ ከፊት ቀድሞ የንጉሡን መምጣት በማብሠር፥ ሕዝቡ ንጉሡን ለመቀበል ጥርጊያውን እንዲያቀና ከሚደረግ መልእክተኛ ተልእኮ ጋር የሚነጻጸር ነው። ይሁን እንጂ የዮሐንስ ዝግጅት ከሥነ-ምግባርና ከአመለካከት ጋር የተዛመደ ነበር። የእስራኤል ሕዝብ በብሉይ ኪዳን ነቢያት አማካይነት የተነገረላቸውን የተስፋ መንግሥት ፍጻሜ ይቀበሉ ዘንድ ንስሐ አስፈለጋቸው። በዚሁ መሠረት የዮሐንስ ጥምቀት እንዲህ ያለውን የሥነ ምግባር ዝግጅት ለመቀበል የተሰናዱትን የለየ ነበር።

(ማቴዎስ 3፡1-6 የቀጠለ)

ድምፅ” የተባለለት ይህ ነውና። [ኢሳይያስ 40፡3]

4 ራሱም ዮሐንስ የግመል ጠጉር ልብስ ነበረው፥ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና የበረሀ ማር ነበረ። 5 ያን ጊዜ ኢየሩሳሌም ይሁዳም ሁሉ በዮርዳኖስም ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፤ 6 ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር።

(ማርቆስ 1፡2-6 የቀጠለ)

በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ፥

4 ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ። 5 የይሁዳም አገር ሁሉ የኢየሩሳሌምም ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፥ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር። 6 ዮሐንስም የግመል ጠጉር ለብሶ በወገቡ ጠፍር ይታጠቅ አንበጣና የበረሀ ማርም ይበላ ነበር።

(ሉቃስ 3፡3-6 የቀጠለ)

የቀና መንገድ ይሁን፥ ሸካራውም መንገድ ትክክል ይሁን፤ ሥጋም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ ተብሎ እንደ ተጻፈ ለኃጢአት ስርየት የንስሐን ጥምቀት እየሰበከ በዮርዳኖስ ዙሪያ ወዳለችው አገር ሁሉ መጣ።”

## ♦ ክፍል 22. ለፈሪሳውያን፥ ለሰዱቃውያን፥ ለተሰበሰቡ ሰዎች፥ ለቀራጮች፥ እና ለወታደሮች ያስተላለፉቸው መልእክቶች

- በይሁዳ ምድረ በዳና በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ ባለ አገር -

ማቴዎስ 3፡7-10

7 ዳሩ ግን ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ብዙዎች ወደ ጥምቀቱ ሲመጡ ባየ ጊዜ፥ እንዲህ አላቸው፦ እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ ከሚመጣው ቍጣ[14] እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? 8 እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤ 9 በልባችሁም፦ አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ፤ እላችኋለሁና፦ ከነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር ይችላል። 10 አሁንስ ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤

ሉቃስ 3፡7-14

7 ስለዚህ ከእርሱ ሊጠመቁ ለወጡት ሕዝብ እንዲህ ይላቸው ነበር፦ እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ ከሚመጣው ቍጣ[14] እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? 8 እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤ በልባችሁም፦ አብርሃም አባት አለን ማለትን አትጀምሩ፤ ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር እንዲችል እላችኋለሁና። 9 አሁንስ ምሳር ደግሞ በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤ እንግዲህ መልካም ፍሬ

---

14 [ማቴ. 3፡7፤ ሉቃስ 3፡7] “የሚመጣው ቁጣ” የተሰኘውና በሚገባ የታወቀው ሁኔታ፥ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ቀደም ብሎ ይከናወናል። ብሉይ ኪዳን ይህን ጊዜ “ከጌታ ቀን” ጅማሬ ጋር ያገናኘውና፥ የመሢሑ የግዛት ዘመን ዋዜማ ያደርገዋል (ኢሳ. 3፡16-24፤ 13፡9-11፤ ኤር. 30፡7፤ ሕዝ. 38-39፤ አሞጽ 5፡18-19፤ ሰፎ. 1፡14-18ን ከማቴ. 24፡21፤ 1ኛ ተሰ. 1፡10፤ 5፡9፤ ራእይ 6፡16-17 ጋር ያነጻጽሩ)። የመሢሑ ለመምጣት በመጀመሪያ መምጣት ያን ጊዜ በዮሐንስ አእምሮ የታሰበ ነገር አልነበረም። ለነዚያ በአእምሮ ሳልተዘጋጁ ሰዎች የእርሱ መልእክት ይዘት የሚመጣው ፍርድ አስፈሪነት ነበር። የቃል ኪዳኑ ሕዝብ አባል መሆን፥ ብዙ አይሁዳውያን እንዳሰቡት፥ የቃል ኪዳኑ በረከት ተሳታፊ መሆን አልነበረም። በግል የሚደረግ ሥነ-ምግባራዊ ዝግጅትም አስፈላጊ ሆኗል።

(ማቴዎስ 3፡7-10 የቀጠለ)

እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይዳረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።

(ሉቃስ 3፡7-14 የቀጠለ)

የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ
እሳትም ይጣላል።
10 ሕዝቡም፡- እንግዲህ ምን እናድርግ?
ብለው ይጠይቁት ነበር። 11 መልሶም፡-
ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል፥
ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ ይል
ነበር። 12 ቀራጮችም ደግሞ ሊጠመቁ
መጥተው፡- መምህር ሆይ፥ ምን
እናድርግ? አሉት። 13 ከታዘዘላችሁ
አብልጣችሁ አትውሰዱ አላቸው። 14
ጭፍሮችም ደግሞ፡- እኛ ደግሞ ምን
እናድርግ? ብለው ይጠይቁት ነበር።
እርሱም፡- በማንም ግፍ አትሥሩ ማንንም
በሐሰት አትክሰሱ፥ ደመወዛችሁም
ይብቃችሁ አላቸው።

## ♦ ክፍል 23. ስለ ክርስቶስ የሰጠው መግለጫ

[ክፍል 26ን ይመልከቱ]

- በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ ባለ አገር -

ማቴዎስ 3፡11-12

11 እኔስ ለንስሐ በውኃ
አጠምቃችኋለሁ፤
ጫማውን እሸከም ዘንድ
የማይገባኝ ከእኔ በኋላ
የሚመጣው ግን ከእኔ
ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ
በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም
ያጠምቃችኋል፤

12 መንሹም በእጁ ነው፥
አውድማውንም ፈጽሞ
ያጠራል፥ ስንዴውንም
በጎተራው ይከታል፥
ገለባውን ግን በማይጠፋ
እሳት ያቃጥለዋል።

ማርቆስ 1፡7-8

7 ተጎንብሼ የጫማውን
ጠፍር መፍታት የማይገባኝ
ከእኔ የሚበረታ በኋላዬ
ይመጣል። 8 እኔ በውኃ
አጠመቅኋችሁ እርሱ ግን
በመንፈስ ቅዱስ
ያጠምቃችኋል እያለ
ይሰብክ ነበር።

ሉቃስ 3፡15-18

15 ሕዝቡም ሲጠብቁ ሳሉ
ሁሉም በልባቸው ስለ
ዮሐንስ፡- ይህ ክርስቶስ ይሆ
ንን? ብለው ሲያስቡ ነበር፥
16 ዮሐንስ መለሰ፡- እኔስ
በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤
ነገር ግን የጫማውን ጠፍር
መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ
የሚበረታ ይመጣል፤ እርሱ
በመንፈስ ቅዱስና በእሳት
ያጠምቃችኋል፤ 17
መንሹም በእጁ ነው፥
አውድማውንም ፈጽሞ
ያጠራል፥ ስንዴውንም
በጎተራው ይከታል፥
ገለባውን ግን በማይጠፋ
እሳት ያቃጥለዋል አላቸው።
18 ስለዚህ ሕዝቡን በብዙ
ሌላ ምክር እየመከራቸው
ወንጌልን ይሰብክላቸው
ነበር፤

# 5

# የዮሐንስ አገልግሎት ማብቃትና የክርስቶስ ሕዝባዊ አገልግሎት መጀመር

## ♦ ክፍል 24. የኢየሱስ በዮሐንስ መጠመቅ

[ክፍል 27ና 85ን ይመልከቱ]

- በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ በኩል በሚገኘው ቢታንያ[15] -

| ማቴዎስ 3፡13-17 | ማርቆስ 1፡9-11 | ሉቃስ 3፡21-23ሀ |
| --- | --- | --- |
| 13 ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። 14 ዮሐንስ ግን፦ እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር። | 9 በዚያ ወራትም ኢየሱስ ከገሊላ ናዝሬት መጥቶ ከዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ። | |
| 15 ኢየሱስም መልሶ፦ አሁንስ ፍቀድልኝ፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው። ያን ጊዜ ፈቀደለት። | | |
| 16 ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም፥ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ 17 እነሆም፥ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ። | 10 ወዲያውም ከውኃው በወጣ ጊዜ ሰማያት ሲቀደዱ መንፈስም እንደ ርግብ ሲወርድበት አየና፦ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ 11 በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅ ከሰማያት መጣ። | 21 ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ። ሲጸልይም ሰማይ ተከፈተ፥ 22 መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅም ከሰማይ መጣ። |
| | | 23 ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖ ነበር፥ |

15 ይህ ቢታኒያ፥ ኢየሩሳሌም አጠገብ ከነበረው ቢታኒያ የተለየ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል (ክፍል 104ን ይመልከቱ፤ እንዲሁም ከ105-110 ያሉትን ክፍሎች ያነጻጽሩ)።

## ♦ ክፍል 25. የኢየሱስ በበረሃ መፈተን

- በይሁዳ ምድረ በዳ -

**ማቴዎስ 4፥1-11**

1 ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፥ 2 አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ[16] ተራበ። 3 ፈታኝም ቀርቦ፦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው።

4 እርሱም መልሶ፦ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው። [ዘዳግም 8፥3]

5 ከዚህ በኋላ ዲያቢሎስ ወደ ቅድስት ከተማ ወሰደውና እርሱን በመቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ፦

> 6 "መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል"

ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፥ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው። [መዝሙር 91፥11-12]

7 ኢየሱስም፦ ጌታን

**ማርቆስ 1፥12-13**

12 ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው። 13 በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ ከአራዊትም ጋር ነበረ፥

**ሉቃስ 4፥1-13**

1 ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ መልቶበት ከዮርዳኖስ ተመለሰ፥ በመንፈስም ወደ ምድረ በዳ ተመርቶ፥ 2 አርባ ቀን ከዲያብሎስ ተፈተነ። በነዚያም ቀኖች ምንም አልበላም፥ ከተጨረሱም በኋላ ተራበ።

3 ዲያብሎስም፦ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ ይህን ድንጋይ፦ እንጀራ ሁን ብለህ እዘዝ አለው።

4 ኢየሱስም፦ ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል ብሎ መለሰለት። [ዘዳግም 8፥3]

5 ዲያብሎስም ረጅም ወደ ሆነ ተራራ አውጥቶ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ በቅጽበት አሳየው። 6 ዲያብሎስም፦ ይህ ሥልጣን ሁሉ ክብራቸውም ለእኔ ተሰጥቶአል ለምወደውም ለማንም እሰጠዋለሁና ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ 7 ስለዚህ አንተ በእኔ ፊት ብትሰግድ፥ ሁሉ ለአንተ ይሆናል አለው።

---

[16] [ማቴ. 4፡2] በአንቀጹ የተጠቀሱት ሦስት ፈተናዎች የመጡት ኢየሱስ በተጻከመበት በአርባው ቀን መጠናቀቂያ ላይ ነው። ማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የተጠቀሱት ፈተናዎች ቅደም ተከተል፥ ሉቃስ ውስጥ ከተጠቀሱት (ማቴ. 4፡5 ላይ "ከዚያ በኋላ" የሚለውን ያነጻጽሩ) ይልቅ ተመርጧል። ኢየሱስ ዲያብሎስን የተጋፈጠበትን ባለድል ፍጥጫ፥ ከአዳም ጋር (ዘፍጥ. 3) እና በምድረበዳ ከነበሩት እስራኤላውያን ጋር በተነጻጻሪነት ያስቀምጠዋል። ኢየሱስ ለሰይጣን የሰጠውን እያንዳንዱን መልስ የወሰደው፥ የምድረ በዳውን ጉዞ ልምድ ከሚዘረዝረው ከዘዳግም መጽሐፍ ነበር። የበረሃው ውስጥ ሽንፈት አሁን ደግሞ የበረሃው ውስጥ ድል ሆነ። ክርስቲያኖች አሁን በኢየሱስ የማጽናናት ድጋፍ ፈተናን ድል ለማድረግ የእርግጠኝነት መሠረት አላቸው (ዕብ. 2፡18፤ 4፡14-16)።

(ማቴዎስ 4:1-11 የቀጠለ)

አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ደግሞ ተጽፎአል አለው።

8 ደግሞ ዲያቢሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ፡- 9 ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው።

10 ያን ጊዜ ኢየሱስ፡- ሂድ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው። [ዘዳግም 6፡13]

11 ያን ጊዜ ዲያቢሎስ ተወው፥ እነሆም፥ መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር።

(ማርቆስ 1:12-13 የቀጠለ)

መላእክቱም አገለገሉት።

(ሉቃስ 4:1-13 የቀጠለ)

8 ኢየሱስም መልሶ፡- ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል አለው። [ዘዳግም 6፡13]

9-11 ወደ ኢየሩሳሌም ደግሞ ወሰደው፤ በመቅደስም ጫፍ ላይ አቆሞ፡-

> ‘‘ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል፥ እግርህንም በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል’’

ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፥ ከዚህ ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው። [መዝሙር 91፡11-12]

12 ኢየሱስም መልሶ፡- ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎአል አለው። [ዘዳግም 6:16]

13 ዲያቢሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ እስከ ጊዜው ከእርሱ ተለየ።

## ♦ ክፍል 26. ዮሐንስ ለካህናትና ሌዋውያን ስለ ራሱ የሰጠው ምስክርነት [ክፍል 21ና 23ን ይመልከቱ]

- በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ በኩል በሚገኘው ቢታንያ[15] -

(ዮሐንስ 1፡19-28)

19 አይሁድም፡- አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ፥ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው። 20 መሰከረም አልካደምም፤ እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ።

21 እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው ጠየቁት። አይደለሁም አለ። ነቢዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ።

(ዮሐንስ 1፡ 19-28 የቀጠለ)

22 እንኪያስ፡- ማን ነህ? ለላኩን መልስ እንድንሰጥ፤ ስለራስህ ምን ትላለህ? አሉት።

23 እርሱም፡- ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ፡- የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ
የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ። [ኢሳይያስ 40፡3]

24-25 የተላኩትም ከፈሪሳውያን ነበሩና፡- እንኪያስ አንተ ክርስቶስ ወይም ኤልያስ
ወይም ነቢዩ ካይደለህ፥ ስለ ምን ታጠምቃለህ? ብለው ጠየቁት።

26 ዮሐንስ መልሶ፡- እኔ በውኃ አጠምቃለሁ፤ ዳሩ ግን እናንተ የማታውቁት
በመካከላችሁ ቆሞአል፤ 27 እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ፥ ከእኔ በኋላ
የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው አላቸው።

28 ይህ ነገር ዮሐንስ ያጠምቅበት በነበረው በዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ በቤተ ራባ ሆነ።

## ♦ ክፍል 27. ዮሐንስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ስለመሆኑ የሰጠው ምስክርነት [ክፍል 24ን ይመልከቱ]

- በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ በኩል በሚገኘው ቢታንያ -

ዮሐንስ 1፡ 29-34

29 በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፡- እነሆ የዓለምን
ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።[17] 30 አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል፥
ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል ብዬ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነው። 31
እኔም አላውቀውም ነበር፥ ዳሩ ግን ለእስራኤል ይገለጥ ዘንድ ስለዚህ በውኃ
እያጠመቅሁ እኔ መጣሁ።

32 ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ፡- መንፈስ ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ
አየሁ፤ በእርሱ ላይም ኖረ። 33 እኔም አላውቀውም ነበር፥ ዳሩ ግን በውኃ አጠምቅ
ዘንድ የላከኝ እርሱ፡- መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ
የሚያጠምቅ እርሱ ነው አለኝ። 34 እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ
እንደ ሆነ መስክሬአለሁ።

---

[17] [ዮሐ. 1፡29] ዮሐንስ ብሉይ ኪዳንን፥ በተለይም የኢሳይያስን ትንቢቶች የሚያጠና ተማሪ ነበር (ክፍል 21ን ከኢሳ. 40፡3-5 ጋር ያነጻጽሩት)። በመሆኑም በክርስቶስ የማዳን ተግባር ላይ ማትኮሩ አያስደንቅም ("እነሆ የእግዚአብሔር በግ" በማለት ዮሐንስ የተናገረውን ኢሳ. 53፡6-7 ውስጥ ካለው ትንቢት ጋር ያነጻጽሩት)። ይህ ብቻም አይደል የዮሐንስ ትኩረት፥ በፍጻሜው ዘመን የሚሆነው የኢየሱስ ተግባርም ተመልክቷል ("መንግሥት ሰማያት ቀርባለች" ማቴ. 3፡2፥ ክፍል 21)። ሁለቱ የኢየሱስ አገልግሎቶች የሚጣመሩበትን ሁኔታ ዮሐንስ ሙሉ በሙሉ አልተረዳም (ማቴ. 11፡2-3፥ ክፍል 57ን ከ1ኛ ጴጥ. 1፡10-11 ጋር ያነጻጽሩ)። የኢየሱስ የቅርብ ተከታዮች እንኳን ከሞት እስከተነሣበት ዕለት ድረስ ለምን መሞት እንደነበረበት አልተረዱም።

[18] እነዚህ ተከታዮቹ በተለያየ ሁኔታ ነው ወደ ጌታ የመጡት፡- የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በዮሐንስ ምስክርነት (ቁጥር 36)፤ ስምኦን ጴጥሮስ ከእነዚህ ከሁለቱ በአንደኛው ማለት፥ በእንድርያስ ምስክርነት (ቁጥር 40-42)፤ ፊልጶስ በኢየሱስ ጥሪ (ቁጥር 43)፤ ናትናኤል ደግሞ በፊልጶስ ምስክርነት (ቁጥር 46-47)። እያንዳንዳቸው የኢየሱስን መሢሕነት የተቀበሉ ይመስላሉ (ቁጥር 41፥ 45፥ 49)፤ ይህ የሆነው በዮሐንስ ምስክርነት ላይ በመመሥረት ነው (ቁጥር 29፥ 34፥ 36)። ቢሆንም በዚህ ጊዜ ቋሚ ተከታዮቹ አልሆኑም፥ ምክንያቱም ቢያንስ ሁለቱ ዓሣ ወደማጥመድ ተግባራቸው ተመልሰው ነበር። ክፍል 41 ላይ ፊደል (ረ)ን ይመልከቱ።

## ♦ ክፍል 28. የኢየሱስ የመጀመሪያዎቹ ተከታዮች[18]

[ክፍል 41ና 47ሀን ይመልከቱ]

- በዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ በኩል በሚገኘው ቢታንያ እና በገሊላ -

<u>ዮሐንስ 1፡35-52</u>

35 በነገው ደግሞ ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ቆመው ነበር፥ 36 ኢየሱስም
ሲሄድ ተመልክቶ:- እነሆ የእግዚአብሔር በግ አለ።

37 ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሲናገር ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት። 38 ኢየሱስም
ዘወር ብሎ ሲከተሉትም አይቶ:- ምን ትፈልጋላችሁ? አላቸው።

39 እነርሱም:- ረቢ፥ ወዴት ትኖራለህ? አሉት፤ ትርጓሜው መምህር ሆይ ማለት
ነው።

40 መጥታችሁ እዩ አላቸው። መጥተው የሚኖርበትን አዩ፥ በዚያም ቀን በእርሱ
ዘንድ ዋሉ፤ አሥር ሰዓት ያህል ነበረ። 41 ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት
ከሁለቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ። 42 እርሱ አስቀድሞ
የራሱን ወንድም ስምዖንን አገኘውና:- መሲሕን አግኝተናል አለው፤ ትርጓሜውም
ክርስቶስ ማለት ነው።

43 ወደ ኢየሱስም አመጣው። ኢየሱስም ተመልክቶ:- አንተ የዮና ልጅ ስምዖን
ነህ፤ አንተ ኬፋ ትባላለህ አለው፤ ትርጓሜው ጴጥሮስ ማለት ነው።

44 በነገው ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊወጣ ወደደ፥ ፊልጶስንም አገኘና:- ተከተለኝ
አለው። 45 ፊልጶስም ከእንድርያስና ከጴጥሮስ ከተማ ከቤተ ሳይዳ ነበረ።

46 ፊልጶስ ናትናኤልን[19] አግኝቶ:- ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን
የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል አለው።

47 ናትናኤልም:- ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን? አለው። ፊልጶስ:-
መጥተህ እይ አለው።

48 ኢየሱስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ እርሱ:- ተንኰል የሌለበት
በእውነት የእስራኤል ሰው እነሆ አለ።

49 ናትናኤልም:- ከወዴት ታውቀኛለህ? አለው። ኢየሱስም መለሰ:- ፊልጶስ
ሳይጠራህ፥ ከበለስ በታች ሳለህ፥ አየሁህ አለው።

50 ናትናኤልም መለሰ:- መምህር ሆይ፥ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ
የእስራኤል ንጉሥ ነህ አለው። 51 ኢየሱስም መለሰ:- ከበለስ በታች አየሁህ ስላልሁህ
አመንህን? ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ አለው። 52 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥
ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ[20] ላይ ሲወጡና ሲወርዱ
ታያላችሁ አለው።

---

19 [ዮሐ. 1፡45] ናትናኤል ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ቢሆን ኖሮ በተዛማጆቹ ወንጌላት (ማለት ማቴዎስ፥ ማርቆስ፥ ሉቃስ) እና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በተጠቀሱት ዝርዝሮች ውስጥ ምናልባት ከበርጠሜዎስ ጋር ይጠቀስ ነበር። በመሆኑም ከተመረጡት አንዱ ነበር ብሎ በቀኖናዊነት መደምደም አይቻልም።

20 [ዮሐ. 1፡51] "የሰው ልጅ" የሚለው መጠሪያ ጌታ ለራሱ የሰጠው ስያሜ ነበር። የዚህ ስያሜ ምንጩ ዳን. 7፡13-14 ነው። አሰያየሙ መሲሕነቱን ግልጥም፥ የተሸፈነም አድርጎታል። አድማጮች ምናልባት ከኢየሱስ የተረዱትን ያህል ብቻ ስለስያሜው አንብበው ይሆናል። ትርጉሙ ሰፊ ነው፤ መለኮታዊነት፥ ሰብአዊነት፥ የጠፋውን የሰው ዘር መቤዠት እና ሌሎቹ ከሚጠቀሱት መካከል ናቸው።

## ♦ ክፍል 29. የኢየሱስ የመጀመሪያ ተአምር፦ ውኃ ወደ ወይንጠጅ መለወጡ

- በገሊላ ቃና -

<u>ዮሐንስ 2፥1-11</u>

1 በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ፥ የኢየሱስም እናት[21] በዚያ ነበረች፤ 2
ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ። 3 የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ
የኢየሱስ እናት፦ የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው።

4 ኢየሱስም፦ አንቺ ሴት፥ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት።

5 እናቱም ለአገልጋዮቹ፦ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው።

6 አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ
ተቀምጠው ነበር፥ እያንዳንዳቸውም ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር።

7 ኢየሱስም፦ ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሙሉአቸው
አላቸው። እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው።

8 አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው፤ ሰጡትም።

9 አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ
አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር፤ አሳዳሪው ሙሽራውን
ጠርቶ፦ 10 ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ
መናኛውን፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው።

11 ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ
መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።

## ♦ ክፍል 30. ኢየሱስ ከዘመዶቹና ከመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት ጋር በቅፍርናሆም ያደረገው ቆይታ

- ቅፍርናሆም -

<u>ዮሐንስ 2፥12</u>

12 ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርናሆም
ወረደ፥ በዚያም ጥቂት ቀን ኖሩ።

## ♦ ክፍል 31. በፋሲካ በዓል የቤተ መቅደሱ የመጀመሪያ ጽዳት[22]

[ክፍል 129ለን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 2፥13-22</u>

13 የአይሁድ ፋሲካም[23] ቀርቦ ነበር፥ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። 14
በመቅደስም በሬዎችንና በጎችን ርግቦችንም የሚሸጡትን ገንዘብ ለዋጮችንም
ተቀምጠው አገኘ፤ 15 የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም

---

[21] [ዮሐ. 2፥3] መጥምቁ ዮሐንስና ጴጥሮስ በኋላ እንዳደረጉት የኢየሱስ እናትም ተመሳሳይ የማንዛቤ ችግር ነበረባት (ክፍል 57 ውስጥ ማቴ. 11፥2-3፥ ክፍል 83 ውስጥ ደግሞ ማቴ. 16፥22)። እነሱ የኢየሱስን መሢሕነት ቢያውቁም የክብሩን መገለጥ ሁኔታና ጊዜ በተመለከተ ግን ተሳስተው ነበር (ዮሐ. 2፥4)። ኢየሱስ መሢሕነቱን ለማወጅ ሳይሆን፥ የሰዎችን ችግር ለማሟላት ተአምራትን አድርጓል (ዮሐ. 2፥9፥ 11)።

(ዮሐንስ 2፡13-22 የቀጠለ)

ከመቅደስ አወጣቸው፥ የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ ገበታዎቻቸውንም ገለበጠ፥ 16
ርግብ ሻጪዎችንም፦ ይህን ከዚህ ውሰዱ፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት
አላቸው።

17 ደቀ መዛሙርቱም፦ የቤትህ ቅናት ይበላኛል ተብሎ እንደ ተጻፈ አሰቡ።
[መዝሙር 69፡9]

18 ስለዚህ አይሁድ መልሰው፦ ይህን ስለምታደርግ ምን ምልክት ታሳየናለህ?
አሉት።

19 ኢየሱስም መልሶ፦ ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ
አላቸው።

20 ስለዚህ አይሁድ፦ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥
አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። 21 እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ
ይል ነበር። 22 ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ
አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ።

## ♦ ክፍል 32ሀ. ስለ ኢየሱስ የመጀመሪያ ተአምራት ሕዝቡ የነበረው አስተሳሰብ

- ኢየሩሳሌም -

ዮሐንስ 2፡23-25

23 በፋሲካ በዓልም በኢየሩሳሌም ሳለ፥ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች
በስሙ አመኑ፤ 24-25 ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም
ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን
ያውቅ ነበርና።

## ♦ ክፍል 32ለ. ኒቆዲሞስ ከኢየሱስ ጋር ያደረገው የአሳብ ልውውጥ

- ኢየሩሳሌም -

ዮሐንስ 3፡1-21

1 ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤
እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ፦ 2 መምህር ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና
መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን አለው።

3 ኢየሱስም መልሶ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ
በቀር[24] የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።

4 ኒቆዲሞስም፦ ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ
እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው።

[22] ይህ ቤተመቅደስን የማጽዳት ተግባር፥ ክርስቶስ በአገልግሎቱ ማብቂያ ገደማ ካከናወናቸው ነገሮች የተለየ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል (ከክፍል 129 ጋር ያነጻጽሩት)። ዮሐንስ ይህን ክንውን የገለጠበት ቅደም ተከተል፥ መነሻና አገላለጥ፥ ሁለቱ ትረካዎች ሁለት የተለያዩ ክንውኖች መሆናቸውን ያረጋግጣል። በተለይ ከአይሁድ መሪዎች ስግብግብነት አንጻር ሲታይ፥ ቤተመቅደስ ውስጥ የመነገዱን ተግባር እንደገና ለመጀመር ለሦስት ዓመት መዘግየቱ ሰፊ ጊዜ ነው።

(ዮሐንስ 3፥ 1-21 የቀጠለ)

5 ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፡- እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና
ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም። 6 ከሥጋ
የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። 7 ዳግመኛ ልትወለዱ
ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ። 8 ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፥ ድምፁንም
ትሰማለህ፥ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ
የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።

9 ኒቆዲሞስ መልሶ፡- ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለው።

10 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን
አታውቅምን? 11 እውነት እውነት እልሃለሁ፥ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም
እንመሰክራለን፥ምስክራችንንም አትቀበሉትም። 12 ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ
ጊዜ ካላመናችሁ፥ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? 13 ከሰማይም
ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ
ነው። 14-15 ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ
የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።

16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ
እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። 17 ዓለም
በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም
አልላከውምና። 18 በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ
በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል። 19 ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ
መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ፍርዱ ይህ
ነው። 20 ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ
ብርሃን አይመጣም፤ 21 እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ
እንደ ሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።

## ♦ ክፍል 33. የዮሐንስ በኢየሱስ መተካት

- በሳሌም አቅራቢያ በሄኖን -

ዮሐንስ 3፥ 22-36

22 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ይሁዳ አገር መጣ፥ በዚያም
ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ ያጠምቅ ነበር። 23 ዮሐንስም ደግሞ በሳሌም አቅራቢያ በሄኖን
በዚያ ብዙ ውኃ ነበርና ያጠምቅ ነበር፥ 24 እየመጡም ይጠመቁ ነበር ዮሐንስ ገና ወደ
ወኅኒ አልተጨመረም ነበርና። 25 ስለዚህም በዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና በአይሁድ
መካከል ስለ ማንጻት ክርክር ሆነ። 26 ወደ ዮሐንስም መጥተው፡- መምህር ሆይ፥
በዮርዳኖስ ማዶ ከአንተ ጋር የነበረው አንተም የመሰከርህለት፥ እነሆ፥ እርሱ
ያጠምቃል ሁሉም ወደ እርሱ ይመጣሉ አሉት።

---

23 [ዮሐ. 2፥13] ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕዝብ ፊት አገልግሎት የመጀመሩን ቅደም ተከተል በማመልከቱ ረገድ እንደ አውታር ከሚቆጠሩት አራት የፋሲካ በዓላት የመጀመሪያው ነው። (መጣጥፍ 3ን ይመልከቱ።)

24 [ዮሐ. 3፥3] ስለዳግም ልደት ብሉይ ኪዳን ውስጥ በግልጥ አልተጠቀሰም። ወደዚህ ቀረብ የሚሉት አሳቦች፥ ስለ አዲስ ልብ የተጠቀሱት ሲሆኑ፥ አዲሱን ኪዳንና የእስራኤልን መንግሥት በተመለከተ ይፈጸም ከነበረው የበዓል አከባበር ሥነ ሥርዓት ጋር በመጣመር የሚደረጉት ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ክንውኖች ናቸው (ኤር. 31፥31-34፤ ሕዝ. 36፥26-27፤ ኢዩ. 2፥28-32)።

<u>(ዮሐንስ 3፡22-36 የቀጠለ)</u>

27 ዮሐንስ መለሰ፥ እንዲህ ሲል፡- ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው አንዳች ሊቀበል
አይችልም። 28 እናንተ፡- እኔ ክርስቶስ አይደለሁም፥ ነገር ግን፡- ከእርሱ በፊት
ተልኬአለሁ እንዳልሁ ራሳችሁ ትመሰክሩልኛላችሁ። 29 ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ
ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምጽ እጅግ ደስ ይለዋል።
እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ። 30 እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል።

31 ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤ ከምድር የሚሆነው የምድር ነው
የምድሩንም ይናገራል። ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው። 32 ያየውንና
የሰማውንም ይህን ይመሰክራል፥ ምስክሩንም የሚቀበለው የለም። 33 ምስክሩን
የተቀበለ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደ ሆነ አተመ። 34 እግዚአብሔር የላከው
የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና፤ እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና። 35
አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል። 36 በልጁ የሚያምን የዘላለም
ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል
እንጂ ሕይወትን አያይም።

## ♦ ክፍል 34. የኢየሱስ ይሁዳን ለቆ መሄድ[25]

[ክፍል 71ለን ይመልከቱ]

- ከይሁዳ፥ በሰማርያ በኩል ወደ ገሊላ -

<u>ዮሐንስ 4፡1-4</u>

1 እንግዲህ፡- ኢየሱስ ከዮሐንስ ይልቅ ደቀ መዛሙርት ያደርጋል ያጠምቅማል
ማለትን ፈሪሳውያን እንደ ሰሙ ጌታ ባወቀ ጊዜ፥ 2-3 ይሁዳን ትቶ ወደ ገሊላ ደግሞ
ሄደ፤ ዳሩ ግን ደቀ መዛሙርቱ እንጂ ኢየሱስ ራሱ አላጠመቀም። 4 በሰማርያም
ሊያልፍ ግድ ሆነበት።

<u>ሉቃስ 3፡19-20</u>

19 የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስ ግን፥ ስለ ሄሮድያዳ ስለ ወንድሙ ስለ ፊልጶስ
ሚስትና ሄሮድስ ስላደረገው ሌላ ክፉት ሁሉ ዮሐንስ ስለ ገሠጸው፥ 20 ይህን ደግሞ
ከሁሉ በላይ ጨምሮ ዮሐንስን በወኅኒ አገባው።

| <u>ማቴዎስ 4፡12</u> | <u>ማርቆስ 1፡14-ሀ15</u> | <u>ሉቃስ 4፡14ሀ</u> |
|---|---|---|
| 12 ኢየሱስም ዮሐንስ አልፎ እንደ ተሰጠ በሰማ ጊዜ ወደ ገሊላ ፈቀቅ ብሎ ሄደ። | 14-15 ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ. . .(ወደ ገሊላ መጣ።) | 14 ኢየሱስም በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ፤ |

## ♦ ክፍል 35ሀ. ኢየሱስ ከአንዲት የሰማሪያ ሴት ጋር ያደረገው ውይይት

- ሲካር በምትባል የሰማርያ ከተማ -

<u>ዮሐንስ 4፡5-26</u>

5 ስለዚህ ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ በሰጠው ስፍራ አጠገብ ወደምትሆን ሲካር
ወደምትባል የሰማርያ[26] ከተማ መጣ፤ 6 በዚያም የያዕቆብ ጕድጓድ ነበረ። ኢየሱስም
መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጕድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት
ሰዓት ያህል ነበረ።

<u>(ዮሐንስ 4፥5-26 የቀጠለ)</u>

7 ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች። ኢየሱስም፦ ውኃ አጠጪኝ አላት፤
8 ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደው ነበርና።

9 ስለዚህ ሳምራዊቲቱ፦ አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ
መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? አለችው፤ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም
ነበርና።

10 ኢየሱስ መልሶ፦ የእግዚአብሔርን ስጦታና፦ ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን
መሆኑንስ ብታውቂ፥ አንቺ ትለምኚው ነበርሽ የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር አላት።

11 ሴቲቱ፦ ጌታ ሆይ፥ መቅጃ የለህም ጕድጓዱም ጥልቅ ነው፤ እንግዲህ የሕይወት
ውኃ ከወዴት ታገኛለህ? 12 በእውኑ አንተ ይህን ጕድጓድ ከሰጠን ከአባታችን
ከያዕቆብ ትበልጣለህን? ራሱም ልጆቹም ከብቶቹም ከዚህ ጠጥተዋል አለችው።

13 ኢየሱስም መልሶ፦ ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደ ገና ይጠማል፤ 14 እኔ
ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ
ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት።

15 ሴቲቱ፦ ጌታ ሆይ፥ እንዳልጠማ ውኃም ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውኃ
ስጠኝ አለችው።

16 ኢየሱስም፦ ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ አላት። 17 ሴቲቱ መልሳ፦ ባል
የለኝም አለችው። ኢየሱስ፦ ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤ 18 አምስት
ባሎች ነበሩሽና፥ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ
አላት።

19 ሴቲቱ፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ። 20 አባቶቻችን በዚህ
ተራራ ሰገዱ፤ እናንተም፦ ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው
ትላላችሁ አለችው።

21 ኢየሱስም እንዲህ አላት፦ አንቺ ሴት፥ እመኚኝ፥ በዚህ ተራራ ወይም
በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። 22 እናንተስ ለማታውቁት
ትሰግዳላችሁ፤ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን። 23 ነገር ግን
በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም
ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤ 24 እግዚአብሔር መንፈስ
ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።

25 ሴቲቱ፦ ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ አውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን
ይነግረናል አለችው።

26 ኢየሱስ፦ የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት።[27]

---

[25] ኢየሱስ በዚህ ጊዜ ከይሁዳ ወደ ገሊላ የሚሄድበት ሁለት ግልጥ ምክንያቶች ነበሩት፤ እነዚህም ከፈሪሳውያን የሚነሣ ተቃውሞ (ዮሐ. 4፥1-3) እና የመጥምቁ ዮሐንስ መታሠር (ማቴ. 4፥12፤ ማር. 1፥14ሀ፤ ሉቃስ 4፥14ሀ) ናቸው። በሉቃስ አገላለጥ መሠረት ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን ያሠረው፥ የወንድምህን ሚስት ማግባትህ ትክክል አይደለም ብሎ ስለነቀፈው ነበር። ጆሲፈስ በተባለው ዓለማዊ የታሪክ ዘጋቢ አባባል ደግሞ፥ ሄሮድስ ይህን ያደረገው፥ በዮሐንስ አማካይነት የተቃውሞ ንቅናቄ ይነሣብኛል ብሎ ስለፈራ ነው።

[26] [ዮሐ. 4፥5] ከወንጌል ጸሐፊዎች መካከል ሉቃስ እና ዮሐንስ ብቻ ናቸው ለሰማርያና ለሳምራዊያን የተለየ ትኩረት የሰጧቸው። እነዚህ ሁለት ወንጌላት ኢየሱስ አይሁዳውያን ያልሆኑ ሰዎችን ፍላጎት ስለማገልገሉ ያስገነዘቡት፥ በሚጻፉበት ጊዜ አሕዛብ አንባቢያንን በማሰብ የተዘጋጁ በመሆናቸው ነው።

## ♦ ክፍል 35ለ. የመንፈሳዊ ፍሬ ፈተና

- ሲካር በምትባል የሰማርያ ከተማ -

<u>ዮሐንስ 4፥27-38</u>

27 በዚያም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ መጡና ከሴት ጋር በመነጋገሩ ተደነቁ፤[28] ነገር
ግን፦ ምን ትፈልጊያለሽ? ወይም፦ ስለ ምን ትናገራታለህ? ያለ ማንም አልነበረም።

28 ሴቲቱም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ሄደች ለሰዎችም፦ 29 ያደረግሁትን ሁሉ
የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? አለች። 30 ከከተማ ወጥተው
ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።

31 ይህም ሲሆን ሳለ ደቀ መዛሙርቱ፦ መምህር ሆይ፥ ብላ ብለው ለመኑት።

32 እርሱ ግን፦ እናንተ የማታውቁት የምበላው መብል ለእኔ አለኝ አላቸው።

33 ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ፦ የሚበላው አንዳች ሰው አምጥቶለት ይሆንን? ተባባሉ።

34 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፦ የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ
ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው። 35 እናንተ፦ ገና አራት ወር ቀርቶአል መከርም
ይመጣል ትሉ የለምን? እነሆ እላችኋለሁ፥ ዓይናችሁን አንሡ አዝመራውም አሁን
እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ። 36 የሚያጭድ ደመወዝን ይቀበላል፥ የሚዘራና
የሚያጭድም አብረው ደስ እንዲላቸው ለዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል። 37
አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና። 38 እኔም
እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም
በድካማቸው ገባችሁ።

## ♦ ክፍል 35ሐ. ለሲካር ወንጌል ማድረሱ

- ሲካር በምትባል የሰማርያ ከተማ -

<u>ዮሐንስ 4፥39-42</u>

39 ሴቲቱም፦ ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ስለ መሰከረችው ቃል ከዚያች ከተማ
የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት። 40 የሰማርያ ሰዎችም ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ
በእነርሱ ዘንድ እንዲኖር ለመኑት፤ በዚያም ሁለት ቀን ያህል ኖረ። 41 ስለ ቃሉ
ከፊተኞች ይልቅ ብዙ ሰዎች አመኑ፤

42 ሴቲቱንም፦ አሁን የምናምን ስለ ቃልሽ አይደለም፥ እኛ ራሳችን ሰምተነዋልና፤
እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት[29] እንደ ሆነ እናውቃለን ይሉአት ነበር።

## ♦ ክፍል 36. ገሊላ መድረስ

[ክፍል 37፥ 39ና 69ን ይመልከቱ]

- ከሰማርያ ወደ ገሊላ -

<u>ዮሐንስ 4፥43-45</u>

43 ከሁለቱ ቀኖችም በኋላ ከዚያ ወጥቶ ወደ ገሊላ ሄደ። 44 ነቢይ በገዛ አገሩ
እንዳይከበር ኢየሱስ ራሱ መስክሮአልና። 45 ወደ ገሊላም በመጣ ጊዜ፥ የገሊላ ሰዎች
ራሳቸው ደግሞ ለበዓል መጥተው ነበርና በበዓል በኢየሩሳሌም ያደረገውን ሁሉ ስላዩ
ተቀበሉት።

---

[27] [ዮሐ. 4፥26] ይህ ብቻ ነው ኢየሱስ ለፍርድ እስከቀረበ ድረስ መሲሕነቱን የገለጠበት ክፍል። ክፍል 155 ውስጥ ማር. 14፥62ን ይመልከቱ።

# 6

# የክርስቶስ የገሊላ አገልግሎት

## > በይሁዳ አካባቢ ተቃውሞ የተነሣ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ <

### ♦ ክፍል 37. የገሊላ አገልግሎት ባሕርይ[30]

[ክፍል 36፥ 39ና 69ን ይመልከቱ]

- ገሊላ -

| ማቴዎስ 4፡ 17 | ማርቆስ 1:14ለ-15 | ሉቃስ 4፡ 14ለ-15 |
| --- | --- | --- |
| 17 የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ። ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ፡- መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር። | . . . ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየ ሰበከና፡- ዘመኑ[31] ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ። | ስለ እርሱም በዙሪያው ባለችው አገር ሁሉ ዝና ወጣ። 15 እርሱም በምኵራባቸው ያስተምር፥ ሁሉም ያመሰግኑት ነበር። |

### ♦ ክፍል 38. በገሊላ ቃና በነበረበት ጊዜ አንድ የቅፍርናሆም ልጅ በኢየሱስ መፈወስ

[ክፍል 55ን ይመልከቱ]

- በገሊላ ቃና -

ዮሐንስ 4፡46-54

46 ኢየሱስም ውኃውን የወይን ጠጅ ወዳደረገባት ወደ ገሊላ ቃና ዳግመኛ መጣ። በቅፍርናሆምም ልጁ የታመመበት ከንጉሥ ቤት አንድ ሹም ነበረ። 47 እርሱም ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ እንደ መጣ ሰምቶ ልጁ ሊሞት ስላለው ወደ እርሱ ሄደ ወርዶም እንዲፈውስለት ለመነው።

48 ስለዚህም ኢየሱስ፡- “ምልክትና ድንቅ ነገር ካላያችሁ[32] ከቶ አታምኑም” አለው።

49 ሹሙም፡- “ጌታ ሆይ፥ ብላቴናዬ ሳይሞት ውረድ” አለው።

50 ኢየሱስም፡- “ሂድ፤ ልጅህ በሕይወት አለ” አለው።

ሰውዬውም ኢየሱስ የነገረውን ቃል አምኖ ሄደ። 51 እርሱም ሲወርድ ሳለ ባሮቹ ተገናኙትና፡- ብላቴናህ በሕይወት አለ ብለው ነገሩት። 52 እርሱም በኀ የሆነበትን ሰዓት ጠየቃቸው፤ እነርሱም፡- ትናንት በሰባት ሰዓት ንዳዱ ለቀቀው አሉት።

---

[28] [ዮሐ. 4፡27] ደቀ መዛሙርቱ የተደነቁት በኢየሱስ ያልተለመደ ድርጊት ነው። የአይሁድ መምህራን፥ ሴቶች በማንኛውም ሁኔታ ዝቅተኞች ናቸው ብለው ስለሚያምኑ፥ ከነርሱ ጋር አይወያዩም። ይሁን እንጂ፥ ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ጉዳይ ጥያቄ አላነሡም። ምክንያቱም ኢየሱስ የአይሁድ መምህራንን ልማድ እንደማያደርግ አብረውት በቆዩበት ረጅም ጊዜ ተረድተዋል።

[29] [ዮሐ. 4፡42] ዮሐንስ የሳምራውያንን ደኅንነት ማግኘት የመዘገበበት ዘዴ፥ በክርስቶስ የሚገኘው ደኅንነት፥ ዘር ሳይለይ ለሁሉም መሆኑን በአመዛኙ አሕዛብ ለነበሩት አንባቢዎቹ ያስገነዘበበት መንገድ ነው።

(ዮሐንስ 4፡46-54 የቀጠለ)

53 አባቱም ኢየሱስ፡- ልጅህ በሕይወት አለ ባለው በዚያ ሰዓት እንደ ሆነ አወቀ፤
እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር አመነ።

54 ይህም ደግሞ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መጥቶ ያደረገው ሁለተኛ ምልክት
ነው።

## ♦ ክፍል 39. የናዝሬት አገልግሎቱና ተቀባይነት አለማግኘቱ

[ክፍል 36፥ 37ና 69ን ይመልከቱ]

- ናዝሬት -

ሉቃስ 4፡16-31ሀ

16 ወዳደጉበትም ወደ ናዝሬት መጣ፤ እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ
ገባ፥ ሊያነብም ተነሣ። 17-19 የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፥
መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ፡- [ኢሳይያስ 61፡1-2]

"የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ።"

20 መጽሐፉንም ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና ተቀመጠ፤ በምኩራብም የነበሩት
ሁሉ ትኩር ብለው ይመለከቱት ነበር። 21 እርሱም፡- ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ
ተፈጸመ ይላቸው ጀመር።

22 ሁሉም ይመሰክሩለት ነበር ከአፉም ከሚወጣው ከጸጋው ቃል የተነሣ
እየተደነቁ፡- ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? ይሉ ነበር።

23 እርሱም፡- ያለ ጥርጥር ይህን ምሳሌ፡- ባለ መድኃኒት ሆይ፥ ራስህን ፈውስ፤
በቅፍርናሆም እንዳደረግኸው የሰማነውን ሁሉ በዚህ በገዛ አገርህ ደግሞ አድርግ
ትሉኛላችሁ አላቸው።

24 እንዲህም አለ፡- እውነት እላችኋለሁ፥ ነቢይ በገዛ አገሩ ከቶ አይወደድም። 25
ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፥ በኤልያስ ዘመን ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሰማይ
ተዘግቶ ሳለ በምድር ሁሉ ብርቱ ራብ በነበረ ጊዜ፥ በእስራኤል ብዙ መበለቶች ነበሩ፤
26 ኤልያስም በሲዶና አገር ወዳለች ወደ ሰራፕታ ወደ አንዲት መበለት እንጂ
ከእነርሱ ወደ አንዲቱ አልተላከም። 27 በነቢዩ በኤልሳዕ ዘመንም በእስራኤል ብዙ
ለምጻሞች ነበሩ፥ ከሶርያዊው ከንዕማን በቀር ከእነርሱ አንድ ስንኳ አልነጻም።

28 በምኩራብም የነበሩ ሁሉ ይህን ሰምተው ቍጣ ሞላባቸው፥ ተነሥተውም
ከከተማ ወደ ውጭ አወጡት፥ 29 ይጥሉትም ዘንድ ከተማቸው ተሠርታባት ወደ
ነበረች ወደ ተራራው አፋፍ ወሰዱት፤ 30 እርሱ ግን በመካከላቸው አልፎ ሄደ።

31 ወደ ገሊላ ከተማም ወደ ቅፍርናሆም ወረደ።

---

[30] ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ ገሊላ ውስጥ ስላለፈው ጊዜ በወንጌላቸው ውስጥ ብዙ ሥፍራ ይሰጣሉ። የወቅቶቹ የመጀመሪያ ክፍል ያድግ የነበረውንና በመጨረሻ፥ ምናልባትም በተራራው ስብከት መዳረሻ ገደማ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰውን ተወዳጅነት ያመለክታል። በዚህ ወቅት ሰንበትን በማክበር ጉዳይ በአይሁድ የተጀመረው ተከታታይ ተቃውሞም ታይቷል። ይህ ከዳር የደረሰው፥ የአይሁድ መሪዎች በኢየሱስ ላይ ግልጥ ተቃውሞ ባደረጉ ጊዜ ነበር። ያ ወቅት ወደፍጻሜው ሲቃረብ፥ ኢየሱስ ተቀባይ ልቦና ላላቸው እውነትን ለመግለጥና፥ ልባቸው ከደነደነባቸው ሚስጥሩን ለመደበቅ ሲል ምሳሌያዊ ትምህርቱን በግልጥ ጀመረ።

## ♦ ክፍል 40. ወደ ቅፍርናሆም መሄዱ

- ቅፍርናሆም -

<u>ማቴዎስ 4፡13-16</u>

13 ናዝሬትንም ትቶ በዛብሎንና በንፍታሌም አገር በባሕር አጠገብ ወደ አለችው ወደ
ቅፍርናሆም[33] መጥቶ ኖረ። 14-16 በነቢዩም በኢሳይያስ፡- የዛብሎን ምድርና
የንፍታሌም ምድር፥ የባሕር መንገድ፥ በዮርዳኖስ ማዶ፥ የአሕዛብ ገሊላ፤ በጨለማ
የተቀመጠው ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፥ በሞት አገርና ጥላ ለተቀመጡትም ብርሃን
ወጣላቸው። [ኢሳይያስ 9፡1-2]

# > የሐዋርያት መጠራትና በመላው ገሊላ ያደረጉት አገልግሎት <

## ♦ ክፍል 41. የአራቱ መጠራት

[ክፍል 28ና 47ሀን ይመልከቱ]

- በገሊላ ባሕር አጠገብ፥ በቅፍርናሆም አቅራቢያ -

<u>ማቴዎስ 4፡18-22</u>

18 በገሊላ ባሕር አጠገብ
ሲመላለስም ሁለት
ወንድማማች ጴጥሮስ
የሚሉትን ስምዖንን
ወንድሙንም እንድርያስን
መረባቸውን ወደ ባሕር
ሲጥሉ አየ፥ ዓሣ
አጥማጆች ነበሩና። 19
እርሱም፦ በኋላዬ ኑና
ሰዎችን አጥማጆች
እንድትሆኑ
አደርጋችኋለሁ አላቸው።
20 ወዲያውም
መረባቸውን ትተው
ተከተሉት።

21 ከዚያም እልፍ ብሎ
ሌሎችን ሁለት
ወንድማማች የዘብዴዎስን
ልጅ ያዕቆብን ወንድ
ሙንም ዮሐንስን
ከአባታቸው ከዘብዴዎስ
ጋር በታንኳ መረባቸውን
ሲያበጁ አየ፤
ጠራቸውም። 22 እነርሱም
ወዲያው ታንኳይቱንና
አባታቸውን ትተው
ተከተሉት።

<u>ማርቆስ 1፡16-20</u>

16 በገሊላ ባሕርም
አጠገብ ሲያልፍ ስምዖንን
ወንድሙንም እንድርያስን
መረባቸውን ወደ ባሕር
ሲጥሉ አየ፥ ዓሣ አጥማጆች
ነበሩና። 17 ኢየሱስም፡-
በኋላዬ ኑና ሰዎችን
አጥማጆች እንድትሆኑ
አደርጋችኋለሁ አላቸው።
18 ወዲያውም መረባቸውን
ትተው ተከተሉት።

19 ከዚያም ጥቂት እልፍ
ብሎ የዘብዴዎስን ልጅ
ያዕቆብን ወንድሙንም
ዮሐንስን ደግሞ በታንኳ
ላይ መረባቸውን ሲያበጁ
አየ። 20 ወዲያውም
ጠራቸው አባታቸውንም
ዘብዴዎስን ከሞያተኞቹ
ጋር በታንኳ ላይ ትተው
ተከትለውት ሄዱ።

<u>ሉቃስ 5፡1-11</u>

1 ሕዝቡም
የእግዚአብሔርን ቃል
እየሰሙ ሲያስጠብቡት
ሳሉ፥ እርሱ ራሱ
በጌንሳሬጥ ባሕር ዳር ቆሞ
ነበር፤ 2 በባሕር ዳርም
ቆመው የነበሩትን ሁለት
ታንኳዎች አየ፤ ዓሣ
አጥማጆች ግን ከእነርሱ
ውስጥ ወጥተው
መረቦቻቸውን ያጥቡ
ነበር። 3 ከታንኳዎቹም
የስምዖን ወደ ነበረች ወደ
አንዲቱ ገብቶ ከምድር
ጥቂት ፈቀቅ
እንዲያደርጋት ለመነው፤
በታንኳይቱም ተቀምጦ
ሕዝቡን ያስተምር ነበር።

4 ነገሩንም ከጨረሰ
በኋላ፥ ስምዖንን፡- ወደ
ጥልቁ ፈቀቅ በል
መረቦቻችሁንም
ለማጥመድ ጣሉ አለው።

5 ስምዖንም መለሰ፡-
አቤቱ፥ ሌሊቱን ሁሉ
አድረን ስንደክም ምንም

(ሉቃስ 5፡ 1-11 የቀጠለ)

አልያዝንም፤ ነገር ግን በቃልህ መረቦቼን እጥላለሁ አለው።

6 ይህንም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፤ መረቦቻቸውም ተቀደዱ። 7 በሌላ
ታንኳም የነበሩትን ጓደኞቻቸውን መጥተው እንዲያግዙአቸው ጠቀሱ፤ መጥተውም
ሁለቱ ታንኳዎች እስኪሰጥሙ ድረስ ሞሉአቸው።

8 ስምዖን ጴጥሮስ ግን ባየ ጊዜ በኢየሱስ ጉልበት ላይ ወድቆ፦ ጌታ ሆይ፥ እኔ
ኃጢአተኛ ነኝና ከኔ ተለይ አለው። 9 ስላጠመዱት ዓሣ እርሱ ከእርሱ ጋርም የነበሩ
ሁሉ ተደንቀዋልና፥ 10 እንዲሁም ደግሞ የስምዖን ባልንጀሮች የነበሩ የዘብዴዎስ
ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ተደነቁ።

ኢየሱስም ስምዖንን፦ አትፍራ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ
አለው። 11 ታንኳዎችንም ወደ ምድር አድርሰው ሁሉን ትተው ተከተሉት።

## ♦ ክፍል 42. በቅፍርናሆም[34] በምኩራብ ውስጥ ማስተማሩና ርኩስ መንፈስ ያለባቸውን በመፈወስ ባለሥልጣንነቱን ማሳየቱ

- በቅፍርናሆም፥ ምኵራብ ውስጥ -

ማርቆስ 1፡ 21-28

21 ወደ ቅፍርናሆምም ገቡ፤ ወዲያውም
በሰንበት ወደ ምኵራብ ገብቶ አስተማረ።
22 እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበር
እንጂ እንደ ጻፎች አይደለምና በትምህርቱ
ተገረሙ። 23 በዚያን ጊዜም በምኩራ
ባቸው ርኵስ መንፈስ ያለው ሰው ነበረ፤
24 እርሱም፦ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥
ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን
መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄአለሁ፥

ሉቃስ 4፡ 31ለ-37

በሰንበትም ያስተምራቸው ነበር፤ 32
ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ
ተገረሙ።

33 በምኵራብም የርኵስ ጋኔን መንፈስ
ያደረበት ሰው ነበረ፥ በታላቅ ድምፅም
ጮኸ፦ 34 ተው፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ
ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን
መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄሃለሁ፥
አንተ የእግዚአብሔር ቅዱሱ አለ።

---

31 [ማር. 1፡ 15] በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር የጊዜ ፕሮግራም መጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮ ነው። የመጀመሪያው የክርስቶስ ምጽዓት (ገላ. 4፡4) እና ሁለተኛው (ሐዋ. 1፡7፤ 3፡ 19-21) እግዚአብሔር ለዓለም ታሪክ ላለው ፕሮግራም መሠረቶች ናቸው።

32 [ዮሐ. 4፡48] ኢየሱስ የንጉሡን ቤት ሹም መገሰጹ ሳይሆን፥ በገሊላውያን አስተሳሰብ ማዘኑን መግለጡ ነበር። ሹሙ በኢየሱስ ቃል ሙሉ እምነት በማሳየቱ ከሌሎቹ የተለየ ነበር (ዮሐ. 4፡ 50)።

33 [ማቴ. 4፡ 13] ኢየሱስ ናዝሬት ውስጥ ተቃውሞ ከገጠመው በኋላ፥ ቅፍርናሆም አዲሱ ሥፍራው ሆነ። ቅፍርናሆም የቀረጥ ቢሮ (ማቴ. 9፡9፥ ክፍል 47) እና ለሮማውያን ወታደሮች የጦር ሠፈር (ማቴ. 8፡9፥ ክፍል 55) የተሠራባት በመሆኗ በአዲስ ኪዳን ጊዜ ወደ ከተማነት አድጋ ነበር። ቀደም ሲል ኢየሱስ ከተማይቱን ጎብኝቷታል (ዮሐ. 2፡12፥ ክፍል 30)። ጴጥሮስንና እንድርያስን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ያገኛቸውም እዚያ ነው። ሁለቱም ከርሱ ጋር ወደ ናዝሬት የሄዱ አይመስልም። የዘብዴዎስ ልጆች የሆኑትን ያዕቆብንና ዮሐንስን ያገኛቸውም እዚያው ነው (ማቴ. 4፡ 18-22፤ ማር. 1፡ 16-20፥ ክፍል 41)። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እዚያችው ከተማ መልካሙ መቶ አለቃ በሠራው እና እያኢሮስ አለቃ በሆነበት (ማር. 5፡22፥ ክፍል 67) ምኩራብ ውስጥ ያስተምር ነበር (ሉቃስ 7፡5፥ ክፍል 55)። የሕይወት እንጀራ የተሰኘው እውቅ የኢየሱስ መልእክት የተላለፈውም እዚያ ነው (ዮሐ. 6፡59፥ ክፍል 76)። በመሆኑም ማቴዎስ ቅፍርናሆምን፥ “የገዛ ከተማው” (ማቴ. 9፡1፥ ክፍል 46) ብሎ ቢጠራት አይደንቅም።

(ማርቆስ 1፡21-28 የቀጠለ)

የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ።
25 ኢየሱስም፡- ዝም በል[35] ከእርሱም
ውጣ ብሎ ገሠጸው። 26 ርኩሱም
መንፈስ አንፈራገጠውና በታላቅ ድምፅ
ጮኾ ከእርሱ ወጣ።
27 ሁሉም፡- ይህ ምንድር ነው?
በሥልጣን ርኩሳን መናፍስትን ያዝዛል፤
እነርሱም ይታዘዙለታልና ይህ አዲስ
ትምህርት ምንድር ነው? ብለው
እስኪጠያየቁ ድረስ አደነቁ። 28 ዝናውም
ወዲያው በየስፍራው ወደ ገሊላ ዙሪያ
ሁሉ ወጣ።

(ሉቃስ 4፡31ለ-37 የቀጠለ)

35 ኢየሱስም፡- ዝም በል[35] ከእርሱም
ውጣ ብሎ ገሠጸው። ጋኔኑም በመካከላቸው
ጥሎት ሳይጐዳው ከእርሱ ወጣ።
36 ሁሉንም መደነቅ ያዛቸው፥ እርስ
በርሳቸውም፡- ይህ ቃል ምንድር ነው?
በሥልጣንና በኃይል ርኩሳን መናፍስትን
ያዝዛልና፥ ይወጡማል ብለው ተነጋገሩ።
37 ዝናም በዙሪያው ባለች አገር ወደ
ስፍራው ሁሉ ስለ እርሱ ወጣ።

## ♦ ክፍል 43. የጴጥሮስ አማትና ሌሎች መፈወሳቸው

- በቅፍርናሆም፥ ጴጥሮስ ቤት ውስጥ -

ማቴዎስ 8፡14-17

14 ኢየሱስም ወደ
ጴጥሮስ ቤት ገብቶ
አማቱን በንዳድ ታማ
ተኝታ አያት፤ 15
እጅዋንም ዳሰሰ፥[36]
ንዳዱም ለቀቃት፤
ተነሥታም
አገለገለቻቸው።
16-17 በመሸም ጊዜ
አጋንንት ያደረባቸውን
ብዙዎችን ወደ እርሱ
አመጡ፤ በነቢዩ
በኢሳይያስ፡- ‘‘እርሱ
ድካማችንን ተቀበለ
ደዌያችንንም ተሸከመ’’
የተባለው ይፈጸም
ዘንድ፥ መናፍስትን
በቃሉ አወጣ፥
የታመሙትንም ሁሉ
ፈወሰ። [ኢሳይያስ
53፡4]

ማርቆስ 1፡29-34

29 ወዲያውም ከምኵራብ
ወጥቶ ከያዕቆብና ከዮሐንስ
ጋር ወደ ስምዖንና ወደ
እንድርያስ ቤት ገባ። 30
የስምዖንም አማት በንዳድ
ታማ ተኝታ ነበር፥ ስለ
እርስዋም ወዲያው ነገሩት።
31 ቀርቦም እጅዋን ይዞ[36]
አስነሣት ንዳዱም ወዲያው
ለቀቃትና አገለገለቻቸው።
32 ፀሐይም ገብቶ በመሸ
ጊዜ፥ የታመሙትንና
አጋንንት ያደረባቸውን ሁሉ
ወደ እርሱ አመጡ፤ 33
ከተማይቱም ሁላ በደጅ
ተሰብስባ ነበር። 34 በልዩ
ልዩ ደዌም የታመሙትን
ብዙዎችን ፈወሰ፥
ብዙዎችንም አጋንንት
አወጣ፥ አጋንንትም ክርስቶስ
መሆኑን አውቀው ነበርና
ሊናገሩ አልፈቀደላቸውም።

ሉቃስ 4፡38-41

38 በምኵራብም ተነሥቶ
ወደ ስምዖን ቤት ገባ።
የስምዖንም አማት በብርቱ
ንዳድ ታማ ነበር ስለ
እርስዋም ለመኑት። 39
በአጠገብዋም ቆሞ ንዳዱን
ገሠጸውና[36] ለቀቃት፤
ያንጊዜውንም ተነሥታ
አገለገለቻቸው።
40 ፀሐይም በገባ ጊዜ
በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙ
በሽተኞችን ሁሉ ወደ እርሱ
አመጡአቸው፤ እርሱም
በእያንዳቸው ላይ እጁን
ጭኖ ፈወሳቸው። 41
አጋንንትም ደግሞ፡- አንተ
ክርስቶስ የእግዚአብሔር
ልጅ ነህ እያሉ እየጮኹም
ከብዙዎች ይወጡ ነበር፤
ገሠጻቸውም ክርስቶስም
እንደ ሆነ አውቀውት ነበርና
እንዲናገሩ
አልፈቀደላቸውም።

---

[34] ኢየሱስ ቅፍርናሆም ውስጥ ተቀባይነት ያገኘባቸው ሁለት ጉልህ ሁኔታዎች አሉ። የመጀመሪያው ነዋሪዎቹ በሞቀ ፍቅር ነው የተቀበሉት። ናዝሬት ውስጥ የገጠመው ግን የዚህ ተቃራኒ ነበር። ሁለተኛው ሁኔታ ኢየሱስ በኋላ ደጋግሞ እንዳደረገው፥ እንዲህ ያለውን ሥራ በሰንበት ሲያከናውን ተቃውሞ አልገጠመውም (ክፍል 49፥ 50፥ 51)። ይህ ሁሉ ሲደረግ ኢየሩሳሌም ውስጥ የነበሩት የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን የሚቃወሙ ወኪሎቻቸውን ለመላክ ገና ያሰቡ አይመስሉም።

## ♦ ክፍል 44. ከስምዖንና ከሌሎች ጋር በገሊላ ያደረገው ጉብኝት

- ገሊላ -

ማቴዎስ 4፡23-25

23 ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ [37] የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር። 24 ዝናውም ወደ ሶርያ ሁሉ ወጣ፤ በልዩ ልዩ ደዌና ሥቃይም ተይዘው የታመሙትን ሁሉ አጋንንትም ያደሩባቸውን በጨረቃም የሚነሣባቸውን ሽባዎችንም ወደ እርሱ አመጡ፥ ፈወሳቸውም። 25 ከገሊላም ከአሥሩ ከተማም ከኢየሩሳሌምም ከይሁዳም ከዮርዳኖስም ማዶ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት።

ማርቆስ 1፡35-39

35 ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ። 36 ስምዖንና ከእርሱ ጋር የነበሩትም ገሥግሠው ተከተሉት፥ 37 ባገኙትም ጊዜ፦ ሁሉ ይፈልጉሃል አሉት።

38 እርሱም፦ በዚያ ደግሞ ልሰብክ ወደ ሌላ ስፍራ በቅርብ ወዳሉ መንደሮች እንሂድ ስለዚህ ወጥቻለሁና አላቸው። 39 በምኵራባቸውም እየሰበከ አጋንንትንም እያወጣ ወደ ገሊላ ሁሉ መጣ።

ሉቃስ 4፡42-44

42 በጸባም ጊዜ ወጥቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ፤ ሕዝቡም ይፈልጉት ነበር፤ ወደ እርሱም መጡ፥ ከእነርሱም ተለይቶ እንዳይሄድ ሊከለክሉት ወደዱ። 43 እርሱ ግን፦ ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌሎቹ ከተማዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እሰብክ ዘንድ ይገባኛል አላቸው።

44 በገሊላም ምኵራቦች ይሰብክ ነበር።

---

[35] [ማር. 1፡25፤ ሉቃስ 4፡35] የኢየሱስ መሢሕነት በክፉው አለቃ ወኪሎች መገለጡ ተገቢ አልነበረም። እርኩሳን መናፍስቱን ባይገስጻቸውና ማንነቱ እንዲገለጥ ቢፈቅድ ኑሮ፥ የኋላ ኋላ ፈሪሳውያን የሰይጣን ተባባሪ ነው (ማቴ. 12፡24፤ ማር. 3፡22፥ ክፍል 61) ሲሉ ላቀረቡበት ክስ መሠረት የሚሆናቸው ነገር ያስገኝላቸው ነበር። ክፍል 43 ውስጥ ማር. 1፡34፤ ሉቃስ 4፡41ን ከዚህ ጋር ያስተያዩ።

[36] [ማቴ. 8፡15፤ ማር. 1፡31፤ ሉቃስ 4፡39] የነዚህ ተመሳሳይ ወንጌላት ጸሐፊዎች ትኩረትና መነሻ ይለያያል። ማቴዎስ እዚህ ሥፍራ ክርስቶስን እንደ ንጉሥ ሲገልጠው፥ በቀላሉ "እጅዋንም ዳሰሰ፥ ንዳዱም ለቀቃት" ብሏል። ማርቆስ ደግሞ ክርስቶስን ጥቂት ለየት ባለ አኳያ እንደ አገልጋይ ሲገልጠው "ቀርቦም እጅዋን ይዞ አስነሣት" ይላል። ሐኪሙ ሉቃስ ደግሞ ስለሴቲቱ ሕመም ሞያዊ ገለጣ ካደረገ በኋላ፥ ክርስቶስን፥ የሴቲቱን ትኩሳት በቀላሉ የሚገስጽ አድርጎ ነው ያቀረበው። ሉቃስ ብቻ ነው ክርስቶስ እንደ ሰው በተከታታይ የመፈወስ ተግባሩን "በሁሉም ላይ እጁን በመጫኑ" የገለጠው (ሉቃስ 4፡40)። ይህን በማድረግ ኢየሱስ ለሰዎች በግል ያለውን ጥልቅ መጨነቅ ወይም ፍቅር አመልክቷል።

## ♦ ክፍል 45. የለምጻሙ ሰው መንጻት ለሕዝቡ ይፋ ሆኖ መወራቱ

- በገሊላ ባሕር አጠገብ በሚገኝ ከተማ ውስጥ -

<u>ማቴዎስ 8፡2-4</u>

2 እነሆም፥ ለምጻም ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ እያለ ሰገደለት።

3 እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፦ እወዳለሁ፥ ንጻ አለው። ወዲያውም ለምጹ ነጻ።

4 ኢየሱስም፦ ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ፥[38] ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ሙሴ ያዘዘውን መባ አቅርብ አለው።

<u>ማርቆስ 1፡40-45</u>

40 ለምጻምም ወደ እርሱ መጥቶ ተንበረከከና፦ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ ብሎ ለመነው።

41 ኢየሱስም አዘነለት እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፦ እወድዳለሁ፤ ንጻ አለው። 42 በተናገረም ጊዜ ለምጹ ወዲያው ለቀቀውና ነጻ።

43 በብርቱም ተናግሮ ወዲያው አወጣው፤ 44 ለማንም እንዳች እንዳትናገር ተጠንቀቅ፥[38] ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለ መንጻትህ ሙሴ ያዘዘውን አቅርብ አለው። 45 እርሱ ግን ሲወጣ ብዙ ሊሰብክና ነገሩን ሊያወራ ጀመረ፥ ስለዚህም ኢየሱስ ተገልጦ ወደ ከተማ መግባት ወደ ፊት ተሳነው፥ ነገር ግን በውጭ በምድረ በዳ ይኖር ነበር፤ ከየስፍራውም ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።

<u>ሉቃስ 5፡12-16</u>

12 ከከተማዎችም በአንዲቱ ሳለ፥ እነሆ፥ ለምጽ የሞላበት ሰው ነበረ፤ ኢየሱስንም አይቶ በፊቱ ወደቀና፦ ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ፥ ልታነጻኝ ትችላለህ ብሎ ለመነው።

13 እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና፦ እወዳለሁ፥ ንጻ አለው፤ ወዲያውም ለምጹ ለቀቀው።

14 እርሱም ለማንም እንዳይናገር[38] አዘዘው፥ ነገር ግን፦ ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለ መንጻትህ ሙሴ እንዳዘዘ መሥዋዕት አቅርብ አለው።

15 ወሬው ግን አብዝቶ ወጣ፥ ብዙ ሕዝብም ሊሰሙትና ከደዌአቸው ሊፈወሱ ይሰበሰቡ ነበር፤ 16 ነገር ግን እርሱ ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ ይጸልይ ነበር።

---

37 [ማቴ. 4፡23] የኢየሱስ ሦስት አገልግሎቶች በዚህ ክፍል ታይተዋል። በአይሁድ ምኩራቦች አስተምሯል፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት አውጇል፤ በሽታና ደዌ ያለባቸውን በመፈወስ የትምህርቱንና የስብከቱን ሥልጣን አረጋግጧል።

38 [ማቴ. 8፡4፤ ማር. 1፡44፤ ሉቃስ 5፡14] የማንፃትን ሥርዓት መፈጸምና የመሚሑን መምጣት ማብሰር የካሕናት ተግባር ነበር። ክርስቶስ ለሌሎች እንዳይናገር ያዘዘውን ትእዛዝ ለምጻሙ አልተቀበለም፤ ስለዚህ ወደ ካሕናት ሂድና አሳይ ብሎ ኢየሱስ ያዘዘውን ትእዛዝ መፈጸሙ ያጠራጥራል። ከለምጽ የተፈወሰው ይህ ሰው በመካከላቸው ቢሆንም እንኳ፥ ካህናቱ የኢየሱስን መሚሕነት መቀበላቸው በውል አልታወቀም። ይህም ዘግየት ብሎ ሰዱቃውያን ስለርሱ ያላቸውን አመለካከት በገለጡ ጊዜ ተረጋግጧል።

## ♦ ክፍል 46. ሽባው ይቅር መባሉና መፈወሱ

- ቅፍርናሆም -

**ማቴዎስ 9፥ 1-8**

1 በታንኳም ገብቶ
ተሻገረና ወደ ገዛ ከተማው
መጣ።

2 እነሆም፥ በአልጋ የተኛ
ሽባ ወደ እርሱ አመጡ።

ኢየሱስም እምነታቸውን
አይቶ ሽባውን፦

አንተ ልጅ፥ አይዞህ፥
ኃጢአትህ ተሰረየችልህ
አለው።

3 እነሆም፥ ከጻፎቹ
አንዳንዱ በልባቸው፦
ይህስ ይሳደባል አሉ።

4 ኢየሱስም አሳባቸውን
አውቆ እንዲህ አለ፦ ስለ
ምን በልባችሁ ክፉ
ታስባላችሁ? 5 ኃጢአትህ
ተሰረየችልህ ከማለት
ወይስ፦ ተነሣና ሂድ
ከማለት ማናቸው ይቀላል?

**ማርቆስ 2፥ 1-12**

1 ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ
ቅፍርናሆም ደግሞ ገብቶ
በቤት እንደ ሆነ ተሰማ። 2
በደጅ ያለው ስፍራም
እስኪጠባቸው ድረስ ብዙ
ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ቃሉንም
ይነግራቸው ነበር። 3 አራት
ሰዎችም የተሸከሙትን ሽባ
አመጡለት። 4 ስለ
ሕዝቡም ብዛት ወደ እርሱ
ማቅረብ ቢያቅታቸው
እርሱ ያለበትን የቤቱን
ጣራ አነሡ፥ ነድለውም
ሽባው የተኛበትን አልጋ
አወረዱ። 5 ኢየሱስም
እምነታቸውን አይቶ
ሽባውን፦ አንተ ልጅ፥
ኃጢአትህ ተሰረየችልህ
አለው።

6 ከጻፎችም አንዳንዶቹ
በዚያ ተቀምጠው ነበር
በልባቸውም፦ ይህ ሰው
ስለ ምን እንደዚህ ያለ
ስድብ ይናገራል? 7
ከአንዱ ከእግዚአብሔር
በቀር ኃጢአት
ሊያስተሰርይ ማን
ይችላል? ብለው አሰቡ።

8 ወዲያውም ኢየሱስ
በልባቸው እንዲህ እንዳሰቡ
በመንፈስ አውቆ እንዲህ
አላቸው፦ በልባችሁ ይህን
ስለ ምን ታስባላችሁ? 9
ሽባውን፦ ኃጢአትህ

**ሉቃስ 5፥ 17-26**

17 አንድ ቀንም
ያስተምር ነበር፤ ከገሊላና
ከይሁዳ መንደሮችም ሁሉ
ከኢየሩሳሌምም መጥተው
የነበሩ ፈሪሳውያንና[39]
የሕግ መምህራን ይቀመጡ
ነበር፤ እርሱም
እንዲፈውስ የጌታ ኃይል
ሆነለት። 18 እነሆም፥
አንድ ሽባ በአልጋ
ተሸክመው አመጡ፤
አግብተውም በፊቱ
ሊያኖሩት ይሹ ነበር። 19
ስለ ሕዝቡም ብዛት
እንዴት አድርገው
እንዲያገቡት
ሲያቅታቸው፥ ወደ ሰገነቱ
ወጡ የጣራውንም ጡብ
አሳልፈው በመካከል
በኢየሱስ ፊት ከነአልጋው
አወረዱት።

20 እምነታቸውንም
አይቶ፦ አንተ ሰው፥
ኃጢአትህ ተሰረየችልህ
አለው።

21 ጻፎችና
ፈሪሳውያንም፦ ይህ
የሚሳደብ ማን ነው?
ከአንዱ ከእግዚአብሔር
በቀር ኃጢአት
ሊያስተሰርይ ማን
ይችላል? ብለው ያስቡ
ጀመር።

22 ኢየሱስም አሳባቸውን

---

[39] [ሉቃስ 5፥ 17] በሉቃስ ወንጌል ስለፈሪሳውያን ሲገለጥ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ከሃይማኖት መሪዎችም በገሊላ ኢየሱስ ተቃውሞ ሲደርስበት ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ተቃውሞው የጀመረው ቀደም ብሎ በኢየሩሳሌም ሲሆን፥ የተቃውሞውም ምክንያት ቅንዓት ነበር (ዮሐ. 4፥ 1-4፥ ክፍል 34)። ተቃውሞውን ለመቀጠል የተወከሉ ሰዎች ከይሁዳ መጡ። በቅርቡ ወደ ገሊላ የተደረገው ጉዞ (ክፍል 44) ሰፊ ትኩረትን ስለሳበ የአይሁድ መሪዎች ጉዳዩን መመርመርና የዚህን ታዋቂ ሰው (ኢየሱስ) እንቅስቃሴ መግታቱ አስፈለጋቸው።

| (ማቴዎስ 9፥ 1-8 የቀጠለ) | (ማርቆስ 2፥ 1-12 የቀጠለ) | (ሉቃስ 5፥ 17-26 የቀጠለ) |
| --- | --- | --- |
| 6 ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአትን ያስተሰርይ ዘንድ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፥ በዚያን ጊዜ ሽባውን፦ ተነሣ፤ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው። | ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ፦ ተነሣ አልጋህንም ተሸከምና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል? 10 ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፤ 11 ሽባውን፦ አንተን እልሃለሁ፥ ተነሣ፥ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው። | እያወቀ መልሶ፦ በልባችሁ ምን ታስባላችሁ? 23 ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ፦ ተነሣና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል? 24 ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአት ሊያስተሰርይ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ብሎ፥ ሽባውን፦ አንተን እልሃለሁ፥ ነተሣ፥ አልጋህን ተሸከመህ ወደ ቤትህ ሂድ አለው። |
| 7 ተነሥቶም ወደ ቤቱ ሄደ። | 12 ተነሥቶም ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት ወጣ፥ | 25 በዚያን ጊዜም በፊታቸው ተነሣ፥ ተኝቶበትም የነበረውን ተሸክሞ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤቱ ሄደ። |
| 8 ሕዝቡም አይተው ተደነቁ፥ ለሰውም እንዲህ ያለ ሥልጣን የሰጠ እግዚአብሔርን አከበሩ። | ስለዚህም ሰዎች ሁሉ ተገረሙና፦ እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ። | 26 ሁሉንም መገረም ያዛቸው፥ እግዚአብሔርንም አመሰገነው፦ ዛሬስ ድንቅ ነገር አየን እያሉ ፍርሃት ሞላባቸው። |

40 [ማቴ. 9፡9፤ ማር. 2፡14፤ ሉቃስ 5፡27] እንደ ማቴዎስ ያሉ ቀራጮች (ሌዊ ተብሎም ይጠራል) ከነጋዴዎች ተመን በማውጣት ለሮም መንግሥት ከነጋዴዎች ይቀርጡ ነበር። ማቴዎስ በገሊላ ባሕር ላይ በመርከብ ከሚደረገው ንግድ ለመቅረጥ የተሠማራ ሳይሆን አይቀርም (ማር. 2፡13)። ግልጥ ተመን ባልወጣላቸው ዕቃዎች ላይ ቀረጡን ከፍ በማድረግ ለራሱ ትርፍ እንዲወስድ ይፈቀድለት ነበር። ማቴዎስ ታማኝ ካልነበሩት ብዙ ቀራጮች መካከል ይሁን አይሁን የሚታወቅ ነገር የለም። ቀራጭ በመሆኑ ብቻ በአይሁዳውያን ወገኖቹ ዘንድ የተገለለና የተጠላ ነበር። ከሮማውያን ጋር መተባበሩ ከወገኖቹ ለየው። ኢየሱስ እንዲህ ያለውን ሰው በመጥራት ሃይማኖት አክራሪ ከሆኑት ሕግ አስተማሪዎችና ፈሪሳውያን አሠራር የሚቃረን ድርጊት ፈጸመ። ማቴዎስም ሥራውን በመተው ዳግመኛ ወደ ቀድሞ ሥራው ላለመመለስ ወስኖ ተከተለው (በሉቃስ 5፡28 ላይ "ሁሉንም" የሚለውን ከሉቃስ 5፡11 ፥ ክፍል 41 ጋር ያነጻጽሩ።

## ♦ ክፍል 47ሀ. የማቴዎስ መጠራት

[ክፍል 28ና 41ን ይመልከቱ]

- ቅፍርናሆም -

| ማቴዎስ 9፡9 | ማርቆስ 2፡13-14 | ሉቃስ 5፡27-28 |
|---|---|---|
| 9 ኢየሱስም ከዚያ አልፎ በመቅረጫው[40] ተቀምጦ የነበረ ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው አየና፡- ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው። | 13 ደግሞም በባሕር አጠገብ ወጣ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡና አስተማራቸው። 14 ሲያልፍም በመቅረጫው[40] ተቀምጦ የነበረውን የእልፍዮስን ልጅ ሌዊን አየና፡- ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው። | 27 ከዚህም በኋላ ወጥቶ ሌዊ የሚባል ቀራጭ[40] በመቅረጫው ተቀምጦ ተመለከተና፡- ተከተለኝ አለው። 28 ሁሉንም ተወ፤ ተነሥቶም ተከተለው። |

## ♦ ክፍል 47ለ. በማቴዎስ ቤት የተደረገው ግብዣ

- ቅፍርናሆም -

| ማቴዎስ 9፡10-13 | ማርቆስ 2፡15-17 | ሉቃስ 5፡29-32 |
|---|---|---|
| 10 በቤቱም በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፥ እነሆ፥ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች መጥተው ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብረው ተቀመጡ። 11 ፈሪሳውያንም አይተው ደቀ መዛሙርቱን፡- መምህራችሁ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር አብሮ ስለ ምን ይበላል? አሉአቸው። 12 ኢየሱስም ሰምቶ፡- ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤ 13 ነገር ግን ሄዳችሁ፡- ምሕረትን እወዳለሁ | 15 በቤቱም በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፥ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጡ፤ ብዙ ነበሩ ይከተሉትም ነበር። 16 ጻፎችና ፈሪሳውያንም ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ሲበላ አይተው ለደቀ መዛሙርቱ፡- ከቀራ ጮችና ከኃጢአተኞች ጋር የሚበላና የሚጠጣ ስለ ምንድር ነው? አሉ። 17 ኢየሱስም ሰምቶ፡- ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም | 29 ሌዊም በቤቱ ታላቅ ግብዣ አደረገለት፤ ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩ ከቀራጮችና ከሌሎች ሰዎች ብዙ ሕዝብ ነበሩ። 30 ፈሪሳውያንና ጻፎቻቸውም በደቀ መዛሙርቱ ላይ፡- ስለ ምን ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ትበላላችሁ ትጠጡማላችሁ? ብለው አንጐራጐሩ። 31 ኢየሱስም መልሶ፡- ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኃኒት |

[41] [ሉቃስ 5፡36] ሉቃስ ማለት በምሳሌ አገላለጥ ሥዕላዊ መግለጫ ማለት ነው። ጌታ በምሳሌ በማስተማር ዘዴ በመጠቀሙ፥ በማስተማር ቴክኒኩ ላይ በኋላ የጎላ ለውጥ ታይቷል (ክፍል 64ን ይመልከቱ)። በኋለኛው የምሳሌ አጠቃቀሙ እውነትን ከማያምኑት ለመሰወሪያና፥ ለሚያምኑ ግን ለመግለጫነት ተጠቅሞበታል። የመጀመሪያው አሳብ እዚህ በመረጃነት አልቀረበም።

| (ማቴዎስ 9፡ 10-13 የቀጠለ) | (ማርቆስ 2፡ 15-17 የቀጠለ) | (ሉቃስ 5፡ 29-32 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| መሥዋዕትንም አይደለም [ሆሴዕ 6፡6] ያለው ምን እንደ ሆነ ተማሩ፤ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና አላቸው። | ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው። | አያስፈልጋቸውም፤ 32 ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው። |

## ♦ ክፍል 48. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ከመጾም ፋንታ ለምን ድግስ እንደሚበሉ ለማስረዳት ሦስት ምሳሌዎች ማቅረቡ

- ቅፍርናሆም -

| ማቴዎስ 9፡ 14-17 | ማርቆስ 2፡ 18-22 | ሉቃስ 5፡ 33-39 |
|---|---|---|
| 14 በዚያን ጊዜ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ቀርበው፡- እኛና ፈሪሳውያን፥ ብዙ ጊዜ የምንጦመው፥ ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጦሙት ስለ ምንድር ነው? አሉት። | 18 የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን ይጦሙ ነበር። መጥተውም፡- የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት የሚጦሙት የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጦሙት ስለ ምንድር ነው? አሉት። | 33 እነርሱም፡- የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለ ምን ብዙ ይጦማሉ ጸሎትስ ስለ ምን ያደርጋሉ፥ ደግሞም የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት ስለ ምን እንደዚሁ ያደርጋሉ፤ የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን ይበላሉ ይጠጣሉም? አሉት። |
| 15 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡- ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፥ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ። | 19 ኢየሱስም አላቸው፡- ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሚዜዎች ሊጦሙ ይችላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊጦሙ አይችሉም። 20 ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፥ በዚያ ወራትም ይጦማሉ። | 34 ኢየሱስም፡- ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሚዜዎችን ልታስጦሙ ትችላላችሁን? 35 ነገር ግን ወራት ይመጣል፥ ሙሽራውም ከእነርሱ ሲወሰድ ያንጊዜ፥ በዚያ ወራት ይጦማሉ አላቸው። |
| 16 በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚያኖር የለም፤ መጣፊያው ልብሱን ይቦጫቀዋልና፥ መቀደዱም የባሰ ይሆናል። 17 በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን፥ | 21 በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚጥፍ የለም፤ ቢደረግ ግን፥ አዲሱ መጣፊያ አሮጌውን ይቦጫቀዋል፥ መቀደዱም የባሰ ይሆናል። 22 በአረጀ አቁማዳም አዲስ የወይን | 36 ደግሞም ምሳሌ[41] እንዲህ ሲል ነገራቸው፡- የአዲስ ልብስ እራፊ ባረጀ ልብስ ላይ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን አዲሱን ይቀደዋል ደግሞም አዲስ እራፊ ለአሮጌው አይስማማውም። |

(ማቴዎስ 9፡ 14-17 የቀጠለ)

አቁማዳው ይፈነዳል፥ የወይን ጠጁም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል፤ ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ያኖረዋል፥ ሁለቱም ይጠባበቃሉ።

(ማርቆስ 2፡ 18-22 የቀጠለ)

ጠጅ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን፥ የወይን ጠጁ አቁማዳውን ያፈነዳል የወይኑም ጠጅ ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል አዲሱን የወይን ጠጅ ግን በአዲስ አቁማዳ ያኖራሉ።

(ሉቃስ 5፡33-39 የቀጠለ)

37 ባረጀ አቁማዳም አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን አዲሱ የወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈነዳል፥ እርሱም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል። 38 አዲሱን የወይን ጠጅ ግን በአዲስ አቁማዳ ማኖር ይገባል፥ ሁለቱም ይጠባበቃሉ። 39 አሮጌ የወይን ጠጅ ሲጠጣ አዲሱን የሚሻ ማንም የለም፤ አሮጌው ይጣፍጣል ይላልና።

# > ስለ ሰንበት አከባበር የተነሣ ውዝግብ እና የኢየሱስ ከአካባቢው ፈቀቅ ማለት <

## ♦ ክፍል 49ሀ. ኢየሱስ በሰንበት ዕለት አንድ ድውይ ፈወሰ

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 5፡ 1-9</u>

1 ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፥ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። 2
በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት
መጠመቂያ ነበረች፤ አምስትም መመላለሻ ነበረባት። 3 በእነዚህ ውስጥ የውኃውን
መንቀሳቀስ እየጠበቁ በሽተኞችና ዕውሮች አንካሶችም ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ
ሕዝብ ይተኙ ነበር። 4 አንዳንድ ጊዜ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያይቱ ወርዶ
ውኃውን ያናውጥ ነበርና፤ እንግዲህ ከውኃው መናወጥ በኋላ በመጀመሪያ የገባ
ከማናቸው ካለበት ደዌ ጤናማ ይሆን ነበር። 5 በዚያም ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ
የታመመ አንድ ሰው ነበረ፤ 6 ኢየሱስ ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ፥ እስከ አሁን ብዙ
ዘመን እንዲሁ እንደ ነበረ አውቆ፦ ልትድን ትወዳለህን? አለው።

7 ድውዩም፦ ጌታ ሆይ፥ ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚያኖረኝ
ሰው የለኝም ነገር ግን እኔ ስመጣ ሳለሁ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል ብሎ መለሰለት።

8 ኢየሱስ፦ ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለው። 9 ወዲያውም ሰውዬው ዳነ
አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ።

## ♦ ክፍል 49ለ. ኢየሱስ ሰንበትን በመሻሩና ከአብ ጋር አንድ ነኝ በማለቱ እርሱን ለመግደል የተደረገ ጥረት

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 5፡ 10-18</u>

10 ያም ቀን ሰንበት[42] ነበረ። ስለዚህ አይሁድ የተፈወሰውን ሰው፦ ሰንበት ነው
አልጋህንም ልትሸከም አልተፈቀደልህም አሉት።

11 እርሱ ግን፦ ያዳነኝ ያ ሰው፦ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለኝ ብሎ መለሰላቸው።

12 እነርሱም፦ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ያለህ ሰው ማን ነው? ብለው ጠየቁት።

13 ዳኑ ግን በዚያ ስፍራ ሕዝብ ስለ ነበሩ ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ነበርና የተፈወሰው ሰው
ማን እንደ ሆነ አላወቀም።

14 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና፦ እነሆ፥ ድነሃል፤ ከዚህ የሚብስ
እንዳይደርስብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ አለው። 15 ሰውዬው ሄዶ ያዳነው ኢየሱስ
እንደ ሆነ ለአይሁድ ነገረ።

---

42 [ዮሐ. 5፡ 10] ከየትኛውም ጉዳይ ይልቅ የሰንበት ጉዳይ የሃይማኖት መሪዎችን ከጌታ ለይቷቸዋል (በክፍል 50 እና 51)። ይህ ከመጀመሪያዎቹ ሦስት አከራካሪ ጉዳዮች ቀዳሚው ሆኖ ቀርቧል። የሃይማኖት መምህራን በሰንበት ሊከናወኑ አይገባቸውም ያሏቸውን 39 ዋና ዋና ተግባራት መዝግበው ነበር። ከእነዚህም አንዱ አጠቃላይ የቤት ውስጥ ተራ ሥራ ነበር። አልጋን የመሳሰሉ መኝታዎችን መሸከም ተከልክሏል። የኢየሱስ አገልግሎት ገና አንድ ዓመት ተኩል ሲቀረው የኢየሩሳሌም ባለሥልጣናት ሊገድሉት እንዳቀዱ (ዮሐ. 5፡ 18)፥ ይህ ጠላትነት ወደ ገሊላም በፍጥነት ተዛመተ (ማር. 3፡ 6፥ ክፍል 51)።

(ዮሐንስ 5፡ 10-18 የቀጠለ)

16 ስለዚህም በሰንበት ይህን ስላደረገ አይሁድ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበር ሊገድሉትም
ይፈልጉ ነበር። 17 ኢየሱስ ግን፦ አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ
ብሎ መለሰላቸው። 18 እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ደግሞ
ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ፦ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ፥ ስለዚህ
አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር።

## ♦ ክፍል 49ሐ. የወልድን ከአብ ጋር አቻ መሆን ያመለከተ ገለጣ

- ኢየሩሳሌም -

ዮሐንስ 5፡ 19-47

19 ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ
ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ ያ
የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና። 20 አብ ወልድን
ይወዳልና፥ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል፤ እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ
ሥራ ያሳየዋል። 21 አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁ
ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል። 22-23 ሰዎች ሁሉ አብን
እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ
በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።

24 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም
ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። 25
እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት
ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ። 26 አብ
በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው
ሰጥቶታልና። 27 የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው።

28-29 በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም
ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ
አታድንቁ። 30 እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ
ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።

31 እኔ ስለ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም፤ 32 ስለ እኔ
የሚመሰክር ሌላ ነው፥ እርሱም ስለ እኔ የሚመሰክረው ምስክር እውነት እንደ ሆነ
አውቃለሁ።

33 እናንተ ወደ ዮሐንስ ልካችኋል እርሱም ለእውነት መስክሮአል። 34 እኔ ግን
ከሰው ምስክር አልቀበልም፥ እናንተ እንድትድኑ ይህን እላለሁ እንጂ። 35 እርሱ
የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ፥ እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ
ወደዳችሁ።

36 እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክር የሚበልጥ ምስክር አለኝ፤ አብ ልፈጽመው የሰጠኝ
ሥራ፥ ይህ የማደርገው ሥራ፥ አብ እንደ ላከኝ ስለ እኔ ይመሰክራልና። 37 የላከኝ
አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል። ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፥ መልኩንም
አላያችሁም፤ 38 እርሱም የላከውን እናንተ አታምኑምና በእናንተ ዘንድ የሚኖር ቃሉ
የላችሁም። 39 እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና
እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ 40 ነገር ግን

(ዮሐንስ 5፡ 19-47 የቀጠለ)

ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም።

41-42 ከሰው ክብርን አልቀበልም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ፍቅር በራሳችሁ እንደ
ሌላችሁ አውቃችኋለሁ። 43 እኔ በአባቴ ስም መጥቻለሁ አልተቀበላችሁኝምም፤
ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ። 44 እናንተ እርስ በርሳችሁ ክብር
የምትቀባበሉ ከአንዱም ከእግዚአብሔር ያለውን ክብር የማትፈልጉ፥ እንዴት
ልታምኑ ትችላላችሁ?

45 እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ፤ የሚከሳችሁ አለ፤ እርሱም ተስፋ
የምታደርጉት ሙሴ ነው። 46 ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለ
እኔ ጽፎአልና። 47 መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?

## ♦ ክፍል 50. ደቀ መዛሙርት በሰንበት ዕለት እሸት በመቅጠፋቸው የተፈጠረ ውዝግብ

- ምናልባት በገሊላ -

ማቴዎስ 12፡ 1-8

1 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ
በሰንበት ቀን[43] በእርሻ
መካከል አለፈ፤ ደቀ
መዛሙርቱም ተራቡና
እሸት ይቀጥፉ ይበሉም
ጀመር። 2 ፈሪሳውያንም
አይተው፡- እነሆ፥ ደቀ
መዛሙርትህ በሰንበት
ማድረግ ያልተፈቀደውን
ያደርጋሉ አሉት።

3-4 እርሱ ግን እንዲህ
አላቸው፡- 44 ዳዊትና
ከእርሱ ጋር የነበሩት
በተራቡ ጊዜ፥ እርሱ
ያደረገውን፥ ወደ
እግዚአብሔር ቤት እንደ
ገባ ካህናትም ብቻ እንጂ
እርሱና ከእርሱ ጋር
የነበሩት ሊበሉት
ያልተፈቀደውን
የመሥዋዕቱን ኅብስት
እንደ በላ

ማርቆስ 2፡ 23-28

23 በሰንበትም[43] በእርሻ
መካከል ሲያልፍ ደቀ
መዛሙርቱ እየሄዱ እሸት
ይቀጥፉ ጀመር። 24
ፈሪሳውያንም፡- እነሆ፥
በሰንበት ያልተፈቀደውን
ስለ ምን ያደርጋሉ?
አሉት።

25 እርሱም፡- ዳዊት
ባስፈለገውና በተራበ ጊዜ፥
እርሱ አብረውት ከነበሩት
ጋር ያደረገውን፥
አብያተር ሊቀ ካህናት
በነበረ ጊዜ ወደ
እግዚአብሔር ቤት እንደ
ገባ፥ 26 ከካህናት በቀር
መብላት ያልተፈቀደውን
የመሥዋዕትን እንጀራ
እንደ በላ፥ ከእርሱም ጋር
ለነበሩት እንደ ሰጣቸው
ከቶ አላነበባችሁምን?
አላቸው።

ሉቃስ 6፡ 1-5

1 በሰንበትም[43] በእርሻ
መካከል ያልፍ ነበር ደቀ
መዛሙርቱም እሸት
ይቀጥፉ በእጃቸውም እያሹ
ይበሉ ነበር። 2 ከፈሪሳውያን
ግን አንዳንዶቹ፡- በሰንበት
ሊያደርግ ያልተፈቀደውን
ስለ ምን ታደርጋላችሁ?
አሉአቸው።

3-4 ኢየሱስም ለእነርሱ
መልሶ፡- ዳዊት በተራበ ጊዜ
እርሱ አብረውት ከነበሩ ጋር
ያደረገውን፥ ወደ
እግዚአብሔር ቤት እንደ ገባ
ከካህናት ብቻ በቀር
መብላቱ ያልተፈቀደውን
የመሥዋዕትን እንጀራ ይዞ
እንደ በላ፥ ከእርሱም ጋር
ለነበሩት ደግሞ እንደ
ሰጣቸው ይህን
አላነበባችሁምን? አለ።

43 [ሉቃስ 6፡1] በሃይማኖት መምህራኑ ባህል መሠረት እሸት "መቅጠፍ" እና "ማሸት" እንደማጨድ፥ እንደመውቃት፥ ፍሬውን ከእብቅ እንደመለየትና ለምግብ እንደማዘጋጀት ይቆጠር ነበር። ለዚህ ነው የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሰንበትን እንደሻሩ የተቆጠሩት።

(ማቴዎስ 12፡1-8 የቀጠለ)

አላነበባችሁምን? 5
ካህናትም በሰንበት
በመቅደስ ሰንበትን
እንዲያረክሱ ኃጢአትም
እንዳይሆንባቸው በሕጉ
አላነበባችሁምን? 6 ነገር
ግን እላችኋለሁ፥ ከመቅደስ
የሚበልጥ ከዚህ አለ። 7
ምሕረትን እወዳለሁ
መሥዋዕትንም አይደለም
[ሆሴዕ 6፡6] ያለው ምን
እንደሆነ ብታውቁስ
ኃጢአት የሌለባቸውን
ባልኰነናችሁም ነበር። 8
የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ
ነውና።

(ማርቆስ 2:23-28 የቀጠለ)

27 ደግሞ፡- ሰንበት ስለ
ሰው ተፈጥሮአል እንጂ
ሰው ስለ ሰንበት
አልተፈጠረም፤

28 እንዲሁም የሰው ልጅ
ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነው
አላቸው።

(ሉቃስ 6፡1-5 የቀጠለ)

5 የሰው ልጅ የሰንበት
ጌታ ነው አላቸውም።

## ♦ ክፍል 51. እጁ የሰለለችበትን ሰው በሰንበት መፈወስ

- በገሊላ ምኩራብ ውስጥ -

ማቴዎስ 12፡9-14

9 ከዚያም አልፎ ወደ
ምኩራባቸው ገባ። 10
እነሆም፥ እጁ የሰለለች
ሰው ነበረ፤ ይከሱትም
ዘንድ፡- በሰንበት መፈወስ
ተፈቅዶአልን? ብለው
ጠየቁት።

11 እርሱ ግን፡- ከእናንተ
አንድ በግ ያለው በሰንበት
በጉድጓድ ቢወድቅበት፥
ይዞ የማያወጣው ሰው ማን
ነው? 12 እንግዲህ ሰው
ከበግ ይልቅ እንደምን
አይበልጥም!

ማርቆስ 3፡1-6

1 ደግሞም ወደ ምኩራብ
ገባ፥ በዚያም እጁ የሰለለች
ሰው ነበር፤ 2 ሊከሱትም፥
በሰንበት ይፈውሰው እንደ
ሆነ ይጠባበቁት ነበር። 3
እጁ የሰለለችውንም ሰው፡-
ተነሥተህ ወደ መካከል ና
አለው።

4 በሰንበት በጎ ማድረግ
ተፈቅዶአልን? ወይስ ክፉ?
ነፍስ ማዳን ወይስ መግደል?
አላቸው፤ እነርሱም ዝም
አሉ።

5 ስለ ልባቸውም ድንዛዜ
አዝኖ ዙሪያውን
እየተመለከተ በቍጣ

ሉቃስ 6፡6-11

6 በሌላው ሰንበትም ወደ
ምኵራብ ገብቶ አስተማረ፤
በዚያም ቀኝ እጁ የሰለለች
ሰው ነበረ፤ 7 ጻፎችና
ፈሪሳውያንም መክሰሻ
ሊያገኙበት በሰንበት
ይፈውስ እንደ ሆነ
ይጠባበቁት ነበር። 8 እርሱ
ግን አሳባቸውን አውቆ እጁ
የሰለለችውን ሰው፡- ተነሣና
በመካከል ቁም[45] አለው፤
ተነሥቶም ቆመ።

9 ኢየሱስም፡-
እጠይቃችኋለሁ፤ በሰንበት
በጎ ማድረግ ተፈቅዶአልን
ወይስ ክፉ? ነፍስ ማዳንን

[44] [ማቴ. 12፡3] ኢየሱስ ለቀረቡት ክሶች በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የሰጣቸው አምስት ማፍረሻዎች፡-

(1) የዳዊት ምሳሌነት (12፡3-4) (2) የሕግ ትምህርት (12፡5) (3) ከቤተ መቅደስ የሚበልጥ ጌታ የሚመጣ ስለመሆኑ የተነገረ ትንቢት (12፡6) (4) ሰንበት የተሠራው ለሰው ስለመሆኑ (12፡7፤ ማር. 2፡27) እና (5) መሢሑ የሰንበት ጌታ ስለመሆኑ (12፡8)

| (ማቴዎስ 12፥9-14 የቀጠለ) | (ማርቆስ 3፥1-6 የቀጠለ) | (ሉቃስ 6፥6-11 የቀጠለ) |
| --- | --- | --- |
| ስለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዶአል አላቸው። 13 ከዚያም በኋላ ሰውየውን፦ እጅህን ዘርጋ አለው። ዘረጋትም፥ እንደ ሁለተኛይቱም ደህና ሆነች። 14 ፈሪሳውያን ግን ወጥተው እንዴት አድርገው እንዲያጠፉት ተማከሩበት። | አያቸው፥ ሰውየውንም፦ እጅህን ዘርጋ አለው። 6 ዘረጋትም፥ እጁም ዳነች። ፈሪሳውያንም ወጥተው ወዲያው እንዴት አድርገው እንዲያጠፉት ከሄሮድስ ወገን ጋር ተማከሩበት። | ወይስ መግደል? አላቸው። 10 ሁላቸውንም ዙሪያውን አየና ሰውዬውን፦ እጅህን ዘርጋ አለው። እርሱም እንዲህ አደረገ፥ እጁም እንደ ሁለተኛይቱ ዳነች። 11 እነርሱም ቍጣ ሞላባቸው፥ በኢየሱስም ምን እንዲያደርጉበት እርስ በርሳቸው ተባባሉ። |

## ♦ ክፍል 52. ኢየሱስ ከተለያየ ሥፍራ ከመጡ ብዙ ሰዎች ጋር ወደ ገሊላ ባሕር እልፍ ማለቱ

- በገሊላ ባሕር -

| ማቴዎስ 12፥15-21 | ማርቆስ 3፥7-12 |
| --- | --- |
| 15 ኢየሱስም አውቆ ከዚያ ፈቀቅ አለ። ብዙ ሰዎችም ተከተሉት፥ ሁሉንም ፈወሳቸው፥ እንዳይገልጡትም አዘዛቸው፤<br><br>16-17 በነቢዩ በኢሳይያስ የተባለው ይፈጸም ዘንድ እንዲህ ሲል፦<br><br>18 "እነሆ የመረጥሁት ብላቴናዬ፥ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ወዳጄ፤ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፥ ፍርድንም ለአሕዛብ ያወራል። 19 አይከራከርም አይጮህምም፥ ድምፁንም በአደባባይ የሚሰማ የለም። 20 ፍርድን ድል ለመንሣት እስኪያወጣ፥ የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም የሚጤስን የጥዋፍ ክርም አያጠፋም። 21 አሕዛብም በስሙ ተስፋ ያደርጋሉ።" [ኢሳይያስ 42፥1-4] | 7 ኢየሱስም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ባህር ፈቀቅ አለ፤ ከገሊላ የመጡም ብዙ ሰዎች ተከተሉት፤ 8 እንዴት ትልቅ ነገርም እንዳደረገው ሰምተው ብዙ ሰዎች ከይሁዳ ከኢየሩሳሌምም ከኤዶምያስም ከዮርዳኖስ ማዶም ከጢሮስና ከሲዶና ምድርም ወደ እርሱ መጡ። 9 ሰዎቹም እንዳያጋፉት ታንኳን ያቆዩለት ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው፤ 10 ብዙ ሰዎችን አድኖ ነበርና፥ ስለዚህም ሥቃይ ያለባቸው ሁሉ እንዲዳስሱት ይወድቁበት ነበር። 11 ርኩሳን መናፍስትም ባዩት ጊዜ በፊቱ ተደፍተው፦ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ እያሉ ጮኹ። 12 እንዳይገልጡትም በጣም አዘዛቸው። |

45 [ሉቃስ 6፥8] ኢየሱስ ይህን አጋጣሚ ለሥነ-መለኮታዊ ክርክር መጠቀሚያ የፈለገው መሆኑ ግልጥ የሆነው "ተነሣና በመካከል ቁም" (ሉቃስ 6፥8) ብሎ በተናገረ ጊዜ ነበር። ይህ የሰንበት ዕለት ፈውስ ከፍተኛ ዜና ሆነ።

# > የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መመረጥና የተራራው ስብከት <

## ♦ ክፍል 53. አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ተመረጡ

[ክፍል 70ለና ሐዋርያት ሥራ 1፡13ን ይመልከቱ]

- በገሊላ ባሕር አጠገብ በሚገኝ ተራራ -

ማርቆስ 3፡13-19

13 ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም
የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ
እርሱም ሄዱ። 14 ከእርሱም ጋር
እንዲኖሩና ለመስበክ እንዲልካቸው፥ 15
ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም
ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ
አሥራ ሁለት አደረገ፤[46] 16 ስምዖንንም
ጴጥሮስ ብሎ ሰየመው፤ 17
የዘብዴዎስንም ልጅ ያዕቆብን የያዕቆ
ብንም ወንድም ዮሐንስን በአኔርጌስ ብሎ
ሰየማቸው፥ የነጎድጓድ ልጆች ማለት
ነው፤ 18 እንድርያስንም ፊልጶስንም
በርተሎሜዎስንም ማቴዎስንም ቶማስንም
የእልፍዮስን ልጅ ያዕቆብንም ታዴዎስንም
ቀነናዊውንም ስምዖንን፥ 19 አሳልፎ
የሰጠውንም የአስቆሮቱን ይሁዳን።

ሉቃስ 6፡12-16

12 በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ
ተራራ ወጣ፥ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ
እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ። 13 በነጋም
ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም
አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት
ብሎ ሰየማቸው፤

14 እነርሱም፥[46] ጴጥሮስ ብሎ እንደ ገና
የሰየመው ስምዖን፥ ወንድሙም
እንድርያስ፥ ያዕቆብም ዮሐንስም፥
ፊልጶስም በርተሎሜዎስም፥ 15
ማቴዎስም ቶማስም፥ የእልፍዮስ ልጅ
ያዕቆብም ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም፥
16 የያዕቆብ ይሁዳም፥ አሳልፎ የሰጠውም
የአስቆሮቱ ይሁዳ ናቸው።

## ♦ ክፍል 54ሀ. የተራራው ስብከት መጀመር

- በተራራው ላይ በተካከለ ስፍራ -

ማቴዎስ 5፡1-2

1 ሕዝቡንም አይቶ ወደ ተራራ[47]
ወጣ፤[47] በተቀመጠም ጊዜ ደቀ
መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀረቡ፤ 2 አፉንም
ከፍቶ አስተማራቸው እንዲህም አለ፦

ሉቃስ 6፡17-19

17 ከእነርሱም ጋር ወርዶ በተካከለ ስፍራ[47]
ቆመ፥ ከደቀ መዛሙርቱም ወገን ብዙ ሕዝብ
ነበረ፥ ደግሞም ሊሰሙትና ከደዌአቸው
ሊፈወሱ ከይሁዳ ሁሉ ከኢየሩሳሌምም
ከጢሮስና ከሲዶና ባሕር ዳርም የመጡ ብዙ
ሰዎች ነበሩ፤ 18 ከርኩሳንም መናፍስት
ይሠቃዩ የነበሩት ተፈወሱ፤ 19 ከእርሱም
ኃይል ወጥቶ ሁሉን ይፈውስ ነበርና ሕዝቡ
ሁሉ ሊዳስሱት ይሹ ነበር።

---

[46] [ማር. 3፡16፤ ሉቃስ 6፡14] ማቴዎስ 10፡2-4፤ ክፍል 70ለ እና የሐዋርያት ሥራ 1፡13 ውስጥ ሌላ ሁለት ሥፍራ ላይ የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም ዝርዝር ተገልጧል። ታዴዎስ፥ የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ ሌላኛው ስም መሆኑን ልብ ካልን፥ ከቅደም ተከተሉ በቀር የስም ዝርዝሮቹ አንዱ ከሌላው ጋር ይመሳሰላሉ። ስምኦን ጴጥሮስ በአራቱም ዝርዝር ውስጥ የመጀመሪያው ነበር። ከይሁዳ ወገን ከሆነው ከአስቆሮቱ ይሁዳ በስተቀር ሌሎች የገሊላ ሰዎች ነበሩ።

## ♦ ክፍል 54ለ. የመንግሥቱ ወራሾች ለሆኑት በረከት፥ ለዚያ ለማይበቁት ደግሞ ወዮታ[48]

<u>ማቴዎስ 5፡3-12</u>

3 በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን
ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ
ናትና። 4 የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥
መፅናናትን ያገኛሉና። 5 የዋሆች
ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን
ይወርሳሉና። 6 ጽድቅን የሚራቡና
የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥
ይጠግባሉና። 7 የሚምሩ ብፁዓን
ናቸው፥ ይማራሉና። 8 ልበ ንጹሖች
ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን
ያዩታልና። 9 የሚያስተራርቁ
ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር
ልጆች ይባላሉና። 10 ስለ ጽድቅ
የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥
መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።

11 ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ
በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት
ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። 12
ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ
ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ
በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ
አሳድደዋቸዋልና።

<u>ሉቃስ 6፡20-26</u>

20 እርሱም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዓይኑን
አንሥቶ እንዲህም አላቸው:-

እናንተ ድሆች ብፁዓን ናችሁ፥
የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ
ነውና። 21 እናንተ አሁን የምትራቡ
ብፁዓን ናችሁ፥ ትጠግባላችሁና።
እናንተ አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን
ናችሁ፥ ትስቃላችሁና። 22 ሰዎች ስለ
ሰው ልጅ ሲጠሉአችሁ ሲለዩአችሁም
ሲነቅፉአችሁም ስማችሁንም እንደ
ክፉ ሲያወጡ፥ ብፁዓን ናችሁ።

23 እነሆ፥ ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና
በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ ዝለሉም፤
አባቶቻቸው ነቢያትን እንዲህ
ያደርጉባቸው ነበርና።

24 ነገር ግን እናንተ ባለ ጠጎች
ወዮላችሁ፥ መጽናናታችሁን
ተቀብላችኋልና። 25 እናንተ አሁን
የጠገባችሁ ወዮላችሁ፥
ትራባላችሁና። እናንተ አሁን
የምትስቁ ወዮላችሁ፥ ታዝናላችሁና
ታለቅሱማላችሁ። 26 ሰዎች ሁሉ
መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ፤
አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት
እንዲሁ ያደርጉላቸው ነበርና።

---

47 [ማቴ. 5፡1፤ ሉቃስ 6፡17] አንዳንድ ሰዎች "የተራራው ስብከት" በተለያዩ ጊዜያት የተሰጡ ትምህርቶችን የያዘ ነው ቢሉም፥ ማቴዎስና ሉቃስ ከመዘገቡት ለመረዳት እንደሚቻለው ግን፥ በአንድ በተለየ ጊዜ የተነገረ ቃል መሆኑን ለማረጋገጥ ይቻላል። ሁለቱ ወንጌሎች አንድ ዓይነት መልእክት ያላቸው መሆኑም በሚገባ ተቀባይነት አግኝቷል።

በሁለቱ መካከል ያለው ተመሳሳይነት ሰፊ በመሆኑ ሁለት የተለያዩ መልእክቶች ናቸው ለማለት አያስደፍርም። ኢየሱስ ይህን መልእክት ያስተላለፈው፥ በተራራው አንድ ወገን ላይ በነበረ ደልዳላ ሥፍራ ላይ ነው። መልእክቱም ለደቀ መዛሙርቱ ነበር (ማቴ. 5፡1-2፤ ሉቃስ 6፡20)። ይሁን እንጂ ሌሎች እያሌ ሰዎችም የመልእክቱ ተጠቃሚ ሆነዋል (ማቴ. 7፡28፥ ክፍል 54 እና ሉቃስ 6፡19፤ 7፡1፥ ክፍል 55)። መልእክቱ ከተመዘገበው ይልቅ የረዘመ ሳይሆን አይቀርም። ይህን ለማለት የሚያስችለው፥ አንደኛው የወንጌል ጸሐፊ ሌላው ከመዘገበው በላይ ጽፎ መገኘቱ ነው። በተጨማሪም በአንዳንድ አባባሎች የተለያዩ ዝርዝር ጉዳዮች ኢየሱስ ቃላቱን በመቀያየር አባባሉን የደጋገመ መሆኑን ስለሚያመለክቱ፥ ምናልባት በሁለቱም ወንጌላት ያልተካተቱ ሌሎች ጉዳዮች ይኖሩ ይሆናል።

48 እያንዳንዱ ባርኮት የእግዚአብሔር መንግሥት ተሳታፊ ለሆኑ ሰዎች ከተሰጠው የብሉይ ኪዳን ተስፋ ጋር የተያያዘ ነው። በዚህ ሁኔታ ነው ኢየሱስ ይናገር የነበረው ስለየትኛው መንግሥት መሆኑን ያስታወቀው።

## ♦ ክፍል 54ሐ. መንግሥቱን በመጠበቅ ወቅት የአኗኗር ኃላፊነት

[ክፍል 64ለ፥ 91፥ 106ና 115ን ይመልከቱ]

<u>ማቴዎስ 5፡13-16</u>

13 እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ
ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም።

14 እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር
አይቻላትም። 15 መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ
ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል። 16 መልካሙን ሥራችሁን አይተው
በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።

## ♦ ክፍል 54መ. ሕግ፥ ጽድቅና መንግሥት

[ክፍል 117ለን ይመልከቱ]

<u>ማቴዎስ 5፡17-20</u>

17 እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤[49] ልፈጽም እንጂ ለመሻር
አልመጣሁም። 18 እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ
አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። 19
እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ
የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን
የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል። 20
እላችኋለሁና፦ ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ
ሰማያት ከቶ አትገቡም።

## ♦ ክፍል 54ሠ. ሕግን በመተርጎም ረገድ ስድስት ማነጻጸሪያዎች

[ክፍል 91፥ 108ሠ፥ 117ለ፥ 122ና 137ሀን ይመልከቱ]

<u>ማቴዎስ 5፡21-48</u>

21 ለቀደሙት፦ አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል [ዘጸአት 20፡13፥ ዘዳግም
5፡17]፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። 22 እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ
የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ
ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።

23 እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች
በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥ 24 በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥
አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።

25 አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ
እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው፥ ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤ 26 እውነት እልሃለሁ፥

---

49 [ማቴ. 5፡17] ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ትምህርቶች ከመሻር ይልቅ ትክክለኛውን ሕግ በዘመኑ ከነበሩት መምህራን ትርጉም ጋር በማነጻጸር ፍሬ እንዲያፈሩ ያስችላቸው ዘንድ መጣ። በመሆኑም የስብከቱ ዋነኛ ጥቅስ ማቴዎስ 5፡20 ነበር። የሕግ መምህራንና ያፈሪሳውያን ጽድቅ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊያስገባቸው አይችልም። ምክንያቱም ጽድቃቸው ውጫዊ ባሕርይ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ነው። ወደተስፋው መንግሥት የመግቢያው መስፈርት ኢየሱስ በትምህርቱ ላይ ያቀረበው ነው (ማቴ. 7፡21፥ ክፍል 54ሸ)።

(ማቴዎስ 5፡21-48 የቀጠለ)

የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም።

27 አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል [ዘጸአት 20፡14፥ ዘዳግም 5፡18]። 28 እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኘትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል። 29 ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና። 30 ቀኝ እጅህም ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻላልና።

31 ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ [ዘዳግም 24፡1፥ 3]። 32 እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።

33 ደግሞ ለቀደሙት፦ በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደተባለ ሰምታችኋል። [ዘሌዋውያን 19፡12፤ ዘኍልቍ 30፡2፤ ዘዳግም 23፡21] 34 እኔ ግን እላችኋለሁ፦ ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ 35 በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤ [መዝሙር 48፡2] 36 በራስህም አትማል፥ አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና። 37 ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።

38 ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። [ዘጸአት 21፡24፤ ዘሌዋውያን 24፡20፤ ዘዳግም 19፡21] 39 እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤ 40 እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት፤ 41 ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ። 42 ለሚለምንህ ስጥ፥ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል።

43 ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። [ዘሌዋውያን 19፡18] 44-45 እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።

46 የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? 47 ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ

ሉቃስ 6፡27-30፥ 32-36

27 ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ፥ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ፥ 28 የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ። 29 ጉንጭህን ለሚመታህ ደግሞ ሁለተኛውን ስጠው፥ መጐናጸፊያህንም ለሚወስድ እጀ ጠባብህን ደግሞ አትከልክለው። 30 ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ፥ ገንዘብህንም የሚወስድ እንዲመልስ አትጠይቀው።

32 የሚወዱአችሁንማ ብትወዱ፥ ምን ምስጋና አላችሁ? ኃጢአተኞች ደግሞ የሚወዱአቸውን ይወዳሉና። 33 መልካምም ለሚያደርጉላችሁ መልካም ብታደርጉ፥ ምን ምስጋና አላችሁ? ኃጢአተኞች ደግሞ ያን ያደርጋሉና። 34

(ማቴዎስ 5፡21-48 የቀጠለ)

ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ?
አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?

48 እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም
እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።

(ሉቃስ 6፡27-30፥ 32-36 የቀጠለ)

እንድትወስዱባቸው ተስፋ
ለምታደርጉአቸው ብታበድሩ፥ ምን
ምስጋና አላችሁ? ኃጢአተኞች ደግሞ
በትክክል እንዲቀበሉ ለኃጢአተኞች
ያበድራሉ። 35 ነገር ግን ጠላቶቻችሁን
ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤ ምንም ተስፋ
ሳታደርጉም አበድሩ፥ ዋጋችሁም ታላቅ
ይሆናል፥ የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ፥
እርሱ ለማያመሰግኑ ለክፉዎችም ቸር
ነውና። 36 አባታችሁ ርኅሩኅ እንደ ሆነ
ርኅሩኆች ሁኑ።

## ♦ ክፍል 54ረ. ሊወገዱ የሚገባቸውና ግብዝነት ያለባቸው ሦስት "የጽድቅ ሥራዎች"[50]

[ክፍል 105፥ 121ና 131ን ይመልከቱ]

ማቴዎስ 6፡1-18

1 ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ
በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም።

2 እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ፥ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም
እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን
ተቀብለዋል። 3-4 አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ
የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።

5 ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ
ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። 6
አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ
ጸልይ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል። 7 አሕዛብም በመናገራቸው
ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ። 8 ስለዚህ
አትምሰሉአቸው፤ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና።

9 እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡-

"በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ 10 ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ 11 የዕለት እንጀራችንን
ዛሬ ስጠን፤ 12 እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤
13 ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም
ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።"

14 ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር
ይላችኋልና፤ 15 ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ፥ አባታችሁም
ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።

50 በግልጥ የተነገሩ ሦስት "የጽድቅ ሥራዎች" ምፅዋት መስጠት (6፡2-4)፥ ጸሎት (6፡5-15) እና ጾም (6፡16-18) ናቸው። ፈሪሳውያን እነዚህን ይፈጽሙ የነበሩት ለታይታ ስለነበር፥ የማንኛውንም መለከታዊ ስጦታ ተስፋ አጡ።

(ማቴዎስ 6፡ 1-18 የቀጠለ)

16 ስትጦሙም፥ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። 17-18 አንተ ግን ስትጦም፥ በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።

## ♦ ክፍል 54ሰ. ንፉግነትን፥ የከፋ ፍርድን እና ብልህነት በጎደለው አኳኋን ቅዱስ የሆኑ ነገሮችን ማቃለልን በተመለከተ የቀረቡ ሦስት ክልከላዎች

[ክፍል 64ለ፥ 70ለ፥ 106፥ 108ሀ፥ 108ለ፥ 117፥ 145ና 150ለን ይመልከቱ]

ማቴዎስ 6፡ 19-7፡ 6

19 ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ 20 ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ 21 መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና።

22 የሰውነት መብራት ዓይን ናት። ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤ 23 ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፥ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ!

24 ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።

25 ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፥ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፤ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን? 26 ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፥ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? 27 ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው?

28 ስለ ልብስስ ስለ ምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፤ 29 አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም። 30 እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት? 31 እንግዲህ፡- ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ 32 ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና። 33 ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል። 34 ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል።

(ማቴዎስ 6፡19-7፡6 የቀጠለ)

1-2 እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፥ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል።

3 በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፥ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም? 4 ወይም ወንድምህን፦ ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም፥ በዓይንህ ምሰሶ አለ። 5 አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ፥ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።

6 በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም እንዳይነክሱአችሁ፥ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፥ ዕንቁዎቻችሁንም በእሪያዎች ፊት አትጣሉ።

ሉቃስ 6፡37-42

37 አትፍረዱ አይፈረድባችሁምም፤ አትኰንኑ አትኰነኑምም። ይቅር በሉ ይቅርም ትባላላችሁ። 38 ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፥ የተጨቈነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል።

39 ምሳሌም አላቸው፦ ዕውር ዕውርን ሊመራ ይችላልን? ሁለቱ በጉድጓድ አይወድቁምን? 40 ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል።

41 በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለ ምን ታያለህ፥ በራስህ ዓይን ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም? 42 በዓይንህ ያለውን ምሰሶ ራስህ ሳታይ፥ እንዴት ወንድምህን፦ ወንድሜ ሆይ፥ በዓይንህ ያለውን ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ ልትል ትችላለህ? አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያም በኋላ በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።

## ♦ ክፍል 54ሽ. ተግባርና ድምዳሜው

[ክፍል 61፥ 105ና 113ሀን ይመልከቱ]

ማቴዎስ 7፡7-27

7 ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል። 8 የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።

9 ወይስ ከእናንተ፥ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው? 10 ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን? 11 እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን

ሉቃስ 6፡31፥ 43-49

<u>(ማቴዎስ 7፡7-27 የቀጠለ)</u>

ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ
ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም
ነገርን ይሰጣቸው? 12 እንግዲህ ሰዎች
ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ
እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤
ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና።

13 በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት[51]
የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ
ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች
ናቸው፤ 14 ወደ ሕይወት የሚወስደው
ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥
የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።

15 የበግ ለምድ ለብሰው
ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን
ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች
ነቢያት ተጠንቀቁ። 16 ከፍሬያቸው
ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን
ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? 17
እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ
ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ
ያደርጋል። 18 መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ
ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ
ማፍራት አይቻለውም። 19 መልካም ፍሬ
የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ
እሳትም ይጣላል። 20 ስለዚህም
ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።

21 በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ
የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥
የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ
አይደለም። 22 በዚያ ቀን ብዙዎች፡- ጌታ
ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት
አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን
አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን
አላደረግንምን? ይሉኛል። 23 የዚያን
ጊዜም፡- ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ
ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክር
ባቸዋለሁ።

24 ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ
የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ

<u>(ሉቃስ 6፡31፥ 43-49 የቀጠለ)</u>

31 ሰዎችም ሊያደርጉላችሁ
እንደምትወዱ እናንተ ደግሞ እንዲሁ
አድርጉላቸው።

43 ክፉ ፍሬ የሚያደርግ መልካም ዛፍ
የለምና፥ እንዲሁም መልካም ፍሬ
የሚያደርግ ክፉ ዛፍ የለም። 44 ዛፍ ሁሉ
ከፍሬው ይታወቃልና፤ ከእሾህ በለስ
አይለቅሙም፥ ከአጣጥ ቍጥቋጦም ወይን
አይቈርጡም። 45 በልብ ሞልቶ
ከተረፈው አፉ ይናገራልና መልካም ሰው
ከልብ መልካም መዝገብ መልካሙን
ያወጣል፥ ክፉ ሰውም ከልብ ክፉ መዝገብ
ክፉውን ያወጣል።

46 ስለ ምን፡- ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥
ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም አታደርጉም?

47 ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም
ሰምቶ የሚያደርገው፥ ማንን እንዲመስል
አሳያችኋለሁ። 48 ቤት ሲሠራ አጥልቆ

51 [ማቴ. 7፡13-14፥ 21፥ 23] በኢየሱስ ትምህርት መሠረት ሕይወት ማግኘትና ወደ መንግሥቱ መግባት ተመሳሳይ ናቸው። በአንጻሩም ወደ ጥፋት መሄድ ከመንግሥቱ መወገድ ነው። በመሆኑም አንድ ሰው ከሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ጋር ግንኙነት መፍጠሩ ወሳኝ ይሆናል።

(ማቴዎስ 7፡7-27 የቀጠለ)

የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። 25
ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ
ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ
ተመሠረተ አልወደቀም። 26 ይህንም
ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ
ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን
ይመስላል። 27 ዝናብም ወረደ ጎርፍም
መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፥
ወደቀም፥ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ።

(ሉቃስ 6፡31፥ 43-49 የቀጠለ)

የቆፈረ በዓለት ላይም የመሠረተ ሰውን
ይመስላል፤ ጐርፍም በመጣ ጊዜ ወንዙ
ያን ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ
ተመሠረተ ሊያናውጠው አልቻለም። 49
ሰምቶ የማያደርገው ግን ያለ መሠረት
በምድር ላይ ቤቱን የሠራ ሰውን
ይመስላል፤ ወንዙም ገፋው ወዲያውም
ወደቀ የዚያ ቤት አወዳደቅም ታላቅ ሆነ።

## ♦ ክፍል 54ቀ. የሕዝቡ አጸፋ

ማቴዎስ 7፡28-8፡1

28 ኢየሱስም ይህን ነገር በጨረሰ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ፤ እንደ ጻፎቻቸው
ሳይሆን 29 እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና።

1 ከተራራም በወረደ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት።

# > በማደግ ላይ ያለ ዝናና ለንስሐ የተሰጠው ትኩረት<

## ♦ ክፍል 55. የመቶ አለቃው እምነትና የአገልጋዩ መፈወስ

- ቅፍርናሆም -

ማቴዎስ 8፡5-13

5 ወደ ቅፍርናሆምም በገባ ጊዜ የመቶ
አለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ፡- ጌታ ሆይ፥ 6
ብላቴናዬ ሽባ ሆኖ እጅግ እየተሠቀየ
በቤት ተኝቶአል ብሎ ለመነው።

7 ኢየሱስም፡- እኔ መጥቼ
እፈውሰዋለሁ አለው።

8 የመቶ አለቃውም መለሰ፡- ጌታ
ሆይ፥ በቤቴ ጣራ ከታች ልትገባ
አይገባኝም፤ ነገር ግን ቃል ብቻ ተናገር፥
ብላቴናዬም ይፈወሳል።

ሉቃስ 7፡1-10

1 ቃሉን ሁሉ በሕዝብ ጆሮዎች በጨረሰ
ጊዜ ወደ ቅፍርናሆም ገባ። 2 አንድ የመቶ
አለቃም ነበረ፤ የሚወደውም ባሪያው ታሞ
ሊሞት ቀርቦ ነበር። 3 ስለ ኢየሱስም በሰማ
ጊዜ የአይሁድን ሽማግሎች ወደ እርሱ
ላከና መጥቶ ባሪያውን እንዲያድን
ለመነው። 4 እነርሱም ወደ ኢየሱስ
መጥተው፡- ይህን ልታደርግለት
ይገባዋል፤ 5 ሕዝባችንን ይወዳልና
ምኵራብም ራሱ ሠርቶልናል ብለው
አጽንተው ለመኑት። 6 ኢየሱስም ከእነርሱ
ጋር ሄደ።

አሁንም ወደ ቤቱ በቀረበ ጊዜ የመቶው
አለቃ ወዳጆቹን ወደ እርሱ ላከ፤
አለውም፡- ጌታ ሆይ በቤቴ ጣራ በታች

52 [ማቴ. 8፡10፤ ሉቃስ 7፡9] ኢየሱስ ይህን መቶ አለቃ ከመሳሰሉና አይሁዳውያን ካልሆኑ ሰዎች ጋር መገናኘቱ በግልጥ ከታወቀውና የጠፉትን የእስራኤል ቤት በጎች መፈለግ ከሆነው ዓላማው (ማቴ. 15፡24፥ ክፍል 79) አንጻር ሲታይ አስደናቂ ነው። የአገልግሎቱ የቅርብ ተጠቃሚዎች የሆኑት አይሁዳውያን ከዚህ ሰው ብዙ ሊማሩ ይገባቸው ነበር።

(ማቴዎስ 8፡5-13 የቀጠለ)

9 እኔ ደግሞ ለሌሎች ተገዥ ነኝና፥ ከእኔም በታች ጭፍራ አለኝ፤ አንዱንም፦ ሂድ ብለው ይሄዳል፥ ሌላውንም፦ ና ብለው ይመጣል፥ ባሪያዬንም፦ ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል አለው።

10 ኢየሱስም ሰምቶ ተደነቀና ለተከተሉት እንዲህ አለ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ በእስራኤል[52] እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም። 11 እላችኋለሁም፥ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ፤ 12 የመንግሥት ልጆች ግን በውጭ ወደ አለው ጨለማ ይጣላሉ፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

13 ኢየሱስም ለመቶ አለቃ፦ ሂድና እንዳመንህ ይሁንልህ አለው። ብላቴናውም በዚያች ሰዓት ተፈወሰ።

(ሉቃስ 7፡1-10 የቀጠለ

ልትገባ አይገባኝምና አትድከም፤ 7 ስለዚህም ወደ አንተ ልመጣ እንዲገባኝ ሰውነቴን አልቈጠርሁትም፤ ነገር ግን ቃል ተናገር፥ ብላቴናዬም ይፈወሳል። 8 እኔ ደግሞ ከሌሎች በታች የምገዛ ሰው ነኝ፥ ከእኔም በታች ወታደሮች አሉኝ፥ አንዱንም፦ ሂድ ብለው ይሄዳል፥ ሌላውንም፦ ና ብለው ይመጣል፥ ባሪያዬንም፦ ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል።

9 ኢየሱስም ይህን ሰምቶ በእርሱ ተደነቀ፥ ዘወርም ብሎ ለተከተሉት ሕዝብ፦ እላችኋለሁ፥ በእስራኤልስ[52] እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም አላቸው።

10 የተላኩትም ወደ ቤት ተመልሰው ባሪያውን ባለ ጤና ሆኖ አገኙት።

## ♦ ክፍል 56. ናይን በተባለው ሥፍራ የአንዲት መበለት ልጅ ከሞት ተነሣ

- ናይን -

ሉቃስ 7፡11-17

11 በነገውም ናይን ወደምትባል ወደ አንዲት ከተማ ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ሕዝብም ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ። 12 ወደ ከተማይቱም በር በቀረበ ጊዜ፥ እነሆ፥ የሞተ ሰው ተሸከመው አወጡ፤ እርሱም ለእናቱ አንድ ልጅ ነበረ፥ እርስዋም መበለት ነበረች፥ ብዙም የከተማ ሕዝብ ከእርስዋ ጋር አብረው ነበሩ። 13 ጌታም ባያት ጊዜ አዘነላትና፦ አታልቅሺ አላት።

14 ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ፥ የተሸከሙትም ቆሙ፤ አለውም፦ አንተ ጐበዝ፥ እልሃለሁ፥ ተነሣ። 15 የሞተውም ቀና[53] ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ፥ ለእናቱም ሰጣት።

16 ሁሉንም ፍርሃት ያዛቸውና፦ ታላቅ ነቢይ በእኛ መካከል ተነሥቶአል፥ ደግሞ፦ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጐበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። 17 ይህም ዝና ስለ እርሱ በይሁዳ ሁሉ በዙሪያውም ባለች አገር ሁሉ ወጣ።

[53] [ሉቃስ 7፡15] ኢየሱስ በሌላ ጊዜ ሙታንን በማስነሣቱ ይታወቃል (ክፍል 67፤ 118ለ)። ሉቃስ 7፡22 (ክፍል 57) እንደሚያመለክተው፥ በግልጥ ባልታወቁ ጊዜያት ነበር ይህን የሚያደርገው።

## ♦ ክፍል 57. መጥምቁ ዮሐንስ ከመንግሥት ጋር ያለው ግንኙነት

- ገሊላ -

ማቴዎስ 11፡2-19

2 ዮሐንስም በወህኒ ሳለ የክርስቶስን
ሥራ ሰምቶ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት
ላከና፦[55] 3 የሚመጣው አንተ ነህን?[54]
ወይስ ሌላ እንጠብቅ? አለው።

4 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦
ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም
ለዮሐንስ አውሩለት፤ 5 ዕውሮች ያያሉ
አንካሶችም ይሄዳሉ፥ ለምጻሞችም
ይነጻሉ ደንቆሮችም ይሰማሉ፥ ሙታንም
ይነሣሉ 6 ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል
[ኢሳይያስ 35፡5-6፥ 61፡1]፤ በእኔም
የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው።

7 እነዚያም ሲሄዱ ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ
ዮሐንስ ሊናገር ጀመረ እንዲህም አለ፦
ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ? 8
ነፋስ የሚወዘውዘውን ሸምበቆን? ወይስ
ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ
የለበሰ ሰውን? እነሆ፥ ቀጭን ልብስ
የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ። 9 ወይስ
ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን
እላችኋለሁ፥ ከነቢይም የሚበልጠውን።

10 "እነሆ፥ መንገድህን በፊትህ
የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ
እልካለሁ"

ሉቃስ 7፡18-35

18 ደቀ መዛሙርቱም ለዮሐንስ እነዚህን
ሁሉ አወሩ። 19 ዮሐንስም ከደቀ
መዛሙርቱ ሁለት ወደ እርሱ ጠርቶ፦
የሚመጣው አንተ ነህን[54] ወይስ ሌላውን[55]
እንጠብቅ? ብሎ ወደ ኢየሱስ ላከ።

20 ሰዎቹም ወደ እርሱ መጥተው፦
መጥምቁ ዮሐንስ፦ የሚመጣው አንተ
ነህን ወይስ ሌላውን እንጠብቅ? ብሎ ወደ
አንተ ላከን አሉት።

21 በዚያች ሰዓት ከደዌና ከሥቃይ
ከክፉዎች መናፍስትም ብዙዎችን ፈወሰ፥
ለብዙ ዕውሮችም ማየትን ሰጠ። 22
ኢየሱስም መልሶ፦ ሄዳችሁ ያያችሁትን
የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤
ዕውሮች ያያሉ፥ አንካሶችም ይሄዳሉ፥
ለምጻሞችም ይነጻሉ፥ ደንቆሮዎችም
ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ፥ ለድሆችም
ወንጌል ይሰበካል፤ [ኢሳይያስ 35፡5-6፥
61፡1] 23 በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ
ብፁዕ ነው አላቸው።

24 የዮሐንስ መልክተኞችም ከሄዱ
በኋላ፥ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ይናገር ጀመር
እንዲህም አለ፦ ምን ልታዩ ወደ ምድረ
በዳ ወጣችሁ? ነፋስ የሚወዘውዘውን
ሸምበቆን? ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ?
25 ቀጭን ልብስ የለበሰውን ሰውን? እነሆ
፥ ጌጠኛ ልብስ የሚለብሱና በቅምጥልነት
የሚኖሩ በነገሥታት ቤት አሉ። 26 ወይስ
ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን
እላችኋለሁ፥ ከነቢይም የሚበልጠውን።

27 "እነሆ፥ መንገድህን በፊትህ
የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ
እልካለሁ" [ሚልክያስ 3፡1]

---

[54] [ማቴ. 11፡3፤ ሉቃስ 7፡19] አንዳንዶች ዮሐንስ በዚህ ጊዜ በእምነቱ ፈራ ተባ በማለቱ ይወቅሱታል። ይህ ግን ትክክል አይመስልም። የዮሐንስ ጥያቄ ክርስቶስ ከመንገሡ ይልቅ ሞቱ ለምን ይቀድማል በማለትና ትዕግሥት ከማጣት የግል ችግር የመነጨ ሊሆን ይችላል። ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት ይህን የድርጊቶች ቅደም ተከተል የተረዳ ሰው አልነበረም።

[55] [ማቴ. 11፡3፤ ሉቃስ 7፡19] "የሚመጣው" የሚለው ቃል የእስራኤል መሢሕ የታወቀ መጠሪያ ነበር።

(ማቴዎስ 11፡2-19 የቀጠለ)

11 ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነውና [ሚልክያስ 3፡1]። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም፤ በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል። 12 ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፥ ግፈኞችም ይናጠቋታል። 13 ነቢያት ሁሉና ሕጉ እስከ ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ፤ 14 ልትቀበሉትስ ብትወዱ፥ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው። 15 የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።

16 ነገር ግን ይህን ትውልድ በምን እመስለዋለሁ? በገበያ የሚቀመጡትን ልጆች ይመስላሉ፥ እነርሱም ባልንጀሮቻቸውን እየጠሩ:-

> 17 "እንቢልታ ነፋንላችሁ ዘፈንም አልዘፈናችሁም ሙሾ አወጣንላችሁ ዋይ ዋይም አላላችሁም" ይሉአቸዋል።

18 ዮሐንስ ሳይበላና ሳይጠጣ መጣ፥ እነርሱም:- ጋኔን አለበት አሉት። 19 የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፥ እነርሱም:- እነሆ፥ በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጭ፥ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ ይሉታል። ጥበብም በልጆችዋ ጸደቀች።

(ሉቃስ 7፡18-35 የቀጠለ)

ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነው።

28 እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል።

29 የሰሙትም ሕዝብ ሁሉ ቀራጮች እንኳ ሳይቀሩ በዮሐንስ ጥምቀት ተጠምቀው እግዚአብሔርን አጸደቁ፤ 30 ፈሪሳውያንና ሕግ አዋቂዎች ግን በእርሱ ስለ አልተጠመቁ የእግዚአብሔርን ምክር ከራሳቸው ጣሉ።

31 እንግዲህ የዚችን ትውልድ ሰዎች በምን አስመስላቸዋለሁ? ማንንስ ይመስላሉ? 32 በገበያ የሚቀመጡትን ልጆች ይመስላሉ፥ እርስ በርሳቸውም እየተጠራሩ:-

> "እንቢልታ ነፋንላችሁ አልዘፈናችሁምም፤ ሙሾ አወጣንላችሁ አላለቀሳችሁምም" ይላል።

33 መጥምቁ ዮሐንስ እንጀራ ሳይበላ የወይን ጠጅም ሳይጠጣ መጥቶ ነበርና:- ጋኔን አለበት አላችሁት። 34 የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጥቶአልና:- እነሆ፥ በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጭ፥ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ አላችሁት። 35 ጥበብም ለልጆችዋ ሁሉ ጸደቀች።

## ♦ ክፍል 58. የኮራዚ እና የቤተ ሳይዳ ከተማዎች ንስሐ ባለመግባታቸው ወየውላችሁ መባላቸው

[ክፍል 102ህን ይመልከቱ]

-ገሊላ-

ማቴዎስ 11፡20-30

20 በዚያን ጊዜ የሚበዙ ተአምራት የተደረገባቸውን ከተማዎች ንስሐ ስላልገቡ ሊነቅፋቸው ጀመረ[56] እንዲህም አለ:- 21 ወዮልሽ ኮራዚ፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ማቅ ለብሰው

(ማቴዎስ 11፡20-30 የቀጠለ)

አመድም ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበርና። 22 ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል። 23 አንቺም ቅፍርናሆም፥ እስከ ሰማይ ከፍ አልሽን? ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረገው ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን፥ እስከ ዛሬ በኖረች ነበርና። 24 ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ለሰዶም አገር ይቀልላታል።

25 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ፦ አባት ሆይ፥ የሰማይና የምድር ጌታ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤
26 አዎን፥ አባት ሆይ፥ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና።

27 ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፤ ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፥ ከወልድም በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም።

28 እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ[57] የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።
29 ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ 30 ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።

## ♦ ክፍል 59. በኃጢአቷ የተጸጸተች ሴት የክርስቶስን እግሮች ሽቶ ቀባቻቸው

[ክፍል 141ን ይመልከቱ]

- በገሊላ፥ በፈሪሳዊው ስምዖን ቤት -

ሉቃስ 7፡36-50

36 ከፈሪሳውያንም[58] አንድ ከእርሱ ጋር ይበላ ዘንድ ለመነው፤ በፈሪሳዊው ቤትም ገብቶ በማዕድ ተቀመጠ። 37 እነሆም በዚያች ከተማ ኃጢአተኛ የነበረች አንዲት ሴት፤[59] በፈሪሳዊው ቤት በማዕድ እንደ ተቀመጠ ባወቀች ጊዜ፥ ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ አመጣች። 38 በስተ ኋላውም በእግሩ አጠገብ ቆማ እያለቀሰች በእንባዋ እግሩን ታርስ ጀመረች፥ በራስ ጠጕርዋም ታብሰው እግሩንም ትስመው ሽቱም ትቀባው ነበረች።

39 የጠራው ፈሪሳዊም አይቶ፦ ይህስ ነቢይ ቢሆን፥ ይህች የምትዳስሰው ሴት ማን እንደ ሆነች እንዴትስ እንደ ነበረች ባወቀ ነበር፥ ኃጢአተኛ ናትና ብሎ በልቡ አሰበ።

---

56 [ማቴ. 11፡20] የክርስቶስ አገልግሎት ሌላ ጅማሬ እዚህ ተመልክቷል። ይኸውም የርሱንም ሆነ የመጥምቁ ዮሐንስን ስብከት ሰምተው ንስሐ ለመግባት ባልፈቀዱት ላይ የተገለጠ ፍርድ ነበር። እዚህ ላይ የጌታ ቃላት ይበልጥ ከረር ብለዋል። ስለሌሎቹ ጅማሬዎች (ማቴ. 4፡17፥ ክፍል 37 እና ማቴ. 16፡21፥ ክፍል 83ን) ይመልከቱ።

57 [ማቴ. 11፡28] ከባዱ ሸክም ምናልባት የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን በሕዝቡ ላይ የጫኑት ሰው ሠራሽ ሥርዓት ሳይሆን አይቀርም (ማቴ. 23፡4፥ ክፍል 137ሀ)።

58 [ሉቃስ 7፡36] በኢየሱስና በፈሪሳውያን መካከል የነበረው ጸብ እየከረረ ቢመጣም፥ ገና ከሚበጠስበት ደረጃ ላይ አልደረሰም። ስምዖን ከማን ጋር መወገን እንዳለበት ገና ያልወሰነ ይመስላል። ኢየሱስ ነቢይ መሆኑን አምኗል (7፡39)። ለእርሱ ያለው ፍቅር ከኃጢአተኛይቱ ሴት ጋር ሲወዳደር ግን ዝቅተኛ ነበር።

59 [ሉቃስ 3፡37] ይህች ሴት በኋላም የጌታን እግር ሽቶ ከቀባችው የቢታንያዋ ማርያም የተለየች መሆኗ ሊታወቅ ይገባል (ክፍል 118ሀ፤ 141)።

(ሉቃስ 7፤36-50 የቀጠለ)

40 ኢየሱስም መልሶ፡- ስምዖን ሆይ፥ የምነግርህ ነገር አለኝ አለው። እርሱም፡-
መምህር ሆይ፥ ተናገር አለ።

41 ለአንድ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት በአንዱ አምስት መቶ ዲናር ነበረበት
በሁለተኛውም አምሳ። 42 የሚከፍሉትም ቢያጡ ለሁለቱም ተወላቸው። እንግዲህ
ከእነርሱ አብልጦ የሚወደው ማንኛው ነው?

43 ስምዖንም መልሶ፡- ብዙ የተወለቱ ይመስለኛል አለ። እርሱም፡- በእውነት
ፈረድህ አለው።

44 ወደ ሴቲቱም ዘወር ብሎ ስምዖንን እንዲህ አለው፡- ይህችን ሴት ታያለህን? እኔ
ወደ ቤትህ ገባሁ፥ ውኃ ስንኳ ለእግሬ አላቀረብህልኝም፤ እርስዋ ግን በእንባዋ እግሬን
አራሰች በጠጕርዋም አበሰች። 45 አንተ አልሳምኸኝም፤ እርስዋ ግን ከገባሁ ጀምራ
እግሬን ከመሳም አላቋረጠችም። 46 አንተ ራሴን ዘይት አልቀባኸኝም፤ እርስዋ ግን
እግሬን ሽቱ ቀባች። 47 ስለዚህ እልሃለሁ፥ እጅግ ወዳለችና ብዙ ያለው ኃጢአትዋ
ተሰርዮላታል፤ ጥቂት ግን የሚሰረይለት ጥቂት ይወዳል።

48 እርስዋንም፡- ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል አላት።

49 ከእርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩት በልባቸው፡- ኃጢአትን እንኳ
የሚያስተሰርይ ይህ ማን ነው? ይሉ ጀመር።

50 ሴቲቱንም፡- እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ አላት።

# > የአይሁድ መሪዎች የመጀመሪያ ግልጥ ተቃውሞ <

## ♦ ክፍል 60. ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርትና ከሌሎች ጋር የተደረገ ጉዞ

- ገሊላ -

ሉቃስ 8፤1-3

1 ከዚህም በኋላ እየሰበከና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች እየተናገረ
በየከተማይቱ በየመንደሩም ያልፍ ነበር፤ 2 አሥራ ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፥
ከክፉዎች መናፍስትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች፤[60] እነርሱም ሰባት
አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የምትባል ማርያም፥ 3 የሄሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት
ዮሐናም ሶስናም ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር።

60 [ሉቃስ 8፤2] የሃይማኖት መምህራንን ለመርዳት ብዙ ገንዘብ ማውጣት በአንደኛው ክፍለ ዘመን ለነበረች አይሁዳዊት ሴት የተለመደ ጉዳይ ነበር። ለሰጪዎቹ የሚገኝ ተጨማሪው ማበረታቻ ግን፥ ከኢየሱስ የሚሰጣቸው መንፈሳዊና አካላዊ እርዳታ ነበር። ይህ ሴቶች ተከታዮችንና አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ያካተተ ጉዞ፥ በወንጌሉ ለሴቶች ልዩ ሥፍራ በሚሰጠው ሉቃስ ብቻ ነው የተጠቀሰው።

## ♦ ክፍል 61. ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን በክርስቶስ ላይ ያቀረቡት ስድብ አዘል ክስ

[ክፍል 54ሽ፥ 68፥ 91፥ 106ና 108ሀን ይመልከቱ]

- ገሊላ -

<u>ማቴዎስ 12፡22-37</u>

22 ከዚህም በኋላ ጋኔን ያደረበትን ዕውር ዲዳም ወደ እርሱ አመጡ፤ ዕውሩም ዲዳውም እስኪያይና እስኪናገር ድረስ ፈወሰው። 23 ሕዝቡም ሁሉ ተገረሙና፦ እንጃ ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን?[61] አሉ።

24 ፈሪሳውያን ግን ሰምተው፦ ይህ በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም አሉ።

25 ኢየሱስ ግን አሳባቸውን አውቆ እንዲህ አላቸው፦ እርስ በርስዋ የምትለያይ መንግሥት ሁላ ትጠፋለች፥ እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም። 26 ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያወጣ ከሆነ፥ እርስ በርሱ ተለያየ፥ እንግዲህ መንግሥቱ እንዴት ትቆማለች? 27 እኔስ በብዔል ዜቡል አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ ልጆቻችሁ በማን ያወጡአቸዋል? ስለዚህ እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባችኋል። 28 እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት[62] ወደ እናንተ ደርሳለች።

<u>ማርቆስ 3፡20-30</u>

20 ወደ ቤትም መጡ፤ እንጀራም መብላት ስንኳ እስኪሳናቸው ድረስ እንደ ገና ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ። 21 ዘመዶቹም ሰምተው፦ አበደ ብለዋልና ሊይዙት ወጡ።

22 ከኢየሩሳሌም የወረዱ ጻፎችም፦ ብዔል ዜቡል አለበት፤ ደግሞ፦ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ብለው ተናገሩ።

23 እነርሱንም ወደ እርሱ ጠርቶ በምሳሌ አላቸው፦ ሰይጣን ሰይጣንን ሊያወጣው እንዴት ይችላል? 24 መንግሥትም እርስ በርስዋ ከተለያየች ያች መንግሥት ልትቆም አትችልም፤ 25 ቤትም እርስ በርሱ ከተለያየ ያ ቤት ሊቆም አይችልም። 26 ሰይጣንም ራሱን ተቃውሞ ከተለያየ፥ መጨረሻ ይሆንበታል እንጂ ሊቆም አይችልም።

---

61 [ማቴ. 12፡23] ይህ ጥያቄ በኢየሱስና በአይሁድ ባለሥልጣናት መካከል እያደገ በመጣው ቅራኔ ላይ በመመሥረት የመጀመሪያውን የሕዝብ ተቃውሞ አስነሣ። "የዳዊት ልጅ" የሚለው ቃል ለመሲሑ ብዙ ጊዜ አገልግሏል። ስለዚህ ኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉት የተቃዋሚ አይሁዳውያን ወኪሎች (ማር. 3፡22)፥ ኢየሱስ ራሱን ከስሙ ጋር በማገናኘቱ እጅግ በተቃውሞ ለመናገር ተገደዱ። ተቃውሞው የኢየሱስ ዘመዶች እንኳን አብዷል ብለው (ማር. 3፡21) እስኪያስቡ ድረስ የከረረ ነበር። ይህ ተቃውሞ በኢየሱስ አገልግሎት ዋናው የአቅጣጫ መለወጫ ነጥብ ሆነ።

(ማቴዎስ 12፡22-37 የቀጠለ)

29 ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል።

30 ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፥ ከእኔ ጋርም የማያከማች ይበትናል። 31 ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፥ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም። 32 በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም።

33 ዛፍ ከፍሬዋ ትታወቃለችና ዛፍዋን መልካም፥ ፍሬዋንም መልካም አድርጉ፥ ወይም ዛፍዋን ክፉ ፍሬዋንም ክፉ አድርጉ። 34 እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና። 35 መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል፥ ክፉ ሰውም ከክፉ መዝገብ ክፉ ነገርን ያወጣል። 36 እኔ እላችኋለሁ፥ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ 37 ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ።

(ማርቆስ 3፡20-30 የቀጠለ)

27 ነገር ግን አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊበዘብዝ የሚችል የለም፥ ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል። 28 እውነት እላችኋለሁ፥ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሁሉ የሚሳደቡትም ስድብ ሁሉ ይሰረይላቸዋል፤ 29 በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ ግን የዘላለም ኃጢአት ዕዳ ይሆንበታል እንጂ ለዘላለም አይሰረይለትም።

30 ርኩስ መንፈስ አለበት ይሉ ነበርና።

## ♦ ክፍል 62. ክርስቶስ ምልክት እንዲያሳይ ተጠይቆ እምቢ አለ

[ክፍል 80ና 106ን ይመልከቱ]

- ገሊላ -

ማቴዎስ 12፡38-45

38 በዚያን ጊዜ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ መለሱና፦ መምህር ሆይ፥ ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወዳለን አሉ።

39 እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። 40 ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ [ዮናስ 1፡17]፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል። 41 የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋልና፥ እነሆም፥ ከዮናስ

(ማቴዎስ 12፡38-45 የቀጠለ)

የሚበልጥ ከዚህ አለ። 42 ንግሥተ ዓዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ
ትፈርድበታለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፥ እነሆም፥
ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ።

43 ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ፥ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ
ያልፋል፥ አያገኝምም። 44 በዚያን ጊዜም፦ ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤
ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል። 45 ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ
የከፉትን ሰባት ሌሎችን አጋንንት ከእርሱ ጋር ይወስዳል፥ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤
ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል። ለዚህ ክፉ ትውልድ ደግሞ
እንዲሁ ይሆንበታል።

## ♦ ክፍል 63. የአዲሱ መንፈሳዊ አንድነት መገለጥ

- ገሊላ -

ማቴዎስ 12፡46-50

46 ገናም ለሕዝቡ
ሲናገር፥ እነሆ፥ እናቱና
ወንድሞቹ[63] ሊነጋገሩት
ፈልገው በውጭ ቆመው
ነበር። 47 አንዱም፦
እነሆ፥ እናትህና
ወንድሞችህ ሊነጋገሩህ
ፈልገው በውጭ ቆመዋል
አለው።

48 እርሱ ግን ለነገረው
መልሶ፦ እናቴ ማን ናት?
ወንድሞቼስ እነማን
ናቸው? አለው። 49
እጁንም ወደ ደቀ
መዛሙርቱ ዘርግቶ፦ እነሆ
እናቴና ወንድሞቼ፤ 50
በሰማያት ያለውን የአባቴን
ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥
እርሱ ወንድሜ እኅቴም
እናቴም ነውና አለ።

ማርቆስ 3፡31-35

31 እናቱና[63]
ወንድሞቹም መጡ
በውጭም ቆመው ወደ
እርሱ ልከው አስጠሩት።
32 ብዙ ሰዎችም
በዙሪያው ተቀምጠው
ነበሩና፦ እነሆ፥ እናትህ
ወንድሞችህም በውጭ
ቆመው ይፈልጉሃል
አሉት።

33 መልሶም፦ እናቴ
ማን ናት? ወንድሞቼስ እነ
ማን ናቸው? አላቸው።

34 በዙሪያው
ተቀምጠው ወደ ነበሩትም
ተመለከተና፦ እነሆ እናቴ
ወንድሞቼም። 35
የእግዚአብሔርን ፈቃድ
የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ
ወንድሜ ነው እኅቴም
እናቴም አለ።

ሉቃስ 8፡19-21

19 እናቱና[63]
ወንድሞቹም ወደ እርሱ
መጡ፥ ከሕዝቡም ብዛት
የተነሣ ሊያገኙት
አልተቻላቸውም። 20
እናትህና ወንድሞችህ
ሊያዩህ ወድደው በውጭ
ቆመዋል ብለው ነገሩት።

21 እርሱም መልሶ፦
እናቴና ወንድሞቼስ
የእግዚአብሔርን ቃል
ሰምተው የሚያደርጉት
እነዚህ ናቸው አላቸው።

---

62 [ማቴ. 12፡28] የእግዚአብሔር መንግሥት መምጫ ከንጉሡ መምጫ ጋር ተገናኝቷል። ሆኖም መልካም ያልሆነው የእስራኤል ግንዛቤ ስለዚህ ጉዳይ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የተነገረውን የትንቢት ፍጻሜ አዘገየው። ያለጥርጥር፥ ኢየሱስም የሚጠበቁ ነገሮች ሁሉ ስለሚከናወኑበት የወደፊት የእግዚአብሔር መንግሥት ተናግሯል (ማቴ. 25፡31፥ ክፍል 139ሰ)።

# > የእግዚአብሔር መንግሥት ምሥጢራት በምሳሌ ተገለጡ <

## -- ባሕሩ ዳር ለተሰበሰቡ ሕዝቦች --

### ♦ ክፍል 64ሀ. የምሳሌዎቹ አጀማመር

| ማቴዎስ 13፡1-3ሀ | ማርቆስ 4፡1-2 | ሉቃስ 8፡4 |
|---|---|---|
| 1 በዚያን ቀን ኢየሱስ ከቤት ወጥቶ በባሕር አጠገብ ተቀመጠ፤ 2 እርሱም በታንኳ ገብቶ እስኪቀመጥ ድረስ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፥ ሕዝቡም ሁሉ በወደቡ ቆመው ነበር። 3 በምሳሌም ብዙ ነገራቸው እንዲህም አላቸው፡- | 1 ደግሞም በባሕር ዳር ሊያስተምር ጀመረ። እጅግ ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ ስለ ተሰበሰቡ እርሱ በታንኳ ገብቶ በባሕር ላይ ተቀመጠ፤ ሕዝቡም ሁሉ በባሕር ዳር በምድር ላይ ነበሩ። 2 በምሳሌም ብዙ ያስተምራቸው ነበር፥ በትምህርቱም አላቸው፡- ስሙ። | 4 ብዙ ሕዝብም በተሰበሰቡ ጊዜ ከከተማዎችም ሁሉ ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ በምሳሌ እንዲህ ሲል ተናገ ራቸው፡- |

### ♦ ክፍል 64ለ. የአፈሮቹ ምሳሌ

[ክፍል 54ሐ፥ 54ሰ፥ 71ሀ፥ 106ና 108ለን ይመልከቱ]

| ማቴዎስ 13፡3ለ-23 | ማርቆስ 4፡3-25 | ሉቃስ 8፡5-18 |
|---|---|---|
| እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ። 4 እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፥ ወፎችም መጥተው በሉት። 5 ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፥ 6 ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው | 3-4 እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ። ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀና ወፎች መጥተው በሉት። 5 ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀና ጥልቅ መሬት ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤ 6 ፀሐይም ሲወጣ ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። 7 | 5 ዘሪ ዘሩን ሊዘራ ወጣ። ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ ተረገጠም፥ የሰማይ ወፎችም በሉት። 6 ሌላውም በዓለት ላይ ወደቀ፥ በበቀለም ጊዜ እርጥበት ስላልነበረው ደረቀ። 7 ሌላውም በእሾህ |

63 [ማቴ. 12፡46፤ ማር. 3፡31፤ ሉቃስ 8፡19] የኢየሱስ ቤተሰብ አመጣጥ እርሱን ለመርዳት ቢሆንም፥ አብዷል የሚል ጥርጣሬም ነበራቸው። ማርያም ትዕግሥቷ ያለቀ መሆኑን አመልክታለች (ዮሐ. 2፡3፥ ክፍል 29)። ወንድሞቹም ተችዎቹ ነበሩ (ዮሐ. 7፡3-5፥ ክፍል 94)። የሃይማኖት መሪዎቻቸውን መቃወሙን እንዲገታ ፈልገዋል። እርሱም የቤተሰቡን ፍላጎት አውቆ መንፈሳዊ ዝምድና ከሥጋዊ ዝምድና የሚቀድም መሆኑን ለመግለጥ አጋጣሚውን ተጠቀመ። የራሱ ወገኖች፥ ሥራው ከሰይጣን ጋር ግንኙነት አለው በማለት ወንጅለው በተለዩት ጊዜ የመጣ ጥሩ ትምህርት ነበር።

(ማቴዎስ 13፡3ለ-23 የቀጠለ)

ደረቀ። 7 ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው።

8 ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ። 9 የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።

10 ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፦ ስለ ምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ? አሉት።

11 እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፥ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም። 12 ላለው ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። 13 ስለዚህ

> "እያዩ ስለማያዩ እየሰሙም ስለማይሰሙ ስለማያስተውሉም"

በምሳሌ እነግራቸዋለሁ።

> 14 "መስማትን ትሰማላችሁና አታስተውሉም፥ ማየትም ታያላችሁና አትመለከቱም። 15 በዓይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥

(ማርቆስ 4፡3-25 የቀጠለ)

ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው፥ ፍሬም አልሰጠም። 8 ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀና ወጥቶ አድጎ ፍሬ ሰጠ፥ አንዱም ሠላሳ አንዱም ስድሳ አንዱም መቶ አፈራ።

9 የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ አለ።

10 ብቻውንም በሆነ ጊዜ፥ በዙሪያው የነበሩት ከአሥራ ሁለቱ ጋር ስለ ምሳሌው ጠየቁት።

11-12 እንዲህም አላቸው፦ ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ በውጭ ላሉት[64] ግን፥

> "አይተው እንዲያዩ እንዳይመለከቱም፥ ሰምተውም እንዲሰሙ እንዳያስተውሉም፥ እንዳይመለሱ ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸው ነገር ሁሉ በምሳሌ ይሆንባቸዋል።" [ኢሳያይስ 6፡9-10]

(ሉቃስ 8፡5-18 የቀጠለ)

መካከል ወደቀ፥ እሾሁም አብሮ በቀለና አነቀው።

8 ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀ፤ በበቀለም ጊዜ መቶ እጥፍ አፈራ።

ይህን በተናገረ ጊዜ፦ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ ብሎ ጮኸ።

9 ደቀ መዛሙርቱም፦ ይህ ምሳሌ ምንድር ነው? ብለው ጠየቁት።

10 እርሱም እንዲህ አለ፦ ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ ለሌሎች ግን

> "እያዩ እንዳያዩ እየሰሙም እንዳያስተውሉ" [ኢሳይያስ 6፡9]

በምሳሌ ነው።

---

64 [ማር. 4፡12] ኢየሱስ እውነቱን የርሱ ካልሆኑት ለመሰወር የነበረው ውሳኔ፥ በጠዋት በተከናወኑ ሁኔታዎች መታወቁ ትኩረት የሚስብ ነገር ነው። ይህን ሲናገር ከጥቂት ሰዓታት በፊት መለኮታዊ ሥልጣኑን አናምንም ያሉትን ሰዎች እያሰበ ነበር (ክፍል 61ን ይመልከቱ)።

(ማቴዎስ 13፡3ለ-23 የቀጠለ)

ተመልሰውም
እንዳልፈውሳቸው፥
የዚህ ሕዝብ ልብ
ደንድኖአልና
ጆሮአቸውም
ደንቁሮአል
ዓይናቸውንም
ጨፍነዋል”
የሚል የኢሳይያስ ትንቢት
በእነርሱ ይፈጸማል።
[ኢሳይያስ 6:9-10]

16 የእናንተ ግን
ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ
ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ
ብፁዓን ናቸው። 17 እውነት
እላችኋለሁ፥ ብዙዎች
ነቢያትና ጻድቃን
የምታዩትን ሊያዩ
ተመኝተው አላዩም፥
የምትሰሙትንም ሊሰሙ
ተመኝተው አልሰሙም።

18 እንግዲህ እናንተ
የዘሪውን ምሳሌ ስሙ። 19
የመንግሥትን ቃል ሰምቶ
በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው
ይመጣል፥ በልቡ
የተዘራውንም ይነጥቃል፤
በመንገድ ዳር የተዘራው
ይህ ነው። 20 በጭንጫ ላይ
የተዘራውም ይህ ቃሉን
ሰምቶ ወዲያው በደስታ
የሚቀበለው ነው፤ 21 ነገር
ግን ለጊዜው ነው እንጂ
በእርሱ ሥር የለውም፥
በቃሉ ምክንያትም መከራ
ወይም ስደት በሆነ ጊዜ
ወዲያው ይሰናከላል። 22
በእሾህ መካከል
የተዘራውም ይህ ቃሉን
የሚሰማ ነው፥ የዚህም
ዓለም አሳብና የባለጠግነት
መታለል ቃሉን ያንቃል፥

(ማርቆስ 4፡3-25 የቀጠለ)

13 አላቸውም፡- ይህን
ምሳሌ አታውቁምን?
እንዴትስ ምሳሌዎቹን
ሁሉ ታውቃላችሁ? 14
ዘሪው ቃሉን ይዘራል።
ቃልም በተዘራበት
በመንገድ ዳር የሆኑት
እነዚህ ናቸው፥ 15
በሰሙት ጊዜም ሰይጣን
ወዲያው መጥቶ በልባቸው
የተዘራውን ቃል
ይወስዳል። 16 እንዲሁም
በጭንጫ ላይ የተዘሩት
እነዚህ ናቸው፥ ቃሉንም
ሰምተው ወዲያው በደስታ
ይቀበሉታል፥ 17
ለጊዜውም ነው እንጂ
በእነርሱ ሥር የላቸውም፥
ኋላም በቃሉ ምክንያት
መከራ ወይም ስደት በሆነ
ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ።
18 በእሾህም የተዘሩት
ሌሎች ናቸው፥ ቃሉን
የሰሙት እነዚህ ናቸው፥
19 የዚህም ዓለም አሳብና
የባለጠግነት ማታለል
የሌላውም ነገር ምኞት
ገብተው ቃሉን ያንቃሉ፥
የማያፈራም ይሆናል። 20
በመልካምም መሬት
የተዘሩት ቃሉን ሰምተው
የሚቀበሉት አንዱም ሠላሳ
አንዱም ስድሳ አንዱም
መቶ ፍሬ የሚያፈሩት
እነዚህ ናቸው።

21 እንዲህም አላቸው፡-
መብራትን ከዕንቅብ ወይስ
ከአልጋ በታች ሊያኖሩት
ያመጡታልን? በመቅረዝ
ላይ ሊያኖሩት

(ሉቃስ 8፡5-18 የቀጠለ)

11 ምሳሌው ይህ ነው።
ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል
ነው። 12 በመንገድ ዳርም
ያሉት የሚሰሙ ናቸው፤
ከዚህ በኋላም ዲያብሎስ
ይመጣል አምነውም
እንዳይድኑ ቃሉን
ከልባቸው ይወስዳል። 13
በዓለት ላይም ያሉት
ሲሰሙ ቃሉን በደስታ
የሚቀበሉ ናቸው፤
እነርሱም ለጊዜው ብቻ
ያምናሉ እንጂ በፈተና ጊዜ
የሚክዱ ሥር የሌላቸው
ናቸው። 14 በእሾህ
መካከልም የወደቀ እነዚህ
የሚሰሙት ናቸው፤
መንገዳቸውንም ሄደው
በሕይወት ዘመን በአሳብና
በባለ ጠግነት ምቾት
ይታነቃሉ፥ ሙሉ ፍሬም
አያፈሩም። 15 በመልካም
መሬት ላይም የወደቀ
እነርሱ በመልካምና በበጎ
ልብ ቃሉን ሰምተው
የሚጠብቁት በመጽናትም
ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው።

16 መብራትንም አብርቶ
በዕቃ የሚከድነው ወይም
ከአልጋ በታች የሚያኖረው
የለም፥ የሚገቡት ሰዎች
ብርሃኑን እንዲያዩ

(ማቴዎስ 13፡3ለ-23 የቀጠለ)

የማያፈራም ይሆናል። 23
በመልካም መሬት
የተዘራውም ይህ ቃሉን
ሰምቶ የሚያስተውል ነው፤
እርሱም ፍሬ ያፈራል
አንዱም መቶ አንዱም
ስድሳ አንዱም ሠላሳ
ያደርጋል።

(ማርቆስ 4፡3-25 የቀጠለ)

አይደለምን? 22 እንዲገለጥ
ባይሆን የተሰወረ የለምና፤
ወደ ግልጥ እንዲመጣ እንጂ
የተሸሸገ የለም። 23
የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር
ይስማ።

24 አላቸውም፦ ምን
እንድትሰሙ ተጠበቁ።
በምትሰፍሩበት መስፈሪያ
ይሰፈርላችኋል ለእናንተም
ይጨመርላችኋል። 25
ላለው ይሰጠዋልና፤
ከሌለውም ያው ያለው
እንኳ ይወሰድበታል።

(ሉቃስ 8፡5-18 የቀጠለ)

በመቅረዝ ላይ ያኖረዋል
እንጂ። 17 የማይገለጥ
የተሰወረ የለምና፥
የማይታወቅም ወደ
ግልጥም የማይመጣ
የተሸሸገ የለም። 18
እንግዲህ እንዴት
እንድትሰሙ ተጠበቁ፤
ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና፥
ከሌለውም ሁሉ፥ ያው
ያለው የሚመስለው እንኳ
ይወሰድበታል።

## ♦ ክፍል 64ሐ. የዘሩ ፈጣን እድገት ምሳሌ

ማርቆስ 4፡26-29

26 እርሱም አለ፦ በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት
እንደዚህ ናት ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም፥ 27 እርሱም እንዴት እንደሚሆን
ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማል። 28 ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም
ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች። 29 ፍሬ ግን ሲበስል መከር ደርሶአልና
ወዲያው ማጭድ ይልካል።

## ♦ ክፍል 64መ. የእንክርዳዱ ምሳሌ

ማቴዎስ 13፡24-30

24 ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ፦ መንግሥተ ሰማያት በእርሻው
መልካም ዘርን የዘራን ሰው ትመስላለች። 25 ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና
በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ። 26 ስንዴውም በበቀለና በአፈራ ጊዜ
እንክርዳዱ ደግሞ ያን ጊዜ ታየ።

27 የባለቤቱም ባሮች ቀርበው፦ ጌታ ሆይ፥ መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ
አልነበርህምን? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ? አሉት።

28 እርሱም፦ ጠላት ይህን አደረገ አላቸው። ባሮቹም፦ እንግዲህ ሄደን ብንለቅመው
ትወዳለህን? አሉት።

29 እርሱ ግን፦ እንክርዳዱን ስትለቅሙ ስንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትነቅሉት
አይሆንም። 30 ተዉአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ፤ በመከር ጊዜም
አጫጆችን፦ እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው
እሰሩ፥ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ አለ።

## ♦ ክፍል 64ሠ. የሰናፍጭ ዛፍ ምሳሌ

[ክፍል 110ን ይመልከቱ]

<u>ማቴዎስ 13፡31-32</u>

31 ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ፡- መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤ 32 እርስዋም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፥ በአደገች ጊዜ ግን፥ ከአታክልቶች ትበልጣለች የሰማይም ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪሰፍሩ ድረስ ዛፍ ትሆናለች።

<u>ማርቆስ 4፡30-32</u>

30 እርሱም አለ፡- የእግዚአብሔርን መንግሥት በምን እናስመስላታለን? ወይስ በምን ምሳሌ እንመስላታለን? 31 እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ናት፥ እርስዋም በምድር በተዘራች ጊዜ በምድር ካለ ዘር ሁሉ ታንሳለች፤ በተዘራችም ጊዜ ትወጣለች ከአትክልትም ሁሉ የምትበልጥ ትሆ ናለች፥ 32 የሰማይ ወፎችም በጥላዋ ሊሰፍሩ እስኪችሉ ታላላቅ ቅርንጫፎች ታደርጋለች። [መዝሙር 104፡12፤ ሕዝቅኤል 17፡23፥ 31፡6፤ ዳንኤል 4፡12]

## ♦ ክፍል 64ረ. ዱቄት ውስጥ ስለተሸሸገ እርሾ የተነገረ ምሳሌ

[ክፍል 110ን ይመልከቱ]

<u>ማቴዎስ 13፡33-35</u>

33 ሌላ ምሳሌ ነገራቸው እንዲህም አለ፡- መንግሥተ ሰማያት ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች።

34-35 ኢየሱስም ለሕዝቡ ይህን ሁሉ በምሳሌ ተናገረ፤ በነቢዩም፡- ‘‘በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ’’ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ያለ ምሳሌ አልተናገራቸውም። [መዝሙር 78፡2]

<u>ማርቆስ 4፡33-34</u>

33 መስማትም በሚችሉበት መጠን እነዚህን በሚመስል በብዙ ምሳሌ ቃሉን ይነግራቸው ነበር፤ ያለ ምሳሌ ግን አልነገራቸውም፥ 34 ለብቻቸውም ሲሆኑ ነገሩን ሁሉ ለገዛ ደቀ መዛሙርቱ ይፈታላቸው ነበር።

## -- ቤት ውስጥ ለነበሩ ሐዋርያት --

## ♦ ክፍል 64ሰ. የእንክርዳዱ ምሳሌ ተብራራ

<u>ማቴዎስ 13፡36-43</u>

36 በዚያን ጊዜ ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ። ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው፡- የእርሻውን እንክርዳድ ምሳሌ ተርጉምልን[65] አሉት።

37 እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤ እርሻውም ዓለም ነው፤ 38 መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤ 39 እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፥ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፤ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፥ አጫጆችም መላእክት ናቸው።

(ማቴዎስ 13፡36-43 የቀጠለ)

40 እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፥ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ
ይሆናል። 41 የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ
ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥ 42 ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ
ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። 43 በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት
እንደ ፀሐይ ይበራሉ። [ዳንኤል 12፡3] የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።

## ♦ ክፍል 64ሸ. የተሰወረው መዝገብ ምሳሌ

ማቴዎስ 13፡44

44 ደግሞ መንግሥተ ሰማያት በእርሻ ውስጥ የተሰወረውን መዝገብ ትመስላለች፤
ሰውም አግኝቶ ሰወረው፥ ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን እርሻ ገዛ።

## ♦ ክፍል 64ቀ. ዋጋዋ የበዛ እንቁ ምሳሌ

ማቴዎስ 13፡45-46

45 ደግሞ መንግሥተ ሰማያት መልካምን ዕንቁ የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች፤ 46
ዋጋዋም እጅግ የበዛ አንዲት ዕንቁ በአገኘ ጊዜ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ገዛት።

## ♦ ክፍል 64በ. የመረቡ ምሳሌ

ማቴዎስ 13፡47-50

47 ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ወደ ባሕር የተጣለች ከሁሉም ዓይነት የሰበሰበች
መረብን[66] ትመስላለች፤ 48 በሞላችም ጊዜ ወደ ወደቡ አወጡአት፥ ተቀምጠውም
መልካሙን ለቅመው በዕቃዎች ውስጥ አከማቹ ክፉውን ግን ወደ ውጭ ጣሉት። 49
በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፤ መላእክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻድቃን
መካከል ይለዩአቸዋል፥ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፤ 50 በዚያ ልቅሶና ጥርስ
ማፋጨት ይሆናል።

## ♦ ክፍል 64ተ. የባለቤቱ ምሳሌ

ማቴዎስ 13፡51-53

51 ኢየሱስም፡- ይህን ሁሉ አስተዋላችሁን? አላቸው፤ አዎን አሉት።

52 እርሱም፡- ስለዚህ የመንግሥተ ሰማያት ደቀ መዝሙር የሆነ ጻፊ ሁሉ ከመዝገቡ
አዲሱንና አሮጌውን የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል አላቸው።

53 ኢየሱስም እነዚህም ምሳሌዎች ከጨረሰ በኋላ ከዚያ ሄደ።

---

65 መጥምቁ ዮሐንስ (በማቴዎስ 3፡2፥ ክፍል 21 ውስጥ፥ እንዲሁም ማቴ. 3፡10-12፥ ክፍል 22 እና 23 ውስጥ)፥ እና ኢየሱስ (በማቴዎስ 4፡17፥ ክፍል 37 ውስጥ) የመለኮታዊው ፍርድ ቀንና የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ የሚመሠረትበት ቀን መቃረቡን ተንብየዋል።

እነዚህ ነገሮች እስከሚፈጸሙ ድረስ ረጅም ጊዜ እንደሚያልፍ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው። ደቀ መዛሙርቱ በእነዚህ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ በሚመስሉ ትንቢቶች ግር ተሰኙ።

ኢየሱስ ስለ መሢሑ መምጣት ለአይሁዶች ያስተላለፈው መልእክት፥ ወደፊት ስለሚፈጸመው ፍርድ በተነገረው ትንቢት መቀየሩን ያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ አላስተዋሉም ነበር።

# > ያልተቋረጠ ተቃውሞ <

## ♦ ክፍል 65. ባሕሩን ማቋረጥና ማዕበሉን መገሰጽ

- በገሊላ ባሕር ላይ -

**ማቴዎስ 8፡18፥ 23-27**

18 ኢየሱስም ብዙ ሰዎች ሲከቡት አይቶ ወደ ማዶ እንዲሻገሩ አዘዘ።

23 ወደ ታንኳም ሲገባ ደቀ መዛሙርቱ ተከተሉት። 24 እነሆም፥ ማዕበሉ ታንኳይቱን እስኪደፍናት ድረስ በባሕር ታላቅ መናወጥ ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር።

25 ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፦ ጌታ ሆይ፥ አድነን፥ ጠፋን እያሉ አስነሡት።

26 እርሱም፦ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ? አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፥ ታላቅ ጸጥታም[67] ሆነ።

27 ሰዎቹም፦ ነፋሳትና ባሕርስ ስንኳ የሚታዘዙለት፥ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው? እያሉ ተደነቁ።

**ማርቆስ 4፡35-41**

35 በዚያም ቀን በመሸ ጊዜ፦ ወደ ማዶ እንሻገር አላቸው። 36 ሕዝቡንም ትተው በታንኳ እንዲያው ወሰዱት፥ ሌሎች ታንኳዎችም ከእርሱ ጋር ነበሩ። 37 ብርቱ ዐውሎ ነፋስም ተነሣና ውኃ በታንኳይቱ እስኪሞላ ድረስ ማዕበሉ በታንኳይቱ ይገባ ነበር። 38 እርሱም በስተኋላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር፤ አንቅተውም፦ መምህር ሆይ፥ ስንጠፋ አይገድህምን? አሉት።

39 ነቅቶም ነፋሱን ገሠጸው ባሕሩንም፦ ዝም በል፥ ፀጥ በል አለው። ነፋሱም ተወ ታላቅ ፀጥታም ሆነ።[67]

40 እንዲህ የምትፈሩ ስለ ምን ነው? እንዴትስ እምነት የላችሁም? አላቸው።

41 እጅግም ፈሩና፦ እንግዲህ ነፋስም ባሕርም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው? ተባባሉ።

**ሉቃስ 8፡22-25**

22 ከዕለታቱም በአንዱ እርሱ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳ ገብቶ፦ ወደ ባሕር ማዶ እንሻገር አላቸው፤ ተነሡም። 23 ሲሄዱም አንቀላፋ። ዓውሎ ነፋስም በባሕር ላይ ወረደ፥ ውኃውም ታንኳይቱን ይሞላ ነበርና ይጨነቁ ነበር።

24 ቀርበውም፦ አቤቱ፥ አቤቱ ጠፋን እያሉ አስነሡት።

እርሱም ነቅቶ ነፋሱንና የውኃውን ማዕበል ገሠጻቸው፤ ተዉም፥ ጽጥታም[67] ሆነ።

25 እርሱም፦ እምነታችሁ የት ነው? አላቸው።

ፈርተውም ተደነቁ፥ እርስ በርሳቸውም፦ እንዲህ ነፋሳትንና ውኃን እንኳ የሚያዝ ለእርሱም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው? አሉ።

---

66 ይህ ምሳሌ በብዙ መንገዶች ስለ እንክርዳድ ከተነገረው ትንቢት ጋር ቢመሳሰልም (ማቴ. 13፡24-30፥ ክፍል 64መ፤ ማቴ. 13፡36-43፥ ክፍል 64መ)፥ የእንክርዳዱ ምሳሌ ይህ ዘመን ከመፈጸሙ በፊት ስለሚከሰቱ ነገሮች የሚያመለክት ነው። የዓሣው ምሳሌ ደግሞ ስለመጨረሻው ዘመን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይሰጣል።

67 [ማቴ. 8፡26፤ ማር. 4፡39፤ ሉቃስ 8፡24] እዚህ የተፈጸመው ጥምር ተአምር ሲሆን፥ እሱም የነፋሱ ጸጥ ማለትና የባሕሩ ሞገድ መቆም ነው። በተለምዶ የሚታወቀው ነፋስ ጸጥ ካለ በኋላ እንኳ ማዕበሉ ለጥቂት ጊዜ የሚቆይ መሆኑ ሲሆን አሁን ግን ይህ አልሆነም።

## ♦ ክፍል 66. አጋንንት ያደሩባቸውን የጌርጌሴኖን ሰዎች መፈወስና ከዚያ የተከተለው ተቃውሞ

- የጌርጌሶን አገር -

### ማቴዎስ 8፡28-34

28 ወደ ማዶም ወደ
ጌርጋሴኖን አገር በመጣ
ጊዜ፥ አጋንንት
ያደሩባቸው ሁለት[68]
ሰዎች ከመቃብር ወጥተው
ተገናኙት፤ እነርሱም ሰው
በዚያ መንገድ ማለፍ
እስኪሳነው ድረስ እጅግ
ክፉዎች ነበሩ።

29 እነሆም፡- ኢየሱስ ሆ
ይ፥ የእግዚአብሔር ልጅ፥
ከአንተ ጋር ምን አለን?
ጊዜው ሳይደርስ
ልትሣቅየን ወደዚህ
መጣህን? እያሉ ጮኹ።

### ማርቆስ 5፡1-20

1 ወደ ባሕር ማዶም ወደ
ጌርጌሴኖን አገር መጡ። 2
ከታንኳይቱም በወጣ ጊዜ፥
ርኵስ መንፈስ የያዘው
ሰው[68] ከመቃብር ወጥቶ
ወዲያው ተገናኘው፤ 3
እርሱም በመቃብር ይኖር
ነበር፥ በሰንሰለትም ስንኳ
ማንም ሊያስረው በዚያን
ጊዜ አይችልም ነበር፤ 4
ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና
በሰንሰለት ይታሰር ነበርና
ዳሩ ግን ሰንሰለቱን
ይበጣጥስ እግር ብረቱንም
ይሰባብር ነበር፥
ሊያሸንፈውም የሚችል
አልነበረም፤ 5 ሁልጊዜም
ሌሊትና ቀን በመቃብርና
በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር
ሰውነቱንም በድንጋይ
ይቧጭር ነበር።

6 ኢየሱስንም ከሩቅ ባየ
ጊዜ ሮጦ ሰገደለት፥ 7
በታላቅ ድምፅም እየጮኸ፡-
የልዑል እግዚአብሔር ልጅ
ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር
ምን አለኝ? እንዳታሠቃየኝ
በእግዚአብሔር አምልሃለሁ
አለ፤ 8 አንተ ርኵስ
መንፈስ፥ ከዚህ ሰው ውጣ
ብሎት ነበርና።

9 ስምህ ማን ነው? ብሎ
ጠየቀው። ብዙዎች ነንና
ስሜ ሌጌዎን ነው አለው፥
10 ከአገርም ውጭ

### ሉቃስ 8፡26-39

26 በገሊላም አንጻር
ወዳለችው ወደ ጌርጌሴኖን
አገር በታንኳ ደረሱ። 27
ወደ ምድርም በወጣ ጊዜ
አጋንንት ያደሩበት አንድ
ሰው[68] ከከተማ ወጥቶ
ተገናኘው፥ ከብዙ ዘመንም
ጀምሮ ልብስ ሳይለብስ
በመቃብር እንጂ በቤት
አይኖርም ነበር።

28 ኢየሱስንም ባየ ጊዜ
ጮኾ በፊቱ ተደፋ በታላቅ
ድምፅም፡- የልዑል
እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ
ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን
አለኝ? እንዳትሣቀየኝ
እለምንሃለሁ አለ። 29
ርኵሱን መንፈስ
ከሰውዬው እንዲወጣ
ያዘው ነበርና። ብዙ
ዘመንም ይዞት ነበርና፥
በሰንሰለትና በእግር
ብረትም ታስሮ ይጠበቅ
ነበር፤ እስራቱንም ሰብሮ
በጋኔኑ ወደ ምድረ በዳ
ይነዳ ነበር።

68 [ማቴ. 8፡28፤ ማር. 5፡2፤ ሉቃስ 8፡27] በአጋንንት የተያዙ ሁለት ሰዎች በስፍራው የነበሩ ይመስላል። ማርቆስና ሉቃስ የሚናገሩት ግን መሪ ስለሆነው ነው።

(ማቴዎስ 8፡28-34 የቀጠለ)

30 ከእነርሱም ርቆ የብዙ እሪያ[69] መንጋ ይሰማራ ነበር። 31 አጋንንቱም፦ ታወጣንስ እንደሆንህ፥ ወደ እሪያው መንጋ ስደደን ብለው ለመኑት። ሂዱ አላቸው።

32 እነርሱም ወጥተው ወደ እሪያዎቹ ሄዱና ገቡ፤ እነሆም፥ የእሪያዎቹ መንጋ ሁሉ ከአፋፉ ወደ ባሕር እየተጣደፉ ሮጡ በውኃም ውስጥ ሞቱ። 33 እረኞችም ሸሹ፥ ወደ ከተማይቱም ሄደው ነገሩን ሁሉ አጋንንትም በአደሩባቸው የሆነውን አወሩ።

34 እነሆም፥ ከተማው ሁሉ ኢየሱስን ሊገናኝ ወጣ፥

ባዩትም ጊዜ ከአገራቸው እንዲሄድላቸው ለመኑት።

(ማርቆስ 5፡1-20 የቀጠለ)

እንዳይሰዳቸው አጥብቆ ለመነው።

11 በዚያም በተራራ ጥግ ብዙ የእሪያ[69] መንጋ ይሰማራ ነበርና፦ 12 ወደ እሪያዎቹ እንድንገባ ስደደን ብለው ለመኑት። 13 ኢየሱስም ፈቀደላቸው። ርኵሳን መናፍስቱም ወጥተው ወደ እሪያዎቹ ገቡ፥ ሁለት ሺህም የሚያህል መንጋ ከአፋፉ ወደ ባሕር ተጣደፉና በባሕር ሰጠሙ።

14 እረኞቹም ሸሽተው በከተማውና በአገሩ አወሩ፤ ነገሩም ምን እንደ ሆነ ለማየት መጡ። 15 ወደ ኢየሱስም መጡ፥ አጋንንትም ያደሩበትን ሌጌዎንንም የነበረበትን ሰው ተቀምጦ ለብሶም ልቡም ተመልሶ አዩና ፈሩ። 16 ያዩት ሰዎችም አጋንንት ላደሩበት ሰው የሆነውንና ስለ እሪያዎቹ ተረኩላቸው። 17 ከአገራቸውም እንዲሄድላቸው ይለምኑት ጀመር።

18 ወደ ታንኳይቱም በገባ ጊዜ አጋንንት አድረውበት የነበረው ሰው

(ሉቃስ 8፡26-39 የቀጠለ)

30 ኢየሱስም፦ ስምህ ማን ነው? ብሎ ጠየቀው።

እርሱም ብዙዎች አጋንንት ገብተውበት ነበርና፦ ሌጌዎን አለው።

31 ወደ ጥልቁም ሊሄዱ እንዳያዛቸው ለመኑት።

32 በዚያም በተራራው የብዙ እሪያ[69] መንጋ ይሰማሩ ነበር፤ ወደ እነርሱም ሊገቡ እንዲፈቅድላቸው ለመኑት፤ ፈቀደላቸውም። 33 አጋንንትም ከሰውዬው ወጥተው ወደ እሪያዎች ገቡ፥ መንጋውም ከአፋፉ ወደ ባሕር ተጣደፉና ሰጠሙ።

34 እረኞችም የሆነውን ባዩ ጊዜ ሸሽተው በከተማውና በአገሩ አወሩት። 35 የሆነውን ነገር ሊያዩ ወጥተውም ወደ ኢየሱስ መጡ፥ አጋንንትም የወጡለትን ሰው ለብሶ ልቡም ተመልሶ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጦ አገኙትና ፈሩ። 36 ያዩትም ደግሞ አጋንንት ያደሩበት ሰው እንዴት እንደ ዳነ አወሩላቸው። 37 በዙሪያውም በጌርጌሴኖን አገር ያሉት ሕዝብ ሁሉ ታላቅ ፍርሃት ይዞአቸዋልና ከእነርሱ እንዲሄድ ለመኑት በታንኳም ገብቶ ተመለሰ።

[69] [ማቴ. 8፡30፤ ማር. 5፡11፤ ሉቃስ 8፡32] አረማውያን በብዛት በሚኖሩበት ሥፍራ አሳማዎች መርባታቸው አያስደንቅም። አሳማዎች በአይሁዳውያን ዘንድ የረከሱ እንስሳት ሆነው ይቆጠራሉ።

(ማርቆስ 5፡1-20 የቀጠለ)

ከእርሱ ጋር እንዲኖር ለመነው። 19
ኢየሱስም አልፈቀደለትም፥ ነገር ግን፦
ወደ ቤትህ በቤተ ሰዎችህ ዘንድ ሄደህ
ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር
እንዳደረገልህ እንዴትስ እንደ ማረህ
አውራላቸው አለው።[70] 20 ሄዶም
ኢየሱስ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር
እንዳደረገለት አሥር ከተማ በሚባል አገር
ይሰብክ ጀመር፥ ሁሉም ተደነቁ።

(ሉቃስ 8፡26-39 የቀጠለ)

38 አጋንንት የወጡለት ሰውም ከእርሱ
ጋር ይኖር ዘንድ ለመነው፤ 39 ነገር ግን፦
ወደ ቤትህ ተመለስ፥ እግዚአብሔር
እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረግልህ
ንገር[70] ብሎ አሰናበተው። ኢየሱስም
እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገለት
በከተማው ሁሉ እየሰበከ ሄደ።

## ♦ ክፍል 67. ወደ ገሊላ መልስ፥ የኢየሱስን ልብስ የነካች ሴት መፈወስና የኢያሲሮስ ልጅ ከሞት መነሣት

- ገሊላ ባሕር አጠገብ -

ማቴዎስ 9፡18-26

18 ይህንም
ሲነግራቸው፥ አንድ
መኰንን መጥቶ፦[71] ልጄ
አሁን ሞተች፤ ነገር ግን
መጥተህ እጅህን ጫንባት፥
በሕይወትም ትኖራለች
እያለ ሰገደለት። 19
ኢየሱስም ተነሥቶ ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር
ተከተለው።

ማርቆስ 5፡21-43

21 ኢየሱስም ደግሞ
በታንኳይቱ ወደ ማዶ
ከተሻገረ በኋላ ብዙ ሰዎች
ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፥
በባሕርም አጠገብ ነበረ።
22 ኢያኢሮስ የተባለ
ከምኲራብ አለቆች አንዱ
መጣ፤ ባየውም ጊዜ
በእግሩ ላይ ወደቀና፦ 23
ታናሽቱ ልጄ ልትሞት
ቀርባለችና እንድትድንና
በሕይወት እንድትኖር
መጥተህ እጅህን ጫንባት
ብሎ አጥብቆ ለመነው።[71]
24 ከእርሱም ጋር ሄደ።

ብዙ ሕዝብም ተከተሉት

ሉቃስ 8፡40-56

40 ኢየሱስም በተመለሰ
ጊዜ ሁሉ ይጠብቁት ነበርና
ሕዝቡ ተቀበሉት። 41 እነሆ
ም፥ ኢያኢሮስ የሚባል
ሰው መጣ፥ እርሱም
የምኵራብ አለቃ ነበረ
በኢየሱስም እግር ላይ
ወድቆ ወደ ቤቱ እንዲገባ
ለመነው፤[71] 42 አሥራ
ሁለት ዓመት የሆናት
አንዲት ሴት ልጅ
ነበረችውና፤ እርስዋም
ለሞት ቀርባ ነበረች።

ሲሄድም ሕዝቡ
ያጨናንቁት ነበር። 43
ከአሥራ ሁለት ዓመትም

70 [ማር. 5፡19፤ ሉቃስ 8፡39] ኢየሱስ በተለያዩ ምክንያቶች ሰዎች ስለመፈወሳቸው እንዳይናገሩ ከልክሏል። በከፊል አረማውያን በሚኖሩባትና ይህ ተአምር በተፈጸመባት ፖርያ ውስጥ የነበረው ሁኔታ ግን የተለየ ነበር። ከአይሁዳውያን ተፃራሪዎች የሚመጣ የፖለቲካ ተቃውሞ አልነበረም። ከሁሉም ይልቅ ሌሎች መልእክተኞች ወደ አካባቢው አልተላኩም።

71 [ማቴ. 9፡18፤ ማር. 5፡23፤ ሉቃስ 8፡41] ኢየሱስ ዋና የሥራ ቦታውን ቅፍርናሆም ውስጥ በማድረጉ (ክፍል 40ን ይመልከቱ)፥ ኢያኢሮስ ቀደም ሲል ከነርሱ ጋር ግንኙነት ሳያደርግ አልቀረም። የከተማይቱ የምኲራብ አለቃ እንደመሆኑ፥ የንጉሥ ቤት ባለሥልጣን ልጅ (ክፍል 38)፥ እንዲሁም የመቶ አለቃው አገልጋይ በኢየሱስ መፈወሳቸውን ሳይሰማ አይቀርም (ክፍል 55)። እነዚህ ሁኔታዎች ናቸው የኢየሱስን እርዳታ እንዲፈልግ ያነሣሡት።

(ማቴዎስ 9:18-26 የቀጠለ)

20 እነሆም፥ ከአሥራ
ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም
የሚፈስሳት ሴት በኋላው
ቀርባ

የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች፤
21 በልብዋ:- ልብሱን
ብቻ የዳሰስሁ እንደ ሆነ፥
እድናለሁ ትል ነበረችና።

22 ኢየሱስም ዘወር ብሎ
አያትና:- ልጄ ሆይ፥
አይዞሽ፤ እምነትሽ
አድኖሻል አላት።

(ማርቆስ 5:21-43 የቀጠለ)

አጋፉትም። 25 ከአሥራ
ሁለት ዓመትም ጀምሮ
ደም የሚፈሳት ሴት
ነበረች፥ 26 ከብዙ ባለ
መድኃኒቶችም ብዙ
ተሠቃየች፤[72] ገንዘብዋንም
ሁሉ ከስራ ባሰባት እንጂ
ምንም አልተጠቀመችም፤
27 የኢየሱስንም ወሬ
ሰምታ በስተኋላው በሰዎች
መካከል መጥታ ልብሱን
ዳሰሰች:- 28 ልብሱን ብቻ
የዳሰስሁ እንደ ሆነ
እድናለሁ ብላለችና። 29
ወዲያውም የደምዋ ምንጭ
ደረቀ ከሥቃይዋም
እንደዳነች በሰውነትዋ
አወቀች።

30 ወዲያውም ኢየሱስ
ከእርሱ ኃይል እንደ ወጣ
በገዛ ራሱ አውቆ በሕዝቡ
መካከል ዘወር ብሎ:-
ልብሴን የዳሰሰ ማን ነው?
አለ።

31 ደቀ መዛሙርቱም:-
ሕዝቡ ሲያጋፉህ እያየህ:-
ማን ዳሰሰኝ ትላለህን?
አሉት።

32 ይህንም ያደረገችውን
ለማየት ዘወር ብሎ
ይመለከት ነበር። 33
ሴቲቱ ግን የተደረገላትን
ስላወቀች፥ እየፈራች
እየተንቀጠቀጠችም፥
መጥታ በፊቱ ተደፋች
እውነቱንም ሁሉ
ነገረችው። 34 እርሱም:-
ልጄ ሆይ፥ እምነትሽ
አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ

(ሉቃስ 8:40-56 የቀጠለ)

ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት
ነበረች፥ ትዳርዋንም ሁሉ
ለባለመድኃኒቶች[72] ከስራ
ማንም ሊፈውሳት
አልተቻለውም።

44 በኋላውም ቀርባ
የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች፥
የደምዋም ፈሳሽ በዚያን
ጊዜ ቆመ።

45 ኢየሱስም:- የዳሰሰኝ
ማን ነው? አለ።

ሁሉም በካዱ ጊዜ፥
ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር
የነበሩት:- አቤቱ፥ ሕዝቡ
ያጨንቁሃልና ያጋፉሃል፤
የዳሰሰኝ ማን ነው
ትላለህን? አሉ።

46 ኢየሱስ ግን:- አንድ
ሰው ዳሰሰኝ፥ ኃይል
ከእኔ እንደ ወጣ እኔ
አውቃለሁና አለ።

47 ሴቲቱም
እንዳልተሰወረች ባየች ጊዜ
እየተንቀጠቀጠች መጥታ
በፊቱ ተደፋች፥ በምን
ምክንያትም እንደ
ዳሰሰችው ፈጥናም እንደ
ተፈወሰች በሕዝቡ ሁሉ

---

72 [ማር. 5:26፤ ሉቃስ 8:43] ሐኪም የነበረው ሉቃስ ሞያውን የሚመለከት ታሪክ ሲገልጥ ከማርቆስ በተሻለ ያቀናብር ነበር።

(ማቴዎስ 9፡ 18-26 የቀጠለ)

ሴቲቱም ከዚያች ሰዓት
ጀምራ ዳነች።

23 ኢየሱስም ወደ
መኰንኑ ቤት በደረሰ
ጊዜ፥ እምቢልተኞችንና
የሚንጫጫውን ሕዝብ
አይቶ፦ 24 ብላቴናይቱ
ተኝታለች እንጂ
አልሞተችምና ፈቀቅ በሉ
አላቸው። በጣምም
ሳቁበት።

(ማርቆስ 5፡21-43 የቀጠለ)

ከሥቃይሽም ተፈወሺ
አላት።

35 እርሱም ገና ሲናገር
ከምኵራብ አለቃው ቤት
ዘንድ የመጡት፦ ልጅህ
ሞታለች፤ ስለ ምን
መምህሩን አሁን
ታደክመዋለህ? አሉት።

36 ኢየሱስ ግን
የተናገሩትን ቃል አድምጦ
ለምኵራቡ አለቃ፦ እመን
ብቻ እንጂ አትፍራ
አለው።

37 ከጴጥሮስም
ከያዕቆብም ከያዕቆብም
ወንድም ከዮሐንስ በቀር
ማንም እንዲከተለው
አልፈቀደም። 38 ወደ
ምኵራቡ አለቃ ቤትም
መጥቶ ሰዎች ሲንጫጩና
ሲያለቅሱ ዋይታም
ሲያበዙ አየ፤ 39
ገብቶም፦ ስለ ምን
ትንጫጫላችሁ
ታለቅሳላችሁም?
ብላቴናይቱ ተኝታለች
እንጂ አልሞተችም
አላቸው። 40 በጣምም
ሳቁበት።

እርሱ ግን ሁሉን
አስወጥቶ የብላቴናይቱን
አባትና እናትም ከእርሱ
ጋር የነበሩትንም ይዞ
ብላቴናይቱ ወዳለችበት
ገባ። 41 የብላቴናይቱንም

(ሉቃስ 8፡40-56 የቀጠለ)

ፊት አወራች። 48
እርሱም፦ ልጂ ሆይ፥
እምነትሽ አድኖሻል፤
በሰላም ሂጂ አላት።

49 እርሱም ገና ሲናገር
አንድ ሰው ከምኵራብ
አለቃው ቤት መጥቶ፦
ልጅህ ሞታለች፤ እንግዲህ
መምህሩን አታድክም
አለ።

50 ኢየሱስ ግን ሰምቶ፦
አትፍራ፤ እመን ብቻ
ትድንማለች ብሎ
መለሰለት።

51 ወደ ቤትም ሲገባ
ከጴጥሮስና ከያዕቆብ
ከዮሐንስም
ከብላቴናይቱም አባትና
እናት በቀር ማንም ከእርሱ
ጋር ይገባ ዘንድ
አልፈቀደም። 52 ሁሉም
እያለቀሱላት ዋይ ዋይ ይሉ
ነበር። እርሱ ግን፦
አታልቅሱ፤ ተኝታለች
እንጂ አልሞተችም አለ።

53 እንደ ሞተችም
አውቀው በጣም ሳቁበት።

[73] [ማር. 5፡43፤ ሉቃስ 8፡56] ልጅቱ ከሞት የተነሣችበት ሁኔታ በክርስቶስ ያመኑት ብቻ የሚያዩትና፥ ከማያምኑትና ድርጊቱን ከሚያናንቁ ሐዘንተኞች መደበቅ (ማር. 5፡40፤ ሉቃስ 8፡53) ነበረበት (ማር. 5፡36፤ ሉቃስ 8፡50)። ድርጊቱ የተፈጸመው ቀደም ሲል (ምናልባት በዚያው ዕለት) አገልግሎቱ "ዘላለማዊ ኃጢአት" ይሆናል በተባለው ጉዳይ (ማር. 3፡29፥ ክፍል 61) ሳቢያ መልኩን በቀየረበት በቅፍርናሆም ነው። ጌታ በዚህ ጊዜ የወንጌሉ የምሥራች ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ሰዎች በመለየቱ ረገድ ጥንቃቄ አደረገ።

| (ማቴዎስ 9፡18-26 የቀጠለ) | (ማርቆስ 5፡21-43 የቀጠለ) | (ሉቃስ 8፡40-56 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| 25 ሕዝቡን ግን ከአስወጡ በኋላ ገብቶ እጅዋን ያዛት፥ ብላቴናይቱም ተነሣች። | እጅ ይዞ፦ ጣሊታ ቁሚ አላት፤ ፍችውም አንቺ ብላቴና ተነሽ እልሻለሁ ነው። 42 ብላቴናይቱም የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበረችና ወዲያው ቆማ ተመላለሰች። ወዲያውም ታላቅ መገረም ተገረሙ። 43 ይህንም ማንም እንዳያውቅ[73] አጥብቆ አዘአቸው፦ የምትበላውን ስጡአት አላቸው። | 54 እርሱ ግን እጅዋን ይዞ፦ አንቺ ብላቴና፥ ተነሺ ብሎ ጮኸ። 55 ነፍስዋም ተመለሰች፥ ፈጥናም ቆመች፥ የምትበላውንም እንዲሰጡአት አዘዘ። |
| 26 ያም ዝና ወደዚያ አገር ሁሉ ወጣ። | | 56 ወላጆችዋም ተገረሙ፤ እርሱ ግን የሆነውን ለማንም እንዳይነግሩ[73] አዘዛቸው። |

## ♦ ክፍል 68. ሦስት የፈውስ ተአምራትና ሌላው ስድብ አዘል ክስ

[ክፍል 61፥ 106ና 126ን ይመልከቱ]

- ገሊላ -

ማቴዎስ 9፡27-34

27 ኢየሱስም ከዚያ ሲያልፍ ሁለት ዕውሮች፦ የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ማረን ብለው እየጮሁ ተከተሉት።

28 ወደ ቤትም በገባ ጊዜ ዕውሮቹ ወደ እርሱ ቀረቡ፥ ኢየሱስም፦ ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን? አላቸው።

አዎን፥ ጌታ ሆይ አሉት።

29 በዚያን ጊዜ፦ እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዓይኖቻቸውን[74] ዳሰሰ። 30
ዓይኖቻቸውም ተከፈቱ። 31 ኢየሱስም፦ ማንም እንዳያውቅ ተጠንቀቁ ብሎ በብርቱ
አዘዛቸው። እነርሱ ግን ወጥተው በዚያ አገር ሁሉ ስለ እርሱ አወሩ።

32 እነርሱም ሲወጡ እነሆ፥ ጋኔን ያደረበትን ዲዳ ሰው ወደ እርሱ አመጡ። 33
ጋኔኑንም ካወጣው በኋላ ዲዳው ተናገረ። ሕዝቡም፦ እንዲህ ያለ በእስራኤል ዘንድ ከቶ
አልታየም እያሉ ተደነቁ።

34 ፈሪሳውያን ግን፦ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል አሉ።

---

74 [ማቴ. 9፡31] የተፈወሰው ዓይነ ሥውር ለማንም እንዳይናገር የመከልከሉ ምክንያት፥ ኢየሱስን በተመለከተ ገሊላ ውስጥ የነበረው ተቃውሞ ነበር። ተአምራዊ ድርጊቱን በተመለከተ የተፈጠረው የተሳሳተ አመለካከት፥ ተቃዋሚዎች መንፈስ ቅዱስን የሚሰድቡበት ሌላ ተጨማሪ ዕድል ፈጠረላቸው (ማቴ. 9፡34፥ ክፍል 61)። ተቃዋሚዎቹ ሌላ ምልክት አልተገባቸውም (ማቴ. 12፡39፥ ክፍል 62)።

75 [ማቴ. 13፡58፤ ማር. 6፡6] ይህ የናዝሬት ጉብኝት የከተማው ሰዎች ኢየሱስን ሊገድሉት ሙከራ ካደረጉ ከአንድ ዓመት በኋላ የሆነ ነው (ሉቃስ 4፡29፥ ክፍል 39)። ባለፈው ጊዜ ያደረጉት ሁኔታ ከሳምራውያንና (ክፍል 35ሐ) ከቤተመንግሥቱ ባለሥልጣን (ክፍል 38) እምነት ጋር ይነጻጸራል። የአሁኑ አለማመን ደግሞ ቅፍርናሆም ውስጥ በኢየሱስ አገልግሎት ከተጠቀሙ ሰዎች እምነት ጋር ሲተያይ የጎላ ተነጻጻሪነት አለው (ክፍል 67 እና 68)።

## ♦ ክፍል 69. እምነት የለሿን ናዝሬትን ለመጨረሻ ጊዜ መጎብኘት

[ክፍል 36፥ 37ና 39ን ይመልከቱ]

- ናዝሬት -

ማቴዎስ 13፡54-58

54 ወደ ገዛ አገሩም መጥቶ እስኪገረሙ ድረስ በምኩራባቸው ያስተምራቸው ነበር፤ እንዲህም አሉ፦ ይህን ጥበብና ተአምራት ይህ ከወዴት አገኘው?

55 ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን? 56 እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን? እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ተሰናከሉበትም።

57 ኢየሱስ ግን፦ ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው።

58 በአለማመናቸውም ምክንያት[75] በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም።

ማርቆስ 6፡1-6ሀ

1 ከዚያም ወጥቶ ወደ ገዛ አገሩ መጣ ደቀ መዛሙርቱም ተከተሉት። 2 ሰንበትም በሆነ ጊዜ በምኩራብ ያስተምር ጀመር፤ ብዙዎችም ሰምተው ተገረሙና፦

እነዚህን ነገሮች ይህ ከወዴት አገኛቸው? ለዚህ የተሰጠችው ጥበብ ምንድር ናት? በእጁም የሚደረጉ እንደነዚህ ያሉ ተአምራት ምንድር ናቸው? 3 ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ ይሰናከሉበትም ነበር።

4 ኢየሱስም፦ ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ዘመዶቹ ከገዛ ቤቱም በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው። 5 በዚያም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር፥ ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም። 6 ስለ አለማመናቸውም[75] ተደነቀ።

# > በገሊላ የተደረገ የመጨረሻ ጥረት (ዘመቻ) <

## ♦ ክፍል 70ሀ. የሠራተኞች ጥቂት መሆን

[ክፍል 70ለና 102ሀን ይመልከቱ]

- በገሊላ መዘዋወር -

ማቴዎስ 9፡35-38

35 ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር። 36 ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች[76] ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና

ማርቆስ 6፡6ለ

በመንደሮችም እያስተማረ ይዞር ነበር።

(ማቴዎስ 9፡35-38 የቀጠለ)

አዘነላቸው። 37 በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፡- መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ 38 እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው።

## ♦ ክፍል 70ለ. ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ሥልጣን መስጠት

[ክፍል 53፥ ሐዋርያት ሥራ 1፡13፥ 54ሰ፥ 70ሀ፥ 83፥ 91፥ 102ሀ፥ 108ሀ፥ 108መ፥ 115፥ 139ለ፥ 145ና 150ለን ይመልከቱ]

- ገሊላ -

| ማቴዎስ 10፡1-42 | ማርቆስ 6፡7-11 | ሉቃስ 9፡1-5 |
|---|---|---|
| 1 አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፥ እንዲያወጡአቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው።<br>2 የአሥራ ሁለቱም ሐዋርያት ስም ይህ ነው፤ መጀመሪያው ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን ወንድሙ እንድርያስም፥ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብም ወንድሙ ዮሐንስም፥ 3 ፊልጶስም በርተሎሜዎስም፥ ቶማስም ቀራጩ ማቴዎስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ታዴዎስም የተባለው ልብድዮስ፥ 4 ቀነናዊውም ስምዖን ደግሞም አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ።<br>5 እነዚህን አሥራ ሁለቱን ኢየሱስ ላካቸው፥ | 7 አስራ ሁለቱንም ወደ እርሱ ጠራ ሁለት ሁለቱንም ይልካቸው ጀመር፥ በርኵሳን መናፍስትም ላይ ሥልጣን ሰጣቸው፥ | 1 አሥራ ሁለቱንም ሐዋርያት በአንድነት ወደ እርሱ ጠርቶ በአጋንንት ሁሉ ላይ ደዌንም ይፈውሱ ዘንድ ኃይልና ሥልጣን ሰጣቸው፤ 2 የእግዚአብሔርንም መንግሥት እንዲሰብኩና ድውዮችን እንዲፈውሱ ላካቸው፥ |

76 [ማቴ. 9፡36] ‘‘በጎች’’ ማቴዎስ 10፡6 ውስጥ ‘‘የእስራኤል ቤት የሚሆኑ የጠፉ በጎች’’ በሚለው ይበልጥ ታውቀዋል። ለነዚህ ሰዎች የወንጌሉን የምሥራች በጥንቃቄ ማድረስ የጊዜው ዓላማ ነበር። ምንም እንኳን መሪዎቹ ለንጉሡ ጀርባቸውን ቢሰጡ፥ ማንኛውም ሰው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች የመስማት መብት ነበረው (ክፍል 61)።

77 [ማቴ. 10፡5] ኢየሱስም ሆነ ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት ተስፋ ወደተሰጣቸው ሰዎች መሄዳቸውን አቁመው ነበር። ኢየሱስን አንቀበልም የሚለው የገዛ ሕዝቦቹ ተቃውሞ እርሱን እስከመስቀል የደረሰ መሆኑ ይበልጥ የጎላ እስኪሆን ድረስ የኃላፊነታቸው ስፋት ግንዛቤ አላገኘም ነበር። ከዚያ በኋላ ነው ደቀ መዛሙርቱ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱ የተነገራቸው (ቁጥር 181)።

(ማቴዎስ 10፡ 1-42 የቀጠለ)

አዘዛቸውም፥ እንዲህም
አለ፡-77 በአሕዛብ መንገድ
አትሂዱ፥ ወደ
ሳምራውያንም ከተማ
አትግቡ፤ 6 ይልቅስ
የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ
ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ
እንጂ። 7 ሄዳችሁም፡-
መንግሥተ ሰማያት
ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ። 8
ድውዮችን ፈውሱ፤
ሙታንን አስነሡ፤
ለምጻሞችን አንጹ፤
አጋንንትን አውጡ፤ በከንቱ
ተቀበላችሁ፥ በከንቱ ስጡ።
9 ወርቅ ወይም ብር ወይም
ናስ በመቀነታችሁ፥ 10
ወይም ለመንገድ ከረጢት
ወይም ሁለት እጀ ጠባብ
ወይም ጫማ ወይም በትር
አታግኙ፤ ለሠራተኛ ምግቡ
ይገባዋልና።

11 በምትገቡባትም
በማናቸይቱም ከተማ ወይም
መንደር፥ በዚያ የሚገባው
ማን እንደ ሆነ በጥንቃቄ
መርምሩ፤ እስክትወጡም
ድረስ በዚያ ተቀመጡ። 12
ወደ ቤትም ስትገቡ ሰላምታ
ስጡ፤ 13 ቤቱም የሚገባው
ቢሆን ሰላማችሁ
ይድረስለት፤ ባይገባው ግን
ሰላማችሁ ይመለስላችሁ።
14 ከማይቀበላችሁም
ቃላችሁንም ከማይሰሙ
ሁሉ፥ ከዚያ ቤት ወይም
ከዚያች ከተማ ስትወጡ
የእግራችሁን ትቢያ
አራግፉ። 15 እውነት
እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን
ከዚያች ከተማ ይልቅ
ለሰዶምና ለገሞራ አገር

(ማርቆስ 6፡7-11 የቀጠለ)

8 ለመንገድም ከበትር
በቀር እንጀራም ቢሆን
ከረጢትም ቢሆን
መሐለቅም በመቀነታቸው
ቢሆን እንዳይዙ አዘዛቸው።
9 በእግራችሁ ጫማ
አድርጉ እንጂ ሁለት እጀ
ጠባብ አትልበሱ አለ። 10
በማናቸውም ስፍራ ወደ
ቤት ብትገቡ ከዚያ
እስክትወጡ ድረስ በዚያው
ተቀመጡ።

11 ከማይቀበሉአችሁና
ከማይሰሙአችሁ ስፍራ
ሁሉ፥ ከዚያ ወጥታችሁ
ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ
ከእግራችሁ በታች ያለውን
ትቢያ አራግፉ። እውነት
እላችኋለሁ፥ ከዚያች
ከተማ ይልቅ ለሰዶምና
ለገሞራ በፍርድ ቀን
ይቀልላቸዋል አላቸው።

(ሉቃስ 9፡1-5 የቀጠለ)

3 እንዲህም አላቸው፡-
በትርም ቢሆን፥
ከረጢትም ቢሆን፥
እንጀራም ቢሆን፥ ብርም
ቢሆን ለመንገድ ምንም
አትያዙ፥ ሁለት እጀ
ጠባብም አይሁንላችሁ። 4
በማናቸውም በምትገቡበት
ቤት በዚያ ተቀመጡ
ከዚያም ውጡ።

5 ማናቸውም
የማይቀበሉአችሁ ቢሆኑ፥
ከዚያ ከተማ ወጥታችሁ
ምስክር እንዲሆንባቸው
ከእግራችሁ ትቢያ
አራግፉ።

(ማቴዎስ 10፡ 1-42 የቀጠለ)

ይቀልላቸዋል። 16 እነሆ፥ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ።

17 ነገር ግን ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ በምኩራቦቻቸውም ይገርፉአችኋልና ከሰዎች ተጠበቁ፤ 18 ለእነርሱና ለአሕዛብም ምስክር እንዲሆን፥ ስለ እኔ ወደ ገዥዎች ወደ ነገሥታትም ትወሰዳላችሁ። 19 አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ፥ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ፤ 20 በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፥ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።

21 ወንድምም ወንድሙን፥ አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፥ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ ይገድሉአቸውማል። 22 በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። 23 በአንዲቱ ከተማም መከራ ቢያሳዩአችሁ ወደ ሌላይቱ ሽሹ፤ እውነት እላችኋለሁና፥ የሰው ልጅ እስኪመጣ ድረስ የእስራኤልን ከተማዎች አትዘልቁም።

24 ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፥ ባሪያም ከጌታው አይበልጥም። 25 ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ፥ ባሪያም እንደ ጌታው መሆኑ ይበቃዋል። ባለቤቱን ብዔል ዜቡል ካሉት፥ ቤተሰዎቹንማ እንዴት አብዝተው አይሉአቸው!

26 እንግዲህ አትፍሩአቸው፤ የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለምና። 27 በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፤ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ስበኩ። 28 ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ። 29 ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም። 30 የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል። 31 እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ።

32 ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ 33 በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።

34 በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም። 35 ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤ 36 ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል። [ሚክያስ 7፡6]

37 ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ 38 መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም። 39 ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።

40 እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። 41 ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። 42 ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም።

## ♦ ክፍል 70ሐ. ሠራተኞች ተላኩ

| ማቴዎስ 11፥1 | ማርቆስ 6፥12-13 | ሉቃስ 9፥6 |
|---|---|---|
| 1 ኢየሱስም አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ማዘዝ በፈጸመ ጊዜ በከተሞቻቸው ሊያስተምርና ሊሰብክ ከዚያ አለፈ። | 12 ወጥተውም ንስሐ እንዲገቡ ሰበኩ፥ ብዙ አጋንንትንም አወጡ፥ 13 ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው። | 6 ወጥተውም ወንጌልን እየሰበኩና በስፍራው ሁሉ እየፈወሱ በየመንደሩ ያልፉ ነበር። |

## ♦ ክፍል 71ሀ. ሄሮድስ የኢየሱስን ማንነት ማወቅ ተሳነው

| ማቴዎስ 14፥1-2 | ማርቆስ 6፥14-16 | ሉቃስ 9፥7-9 |
|---|---|---|
| 1 በዚያ ዘመን የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስ የኢየሱስን ዝና ሰማ፥[78] 2 ለሎሌዎቹም፦ ይህ መጥምቁ ዮሐንስ ነው፤ እርሱ ከሙታን ተነሥቶአል፥ ስለዚህም ኃይል በእርሱ ይደረጋል አለ። | 14 ስሙም ተገልጦአልና ንጉሡ ሄሮድስ በሰማ ጊዜ፦[78] መጥምቁ ዮሐንስ ከሙታን ተነሥቶአል ስለዚህም ኃይል በእርሱ ይደረጋል አለ። 15 ሌሎችም፦ ኤልያስ ነው አሉ፤ ሌሎችም፦ ከነቢያት እንደ አንዱ ነቢይ ነው አሉ። 16 ሄሮድስ ግን ሰምቶ፦ እኔ ራሱን ያስቈረጥሁት ዮሐንስ ይህ ነው እርሱ ከሙታን ተነሥቶአል አለ። | 7 የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስም የተደረገውን ነገር ሁሉ ሰምቶ፥[78] አንዳንድ ሰዎች፦ 8 ዮሐንስ ከሙታን ተነሣ፥ ሌሎችም፦ ኤልያስ ተገለጠ፥ ሌሎችም፦ ከቀደሙት ነቢያት አንዱ ተነሥቶአል ይሉ ስለ ነበሩ አመነታ። 9 ሄሮድስም፦ ዮሐንስንስ እኔ ራሱን አስቈረጥሁት፤ ይህ እንዲህ ያለ ነገር የምሰማበት ማን ነው? አለ። ሊያየውም ይሻ ነበር። |

[78] [ማቴ. 14፥1፤ ማር. 6፥14፤ ሉቃስ 9፥7] የኢየሱስን ዝና ከፍ ያደረገው፥ በአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አማካይነት የተሠራጨው አገልግሎቱ (ክፍል 70ለ እና 70ሐ) ነበር። ገሊላንና ፖርያን ያስተዳድር የነበረው ሄሮድስ አንቲጳስም ኢየሱስን በትኩረት ሊከታተለው የተገደደው በዚህ ጊዜ ነው።

## ♦ ክፍል 71ለ. የመጥምቁ ዮሐንስ መታሠርና የራሱ መቆረጥ[79]

[ክፍል 34ን ይመልከቱ]

- በጥብርያዶስ፥ ሳይሆን አይቀርም -

<u>ማቴዎስ 14፡3-12</u>

3 ሄሮድስ በወንድሙ በፊልጶስ ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያት ዮሐንስን አስይዞ አሳስሮት በወህኒ አኑሮት ነበርና፤ 4 ዮሐንስ፦ እርስዋ ለአንተ ትሆን ዘንድ አልተፈቀደም ይለው ነበርና። 5 ሊገድለውም ወዶ ሳለ፥ ሕዝቡ እንደ ነቢይ ስለ አዩት ፈራቸው።

6 ነገር ግን ሄሮድስ የተወለደበት ቀን በሆነ ጊዜ፥ የሄሮድያዳ ልጅ በመካከላቸው ዘፈነች ሄሮድስንም ደስ አሰኘችው፤ 7 ስለዚህም የምትለምነውን ሁሉ እንዲሰጣት በመሐላ ተስፋ አደረገላት።

8 እርስዋም በእናትዋ ተመክራ፦ የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በዚህ በወጭት ስጠኝ አለችው። 9 ንጉሡም አዘነ፥ ነገር ግን ስለ መሐላው ከእርሱም ጋር ተቀምጠው ስላሉት ሰዎች እንዲሰጡአት አዘዘ፤ 10 ልኮም

<u>ማርቆስ 6፡17-29</u>

17 ሄሮድስ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮድያዳን አግብቶ ነበርና በእርስዋ ምክንያት ራሱ ልኮ ዮሐንስን አስይዞ በወኅኒ አሳስሮት ነበር፤ 18 ዮሐንስ ሄሮድስን፦ የወንድምህ ሚስት ለአንተ ልትሆን አልተፈቀደም ይለው ነበርና። 19 ሄሮድያዳ ግን ተቃውማው ልትገድለው ትፈልግ ነበር አልቻለችም፤ 20 ሄሮድስ ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው እንደ ሆነ አውቆ ይፈራውና ይጠባበቀው ነበር፤ እርሱንም ሰምቶ በብዙ ነገር ያመነታ ነበር፤

21 በደስታም ይሰማው ነበር። ሄሮድስም በተወለደበት ቀን ለመኳንንቱና ለሻለቆቹ ለገሊላም ሹማምንት ግብር ባደረገ ጊዜ ምቹ ቀን ሆነላትና 22 የሄሮድያዳ ልጅ ገብታ ስትዘፍን ሄሮድስንና ከእርሱ ጋር የተቀመጡትን ደስ አሰኘቻቸው።

ንጉሡም ብላቴናይቱን፦ የምትወጂውን ሁሉ ለምኚኝ እሰጥሻለሁ አላት፤ 23 የመንግሥቴ እኩሌታ ስንኳ ቢሆን የምትለምኚውን ሁሉ እሰጥሻለሁ ብሎ ማለላት።

24 ወጥታም ለእናትዋ፦ ምን ልለምነው? አለች።

እርስዋም፦ የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ አለች።

25 ወዲያውም ፈጥና ወደ ንጉሡ ገብታ፦ የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በወጭት አሁን ልትሰጠኝ እወዳለሁ ብላ ለመነችው።

26 ንጉሡም እጅግ አዘነ ስለ መሐላው ከእርሱም ጋር ስለ ተቀመጡት ሊንሣት

[79] ይህ ክፍል የዮሐንስን መገደል አስመልክቶ የቀረበ ታሪካዊ ትውስታ ሆኖ፥ እዚህ በቅደም ተከተሉ ተመዝግቧል። ዮሐንስ የታሰረው ከዓመት ከስድስት ወር በፊት ኢየሱስ አገልግሎቱን ገሊላ ውስጥ በጀመረ ጊዜ ነበር (ክፍል 34)።

(ማቴዎስ 14፡3-12 የቀጠለ)

የዮሐንስን ራስ በወህኒ አስቆረጠው። 11 ራሱንም በወጭት አምጥተው ለብላቴናይቱ ሰጡአት፥ ወደ እናትዋም ወሰደችው። 12 ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው በድኑን ወሰዱና ቀበሩት፥ መጥተውም ለኢየሱስ አወሩለት።

(ማርቆስ 6፡17-29 የቀጠለ)

አልወደደም። 27 ወዲያውም ንጉሡ ባለ ወግ ልኮ ራሱን እንዲያመጣ አዘዘው። ሄዶም በወኅኒ ራሱን ቈረጠ፥ 28 ራሱንም በወጭት አምጥቶ ለብላቴናይቱ ሰጣት፥ ብላቴናይቱም ለእናትዋ ሰጠች። 29 ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው መጡ በድኑንም ወስደው ቀበሩት።

# 7

# በገሊላ ዙሪያ የክርስቶስ አገልግሎት

## > ስለ ሕይወት እንጀራ የተሰጠ ትምህርት <

### ♦ ክፍል 72ሀ. የሠራተኞች መመለስ

- ገሊላ -

| ማርቆስ 6፥30 | ሉቃስ 9፥10ሀ |
|---|---|
| 30 ሐዋርያትም ወደ ኢየሱስ ተሰብስበው ያደረጉትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት። | 10 ሐዋርያትም ተመልሰው ያደረጉትን ሁሉ ነገሩት። |

### ♦ ክፍል 72ለ. ከገሊላ መውጣት

- ከገሊላ ወደ ቤተ ሳይዳ ከዩሊያስ አጠገብ[80] -

| ማቴዎስ 14፥13-14 | ማርቆስ 6፥31-34 | ሉቃስ 9፥10ለ-11 | ዮሐንስ 6፥1-3 |
|---|---|---|---|
| | 31 እናንት ራሳችሁ ብቻችሁን ወደ ምድረ በዳ ኑና ጥቂት ዕረፉ አላቸው፤[82] የሚመጡና የሚሄዱ ብዙዎች ነበሩና፥ ለመብላት እንኳ ጊዜ አጡ። | | |
| 13 ኢየሱስም በሰማ ጊዜ ከዚያ ብቻውን ወደ | 32 በታንኳውም ብቻቸውን ወደ ምድረ በዳ ሄዱ። 33 ሰዎችም ሲሄዱ | ከእርሱ ጋርም ወስዶአቸው ቤተ ሳይዳ ከምትባል | 1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ ተሻገረ፤ |

80 ሁለት መንደሮች ቤተሳይዳ የሚል መጠሪያ ያላቸው ይመስላል። ሉቃስ 9፥10 ውስጥ የተጠቀሰችው ቤተሳይዳ ከገሊላ ባሕር ሰሜን ምሥራቅ ዩሊያስ በተባለው ሥፍራ አቅራቢያ የምትገኘው መሆኑ መታወቅ አለበት። ማርቆስ 6፥45 (ክፍል 73) ውስጥ ያለው ስም የሚያመለክተው ግን ከባሕሩ በስተምዕራብ ቅፍርናሆም አጠገብ ያለችውን መንደር ነው።

81 [ማር. 6፥31] ይህ ሁኔታ በአብዛኛው ሕዝባዊ ከሆነው አገልግሎት፥ ግላዊ ወደሆነው መዛወርን ያመለክታል። በዚህ ሥፍራ ሌሎች ሽግግሮችም ይታያሉ። መንግሥቱ ላይ የነበረው ትኩረት ንጉሡ ላይ ወደማትኮር ተለውጧል። ዝግጅቱ ጌታ ስላለበት ሳይሆን ስለማይኖርበት ጊዜ ነበር። ጌታ አልፎ አልፎ ገሊላን ከመጎብኘቱ በቀር ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አገልግሎቱን ከአካባቢው ውጭ ወስኖታል።

82 [ማቴ. 14፥13፤ ሉቃስ 9፥10ለ] አገልግሎቱ እዚህ ነጥብ ላይ ሲደርስ ኢየሱስ ከሕዝቡ ጋር የነበረው ግንኙነት ተለወጠ። ከዚህ ቀደም ሲል፥ አልፎ አልፎ የተለዩ ሁኔታዎች ቢኖሩም (ክፍል 65)፥ ብዙ ጊዜ ወደ እነርሱ ይሄድ ነበር። ከዚያ ቀጥሎ የነበሩት ወራት ከነርሱ የተለየባቸው ሆነው ነው በተለይ የሚታወቁት። ከዚህ በተጨማሪ ክፍል 73፥ 78፥ 79ሀ እና 81ሀን ይመልከቱ። ለመለየቱ መሠረት የሚሆኑት አምስት ሁኔታዎች ናቸው። (የግርጌ ማስታወሻው በተከታዩ ገጽ ይቀጥላል።)

| (ማቴዎስ 14፡13-14 የቀጠለ) | (ማርቆስ 6፡31-34 የቀጠለ) | (ሉቃስ 9፡10ለ-11 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 6፡1-3 የቀጠለ) |
|---|---|---|---|
| ምድረ በዳ በታንኳ ፈቀቅ አለ፤[81] ሕዝቡም ሰምተው ከከተማዎቹ በእግር ተከተሉት። 14 ወጥቶም ብዙ ሕዝብ አየና አዘነላቸው ድውዮቻቸውንም ፈወሰ። | አዩአቸው ብዙዎችም አወቁአቸውና ከከተሞች ሁሉ በእግር እየሮጡ ወዲያ ቀደሙአቸው ወደ እርሱም ተሰበሰቡ። 34 ኢየሱስም ወጥቶ ብዙ ሕዝብ አየና እረኛ እንደሌላቸው በጎች ስለ ነበሩ አዘነላቸው፥ ብዙም ነገር ያስተምራቸው ጀመር። | ከተማ አጠገብ ወደ ምድረ በዳ ለብቻው ፈቀቅ አለ።[81] 11 ሕዝቡም አውቀው ተከተሉት፤ ተቀብሎአቸውም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ይነግራቸው ነበር፥ መፈወስ ያስፈለጋቸውንም ፈወሳቸው። | እርሱም የጥብርያዶስ ባሕር ነው። 2 በበሽተኞችም ያደረገውን ምልክቶች ስላዩ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት። 3 ኢየሱስም ወደ ተራራ ወጣና በዚያ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ። |

## ♦ ክፍል 72ሐ. አምስት ሺህዎችን መመገብ

[ክፍል 79ለና 81ሀን ይመልከቱ]

- ቤተ ሳይዳ -

| ማቴዎስ 14፡15-21 | ማርቆስ 6፡35-44 | ሉቃስ 9፡12-17 | ዮሐንስ 6፡4-13 |
|---|---|---|---|
| 15 በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው፦ ቦታው ምድረ በዳ ነው አሁንም ሰዓቱ አልፎአል፤ ወደ መንደሮች ሄደው ለራሳቸው ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብት አሉት። | 35 በዚያን ጊዜም ብዙ ሰዓት ካለፈ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው፦ ቦታው ምድረ በዳ ነው አሁንም መሽቶአል፤ 36 የሚበሉት የላቸውምና በዙሪያ ወዳሉ ገጠሮችና መንደሮች ሄደው እንጀራ ለራሳቸው | 12 ቀኑም ይመሽ ጀመር፤ አሥራ ሁለቱም ቀርበው፦ በዚህ በምድረ በዳ ነንና በዙሪያችን ወዳሉ መንደሮችና ገጠሮች ሄደው እንዲያድሩና ምግብ እንዲያገኙ ሕዝቡን አሰናብት አሉት። | 4 የአይሁድ በዓልም ፋሲካ ቀርቦ ነበር። 5 ኢየሱስም ዓይኖቹን አንሥቶ |

(1.) የሄሮድስ አንቲጳስ ቅናት (ማቴ. 14፡13፤ ማር. 6፡30፥ ክፍል 72ሀ)። የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የእርሱን የመቀበር ዜና ይዘው መምጣታቸው፥ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ገሊላ ውስጥ አስተምረው ከመመለሳቸው ጋር የተገናኘ ይመስላል። ገሊላ ከሄሮድስ ግዛቶች አንዷ ናት። ኢየሱስ ከአካባቢው የራቀው፥ የአሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ጉብኝት አስመልክቶ በተሰራጨው ወሬ ምክንያት ሄሮድስ ከሚወስደው የበቀል ድርጊት ዞር ለማለት ነው።

(2.) ኢየሱስ የዳዊትን ዙፋን ያለጊዜው እንዲረከብ ሊያስገድዱት የፈለጉ ተከታዮቹ የተሳሳተ ፍላጎት (ዮሐ. 6፡15፥ ክፍል 73)። ኢየሱስ እንዲህ ካለው ግጭት የሚፈጥር ሁኔታና ሊያስከትል ከሚችለው ውጤት ራቀ። (የግርጌ ማስታወሻው በተከታዩ ገጽ ይቀጥላል።)

| (ማቴዎስ 14፡15-21 የቀጠለ) | (ማርቆስ 6፡35-44 የቀጠለ) | (ሉቃስ 9፡12-17 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 6፡4-13 የቀጠለ) |
|---|---|---|---|
| | እንዲገዙ አሰናብታቸው አሉት። | | ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየና ፊልጶስን፦ እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን? አለው። 6 ራሱ ሊያደርግ ያለውን ያውቅ ነበርና ሊፈትነው ይህን ተናገረ። |
| 16 ኢየሱስም፦ እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው እንጂ ሊሄዱ አያስፈልግም አላቸው። | 37 እርሱ ግን መልሶ፦ እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው አላቸው። ሄደን እንጀራ በሁለት መቶ ዲናር[83] እንግዛላቸውን? እንዲበሉም እንስጣቸውን? አሉት። 38 እርሱም፦ ስንት እንጀራ አላችሁ? ሂዱና እዩ አላቸው። | 13 እርሱ ግን፦ እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው አላቸው። | 7 ፊልጶስ፦ እያንዳንዳቸው ትንሽ ትንሽ እንኳ እንዲቀበሉ የሁለት መቶ ዲናር[83] እንጀራ አይበቃቸውም ብሎ መለሰለት። |
| 17 እነርሱም፦ ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ በቀር በዚህ የለንም አሉት። 18 እርሱም፦ እነዚያን ወደዚህ አምጡልኝ አላቸው። 19 ሕዝቡም በሣር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፥ አምስቱንም | ባወቁም ጊዜ፦ አምስት፥ ሁለትም ዓሣ አሉት። 39 ሁሉንም በየክፍሉ በለመለመ ሣር ላይ እንዲያስቀምጡአቸው አዘዛቸው። 40 መቶ መቶውና አምሳ አምሳው እየሆኑ በተራ በተራ ተቀመጡ። 41 | እነርሱም፦ ሄደን ለዚህ ሁሉ ሕዝብ ምግብ ካልገዛን፥ ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ የሚበልጥ የለንም አሉት፤ 14 አምስት ሺህ ሰዎች[84] ያህሉ ነበሩና። ለደቀ መዛሙርቱ፦ | 8 ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ፦ 9 አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና በዚህ አለ፤ ነገር ግን እነዚህን ለሚያህሉ ሰዎች ይህ ምን ይሆናል? አለው። 10 ኢየሱስም፦ ሰዎቹን እንዲቀመጡ |

(3.) የአይሁድ መሪዎች ጠላትነት (ማር. 7፡1-23፥ ክፍል 77)። ገሊላ ውስጥ የነበረው የኢየሱስ አገልግሎት ሲያድግ፥ በከፍተኛ ስፍራ የነበሩ መሪዎች ተቃውሞ ገሐድ መሆን ጀምሮ ነበር። አሁን ግን ገሊላ ውስጥ የነበረው አገልግሎት ፍጹም እንዲገታ እስከ ማድረግ ድረስ አደገ።

(4.) ደቀ መዛሙርቱ አድካሚ ከሆነው ጉዞ በኋላ ዕረፍት መፈለጋቸው (ማር. 6፡31)። ከሞቃቱ የገሊላ ባሕር ዳርቻ ወደ ቀዝቃዛው ተራራማ አካባቢ መዛወሩ ለዕረፍቱ መልካም ሁኔታን ፈጠረ።

(5.) ለደቀ መዛሙርቱ በተለይ የተሻለ ትምህርት የመስጠቱ ዕድል (ክፍል 72ለ-95)። ገሊላ ውስጥ የነበራቸው አገልግሎት ብዙ ጥያቄዎችን ፈጥሮ ይሆናል። ለዚህ ነው ጌታ ስለ እርሱና ከእርሱ እንዲማሩ የተለያዩ ዕድሎችን የሰጣቸው።

(ማቴዎስ 14:15-21 የቀጠለ)

እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፥ እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ። 20 ሁሉም በልተው ጠገቡ፥ የተረፈውንም ቁርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ። 21 ከሴቶችና ከልጆችም በቀር የበሉት አምስት ሺህ ወንዶች[84] ያህሉ ነበር።

(ማርቆስ 6:35-44 የቀጠለ)

አምስቱንም እንጀራ ሁለቱንም ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፥ እንጀራውንም ቈርሶ እንዲያቀርቡላቸው ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ 42 ሁለቱን ዓሣ ደግሞ ለሁሉ ከፈለ። ሁሉም በልተው ጠገቡ፤ 43 ከቍርስራሹም አሥራ ሁለት መሶብ የሞላ አነሡ ከዓሣውም ደግሞ። 44 እንጀራውንም የበሉት ወንዶቹ አምስት ሺህ[84] ነበሩ።

(ሉቃስ 9:12-17 የቀጠለ)

በየክፍሉ አምሳ አምሳውን አስቀምጡአቸው አላቸው። 15 እንዲህም አደረጉ ሁሉንም አስቀመጡአቸው። 16 አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ፥ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረካቸው ቆርሶም ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ ለደቀ መዛርሙርቱ ሰጠ። 17 ሁሉም በልተው ጠገቡ፥

ከእነርሱም የተረፈውን ቍርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ወሰዱ።

(ዮሐንስ 6:4-13 የቀጠለ)

አድርጉ አለ። በዚያም ስፍራ ብዙ ሣር ነበረበት። ወንዶችም ተቀመጡ ቍጥራቸውም አምስት ሺህ[84] የሚያህል ነበር። 11 ኢየሱስም እንጀራውን ያዘ፥ አመስግኖም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለተቀመጡት ሰዎች ሰጡአቸው እንዲሁም ከዓሣው በፈለጉት መጠን።

12 ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን፦ አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርስራሽ አከማቹ አላቸው። 13 ስለዚህ አከማቹ፥ ከበሉትም ከአምስቱ የገብስ እንጀራ የተረፈውን ቍርስራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ።

[83] [ማር. 6፡37፤ ዮሐ. 6፡7] ሁለት መቶ ዲናር የአንድ ሰው የስምንት ወር ደመወዝ ይሆናል። ብዙ ባይሆንም፥ ይህ ገንዘብ ደቀ መዛሙርቱ በግምጃ ቤታቸው ካላቸው የሚልቅ ሳይሆን አይቀርም። ይህን ያህል ቢኖራቸውም እንኳ ለዚያ ሁሉ ሰው ምግብ መግዣ አይበቃም ነበር።

## ♦ ክፍል 73. ኢየሱስን ለማንገሥ ያለ ጊዜው የተደረገ ሙከራ ተገታ

- በተራራው ላይ ለብቻው -

ማቴዎስ 14፡22-23

22 ወዲያውም ሕዝቡን ሲያሰናብት ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ በታንኳይቱ ገብተው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት ግድ አላቸው። 23 ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ። በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ።

ማርቆስ 6፡45-46

45 ወዲያውም ሕዝቡን ሲያሰናብት ሳለ ደቀ መዛሙርቱ በታንኳ ገብተው ወደ ማዶ ወደ ቤተ ሳይዳ እንዲቀድሙት ግድ አላቸው። 46 ካሰናበታቸውም በኋላ ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ።

ዮሐንስ 6፡14-15

14 ከዚህ የተነሣ ሰዎቹ ኢየሱስ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ፦ ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው አሉ። 15 በዚህም ምክንያት ኢየሱስ ያነግሡት ዘንድ ሊመጡና ሊነጥቁት እንዳላቸው አውቆ ደግሞ ወደ ተራራ ብቻውን ፈቀቅ አለ።[85]

## ♦ ክፍል 74. በማዕበል በተናወጠ ባሕር ላይ መራመድ

- በገሊላ ባሕር ላይ -

ማቴዎስ 14፡24-33

24 ታንኳይቱም አሁን በባሕር መካከል ሳለች፥ ነፋስ ከወደ ፊት ነበርና በማዕበል ትጨነቅ ነበር።

25 ከሌሊቱም በአራተኛው ክፍል[86] ኢየሱስ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ። 26 ደቀ መዛሙርቱም በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ፦ ምትሐት ነው ብለው ታወኩ በፍርሃትም ጮኹ።

ማርቆስ 6፡47-52

47 በመሸም ጊዜ ታንኳይቱ በባሕር መካከል ሳለች እርሱ ብቻውን በምድር ላይ ነበረ። 48 ነፋስ ወደ ፊታቸው ነበረና እየቀዘፉ ሲጨነቁ አይቶ፥ ከሌሊቱ በአራተኛው ክፍል[86] በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ፤ ሊያልፋቸውም ይወድ ነበር። 49 እነርሱ ግን በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት

ዮሐንስ 6፡16-21

16 በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕር ወረዱ፥ 17 በታንኳም ገብተው በባሕር ማዶ ወደ ቅፍርናሆም ይመጡ ነበር። አሁንም ጨልሞ ነበር፤ ኢየሱስም ገና ወደ እነርሱ አልመጣም ነበር፤ 18 ብርቱ ነፋስም ስለ ነፈሰ ባሕሩ ተናወጠ። 19 ሀያ አምስት ወይም ሠላሳ ምዕራፍ ከቀዘፉ በኋላም፥ ኢየሱስ

---

[84] [ማቴ. 14፡21፤ ማር. 6፡44፤ ሉቃስ 9፡14፤ ዮሐ. 6፡10] አምስት ሺህ ሰዎች (ወንዶች ማለት ነው) ነበሩ ሲባል፥ ይህንኑ ቁጥር ያህል ሴቶች እና ቢያንስ ይህንኑ ያህል ሕፃናት መኖራቸውን በሚገባ ያመለክታል። የተመገበው ሕዝብ ከአሥራ አምስት ሺህ ሳይበልጥ አይቀርም።

[85] [ዮሐ. 6፡15] ኢየሱስ እንደገና በሕዝቡ ፍላጎት አልስማማም አለ (ዮሐ. 2፡23፥ ክፍል 32ሀ)። በመጨረሻው በምድር ሁሉ ላይ የሚነግሥ መሆኑን አልካዱም፤ ነገር ግን የራሱ የሚሆኑት እርሱ ወደሚመሠርተው መንግሥት ለመግባት የሚያስችላቸውን ሥነ-ምግባራዊ ሁኔታዎች እስኪያሟሉ ድረስ መሪነቱን በቀጥታ ሊቀበል አልፈቀደም (የተራራው ስብከት ክፍል 54ሀ፥ 54ቀ)። ገሊላ ውስጥ ሕዝቡ እርሱን አንቀበልህም ማለታቸውና፥ በአሁኑ አጋጣሚ የሚያሳዩት የራስ ወዳድነት ዓላማ፥ ለመንግሥቱ የተዘጋጁ ላለመሆናቸው ግልጥ ማረጋገጫ ነው።

| (ማቴዎስ 14:24-33 የቀጠለ) | (ማርቆስ 6:47-52 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 6:16-21 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| 27 ወዲያውም ኢየሱስ ተናገራቸውና:- አይዞአችሁ፥ እኔ ነኝ፤ አትፍሩ አላቸው። | ጊዜ ምትሀት መሰላቸውና ጮኹ፥ 50 ሁሉ አይተውታልና፥ ታወኩም። | በባሕር ላይ እየሄደ ወደ ታንኳይቱ ሲቀርብ አይተው ፈሩ። |
| 28 ጴጥሮስም መልሶ:- ጌታ ሆይ፥ አንተስ ከሆንህ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ አለው። | ወዲያውም ተናገራቸውና:- አይዞአችሁ፤ እኔ ነኝ፥ አትፍሩ አላቸው። | 20 እርሱ ግን:- እኔ ነኝ፤ አትፍሩ አላቸው። |
| 29 እርሱም:- ና አለው። | | |
| ጴጥሮስም ከታንኳይቱ ወርዶ ወደ ኢየሱስ ሊደርስ በውኃው ላይ ሄደ። 30 ነገር ግን የነፋሱን ኃይል አይቶ ፈራ፥ ሊሰጥምም በጀመረ ጊዜ:- ጌታ ሆይ፥ አድነኝ ብሎ ጮኸ። | | |
| 31 ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና:- አንተ እምነት የጎደለህ፥ ስለምን ተጠራጠርህ? አለው። | | |
| 32 ወደ ታንኳይቱም በወጡ ጊዜ ነፋሱ ተወ። 33 በታንኳይቱም የነበሩት:- በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት። | 51 ወደ እነርሱም ወደ ታንኳይቱ ገባ፥ ነፋሱም[87] ተወ፤ በራሳቸውም ያለ መጠን እጅግ ተገረሙ፤ 52 ስለ እንጀራው አላስተዋሉምና፤ ነገር ግን ልባቸው ደንዝዞ ነበር። | 21 ስለዚህ በታንኳይቱ ሊቀበሉት ወደዱ፤ ወዲያውም[87] ታንኳይቱ ወደሚሄዱበት ምድር ደረሰች። |

86 [ማቴ. 14፡25፤ ማር. 6፡48] ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ከተለየ ከዘጠኝ እስከ አሥራ ሁለት ሰዓታት የሚሆን ጊዜ ሳያልፍ አልቀረም። የተለያቸው ከቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ነው ("በመሸ ጊዜ"፥ ማር. 6፡47)። እንደገና የተገናኙት በማግስቱ ከሌሊቱ ከ9 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ("በአራተኛው ክፍል") ነው። ይህን ሁሉ ሰዓት እነርሱ ከማዕበል ጋር ይታገሉ፥ እርሱ ደግሞ ይጸልይ ነበር።

87 [ማር. 6፡51፤ ዮሐ. 6፡21] ሁለት ተአምራት ተፈጸሙ፥ የነፋሱ መተውና የጀልባይቱ ጉዞ ማብቃት።

88 ጌንሴሬጥ ቅፍርናሆምና ቤተሳይዳ አቅራቢያ ነው የምትገኘው። ማርቆስ 6፡53ን ከዮሐንስ 6፡17፥ ክፍል 74 እና ከማርቆስ 6፡45፥ ክፍል 73 ጋር ያስተያዩ።

89 [ማቴ. 14፡34፤ ማር. 6፡53] ጌንሴሬጥ ከገሊላ ባሕር ምዕራብ ዳር፥ ከቅፍርናሆም በስተደቡብ የምትገኝ ለምና ሜዳማ ሥፍራ ናት። በዚህ የኢየሱስ አጭር የገሊላ ጉብኝት፥ ቀደም ሲል መሢሕነቱን ያልተቀበሉ ወገኖች (ክፍል 61 እና 68) መሢሕነቱን ካረጋገጡት ተአምራት ተጠቃሚዎች ለመሆን ፈቃደኞች ነበሩ።

## ♦ ክፍል 75. ጌንሴሬጥ በተባለ ሥፍራ የተከናወነ ፈውስ

- ጌንሴሬጥ[88] -

<u>ማቴዎስ 14፡34-36</u>

34 ተሻግረውም ወደ ጌንሴሬጥ[89]
ምድር መጡ። 35 የዚያ ቦታ ሰዎችም
ባወቁት ጊዜ በዙርያው ወዳለ አገር ሁሉ
ላኩ፥

ሕመምተኞችንም ሁሉ ወደ እርሱ
አመጡ፤ 36 የልብሱንም ጫፍ ብቻ
ሊዳስሱ ይለምኑት ነበር፤ የዳሰሱትም
ሁሉ ዳኑ።

<u>ማርቆስ 6፡53-56</u>

53 ተሻግረውም ወደ ምድር ወደ
ጌንሴሬጥ[89] ደረሱ ታንኳይቱንም
አስጠጉ። 54 ከታንኳይቱም ሲወጡ
ወዲያው አውቀውት 55 በዚያች አገር
ሁሉ ዙሪያ ሮጡና እርሱ እንዳለ ወደ
ሰሙበት ስፍራ ሕመምተኞችን በአልጋ
ላይ ያመጡ ጀመር። 56 በገባበትም ስፍራ
ሁሉ፥ መንደርም ከተማም ገጠርም ቢሆ
ን፥ በገበያ ድውዮችን ያኖሩ ነበር፤
የልብሱንም ጫፍ እንኳ ሊዳስሱ
ይለምኑት ነበር የዳሰሱትም ሁሉ ዳኑ።

## ♦ ክፍል 76ሀ. ስለ እውነተኛው የሕይወት እንጀራ የተደረገ ገለጣ

- ቅፍርናሆም -

<u>ዮሐንስ 6፡22-59</u>

22 በነገው በባሕር ማዶ ቆመው የነበሩ ሕዝቡ ከአንዲት ጀልባ በቀር በዚያ ሌላ ጀልባ
እንዳልነበረች፥ ደቀ መዛሙርቱም ለብቻቸው እንደ ሄዱ እንጂ ኢየሱስ ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳይቱ እንዳልገባ አዩ፤ 23 ዳሩ ግን ሌሎች ጀልባዎች ጌታ
የባረከውን እንጀራ ወደ በሉበት ስፍራ አጠገብ ከጥብርያዶስ መጡ። 24 ሕዝቡም
ኢየሱስ ወይም ደቀ መዛሙርቱ በዚያ እንዳልነበሩ ባዩ ጊዜ፥ ራሳቸው በጀልባዎቹ
ገብተው ኢየሱስን እየፈለጉ ወደ ቅፍርናሆም መጡ።

25 በባሕር ማዶም ሲያገኙት፦ መምህር ሆይ፥ ወደዚህ መቼ መጣህ? አሉት።

26 ኢየሱስም መለሰ፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የምትፈልጉኝ እንጀራን ስለ
በላችሁና[90] ስለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም። 27 ለሚጠፋ
መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ
ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና።

28 እንግዲህ፦ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ? አሉት።

29 ኢየሱስ መለሰ፦ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው
አላቸው።

30 እንግዲህ፦ እንኪያ አይተን እንድናምንህ አንተ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ
ትሠራለህ? 31 ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ አባቶቻችን
በምድረ በዳ መና በሉ አሉት። [ዘጸአት 16፡4፥ 15፤ ነህምያ 9፡15፤ መዝሙር
78፡24፥ 105፡40]

32 ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ
የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤ 33
የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና
አላቸው።

(ዮሐንስ 6፡22-59 የቀጠለ)

34 ስለዚህ፡- ጌታ ሆይ፥ ይህን እንጀራ ዘወትር ስጠን አሉት።

35 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡- የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤[91] ወደ እኔ የሚመጣ
ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም። 36 ነገር ግን አይታችሁኝ
እንዳላመናችሁ አልኋችሁ። 37 አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፥ ወደ እኔም
የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤ 38 ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ
የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና። 39 ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ
እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው። 40
ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ
ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።

41 እንግዲህ አይሁድ፡- ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ ስላለ ስለ እርሱ
አንጐራጐሩና፡- 42 አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው ይህ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ
አይደለምን? እንግዲህ፡- ከሰማይ ወርጃለሁ እንዴት ይላል? አሉ።

43 ኢየሱስ መለሰ አላቸውም፡- እርስ በርሳችሁ አታንጐራጕሩ። 44 የላከኝ አብ
ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፥ እኔም በመጨረሻው ቀን
አስነሣዋለሁ። 45 ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ተብሎ በነቢያት
ተጽፎአል፤ [ኢሳያይስ 54፡13] እንግዲህ ከአብ የሰማ የተማረም ሁሉ ወደ እኔ
ይመጣል። 46 አብን ያየ ማንም የለም፤ ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር፥ እርሱ አብን
አይቶአል። 47 እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።
48 የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። 49 አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም፤ 50
ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። 51 ከሰማይ
የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም
ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።

52 እንግዲህ አይሁድ፡- ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?
ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ።

53 ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ
ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። 54 ሥጋዬን
የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን
አስነሣዋለሁ። 55 ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። 56
ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ። 57 ሕያው
አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ
ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል። 58 ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና
በልተው እንደ ሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል 59
በቅፍርናሆም ሲያስተምር ይህን በምኵራብ አለ።

---

[90] [ዮሐ. 6፡26] ቀደም ሲል ከባሕሩ ማዶ ከዳቦና ከዓሣው በበሉ ሰዎች ዘንድ አሁንም ተመሳሳይ የራስ ወዳድነት ዓላማ (ክፍል 73) ይታያል። እነዚያ ሰዎች ከጌታ መንግሥት ጋር የተያያዙ ስጦታዎችን ሊቀበሉ የተዘጋጁ ነበሩ። ሥነ-ምግባራዊ ኃላፊነቶቹ ግን አልተዋሀዷቸውም።

[91] [ዮሐ. 6፡35] ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ "እኔ ነኝ" የሚሉት ሐረጎች ሰፊ ቁም ነገር አላቸው። በሌሎች ሥፍራዎች እንደተጠቀሰው ሁሉ ምናልባት ሙሴ ከሚቃጠለው ቁጥቋጦ የሰማውን የእግዚአብሔር ስም ዘጸአት 3፡14ን ይጠቅስ ይሆናል። ይህ ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከተጠቀሱት ሰባት እንዲህ ያሉ አባባሎች የመጀመሪያው ነው (ዮሐ. 8፡12፤ 10፡7፥ 9፤ 10፡11፥ 14፤ 11፡25፤ 14፡6፤ 15፡1፥ 5)።

## ♦ ክፍል 76ለ. ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎቹ ወደ ኋላ መመለሳቸው

[ክፍል 82ን ይመልከቱ]

- ቅፍርናሆም -

<u>ዮሐንስ 6፥60-71</u>

60 ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ፦ ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል? አሉ።

61 ኢየሱስ ግን ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ እንዳንጐራጐሩ በልቡ አውቆ አላቸው፦ ይህ
ያሰናክላችኋልን? 62 እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ
እንዴት ይሆናል? 63 ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤
እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው። 64 ነገር ግን ከእናንተ የማያምኑ
አሉ። ኢየሱስ የማያምኑት እነማን እንደ ሆኑ አሳልፎ የሚሰጠውም ማን እንደ ሆነ
ከመጀመሪያ ያውቅ ነበርና። 65 ደግሞ፦ ስለዚህ አልኋችሁ፥ ከአብ የተሰጠው ካልሆነ
ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም አለ።

66 ከዚህም የተነሣ ከደቀ መዛሙርቱ[92] ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም።

67 ኢየሱስም ለአሥራ ሁለቱ፦ እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን? አለ።

68 ስምዖን ጴጥሮስ፦ ጌታ ሆይ፥ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል
አለህ፤ 69 እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል[93]
አውቀናልም ብሎ መለሰለት።

70 ኢየሱስም፦ እኔ እናንተን አሥራ ሁለታችሁን የመረጥኋችሁ አይደለምን?
ከእናንተም አንዱ ዲያብሎስ ነው ብሎ መለሰላቸው። 71 ስለ ስምዖንም ልጅ ስለ
አስቆሮቱ ይሁዳ ተናገረ፤ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነ እርሱ አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ
አለውና።

92 [ዮሐ. 6፥66] ለውጫዊው ባሕርይ ለውጥ የውስጣዊው ሰው መለወጥ ብቸኛውና ትክክለኛው መሠረት መሆኑ ጠንካራ ትኩረት የተሰጠው ቢሆንም፥ አሳቡን ብዙ አድማጮች አይቀበሉትም ነበር (ዮሐ. 6፥60)። በመሆኑም ደቀ መዛሙርት ይሆናሉ ከተባሉት ብዙዎቹ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አልተከተሉትም። ዮሐንስ 6፥66 ወንጌሉ ውስጥ "ደቀ መዝሙር" የሚለው ቃል አጠቃቀም የተለወጠበት ነው። ከዚህ ጊዜ በኋላ "ደቀ መዝሙር" የሚለው ቃል "እውነተኛ ደቀ መዝሙር" የሚል ስሜት ኖረው።

93 [ዮሐ. 6፥69] ጴጥሮስና ሌሎች ደቀ መዛሙርት ጓደኞቹ በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ከሚሰጣቸው ትምህርት መግቢያ ላይ ደርሰው ነበር። ይህ የእምነት ኑዛዜያቸው ቀደም ሲል ካደረጉት ይልቅ የበረታ ቢሆንም (ማቴ. 14፥33፥ ክፍል 74) መሆን እንደሚገባው ቁርጥ ያለ ወይም ግልጥ አልነበረም (ማቴ. 16፥16፥ ክፍል 82)። "የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ" ማለት እግዚአብሔር ለንጉሥነት የቀባው ከማለት በቀር ሌላ ሊሆን አይችልም (መዝ. 16፥10፤ 71፥22፤ 78፥41፤ 89፥18፤ ኢሳ. 1፥4)። ሌሎች ሰዎች ባይቀበሉትም፥ ኢየሱስ በደቀ መዛሙርቱ ዘንድ ተቀባይነት የማግኘቱ ሁኔታ እየጨመረ ሄደ።

# > የፈሪሳውያንን፥ የሰዱቃውያንና የሄሮዳውያንን እርሾ አስመልክቶ የተሰጠ ትምህርት <

## ♦ ክፍል 77. ሥርዓታዊ ንጽሕናን ባለመጠበቅ የተፈጠረ ውዝግብ

- በገሊላ፥ ምናልባት በቅፍርናሆም -

<u>ማቴዎስ 15፡1-3ሀ፥ 7-9፥ 3ለ-6፥ 10-20</u>

1 በዚያን ጊዜ ጻፎችና ፈሪሳውያን[94] ከኢየሩሳሌም ወደ ኢየሱስ ቀረቡና፡-

2 ደቀ መዛሙርትህ ስለ ምን የሽማግሎችን ወግ ይተላለፋሉ? እንጀራ ሲበሉ እጃቸውን አይታጠቡምና አሉት።

3ሀ እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፡-

7 እናንተ ግብዞች፥ ኢሳይያስ ስለ እናንተ፡-

<u>ማርቆስ 7፡1-23</u>

1 ፈሪሳውያንና[94] ከጻፎች ወገን ከኢየሩሳሌም የመጡትም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ። 2 ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንድ በርኵስ ማለት ባልታጠበ እጅ እንጀራ ሲበሉ አዩ። 3 ፈሪሳውያንና አይሁድም ሁሉ የሽማግሎችን ወግ ሲጠብቁ እጃቸውን ደኅና አድርገው ሳይታጠቡ አይበሉምና፥ 4 ከገበያም ተመልሰው ካልታጠቡ አይበሉም፥ ጽዋንም ማድጋንም የናስ ዕቃንም አልጋንም እንደ ማጠብ ሌላ ነገር ሊጠብቁት የተቀበሉት ብዙ አለ።

5 ፈሪሳውያንም ጻፎችም፡- ደቀ መዛሙርትህ እንደ ሽማግሌዎች ወግ ስለ ምን አይሄዱም? ነገር ግን እጃቸውን ሳይታጠቡ እንጀራ ይበላሉ ብለው ጠየቁት።

6 እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፡- ኢሳይያስ ስለ እናንተ ስለ ግብዞች፡-

<u>ዮሐንስ 7፡1</u>

1 ከዚህም በኋላ ኢየሱስ አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉ ስለ ነበር በይሁዳ ሊመላለስ አይወድም ነበርና በገሊላ ይመላለስ ነበር።

---

94 [ማቴ. 15፡1፤ ማር. 7፡1] እነዚህ ኢየሩሳሌም ውስጥ ያሉ መሪዎችን የወከሉ ናቸው። ቀደም ሲል ኢየሱስን ሰንበትን በማክበር ጉዳይ ሊያጠምዱ ስላልቻሉ (ክፍል 49ሀ፥ 50፥ 51ን ይመልከቱ) ሌላ ጉዳይ ለማንሣት ወደ ገሊላ መጡ። ይሄውም ከምግብ በፊት እጅ መታጠብን የተመለከተ የሽማግሌዎች ወግ ነበር።

(ማቴዎስ 15፡ 1-3ሀ፥ 7-9፥ 3ለ-6፥ 10-20 የቀጠለ)

8 "ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብ ረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ 9 የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል"

ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ።

3ለ እናንተስ ስለ ወጋችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለ ምን ትተላለፋላችሁ?

4 እግዚአብሔር፦ አባትህንና እናትህን አክብር፤ [ዘጸአት 20፡ 12፤ ዘዳግም 5፡ 16] ደግሞ፦ አባቱን ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ብሎአልና [ዘጸአት 21፡ 17 ዘሌዋውያን 20፡ 9]፤ 5 እናንተ ግን፦[95] አባቱን ወይም እናቱን፦ ከእኔ የምትጠቀምበት መባ ነው የሚል ሁሉ፥ 6 አባቱን ወይም እናቱን አያከብርም ትላላችሁ፤ ስለ ወጋችሁም የእግዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ።

10 ሕዝቡንም ጠርቶ፦ ስሙ አስተውሉም፤ 11 ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም፥ ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው አላቸው።

12 በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው፦ ፈሪሳውያን ይህን ቃል ሰምተው እንደ ተሰናከሉ አወቅህን? አሉት።

(ማርቆስ 7፡ 1-23 የቀጠለ)

"ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ 7 የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል"

ተብሎ እንደ ተጻፈ በእውነት ትንቢት ተናገረ። [ኢሳይያስ 29፡ 13]

8 የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ ጽዋን ማድጋንም እንደ ማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ፥ ይህንም የመሰለ ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ።

9 እንዲህም አላቸው፦ ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል። 10 ሙሴ፦ አባትህንና እናትህን አክብር [ዘጸአት 20፡ 12፤ ዘዳግም 5፡ 16]፤ ደግሞ፦ አባቱን ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ብሎአልና። [ዘጸአት 21፡ 17፤ ዘሌዋውያን 20፡ 9] 11 እናንተ ግን ትላላችሁ፦[95] ሰው አባቱን ወይም እናቱን፦ ከእኔ የምትጠቀምበት ነገር ሁሉ ቍርባን ማለት መባ ነው ቢል፥ 12 ለአባቱና ለእናቱ ምንም እንኳ ሊያደርግ ወደ ፊት አትፈቅዱለትም፤ 13 ባስተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፤ እንደዚሁም ይህን የሚመስል ብዙ ነገር ታደርጋላችሁ።

14 ደግሞም ሕዝቡን ጠርቶ፦ ሁላችሁ እኔን ስሙ አስተውሉም። 15 ከሰው የሚወጡት ሰውን የሚያረክሱ ናቸው እንጂ ከሰው ውጭ የሚገባው ሰው ሊያረክሰው የሚችል ምንም የለም። 16 የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ አላቸው።

[95] [ማቴ. 15፡ 5፤ ማር. 7፡ 11] ይህ በሕግ መምህራንና በፈሪሳውያን የተደገፈ ልዩ ልማድ ነው። ይህን ልማድ በመከተል ወላጆቻቸውን ያከብሩ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ትእዛዝ ይሽሩ ነበር። ውጫዊ ሁኔታ ላይ የሚያተኩረው ሥርዓታቸው፥ ውስጣዊ ባሕርይን በዋናነት የሚመለከተውን የኢየሱስ ትምህርት ይቃረን ነበር (ማቴ. 15፡ 11፤ ማር. 7፡ 15)። ይህን ጉዳይ ግልጥ ሊያደርግ ነው የፈለገው፤ በተለይ ለደቀ መዛሙርቱ (ማቴ. 15፡ 12-20፤ ማር. 7፡ 17-23)።

(ማቴዎስ 15፡1-3ሀ፥ 7-9፥ 3ለ-6፥ 10-20 የቀጠለ)

13 እርሱ ግን መልሶ፡- የሰማዩ አባቴ
ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል። 14
ተዉአቸው፤ ዕውሮችን የሚመሩ ዕውሮች
ናቸው፤ ዕውርም ዕውርን ቢመራው
ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ አለ።

15 ጴጥሮስም መልሶ፡- ምሳሌውን
ተርጉምልን አለው።

16 ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- እናንተ
ደግሞ እስካሁን የማታስተውሉ ናችሁን?
17 ወደ አፍ የሚገባ ሁሉ ወደ ሆድ አልፎ
ወደ እዳሪ እንዲጣል አትመለከቱምን?
18 ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይወጣል፥
ሰውንም የሚያረክሰው ያ ነው።

19 ከልብ ክፉ አሳብ፥ መግደል፥
ምንዝርነት፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ በውሸት
መመስከር፥ ስድብ ይወጣልና። 20 ሰውን
የሚያረክሰው ይህ ነው እንጂ፥ ባልታጠበ
እጅ መብላትስ ሰውን አያረክሰውም።

(ማርቆስ 7፡1-23 የቀጠለ)

17 ከሕዝቡ ዘንድ ወደ ቤት ከገባ በኋላ
ደቀ መዛሙርቱ ምሳሌውን ጠየቁት። 18
እርሱም፡- እናንተ ደግሞ እንደዚህ
የማታስተውሉ ናችሁን? ከውጭ ወደ ሰው
የሚገባ ሊያረክሰው ምንም እንዳይችል
አትመለከቱምን? 19 ወደ ሆድ ገብቶ ወደ
እዳሪ ይወጣል እንጂ ወደ ልብ አይገባምና፤
መብልን ሁሉ እያጠራ አላቸው።

20 እርሱም አለ፡- ከሰው የሚወጣው
ሰውን የሚያረክስ ያ ነው።

21 ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ
አሳብ፥ 22 ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥
ምንዝርነት፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥
ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥
ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና፤ 23 ይህ ክፉው
ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውን ያረክሰዋል።

## ♦ ክፍል 78. ለአማኟ ከነናዊት ጢሮስ እና ሲዶና ውስጥ የተደረገላት አገልግሎት

- በጢሮስና ሲዶና አካባቢ -

ማቴዎስ 15፡21-28

21 ኢየሱስም ከዚያ ወጥቶ ወደ ጢሮስና
ወደ ሲዶና አገር ሄደ። 22 እነሆም፥
ከነናዊት ሴት ከዚያ አገር ወጥታ፡- ጌታ
ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረኝ፤ ልጄን ጋኔን
ክፉኛ ይዞአታል ብላ ጮኸች።

23 እርሱ ግን አንዳች አልመለሰላትም።
ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው፡- በኋላችን
ትጮኻለችና አሰናብታት እያሉ ለመኑት።

24 እርሱም መልሶ፡- ከእስራኤል ቤት
ለጠፉት በጎች በቀር[96] አልተላክሁም
አለ።

ማርቆስ 7፡24-30

24 ከዚያም ተነሥቶ ወደ ጢሮስና ወደ
ሲዶና አገር ሄደ። ወደ ቤትም ገብቶ
ማንም እንዳያውቅበት ወደደ ሊሰወርም
አልተቻለውም፤ 25 ወዲያው ግን ታናሺቱ
ልጅዋ ርኩስ መንፈስ ያደረባት አንዲት
ሴት ስለ እርሱ ሰምታ መጣችና በእግሩ
ላይ ተደፋች 26 ሴቲቱም ግሪክ፥
ትውልድዋም ሲሮፊኒቃዊት ነበረች፤
ከልጅዋ ጋኔን ያወጣላት ዘንድ ለመነችው።

96 [ማቴ. 15፡24] በመቀጠል ላይ የነበረው የኢየሱስ ተልእኮ ልዩ አሠራር (ማቴ. 10፡5-6፥ ክፍል 70ለ) እዚህ ከሆነው ይልቅ የትም በግልጥ አልታየም። ከፈሪሳውያን ጠላቶቹ ወደ አረማውያን ክልል በመሸሽ ላይ ሳለ (ማቴ. 15፡21፤ ማር. 7፡24) የዚህችን ሴትዮ ጥያቄ በመጀመሪያ በፍጹም አልተቀበለም (ማቴ. 15፡23)። ሴትዮይቱ ከእስራኤል ወገን ባለመሆኗ መልካም እንዲደረግላት የመጠየቅ መብት አልነበራትም። አረማውያን በረከት የሚያገኙት፥ እግዚአብሔር እስራኤልን ሲባርክ በተዘዋዋሪ መንገድ ብቻ መሆኑን መገንዘቧን ከገለጠች በኋላ ግን፥ ኢየሱስ አመለካከትና እምነቷን አድንቆ እንደጥያቄዋ አደረገላት (ማቴ. 15፡27-28፤ ማር. 7፡29-30)።

(ማቴዎስ 15፡21-28 የቀጠለ)

25 እርስዋ ግን መጥታ፡- ጌታ ሆይ፥ እርዳኝ እያለች ሰገደችለት።

26 እርሱ ግን መልሶ፡- የልጆችን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም አለ።

27 እርስዋም፡- አዎን ጌታ ሆይ፤ ቡችሎችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ አለች።

28 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ፡- አንቺ ሴት፥ እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደወደድሽ ይሁንልሽ አላት። ልጅዋም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ዳነች።

(ማርቆስ 7፡24-30 የቀጠለ)

27 ኢየሱስ ግን፡- ልጆቹ በፊት ይጠግቡ ዘንድ ተዪ የልጆቹን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባምናአላት።

28 እርስዋም መልሳ፡- አዎን፥ ጌታ ሆይ፥ ቡችሎች እንኳ ከማዕድ በታች ሆነው የልጆችን ፍርፋሪ ይበላሉ አለችው።

29 እርሱም፡- ስለዚህ ቃልሽ ሂጂ ጋኔኑ ከልጅሽ ወጥቶአል አላት።

30 ወደ ቤትዋም ሄዳ ጋኔኑ ወጥቶ ልጅዋም በአልጋ ላይ ተኝታ አገኘች።

## ♦ ክፍል 79ሀ. "አሥር ከተማ" በተባለው ሥፍራ የተከናወነ ፈውስ

- ከጢሮስ ገሊላ ባሕር አጠገብ ወደምትገኘው አሥር ከተማ -

ማቴዎስ 15፡29-31

29 ኢየሱስም ከዚያ አልፎ ወደ ገሊላ ባሕር አጠገብ መጣ፥ ወደ ተራራም ወጥቶ በዚያ ተቀመጠ።

30 ብዙ ሕዝብም አንካሶችን፥ ዕውሮችንም፥ ዲዳዎችንም፥ ጉንድሾችንም፥ ሌሎችንም ብዙ ይዘው ወደ እርሱ ቀረቡ፥ በኢየሱስም እግር አጠገብ ጣሉአቸው፤ ፈወሳቸውም፤ 31 ስለዚህም ሕዝቡ ዲዳዎች ሲናገሩ፥ ጉንድሾችም ሲድኑ፥ አንካሶችም ሲሄዱ፥ ዕውሮችም ሲያዩ አይተው ተደነቁ፤ የእስራኤልንም አምላክ አከበሩ።

ማርቆስ 7፡31-37

31 ደግሞም ከጢሮስ አገር ወጥቶ በሲዶና[97] አልፎ አሥር ከተማ በሚባል አገር መካከል ወደ ገሊላ ባሕር መጣ። 32 ደንቆሮና ኰልታፋም የሆነ ሰው ወደ እርሱ አመጡ፥

33 እጁንም ይጭንበት ዘንድ ለመኑት። ከሕዝቡም ለይቶ ለብቻው ወሰደው፥ ጣቶቹንም በጆሮቹ አገባ እንትፍም ብሎ መላሱን ዳሰሰ፤ 34 ወደ ሰማይም አሻቅቦ አይቶ ቃተተና፡- ኤፍታህ አለው፥ እርሱም ተከፈት ማለት ነው። 35 ወዲያውም ጆሮቹ ተከፈቱ የመላሱም እስራት ተፈታ አጥርቶም ተናገረ።

36 ለማንም እንዳይናገሩ ብሎ አዘዛቸው[98] እነርሱ ግን ባዘዛቸውም መጠን ይልቅ እጅግ አወሩት። 37 ያለ መጠንም ተገረሙና፡- ሁሉን ደኅና አድርጎአል፤ ደንቆሮችም እንዲሰሙ ዲዳዎችም እንዲናገሩ ያደርጋል አሉ።

---

[97] [ማር. 7፡31] ኢየሱስ ከሜዲትራኒያን ዳርቻ እስከ ገሊላ ባሕር ምሥራቅ ዳር ያለውን ረጅምና ጠመዝማዛ መንገድ የተጓዘው፥ ምናልባት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ለብቻው ለመሆን ስለፈለገ ይሆናል። ይህ ጉዞ አጋንንት ያደረባቸውን ሁለት ሰዎች ፈውሶበት ወደነበረና ጌርጌሴኖር የተባለ ስፍራ መራው (ክፍል 66)።

## ♦ ክፍል 79ለ. “አሥር ከተማ” ውስጥ አራት ሺዎችን መመገብ

[ክፍል 72ሐና 81ሀን ይመልከቱ]

- የአሥር ከተማ -

### ማቴዎስ 15፡32-38

32 ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ፡- ሕዝቡ ከእኔ ጋር እስካሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለ ሌላቸው አዝንላቸዋለሁ፤ በመንገድም እንዳይዝሉ ጦማቸውን ላሰናብታቸው አልወድም አላቸው። 33 ደቀ መዛሙርቱም፡- ይህን ያህል ሕዝብ የሚያጠግብ ይህን ያህል እንጀራ በምድረ በዳ ከወዴት[99] እናገኛለን? አሉት።

34 ኢየሱስም፡- ስንት እንጀራ አላችሁ? አላቸው።

እነርሱም፡- ሰባት፥ ጥቂትም ትንሽ ዓሣ አሉት።

35 ሕዝቡም በምድር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፤ 36 ሰባቱንም እንጀራ ዓሣውንም ይዞ አመሰገነ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ።

37 ሁሉም በሉና ጠገቡ፥ የተረፈውንም ቍርስራሽ ሰባት ቅርጫት ሙሉ አነሡ። 38 የበሉትም ከሴቶችና ከልጆች በቀር አራት ሺህ ወንዶች ነበሩ።

### ማርቆስ 8፡1-9ሀ

1 በዚያ ወራት ደግሞ ብዙ ሕዝብ ነበረ የሚበሉትም ስለሌላቸው ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ፡- 2 ሕዝቡ ከእኔ ጋር እስካሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋለሁ፤ 3 ከእነርሱም አንዳንዶቹ ከሩቅ መጥተዋልና ጦማቸውን ወደ ቤታቸው ባሰናብታቸው በመንገድ ይዝላሉ አላቸው።

4 ደቀ መዛሙርቱም፡- በዚህ በምድረ በዳ እንጀራ ከየት[99] አግኝቶ ሰው እነዚህን ማጥገብ ይችላል? ብለው መለሱለት።

5 እርሱም፡- ስንት እንጀራ አላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው፥

እነርሱም፡- ሰባት አሉት።

6 ሕዝቡም በምድር እንዲቀመጡ አዘዘ። ሰባቱንም እንጀራ ይዞ አመሰገነ፥ ቈርሶም እንዲያቀርቡላቸው ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ለሕዝቡም አቀረቡ። 7 ጥቂትም ትንሽ ዓሣ ነበራቸው፤ ባረከውም ይህንም ደግሞ እንዲያቀርቡላቸው አዘዘ። 8 በሉም ጠገቡም፥ የተረፈውንም ቍርስራሽ ሰባት ቅርጫት አነሡ። 9ሀ የበሉትም አራት ሺህ ያህል ነበሩ።

---

98 [ማር. 7፡36] ለማንም እንዳትናገሩ ተብሎ እዚህ በታዘዘውና ቀደም ሲል ወሬው እንዲሠራጭ በተሰጠው (ማር. 5፡19፥ ክፍል 66) ትእዛዝ መካከል ያለው ልዩነት ሰፊ ነው። ኢየሱስ ቀደም ሲል መልእክቱን ለብዙዎች ያደርስ ነበር፤ አሁን ግን የወሬው መሠራጨት አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት የማሰልጠኑን ልዩ ሥራ የሚያደናቅፍበት መሆኑ ግልጥ ሆነ። ሕመምተኞችን በሚፈውስበት ጊዜም እንኳን ከብዙ ሰዎች እይታ ለመሠወር ልዩ ጥረት ያደርግ ነበር (ማር. 7፡33)።

99 [ማቴ. 15፡33፤ ማር. 8፡4] ከጥቂት ጊዜ በፊት አምስት ሺህ ሰዎች መመገባቸውን ደቀ መዛሙርቱ መርሳታቸው (ክፍል 72ሐ) የሚገርም ነው። ምናልባት ኢየሱስ ቀደም ሲል በዚያ የነበሩትን ብዙ ሰዎች በራስ ወዳድነታቸው በጥብቅ መገሰጹን (ዮሐ. 6፡26-27፥ ክፍል 76ሀ) የተገነዘቡት በተሳሳተ መንገድ ይሆናል። ይህን የመሰለ ተአምር ዳግመኛ የሚፈጽም አልመሰላቸውም። ኢየሱስ ይህን የተሳሳተ ግንዛቤ ለማስተካከል ሲል በጣም ብዙ ሰዎችን በተአምር መገበ። ማንነቱንና እንዲያ ያለውን ተአምር ማድረጉ በመሠረቱ ስሕተት እንዳልሆነ ለአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በትዕግሥት አረጋገጠላቸው።

## ♦ ክፍል 80. ወደ ገሊላ መመለስ እና ከፈሪሳውያን፥ እንዲሁም ከሰዱቃውያን ጋር መጋጨት [ክፍል 62ና 106ን ይመልከቱ]

- ከአሥር ከተማ ወደ መጌዶል (ዳልማኑታ) -

<u>ማቴዎስ 15፡39-16፡4</u>

39 ሕዝቡንም ካሰናበተ በኋላ ወደ ታንኳይቱ ገብቶ ወደ መጌዶል[1] አገር መጣ።

1 ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንም ቀርበው ሲፈትኑት ከሰማይ ምልክት[2] እንዲያሳያቸው ለመኑት።

2 እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው:- በመሸ ጊዜ:- ሰማዩ ቀልቶአልና ብራ ይሆናል ትላላችሁ፤ 3 ማለዳም:- ሰማዩ ደምኖ ቀልቶአልና ዛሬ ይዘንባል ትላላችሁ። የሰማዩን ፊትማ መለየት ታውቃላችሁ፥ የዘመኑንስ ምልክት መለየት አትችሉምን? 4 ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። ትቶአቸውም ሄደ።

<u>ማርቆስ 8፡9ለ-12</u>

9ለ አሰናበታቸውም። 10 ወዲያውም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳይቱ ገብቶ ወደ ዳልማኑታ[1] አገር መጣ።

11 ፈሪሳውያንም ወጡና ሊፈትኑት ከሰማይ ምልክት ከእርሱ ፈልገው ከእርሱ ጋር ይከራከሩ ጀመር።

12 በመንፈሱም እጅግ ቃተተና:- ይህ ትውልድ ስለ ምን ምልክት ይፈልጋል? እውነት እላችኋለሁ፥ ለዚህ ትውልድ ምልክት አይሰጠውም አለ።

## ♦ ክፍል 81ሀ. ስለ ፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያንና ሄሮዳውያን ስሕተት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

[ክፍል 72ሐ፥ 79ለና 108ሀን ይመልከቱ]

- በገሊላ ባሕር በስተ ምሥራቅ -

<u>ማቴዎስ 16፡5-12</u>

5 ደቀ መዛሙርቱም ወደ ማዶ በመጡ ጊዜ እንጀራ መያዝን ረሱ። 6 ኢየሱስም:- ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ[3] ተጠንቀቁና ተጠበቁ አላቸው።

<u>ማርቆስ 8፡13-21</u>

13 ትቶአቸውም እንደ ገና ወደ ታንኳይቱ ገብቶ ወደ ማዶ ሄደ።

14 እንጀራ መያዝም ረሱ፥ ለእነርሱም ከአንድ እንጀራ በቀር በታንኳይቱ አልነበራቸውም። 15 እርሱም:- ተጠንቀቁ፤ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ

---

[1] [ማቴ. 15፡39፤ ማር. 8፡10] መጌዶል እና ዳልማኑታ የአንድ አካባቢ ሁለት ስሞች፥ ወይም በአንድ የተቀራረበ አካባቢ የሚገኙ የሁለት የተለያዩ ቦታዎች ስሞች ናቸው።

[2] [ማቴ. 16፡1] ኢየሱስ እንደገና ገሊላን እንደረገጠ ነው ጠላቶቹ የተነሡበት። ምልክት እንዲያሳያቸው ጠየቁት። ምናልባት እግዚአብሔር ለሙሴ (ዘጸ. 16፡15)፥ ለኢያሱ (ኢያሱ 10፡13)፥ ለሳሙኤል (1ኛ ሳሙ. 12፡18)፥ ለኤልያስ (1ኛ ነገሥ. 18፡38) እና ለኢሳይያስ (2ኛ ነገሥ. 20፡11፤ ኢሳ. 38፡8) ስላደረገው ነገር ይሆናል። ሆኖም ኢየሱስ በበፊቱ መልሱ ጸና (ማቴ. 16፡4 ፥ እና ማር. 8፡12ን ከማቴ. 12፡39፥ ክፍል 62 ጋር ያነጻጽሩ)። ኢየሱስን በመቃወሙ ተግባር ሰዱቃውያን ከፈሪሳውያን ጋር ተባበሩ። ሁለቱም ወገኖች በኢየሱስ ላይ ባላቸው ጠላትነት የተነሣ ልዩነታቸውን ለመርሳትም ተስማሙ።

(ማቴዎስ 16፥5-12 የቀጠለ)

7 እነርሱም፡- እንጀራ ባንይዝ ነው ብለው እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ።

8 ኢየሱስም አውቆ እንዲህ አላቸው፡- እናንተ እምነት የጐደላችሁ፥ እንጀራ ስለ ሌላችሁ ስለ ምን እርስ በርሳችሁ ትነጋገራላችሁ? ገና አታስተውሉምን? 9 ለአምስቱ ሺህ አምስቱ እንጀራ፥ ስንት መሶብም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን? 10 ወይስ ለአራቱ ሺህ ሰባቱ እንጀራ፥ ስንት ቅርጫትም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን? 11 ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ እንድትጠበቁ ብዬ ስለ እንጀራ እንዳልተናገርኋችሁ እንዴት አታስተውሉምን? 12 እነርሱም ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት እንጂ ከእንጀራ እርሾ እንዲጠበቁ እንዳላላቸው ያን ጊዜ አስተዋሉ።

(ማርቆስ 8፥13-21 የቀጠለ)

እርሾ[3] ተጠበቁ ብሎ አዘዛቸው።

16 እርስ በርሳቸውም፡- እንጀራ ስለሌለን ይሆናል ብለው ተነጋገሩ።

17 ኢየሱስም አውቆ እንዲህ አላቸው፡- እንጀራ ስለሌላችሁ ስለ ምን ትነጋገራላችሁ? ገና አልተመለከታችሁምን? አላስተዋላችሁምን? 18 ልባችሁስ ደንዝዞአልን? ዓይን ሳላችሁ አታዩምን? ጆሮስ ሳላችሁ አትሰሙምን? [ሕዝቅኤል 12፥2] ትዝስ አይላችሁምን? 19 አምስቱን እንጀራ ለአምስት ሺህ በቈረስሁ ጊዜ፥ ቍርስራሽ የሞላ ስንት መሶብ አነሣችሁ? እነርሱም፡- አሥራ ሁለት አሉት።

20 ሰባቱን እንጀራስ ለአራት ሺህ በቈረስሁ ጊዜ፥ ቍርስራሽ የሞላ ስንት ቅርጫት አነሣችሁ? እነርሱም፡- ሰባት አሉት።

21 ገና አላስተዋላችሁምን? አላቸው።

## ♦ ክፍል 81ለ. ቤተ ሳይዳ ውስጥ አንድ ዓይነ ስውር መፈወሱ

- ቤተ ሳይዳ -

ማርቆስ 8፥22-26

22 ወደ ቤተ ሳይዳም መጡ። ዕውርም አመጡለት፥ እንዲዳስሰውም ለመኑት። 23 ዕውሩንም እጁን ይዞ ከመንደር ውጭ አወጣው፥ በዓይኑም ተፍቶበት እጁንም ጭኖበት፡- አንዳች ታያለህን ብሎ ጠየቀው።

24 አሻቅቦም፡- ሰዎች እንደ ዛፍ ሲመላለሱ አያለሁ አለ።

25 ከዚህም በኋላ ደግሞ እጁን በዓይኑ ላይ ጫነበት አጥርቶም አየና ዳነም ከሩቅም ሳይቀር ሁሉን ተመለከተ።[4] 26 ወደ ቤቱም ሰደደውና፡- ወደ መንደሩ አትግባ በመንደሩም ለማንም አንዳች አትናገር አለው።

[3] [ማቴ. 16፥6፤ ማር. 8፥15] እርሾ የርኩሰት ምሳሌ ሆኖ በሕግ ውስጥ ተጠቅሷል (ዘጸ. 34፥25፤ ዘሌ. 2፥11)። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ይህን ምሳሌ እንደሚረዱ ገምቶ ነበር (ማቴ. 6፥11፤ ማር. 8፥17፥ 21)። ከአምስት ሺሆቹና ከአራት ሺሆቹ ጋር ያደረጋቸው ተአምራት ስለምግብ ችግር ማሰብ የማያሻው መሆኑን አስገንዝቧቸዋል (ክፍል 72ሐ እና 79ለ)። ሰሞኑን ስለ እውነተኛው የርኩሰት ምንጭ የሰጠው መግለጫ በደቀ መዛሙርቱ አእምሮ ገና ትኩስ ነበር (ክፍል 77)። ጌታ ይናገር የነበረው፥ በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ሊመጣ ስለሚችለው ርኩሰት መሆኑን በጥቂት ማስታወስ ብቻ ሊረዱ ይችሉ ነበር። ፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያንና የሄሮድስ ደጋፊዎች ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥትን አሳብ አጣመውታል። ፈሪሳውያን አሳቡ ከሽማግሌዎች ልማድ ጋር እንዲስማማ አድርገው ሊያስተካክሉት ይችሉ ነበር። ሰዱቃውያን በማገናዘብ ዘዴ ተጠቅመው ይህን ጉዳይ በተመለከተ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የተነገረን ትንቢት ለመሻር ሞከሩ። የሄሮድስ ተከታዮች ደግሞ ከሄሮድስ ቤተሰብ አባላት በተስፋ የሚጠበቅ ንጉሥ እንደሚኖር ቆጠሩ። አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ራሳቸውን ከተሣሣተ ግንዛቤ እያራቁ፥ ሊታወቅ ስላለው መሢሕ እውቀት ራሳቸውን ያዘጋጁ ነበር (ክፍል 82)።

# > መሢሐዊነት በትምህርት ተሰጠ፥ ተረጋገጠ <

## ♦ ክፍል 82. ጴጥሮስ ኢየሱስን መሢሕነት ተናገረ፤ ስለ ቤት ክርስቲያን የተነገረ የመጀመሪያ ትንቢት

[ክፍል 76ለን ይመልከቱ]

- ፊልጶስ ቂሣርያ አገር -

ማቴዎስ 16፡13-20

13 ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ[5] አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን፦ ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ።

14 እነርሱም፦ አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት።

15 እርሱም፦ እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?[6] አላቸው።

16 ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፦[7] አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።

ማርቆስ 8፡27-30

27 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም በፊልጶስ ቂሣርያ[5] ወዳሉ መንደሮች ወጡ በመንገድም፦ ሰዎች እኔ ማን እንደ ሆንሁ ይላሉ? ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው።

28 እነርሱም፦ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ከነቢያት አንዱ ብለው ነገሩት።

29 እናንተስ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ?[6] ብሎ ጠየቃቸው።

ጴጥሮስም፦ አንተ ክርስቶስ ነህ ብሎ መለሰለት።

ሉቃስ 9፡18-20

18 ለብቻውም ሲጸልይ ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር ነበሩና፦ ሕዝቡ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ይላሉ? ብሎ ጠየቃቸው።

19 እነርሱም መልሰው፦ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም፦ ኤልያስ፥ ሌሎችም፦ ከቀደሙት ነቢያት አንዱ ተነሥቶአል ይላሉ አሉት።

20 እናንተስ እኔ ማን[6] እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ጴጥሮስም መልሶ፦ ከእግዚአብሔር የተቀባህ ነህ አለ።

---

[4] [ማር. 8፡25] በማርቆስ ብቻ ከተመዘገቡት ሁለት ተአምራት ይህ አንዱ ነው (ክፍል 79ሀ)። አንድ ሰው ከሁለቱ ተአምራት በመነሣት ክርስቶስ ፈውሱን ለመተግበር ችግር የገጠመው ይመስለው ይሆናል። በሁለቱም ጊዜ ኢየሱስ ድርጊቱን ያከናወነው ለብቻው ገለል ብሎ ነው (ማር. 8፡23)። ድርጊቱ በብዙዎች እንዲታወቅም አልፈለገም ነበር (ማር. 8፡26)። ይህ ቤተሳይዳ ውስጥ በሁለት ደረጃ የተከናወነ ጉዳይ፥ ኢየሱስ በዝግታ የፈወሰበት ብቸኛ አጋጣሚ ነው (ማር. 8፡24-25)። ምናልባት አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ተአምራቶች ሁሉ በቅጽበት እንደማይከናወኑ እንዲገነዘቡ ይሆናል። በአንዳንድ ሁኔታዎች መለኮታዊ ኃይል በኃጢአትና በደዌ ላይ የሚኖረው ድል በቀስታ የሚከናወን ይሆናል።

[5] [ማቴ. 16፡13፤ ማር. 8፡27] የዚህ ክልል ገዢ ሄሮድስ ፊልጶስ የተባለው ነው። ከሌሎቹ ወንድሞቹ ማለት ከአርኬላዎስና ከአንቲጳስ ጋር ሲነጻጸር ሄሮድስ ፊልጶስ ትክክለኛ መሪ ነበር። እንደ አንቲጳስ ኢየሱስን የሚጠረጥርበት ምክንያት አልነበረም (ክፍል 72ረ)። ኢየሱስ አረማውያን በብዛት በሚኖሩበትና ጥቂት ሁኔታ ብቻ ከአይሁድ ተቃውሞ በሚያስነሣበት በዚህ አካባቢ ምናልባት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቆይቶ ይሆናል።

[6] [ማቴ. 16፡15፤ ማር. 8፡29፤ ሉቃስ 9፡20] ኢየሱስ ትክክለኛ ማንነቱን ሌሎች መገንዘባቸውን ጠይቆ የመረጃው ትክክለኛ ጊዜ መሆኑን ተረዳ። ከወራት በፊት ከገሊላ ከወጣበት ጊዜ አንሥቶ፥ በአካባቢው ይንቀሳቀስ የነበረበት ዓላማ ይህ ነበር (ክፍል 72ለ)። ማንኛውም እንቅስቃሴው ደቀ መዛሙርቱ በርሱ ማንነት እምነት እንዲያድርባቸው ለማድረግ የታቀደ ነው። ስለሆነም ጌታ ያቀረበውን ጥያቄ በመመለስ የተረዱትን ማረጋገጥ ነበረባቸው።

(ማቴዎስ 16፡ 13-20 የቀጠለ)

17 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡-
የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው
አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን
አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። 18 እኔም
እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም
ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን[8] እሠራለሁ፥
የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም። 19
የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች
እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ
በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም
የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆ
ናል። 20 ያን ጊዜም እርሱ ክርስቶስ እንደ
ሆነ ለማንም እንዳይነግሩ[9] ደቀ
መዛሙርቱን አዘዛቸው።

(ማርቆስ 8፡ 27-30 የቀጠለ)

30 ስለ እርሱም ለማንም እንዳይናገሩ[9]
አዘዛቸው።

[7] [ማቴ. 16፡ 16] የጴጥሮስን ሙሉ መልስ የመዘገበው ማቴዎስ ነው። የኢየሱስ መሢሕነትና መለኮታዊነት ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አዲስ ጽንሰ አሳብ አይደለም (ማቴ. 14፡ 33፥ ክፍል 74፤ ዮሐ. 1፡ 41፥ 49፥ ክፍል 28)። ጴጥሮስና ሌሎቹ ባዩትና በሰሙት መሠረት ማንነቱን አሁን እንዲህ ሊያረጋግጡ ቻሉ። ጴጥሮስ ለቀረበለት ጥያቄ የመለሰው እውነት፥ ኢየሱስ የቅርብ ተከታዮቹ ለሆኑት አሥራ ሁለት ተከታዮቹ ለሚሰጣቸው ተጨማሪ ትምህርት መሠረት ነው።

[8] [ማቴ. 16፡ 18] ይህ ኢየሱስ ሊያከናውነው ያለ አዲስ ሥራ መግለጫ ነው። ገለጣው የተደረገው ቤተ ክርስቲያን ብሎ የጠራት ተቋም አካል ለሚሆኑ ሰዎች ነበር። እነዚህ የጌታ የቅርብ ደቀ መዛሙርት ፈጥነው ሊረዱት ያልቻሉትን፥ በኋላ ግን የሕይወታቸው ዋና ጉዳይ የሆነ ነገር መስማት ጀመሩ።

[9] [ማቴ. 16፡20፤ ማር. 8፡30፤ ሉቃስ 9፡21] የኢየሱስ መሢሕነትና መለኮትነት ምንም እንኳን ለቤተ ክርስቲያን መሠረቶች ቢሆኑ፥ በሰፊው የተሠራጩ ጉዳዮች አልነበሩም። በዚህ ጊዜ የእስራኤል መሪዎች የጌታን ሥልጣን አንቀበልም በማለት ቀና መልስ ለመስጠት የነበራቸውን ዕድል አጡ (ክፍል 61)። ሕዝቡ በበኩሉ ከመሢሑ ምድራዊ አገዛዝ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ለሚጠየቀው ሥነ-ምግባራዊ ሁኔታ ለመገዛት ፈቃደኛ ያለመሆኑን በተመሳሳይ ሁኔታ ያሳይ ጀመር (ክፍል 73)። ኢየሩሳሌም ውስጥ፥ አይሁድ ባለሥልጣኖች ፊት ማንነቱ በግልጥ እስኪታወቅ ድረስ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከሕዝቡና ከመሪዎቹ ጋር መገናኘቱ ተገቢ አልነበረም (ማቴ. 26፡ 63-64፥ ክፍል 155)።

## ♦ ክፍል 83. የክርስቶስ ተቀባይነት ማጣት፥ መስቀሉ እና ትንሣኤው ለመጀመሪያ ጊዜ በቅድሚያ ስለመነገሩ

[ክፍል 70ለ፥ 85፥ 86፥ 88፥ 115፥ 125ሀና 130ሀን ይመልከቱ]

- ፊልጶስ ቂሣርያ አጠገብ -

### ማቴዎስ 16፡21-26

21 ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር።[10]

22 ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ፡- አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።

23 እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን፡- ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።

24 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፡- እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ። 25 ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል። 26 ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?

### ማርቆስ 8፡31-37

31 የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል፥ ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጻፎችም ሊጣል፥ ሊገደልም ከሦስት ቀንም በኋላ ሊነሣ እንዲገባው ያስተምራቸው ጀመር፤[10] ቃሉንም ገልጦ ይናገር ነበር። 32 ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ ይገሥጸው ጀመር።

33 እርሱ ግን ዘወር አለ ደቀ መዛሙርቱንም አይቶ ጴጥሮስን ገሠጸውና፡- ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብምና አለው።

34 ሕዝቡንም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠርቶ እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ። 35 ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል። 36 ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? 37 ሰውስ ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?

### ሉቃስ 9፡21-25

21-22 እርሱ ግን፡- የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል[10] በሽማግሌዎችም በካህናት አለቆችም በጻፎችም ሊጣል ሊገደልም በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ይገባዋል ብሎ ለማንም[9] ይህን እንዳይናገሩ አስጠንቅቆ አዘዘ።

23 ለሁሉም እንዲህ አላቸው፡- በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ። 24 ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን እርሱ ያድናታል። 25 ሰው ዓለሙን ሁሉ አትርፎ ራሱን ቢያጠፋ ወይም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?

## ♦ ክፍል 84. የሰው ልጅ ምጽአትና ፍርድ

- ፊልጶስ ቂሣርያ አጠገብ -

| ማቴዎስ 16፥27-28 | ማርቆስ 8፥38-9፥1 | ሉቃስ 9፥26-27 |
|---|---|---|
| 27 የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል። [መዝሙር 62፥12፤ ምሳሌ 24፥12] 28 እውነት እላችኋለሁ፥ የሰው ልጅ በመንግሥቱ[11] ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ። | 38 በዚህም በዘማዊና በኃጢአተኛ ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፥ የሰው ልጅ ደግሞ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ በእርሱ ያፍርበታል። 1 እውነት እላችኋለሁ፥ በዚህ ከቆሙት ሰዎች የእግዚአብሔር መንግሥት[11] በኃይል ስትመጣ እስኪያዩ ድረስ፥ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ አላቸው። | 26 በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፥ የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል። 27 እውነት እላችኋለሁ፥ በዚህ ከሚቆሙት ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት[11] እስኪያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ። |

## ♦ ክፍል 85. የኢየሱስ በተራራ ላይ መለወጥ

[ክፍል 24፥ 83፥ 86፥ 88ና 125ሀን ይመልከቱ]

- ረጅም ተራራ[12]፥ ምናልባት ሐርሞን ተራራ -

| ማቴዎስ 17፥1-8 | ማርቆስ 9፥2-8 | ሉቃስ 9፥28-36ሀ |
|---|---|---|
| 1 ከስድስት ቀንም በኋላ[13] ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም | 2 ከስድስት ቀንም በኋላ[13] ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ይዞ ወደ ረጅም ተራራ | 28 ከዚህም ቃል በኋላ ስምንት ቀን[13] ያህል ቈይቶ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ያዕቆብንም ይዞ ሊጸልይ ወደ |

10 [ማቴ. 16፥21፤ ማር. 8፥31፤ ሉቃስ 9፥22] ይህ ትንቢት ከጴጥሮስ ቃል መግባት በኋላ ወዲያው የመጣ እንደመሆኑ በትክክል በጴጥሮስ ቃል ሳቢያ የሆነ ነው። ትንቢቱ ከጴጥሮስ ቃል ቀደም ብሎ ቢሆን ኖሮ፥ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ትንቢቱን ሲሰሙ ስለ ጌታ የነበራቸው እምነት ይናጋ ነበር። ምንም እንኳ ቀደም ሲል በተሸፈነ አነጋገር ቢጠቅሳቸውም ከአንድ ዓመት በኋላ ሊሆኑ ስላላቸው ነገሮች ኢየሱስ በግልጥ ሲተነብይ የመጀመሪያው ነው (ዮሐ. 2፥19፥ ክፍል 31)። ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ መሢሕነት እርግጠኛ ስለነበር፥ እንዲህ ያለውን ገለጣ ሊቀበለው አልፈለገም (ማቴ. 16፥22፤ ማር. 8፥32)። ይህ የተሳሳተ ቅንዓቱ ጌታ በሰይጣን ከተፈተነ በኋላ የተናገረውን የግሳጼ ቃል እንዲቀበል አድርጎታል (ማቴ. 4፥10፥ ክፍል 25)።

11 [ማቴ. 16፥28፤ ማር. 9፥1፤ ሉቃስ 9፥27] ይህን የእግዚአብሔር ልጅና የመንግሥት መምጣት ጉዳይ የተለያዩ ሰዎች ከኢየሱስ ትንሣኤና እርገት፥ ከበዓለ አምሳ፥ ከክርስትና መስፋፋት፥ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት፥ ወይም በ70 ዓ.ም. ከደረሰው የኢየሩሳሌም መፈራረስ ጋር በማመሳሰል እንደተጸመ ድርጊት አድርገው የቆጠሩት አሉ። ይሁን እንጂ ከታሪክ እና ከቃሉ አገባብ ጋር የሚጣጣመው ትርጉም፥ ወዲያውኑ በተራራው ላይ በሦስቱ ደቀ መዛሙርት ፊት የተከናወነውን የኢየሱስ መለወጥ ትእይንት አስመልክቶ የተጠቀሰውን መረዳት ነው (ክፍል 85)። የእግዚአብሔርን ልጅ ዳግመኛ መምጣት ምልክት ለሦስት አድማጮች በምድራዊ ሕይወት እያሉ ተገልጦላቸዋል።

(ማቴዎስ 17:1-8 የቀጠለ)

ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። 2 በፊታቸውም ተለወጠ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። 3 እነሆም፥ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው።

4 ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን፦ ጌታ ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ፥ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ።

5 እርሱም ገና ሲናገር፥ እነሆ፥ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፥ እነሆም፥ ከደመናው፦ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።

6 ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው በፊታቸው ወደቁ እጅግም ፈርተው ነበር። 7 ኢየሱስም ቀርቦ ዳሰሳቸውና፦ ተነሡ አትፍሩም አላቸው። 8 ዓይናቸውንም አቅንተው ሲያዩ ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም።

(ማርቆስ 9:2-8 የቀጠለ)

ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ፥ ልብሱም አንጸባረቀ፤ 3 አጣቢም በምድር ላይ እንደዚያ ሊያነጣው እስከማይችል በጣም ነጭ ሆነ። 4 ኤልያስና ሙሴም ታዩአቸው፥ ከኢየሱስም ጋር ይነጋገሩ ነበር።

5 ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን፦ መምህር ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነውና አንድ ለአንተ አንድም ለሙሴ አንድም ለኤልያስ ሦስት ዳሶች እንሥራ አለው። 6 እጅግ ስለ ፈሩ የሚለውን አያውቅም ነበር።

7 ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው፥ ከደመናውም፦ የምወደው ልጄ ይህ ነው፥ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።

8 ድንገትም ዞረው ሲመለከቱ ከእነርሱ ጋር ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም።

(ሉቃስ 9:28-36ሀ የቀጠለ)

ተራራ ወጣ። 29 ሲጸልይም የፊቱ መልክ ተለወጠ፤ ልብሱም ተብለጭልጮ ነጭ ሆነ። 30 እነሆም፥ ሁለት ሰዎች እነርሱም ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር፤ 31 በክብርም ታይተው በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው ስለ መውጣቱ[14] ይናገሩ ነበር። 32 ነገር ግን ጴጥሮስንና ከእርሱ ጋር የነበሩት እንቅልፍ ከበደባቸው፤ ነቅተው ግን ክብሩንና ከእርሱ ጋር ቆመው የነበሩትን ሁለት ሰዎች አዩ። 33 ከእርሱም ሲለዩ ጴጥሮስ ኢየሱስን፦ አቤቱ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነውና አንድ ለአንተ አንድም ለሙሴ አንድም ለኤልያስ ሦስት ዳሶች እንሥራ አለው፤ የሚለውንም አያውቅም ነበር።

34 ይህንም ሲናገር ደመና መጣና ጋረዳቸው፤ ወደ ደመናውም ሲገቡ ሳሉ ፈሩ። 35 ከደመናውም፦ የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው፥ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።

36ሀ ድምፁም ከመጣ በኋላ ኢየሱስ ብቻውን ሆኖ ተገኘ።

## ♦ ክፍል 86. ስለ ትንሣኤ፥ ስለ ኤልያስ እና ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የተደረገ ውይይት [ክፍል 83፥ 85፥ 88ና 125ሀን ይመልከቱ]

- ከተራራው መውረድ -

<u>ማቴዎስ 17፡9-13</u>

9 ከተራራውም በወረዱ ጊዜ ኢየሱስ፡- የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ[15] ያያችሁትን ለማንም አትንገሩ ብሎ አዘዛቸው። 10 ደቀ መዛሙርቱም፡- እንግዲህ ጻፎች፡- ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል ስለ ምን ይላሉ? ብለው ጠየቁት። 11 ኢየሱስም መልሶ፡- ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናል፤ 12 ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ፤ የወደዱትንም ሁሉ አደረጉበት እንጂ አላወቁትም፤ እንዲሁም ደግሞ የሰው ልጅ ከእነርሱ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው አላቸው። 13 በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ስለ መጥምቁ ስለ ዮሐንስ[16] እንደ ነገራቸው አስተዋሉ።

<u>ማርቆስ 9፡9-13</u>

9 ከተራራውም ሲወርዱ የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ[15] ያዩትን ለማንም እንዳይነግሩ አዘዛቸው። 10 ቃሉንም ይዘው፡- ከሙታን መነሣት ምንድር ነው? እያሉ እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ። 11 እነርሱም፡- ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ እንዲገባው ጻፎች ስለ ምን ይላሉ? ብለው ጠየቁት። 12 እርሱም መልሶ፡- ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናናል፤ ስለ ሰው ልጅም እንዴት ተብሎ ተጽፎአል? ብዙ መከራ እንዲቀበል እንዲናቅም። 13 ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ኤልያስ ደግሞ መጥቶአል፥ ስለ እርሱም እንደ ተጻፈ የወደዱትን ሁሉ አደረጉበት አላቸው።

<u>ሉቃስ 9፡36ለ</u>

እነርሱም ዝም አሉ ካዩትም ነገር በዚያ ወራት ምንም ለማንም አላወሩም።

---

[12] ጌታ የተለወጠበት ተራራ በትክክል አልታወቀም። የታቦር ተራራ መሆኑ በተለምዶ ይነገራል። ይህም ቂሶን ከተባለው ወንዝ ጀምሮ ሽቅብ የሚወጣው ነው። ያ ግን ይሆናል ተብሎ ከሚገመትበት ከፊልጶስ ቂሣርያ በጣም የራቀ ነው። ከዚህም ሌላ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ አረማውያን ያመልኩበት ወደነበረ ወደዚያ ተራራ የሚሄዱ አይመስልም። ሌሎቹ ሰዎች ሥፍራው ቅፍርናሆም አጠገብ ከነበሩት ተራራዎች አንዱ ነው ብለዋል። ነገር ግን ከነዚያ ተራራዎች የትኛውም ቢሆን "ረጅም ተራራ" ተብሎ በማቴዎስና በማርቆስ የተነገረለት ሊሆን አይችልም። ለዚህ ገለጣ የሚስማማው አርሞንኤም ተራራ ሲሆን፥ ክርስቶስ በቅርቡ ከነበረበት ከፊልጶስ ቂሣርያ አጠገብም ነበር።

[13] [ማቴ. 17፡1፤ ማር. 9፡2፤ ሉቃስ 9፡28] ሉቃስ "ስምንት ቀን ያህል" ሲል የገለጠው ማቴዎስና ማርቆስ ከገለጡት ስድስት ቀን ጋር ተቀራራቢ ቁጥር ነው። የጴጥሮስ መመስከር፥ ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገረው የመጀመሪያ ትንቢት፥ የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ትንቢት፥ እንዲሁም የንጉሡና የመንግሥቱ ማረጋጋጫ ራእይ የመጣው በዚህ በአንድ ሳምንት ውስጥ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ፥ ቤተ ክርስቲያን እና የመሢሑ የእሥራቱና የሞቱ ትንቢት ስለ መጪው መንግሥት በተነገረው ያልተፈጸመ ትንቢት ላይ እንዴት ተጽእኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ሳያስቡ አይቀሩም። የተራራው ላይ መለወጥ ትንቢቶቹ በትክክል የሚፈጸሙ ለመሆናቸው እንደገና አረጋግጦላቸዋል። ቢያንስ ለጴጥሮስ ይህ እውነት ነበር (2ኛ ጴጥ. 1፡16-19)።

# > ለሌሎች ስለማሰብ የተሰጡ ትምህርቶች <

## ♦ ክፍል 87. *ጋኔን ያደረበት ልጅ መፈወስ እና የእምነት የለሽነት መገሰፅ*

- ኢየሱስ ፍጹም የተለወጠበት ተራራ አጠገብ -

| ማቴዎስ 17፡14-21 | ማርቆስ 9፡14-29 | ሉቃስ 9፡37-43ሀ |
|---|---|---|
| | 14 ወደ ደቀ መዛሙርቱም በመጣ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ሲከብቡአቸው ጻፎችም ከእነርሱ ጋር ሲከራከሩ አየ። 15 ወዲያውም ሕዝቡ ሁሉ ባዩት ጊዜ ደነገጡ፥ ወደ እርሱም ሮጠው እጅ ነሡት። | |
| 14 ወደ ሕዝቡም ሲደርሱ አንድ ሰው ወደ እርሱ ቀረበና ተንበርክኮ፦ ጌታ ሆይ፥ ልጄን ማርልኝ፥ በጨረቃ እየተነሣበት ክፉኛ ይሣቀያልና፤ 15 ብዙ ጊዜ በእሳት ብዙ ጊዜም በውኃ ይወድቃልና። 16 ወደ ደቀ መዛሙርትህም አመጣሁት ሊፈውሱትም አቃታቸው አለው። | 16 ጻፎችንም፦ ስለ ምን ከእነርሱ ጋር ትከራከራላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። 17 ከሕዝቡ አንዱ መልሶ፦ መምህር ሆይ፥ ዲዳ መንፈስ ያደረበትን ልጄን ወደ አንተ አምጥቼአለሁ፤ 18 በያዘውም ስፍራ ሁሉ ይጥለዋል፤ አረፋም ይደፍቃል፥ ጥርሱንም ያፋጫል ይደርቃልም፤ እንዲያወጡለትም ለደቀ መዛሙርትህ ነገርኋቸው፥ አልቻሉምም አለው። 19 እርሱም መልሶ፦ | 37 በነገውም ከተራራ ሲወርዱ ብዙ ሕዝብ ተገናኙት። 38 እነሆም፥ ከሕዝቡ አንድ ሰው እንዲህ እያለ ጮኸ፦ መምህር ሆይ፥ ለእኔ አንድ ልጅ ነውና ልጄን እንድታይልኝ እለምንሃለሁ። 39 እነሆም፥ ጋኔን ይይዘዋል፥ ድንገትም ይጮኻል አረፋም እያስደፈቀው ያንፈራግጠዋል፥ እየቀጠቀጠም በጭንቅ ይለቀዋል፤ 40 ደቀ መዛሙርትህንም እንዲያወጡት ለመንሁ፥ አልቻሉምም። |

[14] [ሉቃስ 9፡31] በሙሴ፥ በኤልያስና በኢየሱስ መካከል ንግግር የነበረ መሆኑን የሚገልጠው ሉቃስ ብቻ ነው። “ስለመውጣቱ” የሚለው ቃል ምናልባት ስለ ኢየሱስ ሞት የሚናገር ይሆናል።

[15] [ማቴ. 17፡9፤ ማር. 9፡9] ማርቆስ 9፡10 እንደሚገልጠው ደቀ መዛሙርቱ የሰው ልጅ ከሙታን የመነሣቱን ትንቢት ከሙታን መነሣቱን አይተው እስኪያረጋግጡ ድረስ አልተረዱም ነበር። የተራራው ላይ መለወጥ እውቀታቸውን ቁም ነገር በተገቢው ሁኔታ ሊረዱት የሚችሉት ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ነበር (2ኛ ጴጥ. 1፡16-19)።

[16] [ማቴ. 17፡13] እዚህ ሥፍራ ላይ መጥምቁ ዮሐንስ ከኤልያስ ጋር ተመሳስሏል፤ ቀደም ሲል ግን ኤልያስ ያለመሆኑን መግለጡ ይታወሳል (ዮሐ. 1፡21፤ በተጨማሪም የክፍል 26ን ማብራሪያ ይመልከቱ)። ስለ ኤልያስ የተነገረውን ትንቢት ዮሐንስ የፈጸመበትን ሁኔታ (ሚል. 4፡5-6) መረዳቱ ያስቸግራል። የትንቢቱ ፍጻሜ እስራኤላውያን ዮሐንስንና መሢሑን በመቀበላቸው ቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው (ማቴ. 11፡14-15፥ ክፍል 57)። ዮሐንስና መሢሑን አለመቀበላቸው ደግሞ የትንቢቱን መፈጸም ይሽረዋል (ማቴ. 17፡12፤ ማር. 9፡13)።

(ማቴዎስ 17:14-21 የቀጠለ)

17 ኢየሱስም መልሶ:-[17] የማታምን ጠማማ ትውልድ ሆይ፥ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ወደዚህ ወደ እኔ አምጡት አለ።

(ማርቆስ 9:14-29 የቀጠለ)

የማታምን ትውልድ ሆይ፥[17] እስከመቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ወደ እኔ አምጡት አላቸው።

20 ወደ እርሱም አመጡት። እርሱንም ባየ ጊዜ ያ መንፈስ ወዲያው አንፈራገጠው፤ ወደ ምድርም ወድቆ አረፋ እየደፈቀ ተንፈራፈረ።

21 አባቱንም:- ይህ ከያዘው ስንት ዘመን ነው? ብሎ ጠየቀው።

እርሱም:- ከሕፃንነቱ ጀምሮ ነው፤ 22 ብዙ ጊዜም ሊያጠፋው ወደ እሳትም ወደ ውኃም ጣለው፤ ቢቻልህ ግን እዘንልን እርዳንም አለው።

23 ኢየሱስም:- ቢቻልህ ትላለህ፤ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል አለው።

(ሉቃስ 9:37-43ሀ የቀጠለ)

41 ኢየሱስም መልሶ:-[17] እናንተ የማታምን ጠማማ ትውልድ፥ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ልጅህን ወደዚህ አምጣው አለ።

42 ሲቀርብም ጋኔኑ ጣለውና አንፈራገጠው፤ ኢየሱስ ግን ርኵሱን መንፈስ ገሥጾ ብላቴናውን ፈወሰው ለአባቱም መለሰው። 43ሀ ሁሉም ከእግዚአብሔር ታላቅነት የተነሣ ተገረሙ።

---

[17] [ማቴ. 17፡17፤ ማር. 9፡19፤ ሉቃስ 9፡41] ኢየሱስ የተቆጣበትና በዙሪያው በሚሆነው ነገር ትዕግሥት የማጣት ስሜት ያሳየበት ሁኔታ ይህ ብቻ ነው። ልጁ ታሞበት ወደ ኢየሱስ የመጣውን ሰው በተመለከተም፥ ሁኔታው ምናልባትም በሰውዬውና በሕግ መምህራን መካከል ግንኙነት የነበረ መሆኑን ያመለክታል (ማር. 9፡14)። እነዚህ ሰውዬውንና ልጁን በዘጠኙ ደቀ መዛሙርትና በኢየሱስ ላይ ለክስ የሚሆን ነገር መፈለጊያነት ያገለግሉ ዘንድ የተጠቀሙባቸው ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። የጌታ ጠላቶች ተቃርኖ እንደገና ተሳክቶ ይህ ግሳጼ ገጠመው። ይህን የመሰለው ጠንካራ ቃል ዘጠኙ ሐዋርያት እምነት ስላልነበራቸውና ተአምሩን ለመፈጸም ባለመቻላቸው የተሰነዘረ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ምንም እንኳን ጥቂት ቢሆን እምነት ነበራቸው (ማቴ. 17፡20)።

[18] [ማር. 9፡30] ኢየሱስ በዚህ ጊዜ ከፊልጶስ ቂሣርያ እና ከሰሜን ምሥራቅ ፍልስጥኤም በመነሣት ከስድስት ወራት በኋላ ሞቱና ትንሣኤው ወደሚፈጸምበት ወደ ይሁዳ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በገሊላና በፖርያ በኩል ተጓዘ።

[19] [ማቴ. 17፡25] ማቴዎስ ምንም እንኳን የቀድሞ ሥራው ለቤተ መቅደስ ሳይሆን ለሮም መንግሥት ቀረጥ መሰብሰብ የነበረ ቢሆን፥ ለዚህ ክፍል የተለየ ትኩረት ይሰጠዋል። በዚህ ጊዜ የተፈለገው ቀረጥ፥ ለቤተ መቅደስ ውስጥ አምልኮ መሥዋዕት ለማቅረቢያ ነው። መደበኛው የቀረጥ መክፈያ ጊዜ በልግ ሲሆን፥ አሁን ግን ጸደይ ነው። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በመደበኛው የቀረጥ መክፈያ ጊዜ በአካባቢው አልነበሩም። ቀረጥ ሰብሳቢዎቹ ያቀዱት በጊዜው ያልሰበሰቡትን ቀረጥ ለማሟያ ወይም ኢየሱስን የመክሰሻ ሌላ መንገድ ለመፈለጊያ ነው።

| (ማቴዎስ 17፡ 14-21 የቀጠለ) | (ማርቆስ 9፡ 14-29 የቀጠለ) |
|---|---|
| | 24 ወዲያውም የብላቴናው አባት ጮኾ፡- አምናለሁ፤ አለማመኔን እርዳው አለ። |
| 18 ኢየሱስም ገሠጻው ጋኔኑም ከእርሱ ወጣ፥ ብላቴናውም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰ። | 25 ኢየሱስም ሕዝቡ እንደ ገና ሲራወጥ አይቶ ርኵሱን መንፈስ ገሠጸና፡- አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ፥ እኔ አዝሃለሁ፥ ከእርሱ ውጣ እንግዲህም አትግባበት አለው። |
| | 26 ጮኾም እጅግም አንፈራግጦት ወጣ፤ ብዙዎችም፡- ሞተ እስኪሉ ድረስ እንደ ሙት ሆነ። 27 ኢየሱስ ግን እጁን ይዞ አስነሣው ቆመም። |
| 19 ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ ኢየሱስ ቀረቡና፡- እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምን ነው? አሉት። | 28 ወደ ቤትም ከገባ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ፡- እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምንድር ነው? ብለው ብቻውን ጠየቁት። |
| 20 ኢየሱስም፡- ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ፡- ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም። 21 ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው። | 29 ይህ ወገን በጸሎትና በጦም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም አላቸው። |

## ♦ ክፍል 88. የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለሁለተኛ ጊዜ በቅድሚያ መነገሩ [ክፍል 83፥ 85፥ 86ና 125ሀን ይመልከቱ]

- በገሊላ መዘዋወር -

| ማቴዎስ 17፡22-23 | ማርቆስ 9፡30-32 | ሉቃስ 9፡43ለ-45 |
|---|---|---|
| | 30-31 ከዚያም ወጥተው በገሊላ በኩል አለፉ፤[16] ደቀ መዛሙርቱንም ያስተምር ስለ ነበር ማንም ያውቅ ዘንድ አልወደደም፤ | 43ለ ሁሉም ኢየሱስ ባደረገው ሁሉ ሲደነቁ፥ 44 ለደቀ መዛሙርቱ፡- |

[20] [ማቴ. 18፡1፤ ማር. 9፡34፤ ሉቃስ 9፡46] ደቀ መዛሙርቱ ማዕረግና ቅደም ተከተል ሥርዓት ከሆነበት ባሕል ነው የወጡት። በመለወጥ ተራራ ላይ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ከኢየሱስ ጋር ለመሆን መምረጣቸው (ክፍል 85) እና ከእነሱም ዋናው ወይም የታወቀው ጴጥሮስ መሆኑ (ክፍል 82፤ 89)፥ በዚህ ጊዜ ለተደረገው እንዲህ ያለ ውይይት ዕድል ሰጠ። በዚህ ጊዜ "በመንግሥተ ሰማያት" ታላቅ የመሆን ጥያቄም የመጣ ሲሆን፥ ለዚህም ምክንያቱ ምናልባት የጉዟቸውን መጨረሻ ኢየሩሳሌም በማድረግ "መንግሥተ ሰማያት የመግባት የልብ ትርታቸው" በመጨመሩ ሳይሆን አልቀረም (ሉቃስ 19፡11፥ ክፍል 127ለ)። ኢየሱስ ለዚህም ሲመልስ፥ ትሕትና የታላቅነት መሠረት ብቻ ሳይሆን (ማቴ. 18፡4)፥ ወደ መንግሥቱ ለመግባት ቅድመ ሁኔታ መሆኑን አመልክቷል።

(ማቴዎስ 17:22-23 የቀጠለ)

22 በገሊላም ሲመላለሱ ኢየሱስ፡- የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጥ ዘንድ አለው፥ ይገድሉትማል፥ 23 በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው። እጅግም አዘኑ።

(ማርቆስ 9:30-32 የቀጠለ)

ለእነርሱም፡- የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጣል፥ ይገድሉትማል፥ ተገድሎም በሦስተኛው ቀን ይነሣል ይላቸው ነበር። 32 እነርሱም ነገሩን አላስተዋሉም፥ እንዳይጠይቁትም ፈሩ።

(ሉቃስ 9:43ለ-45 የቀጠለ)

የሰው ልጅ በሰው እጅ ይሰጥ ዘንድ አለውና እናንተ ይህን ቃል በጆሮአችሁ አኑሩ አለ። 45 እነርሱ ግን ይህን ነገር አላስተዋሉም፥ እንዳይገባቸውም ተሰውሮ ባቸው ነበር፤ ስለዚህ ነገርም እንዳይጠይቁት ፈሩ።

## ♦ ክፍል 89. የቤተ መቅደስ ግብር ክፍያ

- ቅፍርናሆም -

ማቴዎስ 17:24-27

24 ወደ ቅፍርናሆምም በመጡ ጊዜ ግብር የሚቀበሉ ሰዎች ወደ ጴጥሮስ ቀረቡና፡- መምህራችሁ ሁለቱን ዲናር አይገብርምን? አሉት። 25 አዎን ይገብራል አለ።

ወደ ቤትም በገባ ጊዜ ኢየሱስ አስቀድሞ፡- ስምዖን ሆይ፥ ምን ይመስልሃል? የምድር ነገሥታት ቀረጥና ግብር ከማን[19] ይቀበላሉ? ከልጆቻቸውን ወይስ ከእንግዶች? አለው።

26 ጴጥሮስም፡- ከእንግዶች ባለው ጊዜ ኢየሱስ፡- እንኪያስ ልጆቻቸው ነጻ ናቸው። 27 ነገር ግን እንዳናሰናክላቸው፥ ወደ ባሕር ሂድና መቃጥን ጣል፥ መጀመሪያም የሚወጣውን ዓሣ ውሰድና አፉን ስትከፍት እስታቴር ታገኛለህ፤ ያን ወስደህ ስለ እኔና ስለ አንተ ስጣቸው አለው።

## ♦ ክፍል 90. በመንግሥት ከሁሉ ስለሚበልጠው ሰው ማንነት የተነሣ ጥያቄና ፉክክር [ክፍል 123ና 145ን ይመልከቱ]

- ቅፍርናሆም -

ማቴዎስ 18:1-5

1 በዚያች ሰዓት ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፡-[20] በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን? አሉት።

ማርቆስ 9:33-37

33 ወደ ቅፍርናሆምም መጣ። በቤትም ሆኖ፡- በመንገድ እርስ በርሳችሁ ምን ተነጋገራችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። 34 እነርሱ ግን በመንገድ፡- ከሁሉ

ሉቃስ 9:46-48

46 ከእነርሱም ማን[20] እንዲበልጥ ክርክር ተነሣባቸው።

[21] [ማር. 9:39፤ ሉቃስ 9:49] ልክ ቀደም ሲል ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን እቅድ በተሣሣተ ሁኔታ እንደተረዳ ሁሉ (ክፍል 83)፥ ዮሐንስም በዚህ አሁን በተፈጠረ ሁኔታ ተሣሣተ። ዘግየት ብሎም ሦስተኛው የተከበረ ደቀ መዝሙር ያዕቆብ፥ ተመሳሳይ ድርጊት ይፈጽማል (125ለ)። እያንዳንዱ የተሣሣተ ግንዛቤ የመጣው ስለ ኢየሱስ ርኅራኄና ትንሣኤ ትንቢት ከተነገረ በኋላ ወዲያኑ ነው።

| (ማቴዎስ 18:1-5 የቀጠለ) | (ማርቆስ 9:33-37 የቀጠለ) | (ሉቃስ 9:46-48 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| | የሚበልጥ ማን ይሆን?[20] ተባብለው ነበርና ዝም አሉ። 35 ተቀምጦም አሥራ ሁለቱን ጠርቶ፦ ሰው ፊተኛ ሊሆን ቢወድ ከሁሉ በኋላ የሁሉም አገልጋይ ይሁን አላቸው። | |
| 2 ሕፃንም ጠርቶ በመካከላቸው አቆመ 3 እንዲህም አለ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም። 4 እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው። | 36 ሕፃንም ይዞ በመካከላቸው አቆመው አቅፎም፦ | 47 ኢየሱስም የልባቸውን አሳብ አውቆ ሕፃንን ያዘ፤ በአጠገቡም አቁሞ፦ |
| 5 እንደዚህም ያለውን አንድ ሕፃን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ | 37 እንደዚህ ካሉ ሕፃናት አንዱን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ የሚቀበለኝም ሁሉ የላከኝን እንጂ እኔን አይቀበልም አላቸው። | 48 ማንም ይህን ሕፃን በስሜ የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ የሚቀበለኝም ሁሉ የላከኝን ይቀበላል፤ ከሁላችሁ የሚያንስ እርሱ ታላቅ ነውና አላቸው። |

## ♦ ክፍል 91. አማኞችን ወደ ኃጢአት መገፋፋትን በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

[ክፍል 54ሐ፥ 54ሠ፥ 61፥ 70ለ፥ 106፥ 115፥ 116ና 117ሐን ይመልከቱ]

- ቅፍርናሆም -

| ማቴዎስ 18፡6-14 | ማርቆስ 9፡38-50 | ሉቃስ 9፡49-50 |
|---|---|---|
| | 38 ዮሐንስ መልሶ፦ መምህር ሆይ፥ አንድ ሰው በስምህ አጋንንትን ሲያወጣ አየነው፥ 39 ስለማይከተለንም ከለከልነው[21] አለው። | 49 ዮሐንስም መልሶ፦ አቤቱ፥ አንድ ሰው በስምህ አጋንንትን ሲያወጣ አየነው፥ ከእኛ ጋርም ስለማይከተል ከለከልነው[21] አለው። |

[22] [ማር. 9፡40] ይህ አባባል ማቴዎስ 12፡30 (ክፍል 61) ውስጥ ከተጠቀሰው ጋር የሚቃረን ይመስላል፤ በትክክል ሲታይ ግን ቃሉን ሙሉ ነው የሚያደርገው። ማቴዎስ 12፡30 ውስጥ ያለው ቃል የሚናገረው፥ የሰው ውስጣዊ ሕይወት ከኢየሱስ ጋር ስላለው ግንኙነት ነው፤ ማርቆስ 9፡40 ደግሞ ስለውጫዊ ባሕርይው ያመለክታል። በጠላትነት ያልተፈረጀ ሰው እንደወዳጅ ሊቆጠር ይችላል፤ በተለይም በዚህ የኢዮስያስን ስም የሚጠራውን በመሰለ ጉዳይ።

| (ማቴዎስ 18:6-14 የቀጠለ) | (ማርቆስ 9:38-50 የቀጠለ) | (ሉቃስ 9:49-50 የቀጠለ) |
| --- | --- | --- |
| | ኢየሱስ ግን አለ፦ በስሜ ተአምር ሠርቶ በቶሎ በእኔ ላይ ክፉ መናገር የሚችል ማንም የለምና አትከልክሉት፤ 40 የማይቃወመን[22] እርሱ ከእኛ ጋር ነውና። 41 የክርስቶስ ስለ ሆናችሁ በስሜ ጽዋ ውኃ የሚያጠጣችሁ ሁሉ፥ ዋጋው እንዳይጠፋበት እውነት እላችኋለሁ። | 50 ኢየሱስ ግን፦ የማይቃወማችሁ ከእናንተ ጋር ነውና አትከልክሉት አለው። |
| 6 በእኔም ከሚያምኑ ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ፥ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር። | 42 በእኔም ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለው ነበር። | |
| 7 ወዮ ለዓለም ስለ ማሰናከያ፤ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፥ ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት። 8 እጅህ[23] ወይም እግርህ[23] ብታሰናክልህ፥ ቈርጠህ ከአንተ ጣላት፤ ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘላለም እሳት ከምትጣል ይልቅ አንካሳ ወይም ጉንድሽ ሆነህ ወደ ህይወት መግባት ይሻልሀል። 9 ዓይንህ[23] ብታሰናክልህ አውጥተህ | 43-44 እጅህ[23] ብታሰናክልህ ቍረጣት፤ ሁለት እጅ ኖሮህ ትላቸው ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም ወደማይጠፋ እሳት ከመሄድ ጉንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻላል። 45-46 እግርህ[23] ብታሰናክልህ ቍረጣት፤ ሁለት እግር | |

---

23 [ማቴ. 18፥8-9፤ ማር. 9፥43፥ 45፥ 47] በጊዜው በነበረ ባሕል መሠረት አይሁዳውያን ኃጢአት የተሠራባቸውን የአካል ክፍሎች እንጂ ጥቃቅን የኃጢአት ድርጊቶችን አይመለከቱም ነበር። ስለዚህ ይህ የሚያመለክተው የራስን አካል ስለመቆራረጥ ሳይሆን፥ ሰውነትን የራስ ስሜት ማርኪያ ማድረግ የማይገባ መሆኑን ነው (ሮሜ 12፥1)።

24 [ማር. 9፥50] "የቃል ኪዳን ጨው" (ዘሌዋ. 2፥13) ይደረግ የነበረው፥ ለሚቀርበው መሥዋዕት ጥራትና በተገቢው እንዲጠበቅ ለማድረግ ሲባል ነው። ደቀ መዛሙርት ስለ ትልቅነት እርስ በርስ ከመጨቃጨቅ ንጹሕ እስከሆኑ ድረስ (ክፍል 90) ዓለምን ከፍርድ ይጠብቋታል። በምሳሌነት የቀረበው ጨው ከሙት ባሕር ይገኝ የነበረው ስለሆነና ለምግብነት በሚገባ የተዘጋጀ ስላልነበረ የጨውነት ጣዕሙን የሚያሳጡ ነገሮች ነበሩበት (ማቴ. 5፥13፥ ክፍል 54ሐ)።

(ማቴዎስ 18፡6-14 የቀጠለ)

ከአንተ ጣላት፤ ሁለት ዓይን ኖሮህ ወደ ገሃነመ እሳት ከምትጣል ይልቅ አንዲት ዓይን ኖራህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል።

10 ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና። 11 የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን መጥቶአልና።

12 ምን ይመስላችኋል? ለአንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት ከእነርሱም አንዱ ቢባዝን፥ ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ትቶ ሄዶም የባዘነውን አይፈልግምን? 13 ቢያገኘውም፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ካልባዘኑቱ ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በእርሱ ደስ ይለዋል። 14 እንደዚሁ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም።

(ማርቆስ 9፡38-50 የቀጠለ)

ኖሮህ ትላቸው ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም ወደማይጠፋ እሳት ከመጣል አንካሳ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል። 47-48 ዓይንህ[23] ብታሰናክልህ አውጣት፤ ሁለት ዓይን ኖሮህ

> "ትላቸው ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት" [ኢሳ. 66፡24]

ወደ ገሃነመ እሳት ከመጣል አንዲት ዓይን ኖራህ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ይሻልሃል።

49 ሰው ሁሉ በእሳት ይቀመማልና፥ መሥዋዕትም ሁሉ በጨው ይቀመማል።

50 ጨው[24] መልካም ነው፤ ጨው ግን አልጫ ቢሆን በምን ታጣፍጡታላችሁ? በነፍሳችሁ ጨው ይኑርባችሁ፥ እርስ በርሳችሁም ተስማሙ።

---

[25] [ማቴ. 18፡21] ጴጥሮስ በጣም ይቅር ባይ የሆነ መስሎት ነበር ሰባት ጊዜ ይቅር ማለት ይገባው እንደሆን የጠቀሰው። ምክንያቱም የሃይማኖት መምህራን አንድ ሰው ሦስት ጊዜ ይቅርታ እንዲያደርግ ነበር የሚጠይቁት። የኢየሱስ መልስ ለይቅርታ ገደብ የለውም የሚል ነው። ቁጥር 22ን በተመለከተ ግሪክኛው አገላለጥ ሰባ ጊዜ ሰባት ወይም ሰባ ሰባት ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ የሁለቱም ውጤት አንድ ነው። ይሄውም ይቅርታ ለማንኛውም ዓላማ ቢሆን እጅግ የበዛና ገደብ የለሽ መሆን አለበት።

[26] [ማቴ. 18፡28] ይቅርታው ገደብ የለሽ የሆነ ደቀ መዝሙር፥ ከአሥር ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚቆጠር ዕዳ ምሕረት ተደርጎለት 150 ብር ለተበደረው ባልንጀራው ምሕረትን እምቢ እንዳለው ባሪያ ነው (ቁ. 24)።

[27] [ማቴ. 8፡22፤ ሉቃስ 9፡60] ኢየሱስን ያናገረው ሰው የአባቱን የቀብር ሥርዓት ሊያከናውን ነው የፈለገው። አባቱ በቅርብ እርፎ ይሆናል። ወይም በባሕል ይታወቅ የነበረውን የ30 ቀናት የሀዘን ጊዜ ለማክበር ይሆናል። የደቀ መዛሙርትነቱ ጥሪ ግን እንደተሰጠ ወዲያው ተቀባይነት ማግኘት ወይም መቅረት ነበረበት። የአባቱን ሞት በተመለከተ፥ የቀብሩንም ሆነ የሀዘኑን ሥርዓት ሊያስፈጽሙ የሚችሉና በመንፈስ ሙታን የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉ።

## ♦ ክፍል 92. በደለኛ ወንድምን በይቅርታ ስለመቅረብ

- ቅፍርናሆም -

ማቴዎስ 18፥15-35

15 ወንድምህም ቢበድልህ፥ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው።
ቢሰማህ፥ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው፤ 16 ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት
ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ
[ዘዳግም 19፥15]፤ 17 እነርሱንም ባይሰማ፥ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ
ክርስቲያንን ባይሰማት፥ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ።

18 እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥
በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።

19 ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ
ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። 20 ሁለት ወይም ሦስት
በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።

21 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ
ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን?[25] አለው።

22 ኢየሱስ እንዲህ አለው፦ እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም።

23 ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቈጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመስላለች። 24
መቈጣጠርም በጀመረ ጊዜ፥ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ
አመጡ። 25 የሚከፍለውም ቢያጣ፥ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ
እንዲሸጥና ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ።

26 ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና፦ ጌታ ሆይ፥ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ
አለው። 27 የዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው፥ ዕዳውንም ተወለት።

28 ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን
አገኘና፦ ዕዳህን ክፈለኝ[26] ብሎ ያዘና አነቀው።

29 ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ፦ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ
ለመነው።

30 እርሱም አልወደደም፥ ግን ሄዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው። 31
ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፥ መጥተውም የሆነውን
ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ።

32 ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ፦ አንተ ክፉ ባሪያ፥ ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ
ተውሁልህ፤ 33 እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ
አይገባህምን? አለው። 34 ጌታውም ተቈጣና ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ
ለሚሣቅዩት አሳልፎ ሰጠው።

35 ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ
ያደርግባችኋል።

# > የዳስ በዓልን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የተደረገ ጉዞ <

## ♦ ክፍል 93. ከተከታዮች ፍጹም የሆነ መሰጠት ተጠየቀ

- በመንገዱ ላይ -

ማቴዎስ 8፡19-22

19 አንድ ጻፊም ቀርቦ፡- መምህር ሆይ፥ ወደምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ አለው።

20 ኢየሱስም፡- ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው።

21 ከደቀ መዛሙርቱም ሌላው፡- ጌታ ሆይ፥ አስቀድሜ እንድሄድ አባቴን እንድቀብር ፍቀድልኝ አለው።

22 ኢየሱስም፡- ተከተለኝ፥ ሙታናቸውንም እንዲቀብሩ[27] ሙታንን ተዋቸው አለው።

ሉቃስ 9፡57-62

57 እነርሱም በመንገድ ሲሄዱ አንድ ሰው፡- ጌታ ሆይ፥ ወደ ምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ አለው።

58 ኢየሱስም፡- ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው።

59 ሌላውንም፡- ተከተለኝ አለው።

እርሱ ግን፡- ጌታ ሆይ፥ አስቀድሜ ልሂድና አባቴን እቀብር ዘንድ ፍቀድልኝ አለ።

60 ኢየሱስም፡- ሙታናቸውን እንዲቀብሩ[27] ሙታንን ተዋቸው፤ አንተስ ሄደህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስበክ አለው።

61 ደግሞ ሌላው፡- ጌታ ሆይ፥ እከተልሃለሁ፤ ነገር ግን አስቀድሜ ከቤቴ ሰዎች እንድሰናበት ፍቀድልኝ አለ።

62 ኢየሱስ ግን፡- ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም አለው።

## ♦ ክፍል 94. የኢየሱስ የሥጋ ወንድሞች ስላቅ

- ገሊላ -

ዮሐንስ 7፡2-9

2 የአይሁድም የዳስ በዓል ቀርቦ ነበር። 3 እንግዲህ ወንድሞቹ፡- ደቀ መዛሙርትህ
ደግሞ የምታደርገውን ሥራ እንዲያዩ ከዚህ ተነሣና ወደ ይሁዳ ሂድ፤ 4 ራሱ ሊገለጥ
እየፈለገ በስውር የሚሠራ የለምና። እነዚህን ብታደርግ ራስህን ለዓለም ግለጥ[28]
አሉት። 5 ወንድሞቹ ስንኳ አላመኑበትም ነበርና።

(ዮሐንስ 7፡2-9 የቀጠለ)

6 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡- ጊዜዬ ገና አልደረሰም፥ ጊዜያችሁ ግን ዘወትር
የተመቸ ነው። 7 ዓለም እናንተን ሊጠላ አይቻለውም፤ እኔ ግን ሥራው ክፉ መሆኑን
እመሰክርበታለሁና እኔን ይጠላኛል። 8 እናንተ ወደዚህ በዓል ውጡ፤ እኔስ ጊዜዬ ገና
ስላልተፈጸመ ወደዚህ በዓል ገና አልወጣም። 9 ይህንም አላቸውና በገሊላ ቀረ።

## ♦ ክፍል 95. በሰማሪያ ምድር የተደረገ ጉዞ

- የኢየሩሳሌም ጉዞ መጀመር -

ሉቃስ 9፡51-56

51 የሚወጣበትም ወራት በቀረበ ጊዜ
ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና፥ 52
በፊቱም መልክተኞችን ሰደደ። ሄደውም
ሊያሰናዱለት ወደ አንድ ወደ ሳምራውያን
መንደር ገቡ፤ 53 ፊቱም ወደ
ኢየሩሳሌም[29] እንደሚሄድ ስለ ነበረ
አልተቀበሉትም። 54 ደቀ መዛሙርቱም
ያዕቆብና ዮሐንስ አይተው፡- ጌታ ሆይ፥
ኤልያስ ደግሞ እንዳደረገ እሳት ከሰማይ
ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን?
አሉት። 55 እርሱ ግን ዘወር ብሎ
ገሠጻቸውና፡- ምን ዓይነት መንፈስ እንደ
ሆነላችሁ አታውቁም፤ 56 የሰው ልጅ
የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ
አልመጣም አለ። ወደ ሌላ መንደርም
ሄዱ።

ዮሐንስ 7፡10

10 ወንድሞቹ ግን ወደ በዓሉ ከወጡ
በኋላ በዚያን ጊዜ እርሱ ደግሞ በግልጥ
ሳይሆን ተሰውሮ ወጣ።

---

28 [ዮሐ. 7፡4] የጌታ ወንድሞች ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ውስጥ ሊደረግ ባለው የዳስ በዓል ላይ በድንገት ራሱን እንዲገልጥ ገፋፉት። እምነት የለሽ ከሆነ አቋማቸው በመነሣት መሢሐዊ በሆነ ሁኔታ ራሱን እንዲገልጥ ነው የጠየቁት። ይህ ጥያቄያቸው በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ጊዜውን ያልጠበቀ ድርጊት እንዲከናወን ነበር (ቁ.8)።

29 [ሉቃስ 9፡53] ለአምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዱ ገሪዛን ተራራ ላይ ያለውን የሳምራውያን ቤተ መቅደስ አለመቀበሉን ነው የሚያመለክተው። ዮሐንስና ያዕቆብ በሳምራውያንና በነርሱ መካከል ለነበረው ጠላትነት አጸፋ ይሆን ዘንድ በቅርቡ እንዳዩት እንደ ኤልያስ (ክፍል 85) ተአምር ለመሥራትና አንቀበላቸው ያሉ ጠላቶቻቸውን ሊያጠፏቸው ፈለጉ (ሉቃስ 9፡54፤ 2ኛ ነገሥ. 1፡10፥ 12)። ሁለቱ "የነጎድጓድ ልጆች" ይህን የሳምራውያን እምቢታ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ምናልባት ይህን የኢየሩሳሌም ጉዞ አስመልክቶ ስለሚገጥመው ተቃውሞ የተነበየው አድርገው ቆጥረውት ይሆናል።

# 8

# ኢየሱስ ይሁዳ ውስጥ ያደረገው የኋላ አገልግሎቱ

## > በዳስ በዓል የተጀመረው አገልግሎት <

### ♦ ክፍል 96ሀ. የኢየሱስን አስተምህሮና ተአምራት በተመለከተ የተከሰቱ ልዩ ልዩ አጸፋዎች

- ኢየሩሳሌም፡- በመቅደሱ ውስጥ -

<u>ዮሐንስ 7፡ 11-31</u>

11 አይሁድም፡- እርሱ ወዴት ነው? እያሉ በበዓሉ[30] ይፈልጉት ነበር።

12 በሕዝብም መካከል ስለ እርሱ ብዙ ማንጐራጐር ነበረ፤ አንዳንዱም፡- ደግ ሰው
ነው፤

ሌሎች ግን፡- አይደለም፥ ሕዝቡን ግን ያስታል ይሉ ነበር። 13 ዳሩ ግን አይሁድን[31]
ስለ ፈሩ ማንም ስለ እርሱ በግልጥ አይናገርም ነበር።

14 አሁንም በበዓሉ እኩሌታ ኢየሱስ ወደ መቅደስ ወጥቶ ያስተምር ነበር። 15
አይሁድም፡- ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል?[32] ብለው ይደነቁ
ነበር።

16 ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፡- ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ
አይደለም፤ 17 ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት
ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል። 18 ከራሱ የሚናገር
የራሱን ክብር ይፈልጋል፤ የላከውን ክብር የሚፈልግ ግን እርሱ እውነተኛ ነው
በእርሱም ዓመፃ የለበትም። 19 ሙሴ ሕግን አልሰጣችሁምን? ከእናንተ ግን ሕግን
የሚያደርግ አንድ ስንኳ የለም። ልትገድሉኝ ስለ ምን ትፈልጋላችሁ?

---

[30] [ዮሐ. 7፡11] ይህ የዳስ በዓል የሚባለው ነው። በዚህ ጊዜ ነው ብርቱ ተቃዋሚዎቹ ወዳሉባት ኢየሩሳሌም የተመለሰው። የተጠበቀው ውጤት፥ ጊዜው ተጀምሮ እስኪያበቃ ድረስ የቆየው ከባድ ውዝግብ ነበር። የመቅደስ መታደስ በዓል የዚህን የሦስት ወራት ጊዜ መፈጸም ያመለክታል (ዮሐ. 10፡22፥ ክፍል 111)። በዚህ ጊዜ አወዛጋቢ ስለነበረው ጉዳይ አንድ ውሳኔ ላይ ተደርሶ ነበር። የቀረ ነገር ቢኖር መሚሑን ከሕዝቡ ለመለየት ውሳኔውን መፈጸም ነው።

[31] [ዮሐ. 7፡13] በዮሐ. 7-8 (ክፍል 96ሀ-99ለ) ውስጥ በኢየሱስ ጠላትነት የተሰባሰቡት "አይሁድ" (7፡11፥ 13፥ 15፥ 35፤ 8፡22፥ 48፥ 52፥ 57)፥ "ፈሪሳውያን" (7፡32፥ 47፤ 8፡13) እንዲሁም "የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን" (7፡32፥ 45) ነበሩ። ኢየሱስን የተቀበሉና ወደ መቀበሉ ያዘነበሉ "ሕዝብ" (7፡12፥ 20፥ 31-32፥ 40-41፥ 43፥ 49)፥ "ኒቆዲሞስ" (7፡50)፥ እና ብዙዎች "በእርሱ ያመኑ" (8፡30) ይባላሉ። ኢየሱስን ለመቀበል ገና እርግጠኛ ያልሆኑት "ሕዝቦች" (7፡12-13)፥ "የኢየሩሳሌም ሕዝብ" (7፡25)፥ "የቤተ መቅደስ ሎሌዎች" (7፡32፥ 45)፥ እና "ያመኑት አይሁዳውያን" (8፡31) ናቸው። ፈጣን በሆነው የታሪክ እንቅስቃሴ የተከሰቱት ልዩ ልዩ አጸፋዎች ወይም ምላሾች የሚከተሉት ናቸው፡- ግልጥ ያልሆኑ ጥያቄዎች (7፡11)፥ ክርክሮች (7፡12፥ 40-43)፥ ፍርሃት (7፡13፥ 30፥ 44)፥ መደነቅ (7፡15፥ 46)፥ ግራ መጋባት (7፡ 25-27)፥ ቅን እምነት (7፡31፤ 8፡30)፥ ግልጥ ጥላቻ (7፡32)፥ ተገቢ ያልሆነ ወቀሳ (7፡23-27፤ 8፡48-53) እና ትምክህተኝነት (8፡33-44)።

(ዮሐንስ 7፡ 11-31 የቀጠለ)

20 ሕዝቡ መለሱና፡- ጋኔን አለብህ፤ ማን ሊገድልህ ይፈልጋል? አሉት።

21 ኢየሱስ መለሰ አላቸውም፡- አንድ ሥራ አደረግሁ ሁላችሁም ታደንቃላችሁ። 22
ስለዚህ ሙሴ መገረዝን ሰጣችሁ፤ ከአባቶችም ነው እንጂ ከሙሴ አይደለም፤
በሰንበትም ሰውን ትገርዛላችሁ። 23 የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ሰው በሰንበት መገረዝን
የሚቀበል ከሆነስ ሰውን ሁለንተናውን በሰንበት ጤናማ ስላደረግሁ ትቈጡኛላችሁን?
24 ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ።

25 እንግዲህ ከኢየሩሳሌም ሰዎች አንዳንዶቹ እንዲህ አሉ፡- ሊገድሉት የሚፈልጉት
ይህ አይደለምን? 26 እነሆም፥ በግልጥ ይናገራል አንዳችም አይሉትም። አለቆቹ ይህ
ሰው በእውነት ክርስቶስ እንደ ሆነ በእውነት አወቁን? 27 ነገር ግን ይህን ከወዴት እንደ
ሆነ አውቀናል፤ ክርስቶስ ሲመጣ ግን ከወዴት እንደ ሆነ ማንም አያውቅም።

28 እንግዲህ ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር፡- እኔንም ታውቁኛላችሁ ከወዴትም
እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፤ እኔም በራሴ አልመጣሁም ነገር ግን እናንተ የማታውቁት
የላከኝ እውነተኛ ነው፤ 29 እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ነኝ እርሱም ልኮኛልና አውቀዋለሁ
ብሎ ጮኸ።

30 ስለዚህ ሊይዙት ይፈልጉ ነበር፤ ነገር ግን ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን
አልጫነበትም። 31 ከሕዝቡ ግን ብዙዎች አመኑበትና፡- ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ይህ
ካደረጋቸው ምልክቶች ይልቅ ያደርጋልን? አሉ።

## ♦ ክፍል 96ለ. ኢየሱስን ለመያዝ የተደረገው ሙከራ መክሸፉ

- ኢየሩሳሌም -

ዮሐንስ 7፡ 32-52

32 ፈሪሳውያንም ሕዝቡ ስለ እርሱ እንደዚህ ሲያንጐራጕሩ ሰሙ፤ የካህናት
አለቆችም ፈሪሳውያም ሊይዙት ሎሌዎችን ላኩ።

33 ኢየሱስም፡- ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር እቆያለሁ ወደ ላከኝም እሄዳለሁ። 34
ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝምም፤ እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አለ።

35 እንግዲህ አይሁድ፡- እኛ እንዳናገኘው ይህ ወዴት ይሄድ ዘንድ አለው? በግሪክ
ሰዎች መካከል ተበትነው ወደሚኖሩት ሊሄድና የግሪክን ሰዎች ሊያስተምር አለውን?
36 እርሱ፡- ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝምም እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ
አትችሉም የሚለው ይህ ቃል ምንድር ነው? ብለው እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ።

37 ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ፡- ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ
ይምጣና ይጠጣ።[33] 38 በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ

[32] [ዮሐ. 7፡ 15] በውይይቱ ጎልተው የነበሩት ሁለት ጉዳዮች ናቸው። እነርሱም የኢየሱስ ሥልጣን ምንጭ ምክንያትና (7፡ 15-24)፥ ራሱን መሢሕ ነኝ ማለቱ (7፡ 25-31) ናቸው።

[33] [ዮሐ. 7፡ 37] እስራኤላውያን ከግብጽ ከወጡ በኋላ በምድረበዳ በተአምር ውኃ መጠጣታቸውን ለማስታወስ በየዕለቱ የውኃ መሥዋዕት ማቅረባቸው የዳሱ በዓል አንድ አካል ነው። በተጨማሪም ነቢያት ስለ እስራኤል ወዳዩትና ወደፊት ለእስራኤል ስለሚሆነው በረከት ያመለክታል (ሕዝ. 47፡ 1፥ 12፤ ኢዩ. 3፡ 18)። ኢየሱስ ይህን ተስፋ ለመፈጸም ያለውን ችሎታ ነው የገለጠው። የዮሐንስ 7፡ 39 ፍቺም ኢየሱስ ከከበረ በኋላ ስለሚመጣው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው የሚያመለክተው።

(ዮሐንስ 7፡32-52 የቀጠለ)

ይፈልቃል ብሎ ጮኸ። 39 ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ
መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።

40 ስለዚህ ከሕዝቡ አያሌ ሰዎች ይህን ቃል ሲሰሙ፡- ይህ በእውነት ነቢዩ ነው አሉ፤

41 ሌሎች፡- ይህ ክርስቶስ ነው አሉ፤

ሌሎች ግን፡- ክርስቶስ በእውኑ ከገሊላ ይመጣልን? 42 ክርስቶስ ከዳዊት ዘር
ዳዊትም ከነበረባት መንደር ከቤተ ልሔም እንዲመጣ መጽሐፍ አላለምን? አሉ። 43
እንግዲህ ከእርሱ የተነሣ በሕዝቡ መካከል መለያየት ሆነ፤ 44 ከእነርሱም አንዳንዶቹ
ሊይዙት ወደዱ ነገር ግን እጁን ማንም አልጫነበትም።

45 ሎሌዎቹም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ፈሪሳውያን መጡ፤ እነዚያም፡-
ያላመጣችሁት ስለ ምን ነው? አሉአቸው።

46 ሎሌዎቹ፡- እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም ብለው መለሱ።

47 እንግዲህ ፈሪሳውያን፡- እናንተ ደግሞ ሳታችሁን? 48 ከአለቆች ወይስ
ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመነ አለን? 49 ነገር ግን ሕግን የማያውቀው ይህ ሕዝብ ርጉም
ነው ብለው መለሱላቸው።

50 ከእነርሱ አንዱ በሌሊት ቀድሞ ወደ እርሱ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ፡- 51 ሕጋችን
አስቀድሞ ከእርሱ ሳይሰማ ምንስ እንዳደረገ ሳያውቅ በሰው ይፈርዳልን? አላቸው።

52 እነርሱም መለሱና፡- አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን? ነቢይ ከገሊላ እንዳይነሣ
መርምርና እይ አሉት።

## ♦ ክፍል 97. በአመንዝራ ለተያዘችው ሴት የኢየሱስ ይቅርታ

- ኢየሩሳሌም፡- በመቅደሱ ውስጥ -

ዮሐንስ 7፡53-8፡11

53 እያንዳንዱም ወደ ቤቱ ሄደ።

1 ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ። 2 ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ ሕዝቡም
ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። ተቀምጦም ያስተምራቸው ነበር። 3 ጻፎችና ፈሪሳውያንም
በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ በመካከልም እርሱዋን አቁመው፡- 4
መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች። 5 ሙሴም እንደነዚህ ያሉት
እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት። 6 የሚከሱበትንም
እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ።

ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፤ 7 መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን
ቀና ብሎ፡- ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው። 8
ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ።

9 እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ
ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ፤ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ ሴቲቱም በመካከል ቆማ
ነበረች። 10 ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ፡- አንቺ ሴት፥
እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት።

11 እርስዋም፡- ጌታ ሆይ፥ አንድ ስንኳ አለች።

ኢየሱስም፡- እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት
አትሥሪ አላት።

## ♦ ክፍል 98. ኢየሱስ የዓለም ብርሃን ነኝ በማለቱ የተፈጠረ ግጭት

- ኢየሩሳሌም፦ በመቅደሱ ውስጥ -

ዮሐንስ 8፡12-20

12 ደግሞም ኢየሱስ፦ እኔ የዓለም ብርሃን[34] ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን
ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።

13 ፈሪሳውያንም፦ አንተ ስለ ራስህ ትመሰክራለህ፤ ምስክርነትህ እውነት አይደለም
አሉት።

14 ኢየሱስ መለሰ አላቸውም፦ እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት
እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምስክርነቴ እውነት ነው፤ እናንተ ግን
ከወዴት እንደ መጣሁ ወዴትም እንድሄድ አታውቁም። 15 እናንተ ሥጋዊ ፍርድን
ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በአንድ ሰው ስንኳ አልፈርድም። 16 የላከኝ አብ ከእኔ ጋር ነው
እንጂ ብቻዬን አይደለሁምና እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው። 17 የሁለት ሰዎችም
ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ በሕጋችሁ ተጽፎአል። 18 ስለ ራሴ የምመሰክር እኔ ነኝ፥
የላከኝም አብ ስለ እኔ ይመሰክራል።

19 እንግዲህ፦ አባትህ ወዴት ነው? አሉት።

ኢየሱስ መልሶ፦ እኔንም ወይም አባቴንም አታውቁም፤ እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን
ደግሞ ባወቃችሁ ነበር አላቸው። 20 ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር በግምጃ ቤት
አጠገብ[35] ይህን ነገር ተናገረ፤ ጊዜው ገና አልደረሰምና ማንም አልያዘውም።

## ♦ ክፍል 99ሀ. ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለው ግንኙነት

- ኢየሩሳሌም፦ በመቅደሱ ውስጥ -

ዮሐንስ 8፡21-30

21 ኢየሱስም ደግሞ፦ እኔ እሄዳለሁ ትፈልጉኛላችሁም በኃጢአታችሁም
ትሞታላችሁ እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አላቸው።

22 አይሁድም፦ እኔ ወደ ምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም ማለቱ ራሱን
ይገድላልን? እንጃ አሉ።

23 እናንተ ከታች ናችሁ፥ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፥ እኔ ከዚህ
ዓለም አይደለሁም። 24 እንግዲህ፦ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ፤ እኔ
እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና አላቸው።

25 እንግዲህ፦ አንተ ማን ነህ? አሉት።

ኢየሱስም፦ ከመጀመሪያ ለእናንተ የተናገርሁት ነኝ። 26 ስለ እናንተ የምናገረው
የምፈርደውም ብዙ ነገር አለኝ፤ ዳሩ ግን የላከኝ እውነተኛ ነው እኔም ከእርሱ

---

34 [ዮሐ. 8፡12] አንዳንድ ሰዎች "ብርሃን" የሚለው ቃል ትኩረትን በምድረበዳ ወደነበረው የእሳት አምድ ስቧል ይላሉ። ምንም እንኳን ይህ ግምት በተዘዋዋሪ ሊሆን ቢችል፥ የተሻለው ግንዛቤ ግን በዳስ በዓል የመጀመሪያ ምሽት የሚበራውን ወርቅማ መቅረዝ የሚጠቁም መሆኑን መረዳቱ ይሆናል። የዚህ ብርሃን መታሰቢያነት እስራኤላውያንን በምድረ በዳ ጉዟቸው የመራቸው ብርሃን ነበር።

35 [ዮሐ. 8፡20] "በግምጃ ቤት አጠገብ" የተባለው ሥፍራ አሥራ ሦስት የስጦታ ሳጥኖች ያሉበትና የሴቶች መቆሚያ በመባል የሚታወቀውን ያመለክታል (ማር. 12፡41፥ 43፤ ሉቃስ 21፡1፥ ክፍል 138)። ይህ ወንዶችም ሴቶችም የሚቆሙበት ሥፍራ ሲሆን እዚያ ለማስተማር ይፈቀዳል። የሚገርመው ኢየሱስን ለማስወገድ ተነሥቶ የነበረው የአይሁድ ዋና ሸንጎ የሚሰበሰበው ከዚህ ሥፍራ ቀጥሎ መሆኑ ነበር።

(ዮሐንስ 8፡21-30 የቀጠለ)

የሰማሁትን ይህን ለዓለም እናገራለሁ አላቸው።

27 ስለ አብ እንደ ነገራቸው አላስተዋሉም። 28 ስለዚህም ኢየሱስ፦ የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ እኔ እሆን ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ። 29 የላከኝም ከእኔ ጋር ነው፤ እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና አብ ብቻዬን አይተወኝም አላቸው። 30 ይህን ሲናገር ብዙዎች በእርሱ አመኑ።

## ♦ ክፍል 99ለ. የኢየሱስ ከአብርሃም ጋር ያለው ግንኙነትና ይህን በመግለጡ የተቃጣበት የድንጋይ ወገራ

- ኢየሩሳሌም፦ በመቅደሱ ውስጥ -

ዮሐንስ 8፡31-59

31 ኢየሱስም ያመኑትን[36] አይሁድ፦ እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ 32 እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።

33 እነርሱም መልሰው፦[37] የአብርሃም ዘር ነን ለአንድም ስንኳ ከቶ ባሪያዎች አልሆንም፤ አንተ፦ አርነት ትወጣላችሁ እንዴት ትላለህ? አሉት።

34 ኢየሱስ መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባርያ ነው። 35 ባርያም ለዘላለም በቤት አይኖርም፤ ልጁ ለዘላለም ይኖራል። 36 እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ። 37 የአብርሃም ዘር መሆናችሁንስ አውቃለሁ ነገር ግን ቃሌ በእናንተ አይኖርምና ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ። 38 እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ፤ እናንተም ደግሞ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ።

39 መልሰውም፦ አባታችንስ አብርሃም ነው አሉት።

ኢየሱስም፦ የአብሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር። 40 ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ፤ አብርሃም እንዲህ አላደረገም። 41 እናንተ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ አላቸው።

እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም አንድ አባት አለን እርሱም እግዚአብሔር ነው አሉት።

42 ኢየሱስም አላቸው፦ እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና። 43

---

[36] [ዮሐ. 8፡31] የግሪክኛው አጻጻፍ ኪዳን እነዚህን ሰዎች ዮሐ. 8፡30 ውስጥ ከተጠቀሱት እውነተኛ አማኞች የሚለይ ሆኖ ነው የቀረበው። "አመኑት" የሚለው ቃል "በእርሱ አመኑ" የሚለውን ያህል ከልብ ኢየሱስን መቀበልን አያመለክትም። በዚህ ክፍል የተገለጡት ቃላት ያነጣጠሩት የኢየሱስ ክርስቶስ መሢሕነት እውነት ለሚገባቸው፥ ነገር ግን ይህ እውነት የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር ለመፈጸም ፈቃደኞች ባልሆኑት ላይ ነው።

[37] [ዮሐ. 8፡33] ኢየሱስንና ትምህርቱን አስመልክቶ ከታዩት የአይሁድ ሃይማኖት የጠላትነት ብዙ መግለጫዎች ይህ የመጀመሪያው ነው። አይሁዳውያን እዚህ ላይ የሚገልጡት፥ በቃሉ ቢኖሩ ስለሚሰጣቸው ነጻነት ኢየሱስ የተናገረውን ተስፋ በመቃረን በአብርሃም በኩል ስለሚወርሱት ነጻነት ነው። ሌሎች የሚሏቸው ነገሮችና ክሶቻቸው የሚገኙባቸው ቁጥሮች 39፥ 41፥ 48፥ 53፥ 57 ናቸው።

(ዮሐንስ 8፡31-59 የቀጠለ)

ንግግሬን የማታስተውሉ ስለ ምንድር ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው። 44
እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ
ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ
በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት
ነውና። 45 እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለ ሆንሁ አታምኑኝም። 46 ከእናንተ ስለ
ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው? እውነት የምናገር ከሆንሁ እናንተ ስለ ምን
አታምኑኝም? 47 ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ እናንተ
ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና ስለዚህ አትሰሙም።

48 አይሁድ መልሰው፦ ሳምራዊ እንደ ሆንህ ጋኔንም እንዳለብህ በማለታችን እኛ
መልካም እንል የለምን? አሉት።

49 ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፦ እኔስ ጋኔን የለብኝም ነገር ግን አባቴን
አከብራለሁ እናንተም ታዋርዱኛላችሁ። 50 እኔ ግን የራሴን ክብር አልፈልግም፤
የሚፈልግ የሚፈርድም አለ። 51 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚጠብቅ
ቢኖር ለዘላለም ሞትን አያይም።

52 አይሁድ፦ ጋኔን እንዳለብህ አሁን አወቅን። አብርሃም ሰንኳ ሞተ ነቢያትም፤
አንተም፦ ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አይቀምስም ትላለህ። 53 በእውኑ
አንተ ከሞተው ከአባታችን ከአብርሃም ትበልጣለህን? ነቢያትም ሞቱ፤ ራስህን ማንን
ታደርጋለህ? አሉት።

54 ኢየሱስም መለሰ አለም፦ እኔ ራሴን ባከብር ክብሬ ከንቱ ነው፤ የሚያከብረኝ
እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው፤ 55 አላወቃችሁትምም፥ እኔ ግን
አውቀዋለሁ። አላውቀውም ብል እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆንሁ፤ ዳሩ ግን አውቀዋለሁ
ቃሉንም እጠብቃለሁ። 56 አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፥
አየም ደስም አለው።

57 አይሁድም፦ ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት።

58 ኢየሱስም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ
አላቸው። 59 ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው
ከመቅደስም ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ።

## ♦ ክፍል 100ሀ. ዓይነ ሥውር ሆኖ የተወለደው ሰው መፈወስ

- ኢየሩሳሌም -

ዮሐንስ 9፡1-7

1 ሲያልፍም ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ። 2 ደቀ መዛሙርቱም፦
መምህር ሆይ፥ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ
ወይስ ወላጆቹ? ብለው ጠየቁት።

3 ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ፦ የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው
እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሠሩም። 4 ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ
ይገባኛል፤ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች። 5 በዓለም ሳለሁ የዓለም
ብርሃን ነኝ።

6 ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን
ዓይኖች ቀባና፦ 7 ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው፤ ትርጓሜው የተላከ
ነው። ስለዚህ ሄዶ ታጠበ እያየም መጣ።

## ♦ ክፍል 100ለ. የዓይነ ሥውሩ ሰውዬ ጎረቤቶች አጸፋ (አስተያየት)

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 9፡8-12</u>

8 ጐረቤቶቹም ቀድሞም ሲለምን አይተውት የነበሩ፡- ይህ ተቀምጦ ይለምን የነበረ አይደለምን? አሉ። 9 ሌሎች፡- እርሱ ነው አሉ፤

ሌሎች፡- አይደለም እርሱን ይመስላል እንጂ አሉ፤

እርሱ፡- እኔ ነኝ አለ።

10 ታድያ፡- ዓይኖችህ እንዴት ተከፈቱ? አሉት።

11 እርሱ መልሶ፡- ኢየሱስ የሚባለው ሰው[38] ጭቃ አድርጎ አይኖቼን ቀባና፡- ወደ ሰሊሆም መጠመቂያ ሄደህ ታጠብ አለኝ፤ ሄጄ ታጥቤም አየሁ አለ።

12 ያ ሰው ወዴት ነው? አሉት።

አላውቅም አለ።

## ♦ ክፍል 100ሐ. የዓይነ ሥውሩ በፈሪሳውያን መመርመርና መወገድ [ክፍል 49ሀ-51፥ 110ና 114ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 9፡13-34</u>

13 በፊት ዕውር የነበረውን ሰው ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት። 14 ኢየሱስም ጭቃ አድርጎ ዓይኖቹን የከፈተበት ቀን ሰንበት ነበረ። 15 ስለዚህ ፈሪሳውያን ደግሞ እንዴት እንዳየ እንደ ገና ጠየቁት። እርሱም፡- ጭቃ በዓይኖቼ አኖረ ታጠብሁም አያለሁም አላቸው።

16 ከፈሪሳውያንም አንዳንዶቹ፡-[39] ይህ ሰው ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚአብሔር አይደለም አሉ።

ሌሎች ግን፡- ኃጢአተኛ ሰው እንደነዚህ ያሉ ምልክቶች ሊያደርግ እንዴት ይችላል? አሉ።

17 በመካከላቸውም መለያየት ሆነ። ከዚህም የተነሣ ዕውሩን፡- አንተ ዓይኖችህን ስለ ከፈተ ስለ እርሱ ምን ትላለህ? ደግሞ አሉት።

እርሱም፡- ነቢይ ነው አለ።

---

38 [ዮሐ. 9፡11] የተፈወሰው ዓይነሥውር በዚህ ደረጃ ስለ ኢየሱስ ማንነት የተረዳው ጥቂት ነው። ሁኔታዎች እየተገለጡ ሲሄዱ ግን እርሱን የማመስገኑ ጉዳይ በፍጥነት ያድጋል። ቁጥር 17 (ክፍል 100ሐ) ውስጥ እርሱ ነቢይ ነው ይላል። ቁጥር 27-28 (ክፍል 100ሐ) ውስጥ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ይሆናል። ቁጥር 31 (ክፍል 100ሐ) ውስጥ የእግዚአብሔር ሰው ይለዋል። ቁጥር 33 (ክፍል 100ሐ) ውስጥ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መሆኑን ያምናል። ቁጥር 35 እና 38 ውስጥ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ልጅ ይቀበለዋል።

39 [ዮሐ. 9፡16] ፈሪሳውያን የነበራቸው እምነት እየቀነሰ መሄዱ ግልጥ ሆነ። ቁጥር 16 ውስጥ ተሰሚ የሆነው ቡድናቸው ኢየሱስን ከእግዚአብሔር አይደለም አለ። ቁጥር 18 ውስጥ ተአምራቱን ይጠራጠራሉ። ቁጥር 24 ውስጥ ኃጢአተኛ ይሉታል። ቁጥር 29 ውስጥ ስለ እርሱ ምንም አለማወቃቸውን ያምናሉ። ቁጥር 41 ውስጥ (ክፍል 100ሠ)፥ ዓይነሥውራን ኃጢአተኞች ተብለዋል።

(ዮሐንስ 9፡ 13-34 የቀጠለ)

18 አይሁድ የዚያን ያየውን ወላጆች እስኪጠሩ ድረስ ዕውር እንደ ነበረ እንዳየም ስለ
እርሱ አላመኑም፥ 19 እነርሱንም፦ እናንተ ዕውር ሆኖ ተወለደ የምትሉት ልጃችሁ
ይህ ነውን? ታድያ አሁን እንዴት ያያል? ብለው ጠየቁአቸው።

20 ወላጆቹም መልሰው፦ ይህ ልጃችን እንደ ሆነ ዕውርም ሆኖ እንደ ተወለደ
እናውቃለን፤ 21 ዳሩ ግን አሁን እንዴት እንዳየ አናውቅም፥ ወይም ዓይኖቹን ማን
እንደ ከፈተ እኛ አናውቅም፤ ጠይቁት እርሱ ሙሉ ሰው ነው፤ እርሱ ስለ ራሱ
ይናገራል አሉ። 22 ወላጆቹ አይሁድን ስለ ፈሩ ይህን አሉ፤ እርሱ ክርስቶስ ነው ብሎ
የሚመሰክር ቢኖር ከምኵራብ እንዲያወጡት[40] አይሁድ ከዚህ በፊት ተስማምተው
ነበርና። 23 ስለዚህ ወላጆቹ፦ ሙሉ ሰው ነው፥ ጠይቁት አሉ።

24 ስለዚህ ዕውር የነበረውን ሰው ሁለተኛ ጠርተው፦ እግዚአብሔርን አክብር፤ ይህ
ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን እኛ እናውቃለን አሉት።

25 እርሱም መለሰ፦ ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም፤ ዕውር እንደ ነበርሁ አሁንም
እንዳይ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ አለ።

26 ደግመውም፦ ምን አደረገልህ? እንዴትስ ዓይኖችህን ከፈተ? አሉት።

27 እርሱም መለሰ፦ አስቀድሜ ነገርኋችሁ አልሰማችሁምም፤ ስለ ምን ዳግመኛ
ልትሰሙ ትወዳላችሁ? እናንተ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ልትሆኑ ትወዳላችሁን?
አላቸው።

28 ተሳድበውም፦ አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ነህ፥ እኛ ግን የሙሴ ደቀ መዛሙርት
ነን፤ 29 እግዚአብሔር ሙሴን እንደ ተናገረው እኛ እናውቃለን፥ ይህ ሰው ግን
ከወዴት እንደ ሆነ አናውቅም አሉት።

30 ሰውዬው መለሰ እንዲህም አላቸው፦ ከወዴት እንደ ሆነ እናንተ አለማወቃችሁ
ይህ ድንቅ ነገር ነው፥ ዳሩ ግን ዓይኖቼን ከፈተ። 31 እግዚአብሔርን የሚፈራ
ፈቃዱንም የሚያደርግ ቢኖር ያንን እግዚአብሔር ይሰማዋል እንጂ ኃጢአተኞችን
እንዳይሰማ እናውቃለን። 32 ዕውር ሆኖ የተወለደውን ዓይኖች ማንም እንደ ከፈተ
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አልተሰማም፤ 33 ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን ምንም
ሊያደርግ ባልቻለም ነበር።

34 መልሰው፦ አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወለድህ፥ አንተም እኛን
ታስተምረናለህን? አሉት። ወደ ውጭም አወጡት።[41]

---

[40] [ዮሐ. 9፡22] ኢየሱስ መሢሕ ነው የሚሉትን ሰዎች ከማኅበረሰቡ በማስወገድ የመቅጣቱ ሁኔታ በዚህ ጊዜ በአንዳንድ የአይሁድ መሪዎች፥ ምናልባትም በሸንጎው አለቃ ጸድቋል። ቅጣቱ ከባድ ሲሆን፥ ውጤቱም ከእስራኤል ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ሕይወት መገለል ነበር። ይህ ቅጣት በጸና ሁኔታ ሥራ ላይ የዋለ አይመስልም። ሐዋርያት ሥራ ውስጥ የተገለጡት ክርስቲያኖች ሻል ባለ ነጻነት በምኵራብና በአካባቢው ይዘዋወሩ ነበር።

[41] [ዮሐ. 9፡34] አማኞችን ከምኵራብና ከማኅበረሰቡ የማግለሉ ቅጣት የዓይነሥውሩን ወላጆች አስፈርቷቸው ነበር (ቁጥር 22፡23)። ዓይነሥውሩ ኢየሱስን በጥብቅ በመከላከሉ ቅጣቱ ተፈጸመበት።

## ♦ ክፍል 100መ. ኢየሱስ ራሱን ለዓይነ ሥውሩ መግለጡ

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 9፡35-38</u>

35 ኢየሱስም ወደ ውጭ እንዳወጡት ሰማ ሲያገኘውም፡- አንተ በእግዚአብሔር
ልጅ ታምናለህን? አለው።

36 እርሱም መልሶ፡- ጌታ ሆይ፥ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው? አለ።

37 ኢየሱስም፦ አይተኸዋልም ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው አለው።

38 እርሱም፦ ጌታ ሆይ፥ አምናለሁ አለ፤ ሰገደለትም።[42]

## ♦ ክፍል 100ሠ. የፈሪሳውያን መንፈሳዊ ዕውርነት

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 9፡39-41</u>

39 ኢየሱስም፦ የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ
መጣሁ አለ።

40 ከፈሪሳውያንም ከእርሱ ጋር የነበሩት ይህን ሰምተው፦ እኛ ደግሞ ዕውሮች ነንን?
አሉት።

41 ኢየሱስም አላቸው፦ ዕውሮችስ ብትሆኑ[43] ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር፤ አሁን
ግን፦ እናያለን ትላላችሁ፤ ኃጢአታችሁ ይኖራል።

## ♦ ክፍል 101ሀ. የመልካሙ እረኛና የሌባው ምሳሌ

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 10፡1-18</u>

1 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ[44] በሌላ መንገድ ግን
የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው፤ 2 በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው። 3 ለእርሱ
በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየስማቸው
ጠርቶ ይወስዳቸዋል። 4 የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፥
በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤ 5 ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ
አይከተሉትም፥ የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና። 6 ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤
እነርሱ ግን የነገራቸው ምን እንደ ሆነ አላስተዋሉም።

7 ኢየሱስም ደግሞ አላቸው፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ። 8
ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፤ ዳሩ ግን በጎቹ አልሰ
ሙአቸውም። 9 በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም
መሰማሪያም ያገኛል። 10 ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ

42 [ዮሐ. 9፡38] የዓይነሥውሩ በኢየሱስ ማመን እዚህ ላይ ከፍጻሜ ይደርሳል። ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ "ስግደት" የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባ ክብር መሆኑን ይገልጣል።

43 [ዮሐ. 9፡41] ፈሪሳውያን መንፈሳዊ እውርነታቸውን ቢቀበሉ ኑሮ፥ ለመንፈሳዊ ብርሃን ይጓጉና ይቅርታን ያገኙ ነበር። እናያለን ስላሉና የኢየሱስን መሢሕነት ስላልተቀበሉ የነሱ ጉዳይ ተስፋ ቢስ ሆነ። ትክክለኞች ነን የሚል ሙሉ እምነት ስላደረባቸው፥ ስለ እርሱ እውነቱን ለማወቅ አልፈለጉም። በዚህም ሳቢያ ከኃጢአት ነጻ የመውጣቱ ተስፋ ሁሉ ተወገደ (ማቴ. 9፡13፤ ማር. 2፡17፤ ሉቃስ 5፡32፥ ክፍል 47)።

<u>(ዮሐንስ 10፡1-18 የቀጠለ)</u>

አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።

11 መልካም እረኛ እኔ ነኝ፡፡ መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል። 12 እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኩላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኩላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል። 13 ሞያተኛ ስለ ሆነ ለበጎቹም ስለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል።

14-15 መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ አብም እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል፤ ነፍሴንም ስለ በጎች አኖራለሁ። 16 ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ። 17 ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። 18 እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን[45] አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።

## ♦ ክፍል 101ለ. በአይሁድ መካከል የተባባሰው መከፋፈል

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 10፡ 19-21</u>

19 እንግዲህ ከዚህ ቃል የተነሣ በአይሁድ መካከል እንደ ገና መለያየት ሆነ። 20 ከእነርሱም ብዙዎች፡- ጋኔን አለበት አብዶአልም፤ ስለ ምንስ ትሰሙታላችሁ? አሉ።

21 ሌሎችም፡- ይህ ጋኔን ያለበት ሰው ቃል አይደለም፤ ጋኔን የዕውሮችን ዓይኖች ሊከፍት ይችላልን? አሉ።

---

[44] [ዮሐ. 10፡1] ለዚህ ምሳሌያዊ ገለጣ ሁኔታውን ያመቻቸው ኢየሱስ የፈወሰው ዓይነሥውር በሃይማኖት መሪዎች መገለሉ ነው (ዮሐ. 9፡34፥ ክፍል 100ሐ)። የተፈወሰው ዓይነሥውር የእስራኤል ቅሪቶች ከሚባሉት አንዱ ነው። ፈሪሳውያን ደግሞ "ሌቦች" (10፡1፥ 8)፥ "ሌላው" (10፡5) እና "ሞያተኛ" (10፡12-13) ተብለዋል። ጌታ የተናገረው "የበጎች በረት" (10፡1፥ 16) የሚለው ቃል የራሱ የሆኑትን የመረጠበትን (10፡3) እና በርሱ ጊዜ የነበረውን አይሁዳዊነት ይወክላል። "ሌሎች በጎች" (10፡16) አሕዛብና በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑት ነበሩ። "አንድ መንጋ" (10፡16) የተባሉት በትንቢት የተነገረላቸውና ከእስራኤል ቅሪቶች እንዲሁም በኢየሱስ ከሚያምኑ አሕዛብ ወጥተው የክርስቶስን አካል የሚመሠርቱት ናቸው። ኢየሱስ የበጎች በር (10፡7፥ 9)፥ እና ለመንጋው የሚጠነቀቅ መልካም እረኛ (10፡11፥ 14) ነው።

[45] [ዮሐ. 10፡18] እዚህና ዮሐንስ 2፡19 (ክፍል 31) ውስጥ ብቻ ነው ኢየሱስ ራሱን ከሞት ስለማስነሣት ወይም ይህን ለማድረግ ሥልጣን እንዳለው የተናገረው። በሌላ ስፍራ ወልድን ከሞት የማስነሣቱ ተግባር ሁልጊዜ የአብ ተግባር ነው።

# > ፍቅር ስለተሞላበት አገልግሎትና ስለ ጸሎት የግል ትምህርቶች <

## ♦ ክፍል 102ሀ. የሰባዎቹ መሾም

[ክፍል 58፥ 70ሀና 70ለን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

<u>ሉቃስ 10፡ 1-16</u>

1 ከዚህም በኋላ ጌታ ሌሎቹን ሰብዓ[46] ሾመ፥ ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ
ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ስፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው። 2 አላቸውም፦ መከሩስ ብዙ
ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዴህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች
እንዲልክ ለምኑት። 3 ሂዱ፤ እነሆ፥ እንደ በጎች በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ። 4
ኮረጆም ከረጢትም ጫማም አትያዙ፤ በመንገድም ለማንም እጅ አትንሡ።

5 ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ፦ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ። 6
በዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር፥ ሰላማችሁ ያድርበታል፤ አለዚያም ይመለስላችኋል። 7
በዚያም ቤት ከእነርሱ ዘንድ ካለው እየበላችሁና እየጠጣችሁ ተቀመጡ፤ ለሠራተኛ
ደመወዙ ይገባዋልና። ከቤት ወደ ቤት አትተላለፉ።

8 ወደምትገቡባትም ከተማ ሁሉ ቢቀበሉአችሁ፥ ያቀረቡላችሁን ብሉ፤ 9 በእርስዋም
ያሉትን ድውዮችን ፈውሱና፦ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀረበች
በሉአቸው።[47] 10 ነገር ግን ወደምትገቡባት ከተማ ሁሉ ባይቀበሉአችሁ፥ ወደ
አደባባይዋ ወጥታችሁ፦ 11 ከከተማችሁ የተጣበቀብንን ትቢያ እንኳን
እናራግፍላችኋለን፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ወደ እናንተ እንደ ቀረበች ይህን
እወቁ በሉ። 12 እላችኋለሁ፥ በዚያን ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶም ይቀልላታል።

13 ወዮልሽ ኮራዚን፥ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና
በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ማቅ ለብሰው በአመድም ተቀምጠው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ
በገቡ ነበር። 14 ነገር ግን በፍርድ ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል። 15
አንቺም ቅፍርናሆም፥ እስከ ሰማይ ከፍ አልሽን? ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ።

16 የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፥ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ
የላከኝን ይጥላል።

---

46 [ሉቃስ 10፡1] ሙሴ ይረዱት ዘንድ ሰባ ሽማግሌዎችን እንደሾመ፥ ኢየሱስም ከመያዙና ከመሰቀሉ በፊት ባለው አጭር ጊዜ ተልእኮውን ያፋጥኑለት ዘንድ ሰባ ሰዎችን ሾመ። የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አገልግሎት ገሊላ ውስጥ ነበር። የሰባዎቹ ግን ፖርያ (ከዮርዳኖስ ማዶ) ወይም ይሁዳ ድረስ ነበር። አሥራ ሁለቱ ይበልጥ ነጻና ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሲሆኑ፥ ሰባዎቹ ግን ከተማዎችንና መንደሮችን ለኢየሱስ ጉብኝት የሚያዘጋጁ ነበሩ።

47 [ሉቃስ 10፡9] አሁንም ቢሆን መልእክቱ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት መቅረብ ነው (ማቴ. 10፡7፥ ክፍል 70ለ)። ገሊላ ውስጥ እንዳሉት ሁሉ በሌላ አካባቢ የሚኖሩትም ይህን አዋጅ የመስማት መብት ነበራቸው። ይህ በሰፊው የተሠራጨ፥ በተለይ ይሁዳ ውስጥ የተከናወነ አገልግሎት እስራኤልን፥ ስድስት ወራት ያህል ለሚቀሩት የንጉሣቸው በድል መምጣት ለማዘጋጀት ረድቷል (ክፍል 128ለ)።

## ♦ ክፍል 102ለ. የሰባዎቹ መመለስ

- ምናልባት በይሁዳ -

ሉቃስ 10፡ 17-24

17 ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው፡-[48] ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት።

18 እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ። 19 እነሆ፥
እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን
ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። 20 ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ
በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።

21 በዚያን ሰዓት ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሤት አደረገና፡- የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግናለሁ፤ አዎን አባት ሆይ፥ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና።

22 ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፥ ወልድንም ማን እንደ ሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፥ አብንም ማን እንደ ሆነ ከወልድ በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር የሚያውቅ የለም አለ።

23 ወደ ደቀ መዛሙርቱም ዘወር ብሎ ለብቻቸው፡- የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች
ብፁዓን ናቸው። 24 እላችኋለሁና፥ እናንተ የምታዩትን ብዙዎች ነቢያትና ነገሥታት
ሊያዩ ወደዱ አላዩምም፥ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ወደደው አልሰሙም አለ።

## ♦ ክፍል 103. የመልካሙ ሳምራዊ ታሪክ

[ክፍል 135ን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

ሉቃስ 10፡ 25-37

25 እነሆም፥ አንድ ሕግ አዋቂ ሊፈትነው ተነሥቶ፡- መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ? አለው።

26 እርሱም በሕግ የተጻፈው ምንድር ነው? እንዴትስ ታነባለህ? አለው።

27 እርሱም መልሶ፡- ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው። [ዘሌዋውያን 19፡ 18፤ ዘዳግም 6፡ 5]

28 ኢየሱስም፡- እውነት መለስህ፤ ይህን አድርግ በሕይወትም ትኖራለህ አለው።

29 እርሱ ግን ራሱን ሊያጸድቅ ወድዶ ኢየሱስን፡- ባልንጀራዬስ ማን ነው? አለው።

30 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ፡- አንድ ሰው[49] ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ
በወንበዴዎችም እጅ ወደቀ፤ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት
መካከልም ትተውት ሄዱ። 31 ድንገትም አንድ ካህን በዚያ መንገድ ወረደ አይቶትም

---

[48] [ሉቃስ 10፡ 17] ሰባዎቹ አንዴ አልተመለሱም፤ ምናልባትም የተመለሱት ወደ አንድ ቦታ አይደለም። በተመለሱ ጊዜ ኢየሱስን ያገኙት እንደ ግንባር ቀደም መልእክተኞች ወደደረሱባቸው ቦታዎች ሲከተላቸው ሳለ ይመስላል። ይህ ውይይት የተካሄደው ሁሉም ከተመለሱ በኋላ ነው።

[49] [ሉቃስ 10፡ 30] ይህ ታሪክ ምንም እንኳን እንደምሳሌ ቢጠቀስ፥ በትክክል የተፈጸመ ድርጊት ሊሆን የመቻሉ ነገር አለ። ታሪኩ እውነት ባይሆን ኖሮ ኢየሱስ ጠላቶቹ (ካሕኑና ሌዋዊው ሊኖራቸው የማይቻላቸውን ባሕርይ አይሰጣቸውም ነበር። በተለይ ጥያቄውን ያቀረበው የሕግ አዋቂ ኢየሱስን ከሚፈትኑት ጸሐፍት አንዱ መሆኑ፥ ይህን አሳብ እውነት ያደርገዋል።

(ሉቃስ 10፡25-37 የቀጠለ)

ገለል ብሎ አለፈ። 32 እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ ወደዚያ ስፍራ መጣና አይቶት ገለል ብሎ አለፈ። 33 አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት፥ 34 ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቍስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው፥ በራሱ አህያም ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደርያ ወሰደው ጠበቀውም። 35 በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና፦ ጠብቀው፥ ከዚህም በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው።

36 እንግዲህ ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል?[50]

37 እርሱም፦ ምሕረት ያደረገለት አለ። ኢየሱስም፦ ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ አለው።

## ♦ ክፍል 104. የኢየሱስ ማርያምንና ማርታን መጎብኘት

- በቢታንያ፥ ኢየሩሳሌም አጠገብ -

ሉቃስ 10፡38-42

38 ሲሄዱም እርሱ ወደ አንዲት መንደር ገባ፤ ማርታ[51] የተባለች አንዲት ሴትም በቤትዋ ተቀበለችው። 39 ለእርስዋም ማርያም የምትባል እኅት ነበረቻት፥ እርስዋም ደግሞ ቃሉን ልትሰማ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጣ ነበረች። 40 ማርታ ግን አገልግሎት ስለ በዛባት ባከነች፤ ቀርባም፦ ጌታ ሆይ፥ እኔ እንድሠራ እኅቴ ብቻዬን ስትተወኝ አይገድህምን? እንኪያስ እንድታግዘኝ ንገራት አለችው።

41 ኢየሱስም መልሶ፦ ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፥ 42 የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት።

---

[50] [ሉቃስ 10፡36] ኢየሱስ የሕግ አዋቂውን ጥያቄ "ባልንጀራዬ ማነው?" ከሚለው (ቁጥር 29) "የማን ባልንጀራ ነኝ?" ወደሚለው ለወጠው። ሕግ አዋቂው "ባልንጀራነቱን ለማን ነው ማረጋገጥ ያለብኝ?" ብሎ ነበር ራሱን መጠየቅ የነበረበት። ስለ መልካሙ ሳምራዊ በተነገረው ታሪክ የኢየሱስ መልስ "ለተቸገረ ሁሉ! የታወቀ ጠላቴ ቢሆን እንኳን" የሚል ነው። ፍቅር እንጂ ማዕረግ ባልንጀርነትን አይፈጥርም።

[51] [ሉቃስ 10፡38-39] በዚህ ክንውን የሚታየው የማርያምና ማርታ ሁኔታ ዮሐንስ 11፡17-44 (ክፍል 116ለ) ውስጥ ወንድማቸው አልአዛር፥ ከሞት ሲነሣ ከነበረው ሁኔታ ጋር በትክክል ይመሳሰላል። የማርያም ድርጊት በተለይ ከአምልኮና ከጥሞና ሕይወት ጋር ሲመሳሰል፥ የማርታ ደግሞ በድርጊትና አገልግሎት ተመስሏል። ሁለቱም ተገቢ ድርጊቶች ናቸው። ስሕተቱ የተፈጠረው ማርታ ትክክለኛ አገልግሎቷን ጭንቀት እንዲያበላሽባት በመፍቀዷ ነው።

## ♦ ክፍል 105. ስለ ጸሎት የተሰጠ ትምህርትና ስለ ደፋሩ ወዳጅ የተነገረ ምሳሌ

[ክፍል 54ሬ፥ 54ሸና 121ን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

ሉቃስ 11፡1-13

1 እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፡-
ጌታ ሆይ፥ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው።

2 አላቸውም፡- ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፡-

"በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፤ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤
ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ 3 የዕለት እንጀራችንን
ዕለት ዕለት ስጠን፤ 4 ኃጢአታችንንም ይቅር በለን፥ እኛ ደግሞ የበደሉንን ሁሉ
ይቅር ብለናልና፤ ከክፉ አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን።"

5 እንዲህም አላቸው፡- ከእናንተ ማናችውም ወዳጅ ያለው፥ በእኩል ሌሊትስ ወደ
እርሱ ሄዶ፡- ወዳጄ ሆይ፥ ሦስት እንጀራ አበድረኝ፥ 6 አንድ ወዳጄ ከመንገድ ወደ እኔ
መጥቶ የማቀርብለት የለኝምና ይላልን?

7 ያም ከውስጥ መልሶ፡- አታድከመኝ፤ አሁን ደጁ ተቈልፎአል ልጆቼም ከእኔ ጋር
በአልጋ ላይ አሉ፤ ተነሥቼ ልሰጥህ አልችልም ይላልን? 8 እላችኋለሁ፥ ወዳጅ ስለ ሆነ
ተነሥቶ ባይሰጠው እንኳ፥ ስለ ንዝነዛው ተነስቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል።

9 እኔም እላችኋለሁ፡- ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን
አንኳኩ፥ ይከፍትላችሁማል። 10 የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልግም ያገኛል፥
መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል።

11 አባት ከሆናችሁ ከእናንተ ከማንኛችሁም ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ እርሱም
ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ደግሞ ቢለምነው በዓሣ ፋንታ እባብ ይሰጠዋልን? 12 ወይስ
እንቍላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? 13 እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ
ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት
እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?

# > ከሕግ መምህራንና ከፈሪሳውያን ጋር የተደረገ ሁለተኛ ክርክር <

## ♦ ክፍል 106. ሦስተኛው ስድብ አዘል ክስ እና ሁለተኛው ክርክር

[ክፍል 54ሐ፥ 54ሰ፥ 61፥ 62፥ 64ለ፥ 68፥ 80፥ 91ና 108ሀን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

<u>ሉቃስ 11፥14-36</u>

14 ዲዳውንም ጋኔን ያወጣ ነበር፤ ጋኔኑም ከወጣ በኋላ ዲዳው ተናገረ ሕዝቡም
ተደነቁ፤ 15 ነገር ግን ከእነርሱ አንዳንዱ፦ በብዔል ዜቡል[52] በአጋንንት አለቃ
አጋንንትን ያወጣል አሉ። 16 ሌሎችም ሲፈትኑት ከሰማይ ምልክት ከእርሱ ይፈልጉ
ነበር።

17 እርሱ ግን አሳባቸውን አውቆ እንዲህ አላቸው፦ እርስ በርስዋ የምትለያይ
መንግሥት ሁሉ ትጠፋለች፤ ቤትም በቤት ላይ ይወድቃል። 18 እኔ አጋንንትን
በብዔል ዜቡል እንዳወጣ ትላላችሁና ሰይጣን ደግሞ እርስ በርሱ ከተለያየ መንግሥቱ
እንዴት ትቆማለች? 19 እኔስ በብዔል ዜቡል አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ ልጆቻችሁ
በማን ያወጡአቸዋል? ስለዚህ እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባችኋል። 20 እኔ ግን
በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር
መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።

21 ኃይለኛ ሰው ጋሻና ጦር ይዞ የራሱን ግቢ ቢጠብቅ፥ ያለው ገንዘቡ በሰላም
ይሆናል፤ 22 ከእርሱ ይልቅ የሚበረታ መጥቶ ሲያሸንፈው ግን፥ ታምኖበት የነበረውን
ጋሻና ጦር ይወስድበታል ምርኮውንም ያካፍላል።

23 ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፥ ከእኔ ጋርም የማያከማች ይበትናል።

24 ርኵስ መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ ዕረፍትን እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፤
ባያገኝም፦ ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ 25 ሲመጣም ተጠርጎ አጊጦም
ያገኘዋል። 26 ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሌሎችን ሰባት አጋንንት ከእርሱ
ጋር ይይዛል፥ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው
ይብስበታል።

27 ይህንም ሲናገር፥ ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፦ የተሸከመችህ
ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው።

28 እርሱ ግን፦ አዎን፥ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት
ናቸው አለ።

---

[52] [ሉቃስ 11፥15] ከአንድ ዓመት በፊት ይሄው ውንጀላ ቀርቦበት ነበር፤ ተመሳሳይ ውዝግብ ነው አሁንም የተከተለው (ክፍል 61)። ቀደም ሲል በነበረው አጋጣሚ የተጠቀመባቸውን ሦስት መከራከሪያ ነጥቦች ነው እዚህም ያነሣው። ሁለቱ ውዝግቦች ወይም ግጭቶች የተለያዩ መሆናቸው በሦስት ነገሮች ታይቷል።

(1.) ሉቃስ ይህን ክርክር ይሁዳ ውስጥ፥ የቀድሞውን ደግሞ ገሊላ ውስጥ ያደረገው ይመስላል። (2.) በሉቃስ አገላለጥ የተፈወሰው ሰው ድዳ ነው። በማቴዎስ አገላለጥ ግን ድዳና ዓይነሥውር ተብሏል። ሉቃስ የሕክምና ባለሞያ ከመሆኑ አንጻር ሰውዬው ዓይነሥውር ቢሆን ኑሮ ይህንኑ መግለጥ አይቸግረውም ነበር። (3.) ከሁለቱ ክንውኖች የተከተሉት ሁኔታዎች እንኳን፥ ማለት ቀደም ባለው ጉዳይ የምሳሌያዊው ትምህርት መነሻ እና በሁለተኛው ከፈሪሳዊው ጋር ቁርስ መመገብ በጣም የተለዩ ናቸው።

<u>(ሉቃስ 11፥14-36 የቀጠለ)</u>

29 ብዙ ሕዝብም በተሰበሰቡ ጊዜ እንዲህ ይል ጀመር፡- ይህ ትውልድ ክፉ ነው፤ ምልክት ይፈልጋል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። 30 ዮናስ ለነነዌ ሰዎች ምልክት እንደ ሆናቸው፥ እንዲሁ ደግሞ የሰው ልጅ ለዚህ ትውልድ ምልክት ይሆናል። 31 ንግሥተ አዜብ በፍርድ ከዚህ ትውልድ ሰዎች ጋር ተነሥታ ትፈርድባቸዋለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፥ እነሆም፥ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ። 32 የነነዌ ሰዎች በፍርድ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋልና፥ እነሆም፥ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ።

33 መብራትንም አብርቶ በስውር ወይም በእንቅብ በታች የሚያኖረው የለም፥ የሚገቡ ሰዎች ብርሃኑን እንዲያዩ በመቅረዝ ላይ ያኖረዋል እንጂ። 34 የሰውነትህ መብራት ዓይንህ ናት። ዓይንህ ጤናማ በሆነች ጊዜ ሰውነትህ ሁሉ ደግሞ ብሩህ ይሆናል። ዓይንህ ታማሚ በሆነች ጊዜ ግን ሰውነትህ ደግሞ የጨለመ ይሆናል። 35 እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን ተመልከት። 36 እንግዲህ ሰውነትህ ሁሉ የጨለማ ቍራጭ የሌለበት ብሩህ ቢሆን፥ መብራት በደመቀ ብርሃን እንደሚያበራልህ በጭራሽ ብሩህ ይሆናል።

## ♦ ክፍል 107. ኢየሱስ አንድ ፈሪሳዊ ቤት ምሳ ተጋብዞ ለፈሪሳውያንና ለሕግ መምህራን ያሰማው ወየውላችሁ

[ክፍል 137ሀን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

<u>ሉቃስ 11፥37-54</u>

37 ይህንንም ሲናገር አንድ ፈሪሳዊ ከእርሱ ጋር ምሳ ይበላ ዘንድ ለመነው ገብቶም ተቀመጠ። 38 ከምሳም በፊት አስቀድሞ እንዳልታጠበ ባየው ጊዜ ፈሪሳዊው[53] ተደነቀ።

39 ጌታም እንዲህ አለው፡- አሁን እናንተ ፈሪሳውያን የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ታጠራላችሁ፥ ውስጣችሁ ግን ቅሚያና ክፋት ሞልቶበታል 40 እናንተ ደንቆሮዎች፥ የውጭውን የፈጠረ የውስጡን ደግሞ አልፈጠረምን? 41 ነገር ግን በውስጥ ያለውን ምጽዋት አድርጋችሁ ስጡ፥ እነሆም፥ ሁሉ ንጹሕ ይሆንላችኋል።

42 ነገር ግን እናንተ ፈሪሳውያን፥ ከአዝሙድና ከጤና አዳም ከአትክልትም ሁሉ አሥራት ስለምታወጡ፥ ፍርድንና እግዚአብሔርን መውደድ ስለምትተላለፉ፥ ወዮላችሁ፤ ነገር ግን ሌላውን ሳትተዉ ይህን ልታደርጉት ይገባችሁ ነበር።

43 እናንተ ፈሪሳውያን፥ በምኵራብ የከበሬታ ወንበር በገበያም ሰላምታ ስለምትወዱ፥ ወዮላችሁ።

---

53 [ሉቃስ 11፥38] የኢየሱስ አስተናጋጅ ከውጭ ከሚያሳየው ሁኔታ ተቃራኒ የሆነው ውስጣዊ ባሕርይ ግልጥ ነው። ኢየሱስን ለማጥፋት ገና በግልጥ ስምምነት ላይ ባይደረስም (ዮሐ. 11፥53፥ ክፍል 119)፥ የካህናቱ አለቃ ዓላማ ለአባላቱ ግልጥ ነበር (ክፍል 96ለ፥ 99ለ)። ለዚህ ነበር ጻሐፍትና ፈሪሳውያን ኢየሱስን በቅርብ ለመመልከትና በይፋ የመክሰሻ ነጥብ ለማግኘት ይረዳቸው ዘንድ ከአባላታቸው አንዱ ኢየሱስን ምሣ እንዲጋብዘው ያደረጉት። ከዚህ ግንኙነት ሳቢያ ጠላትነታቸው ይበልጥ ከረረ (ቁጥር 53-54)። ቀደም ሲል ገሊላ ውስጥ ኢየሱስን ምሣ ጋብዞት የነበረው ፈሪሳዊ ግን እንዲህ ያለ ጠላትነት አላሳየም (ክፍል 59)።

(ሉቃስ 11፡37-54 የቀጠለ)

44 እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄዱበት የተሰወረ
መቃብር ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ።

45 ከሕግ አዋቂዎችም አንዱ መልሶ:- መምህር ሆይ፥ ይህን ማለትህ እኛን ደግሞ
መስደብህ ነው አለው።

46 እርሱም እንዲህ አለ:- እናንተ ደግሞ ሕግ አዋቂዎች፥ አስቸጋሪ ሸክም ለሰዎች
ስለምታሸክሙ፥ ራሳችሁም በአንዲት ጣታችሁ ስንኳ ሸክሙን ስለማትነኩት፥
ወዮላችሁ።

47 አባቶቻችሁ የገደሉአቸውን የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ፥ ወዮላችሁ። 48
እንግዲህ ለአባቶቻችሁ ሥራ ትመሰክራላችሁ ትስማማላችሁም፤ እነርሱ
ገድለዋቸዋልና፥ እናንተም መቃብራቸውን ትሠራላችሁ። 49 ስለዚህ ደግሞ
የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ አለች:- ወደ እነርሱ ነቢያትንና ሐዋርያትን እልካለሁ፥
ከእነርሱም ይገድላሉ ያሳድዱማል፥ 50 ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የፈሰሰው የነቢያት
ሁሉ ደም፥ 51 ከአቤል ደም ጀምሮ በመሠዊያውና በቤተ መቅደስ መካከል እስከ
ጠፋው እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ፥ ከዚህ ትውልድ እንዲፈለግ አዎን እላችኋለሁ፥
ከዚህ ትውልድ ይፈለጋል።

52 እናንተ ሕግ አዋቂዎች፥ የእውቀትን መክፈቻ[54] ስለ ወሰዳችሁ፥ ወዮላችሁ
ራሳችሁ አልገባችሁም የሚገቡትንም ከለከላችሁ።

53-54 ይህንም ሲናገራቸው፥ ጻፎችና ፈሪሳውያን በአፉ የተናገረውን ሊነጥቁ
ሲያደቡ፥ እጅግ ይቃወሙና ስለ ብዙ ነገር እንዲናገር ያነሣሡ ጀመር።

## ♦ ክፍል 108ሀ. ደቀ መዛሙርቱን ስለ ግብዝነት ማስጠንቀቅ

[ክፍል 54ሰ፥ 61፥ 70ለ፥ 81ሀ፥ 106ና 139ለን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

ሉቃስ 12፡1-12

1 በዚያን ጊዜ የሕዝብ አእላፍ እርስ በርሳቸው እስኪረጋገጡ ድረስ ተሰብስበው
ሳሉ፥ ለደቀ መዛሙርቱ[55] እንዲህ ይል ጀመር:- አስቀድማችሁ ከፈሪሳውያን እርሾ
ተጠበቁ፥ እርሱም ግብዝነት ነው። 2 ነገር ግን የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም
የተሰወረ ምንም የለም። 3 ስለዚህ በጨለማ የምትናገሩት ሁሉ በብርሃን ይሰማል፥
በእልፍኝም ውስጥ በጆሮ የምትናገሩት በሰገነት ላይ ይሰበካል።

---

54 [ሉቃስ 11፡52] ኢየሱስ ፈሪሳውያንን (ቁጥር 39፡44) እና ሕግ አዋቂዎችን (ወይም ጸሐፍትን፥ ቁጥር 45-51) የሚወቅስበት ሁኔታ ወደ መጨረሻው የደረሰው፥ ሕግ አዋቂዎች የእውቀትን መክፈቻ ስለመውሰዳቸው በወነጀላቸው ጊዜ ነው። እግዚአብሔርን የማወቂያ ቁልፍ፥ እነሱ በተሳሳተ ትርጉምና ሰው ሠራሽ ልማድ እውነተኛ ትርጉሙን የሸሸጉት ብሉይ ኪዳን ነው። እነዚህ ሕግ አዋቂዎች እግዚአብሔርን በትክክል ወደ ማምለኩ አንገባም አሉ፤ ይህ ብቻም አይደል፥ እነሱ ያስተምራቸው የነበሩ ሰዎችንም በእግዚአብሔር ቃል ላይ የራሳቸውን አሳብ እየጨመሩ ከትክክለኛው አምልኮ አራቋቸው።

55 [ሉቃስ 12፡1] ሉቃስ 12፡1-59 (ክፍል 108ሀ- 108ሠ) ውስጥ ያለው ክፍል በከባዱ ተቃውሞ ላይ የቀጠለ ንግግር ነው። ምናልባት አብዛኛው ጠላት የሆነ በጣም ብዙ ሕዝብ በሥፍራው ነበር። የኢየሱስ ንግግር ግን ምንም እንኳን ጉባዔው ቢያዳምጠው (ቁጥር 1-12፥ 22-53) በአብዛኛው ለደቀ መዛሙርቱ ነበር።

(ሉቃስ 12፥1-12 የቀጠለ)

4 ለእናንተም ለወዳጆቼ እላችኋለሁ፥ ሥጋን የሚገድሉትን በኋላም አንድ ስንኳ
የሚበልጥ ሊያደርጉ የማይችሉትን አትፍሩ። 5 እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ፤
ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ። አዎን እላችኋለሁ፥ እርሱን
ፍሩ። 6 አምስት ድንቢጦች በአሥር ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ
ስንኳ በእግዚአብሔር ፊት አትረሳም። 7 ነገር ግን የእናንተ የራሳችሁ ጠጕር ሁሉ
እንኳ የተቈጠረ ነው፤ እንግዲያስ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ።

8 እላችሁማለሁ፥ በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ሁሉ፥ የሰው ልጅ ደግሞ
በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል፤ 9 በሰውም ፊት የሚክደኝ
በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይካዳል። 10 በሰው ልጅም ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ
ይሰረይለታል፤ መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ ግን አይሰረይለትም።

11 ወደ ምኵራቦችና ወደ መኳንንቶችም ወደ ገዢዎችም ሲጐትቱአችሁ፥ እንዴት
ወይም ምን እንድትመልሱ ወይም እንድትናገሩ አትጨነቁ፤ 12 መንፈስ ቅዱስ
በዚያች ሰዓት ልትናገሩ የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና።

## ♦ ክፍል 108ለ. ንፉግነትንና በሀብት መተማመንን በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ [ክፍል 54ሰን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

ሉቃስ 12፥13-34

13 ከሕዝቡም አንድ ሰው፦ መምህር ሆይ፥ ርስቱን ከእኔ ጋር እንዲካፈል
ለወንድሜ ንገረው አለው።

14 እርሱም፦ አንተ ሰው፥ ፈራጅና አካፋይ በላያችሁ እንድሆን ማን ሾመኝ?
አለው። 15 የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፥ ከመጐምጀትም
ሁሉ ተጠበቁ አላቸው።

16 ምሳሌም ነገራቸው እንዲህ ሲል፦ አንድ ባለ ጠጋ ሰው እርሻ እጅግ ፍሬያም
ሆነችለት። 17 እርሱም፦ ፍሬዬን የማከማችበት ስፍራ አጥቻለሁና ምን ላድርግ?
ብሎ በልቡ አሰበ።

18 እንዲህ አደርጋለሁ፤ ጐተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ፥ በዚያም
ፍሬዬንና በረከቴን ሁሉ አከማቻለሁ፤ 19 ነፍሴንም፦ አንቺ ነፍሴ፥ ለብዙ ዘመን
የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ፥ ብዪ፥ ጠጪ፥ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አለ።

20 እግዚአብሔር ግን፦ አንተ ሰነፍ፥ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት
ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? አለው።

21 ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች፥ በእግዚአብሔር ዘንድም ባለ ጠጋ ያልሆነ እንዲህ
ነው።

22 ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ፦ ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ለነፍሳችሁ በምትበሉት
ወይም ለሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ። 23 ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ
ይበልጣልና። 24 ቍራዎችን ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም፥ ዕቃ ቤትም
ወይም ጎተራ የላቸውም፥ እግዚአብሔርም ይመግባቸዋል፤ እናንተስ ከወፎች እንዴት
ትበልጣላችሁ? 25 ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል

(ሉቃስ 12፥ 13-34 የቀጠለ)

ማን ነው? 26 እንግዲህ ትንሹን ነገር ስንኳ የማትችሉ ከሆናችሁ፥ ስለ ምን በሌላ
ትጨነቃላችሁ?

27 አበቦችን እንዴት እንዲያድጉ ተመልከቱ፤ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር
ግን እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከእነዚህ እንደ አንዲቱ አለበሰም። 28
እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን በሜዳ የሆነውን ሣር
እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጐደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን
እንዴት? 29 እናንተም የምትበሉትን የምትጠጡትንም አትፈልጉ፥ አታወላውሉም፤
30 ይህንስ ሁሉ በዓለም ያሉ አሕዛብ ይፈልጉታልና፤ የእናንተም አባት ይህ
እንዲያስፈልጋችሁ ያውቃል። 31 ዳሩ ግን መንግሥቱን ፈልጉ ይህም ሁሉ
ይጨመርላችኋል።

32 አንተ ታናሽ መንጋ፥ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና
አትፍሩ። 33 ያላችሁን ሽጡ ምጽዋትም ስጡ፤ ሌባ በማይቀርብበት ብልም
በማያጠፋበት በሰማያት የማያልቅ መዝገብ የሚሆኑትን የማያረጁትንም ኮረጆዎች
ለራሳችሁ አድርጉ፤ 34 መዝገባችሁ ባለበት ልባችሁ ደግሞ በዚያ ይሆናልና።

## ♦ ክፍል 108ሐ. ለሰው ልጅ መምጣት ዝግጁ ባለመሆን ላይ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ [ክፍል 139ረን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

ሉቃስ 12፥ 35-48

35 ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን፤ 36 እናንተም ጌታቸው መጥቶ
ደጁን ሲያንኳኳ ወዲያው እንዲከፍቱለት ከሰርግ እስኪመለስ ድረስ የሚጠብቁ
ሰዎችን ምሰሉ 37 ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች
ብፁዓን ናቸው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ታጥቆ በማዕድ ያስቀምጣቸዋል ቀርቦም
ያገለግላቸዋል። 38 ከሌሊቱም በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ክፍል መጥቶ እንዲሁ
ቢያገኛቸው፥ እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው። 39 ይህን ግን እወቁ ባለቤት በምን
ሰዓት ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ፥ ቤቱም እንዲቆፈር ባልፈቀደም ነበር። 40
እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።

41 ጴጥሮስም፦ ጌታ ሆይ፥ ይህን ምሳሌ ለእኛ ወይስ ደግሞ ለሁሉ ትናገራለህን?
አለው።

42 ጌታም አለ፦ እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ
ሰዎቹ ላይ የሚሾመው ታማኝና ልባም መጋቢ ማን ነው? 43 ጌታው መጥቶ እንዲህ
ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው። 44 እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ
ይሾመዋል። 45 ያ ባሪያ ግን፦ ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ
ሎሌዎችንና ገረዶችንም ይመታ ይበላም ይጠጣም ይሰክርም ዘንድ ቢጀምር፥ 46
የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ ከሁለትም
ይሰነጥቀዋል እድሉንም ከማይታመኑ ጋር ያደርጋል።

47 የጌታውንም ፈቃድ አውቆ ያልተዘጋጀ እንደ ፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ
ይገረፋል፤ 48 ያላወቀ ግን መገረፍ የሚገባውንም ያደረገ ጥቂት ይገረፋል። ብዙም
ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፥ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ
አብዝተው ይሹበታል።

## ♦ ክፍል 108መ. ሊመጣ ስላለው መለያየት የተነገረ ማስጠንቀቂያ

[ክፍል 70ለን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

<u>ሉቃስ 12፥49-53</u>

49 በምድር ላይ እሳት ልጥል መጣሁ፥ አሁንም የነደደ ከሆነ ዘንድ ምን
እፈልጋለሁ? 50 ነገር ግን የምጠመቃት ጥምቀት አለችኝ፥ እስክትፈጸምም ድረስ
እንዴት እጨነቃለሁ? 51 በምድር ላይ ሰላምንም ለመስጠት የመጣሁ
ይመስላችኋልን? እላችኋለሁ፥ አይደለም፥ መለያየትን[56] እንጂ። 52 ከአሁን ጀምሮ
በአንዲት ቤት አምስት ሰዎች ይኖራሉና፤ ሦስቱም በሁለቱ ላይ ሁለቱም በሦስቱ ላይ
ተነሥተው ይለያያሉ። 53 አባት በልጁ ላይ ልጅም በአባቱ ላይ፥ እናት በልጅዋ ላይ
ልጅዋም በእናትዋ ላይ፥ አማት በምራትዋ ላይ ምራትም በአማትዋ ላይ ተነሥተው
ይለያያሉ።

## ♦ ክፍል 108ሠ. የአሁኑን ዘመን ከመመርመር መዘናጋትን በተመለከተ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

[ክፍል 54ሠን ይመልከቱ]

- ምናልባት በይሁዳ -

<u>ሉቃስ 12፥54-59</u>

54 ደግሞም ሕዝቡን እንዲህ አለ፦ ደመና ከምዕራብ ሲወጣ ባያችሁ ጊዜ፥
ወዲያው፦ ዝናብ ይመጣል ትላላችሁ፥ እንዲሁም ይሆናል፤ 55 በአዜብም ነፋስ
ሲነፍስ፦ ትኩሳት ይሆናል ትላላችሁ፥ ይሆንማል። 56 እናንተ ግብዞች፥ የምድሩንና
የሰማዩን ፊት ልትመረምሩ ታውቃላችሁ፥ ነገር ግን ይህን ዘመን[57] የማትመረምሩ
እንዴት ነው?

57 ራሳችሁ ደግሞ ጽድቅን የማትፈርዱ ስለ ምን ነው? 58 ከባላጋራህ ጋር ወደ ሹም
ብትሄድ፥ ወደ ዳኛ እንዳይጐትትህ ዳኛውም ለሎሌው አሳልፎ እንዳይሰጥህ ሎሌውም
በወኅኒ እንዳይጥልህ፥ ገና በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ እንድትታረቅ ትጋ። 59
እልሃለሁ፥ የመጨረሻዋን ግማሽ ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከዚያ ከቶ አትወጣም።

---

[56] [ሉቃስ 12፥51] ኢየሱስ የተናገረለት የመከፋፈል ሁኔታ እፊቱ የተሰበሰበውን ሕዝብ የሚመለከት እንጂ ሌላ አልነበረም። ውስጣዊ ንጽሕናን አስመልክቶ ላቀረበው ጥያቄ ቀና መልስ ሳለመስጠት ግትርነት ባሳዩ ጊዜ (ሉቃስ 12፥45፥ ክፍል 108ሐ ውስጥ እንደተመለከተው ያለ ግዴለሽ ባሪያ) ውጤቱ ሌላ ሳይሆን መከፋፈል ነው።

[57] [ሉቃስ 12፥56] "ይህ ዘመን" የሚለው ቃል በዋናነት የመንግሥተ ሰማያትን መቅረብ ያመለክታል (ክፍል 108ሐ)። በጠላትነት መንፈስ ለተሞሉት ተሰብሳቢዎች የጊዜው ምልክት፥ የምድሩንና የሰማዩን ፊት (አየሩን) የመረዳታቸውን ያህል ግልጥ ሊሆንላቸው ይገባ ነበር። እነርሱ ግን ግልጥ የሆነውን የኢየሱስን መሢሕነት ሆን ብለው እንዳልተቀበሉት ሁሉ፥ የመንግሥተ ሰማያትን መቅረብም ያልተረዱ ለመምሰል ሞከሩ።

## ♦ ክፍል 109. *ሁለት አማራጮች፡- በንስሐ መመለስ ወይም መሞት*

- *ምናልባት በይሁዳ* -

<u>ሉቃስ 13፡1-9</u>

1 በዚያን ጊዜም ሰዎች መጥተው ጲላጦስ ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር
ስላደባለቀው ስለ ገሊላ ሰዎች አወሩለት። 2 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡-
እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ስለ ደረሰባቸው ከገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኃጢአተኞች የሆኑ
ይመስሉአችኋልን? 3 እላችኋለሁ፥ አይደለም፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ
እንዲሁ ትጠፋላችሁ።[58] 4 ወይስ በሰሌሆም ግንቡ የወደቀባቸውና የገደላቸው እነዚያ
አሥራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሁሉ ይልቅ በደለኞች
ይመስሉአችኋልን? አይደለም፥ እላችኋለሁ፤ 5 ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ
እንደዚሁ ትጠፋላችሁ።[58]

6 ይህንም ምሳሌ አለ፡- ለአንድ ሰው በወይኑ አትክልት የተተከለች በለስ[59]
ነበረችው፥ ፍሬም ሊፈልግባት መጥቶ ምንም አላገኘም። 7 የወይን አትክልት
ሠራተኛውንም፡- እነሆ፥ ከዚህች በለስ ፍሬ ልፈልግ ሦስት ዓመት እየመጣሁ ምንም
አላገኘሁም፤ ቍረጣት፤ ስለ ምን ደግሞ መሬቱን ታጐስቍላለች? አለው።

8 እርሱ ግን መልሶ፡- ጌታ ሆይ፥ ዙሪያዋን እስክኰተኵትላትና ፋንድያ እስካፈስላት
ድረስ በዚች ዓመት ደግሞ ተዋት። 9 ወደ ፊትም ብታፈራ፥ ደኅና ነው፤ ያለዚያ ግን
ትቈርጣታለህ አለው።

## ♦ ክፍል 110. አንዲት ሕመምተኛ በሰንበት በመፈወሷ የአንድ የምኵራብ አለቃ ተቃውሞ

[ክፍል 49ሀ-51፥ 64ሠ፥ 64ረ፥ 100ሐና 114ን ይመልከቱ]

- *ምናልባት በይሁዳ* -

<u>ሉቃስ 13፡10-21</u>

10 በሰንበትም በአንድ ምኵራብ ያስተምር ነበር። 11 እነሆም፥ ከአሥራ ስምንት
ዓመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት ነበረች፥ እርስዋም ጐባጣ ነበረች
ቀንታም ልትቆም ከቶ አልተቻላትም። 12 ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና፡- አንቺ
ሴት፥ ከድካምሽ ተፈትተሻል አላት፥ እጁንም ጫነባት፤ 13 ያን ጊዜም ቀጥ አለች፥

---

[58] [ሉቃስ 13፡3፥ 5] ከኢዮብ ዘመን ጀምሮ በሰዎች ላይ የሚደርሰው ክፉ ነገር ሁሉ፥ በሰዎቹ ኃጢአት ምክንያት እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠረውን ፍርድ ኢየሱስ ተቃወመ። ምናልባት የሕዝቡ ስቃይ የኃጢአታቸው ውጤት ሊሆን ይችላል። ክርስቶስ በእስራኤል ላይ ሊመጣ ያለውን ፍርድ በመረዳት ንስሐ ያለመግባት የሚያስከትለውን የከፋ ነገር አስጠነቀቀ።

[59] [ሉቃስ 13፡6] ከሉቃስ 13፡1-5 ጋር በተያያዘ ሁኔታ የበለስ ተክል የዚህ የእስራኤል ትውልድ ተምሳሌት መሆን አለበት (ሆሴ. 9፡10፤ ኢዮ. 1፡7፤ ማቴ. 21፡19፤ ማር. 11፡13፤ ፍልስ. 129ሀ)። የበለስ ተክል ለማደግ ሦስት ዓመት እንደሚያሻው፥ የእስራኤል ሕዝብም ለሦስት ዓመታት የክርስቶስን ትምህርት አግኝቷል። ተጨማሪው ዓመት በኢየሱስ ቀሪ አገልግሎት፥ ከትንሣኤ በኋላ እና ከበዓለ አምሳ በኋላ በጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን በነበረው አገልግሎቱ የተካተተ ነበር። ተምሳሌቱ የሰፋ ፍቺ ከተሰጠው፥ የአትክልቱ ስፍራ አብን፥ የአትክልቱ ስፍራ ጠባቂ ክርስቶስን፥ እንዲሁም "መሬቱን ታጎሳቁላለች" የሚለው ቃል (ቁ.7) እግዚአብሔር ለሌሎች ባለው የምሕረት ዓላማ መንገድ ላይ እንቅፋት የምትሆነውን እስራኤልን ይወክላሉ (ሮሜ 9፡19)።

(ሉቃስ 13፡10-21 የቀጠለ)

እግዚአብሔርንም አመሰገነች።

14 የምኵራብ አለቃ ግን ኢየሱስ በሰንበት ስለ ፈወሰ ተቈጥቶ መለሰና ሕዝቡን፦ ሊሠራባቸው የሚገባ ስድስት ቀኖች አሉ፤ እንግዲህ በእነርሱ መጥታችሁ ተፈወሱ እንጂ በሰንበት አይደለም አለ።

15 ጌታም መልሶ፦ እናንተ ግብዞች፥ ከእናንተ እያንዳንዱ በሰንበት በሬውን ወይስ አህያውን ከግርግም ፈትቶ ውኃ ሊያጠጣው ይወስደው የለምን? 16 ይህችም የአብርሃም ልጅ ሆና ከአሥራ ስምንት ዓመት ጀምሮ ሰይጣን ያሰራት በሰንበት ቀን ከዚህ እስራት ልትፈታ አይገባምጆ? አለው።

17 ይህንም ሲናገር ሳለ የተቃወሙት ሁሉ አፈሩ፤ ከእርሱም በተደረገው ድንቅ ሁሉ ሕዝቡ ሁሉ ደስ አላቸው።

18 እርሱም፦ የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ትመስላለች፥ በምንስ አስመስላታለሁ? 19 ሰው ወስዶ በአትክልቱ የጣላትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤ አደገችም ታላቅ ዛፍም ሆነች፥ የሰማይ ወፎችም በቅርንጫፎችዋ ሰፈሩ አለ። [መዝሙር 104፡12፤ ሕዝቅኤል 17፡23፥ 31፡6፤ ዳንኤል 4፡12]

20 ደግሞም፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምን አስመስላታለሁ? 21 ሴት ወስዳ ሁሉ እስኪቦካ ድረስ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች አለ።

## ♦ ክፍል 111. ተሳደበ በማለት ኢየሱስን በመቅደስ መታደስ ዕለት እንደገና ለማሠር ወይም ለመውገር የተደረገ ሙከራ

- ኢየሩሳሌም -

ዮሐንስ 10፡22-39

22 በኢየሩሳሌምም የመቅደስ መታደስ በዓል ሆነ፤ 23 ክረምትም ነበረ። ኢየሱስም በመቅደስ በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ይመላለስ ነበር። 24 አይሁድም እርሱን ከበው፦ እስከ መቼ ድረስ በጥርጣሬ ታቆየናለህ? አንተ ክርስቶስ[60] እንደ ሆንህ ገልጠህ ንገረን አሉት።

25 ኢየሱስም መለሰላቸው፥ እንዲህ ሲል፦ ነገርኋችሁ አታምኑምም እኔ በአባቴ ስም የማደርገው ሥራ ይህ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ 26 እናንተ ግን እንደ ነገርኋችሁ ከበጎቼ ስላልሆናችሁ አታምኑም። 27 በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ 28 እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። 29 የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። 30 እኔና አብ አንድ ነን።

31 አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ። 32 ኢየሱስ፦ ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው።

33 አይሁድም፦ ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት።

---

60 [ዮሐ. 10፥ 24] የውዝግቡ ሁሉ ዋና ጉዳይ ኢየሱስ ሊመጣ ያለው መሢሕ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነበር። ኢየሱስ መሢሕ ለመሆኑ ማረጋገጫ አገለገለ (ቁ.25)፥ ለበጎቹ ሕይወቱን ሰጠ (ቁ.28)፥ እና እንደፍጻሜም ከአብ ጋር ያለውን አንድነት ገለጠ (ቁ.30)። ይህ አባባል ጠላቶቹ ሊታገሱ ከሚችሉት በላይ በመሆኑ፥ እንደገና ሊወግሩት (ቁ.31)፥ እና ሊይዙት (ቁ.39) ፈለጉ።

(ዮሐንስ 10፥22-39 የቀጠለ)

34 ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፦ እኔ፦ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ
በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? [መዝሙር 82፥6] 35 መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና
እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው፥ 36 የእግዚአብሔር
ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን፦ ትሳደባለህ
ትሉታላችሁን? 37 እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ፤ 38 ባደርገው ግን፥ እኔን
ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደ ሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ
ሥራውን እመኑ። 39 እንግዲህ ደግመው ሊይዙት ፈለጉ፤ ከእጃቸውም ወጣ።

# 9

# በፖርያ (በዮርዳኖስ ማዶ) የኢየሱስ አገልግሎት

## > የደቀ መዛሙርትነት መሠረት (ደንብ) <

### ♦ ክፍል 112. ከኢየሩሳሌም ወደ ዮርዳኖስ ማዶ

- ፖርያ[62] -

<u>ዮሐንስ 10፡40-42</u>

40 ዮሐንስም በመጀመሪያ ያጠምቅበት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ ዮርዳኖስ ማዶ እንደ
ገና ሄደ[61] በዚያም ኖረ። 41 ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ መጥተው፡- ዮሐንስ አንድ
ምልክት ስንኳ አላደረገም፥ ነገር ግን ዮሐንስ ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ እውነት
ነበረ አሉ። 42 በዚያም ብዙዎች በእርሱ አመኑ።

### ♦ ክፍል 113ሀ. ስለ ደኅንነትና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስለመግባት የተነሣ ጥያቄ [ክፍል 54ሽ፥ 124ሀና 124ለን ይመልከቱ]

- ከፖርያ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ -

<u>ሉቃስ 13፡22-30</u>

22 ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ከተማዎችንና መንደሮችን እያስተማረ ያልፍ ነበር። 23
አንድ ሰውም፡- ጌታ ሆይ፥ የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን? አለው።

እርሱም እንዲህ አላቸው፡- 24 በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ፤ እላችኋለሁና፥
ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም። 25 ባለቤቱ ተነሥቶ በሩን ከቈለፈ በኋላ፥
እናንተ በውጭ ቆማችሁ፡- ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ክፈትልን እያላችሁ በሩን
ልታንኳኩ ትጀምራላችሁ

እርሱም መልሶ፡- ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም ይላችኋል።

26 በዚያን ጊዜም፡- በፊትህ በላን ጠጣንም በአደባባያችንም አስተማርህ ልትሉ
ትጀምራላችሁ፤

27 እርሱም፡- እላችኋለሁ፥ ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም፤ ሁላችሁ
ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ይላችኋል። [መዝሙር 6፡8]

28 አብርሃምንና ይስሐቅን ያዕቆብንም ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት
ባያችሁ ጊዜ፥ እናንተ ግን ወደ ውጭ ተጥላችሁ ስትቀሩ፥ በዚያ ልቅሶና ጥርስ
ማፋጨት ይሆናል። 29 ከምሥራቅና ከምዕራብም ከሰሜንና ከደቡብም ይመጣሉ፥
በእግዚአብሔርም መንግሥት በማዕድ ይቀመጣሉ። 30 እነሆም፥ ከኋለኞች ፊተኞች
የሚሆኑ አሉ፥ ከፊተኞችም ኋለኞች የሚሆኑ አሉ።

---

61 [ዮሐ. 10፡40] ከዚያ ስፍራ ከተለየ ሦስት ወር ተኩል ሆኖታል፡- ከድንኳን በዓል እስከ ፋሲካ ድረስ። ኢየሱስ ፖርያ ውስጥ ለሰጠው አገልግሎት (ቁ.42) የታየው ምላሽ ኢየሩሳሌም ውስጥ ከነበረው ምላሽ ተጻራሪ ነበር (ዮሐ. 10፡37-39፥ ክፍል 111)።

62 ፖርያ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ባይጠቀስም ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ በኩል በገሊላና በሙት ባህር መካከል የሚገኘውንና በሄሮድስ አንቲጳስ የሚመራውን አገር ያመለክታል።

## ♦ ክፍል 113ለ. ስለ ኢየሱስ ሞት የተደረገ ቅድመ ገለጣ እና ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ማዘኑ [ክፍል 137ለን ይመልከቱ]

- ከፖርያ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ -

ሉቃስ 13፡31-35

31 በዚያን ሰዓት ከፈሪሳውያን አንዳንዱ ቀርበው፡- ሄሮድስ[63] ሊገድልህ ይወዳልና
ከዚህ ውጣና ሂድ አሉት።

32 እንዲህም አላቸው፡- ሄዳችሁ ለዚያች ቀበሮ፡- እነሆ፥ ዛሬና ነገ አጋንንትን
አወጣለሁ በሽተኞችንም እፈውሳለሁ፥ በሦስተኛውም ቀን እፈጸማለሁ በሉአት። 33
ዳሩ ግን ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባውምና ዛሬና ነገ ከነገ በስቲያም
ልሄድ ያስፈልገኛል።

34 ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም
የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን
እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፥ እናንተም አልወደዳችሁም። 35 እነሆ፥ ቤታችሁ
የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል። እላችኋለሁም፥ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው
እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም።

## ♦ ክፍል 114. ኢየሱስ በሰንበት ዕለት ከአንድ የፈሪሳውያን አለቃ ቤት ለምሳ ተጋብዞ በተገኘበት ሆዱ የተነፋ አንድ ሰው መፈወሱ፥ እና በሥነ ሥርዓቱ ላይ የቀረቡ ሦስት ምሳሌዎች

[ክፍል 49ሀ-51፥ 100ሐና 110ን ይመልከቱ]

- ምናልባት በፖርያ -

ሉቃስ 14፡1-24

1 በሰንበትም ከፈሪሳውያን አለቆች[64] ወደ አንዱ ቤት እንጀራ ሊበላ በገባ ጊዜ
እነርሱ ይጠባበቁት ነበር። 2 እነሆም፥ ሆዱ የተነፋ ሰው በፊቱ ነበረ። 3 ኢየሱስም
መልሶ፡- በሰንበት መፈወስ ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም? ብሎ ለሕግ
አዋቂዎችና ለፈሪሳውያን ተናገረ። 4 እነርሱ ግን ዝም አሉ። ይዞም ፈወሰውና
አሰናበተው።

5 ከእናንተ አህያው ወይስ በሬው በጉድጓድ ቢወድቅ በሰንበት ወዲያው የማያወጣው
ማን ነው? አላቸው። 6 ስለዚህ ነገርም ሊመልሱለት አልተቻላቸውም።

7 የታደሙትንም የከበሬታ ስፍራ እንደ መረጡ ተመልክቶ ምሳሌ ነገራቸው እንዲህ
ሲል፡- 8 ማንም ለሰርግ ቢጠራህ በከበሬታ ስፍራ አትቀመጥ፤ ምናልባት ከአንተ
ይልቅ የከበረ ተጠርቶ ይሆናልና አንተን እርሱንም የጠራ መጥቶ፡- 9 ስለዚህ ስፍራ

---

[63] [ሉቃስ 13፡31] ፖርያ እንደ ገሊላ የሄሮድስ አንቲጳስ ግዛት ናት። ስለሆነም እኒህ ፈሪሳውያን ኢየሱስ ቀደም ሲል ከሄሮድስ ጋር የነበረውን ግጭት (ክፍል 72ረ) ለራሳቸው እንደሚበጅ ተጠቅመው፥ እነርሱ ወደሚቆጣጠሩት ወደ ይሁዳ እንዲመለስ ፈለጉ። በሌላ መንገድ፥ የሄሮድስ ታሪክ አልተሠራጨም ነበር፤ ምክንያቱም ክርስቶስ (ቁ. 32-35) የተንኮል አሳባቸውን ቢያውቅም ስላልተቃወማቸው ነው።

(ሉቃስ 14፥1-24 የቀጠለ)

ተውለት ይልሃል፥ በዚያን ጊዜም እያፈርህ በዝቅተኛው ስፍራ ልትሆን ትጀምራለህ።
10 ነገር ግን በተጠራህ ጊዜ፥ የጠራህ መጥቶ፦ ወዳጄ ሆይ፥ ወደ ላይ ውጣ
እንዲልህ፥ ሄደህ በዝቅተኛው ስፍራ ተቀመጥ፤ ያን ጊዜም ከአንተ ጋር በተቀመጡት
ሁሉ ፊት ክብር ይሆንልሃል። 11 ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱንም
የሚያዋርድ ከፍ ይላል።

12 የጠራውንም ደግሞ እንዲህ አለው፦ ምሳ ወይም እራት ባደረግህ ጊዜ፥ እነርሱ
ደግሞ በተራቸው ምናልባት እንዳይጠሩህ ብድራትም እንዳይመልሱልህ፥
ወዳጆችህንና ወንድሞችህን ዘመዶችህንም ባለ ጠጎች ጎረቤቶችህንም አትጥራ። 13
ነገር ግን ግብዣ ባደረግህ ጊዜ ድሆችንና ጉንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችንም ጥራ፤
14 የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትሆናለህ፤ በጻድቃን ትንሣኤ
ይመለስልሃልና።

15 ከተቀመጡትም አንዱ ይህን ሰምቶ፦ በእግዚአብሔር መንግሥት እንጀራ
የሚበላ ብፁዕ ነው አለው።

16 እርሱ ግን እንዲህ አለው፦ አንድ ሰው ታላቅ እራት አድርጎ ብዙዎችን ጠራ፤
17 በእራትም ሰዓት የታደሙትን፦ አሁን ተዘጋጅቶአልና ኑ እንዲላቸው ባሪያውን
ላከ።

18 ሁላቸውም በአንድነት ያመካኙ ጀመር። የፊተኛው፦ መሬት ገዝቼአለሁ
ወጥቼም ላየው በግድ ያስፈልገኛል፤ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው።

19 ሌላውም፦ አምስት ጥምድ በሬዎች ገዝቼአለሁ ልፈትናቸውም እሄዳለሁ፤
ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው።

20 ሌላውም፦ ሚስት አግብቼአለሁ ስለዚህም ልመጣ አልችልም አለው።

21 ባሪያውም ደርሶ ይህን ለጌታው ነገረው። በዚያን ጊዜ ባለቤቱ ተቆጥቶ
ባሪያውን፦ ወደ ከተማ ጎዳናና ወደ ስላች ፈጥነህ ውጣ ድሆችንና ጉንድሾችን
አንካሶችንና ዕውሮችንም ወደዚህ አግባ አለው።

22 ባሪያውም፦ ጌታ ሆይ፥ እንዳዘዝኸኝ ተደርጎአል፥ ገናም ስፍራ አለ አለው።

23 ጌታውም ባሪያውን፦ ቤቱ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጣና ይገቡ
ዘንድ ግድ በላቸው፤ 24 እላችኋለሁና፥ ከታደሙት ከእነዚያ ሰዎች አንድ ስንኳ
እራቴን አይቀምስም አለው።

---

64 [ሉቃስ 14፥1] ኢየሱስ ቀደም ሲል ያወግዛቸው ወደነበሩ ፈሪሳውያን ቤት ለግብዣ መሄዱ የሚገርም ነው። (ሉቃስ 11፥37-54፥ ክፍል 107)። አሁን በግልጥ ለመረዳት እንደሚቻለው፥ ግብዣው የተዘጋጀው እርሱን ለመጠባበቅና (ቁ.1) የመወንጀያ ማስረጃ ለመፈለግ ነበር። አንድ ሕመምተኛ በሰንበት ዕለት በመፈወሱ ሰንበትን ሽሯል በማለት ሊይዙት ፈልገው ነበር።

65 [ሉቃስ 14፥25] የኢየሱስ የፖርያ ውስጥ አገልግሎት ብዙ ትኩረት ስቦ ነበር። ኢየሱስ መሢሕ ነው የሚለውና በሕዝቡ የተሰራጨው ዜና፥ በተለይም ከእግዚአብሔር መንግሥት መቃረብ ጋር በተገናኘ ሁኔታ የነበረው ብሔራዊ ችግር፥ ሰዉ ከኢየሱስ ጋር እንዲቆይ አደረገው። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በቀረበ ጊዜ በአጋጣሚው ይገኝ የነበረ በረከት ሁሉ እንዲያመልጣቸው አልፈለጉም። እውነተኛ ተከታዮቹ ሳይሆኑ፥ ከሕዝቡ ጋር የተቀላቀሉትን ተስፋ ሊያስቆርጣቸው ፈለገ። ደቀ መዛሙርቱም ከበድ ላለ የጠላትነት ታቃውሞ ራሳቸውን ማዘጋጀት ነበረባቸው።

## ◆ ክፍል 115. ደቀ መዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ

[ክፍል 54ሐ፥ 70ለ፥ 83ና 91ን ይመልከቱ]
- ምናልባት በፖርያ -

<u>ሉቃስ 14፡25-35</u>

25 ብዙም ሕዝብ[65] ከእርሱ ጋር ይሄዱ ነበር፥ ዘወር ብሎም እንዲህ አላቸው፦ 26
ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም
እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን
አይችልም። 27 ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን
አይችልም።

28 ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደ ሆነ
አስቀድሞ ተቀምጦ ከሳራውን የማይቈጥር ማን ነው? 29 ያለዚያ መሠረቱን
ቢመሠርት፥ ሊደመድመውም ቢያቅተው፥ ያዩት ሁሉ፦ 30 ይህ ሰው ሊሠራ ጀምሮ
ሊደመድመው አቃተው ብለው ሊዘብቱበት ይጀምራሉ።

31 ወይም ሌላውን ንጉሥ በጦርነት ሊጋጠም የሚሄድ፥ ከሁለት እልፍ ጋር
የሚመጣበትን በአንድ እልፍ ሊገናኝ የሚችል እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ የማያስብ
ንጉሥ ማን ነው? 32 ባይሆንስ ሌላው ገና ሩቅ ሳለ መልክተኞች ልኮ ዕርቅ ይለምናል።
33 እንግዲህ እንደዚሁ ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን
አይችልም።

34 ጨው መልካም ነው፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፈጣል? 35 ለምድር
ቢሆን ለፍግ መቈለያም ቢሆን አይረባም፤ ወደ ውጭ ይጥሉታል። የሚሰማ ጆሮ ያለው
ይስማ።

## ◆ ክፍል 116. ከኃጢአተኞች ጋር የተደረገ ግንኙነትን በመቀበል የተነገሩ ምሳሌዎች [ክፍል 91ን ይመልከቱ]

- ምናልባት በፖርያ -

<u>ሉቃስ 15፡1-32</u>

1 ቀራጮችና ኃጢአተኞችም ሁሉ ሊሰሙት ወደ እርሱ ይቀርቡ ነበር። 2
ፈሪሳውያንና ጻፎችም፦ ይህስ ኃጢአተኞችን ይቀበላል ከእነርሱም ጋር ይበላል ብለው
እርስ በርሳቸው አንጐራጐሩ።

3 ይህንም ምሳሌ ነገራቸው እንዲህ ሲል፦ 4 መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዱ
ቢጠፋ፥ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልገው
የማይሄድ ከእናንተ ማን ነው? 5 ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል፤
6 ወደ ቤትም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹን በአንድነት ጠርቶ፦ የጠፋውን
በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላቸዋል። 7 እላችኋለሁ፥ እንዲሁ
ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ
ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።

8 ወይም አሥር ድሪም ያላት አንድ ድሪም ቢጠፋባት፥ መብራት አብርታ
ቤትዋንም ጠርጋ እስክታገኘው ድረስ አጥብቃ የማትፈልግ ሴት ማን ናት? 9

(ሉቃስ 15፥ 1-32 የቀጠለ)

ባገኘችውም ጊዜ ወዳጆችዋንና ጐረቤቶችዋን በአንድነት ጠርታ፦ የጠፋውን ድሪሜን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ትላቸዋለች። 10 እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።

11 እንዲህም አለ፦ አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት። 12 ከእነርሱም ታናሹ አባቱን፦ አባቴ ሆይ፥ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ክፍል ስጠኝ አለው። ገንዘቡንም አካፈላቸው።

13 ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፥ ከዚያም እያባከነ ገዘቡን በተነ። 14 ሁሉንም ከከሰረ በኋላ በዚያች አገር ጽኑ ራብ ሆነ፥ እርሱም ይጨነቅ ጀመር። 15 ሄዶም ከዚያች አገር ሰዎች ከአንዱ ጋር ተዳበለ፥ እርሱም እሪያ ሊያሰማራ ወደ ሜዳ ሰደደው። 16 እሪያዎችም ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ይመኝ ነበር፥ የሚሰጠውም አልነበረም።

17 ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ፦ እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ። 18 ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና፦ አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ 19 ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ። 20 ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ።

እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው።

21 ልጁም፦ አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም አለው።

22 አባቱ ግን ባሪያዎቹን አለ፦ ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፥ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ፤ 23 የሰባውን ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፥ እንብላም ደስም ይበለን፤ 24 ይህ ልጄሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር።

25 ታላቁ ልጁ በእርሻ ነበረ፤ መጥቶም ወደ ቤት በቀረበ ጊዜ የመሰንቆና የዘፈን ድምፅ ሰማ፤ 26 ከብላቴናዎችም አንዱን ጠርቶ፦ ይህ ምንድር ነው? ብሎ ጠየቀ። 27 እርሱም፦ ወንድምህ መጥቶአልና በደኅና ስላገኘው አባትህ የሰባውን ፊሪዳ አረደለት አለው።

28 ተቈጣም ሊገባም አልወደደም፤ አባቱም ወጥቶ ለመነው። 29 እርሱ ግን መልሶ አባቱን፦ እነሆ፥ ይህን ያህል ዓመት እንደ ባሪያ ተገዝቼልሃለሁ ከትእዛዝህም ከቶ አልተላለፍሁም፤ ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጥቦት ስንኳ አልሰጠኸኝም፤ 30 ነገር ግን ገንዘብህን ከጋለሞቶች ጋር በልቶ ይህ ልጅህ በመጣ ጊዜ፥ የሰባውን ፊሪዳ አረድህለት አለው።

31 እርሱ ግን፦ ልጄ ሆይ፥ አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፥ ለእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው፤ 32 ዳሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ ሕያው ስለ ሆነ ጠፍቶም ነበር ስለ ተገኘ ደስ እንዲለን ፍሥሐም እንድናደርግ ይገባናል አለው።

## ♦ ክፍል 117ሀ. የገንዘብን ትክክለኛ አጠቃቀም ለማስተማር የተነገረ ምሳሌ [ክፍል 54ሰን ይመልከቱ]

**- ምናልባት በፖርያ -**

<u>ሉቃስ 16፥1-13</u>

1 ደግሞም ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፦ መጋቢ የነበረው አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ በእርሱ ዘንድ፦ ይህ ሰው ያለህን ይበትናል ብለው ከሰሱት። 2 ጠርቶም፦ ይህ የምሰማብህ ምንድር ነው? ወደ ፊት ለእኔ መጋቢ ልትሆን አትችልምና የመጋቢነትህን ሂሳብ አስረክበኝ አለው።

3 መጋቢውም በልቡ፦ ጌታዬ መጋቢነቱን ከእኔ ይወስዳልና ምን ላድርግ? ለመቈፈር ኃይል የለኝም፥ መለመንም አፍራለሁ። 4 ከመጋቢነቱ ብሻር በቤታቸው እንዲቀበሉኝ የማደርገውን አውቃለሁ አለ።

5 የጌታውንም ባለ ዕዳዎች እያንዳንዳቸውን ጠርቶ የፊተኛውን፦ ለጌታዬ ምን ያህል ዕዳ አለብህ? አለው።

6 እርሱም፦ መቶ ማድጋ ዘይት አለ። ደብዳቤህን እንካ ፈጥነህም ተቀምጠህ አምሳ ብለህ ጻፍ አለው።

7 በኋላም ሌላውን፦ አንተስ ስንት ዕዳ አለብህ? አለው። እርሱም፦ መቶ ጫን ስንዴ አለ። ደብዳቤህን እንካ ሰማንያ ብለህም ጻፍ አለው።

8 ጌታውም ዓመፀኛውን መጋቢ በልባምነት ስላደረገ አመሰገነው የዚህ ዓለም ልጆች ለትውልዳቸው ከብርሃን ልጆች ይልቅ ልባሞች ናቸውና። 9 እኔም እላችኋለሁ፥ የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ፥ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ[66] አድርጉ።

10 ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው፥ ከሁሉ በሚያንስም የሚያምፅ በብዙ ደግሞ ዓመፀኛ ነው። 11 እንግዲያስ በዓመፃ ገንዘብ ካልታመናችሁ፥ እውነተኛውን ገንዘብ ማን አደራ ይሰጣችኋል? 12 በሌላ ሰው ገንዘብ ካልታመናችሁ፥ የእናንተን ማን ይሰጣችኋል?

13 ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ባርያ ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላልና ሁለተኛውንም ይወዳል፥ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።

---

66 [ሉቃስ 16፥9] ኢየሱስ የደገፈው ሐብትን ለወደፊት ጥቅምና ለቀና ተግባር የማዋሉን ጥበብ እንጂ፥ ሐብቱን ያገኘበትን ታማኝነት የጎደለበት ሁኔታ አይደለም። ገንዘብ በገንዘብነቱ ኃጢአት የለበትም። ለሌሎች በረከት ሊያመጣና ወደ ዘላለም መኖሪያ እንዲገቡ ሊያደርግ በሚችልበት ሁኔታ እንዲያገለግል ለማድረግ ይቻላል። ይህን በማድረግም የሚጠፋ ሐብት ወደሰማያዊ ሐብትነት ሊለወጥ ይችላል።

67 [ሉቃስ 16፥14] ይህ በጣም እምቅ የሆነ አንቀጽ (ቁጥር 14-18) የባለጸጋውንና የአልአዛርን ታሪክ ነው የሚያስተዋውቀው። ኢየሱስ ገንዘብን አስመልክቶ ለደቀ መዛሙርቱ በሚገልጥበት ጊዜ (ሉቃስ 16፥13፥ ክፍል 117ሀ) ሰላሳዩት ቁጣ ወይም ተቃውሞ ንፉጎቹን ፈሪሳውያን ተናገራቸው። ተቃውሞው እግዚአብሔር ያበለጸገን ሕጉን በጥንቃቄ በመፈጸማችን ነው ከሚለው እምነታቸው አንጻር ነበር። ውጫዊውን ሕግ የማክበራቸው ሁኔታ እግዚአብሔርን አላረካውም (ቁ.15)፤ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደ መግቢያ ሊያደርጉት ሞከሩ (ቁ. 16)። ፍቺን መፍቀድን በመሰለ ባሕል አማካይነት ሕግን በመሻር ሊለወጥ የማይችል ሁኔታን ለመለወጥ ሞከሩ (ቁ.17-18)። ቀጥሎ ያለው ታሪክ እንደሚያመለክተው፥ ባለጸግነት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የማግኘት ምልክት አልነበረም።

## ♦ ክፍል 117ለ. የሀብትን አደገኛነት ለማስተማር የተነገረ ታሪክ

[ክፍል 54መ፥ 54ሠና 122ን ይመልከቱ]

-ምናልባት በፖርያ-

ሉቃስ 16፡14-31

14 ገንዘብንም የሚወዱ ፈሪሳውያን[67] ይህን ሁሉ ሰምተው ያፌዙበት ነበር። 15 እንዲህም አላቸው፦ ራሳችሁን በሰው ፊት የምታጸድቁ እናንተ ናችሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችሁን ያውቃል፤ በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኵሰት ነውና።

16 ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ነበሩ፤ ከዚያ ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል፤ ሁሉም ወደ እርስዋ በኃይል ይገቡባታል። 17 ነገር ግን ከሕግ አንዲት ነጥብ ከምትወድቅ ሰማይና ምድር ሊያልፍ ይቀላል።

18 ሚስቱንም የሚፈታ ሁሉ ሌላይቱንም የሚያገባ ያመነዝራል፥ ከባልዋም የተፈታችውን የሚያገባ ያመነዝራል።

19 ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር። 20 አልዓዛርም[68] የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥ 21 ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሉቹን ይልሱ ነበር።

22 ድሀውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ። 23 በሲኦልም[69] በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ። 24 እርሱም እየጮኸ፦ አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ።

25 አብርሃም ግን፦ ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ። 26 ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።

27 እርሱም፦ እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤ 28 እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ።

29 አብርሃም ግን፦ ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይስሙ አለው።

30 እርሱም፦ አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ።

31 ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።

---

68 [ሉቃስ 16፡20] ኢየሱስ ከዚህ ሌላ በየትኛዎቹም ምሳሌዎቹ የሰው ስም ጠቅሶ አያውቅም። ይህ ታሪክ ሁልጊዜ እንደ ምሳሌ ቢጠቀስም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትም ስፍራ ምሳሌ አልተባለም። በመሆኑም በትክክል የሆነ ነገር፥ ወይም ምሳሌ ነው ብሎ በእርግጠኝነት ለመናገር አይቻልም።

## ♦ ክፍል 117ሐ. ደቀ መዝሙርትነትን የሚመለከቱ አራት ትምህርቶች [ክፍል 91ን ይመልከቱ]

- ምናልባት በፖርያ -

<u>ሉቃስ 17፥1-10</u>

1 ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ፦ መሰናክል ግድ ሳይመጣ አይቀርም፥ ነገር ግን
መሰናክሉን ለሚያመጣው ወዮለት፤[70] 2 ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን ከማሰናከል
ይልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይጠቅመው ነበር። 3
ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።

ወንድምህ ቢበድልህ ገሥጸው፥ ቢጸጸትም ይቅር በለው። 4 በቀንም ሰባት ጊዜ እንኳ
ቢበድልህ በቀንም ሰባት ጊዜ፦ ተጸጸትሁ እያለ ወደ አንተ ቢመለስ፥ ይቅር በለው።

5 ሐዋርያትም ጌታን፦ እምነት ጨምርልን አሉት።

6 ጌታም አለ፦ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ሾላ፦
ተነቅለህ ወደ ባሕር ተተከል ብትሉት፥ ይታዘዝላችሁ ነበር።

7 ከእናንተም የሚያርስ ወይም ከብትን የሚጠብቅ ባሪያ ያለው፥ ከእርሻ ሲመለስ፦
ወዲያው ቅረብና በማዕድ ተቀመጥ የሚለው ማን ነው? 8 የምበላውን እራቴን
አሰናዳልኝ፥ እስክበላና እስክጠጣ ድረስ ታጥቀህ አገልግለኝ፥ በኋላም አንተ ብላና
ጠጣ የሚለው አይደለምን? 9 ያንን ባሪያ ያዘዘውን ስላደረገ ያመሰግነዋልን? 10
እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፦ የማንጠቅም ባሪያዎች
ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ።

## ♦ ክፍል 118ሀ. የአልዓዛር ሕመምና ሞት

- ከፖርያ ወደ ቢታንያ፥ ኢየሩሳሌም አጠገብ -

<u>ዮሐንስ 11፥1-16</u>

1 ከማርያምና ከእኅትዋ ከማርታ መንደር ከቢታንያ የሆነ አልዓዛር የሚባል አንድ
ሰው ታሞ ነበር። 2 ማርያምም ጌታን ሽቱ የቀባችው እግሩንም በጠጕርዋ ያበሰችው
ነበረች፤ ወንድምዋም አልዓዛር ታሞ ነበር። 3 ስለዚህ እኅቶቹ ጌታ ሆይ፥ እነሆ
የምትወደው ታሞአል ብለው ወደ እርሱ ላኩ።

4 ኢየሱስም ሰምቶ፦ ይህ ህመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ስለ
እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም አለ። 5 ኢየሱስም ማርታንና
እኅትዋን አልዓዛርንም ይወድ ነበር። 6 እንደ ታመመም በሰማ ጊዜ ያን ጊዜ በነበረበት
ስፍራ ሁለት ቀን ዋለ፤

---

[69] [ሉቃስ 16፥23] "ሲኦል" (በዕብራይስጥ 'ሺኦል'፥ በግሪክ 'ሄይዲስ') ነፍስ ከአካል ከተለየች በኋላ የምትሄድበትን ቦታ የሚያመለክት ነው። ይህም በሁለት ይከፈላል፦ አንደኛው የእግዚአብሔር ቤተሰብ ያልሆኑ ሙታን በታላቁ ነጭ ዙፋን ፊት ለፍርድ እስኪቀርቡ (ራእይ 20፥11-15) ድረስ በጊዜያዊ ቅጣት የሚቆዩበት ነው። በሌላ በኩል፥ ከክርስቶስ ትንሣኤ በፊት የተከናወነው ሁኔታ እንደሚያመለክተው፥ የእግዚአብሔር ሰዎች ከሲኦል ወዲያ ባለ ሥፍራ በሰላማዊ ዕረፍት ላይ ይቆያሉ (ሉቃስ 16፥26)። ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው መካከል በነበረው ጊዜ ወደ ሲኦል ወርዶ ነበር (ሐዋ. 2፥27፥ 31)። ከትንሣኤው በኋላ ግን የኢየሱስ የሆኑት ሁልጊዜ ከርሱ ጋር ይኖራሉ (ፊልጵ. 1፥23)።

(ዮሐንስ 11፥ 1-16 የቀጠለ)

7 ከዚህም በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ:- ወደ ይሁዳ ደግሞ እንሂድ አላቸው።

8 ደቀ መዛሙርቱ:- መምህር ሆይ፥ አይሁድ[71] ከጥቂት ጊዜ በፊት ሊወግሩህ ይፈልጉ ነበር፥ ደግሞም ወደዚያ ትሄዳለህን? አሉት።

9 ኢየሱስም መልሶ:- ቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት አይደለምን? በቀን የሚመላለስ ቢኖር የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና አይሰናከልም፤ 10 በሌሊት የሚመላለስ ቢኖር ግን ብርሃን በእርሱ ስለ ሌለ ይሰናከላል አላቸው።

11 ይህን ተናገረ፤ ከዚህም በኋላ:- ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቶአል፤ ነገር ግን ከእንቅልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ አላቸው።

12 እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ:- ጌታ ሆይ፥ ተኝቶስ እንደ ሆነ ይድናል አሉት። 13 ኢየሱስስ ስለ ሞቱ ተናግሮ ነበር፤ እነርሱ ግን ስለ እንቅልፍ መተኛት እንደ ተናገረ መሰላቸው።

14 እንግዲህ ያን ጊዜ ኢየሱስ በግልጥ:- አልዓዛር ሞተ፤ 15 እንድታምኑም በዚያ ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ወደ እርሱ እንሂድ አላቸው።

16 ስለዚህ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ለባልንጀሮቹ ለደቀ መዛሙርት:- ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሂድ አለ።

## ♦ ክፍል 118ለ. አልዓዛርን ከሞት ማስነሣት

- ቢታንያ፥ ኢየሩሳሌም አጠገብ -

ዮሐንስ 11፥ 17-44

17 ኢየሱስም በመጣ ጊዜ በመቃብር እስከ አሁን አራት ቀን ሆኖት አገኘው። 18 ቢታንያም አሥራ አምስት ምዕራፍ ያህል ለኢየሩሳሌም ቅርብ ነበረች። 19 ከአይሁድም ብዙዎች ስለ ወንድማቸው ሊያጽናኑአቸው ወደ ማርታና ወደ ማርያም መጥተው ነበር። 20 ማርታም ኢየሱስ እንደ መጣ በሰማች ጊዜ ልትቀበለው ወጣች፤ ማርያም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር።

21 ማርታም ኢየሱስን:- ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር፤ 22 አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ አለችው።

23 ኢየሱስም:- ወንድምሽ ይነሣል አላት።

24 ማርታም:- በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው።

25 ኢየሱስም:- ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው

---

70 [ሉቃስ 17፥ 1] ከአራቱ ትምህርቶች የመጀመሪያው ሌሎችን እንዳያሰናክሉ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ (ቁጥር 1-2) ነው። ሌሎቹ ሦስት ይቅርታ የሚጠይቁ ወንድሞችን ይቅር የማለት ግዴታን (ቁጥር 3-4)፥ የእምነት ኃይልን (ቁጥር 5-6)፥ እና ልዩ ክብርን ለማግኘት የራስ መልካም ሥራ በቂ አለመሆኑን (ቁጥር 7-10) የሚመለከቱ ናቸው።

71 [ዮሐ. 11፥8] ቢታኒያ ከኢየሩሳሌም ወደ ሦስት ኪሎ ሜትሮች ያህል ብቻ የምትርቅ በመሆኗ፥ በቅርቡ ኢየሩሳሌም ውስጥ ኢየሱስን በድንጋይ ለመውገር የተደረገውን ሙከራ ደቀ መዛሙርቱ አስታወሱ (ዮሐ. 10፥31፥ ክፍል 111)። የኢየሱስ መልስ፥ በገጠመው ዕድል እንደማንኛውም ሰው መጠቀም ወይም ዕድሉን ማጣት መሆኑን የሚገልጥ ነበር። አደጋ ዓላማን የሚያግድ መሆን አልነበረበትም።

(ዮሐንስ 11፡17-44 የቀጠለ)

ይሆናል፤ 26 ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን
ታምኚያለሽን? አላት።

27 እርስዋም፡-[72] አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ
የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው።

28 ይህንም ብላ ሄደች እኅትዋንም ማርያምን በስውር ጠርታ፡- መምህሩ መጥቶአል
ይጠራሽማል አለቻት። 29 እርስዋም በሰማች ጊዜ ፈጥና ተነሣች ወደ እርሱም መጣች፤
30 ኢየሱስም ማርታ በተቀበለችበት ስፍራ ነበረ እንጂ ገና ወደ መንደሩ አልገባም
ነበር። 31 ሲያጽናኑአት ከእርስዋ ጋር በቤት የነበሩ አይሁድም ማርያም ፈጥና እንደ
ተነሣችና እንደ ወጣች ባዩ ጊዜ፥ ወደ መቃብር ሄዳ በዚያ ልታለቅስ መስሎአቸው
ተከተሉአት።

32 ማርያምም ኢየሱስ ወዳለበት መጥታ ባየችው ጊዜ በእግሩ ላይ ወድቃ፡- ጌታ
ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር አለችው።

33 ኢየሱስም እርስዋ ስታለቅስ ከእርስዋም ጋር የመጡት አይሁድ ሲያለቅሱ አይቶ
በመንፈሱ አዘነ በራሱም ታወከ፤ 34 ወዴት አኖራችሁት? አለም።

እነርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ መጥተህ እይ አሉት።

35 ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ።

36 ስለዚህ አይሁድ፡- እንዴት ይወደው እንደ ነበረ እዩ አሉ።

37 ከእነርሱ ግን አንዳንዶቹ፡- ይህ የዕውሩን ዓይኖች የከፈተ ይህን ደግሞ እንዳይሞት
ያደርግ ዘንድ ባልቻለም ነበርን? አሉ።

38 ኢየሱስም በራሱ አዝኖ ወደ መቃብሩ መጣ፤ እርሱም ዋሻ ነበረ፤ ድንጋይም
ተገጥሞበት ነበር። 39 ኢየሱስ፡- ድንጋዩን አንሡ አለ።

የሞተውም እኅት ማርታ፡- ጌታ ሆይ፥ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል
አለችው።

40 ኢየሱስ፡- ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታዪ አልነገርሁሽምን? አላት።

41 ድንጋዩንም አነሡት። ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ፡- አባት ሆይ፥ ስለ
ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። 42 ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ፤ ነገር ግን አንተ እንደ
ላከኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለ ቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ አለ።

43 ይህንም ብሎ በታላቅ ድምፅ፡- አልዓዛር ሆይ፥ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ። 44
የሞተውም[73] እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ፤ ፊቱም በጨርቅ እንደ
ተጠመጠመ ነበር።

ኢየሱስም፡- ፍቱትና ይሂድ ተዉት አላቸው።

---

[72] [ዮሐ. 11፡27] ማርታ የቱንም ያህል ጥፋተኛ ብትሆን (ሉቃስ 10፡41፥ ክፍል 104) በኢየሱስ የምታምንና የምታፈቅረው ሰው ነበረች። እዚህ የተጠቀሰውና ሦስት እጥፍ የሆነው ንስሐዋ፥ አንድ ሰው ስለ ኢየሱስ ሊኖረው የሚገባውን ከሁሉ የላቀ አመለካከት ይወክላል።

[73] [ዮሐ. 11፡44] ስለዚህ ታላቅ ተአምር ሌሎቹ ወንጌላት (ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ) ምንም አልጠቀሱም። በአንዳንድ ምክንያቶች የእነዚህ ወንጌላት ጸሐፊዎች ኢየሩሳሌም ውስጥ የተደረጉ ታላላቅ ተአምራትን አልመዘገቧቸውም (ክፍል 49ሀ እና 100ሀ)። ከጌታ ሕማማት ሳምንት ቀደም ሲል በነበሩት ሁለት ወራት ስለተከናወኑ ነገሮችም እንዲሁ አልተናገሩም። የተመዘገቡት ሁለት ትንሣኤዎች (ክፍል 56፥ 67) ኢየሱስ በሞት ላይ ያለውን ኃይል ለማመልከት በቂ ናቸው ብለው ሳያስቡ አልቀሩም።

## ♦ ክፍል 119. ኢየሱስ ይገደል ዘንድ የአይሁድ መሪዎች ውሳኔ

- ኢየሩሳሌምና ኤፍሬም[74]፥ በምድረ በዳው አጠገብ -

ዮሐንስ 11፡45-54

45 ስለዚህ ወደ ማርያም ከመጡት፥ ኢየሱስም ያደረገውን ካዩት ከአይሁድ ብዙዎች
በእርሱ አመኑ፤ 46 ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን ወደ ፈሪሳውያን ሄደው ኢየሱስ
ያደረገውን ነገሩአቸው። 47 እንግዲህ የካህናት አለቆችና[75] ፈሪሳውያን ሸንጎ
ሰብስበው፡-

ምን እናድርግ? ይህ ሰው ብዙ ምልክቶች ያደርጋልና። 48 እንዲሁ ብንተወው ሁሉ
በእርሱ ያምናሉ፤ የሮሜም ሰዎች መጥተው አገራችንን ወገናችንንም ይወስዳሉ አሉ።

49 በዚያችም ዓመት ሊቀ ካህናት የነበረ ቀያፋ የሚሉት ከእነርሱ አንዱ፡- እናንተ
ምንም አታውቁም፤ 50 ሕዝቡም ሁሉ ከሚጠፋ አንድ ሰው ስለ ሕዝቡ ይሞት ዘንድ[76]
እንዲሻለን አታስቡም አላቸው።

51 ይህንም የተናገረ ከራሱ አይደለም፥ ነገር ግን በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ነበረና
ኢየሱስ ስለ ሕዝቡ ሊሞት እንዳለው ትንቢት ተናገረ፤ 52 ስለ ሕዝቡም ሁሉ
አይደለም፥ ነገር ግን የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች ደግሞ በአንድነት
እንዲሰበስባቸው ነው እንጂ። 53 እንግዲህ ከዚያ ቀን ጀምረው ሊገድሉት ተማከሩ።[77]

54 ከዚያ ወዲያም ኢየሱስ በአይሁድ መካከል ተገልጦ አልተመላለሰም፤ ነገር ግን
ከዚያ በምድረ በዳ አጠገብ ወዳለች ምድር፥ ኤፍሬም ወደምትባል ከተማ ሄደ፤
በዚያም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ።

---

[74] ኤፍሬም የሚባለው ሥፍራ ምናልባት ከይሁዳ በስተሰሜን ያለውና ወደ ዮርዳኖስ ሸለቆ የሚያመራው ኀርበጥባጣ አካባቢ ሳይሆን አይቀርም።

[75] [ዮሐ. 11፡47] የካህናት አለቆች ኢየሱስን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እስከመጨረሻው በመቃወም ረገድ መሪ የሆኑት የሰዱቃውያን የሥልጣን አባላት ነበሩ (ፈሪሳውያን አሁን ሁለተኛ ተቃዋሚዎች ሆነዋል)። የሞተ ሰው መነሣት ኢየሩሳሌም ውስጥ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ እንደመሆኑ፥ ሰዱቃዊ ትምህርታቸው ትንሣኤን የሚክድ በመሆኑ ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም።

[76] [ዮሐ. 11፡50] ቀያፋ እንዳለው፥ የቃላቱ ትርጉም አይሁዳውያን በሮም ቅኝ ግዛት ሥር ሥልጣናቸውን ያቆዩ ዘንድ፥ ልዩ መብት ላላቸው አይሁዳውያን ሲባል ኢየሱስ መሞት አለበት የሚሉ ነበሩ። ቀያፋ ሊቀካህናት በመሆኑ፥ እግዚአብሔር ይህንኑ መሠረት በማድረግ ራስ ወዳድነቱን ፍጹም ለተለየ ዓላማ የተጠቀመበት መሆኑን ነው ዮሐንስ የተመለከተው። ሊቀካህኑ የክርስቶስን ለእስራኤልና በርሱ ሊያምኑ ላሉት አሕዛብ የሚሞተውን የምትክነት ሞት ሳይታወቀው ተነበየ (ቁጥር 51-52፤ ዮሐ. 10፡16፥ ክፍል 101ሀ)።

[77] [ዮሐ. 11፡53] ይህ ሁኔታ ቀደም ሲል ሸንጎው ምንም እንኳን በመደበኛ ስብሰባ ባይሆን፥ ኢየሱስ እንዲገደል ያጸደቀውን (ቁ.47) ውሳኔ ያመለክታል። በቀያፋ ምክር መሠረት እነዚህ መሪዎች ይህን ጠላት የሆነ ሥልጣናዊ ሰው ከሚያስወግዱበት ውሳኔ ላይ ደረሱ።

# > ወደ ኢየሩሳሌም በተደረገ የመጨረሻ ጉዞ ላይ የተቀረቡ ትምህርቶች <

## ♦ ክፍል 120ሀ. ጌታ በሰማርያና በገሊላ በማለፍ ላይ ሳለ አሥር ለምጻሞችን መፈወሱ

- ሰማርያና ገሊላ -

ሉቃስ 17፡11-21

11 ወደ ኢየሩሳሌምም ሲሄድ በገሊላና በሰማርያ መካከል አለፈ። 12 ወደ አንዲት
መንደርም ሲገባ በሩቅ የቆሙት አሥር ለምጻሞች ተገናኙት፤ 13 እነርሱም
እየጮኹ፡- ኢየሱስ ሆይ፥ አቤቱ፥ ማረን አሉ።

14 አይቶም፡- ሂዱ፥ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ አላቸው።

15 እነሆም፥ ሲሄዱ ነጹ። ከእነርሱም አንዱ እንደ ተፈወሰ ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ
እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ፥ 16 እያመሰገነውም በእግሩ ፊት በግንባሩ ወደቀ፤
እርሱም ሳምራዊ ነበረ።

17 ኢየሱስም መልሶ፡- አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ? 18 ከዚህ ከልዩ
ወገን በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብሩ የተመለሱ አልተገኙም አለ። 19 እርሱንም፡-
ተነሥና ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው።

20 ፈሪሳውያንም፡- የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች ብለው ቢጠይቁት፥
መልሶ፡- የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፤ 21 ደግሞም፡- እንኋት
በዚህ ወይም፡- እንኋት በዚያ አይሉአትም። እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት
በመካከላችሁ ናትና አላቸው።

## ♦ ክፍል 120ለ. ስለ ሰው ልጅ ምጽአት የተሰጡ መግለጫዎች

[ክፍል 139ሐና 139ሠን ይመልከቱ]

- ሰማርያና ገሊላ -

ሉቃስ 17፡22-37

22 ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ፡- ከሰው ልጅ ቀኖች አንዱን ልታዩ
የምትመኙበት ወራት ይመጣል አታዩትምም። 23 እነርሱም፡- እነሆ በዚህ፥ ወይም፡-
እነሆ በዚያ ይሉአችኋል፤ አትሂዱ አትከተሉአቸውም። 24 መብረቅ በርቆ ከሰማይ
በታች ካለ ከአንድ አገር ከሰማይ በታች ወዳለው ወደ ሌላ አገር እንደሚያበራ፥ የሰው
ልጅ በቀኑ እንዲህ ይሆናል። 25 አስቀድሞ ግን ብዙ መከራ እንዲቀበል ከዚህም
ትውልድ እንዲጣል ይገባዋል።

26 በኖኅ ዘመንም እንደ ሆነ፥ በሰው ልጅ ዘመን ደግሞ እንዲሁ ይሆናል። 27 ኖኅ
ወደ መርከብ እስከ ገባበት ቀን ድረስ፥ ይበሉና ይጠጡ ያገቡና ይጋቡም ነበር፥
የጥፋት ውኃም መጣ ሁሉንም አጠፋ።

28 እንዲሁ በሎጥ ዘመን እንደ ሆነ፤ ይበሉ ይጠጡም ይገዙም ይሸጡም ይተክሉም
ቤትም ይሠሩ ነበር፤ 29 ሎጥ ከሰዶም በወጣበት ቀን ግን ከሰማይ እሳትና ዲን ዘነበ
ሁሉንም አጠፋ።

## ♦ ክፍል 122. በፍቺ ጉዳይ ላይ ከፈሪሳውያን አስተምህሮ ጋር የተፈጠረ ግጭት [ክፍል 54ሐና 117ለን ይመልከቱ]

- ፖርያ -

<u>ማቴዎስ 19፡1-12</u>

1 ኢየሱስም ይህን ነገር ከፈጸመ በኋላ፥
ከገሊላ ሄዶ ወደ ይሁዳ አውራጃ ወደ
ዮርዳኖስ ማዶ መጣ። 2 ብዙ ሕዝብም
ተከተሉት፥ በዚያም ፈወሳቸው።

3 ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ ቀረቡና
ሲፈትኑት፦ ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ
ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት።

4 እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ፦ ፈጣሪ
በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥
[ዘፍጥረት 1፡27፥ 5፡2] 5 አለም፦
ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥
ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም
አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል
አላነበባችሁምን? 6 ስለዚህ አንድ ሥጋ
ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም።
እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው
አይለየው።

7 እነርሱም፦ እንኪያስ ሙሴ የፍችዋን
ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈቱአት ስለ ምን
አዘዘ?[81] አሉት። [ዘዳግም 24፡1-4]

<u>ማርቆስ 10፡1-12</u>

1 ከዚያም ተነሥቶ በዮርዳኖስ ማዶ ወደ
ይሁዳ አገር መጣ፥ ደግሞም ብዙ ሰዎች
ወደ እርሱ ተሰበሰቡ እንደ ልማዱም
ደግሞ ያስተምራቸው ነበር።

2 ፈሪሳውያንም ቀርበው፦ ሰው
ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? ብለው
ሊፈትኑት ጠየቁት።

3 እርሱ ግን መልሶ፦ ሙሴ ምን
አዘዛችሁ? አላቸው።

4 እነርሱም፦ ሙሴስ የፍችዋን ጽሕፈት
ጽፎ እንዲፈታት ፈቀደ አሉ። [ዘዳግም
24፡1-4]

5 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦
ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ይህችን ትእዛዝ
ጻፈላችሁ። 6 ከፍጥረት መጀመሪያ ግን
እግዚአብሔር ወንድና ሴት አደረጋቸው
[ዘፍጥረት 1፡27፥ 5፡2]፤ 7 ስለዚህ ሰው
አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር
ይተባበራል፥ 8 ሁለቱም አንድ ሥጋ
ይሆናሉ [ዘፍጥረት 2፡24]፤ ስለዚህ አንድ
ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት
አይደሉም። 9 እግዚአብሔር ያጣመረውን
እንግዲህ ሰው አይለየው።

10 በቤትም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ
ስለዚህ ነገር ጠየቁት።

---

[79] [ሉቃስ 18፡8] ኢየሱስ ባለፈው ክፍል ተነሥቶ የነበረውን ጉዳይ በመቀጠል (ክፍል 120ለ) የመመለሻ ጊዜውን መዘግየት በተመለከተ ደቀ መዛሙርቱን ያዘጋጅ ጀመር። ከምሳሌው የተማሩት፥ ፍርድን በአፋጣኝ በምድር ሊያሰፍን እንደሚመጣ እርግጠኞች ሆነው በእምነትና በጸሎት እንዲበረቱ እንጂ፥ በመዘግየቱ ተስፋ መቁረጥ የሌለባቸው መሆኑን ነው።

[80] [ሉቃስ 18፡9] ምሳሌው ምናልባት ቀደም ሲሉ የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ እንደምትመጣ ለጠየቁ (ሉቃስ 17፡20፥ ክፍል 120ሀ) ፈሪሳውያን የተነገረ ሳይሆን አይቀርም። እብሪታቸው ጸሎታቸው እንዳይሰማ አገደ። በሌላ መልኩ ግን እንደ ቀራጩ ያሉት ሰዎች ከትሕትናቸው የተነሣ ጸሎታቸው ተሰማ።

(ማቴዎስ 19፡ 1-12 የቀጠለ)

8 እርሱም፡- ሙሴስ ስለ ልባችሁ
ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ
ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ
አልነበረም። 9 እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ
ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ
ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥
የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል
አላቸው።

10 ደቀ መዛሙርቱም፡- የባልና የሚስት
ሥርዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት
አይጠቅምም አሉት።

11 እርሱ ግን፡- ይህ ነገር ለተሰጣቸው
ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም፤ 12 በእናት
ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥
ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፥ ስለ
መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ
ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል
ይቀበለው አላቸው።

(ማርቆስ 10፡ 1-12 የቀጠለ)

11 እርሱም፡- ሚስቱን ፈትቶ ሌላ
የሚያገባ ሁሉ በእርስዋ ላይ ያመነዝራል፤
12 እርስዋም ባልዋን ፈትታ ሌላ ብታገባ
ታመነዝራለች አላቸው።

## ♦ ክፍል 123. ከመንግሥተ ሰማያት ጋር በተዛመደ ሁኔታ በምሳሌነት የቀረቡ ትንንሽ ልጆች [ክፍል 90ን ይመልከቱ]

- ፖርያ -

ማቴዎስ 19፡ 13-15

13 በዚያን ጊዜ እጁን
እንዲጭንባቸውና
እንዲጸልይ ሕፃናትን ወደ
እርሱ አመጡ፤ ደቀ
መዛሙርቱም
ገሠጹአቸው።

14 ነገር ግን ኢየሱስ፡-
ሕፃናትን ተዉአቸው፥
ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ
አትከልክሉአቸው፤
መንግሥተ ሰማያት

ማርቆስ 10፡ 13-16

13 እንዲዳስሳቸውም
ሕፃናትን ወደ እርሱ
አመጡ፤ ደቀ
መዛሙርቱም
ያመጡአቸውን
ገሠጹአቸው። 14 ኢየሱስ
ግን አይቶ ተቈጣና፡-
ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ
ዘንድ ተዉ
አትከልክሉአቸው፤
የእግዚአብሔር መንግሥት

ሉቃስ 18፡ 15-17

15 እንዲዳስሳቸውም
ሕፃናትን ደግሞ ወደ እርሱ
አመጡ፤ ደቀ
መዛሙርቱም አይተው
ገሠጹአቸው። 16 ኢየሱስ
ግን ሕፃናትን ወደ እርሱ
ጠርቶ፡- ሕፃናት ወደ እኔ
ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው
አትከልክሉአቸውም፤
የእግዚአብሔር መንግሥት
እንደ እነዚህ ላሉት ናትና።

81 [ማቴ. 19፡7] ኢየሱስ ጋብቻ መፍረስ የሌለበት ስለመሆኑ ባለው አመለካከት የተነሣ፥ ጠላቶቹ የሙሴን አስተምህሮ የሚቃረን ትምህርት ሲያስተምር ያዝነው ብለው ነበር። እርሱ ግን ሙሴ ፍቺን የፈቀደበት ምክንያት እስራኤላውያን ከግብጽ ባርነት እንደወጡ የሥነ-ምግባር እውቀት ስላልነበራቸው መሆኑን ገልጦ ቅራኔውን በቀላሉ አስወገደው። ፈሪሳውያን ዘፍጥረት 2፡24 ላይ ከተጠቀሰው የጋብቻ ባሕል ይልቅ፥ ዘዳግም 24፡1-4 ላይ የተጻፈውን ለማክበር ትኩረት ሰጡ። ሙሴ አንደኛውን አዘዘ፤ (ማር. 10፡3) የፈቀደው ግን የኋለኛውን (ማቴ. 19፡8) ብቻ ነው።

| (ማቴዎስ 19፡ 13-15 የቀጠለ) | (ማርቆስ 10፡ 13-16 የቀጠለ) | (ሉቃስ 18፡ 15-17 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| እንደነዚህ ላሉ ናትና አለ፤<br>15 እጁንም ጫነባቸውና ከዚያ ሄደ። | እንደነዚህ ላሉት ናትና። 15 እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው። 16 አቀፋቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው። | 17 እውነት እላችኋለሁ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አለ። |

## ♦ ክፍል 124ሀ. ብልጽግናና መንግሥት

[ክፍል 113ሀና 113ለን ይመልከቱ]

- ፖርያ -

| ማቴዎስ 19፡ 16-30 | ማርቆስ 10፡ 17-31 | ሉቃስ 18፡ 18-30 |
|---|---|---|
| 16 እነሆም፥ አንድ ሰው ቀርቦ፦ መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? አለው። | 17 እርሱም በመንገድ ሲወጣ አንድ ሰው ወደ እርሱ ሮጦ ተንበረከከለትና፦ ቸር መምህር ሆይ፥ የዘላለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው። | 18 ከአለቆችም አንዱ፦ ቸር መምህር፥ የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው። |
| 17 እርሱም፦ ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ አለው።<br>18 እርሱም፦ የትኞችን? አለው።<br>ኢየሱስም፦ አትግደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ 19 አባትህንና እናትህን አክብር፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው። [ዘጸአት 20፡ 12-16፤ ዘዳግም 5፡ 16-20] | 18 ኢየሱስም፦ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም። 19 ትእዛዛትን ታውቃለህ፤ አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አታታልል፥ አባትህንና እናትህን አክብር አለው። [ዘጸአት 20፡ 12-16፤ ዘዳግም 5፡ 16-20] | 19 ኢየሱስም፦ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም። 20 ትእዛዛቱን ታውቃለህ፥ አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አባትህንና እናትህን አክብር አለው። [ዘጸአት 20፡ 12-16፤ ዘዳግም 5፡ 16-20] |
| 20 ጐበዙም፦ ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ፥ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው? አለው። | 20 እርሱም መልሶ፦ መምህር ሆይ፥ ይህን ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ አለው። | 21 እርሱም፦ ይህን ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ አለ። |

(ማቴዎስ 19፥ 16-30 የቀጠለ)

21 ኢየሱስም፦ ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው።

22 ጐበዙም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ።

23 ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ለባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ጭንቅ ነው።

24 ዳግመኛም እላችኋለሁ፥ ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል አለ።

25 ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው እጅግ ተገረሙና፦[82] እንኪያስ ማን ሊድን ይችላል? አሉ።

26 ኢየሱስም እነርሱን ተመልክቶ፦ ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን

(ማርቆስ 10፥ 17-31 የቀጠለ)

21 ኢየሱስም ወደ እርሱ ተመልክቶ ወደደውና፦ አንድ ነገር ጐደለህ፤ ሂድ፥ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መስቀሉንም ተሸክመህ ና፥ ተከተለኝ አለው።

22 ነገር ግን ስለዚህ ነገር ፊቱ ጠቈረ፥ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነም ሄደ።

23 ኢየሱስም ዘወር ብሎ አይቶ ደቀ መዛሙርቱን፦ ገንዘብ ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ይሆ ናል አላቸው።

24 ደቀ መዛሙርቱም እነዚህን ቃሎች አደነቁ። ኢየሱስም ደግሞ መልሶ፦ ልጆች ሆይ፥ በገንዘብ ለሚታመኑ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ነው። 25 ባለ ጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል አላቸው።

26 እነርሱም ያለ መጠን[82] ተገረሙና እርስ በርሳቸው፦ እንግዲያ ማን ሊድን ይችላል? ተባባሉ።

27 ኢየሱስም

(ሉቃስ 18፥ 18-30 የቀጠለ)

22 ኢየሱስም ይህን ሰምቶ፦ አንዲት ገና ቀርታሃለች፤ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው።

23 እርሱ ግን ይህን ሰምቶ እጅግ ባለ ጠጋ ነበርና ብዙ አዘነ። 24 ኢየሱስም ብዙ እንዳዘነ አይቶ፦ ገንዘብ ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ይሆናል።

25 ባለ ጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ሊገባ ይቀላል አለ።

26 የሰሙትም፦ እንግዲህ ማን ሊድን ይችላል? አሉ።

27 እርሱ ግን፦ በሰው ዘንድ የማይቻል

---

82 [ማቴ. 19፥25፤ ማር. 10፥26] ብልጽግና በእግዚአብሔር የመወደድ ምልክት ሆኖ ይቆጠር ስለነበር፥ ሐብት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የማያስገባ እንቅፋት መሆኑ ያኔ በነበረው የአይሁድ እምነት ፈጽሞ የማይታሰብ ነበር። ሐብት ድሆችን ለመርዳት ሲያገለግል (ዘዳ. 15፥7-8፥ 11)፥ ሃይማኖተኛነትን በግል ለመግለጫነት፥ እንዲሁም የእግዚአብሔር በረከት ውጤት ሆኖ ታይቷል (ኢዮብ 1፥10፤ 42፥10)። ነገር ግን በኢየሱስ ዘመን የነበሩ ብዙ ሰዎች፥ ይህን መሪም ጨምሮ ከእግዚአብሔር ይልቅ ለቁሣዊ ነገሮች ከፍተኛ ግምት በመስጠት ፈተና ላይ ወደቁ።

| (ማቴዎስ 19፡ 16-30 የቀጠለ) | (ማርቆስ 10፡ 17-31 የቀጠለ) | (ሉቃስ 18፡18-30 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| ሁሉ ይቻላል አላቸው። 27 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ:- እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ፤ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን? አለው። 28 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው:- እውነት እላችኋለሁ፥ እናንተስ የተከተላችሁኝ፥ በዳግመኛ ልደት[83] የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ፥ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ። | ተመለከታቸውና:- ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላልና አለ። 28 ጴጥሮስም:- እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ ይለው ጀመር። 29 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ:- እውነት እላችኋለሁ፥ | በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል አለ። 28 ጴጥሮስም:- እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ አለ። 29 እርሱም:- እውነት እላችኋለሁ፥ |
| 29 ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል | ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ፥ 30 አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም እርሻንም መቶ እጥፍ፥ | ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ቤትን ወይም ወላጆችን ወይም ወንድሞችን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን የተወ፥ 30 በዚህ ዘመን ብዙ እጥፍ በሚመጣውም ዓለም የዘላለምን ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም አላቸው። |
| የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል። 30 ነገር ግን ብዙዎቹ ፊተኞች ኋለኞች፥ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ። | በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም። 31 ግን ብዙ ፊተኞች ኋለኞች ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ። | |

83 [ማቴ. 19፡28] "ዳግመኛ ልደት" የሚገልጠው መሲሑ በብሉይ ኪዳን የተተነበየውን የእግዚአብሔር መንግሥት ተስፋ ለመፈጸም በሚመጣ ጊዜ የሚመሠረተውን የዓለም ሥርዓት ነው። የእስራኤል ሕዝቦች እግዚአብሔር ከዓለም ጋር ለሚኖረው ግንኙነት እንደገና ማዕከላዊ አገናኝ ይሆናሉ። እናም እነዚህ አሥራ ሁለቱ (ይሁዳ ሲቀር) በሕዝቡ ላይ ባለሥልጣናት ይሆናሉ። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባቱ እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን (ማር. 10፡24) አስመልክቶ ከኢየሱስ አስደንጋጭ ንግግር ቀጥሎ የመጣው ይህ አስተምህሮ እርዳታ ሳይሆንላቸው አልቀረም።

## ♦ ክፍል 124ለ. የባለሀብቱን መብት አስመልክቶ የተነገረ ምሳሌ

[ክፍል 113ሀና 124ሀን ይመልከቱ]

- ፖርያ -

ማቴዎስ 20፥1-16

1 መንግሥተ ሰማያት ለወይኑ አትክልት ሠራተኞችን ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤት
ሰውን ትመስላለችና። 2 ሠራተኞችንም በቀን አንድ ዲናር ተስማምቶ ወደ ወይኑ
አትክልት ሰደዳቸው።

3 በሦስት ሰዓትም ወጥቶ ሥራ የፈቱ ሌሎችን በአደባባይ ቆመው አየ፥ 4
እነዚያንም፦ እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ የሚገባውንም እሰጣችኋለሁ
አላቸው። እነርሱም ሄዱ። 5 ደግሞም በስድስትና በዘጠኝ ሰዓት ወጥቶ እንዲሁ
አደረገ። 6 በአሥራ አንደኛውም ሰዓት ወጥቶ ሌሎችን ቆመው አገኘና፦ ሥራ
ፈትታችሁ ቀኑን ሁሉ በዚህ ስለ ምን ትቆማላችሁ? አላቸው።

7 የሚቀጥረን ስለ አጣን ነው አሉት።

እርሱም፦ እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ የሚገባውንም ትቀበላላችሁ
አላቸው።

8 በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት ጌታ አዛዡን፦ ሠራተኞችን ጥራና ከኋለኞች
ጀምረህ እስከ ፊተኞች ድረስ ደመወዝ ስጣቸው አለው።

9 በአሥራ አንደኛው ሰዓትም የገቡ መጥተው እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ።
10 ፊተኞችም በመጡ ጊዜ አብዝተው የሚቀበሉ መስሎአቸው ነበር፤ እነርሱም ደግሞ
እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ። 11-12 ተቀብለውም፦ እነዚህ ኋለኞች አንድ
ሰዓት ሠሩ፥ የቀኑንም ድካምና ትኩሳት ከተሸከምን ከእኛ ጋር አስተካከልሃቸው ብለው
በባለቤቱ ላይ አንጐራጐሩ።

13 እርሱ ግን መልሶ ከእነርሱ ለአንዱ እንዲህ አለው፦ ወዳጄ ሆይ፥ አልበደልሁህም
በአንድ ዲናር አልተስማማኸኝምን? 14 ድርሻህን ውሰድና ሂድ፤ እኔ ለዚህ ለኋለኛው
እንደ አንተ ልሰጠው እወዳለሁ፤ በገንዘቤ የወደድሁትን አደርግ ዘንድ መብት
የለኝምን?[84] 15 ወይስ እኔ መልካም ስለ ሆንሁ ዓይንህ ምቀኛ ናትን?

16 እንዲሁ ኋለኞች ፊተኞች፥ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ፤ የተጠሩ ብዙዎች፥
የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና።

---

[84] [ማቴ. 20፥15] ጴጥሮስ ማቴዎስ 19፥27 (ክፍል 12ሀ) ውስጥ ላቀረበው ጥያቄ ኢየሱስ ተጨማሪ መልስ ሲሰጥ፥ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በእግዚአብሔር መንግሥት የሚኖራቸው ስፍራ የረጅም ጊዜ አገልግሎታቸው ወይም የብዙ ሥራቸው ውጤት ነው ብለው እንዳያስቡ አስጠነቀቃቸው። ስጦታዎች ሁሉ በመጨረሻ ከልዑል እግዚአብሔር ጸጋ ነው የሚመጡት። እርሱ በራሱ የፍርድ ዓላማ መሠረት ጥቂት ለሠሩ ይበልጥ ይሰጥ ይሆናል።

## ♦ ክፍል 125ሀ. ስለ ኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ለሦስተኛ ጊዜ በቅድሚያ መነገሩ [ክፍል 83፥ 85፥ 86ና 88ን ይመልከቱ]

- ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በመንገድ ላይ -

<u>ማቴዎስ 20፡ 17-19</u>

17 ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሊወጣ ሳለ፥

በመንገድ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ብቻቸውን ወደ እርሱ አቅርቦ፦ 18 እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች ይሰጣል፤ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፥ 19 ሊዘባበቱበትም ሊገርፉትም ሊሰቅሉትም ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው።

<u>ማርቆስ 10፡ 32-34</u>

32 ወደ ኢየሩሳሌምም ሊወጡ በመንገድ ነበሩ፥ ኢየሱስም ይቀድማቸው ነበርና ተደነቁ፤ የተከተሉትም ይፈሩ ነበር።[85] ደግሞም አሥራ ሁለቱን ወደ እርሱ አቅርቦ ይደርስበት ዘንድ ያለውን ይነግራቸው ጀመር፦ 33 እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች አልፎ ይሰጣል፥ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፥ ለአሕዛብም አሳልፈው ይሰጡታል፥ 34 ይዘብቁበትማል ይተፉበትማል ይገርፉትማል ይገድሉትማል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው።

<u>ሉቃስ 18፡ 31-34</u>

31 አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ አቅርቦ እንዲህ አላቸው፦ እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ ስለ ሰው ልጅም በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል። 32 ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና፥ ይዘብቁበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል፤

33 ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል።

34 እነርሱም ከዚህ ነገር ምንም አላስተዋሉም፥ ይህም ቃል ተሰውሮባቸው ነበር፥ የተናገረውንም አላወቁም።

---

[85] [ማር. 10፡ 32] ይህ ፍርሃት ምናልባት ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ሲደርስ ጠላቶቹ ምን ያደርጉት ይሆን? (ዮሐ. 11፡8፥ ክፍል 118ሀ) ከሚል የመጣ ሳይሆን አይቀርም። ስለ ሥቃዩና ትንሣኤው የተደጋገመ ትንቢት ቢኖርም፥ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ገና አልገባቸውም (ሉቃስ 18፡ 34)፤ ምክንያቱም መንግሥቱን በምድር ላይ የሚመሠርት ድል አድራጊ መሢሕ ይጠብቁ ነበር። ኢየሱስ ሦስት ዓመት ባስተማራቸው ጊዜ ይህን ተስፋ አልነፈጋቸውም። ተስፋው ጥቂት የሚዘገይ መሆኑንም አስተምሯቸዋል (ክፍል 127ለ)።

## ♦ ክፍል 125ለ. በምኞት ስለተሞላ ኩራት የተነገረ ማስጠንቀቂያ

[ክፍል 144ን ይመልከቱ]

- ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በመንገድ ላይ -

ማቴዎስ 20፡20-28

20 በዚያን ጊዜ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከልጆችዋ ጋር እየሰገደችና አንድ ነገር እየለመነች ወደ እርሱ ቀረበች።[86]

21 እርሱም፦ ምን ትፈልጊያለሽ? አላት።

እርስዋም፦ እነዚህ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ አንዱም በግራህ በመንግሥትህ እንዲቀመጡ እዘዝ አለችው። 22 ኢየሱስ ግን መልሶ፦ የምትለምኑትን አታውቁም።

እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አለ። እንችላለን አሉት።

23 እርሱም፦ ጽዋዬንስ ትጠጣላችሁ፤ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም አላቸው።

24 አሥሩም ሰምተው በሁለቱ ወንድማማች ተቈጡ። 25 ኢየሱስ ግን ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ የአሕዛብ አለቆች እንዲገዙአቸው ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ። 26 በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ 27 ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤ 28 እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።

ማርቆስ 10፡35-45

35 የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ወደ እርሱ ቀርበው፦ መምህር ሆይ፥ የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንወዳለን አሉት።[86]

36 እርሱም፦ ምን ላደርግላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው።

37 እነርሱም፦ በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀኝ አንዳችንም በግራህ መቀመጥን ስጠን አሉት።

38 ኢየሱስ ግን፦ የምትለምኑትን አታውቁም። እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፥ እኔ የምጠመቀውንስ ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አላቸው።

39 እነርሱም፦ እንችላለን አሉት።

ኢየሱስም፦ እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ፥ እኔ የምጠመቀውንም ጥምቀት ትጠመቃላችሁ፤ 40 በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ የምሰጥ እኔ አይደለሁም አላቸው።

41 አሥሩም ሰምተው በያዕቆብና በዮሐንስ ይቈጡ ጀመር። 42 ኢየሱስም ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ የአሕዛብ አለቆች ተብለው የምታስቡት እንዲገዙአቸው ታላላቆቻቸውም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ። 43 በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ 44 ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን፤ 45 እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።

---

[86] [ማቴ. 20፡20፤ ማር. 10፡35] ይህ የክብር ሥፍራ ጥያቄ የሚያመለክተው፥ ሐዋርያት ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ የነበረው፥ የወደቀውን የዳዊት ዙፋንና መንግሥት ለመመለስ ነው ብለው ሁልጊዜ ያስቡ እንደነበር ነው። ይህ ምንም እንኳ ራስ ወዳድነት ቢኖርበት፥ ኢየሱስ ቀደም ሲል በእግዚአብሔር መንግሥት በአሥራ ሁለት ዙፋኖች ላይ አሥራ ሁለት ተቀማጮች ስለመኖራቸው ተናግሮ ስለነበር፥ የሚጠበቅ አሳብ ነው (ማቴ. 19፡28፥ ክፍል 124ሀ)። ያዕቆብና ዮሐንስ የትሕትናን ነጥብ መሳት ብቻ ሳይሆን፥ ሊመጣ ካለው የመሢሑ ስቃይ የተነሣ ይህ መዘግየቱ የግድ መሆኑንም ለመገንዘብ አልቻሉም።

## ♦ ክፍል 126. የዓይነ ሥውሩ በርጠሚዎስና የጓደኛው መፈወስ

[ክፍል 68ን ይመልከቱ]

- ኢያሪኮ -

**ማቴዎስ 20፡29-34**

29 ከኢያሪኮም ሲወጡ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት።

30 እነሆም፥ ሁለት ዕውሮች[87] በመንገድ ዳር ተቀምጠው፥ ኢየሱስ እንዲያልፍ በሰሙ ጊዜ፡- ጌታ ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረን ብለው ጮኹ።

31 ሕዝቡም ዝም እንዲሉ ገሠጹአቸው፤ እነርሱ ግን፡- ጌታ ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥[88] ማረን እያሉ አብዝተው ጮኹ።

32 ኢየሱስም ቆሞ ጠራቸውና፡-

ምን ላደርግላችሁ ትወዳላችሁ? አለ።

33 ጌታ ሆይ፥ ዓይኖቻችን ይከፈቱ ዘንድ አሉት።

34 ኢየሱስም አዘነላቸውና ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ፥ ወዲያውም አዩና ተከተሉት።

**ማርቆስ 10፡46-52**

46 ወደ ኢያሪኮም መጡ። ከደቀ መዛሙርቱና ከብዙ ሕዝብ ጋር ከኢያሪኮ ሲወጣ የጤሜዎስ ልጅ ዕውሩ[87] በርጤሜዎስ እየለመነ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ነበር።

47 የናዝሬቱ ኢየሱስም እንደ ሆነ በሰማ ጊዜ፡- የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ማረኝ እያለ ይጮኽ ጀመር።

48 ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ ግን፡- የዳዊት ልጅ ሆይ፥[88] ማረኝ እያለ አብዝቶ ጮኸ።

49 ኢየሱስም ቆመና፡- ጥሩት አለ።

ዕውሩንም፡- አይዞህ፥ ተነሣ፥ ይጠራሃል ብለው ጠሩት። 50 እርሱም እየዘለለ ተነሣና ልብሱን ጥሎ ወደ ኢየሱስ መጣ።

51 ኢየሱስም መልሶ፡- ምን ላደርግልህ ትወዳለህ? አለው።

ዕውሩም፡- መምህር ሆይ፥ አይ ዘንድ አለው።

52 ኢየሱስም፡- ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው። ወዲያውም አየ በመንገድም ተከተለው።

**ሉቃስ 18፡35-43**

35 ወደ ኢያሪኮም በቀረበ ጊዜ

አንድ ዕውር[87] እየለመነ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ነበር። 36 ሕዝብም ሲያልፍ ሰምቶ፡- ይህ ምንድር ነው? ብሎ ጠየቀ። 37 እነርሱም፡- የናዝሬቱ ኢየሱስ ያልፋል ብለው አወሩለት።

38 እርሱም፡- የዳዊት ልጅ፥ ኢየሱስ ሆይ፥ ማረኝ እያለ ጮኸ።

39 በስተ ፊት ይሄዱ የነበሩትም ዝም እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ ግን፡- የዳዊት ልጅ[88] ሆይ፥ ማረኝ እያለ አብዝቶ ጮኸ።

40 ኢየሱስም ቆሞ ወደ እርሱ እንዲያመጡት አዘዘ። በቀረበም ጊዜ፡- ምን ላደርግልህ ትወዳለህ? ብሎ ጠየቀው።

41 እርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ አይ ዘንድ ነው አለው።

42 ኢየሱስም፡- እይ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው። 43 በዚያን ጊዜም አየ፥ እግዚአብሔንም እያከበረ ተከተለው። ሕዝቡም ሁሉ አይተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

## ♦ ክፍል 127ሀ. የዘኪዮስ ደኅንነት ማግኘት

- ኢያሪኮ -

ሉቃስ 19፡ 1-10

1-2 ወደ ኢያሪኮም ገብቶ ያልፍ ነበር። እነሆም ዘኬዎስ የሚባል ሰው፥ እርሱም
የቀራጮች አለቃ ነበረ፥ ባለ ጠጋም ነበረ። 3 ኢየሱስንም የትኛው እንደ ሆነ ሊያይ
ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱም አጭር ነበረና ስለ ሕዝቡ ብዛት አቃተው። 4 በዚያችም
መንገድ ያልፍ ዘንድ አለውና ያየው ዘንድ ወደ ፊት ሮጦ በአንድ ሾላ ላይ ወጣ።

5 ኢየሱስም ወደዚያ ስፍራ በደረሰ ጊዜ፥ አሻቅቦ አየና፦ ዘኬዎስ ሆይ፥ ዛሬ በቤትህ
እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ አለው። 6 ፈጥኖም ወረደ በደስታም
ተቀበለው።

7 ሁሉም አይተው፦ ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ሊውል ገባ ብለው አንጐራጐሩ።

8 ዘኬዎስ ግን ቆሞ ጌታን፦ ጌታ ሆይ፥ ካለኝ ሁሉ እኵሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ፤
ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደ ሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ አለው።

9 ኢየሱስም፦ እርሱ ደግሞ የአብርሃም ልጅ[89] ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን
ሆኖለታል፤ 10 የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው።

## ♦ ክፍል 127ለ. የእግዚአብሔር መንግሥት ቢዘገይ እንኳን አማኞች የሚኖርባቸውን ኃላፊነት ለማስተማር የተነገረ ምሳሌ

[ክፍል 139ረን ይመልከቱ]

- ኢያሪኮ እና ወደ ኢየሩሳሌም የሚደረገው የመጨረሻ ጉዞ -

ሉቃስ 19፡ 11-28

11 እነርሱም ይህን ሲሰሙ፥ ወደ ኢየሩሳሌም መቅረቡ ስለ ሆነ የእግዚአብሔርም
መንግሥት ፈጥኖ[90] ሊገለጥ እንዳለው ስለ መሰላቸው ምሳሌ ጨምሮ ተናገረ። 12
ስለዚህም እንዲህ አላቸው፦ አንድ መኰንን[91] ለራሱ መንግሥትን ይዞ ሊመለስ ወደ
ሩቅ አገር ሄደ። 13 አሥር ባሪያዎችንም ጠርቶ አሥር ምናን ሰጣቸውና፦ እስክመጣ
ድረስ ነግዱ አላቸው።

14 የአገሩ ሰዎች ግን ይጠሉት ነበርና፦ ይህ በላያችን ሊነግሥ አንወድም ብለው
በኋላው መልክተኞችን ላኩ።

15 መንግሥትንም ይዞ በተመለሰ ጊዜ፥ ገንዘብ የሰጣቸውን እነዚህን ባሪያዎች ነግደው
ምን ያህል እንዳተረፉ ያውቅ ዘንድ እንዲጠሩለት አዘዘ።

16 የፊተኛውም ደርሶ፦ ጌታ ሆይ፥ ምናንህ አሥር ምናን አተረፈ አለው።

---

87 [ማቴ. 20፡30፤ ማር. 10፡46፤ ሉቃስ 18፡35] ቀደም ሲል እንደተመለከተው ሁሉ ማቴዎስ ስለ ሁለት ዓይነሥውሮች ሲናገር፥ ማርቆስና ሉቃስ ግን ስለ አንድ ዓይነሥውር ብቻ ነው የጻፉት (ክፍል 66)። የማርቆስና ሉቃስ ወንጌላት ሁለቱ ዓይነሥውሮች አብዝተው መጮኻቸውን ነው ለይተው የሚያመለክቱት። ምንም እንኳን ኢየሱስ ቀደም ሲል ወደ ከተማው ሲቃረብ ሰዎቹን ያገኛቸው ቢሆንም (ሉቃስ 18፡35)፥ ይህ ተአምር የተፈጸመው ግን ከከተማው በመውጣት ላይ በነበረበት ጊዜ ይመስላል (ማቴ. 20፡29፤ ማር. 10፡46)።

88 [ማቴ.20፡31፤ ማር.10፡48፤ ሉቃስ 18፡38] "የዳዊት ልጅ" የሚለው መጠሪያ መሢሐዊ ስም ነው። እነዚህ ዓይነሥውራን፥ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ኢየሱስ የዓይናቸውን ብርሃን የሚያበራ ብቻ ሳይሆን (ኢሳ. 35፡5)፥ ለዳዊት የተነገረለትን ትንቢት የሚፈጽም እንደሆነም ተገንዝበዋል (2ኛ ሳሙ. 7፡12-16፤ መዝ. 89፤ ኢሳ. 11፡1-9፤ ኤር. 23፡5-6፤ ሕዝ. 34፡23-34)።

(ሉቃስ 19፡ 11-28 የቀጠለ)

17 እርሱም፡- መልካም፥ አንተ በጎ ባሪያ፥ በጥቂት የታመንህ ስለ ሆንህ በአሥር ከተማዎች ላይ ሥልጣን ይሁንልህ አለው።

18 ሁለተኛውም መጥቶ፡- ጌታ ሆይ፥ ምናንህ አምስት ምናን አተረፈ አለው።

19 ይህንም ደግሞ፡- አንተም በአምስት ከተማዎች ላይ ሁን አለው።

20 ሌላውም መጥቶ፡- ጌታ ሆይ፥ በጨርቅ ጠቅልዬ የጠበቅኋት ምናንህ እነሆ፤ 21
ፈርቼሃለሁና፥ ጨካኝ ሰው ስለ ሆንህ፤ ያላኖርኸውን ትወስዳለህ ያልዘራኸውንም
ታጭዳለህ አለው።

22 እርሱም፡- አንተ ክፉ ባሪያ፥ አፍህ በተናገረው እፈርድብሃለሁ። እኔ
ያላኖርሁትን የምወስድና ያልዘራሁትን የማጭድ ጨካኝ ሰው እንደ ሆንሁ አወቅህ፤
ምን ነው ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ያልሰጠኸው? 23 እኔም መጥቼ ከትርፉ ጋር
እወስደው ነበር አለው።

24 በዚያም ቆመው የነበሩትን፡- ምናኑን ውሰዱበት አሥሩ ምናን ላለውም ስጡት አላቸው።

25 እነርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ አሥር ምናን አለው አሉት።

26 እላችኋለሁ፥ ላለው ሁሉ ይሰጠዋል፥ ከሌለው ግን ያው ያለው ስንኳ
ይወሰድበታል።[92] 27 ነገር ግን እነዚያን በላያቸው ልነግሥ ያልወደዱትን ጠላቶቼን
ወደዚህ አምጡአቸው በፊቴም እረዱአቸው።

28 ይህንም ከተናገረ በኋላ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ ይቀድማቸው ነበር።

---

89 [ሉቃስ 19፡9] ቀራጭ የሚለው የንቀት ስም፥ የዘኪዮስን የአብርሃም ልጅነት መብት አላሳጣውም። የንስሐ ዕድል ያገኝ ዘንድ ("ይገባኛልና"፥ ቁጥር 5) በሚለው መለኮታዊ ቃል ተገደደ። ኢየሱስ ቀራጮቹን ለንስሐ ለመጥራት ያደረገው ጥረት (ሉቃስ 15፡1-2፥ ክፍል 116) በዚህ ምሳሌ ፍሬው ታይቷል።

90 [ሉቃስ 19፡ 11] ይህ ንግግር የተደረገው 25 ኪሎ ሜትሮች ያህል ብቻ ርቃ በምትገኘው ኢያሪኮ ውስጥ ነው። የመልእክቱ ዓላማም የእግዚአብሔር መንግሥት ምድር ላይ እስከመመሥረት ድረስ ያለው ጊዜ የሚዘገይ መሆኑን ለአድማጮቹ ለማስገንዘብ ነበር። ኢየሱስ ኢየሩሳሌም እንደደረሰ የዳዊትን ዙፋን ይመልስና ዙፋኑ ላይ ይቀመጣል በማለት ተከታዮቹ ጠብቀው ነበር።

91 [ሉቃስ 19፡ 12] ቤተ መንግሥቱን ኢያሪኮ ውስጥ ያሳነጸው የታላቁ ሄሮድስ ልጅ አርኬላዎስ፥ የላቀ የንጉሥነት ሥልጣን ከሮም መንግሥት ለመቀበል በዚያው ጊዜ ከታሪኩ ጋር በሚመሳሰል ሁኔታ ወደ ሮም ሄዶ ነበር (ማቴ. 2፡22፥ ክፍል 16)። የምሳሌውን አተራረክ ሁኔታ ያመለከተው ያ ታሪካዊ አጋጣሚ ሳይሆን አይቀርም።

92 [ሉቃስ 19፡ 26] ከዚህ ምሳሌ ሁለት ትምህርቶችን እናገኛለን፡-

(1) ደቀ መዛሙርቱ መንግሥቱ ከንጉሡ (ከኢየሱስ) መመለስ ጋር እንደሚመጣ አምነው እየጠበቁ ለንጉሡ ሥራ መትጋት ነበረባቸው። (2) ኢየሱስን እንደ ንጉሥ አንቀበልም ያሉ አይሁዳውያን፥ በዚህ ድርጊታቸው ሳቢያ የቅጣት ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው።

# 10

# የኢየሱስ በግልጥ ለእስራኤል መቅረብና ያስከተለው ግጭት

## > በድል ወደኢየሩሳሌም መግባትና አንዲት የበለስ ዛፍ <

### ♦ ክፍል 128ሀ. ቢታንያ መድረስ

- ቢታንያ፥ ኢየሩሳሌም አጠገብ -

<u>ዮሐንስ 11፡55-12፡1፥ 9-11</u>

55 የአይሁድም ፋሲካ ቀርቦ ነበር። ብዙ ሰዎችም ራሳቸውን ያነጹ ዘንድ[93] ከፋሲካ
በፊት ከአገሩ ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ። 56 ኢየሱስንም ይፈልጉት ነበር፤ በመቅደስም
ቆመው እርስ በርሳቸው፡- ምን ይመስላችኋል? ወደ በዓሉ አይመጣም ይሆንን?[94]
ተባባሉ። 57 የካህናት አለቆችም ፈሪሳውያንም ይይዙት ዘንድ እርሱ ያለበትን ስፍራ
የሚያውቀው ሰው ቢኖር እንዲያመለክታቸው አዘው ነበር።

1 ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን[95] ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ
ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ።

9 ከአይሁድም ብዙ ሕዝብ በዚያ እንደ ነበረ አውቀው መጡ፥ ከሙታንም
ያስነሣውን አልዓዛርን ደግሞ እንዲያዩ ነበረ እንጂ[96] ስለ ኢየሱስ ብቻ አይደለም። 10
የካህናት አለቆችም አልዓዛርን ደግሞ ሊገድሉት ተማከሩ፥ 11 ከአይሁድ ብዙዎች
ከእርሱ የተነሣ ሄደው በኢየሱስ ያምኑ ነበርና።

---

93 [ዮሐ. 11፡55] በዚህ በዓል ላይ ለመሳተፍ የሚሄዱ ሰዎች ብዙ እንደመሆናቸው የመንጻቱ በዓል ከሌላው ሁኔታ የበለጠ ጊዜ ጠየቀ። በመሆኑም ብዙ ሰዎች ቀደም ብለው፥ አንዳንዶቹም ከሳምንት በፊት ወደየሥፍራቸው መጡ።

94 [ዮሐ. 11፡56] አጠቃላዩ የሕዝብ አስተያየት ኢየሱስ ወደ በዓሉ ሥፍራ አይመጣም የሚል ይመስላል። ኢየሱስ ያለበትን የሚያውቅ ሰው እንዲገልጥ ባለሥልጣናት ያወጡት ትእዛዝ፥ (ዮሐ. 11፡57) ትእዛዙን የማያከብሩትን ሁሉ ጥፋተኛ ያደርጋቸው ነበር። ከዚህ ትእዛዝ አንጻር የኢየሱስን ኢየሩሳሌም ውስጥ መገኘት ለሚያውቁት ሁሉ ችግር ሆኖባቸው ነበር።

95 [ዮሐ. 12፡1] በዚያ ዓመት ፋሲካ የዋለው አርብ ዕለት ነበር ብለን ብናምን፥ ኢየሱስ ቢታኒያ የደረሰው ከፋሲካ አንድ ሳምንት በፊት በነበረው ቅዳሜ ነው። የነበረውም በአካባቢው መሆን አለበት። እንዲያ ባይሆን ኖሮ ጉዞው ለሰንበት ዕለት ከተወሰነው በላይ ይሆን ነበር።

## ♦ ክፍል 128ለ. ወደ ኢየሩሳሌም በክብር መግባት

- ከቢታንያ ወደ ኢየሩሳሌም፥ ከኢየሩሳሌም ወደ ቢታንያ -

| ማቴዎስ 21፡1-3፥ 6-7፥ 4-5፥ 8-11፥ 14-17 | ማርቆስ 11፡1-11 | ሉቃስ 19፡29-44 | ዮሐንስ 12፡12-19 |
|---|---|---|---|
| 1 ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተ ፋጌ ሲደርሱ፥ ያንጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፥ 2 እንዲህም አላቸው፦ በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥[97] በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ[98] ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ። 3 ማንም አንዳች ቢላችሁ፦ ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም ይሰዳቸዋል። 6 ደቀ መዛሙርቱም ሄደው | 1 ወደ ኢየሩሳሌምም ከደብረ ዘይት አጠገብ ወዳሉቱ ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረቡ ጊዜ፥ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ልኮ፦ 2 በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥[97] ወዲያውም ወደ እርስዋ ገብታችሁ ከሰው ማንም ገና ያልተቀመጠበት ውርንጫ[98] ታስሮ ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ። 3 ማንም፦ ስለ ምን እንዲህ ታደርጋላችሁ? ቢላችሁ፦ ለጌታ ያስፈልገዋል | 29 ደብረ ዘይትም በሚባል ተራራ አጠገብ ወዳሉት ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረበ ጊዜ፥ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ላከና፦ 30 በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥[97] ወደ እርስዋም ገብታችሁ ከሰው ማንም ገና ያልተቀመጠበት ውርንጫ[98] ታስሮ ታገኛላችሁ፥ ፈትታችሁም አምጡት። 31 ማንም፦ ስለ ምን ትፈቱታላችሁ? ብሎ ቢጠይቃችሁ፥ እንዲሁ፦ ለጌታ ያስፈልገዋል በሉ አላቸው። | 12 በማግሥቱ ወደ በዓሉ መጥተው የነበሩ ብዙ ሕዝብ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ በሰሙ ጊዜ፥ |

96 [ዮሐ. 12፡9] የአልዓዛር ከሞት መነሣት ነው በአብዛኛው ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ብዙ ሕዝብ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው እንዲቀበሉት ያደረገው (ዮሐ. 12፡17-18፤ ክፍል 128ለ)። የአልአዛር ከሞት መነሣት በሕዝቡ ዘንድ የታወቀ መሆኑ እንዲገደል የሚል ግልጥ ውሳኔም አስከትሏል (ዮሐ. 12፡10)፤ ይህ ውሳኔ ቀደም ሲል በኢየሱስ ላይ የተወሰነው (ዮሐ. 11፡53፥ ክፍል 119) ዓይነት ነው።

97 [ማቴ.21፡2፤ ማር.11፡2፤ ሉቃስ 19፡30] ኢየሱስ ዘካርያስ 9፡9 ውስጥ እንደተጠቀሰው፥ የእስራኤል ንጉሥነቱን ለማመልከት ብዙ ጥረት አድርጓል። ይህ ጉዳይ በሥፍራው የነበሩት ሁሉ ያልሳቱት ቁም ነገር ነበር (ማቴ. 21፡9፤ ማር. 11፡9-10፤ ሉቃስ 19፡38፤ ዮሐ. 12፡13)። በዮሐንስ ዘገባ መሠረት በሥፍራው የነበሩት ሰዎች የመጡት ከሦስት መነሻዎች ነው። ዮሐንስ 12፡12 ውስጥ እንደተመለከትነው ብዙ ሕዝብ ከሩቅ ስፍራ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቷል። ብዙውን የኢየሱስ አገልግሎት የተመለከቱ በአብዛኛው የገሊላ ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። ዮሐንስ 12፡17 ውስጥ የተገለጡት ደግሞ አልዓዛር ከሞት ሲነሣ የተመለከቱና ከቢታንያ የመጡ (ዮሐ. 11፡42፥ ክፍል 118ለ)፥ ዮሐንስ 12፡18 ውስጥ የተጠቀሱት ደግሞ አልዓዛርን ከሞት ያስነሣውን ሰው ለመመልከት ከኢየሩሳሌም የመጡ ሕዝብ ነበሩ። (የግርጌ ማስታወሻው በተከታዩ ገጽ ይቀጥላል።)

| (ማቴዎስ 21፡1-3፥ 6-7፥ 4-5፥ 8-11፥ 14-17 የቀጠለ) | (ማርቆስ 11፡1-11 የቀጠለ) | (ሉቃስ 19፡29-44 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 12፡12-19 የቀጠለ) |
|---|---|---|---|
| ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፥ | በሉት፥ ወዲያውም ደግሞ ወደዚህ ይሰደዋል አላቸው።<br>4 ሄዱም ውርንጫውንም በመንገድ መተላለፊያ በደጅ ውጭ ታስሮ አገኙት፥ ፈቱትም። 5 በዚያም ከቆሙት አንዳንዶቹ፦ ውርንጫውን የምትፈቱት ምን ልታደርጉት ነው አሉአቸው። 6 እነርሱም ኢየሱስ እንዳዘዘ አሉአቸው፤ ተዉአቸውም። 7 ውርንጫውንም ወደ ኢየሱስ አመጡት፥ ልብሳቸውንም በላዩ ጣሉ፥ ተቀመጠበትም። | 32 የተላኩትም ሄደው እንዳላቸው አገኙ። 33 እነርሱም ውርንጫውን ሲፈቱ ጌቶቹ፦ ውርንጫውን ስለምን ትፈቱታላችሁ? አሉአቸውም<br>34 እነርሱም፦ ለጌታ ያስፈልገዋል አሉ።<br>35 ወደ ኢየሱስም አመጡት፥ በውርንጫውም ላይ ልብሳቸውን ጭነው ኢየሱስን አስቀመጡት። | 13 የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበሉት ወጡና፦<br>"ሆሣዕና፤ በጌታ ስም የሚመጣ የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው"<br>እያሉ ጮኹ። [መዝሙር 118፡25፥ 26]<br>14-15 አንቺ የጽዮን ልጅ አትፍሪ፤<br>"እነሆ፥ ንጉሥሽ በአህያ ውርንጫ98 ላይ ተቀምጦ ይመጣል"<br>ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ኢየሱስ የአህያ ውርንጫ |
| 7 አህያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፥ ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ ጫኑ፥ ተቀመጠባቸውም።<br>4-5 ለጽዮን ልጅ፦<br>"እነሆ፥ ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉአት"<br>ተብሎ በነቢይ የተነገረው ይፈጸም | | | |

ይሁን እንጂ ይህን የኢየሱስ ተልእኮ ሕዝቡ የተረዱት በከፊል ነበር። የጨበጡት ፖለቲካዊ ጠቀሜታውን፥ ማለት ከውጭ ተጽእኖ ነጻ መሆንን ነበር። የመንግሥቱን መንፈሳዊ ነገሮች ግን ሊገነዘቡ አልቻሉም። በመሆኑም የዚያ ትውልድ ብሔራዊ ምኞት ፍጻሜ ብስጭት ሆነ። ኢየሱስ ከሕዝብ ታላቅ አድናቆት ያገኘበት ጊዜ ቢሆንም፥ የዚህ ምኞቱ አለመሳካት አሳዝኖታል (ሉቃስ 19፡41)።

| **(ማቴዎስ 21፡1-3፥ 6-7፥ 4-5፥ 8-11፥ 14-17 የቀጠለ)** | **(ማርቆስ 11፡1-11 የቀጠለ)** | **(ሉቃስ 19፡29-44 የቀጠለ)** | **(ዮሐንስ 12፡12-19 የቀጠለ)** |
|---|---|---|---|
| ዘንድ ይህ ሆነ። [ኢሳይያስ 62፡11፤ ዘካርያስ 9፡9] | | | አግኝቶ በእርሱ ተቀመጠ። [ዘካርያስ 9፡9]<br>16 ደቀ መዛሙርቱም ይህን ነገር በመጀመሪያ አላስተዋሉም፤ ነገር ግን ኢየሱስ ከከበረ በኋላ በዚያን ጊዜ ይህ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይህንም እንዳደረጉለት ትዝ አላቸው።<br>17 አልዓዛርንም ከመቃብር ጠርቶ ከሙታን ሲያስነሣው ከእርሱ ጋር የነበሩት ሕዝብ ይመሰክሩለት ነበር። 18 ስለዚህ ደግሞ ሕዝቡ ይህን ምልክት እንዳደረገ ስለ ሰሙ ሊቀበሉት ወጡ። 19 ስለዚህ ፈሪሳውያን እርስ በርሳቸው፦ አንድ ስንኳ ልታደርጉ እንዳይቻላችሁ ታያላችሁን? እነሆ፥ ዓለሙ በኋላው ተከትሎት ሄዶአል ተባባሉ። |

98 [ማቴ. 21፡2፤ ማር.11፡2፤ ሉቃስ 19፡30፤ ዮሐ.12፡14] ማቴዎስ የሚናገረው ስለ ሁለት እንስሳት፥ ማለት ስለ አንዲት አህያና አንዲት ውርንጫ ሲሆን፥ ሌሎቹ የወንጌል ጸሐፊዎች ግን ውርንጫይቱን ብቻ ነው የጠቀሱት። ይህ ማቴዎስ ከአንድ በላይ ተሳታፊ ያለበትን ጉዳይ ያስታወሰበት ሌላ ምሳሌ ሲሆን፥ የሌሎች ወንጌላት ገለጣዎች ግን አጠቃላይና ስለ አንድ ተሳታፊ ብቻ የሚገልጡ ናቸው (ክፍል 66፥ ማስታወሻ "ተ" እና ክፍል 126፥ ማስታወሻ "ሐ" ላይ የተሰጡትን መግለጫዎች ይመልከቱ)። ማቴዎስ ይህን ዝርዝር ጉዳይ የጨመረው፥ የተከናወነውን ነገር ዘካርያስ 9፡9 ላይ ከተጠቀሰውና ሁለት እንስሳትን ከሚያመለክተው ትንቢት ጋር ይበልጥ ለማያያዝ ነው (ማቴ. 21፡4-5)። ሌሎቹ ሦስት ወንጌላት በተመሳሳይ እንደጠቀሱት፥ ኢየሱስ የተቀመጠው ውርንጫይቱ ላይ ብቻ ይመስላል። "በነርሱ ላይ" (ቁጥር 7) የሚለው ሌላ ገለጣ የሚያመለክተው፥ ኢየሱስ የተቀመጠው በውርንጫይቱና በአህያይቱ ላይ ሳይሆን፥ በልብሶቹ ላይ መሆኑን ነው። የውርንጫዋ እናት የመጀመሪያ ተቀማጭዋን የተሸከመችው ልጇ እርሷን አይታ ዘና እንድትል ከፊት ቀድማ የመራቻት ይመስላል።

<u>(ማቴዎስ 21፡1-3፥ 6-7፥ 4-5፥ 8-11፥ 14-17 የቀጠለ)</u>

8 ከሕዝቡም እጅግ
ብዙዎች ልብሳቸውን
በመንገድ ላይ አነጠፉ፥
ሌሎችም ከዛፍ ጫፍ
ጫፉን እየቈረጡ
በመንገድ ላይ ያነጥፉ
ነበር። 9
የሚቀድሙትም ሕዝብ
የሚከተሉትም፡-

“ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ
በጌታ ስም የሚመጣ
የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና
በአርያም”

እያሉ ይጮኹ ነበር።
[መዝሙር 118፡26]

<u>(ማርቆስ 11፡1-11 የቀጠለ)</u>

8 ብዙ ሰዎችም
ልብሳቸውን በመንገድ ላይ
አነጠፉ፥ ሌሎችም ከዛፍ
ቅጠሎችን እየቈረጡ
ያነጥፉ ነበር። 9
የሚቀድሙትም
የሚከተሉትም፡-

“ሆሣዕና፤ በጌታ ስም
የሚመጣ የተባረከ ነው
[መዝሙር 118፡26]፤

10 በጌታ ስም
የምትመጣ የአባታችን
የዳዊት መንግሥት
የተባረከች ናት፤ ሆሣዕና
በአርያም”

እያሉ ይጮኹ ነበር።

<u>(ሉቃስ 19፡29-44 የቀጠለ)</u>

36 ሲሄድም ልብሳቸውን
በመንገድ ያነጥፉ ነበር።

37 ወደ ደብረ ዘይት
ቍልቍለትም አሁን በቀረበ
ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ
ሁላቸው ደስ እያላቸው
ተአምራትን ሁሉ ስላዩ
በታላቅ ድምፅ
እግዚአብሔርን ሊያመሰግኑ
ጀምረው፡-

38 “በጌታ ስም የሚመጣ
ንጉሥ የተባረከ ነው፤
በሰማይ ሰላም በአርያምም
ክብር”

አሉ። [መዝሙር 118፡26]

39 ከሕዝብም መካከል
ከፈሪሳውያን አንዳንዱ፡-
መምህር ሆይ፥ ደቀ
መዛሙርትህን ገሥጻቸው
አሉት።

40 መልሶም፡-
እላችኋለሁ፥ እነዚህ ዝም
ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ
አላቸው።

41 ሲቀርብም ከተማይቱን
አይቶ አለቀሰላት፥ 42
እንዲህ እያለ፡- ለሰላምሽ
የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ
ስንኳ ብታውቂ፤ አሁን ግን
ከዓይንሽ ተሰውሮአል። 43
ወራት ይመጣብሻልና፥
ጠላቶችሽም ቅጥር
ይቀጥሩብሻል ይከቡሻልም
በየበኩሉም ያስጨንቁሻል፤
44 አንቺንም በአንቺም
ውስጥ የሚኖሩትን ልጆችሽን
ወደ ታች ይጥላሉ፥ በአንቺ
ውስጥም ድንጋይ በድንጋይ
ላይ አይተዉም፥
የመጐብኘትሽን ዘመን
አላወቅሽምና።

| (ማቴዎስ 21፡ 1-3፥ 6-7፥ 4-5፥ 8-11፥ 14-17 የቀጠለ) | (ማርቆስ 11፡ 1-11 የቀጠለ) |
| --- | --- |
| 10 ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ መላው ከተማ፡- ይህ ማን ነው? ብሎ ተናወጠ። | 11 ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም |
| 11 ሕዝቡም፡- ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አሉ። | |
| 14 በመቅደስም ዕውሮችና አንካሶች ወደ እርሱ ቀረቡና ፈወሳቸው። 15 ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች ያደረገውን ድንቃ ድንቅ በመቅደስም፡- ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ እያሉ የሚጮኹትን ልጆች ባዩ ጊዜ፥ ተቈጥተው፡- | ወደ መቅደስ ገባ፤ |
| 16 እነዚህ የሚሉትን አትሰማምን? አሉት። ኢየሱስም፡- እሰማለሁ፤ [መዝሙር 8፡2] “ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ” የሚለውን ቃል ከቶ አላነበባችሁምን? አላቸው። | ዘወር ብሎም ሁሉን ከተመለከተ በኋላ፥ |
| 17 ትቶአቸውም ከከተማ ወደ ቢታንያ ወጣ በዚያም አደረ። | ጊዜው መሽቶ ስለ ነበረ ከአሥራ ሁለቱ ጋር ወደ ቢታንያ ወጣ። |

## ♦ ክፍል 129ሀ. የበለስ ዛፍ ቅጠል እንጂ ፍሬ ስለታጣበት መረገሟ

- ከቢታንያ ወደ ኢየሩሳሌም -

| ማቴዎስ 21፡ 18-19ሀ | ማርቆስ 11፡ 12-14 |
| --- | --- |
| 18 በማለዳም ወደ ከተማ ሲመለስ ተራበ። 19 በመንገድም አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርስዋ መጣ፤ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና፡- | 12 በማግሥቱም ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ። 13 ቅጠልም ያላት በለስ ከሩቅ አይቶ ምናልባት አንዳች ይገኝባት እንደ ሆነ ብሎ መጣ፥ ነገር ግን የበለስ ወራት[99] አልነበረምና መጥቶ ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም። |
| ለዘላለሙ ፍሬ አይገኝብሽ አላት። | 14 መልሶም፡- ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ማንም ከአንቺ ፍሬ አይብላ አላት። ደቀ መዛሙርቱም ሰሙ። |

99 [ማር. 11፡ 13] ኢየሱስ ረሃቡናን ቅጠል ብቻ ያለውን ዛፍ ለደቀ መዛሙርቱ ትምህርት ማቅረቢያነት ተጠቀመበት እንጂ፥ በለስ የፋሲካ በዓል በሚከበርበት ወራት እንደማይፈራ ያውቃል። በለስ በብሉይ ኪዳን ብዙ ጊዜ የእስራኤል ምሳሌ ነው (ኤር. 8፡ 13፤ 29፡ 17፤ ሆሴዕ 9፡ 10፥ 16፤ ኢዩ. 1፡ 7፤ ሚክ. 7፡ 1-6)። ስለዚህ ኢየሱስ ይህን የበለስ ዛፍ መርገሙ (ማቴ. 21፡ 19፤ ማር. 11፡ 14)፥ በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ያለው የእግዚአብሔር ፍርድ ምልክት ነው (ክፍል 131)።

## ♦ ክፍል 129ለ. ቤተ መቅደሱን ለሁለተኛ ጊዜ ማጥራት

[ክፍል 31ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም፥ በመቅደሱ ውስጥ -

**ማቴዎስ 21፡12-13**

12 ኢየሱስም ወደ መቅደስ[1] ገባና በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ፥ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና፡-

13 "ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፥ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት"

አላቸው። [ኢሳይያስ 56፡7፤ ኤርምያስ 7፡11]

**ማርቆስ 11፡15-18**

15 ወደ ኢየሩሳሌምም መጡ። ወደ መቅደስም[1] ገብቶ በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ያወጣ ጀመር፥ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጭዎችንም ወንበሮች ገለበጠ፤ 16 ዕቃም ተሸክሞ ማንም በመቅደስ ሊያልፍ አልፈቀደም። 17 አስተማራቸውም፡-

"ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ የተጻፈ አይደለምን? እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት"

አላቸው። [ኢሳይያስ 56፡7፤ ኤርምያስ 7፡11]

18 የካህናት አለቆችም ጻፎችም ሰምተው፥ ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ ይገረሙ ስለ ነበር ይፈሩት ነበርና እንዴት አድርገው እንዲያጠፉት ፈለጉ።

**ሉቃስ 19፡45-48**

45 ወደ መቅደስም[1] ገብቶ በእርሱ የሚሸጡትን የሚገዙትንም ያወጣ ጀመር፤

46 እርሱም፡-

"ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት"

አላቸው። [ኢሳይያስ 56፡7፤ ኤርምያስ 7፡11]

47 ዕለት ዕለትም በመቅደስ ያስተምር ነበር፤ ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች የሕዝቡ ታላላቆችም ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር፥ 48 የሚያደርጉበትንም አጡ፤ ሕዝቡ ሁሉ ሲሰሙት ተንጠልጥለውበት ነበርና።

---

[1] [ማቴ.21፡12፤ ማር.11፡15፤ ሉቃስ 19፡45] የአሕዛብ አደባባይ የመንጻት ቦታ ነበር። ንጉሡ በአስደናቂ ሁኔታ ወደ ከተማይቱ ከገባ በኋላ (ክፍል 128ለ)፥ በቀጥታ የእስራኤላውያን ችግር ወደሆነው የተበላሸ አምልኳቸው ነው ያመራው። ይህ ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔርን አለማምለክ ነው። ይህ ነው የኢየሱስን "በድል መግባት" ዘላለማዊ እንዳይሆን የገታው።

## ♦ ክፍል 130ሀ. አንዳንድ ግሪካውያን ኢየሱስን ለማየት መሻታቸው እና የሰው ልጅ ከፍ ከፍ የማለቱ አስፈላጊነት

[ክፍል 83ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም -

<u>ዮሐንስ 12፡20-36ሀ</u>

20 በበዓሉም ሊሰግዱ ከወጡት አንዳንዶቹ የግሪክ ሰዎች ነበሩ፤ 21 እነርሱም ከገሊላ
ቤተ ሳይዳ ወደሚሆን ወደ ፊልጶስ መጥተው፡- ጌታ ሆይ፥ ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን
ብለው ለመኑት። 22 ፊልጶስም መጥቶ ለእንድርያስ ነገረው፤ እንድርያስና ፊልጶስ
መጥተው ለኢየሱስ ነገሩት።

23 ኢየሱስም መለሰላቸው፥[2] እንዲህ ሲል፡- የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ ሰዓቱ
ደርሶአል። 24 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ
ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች። 25 ነፍሱን
የሚወድ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት
ይጠብቃታል። 26 የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ
በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል።

27 አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር
ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ። 28 አባት ሆይ፥ ስምህን አክብረው።

ስለዚህም፡- አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ። 29
በዚያ ቆመው የነበሩትም ሕዝብ በሰሙ ጊዜ፡- ነጐድጓድ ነው አሉ፤ ሌሎች፡-
መልአክ ተናገረው አሉ።

30 ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል፡- ይህ ድምፅ ስለ እናንተ መጥቶአል እጂ ስለ
እኔ አይደለም። 31 አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል፤ አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ
ውጭ ይጣላል፤ 32 እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ
እስባለሁ። 33 በምን ዓይነትም ሞት ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያመለክታቸው ይህን
ተናገረ።

34 እንግዲህ ሕዝቡ፡- እኛስ ክርስቶስ ለዘላለም እንዲኖር ከሕግ ሰምተናል፤ አንተስ
የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ይል ዘንድ እንዲያስፈልገው እንዴት ትላላህ? ይህ የሰው ልጅ
ማን ነው? ብለው መለሱለት።

35 ኢየሱስም፡- ገና ጥቂት ጊዜ ብርሃን ከእናንተ ጋር ነው። ጨለማ
እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ፤ በጨለማም የሚመላለስ ወዴት
እንዲሄድ አያውቅም። 36ሀ የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃኑ
እመኑ አላቸው።

---

[2] [ዮሐ. 12፡23] የኢየሱስ መልስ ግሪካውያኑንና ጥያቄያቸውን ከጉዳይ ያላገባ ነበር። ይሁን እንጂ፥ ዮሐንስ ይህን ጉዳይ በታሪኩ ውስጥ ማካተቱ የሰዎቹን አስፈላጊነት ያመለክታል። እነዚህ ሰዎች ሊፈልጉት መምጣታቸው የአገልግሎቱ ፍጻሜ መቃረቡን በተዘዋዋሪም ቢሆን ኢየሱስ እንዲገነዘብ አድርጎታል። ለአይሁዳውያን የተወሰነ አገልግሎቱን የሚፈጽምበትና እንደ ግሪካውያኑ ሁሉ ሌሎችን የሚያገለግልበት ጊዜ ደርሶ ነበር። ይህ የሚሆነው ግን እርሱ ከሞተ በኋላ ብቻ ነበር (ዮሐ. 12፡24፥ 32)።

## ♦ ክፍል 130ለ. ከተሰበሰበው ሕዝብ ለኢየሱስ የተደረጉ አቀባበሎችና እርሱ ለሕዝቡ የሰጠው መልስ

[ክፍል 64ለን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም -

ዮሐንስ 12፡36ለ-50

36ለ ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ሄደና ተሰወረባቸው።

37-38 ነገር ግን ይህን ያህል ምልክት በፊታቸው ምንም ቢያደርግ፤ ነቢዩ ኢሳይያስ፡- [ኢሳይያስ 53፡1]

"ጌታ ሆይ፥ ማን ምስክርነታችንን አመነ? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ?" ብሎ የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ በእርሱ አላመኑም።

39-40 ኢሳይያስ ደግሞ፡- "በዓይኖቻቸው እንዳያዩ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ እንዳይመለሱም፥ እኔም እንዳልፈውሳቸው፥ ዓይኖቻቸውን አሳወረ ልባቸውንም አደነደነ" ብሎአልና ስለዚህ ማመን አቃታቸው። [ኢሳይያስ 6፡10] 41 ክብሩን ስለ አየ ኢሳይያስ ይህን አለ፥ ስለ እርሱም ተናገረ።

42 ከዚህም ጋር ከአለቆች ደግሞ ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ነገር ግን ከምኩራብ እንዳያስወጡአቸው በፈሪሳውያን ምክንያት አልመሰከሩለትም፤ 43 ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና።

44 ኢየሱስም ጮኸ፥ እንዲህም አለ፡- በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፤ 45 እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል። 46 በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ።

47 ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር የምፈርድበት እኔ አይደለሁም። 48 የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል። 49 እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ። 50 ትእዛዙም የዘላለም ሕይወት እንደ ሆነች አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ የምናገረውን አብ እንደ ነገረኝ እንዲሁ እናገራለሁ።

## ♦ ክፍል 131. የደረቀችው የበለስ ዛፍ እና ስለ እምነት የተሰጠ ትምህርት [ክፍል 54ረን ይመልከቱ]

- ወደ ቢታንያ እና ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ -

| ማቴዎስ 21፡19ለ-22 | ማርቆስ 11፡19-26 | ሉቃስ 21፡37-38 |
| --- | --- | --- |
| | 19 ማታ ማታም ከከተማ ወደ ውጭ ይወጣ ነበር። | |
| 19ለ በለሲቱም ያንጊዜውን ደረቀች። 20 ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው፡- በለሲቱ | 20 ማለዳም ሲያልፉ በለሲቱን ከሥርዋ ደርቃ አዩአት። 21 ጴጥሮስም ትዝ ብሎት፡- መምህር ሆይ፥ | |

(ማቴዎስ 21፡19ለ-22
የቀጠለ)

ያንጊዜውን እንዴት
ደረቀች? ብለው ተደነቁ።
21 ኢየሱስም መልሶ:-
እውነት እላችኋለሁ፥
እምነት ቢኖራችሁ
ባትጠራጠሩም፥ በበለሲቱ
እንደ ሆነባት ብቻ
አታደርጉም፤ ነገር ግን
ይህን ተራራ እንኳ:-
ተነቅለህ ወደ ባሕር
ተወርወር ብትሉት ይሆ
ናል፤ 22 አምናችሁም
በጸሎት የምትለምኑትን
ሁሉ ትቀበላላችሁ
አላቸው።

(ማርቆስ 11፡19-26
የቀጠለ)

እነሆ፥ የረገምሃት በለስ
ደርቃለች አለው።
22 ኢየሱስም መልሶ
እንዲህ አላቸው:-
በእግዚአብሔር እመኑ።
23 እውነት እላችኋለሁ፥
ማንም ያለው ነገር
እንዲደረግለት ቢያምን
በልቡ ሳይጠራጠር፥ ይህን
ተራራ:- ተነቅለህ ወደ
ባሕር ተወርወር ቢል ይሆ
ንለታል። 24 ስለዚህ
እላችኋለሁ፥
የጸለያችሁትን
የለመናችሁትንም ሁሉ
እንዳገኛችሁት እመኑ፥
ይሆንላችሁማል። 25
ለጸሎትም በቆማችሁ
ጊዜ፥ በሰማያት ያለው
አባታችሁ ደግሞ
ኃጢአታችሁን ይቅር
እንዲላችሁ፥ በማንም ላይ
አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር
በሉት። 26 እናንተ ግን
ይቅር ባትሉ በሰማያት
ያለው አባታችሁም
ኃጢአታችሁን ይቅር
አይላችሁም።

(ሉቃስ 21፡37-38 የቀጠለ)

37 ዕለት ዕለትም
በመቅደስ ያስተምር ነበር፥
ሌሊት ግን ደብረ ዘይት
ወደምትባል ተራራ ወጥቶ
ያድር ነበር። 38 ሕዝቡም
ሁሉ ይሰሙት ዘንድ
ማልደው በመቅደስ ወደ
እርሱ ይመጡ ነበር።

[3] [ሉቃስ 20፡1] የተሰበከው ምናልባት እነዚህ የካህናት አለቆች የተቃወሙት የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል (ማቴ. 9፡35፤ 24፡14) ይሆናል። ነገር ግን አንድ ቀን ቀደም ሲል የተደረገው የቤተ መቅደስ ማጽዳት ጉዳይ "እነዚህን" በሚለው የካሕናት አለቆች ጥያቄ ውስጥ ሳይካተት አልቀረም (ማቴ. 21፡23፤ ማር. 11፡28፤ ሉቃስ 20፡2)። ይህ ከተለያዩ የአይሁድ መሪዎች ጋር ከተደረጉት ተከታታይ የቃል በቃል ግጭቶች የመጀመሪያው ነው። ግጭቶቹ ሁሉ የሆኑት በኢየሱስ የሕማማት ሰሞን ማክሰኞ ዕለት ነበር።

# > በኢየሱስ ሥልጣን ላይ የተነሣ ግልጥ መገዳደር <

## ♦ ክፍል 132ሀ. ሊቀ ካህናት፥ የሕግ መምህራንና የሕዝብ ሽማግሌዎች ስለ ኢየሱስ ሥልጣን መጠየቃቸው

- ኢየሩሳሌም፥ በመቅደሱ ውስጥ -

ማቴዎስ 21፥23-27

23 ወደ መቅደስም ገብቶ ሲያስተምር የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሎች ወደ እርሱ ቀረቡና፦ በምን ሥልጣን እነዚህን ታደርጋለህ? ይህንስ ሥልጣን ማን ሰጠህ? አሉት።

24 ኢየሱስም መልሶ፦ እኔ ደግሞ አንዲት ነገር እጠይቃችኋለሁ፤ እናንተም ያችን ብትነግሩኝ እኔ ደግሞ እነዚህን በምን ሥልጣን እንዳደርግ እነግራችኋለሁ፤ 25 የዮሐንስ ጥምቀት ከወዴት ነበረች? ከሰማይን ወይስ ከሰው? አላቸው።

እነርሱም እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ፦ ከሰማይ ብንል፦ እንኪያስ ስለ ምን አላመናችሁበትም? ይለናል፤ 26 ከሰው ግን ብንል፥ ዮሐንስን ሁሉም እንደ ነቢይ ያዩታልና ሕዝቡን እንፈራለን አሉ።

27 ለኢየሱስም መልሰው፦ አናውቅም አሉት። እርሱም ደግሞ፦

ማርቆስ 11፥27-33

27 ደግሞም ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። እርሱም በመቅደስ ሲመላለስ፥ የካህናት አለቆችና ጻፎች ሽማግሌዎችም ወደ እርሱ መጥተው፦ 28 እነዚህን በምን ሥልጣን ታደርጋለህ? ወይስ እነዚህን ለማድረግ ይህን ሥልጣን ማን ሰጠህ? አሉት።

29 ኢየሱስም፦ እኔም አንዲት ነገር እጠይቃችኋለሁ፥ እናንተም መልሱልኝ፥ እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን እንዳደርግ እነግራችኋለሁ። 30 የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረችን ወይስ ከሰው? መልሱልኝ አላቸው።

31 እርስ በርሳቸውም ሲነጋገሩ፦ ከሰማይ ነው ብንል፦ እንግዲያውስ ስለ ምን አላመናችሁበትም? ይለናል፤ 32 ነገር ግን፦ ከሰው ነው እንበልን? አሉ፤ ሁሉ ዮሐንስን በእውነት እንደ ነቢይ

ሉቃስ 20፥1-8

1 አንድ ቀንም ሕዝቡን በመቅደስ ሲያስተምር ወንጌልንም[3] ሲሰብክ ላቸው፥ የካህናት አለቆችና ጻፎች ከሽማግሌዎች ጋር ወደ እርሱ ቀረቡና፦ 2 እስኪ ንገረን፤ እነዚህን በምን ሥልጣን ታደርጋለህ ወይስ ይህን ሥልጣን የሰጠህ ማን ነው? ብለው ተናገሩት።

3 መልሶም፦ እኔ ደግሞ አንዲት ነገር እጠይቃችኋለሁ፥ እናንተም ንገሩኝ፤ 4 የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረችን ወይስ ከሰው? አላቸው።

5 እርስ በርሳቸውም ሲነጋገሩ፦ ከሰማይ ብንል፦ ስለ ምን አላመናችሁበትም? ይለናል፤ 6 ከሰው ብንል ግን ሕዝቡ ሁሉ ይወግሩናል፤ ዮሐንስ ነቢይ እንደ ነበረ ሁሉ ያምኑ ነበርና አሉ።

7 መልሰውም፦ ከወዴት እንደ ሆነ አናውቅም አሉት።

| (ማቴዎስ 21፡23-27 የቀጠለ) | (ማርቆስ 11፡27-33 የቀጠለ) | (ሉቃስ 20፡1-8 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን እንዳደርግ አልነግራችሁም አላቸው። | ያዩት ነበርና ሕዝቡን ፈሩ። 33 ለኢየሱስም መልሰው፡- አናውቅም አሉት<br>ኢየሱስም፡- እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን እንዳደርግ አልነግራችሁም አላቸው። | 8 ኢየሱስም፡- እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን እንዳደርግ አልነግራችሁም አላቸው። |

## ♦ ክፍል 132ለ. የኢየሱስ መልሶች ከራሱ ጥያቄዎች ጋር እና ሦስት ምሳሌዎች

- ኢየሩሳሌም፥ በመቅደሱ ውስጥ -

ማቴዎስ 21፡28-22፡14

28 ነገር ግን ምን ይመስላችኋል? አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት፤ ወደ አንደኛው ቀርቦ፡- ልጄ ሆይ፥ ዛሬ ሂድና በወይኔ አትክልት ሥራ አለው።

29 እርሱም መልሶ፡- አልወድም አለ፤ ኋላ ግን ተጸጸተና ሄደ።

30 ወደ ሁለተኛውም ቀርቦ እንዲሁ አለው እርሱም መልሶ፡- እሺ ጌታዬ አለ፤ ነገር ግን አልሄደም።

31 ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ ያደረገ ማን ነው?

ፊተኛው አሉት።

ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡- እውነት እላችኋለሁ፥ ቀራጮችና ጋለሞቶች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት ይቀድሙአችኋል። 32 ዮሐንስ በጽድቅ መንገድ መጥቶላችሁ ነበርና፥ አላመናችሁበትም፤ ቀራጮችና ጋለሞቶች ግን አመኑበት፤ እናንተም ይህን አይታችሁ ታምኑበት ዘንድ በኋላ ንስሐ አልገባችሁም።

| | ማርቆስ 12፡1-12 | ሉቃስ 20፡9-19 |
|---|---|---|
| 33 ሌላ ምሳሌ[4] ስሙ። የወይን አትክልት የተከለ ባለቤት ሰው ነበረ፤ ቅጥርም ቀጠረለት፥ መጥመቂያም ማሰለት፥ ግንብም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። [ኢሳይይስ 5፡2] 34 የሚያፈራበትም ጊዜ ሲቀርብ፥ ፍሬውን ሊቀበሉ ባሮቹን ወደ | 1 በምሳሌም[4] ይነግራቸው ጀመር። አንድ ሰው የወይን አትክልት ተከለ፥ ቅጥርም ቀጠረለት፥ መጥመቂያም ማሰለት፥ ግንብም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። [ኢሳያይስ 5፡2] 2 በጊዜውም ከወይን | 9 ይህንም ምሳሌ[4] ለሕዝቡ ይላቸው ጀመር። አንድ ሰው የወይን አትክልት ተከለ ለገበሬዎችም አከራይቶ ለብዙ ዘመን ወደ ሌላ አገር ሄደ። 10 በጊዜውም ከወይኑ አትክልት ፍሬ እንዲሰጡት አንድ ባሪያ ወደ ገበሬዎች ላከ፤ ገበሬዎቹ ግን |

[4] [ማቴ. 21፡33፤ ማር. 12፡1፤ ሉቃስ 20፡9] ይህ ምሳሌ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ውድ ልጅ (ሉቃስ 20፡13) ሕዝቡ እንዳልተቀበሉት ሲሆን፥ የሁለቱ ልጆች ምሳሌ ደግሞ (ማቴ. 21፡28-32) መጥምቁ ዮሐንስን አንቀበልም ያሉ አድማጮችን የሚከስ ነው።

(ማቴዎስ 21፡28-22፡14 የቀጠለ)

ገበሬዎች ላከ።

35 ገበሬዎቹም ባሮቹን ይዘው አንዱን ደበደቡት አንዱንም ገደሉት ሌላውንም ወገሩት። 36 ደግሞ ከፊተኞች የሚበዙ ሌሎች ባሮችን ላከ፥ እንዲሁም አደረጉባቸው።

37 በኋላ ግን፦ ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ ልጁን ላከባቸው።

38 ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ እርስ በርሳቸው፦ ወራሹ ይህ ነው፤ ኑ፥ እንግደለውና ርስቱን እናግኝ ተባባሉ። 39 ይዘውም ከወይኑ አትክልት አወጡና ገደሉት።

40 እንግዲህ የወይኑ አትክልት ጌታ በሚመጣ ጊዜ በእነዚህ ገበሬዎች ምን ያደርግባቸዋል?

41 እነርሱም፦ ክፉዎችን በክፉ ያጠፋቸዋል፥ የወይኑንም አትክልት ፍሬውን በየጊዜው ለሚያስረክቡ ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጠዋል አሉት።

42 ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፦

‘‘ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን

(ማርቆስ 12፡1-12 የቀጠለ)

አትክልት ፍሬ ከገበሬዎቹ እንዲቀበል አንድ ባሪያ ወደ ገበሬዎቹ ላከ፤ 3 ይዘውም ደበደቡት ባዶውንም ሰደዱት። 4 ዳግመኛም ሌላውን ባሪያ ወደ እነርሱ ላከ እርሱንም ወግረው ራሱን አቈሰሉት አዋርደውም ሰደዱት። 5 ሌላውንም ላከ፤ እርሱንም ገደሉት፥ ከሌሎችም ከብዙዎች አንዳንዱን ደበደቡ አንዳንዱንም ገደሉ።

6 የሚወደው አንድ ልጅ ገና ነበረው፤ ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ እርሱን ከሁሉ በኋላ ወደ እነርሱ ላከ።

7 እነዚያ ገበሬዎች ግን እርስ በርሳቸው፦ ወራሹ ይህ ነው፤ ኑ፥ እንግደለው፥ ርስቱም ለኛ ይሆናል ተባባሉ። 8 ይዘውም ገደሉት፥ ከወይኑም አትክልት ወደ ውጭ ጣሉት።

9 እንግዲህ የወይኑ አትክልት ጌታ ምን ያደርጋል? ይመጣል ገበሬዎቹንም ያጠፋል፥ የወይኑንም አትክልት ለሌሎች ይሰጣል።

10-11 ‘‘ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ

(ሉቃስ 20፡9-19 የቀጠለ)

ደበደቡት ባዶውንም ሰደዱት። 11 ጨምሮም ሌላውን ባሪያ ላከ፤ እነርሱም ያን ደግሞ ደበደቡት አዋርደውም ባዶውን ሰደዱት። 12 ጨምሮም ሦስተኛውን ላከ፤ እነርሱም ይህን ደግሞ አቍስለው አወጡት።

13 የወይኑም አትክልት ጌታ፦ ምን ላድርግ? የምወደውን ልጄን እልካለሁ፤ ምናልባት እርሱን አይተው ያፍሩታል አለ።

14 ገበሬዎቹ ግን አይተውት እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ፦ ወራሹ ይህ ነው፤ ርስቱ ለእኛ እንዲሆን ኑ እንግደለው አሉ። 15 ከወይኑም አትክልት ወደ ውጭ አውጥተው ገደሉት።

እንግዲህ የወይኑ አትክልት ጌታ ምን ያደርጋቸዋል? 16 ይመጣል እነዚህንም ገበሬዎች ያጠፋል፥ የወይኑንም አትክልት ለሌሎች ይሰጣል።

ይህንም በሰሙ ጊዜ፦ ይህስ አይሁን አሉ።

17 እርሱ ግን ወደ እነርሱ ተመልክቶ፦ እንግዲህ፦

| (ማቴዎስ 21፡28-22፡14 የቀጠለ) | (ማርቆስ 12፡1-12 የቀጠለ) | (ሉቃስ 20፡9-19 የቀጠለ) |
| --- | --- | --- |
| ራስ ሆነ፤ ይህም ከጌታ<br>ዘንድ ሆነ፥<br>ለዓይኖቻችንም ድንቅ<br>ነው’’<br>የሚለውን ከቶ በመጽሐፍ<br>አላነበባችሁምን?<br>[መዝሙር 118፡22-23] | የማዕዘን ራስ ሆነ፤<br>ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ፥<br>ለዓይኖቻችንም ድንቅ<br>ነው።’’ [መዝሙር<br>118፡22-23]<br>የሚለውን ይህን መጽሐፍ<br>አላነበባችሁምን? | ‘‘ግንበኞች የናቁት<br>ድንጋይ እርሱ የማዕዘን<br>ራስ ሆነ’’<br>ተብሎ የተጻፈው ይህ<br>ምንድር ነው? [መዝሙር<br>118፡22] |
| 43 ስለዚህ እላችኋለሁ፥<br>የእግዚአብሔር መንግሥት<br>ከእናንተ ትወሰዳለች[5]<br>ፍሬዋንም ለሚያደርግ<br>ሕዝብ ትሰጣለች። 44<br>በዚህም ድንጋይ ላይ<br>የሚወድቅ ይቀጠቀጣል፤<br>ድንጋዩ ግን<br>የሚወድቅበትን ሁሉ<br>ይፈጨዋል። | | 18 በዚያም ድንጋይ ላይ<br>የሚወድቅ ሁሉ<br>ይቀጠቀጣል፤<br>የሚወድቅበትን ሁሉ ግን<br>ይፈጨዋል አለ። |
| 45 የካህናት አለቆችና<br>ፈሪሳውያንም ምሳሌዎቹን<br>ሰምተው ስለ እነርሱ እንደ<br>ተናገረ አስተዋሉ፤ 46<br>ሊይዙትም ሲፈልጉት ሳሉ<br>ሕዝቡ እንደ ነቢይ ስላዩት<br>ፈሩአቸው።<br>22:1 ኢየሱስም መለሰ | 12 ምሳሌውንም ስለ<br>እነርሱ እንደ ተናገረ<br>አውቀዋልና ሊይዙት<br>ፈለጉ፥ ነገር ግን ሕዝቡን<br>ፈሩ። ትተውትም ሄዱ። | 19 የካህናት አለቆችና<br>ጻፎችም ይህን ምሳሌ<br>በእነርሱ ላይ እንደ ተናገረ<br>አውቀው በዚያች ሰዓት<br>እጃቸውን ሊጭኑበት ፈለጉ<br>ነገር ግን ሕዝቡን ፈሩ። |

ደግሞም በምሳሌ ነገራቸው እንዲህም አለ፦ 2 መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሰርግ ያደረገ
ንጉሥን ትመስላለች። 3 የታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ ባሮቹን ላከ
ሊመጡም አልወደዱም።

4 ደግሞ ሌሎችን ባሮች ልኮ፦ የታደሙትን፦ እነሆ፥ ድግሴን አዘጋጀሁ፥
ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፥ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ
በሉአቸው አለ።

5 እነርሱ ግን ቸል ብለው አንዱ ወደ እርሻው፥ ሌላውም ወደ ንግዱ ሄደ፤ 6
የቀሩትም ባሮቹን ይዘው አንገላቱአቸው ገደሉአቸውም። 7 ንጉሡም ተቈጣ፥
ጭፍሮቹንም ልኮ እነዚያን ገዳዮች አጠፋ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ።[6]

[5] [ማቴ. 21፡43] ኢየሱስንና የመንፈሳዊ ሕይወት መስፈርቱን አልቀበል ያለውን ይህን የእስራኤላውያን ትውልድ እግዚአብሔርም ያልተቀበለው የመሆኑ ነገር ትኩረት የሳበ ጉዳይ ነበር (ሉቃስ 19፡41-44፥ ክፍል 128ለ፤ ማቴ. 21፡19፤ ማር. 11፡14፥ ክፍል 129ሀ)። ይህ መንግሥት የሚሰጠው አዲስ “ሕዝብ” በዚህ ጊዜ ለወንጌል ጥሪ ምላሽ ለሚሰጡ አይሁዶችም ሆኑ አሕዛብ (ማቴ. 22፡8-10) ወይም ወደፊት ጥሪውን ሰምተው በንስሐ ለሚመለሱ የእስራኤል ትውልዶች ነው (ማቴ. 23፡39፥ ክፍል 137ለ)።

(ማቴዎስ 21፡28-22፡14 የቀጠለ)

8 በዚያን ጊዜ ባሮቹን፦ ሰርጉስ ተዘጋጅቶአል፥ ነገር ግን የታደሙት የማይገባቸው
ሆኑ፤ 9 እንግዲህ ወደ መንገድ መተላለፊያ ሄዳችሁ ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ጥሩ
አለ። 10 እነዚያም ባሮች ወደ መንገድ ወጥተው ያገኙትን ሁሉ ክፉዎችንም
በጎዎችንም ሰበሰቡ፤ የሰርጉንም ቤት ተቀማጮች ሞሉት።

11 ንጉሡም የተቀመጡትን ለማየት በገባ ጊዜ በዚያ የሰርግ ልብስ ያለበሰ አንድ ሰው
አየና፦ ወዳጄ ሆይ፥ 12 የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው
እርሱም ዝም አለ።

13 በዚያን ጊዜ ንጉሡ አገልጋዮቹን፦ እጁንና እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው
ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ።

14 የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና።

## ♦ ክፍል 133. ፈሪሳውያን እና የሄሮድስ ወገን የሆኑ ሰዎች ለቄሣር ግብር ስለ መክፈል ኢየሱስን በመጠየቅ ሊያጠምዱት ያደረጉት ሙከራ

- ኢየሩሳሌም፥ ምናልባት በመቅደሱ ውስጥ -

ማቴዎስ 22፡15-22

15 ስለዚህ ፈሪሳውያን
ሄዱና እንዴት አድርገው
በነገር እንዲያጠምዱት
ተማከሩ። 16 ደቀ
መዛሙርታቸውንም
ከሄሮድስ ወገን[7] ጋር
ላኩበት፥ እነርሱም፦
መምህር ሆይ፥ እውነተኛ
እንደ ሆንህ በእውነትም
የእግዚአብሔርን መንገድ

ማርቆስ 12፡13-17

13 በንግግርም
ሊያጠምዱት
ከፈሪሳውያንና[7] ከሄሮድስ
ወገን የሆኑትን ወደ እርሱ
ላኩ። 14 መጥተውም፦
መምህር ሆይ፥ የሰውን ፊት
ሳትመለከት በእውነት
የእግዚአብሔር መንገድ
ታስተምራለህና እውነተኛ
እንደ ሆንህ ለማንምም

ሉቃስ 20፡20-26

20 ሲጠባበቁም ወደ ገዢ
ግዛትና ሥልጣን አሳልፈው
እንዲሰጡት ጻድቃን
መስለው በቃሉ
የሚያጠምዱትን ሸማቂዎች
ሰደዱበት። 21
ጠይቀውም፦ መምህር ሆ
ይ፥ እውነትን
እንድትናገርና
እንድታስተምር ለሰው

---

[6] [ማቴ. 22፡7] ይህ በ70 ዓ.ም. ይሆን የነበረውን የኢየሩሳሌም መፍረስ በምሳሌያዊ አባባል የሚያመለክተው ታሪክ፥ ስለ ሁኔታው ከተነገሩት ትንቢቶች አንዱ ነው። ይህን ጉዳይ ኢየሱስ ቀደም ሲል የጠቀሰው ሲሆን (ሉቃስ 19፡43-44፥ ክፍል 128ለ)፥ ያንኑ በድጋሚ ማንሣቱ ነው (ማቴ. 23፡37-38፥ ክፍል 137ለ፤ ማቴ. 24፡1-2፤ ማር. 13፡1-2፤ ሉቃስ 21፡5-6፥ ክፍል 139ሀ)።

[7] [ማቴ. 22፡16፤ ማር. 12፡13] ፈሪሳውያንና የሄሮድስ ተከታዮች በጋራ ዓላማ መተባበራቸው በጣም የተለመደ አይደለም። ሮማውያን የፍልስጥኤም ምድርን መያዛቸው ፈሪሳውያንን፥ በተለይም ቀረጥ እንዲከፍሉ የተደረጉትንና ይሁዳ ውስጥ ያሉትን በጣም ያስቆጣቸዋል (ማቴ. 22፡17)። ማርቆስ 12፡14 በአንጻሩ ደግሞ የሄሮድስ ደጋፊዎች የሮማውያንን በምድሪቱ መገኘት ይደግፉት ነበር። ምክንያቱም የሄሮድስ ቤተሰብ የመሪነት ሥልጣን ምንጭ ሮማውያን ነበሩ። ኢየሱስ ጥያቄያቸውን በየትኛውም አቅጣጫ ቢመልሰው (ማቴ. 22፡17፤ ማር. 12፡15፤ ሉቃስ 20፡22)፥ እነርሱ የሚገነዘቡት ከሁለቱ ቡድኖች የአንዳቸውን ትምህርት እንደሻረ አድርገው ነበር። በመሆኑም ከፈሪሳውያን ጋር የማይስማማ ቢሆን በሕዝቡ (ሉቃስ 20፡26)፥ ከሄሮድስ ደጋፊዎች ጋር ባይስማማ ደግሞ በሄሮድስ ዘንድ (ሉቃስ 20፡20)፥ በደለኛ ይሆን ነበር። ኢየሱስ ግን አስተዋይነት በተሞላ መልሱ ሁለቱንም ወጥመዶች አመለጠ።

<u>(ማቴዎስ 22፥ 15-22 የቀጠለ)</u>

እንድታስተምር እናውቃለን፥ ለማንምም አታደላም፥ የሰውን ፊት አትመለከትምና፤ 17 እንግዲህ ምን ይመስልሃል? ንገረን ለቄሣር ግብር መስጠት ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም? አሉት።

18 ኢየሱስም ክፋታቸውን አውቆ፦ እናንተ ግብዞች፥ ስለ ምን ትፈትኑኛላችሁ? 19 የግብሩን ብር አሳዩኝ አለ። እነርሱም ዲናር አመጡለት። 20 እርሱም፦ ይህች መልክ ጽሕፈቲቱስ የማን ናት? አላቸው።

21 የቄሣር ነው አሉት።

በዚያን ጊዜ፦ እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው።

22 ይህንም ሰምተው ተደነቁ፥ ትተውትም ሄዱ።

<u>(ማርቆስ 12፥ 13-17 የቀጠለ)</u>

እንዳታደላ እናውቃለን፤ ለቄሣር ግብር መስጠት ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም? እንሰጥን ወይስ አንሰጥ? አሉት። 15 እርሱ ግን ግብዝነታቸውን አውቆ፦

ለምን ትፈትኑኛላችሁ? አየው ዘንድ አንድ ዲናር አምጡልኝ አላቸው።

16 እነርሱም አመጡለት። ይህች መልክ ጽሕፈቲቱስ የማን ናት? አላቸው፤ እነርሱም፦

የቄሣር ናት አሉት።

17 ኢየሱስም መልሶ፦ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው።

በእርሱም ተደነቁ።

<u>(ሉቃስ 20፥ 20-26 የቀጠለ)</u>

ፊትም እንዳታደላ እናውቃለን፥ በእውነት የእግዚአብሔርን መንገድ ታስተምራለህ እንጂ፤ 22 ለቄሣር ግብር ልንሰጥ ተፈቅዶአልን? ወይስ አልተፈቀደም? አሉት።

23 እርሱ ግን ተንኰላቸውንም ተመልክቶ፦ ስለ ምን ትፈትኑኛላችሁ? አንድ ዲናር አሳዩኝ፤ 24 መልኩ ጽሕፈቱስ የማን ነው? አላቸው። መልሰውም፦ የቄሣር ነው አሉት።

25 እርሱም፦ እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አስረክቡ አላቸው።

26 በሕዝቡም ፊት በቃሉ ሊያጠምዱት አልቻሉም በመልሱም እየተደነቁ ዝም አሉ።

---

[8] [ማቴ. 22፥23፤ ማር. 12፥18፤ ሉቃስ 20፥27] ግጭቶች በበዙበት አንድ ማክሰኞ ዕለት ሰዱቃውያን እንደ ኢየሱስ በትንሣኤ ሙታን የሚያምን ማንም ሰው ሊመልሰው የማይችለው ሥነ-መለኮታዊ ጥያቄ ያገኙ መሰላቸው (ዮሐ. 11፥23-26፥ ክፍል 118ለ)። የወንድምን ሚስት የማግባት ሕግ (ዘዳ. 25፥7-10) የትንሣኤን መኖር ሽፍኖታል ብለው አመኑ። ኢየሱስ በመልሱ ዘጸአት 3፥6 ውስጥ ያለውን ቃል አብራራው (ማቴ.22፥32፤ ማር.12፥26)። እንዲሁም ያለምንም የትንሣኤ ተስፋ ስለመቅረት ሰዱቃውያን ያስተማሩት አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ በሞቱ ጊዜ ሠርቶ ቢሆን ኖሮ የሙሴ ትእዛዝ ዘጸአት 3፥15-16 (ሉቃስ 20፥37) ፈጽሞ ተገቢ አይሆን እንደነበር ለማመልከት ተናገረ።

## ♦ ክፍል 134. ሰዱቃውያን ስለ ትንሣኤ ያነሡት አደናጋሪ ጥያቄ

- ኢየሩሳሌም፥ ምናልባት በመቅደሱ ውስጥ -

**ማቴዎስ 22፡23-33**

23 በዚያን ቀን፡- ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን[8] ወደ እርሱ ቀረቡ፥ 24 እንዲህም ብለው ጠየቁት፡- መምህር ሆይ፥ ሙሴ አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ሲሞት ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ አለ። [ዘዳግም 25፡5] 25 ሰባት ወንድማማች በእኛ ዘንድ ነበሩ፤ ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ሞተ፥ ዘርም ስለሌለው ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት፤ 26 እንዲሁ ደግሞ ሁለተኛው ሦስተኛውም፥ እስከ ሰባተኛው ድረስ። 27 ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ሞተች። 28 ሁሉ አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀንስ፥ ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች?

29 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ።

**ማርቆስ 12፡18-27**

18 ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን[8] ወደ እርሱ መጥተው ጠየቁት እንዲህም አሉት፡- 19 መምህር ሆይ፥ ሙሴ፡- የአንድ ሰው ወንድም ሚስቱን ትቶ ልጅ ሳያስቀር ቢሞት፥ ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ ብሎ ጻፈልን። [ዘዳግም 25፡5] 20 ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ፤ ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ዘር ሳያስቀር ሞተ፤ 21 ሁለተኛውም አገባት፥ ዘርም ሳይተው ሞተ፤ ሦስተኛውም እንዲሁ፤ 22 ሰባቱም አገቡአት፥ ዘርም አላስቀሩም። ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ደግሞ ሞተች። 23 ሰባቱ አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀን ሲነሡ ከእነርሱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች?

24 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ስለዚህ የምትስቱ አይደለምን?

**ሉቃስ 20፡27-40**

27 ትንሣኤ ሙታንንም የሚክዱ ከሰዱቃውያን[8] አንዳንዶቹ ቀርበው ጠየቁት፥ 28 እንዲህ ሲሉ፡- መምህር ሆይ፥ ሙሴ፡- ሚስት ያለችው የአንድ ሰው ወንድም ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፥ ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ ብሎ ጻፈልን። [ዘዳግም 25፡5] 29 እንግዲያስ ሰባት ወንድማማች ነበሩ፤ የፊተኛውም ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ፤ 30-31 ሁለተኛውም አገባት፥ ሦስተኛውም፥ እንዲሁም ሰባቱ ደግሞ ልጅ ሳይተዉ ሞቱ። 32 ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ደግሞ ሞተች። 33 እንግዲህ ሰባቱ አግብተዋታልና ሴቲቱ በትንሣኤ ከእነርሱ ለማንኛቸው ሚስት ትሆናለች?

34 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡-

የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ ይጋባሉም፥ 35 ያን ዓለምና ከሙታን ትንሣኤ ሊያገኙ የሚገባቸው እነዚያ ግን አያገቡም አይጋቡምም፥ እንደ

(ማቴዎስ 22፥23-33 የቀጠለ)

30 በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም። 31-32 ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን፦ እኔ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን? [ዘጸአት 3፥6] የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም። 33 ሕዝቡም ይህን ሰምተው በትምህርቱ ተገረሙ።

(ማርቆስ 12፥18-27 የቀጠለ)

25 ከሙታንስ ሲነሡ በሰማያት እንዳሉ መላእክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም፥ አይጋቡምም። 26 ስለ ሙታን ግን እንዲነሡ እግዚአብሔር፦ እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ እንዳለው በሙሴ መጽሐፍ በቍጥቋጦው ዘንድ የተጻፈውን አላነበባችሁምን? [ዘጸአት 3፥6] 27 የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም። እንግዲህ እጅግ ትስታላችሁ።

(ሉቃስ 20፥27-40 የቀጠለ)

መላእክት ናቸውና፥ 36 ሊሞቱም ወደ ፊት አይቻላቸውም፥ የትንሣኤም ልጆች ስለ ሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው። 37 ሙታን እንዲነሡ ግን ሙሴ ደግሞ በቍጥቋጦው ዘንድ ጌታን የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ በማለቱ አስታወቀ፤ [ዘጸግም 3፥6] 38 ሁሉ ለእርሱ ሕያዋን ስለ ሆኑ፥ የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም። 39 ከጻፎችም አንዳንዶቹ መልሰው፦ መምህር ሆይ፥ መልካም ተናገርህ አሉት። 40 ወደ ፊትም አንድ ነገር ስንኳ ሊጠይቁት አልደፈሩም።

## ♦ ክፍል 135. የአንድ ፈሪሳዊ ሕግ ነክ ጥያቄ

[ክፍል 103ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም፥ ምናልባት በመቅደሱ ውስጥ -

ማቴዎስ 22፥34-40

34 ፈሪሳውያንም ሰዱቃውያንን ዝም እንዳሰኛቸው በሰሙ ጊዜ አብረው ተሰበሰቡ። 35 ከእነርሱም አንድ ሕግ አዋቂ ሊፈትነው፦ 36 መምህር ሆይ፥ ከሕግ ማናቸይቱ ትእዛዝ ታላቅ ናት? ብሎ ጠየቀው።

37 ኢየሱስም እንዲህ አለው፦ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። [ዘዳግም 6፥5] 38 ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። 39 ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም፦

ማርቆስ 12፥28-34

28 ከጻፎችም አንዱ ቀርቦ ሲከራከሩ ሰማና መልካም አድርጎ እንደ መለሰላቸው አስተውሎ፦ ከሁሉ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ማናቸይቱ ናት? ብሎ ጠየቀው።

29 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ፦ እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥ 30 አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ

(ማቴዎስ 22፡34-40 የቀጠለ)

ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። [ዘሌዋውያን 19፡18] 40 በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል።

(ማርቆስ 12፡28-34 የቀጠለ)

ይህች ናት። [ዘዳግም 6፡4-5] 31 ሁለተኛይቱም፡- ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። [ዘሌዋውያን 19፡18] ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም።

32 ጻፊውም፡- መልካም ነው፥ መምህር ሆይ፤ አንድ ነው ከእርሱም በቀር ሌላ የለም ብለህ በእውነት ተናገርህ፤ 33 በፍጹም ልብ በፍጹም አእምሮም በፍጹም ነፍስም በፍጹም ኃይልም እርሱን መውደድ [ዘሌዋውያን 19፡18፤ ዘዳግም 4፡35፥ 6፡5]፥ ባልንጀራንም እንደ ራስ መውደድ በሙሉ ከሚቃጠል መሥዋዕትና ከሌላው መሥዋዕት ሁሉ የሚበልጥ ነው አለው።

34 ኢየሱስም በአእምሮ[9] እንደ መለሰ አይቶ፡- አንተ ከእግዚአብሔር መንግሥት የራቅህ አይደለህም አለው። ከዚህም በኋላ ማንም ሊጠይቀው አልደፈረም።

# > ከጠላቶቹ ለተሰነዘሩ መገዳደሮች የኢየሱስ መልስ <

## ♦ ክፍል 136. ክርስቶስ ከዳዊት ጋር እንደ ልጅ እና እንደ ጌታ ያለው ግንኙነት

- ኢየሩሳሌም፥ በመቅደሱ ውስጥ -

ማቴዎስ 22፡41-46

41-42 ፈሪሳውያንም ተሰብስበው ሳሉ፥ ኢየሱስ፡-[10] ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው? ብሎ ጠየቃቸው።

የዳዊት ልጅ ነው አሉት። 43-44 እርሱም፡- እንኪያስ ዳዊት፡-

ማርቆስ 12፡35-37

35 ኢየሱስም በመቅደስ ሲያስተምር

መልሶ እንዲህ አለ፡-

ሉቃስ 20፡41-44

41 እንዲህም አላቸው፡- ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው

[9] [ማርቆስ 12፡34] ኢየሱስ ለሰጠው መልስ ይህ የሕግ ሊቅ የነበረው በጎ አመለካከት ባልደረባዎቹ የሆኑ ፈሪሳውያንን ሳያስደነግጣቸው አልቀረም። እንዲህ ካሉ ተንኮለኞች ተቃዋሚዎቹ መካከል፥ ይህን ልቡ ለደጎንነት ቃል የተከፈተ እና ምናልባት ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚበቃ ሰው፥ ለይቶ ማወቁ የኢየሱስን አስደናቂ የመለየት ችሎታ ያመለክታል።

(ማቴዎስ 22፡41-46 የቀጠለ)

‘‘ጌታ ጌታዬን፡- ‘ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው’’’

ሲል እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል? [ምዝሙር 110፡1] 45 ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው፥ እንዴት ልጁ ይሆናል? አላቸው። 46 አንድም ቃል ስንኳ ይመልስለት ዘንድ የተቻለው የለም፥ ከዚያ ቀንም ጀምሮ ወደ ፊት ማንም ሊጠይቀው አልደፈረም።

(ማርቆስ 12፡35-37 የቀጠለ)

ጻፎች ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው እንዴት ይላሉ? 36 ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ፡-

‘‘ጌታ ጌታዬን፡- ‘ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው’’’

አለ። [መዝሙር 110፡1]

37 ዳዊትም ራሱ ጌታ አለው፤ እንዴትስ ልጁ ይሆናል?

ብዙ ሕዝብም በደስታ ይሰሙት ነበር።

(ሉቃስ 20፡41-44 የቀጠለ)

እንዴት ይላሉ? 42-43 ዳዊትም ራሱ በመዝሙራት መጽሐፍ፡-

‘‘ጌታ ጌታዬን፡- ‘ጠላቶችህን ለእግርህ መርገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው’’’

ይላል። [መዝሙር 110፡1]

44 እንግዲህ ዳዊት፡- ጌታ ብሎ ይጠራዋል፥ እንዴትስ ልጁ ይሆናል?

## ♦ ክፍል 137ሀ. ስለ ፈሪሳውያን እና የሕግ መምህራን የተነገሩ ሰባት ወዮታዎች [ክፍል 54ሠና 107ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም፥ በመቅደሱ ውስጥ -

ማቴዎስ 23፡1-36

1 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነገራቸው፡- 2 ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል። 3 ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ[11] ጠብቁትም፥ ነገር ግን እየተናገሩ

ማርቆስ 12፡38-40

38-39 ሲያስተምርም እንዲህ አለ፡- ረጃጅም ልብስ ለብሰው መዞርን፥ በገበያም ሰላምታን፥ በምኵራብም የከበሬታን ወንበር፥ በግብርም የከበሬታን ስፍራ ከሚወዱ ከጻፎች ተጠበቁ፤

ሉቃስ 20፡45-47

45 ሕዝቡም ሁሉ ሲሰሙ ደቀ መዛሙርቱን፡- 46 ረጃጅም ልብስ ለብሰው መዞር ከሚፈልጉ፥ በገበያም ሰላምታ፥ በምኵራብም የከበሬታ ወንበር፥ በምሳም የከበሬታ ስፍራ ከሚወዱ ከጻፎች ተጠበቁ፤

[10] [ማቴ. 22፡41] ኢየሱስ ጠላቶቹን ከገታ በኋላ ራሱ ጥያቄ ያቀርባል። በአንድ ጥያቄ የጠላቶቹን ቅስም በመስበር (ማቴ. 22፡46) እና የተሰበሰበውን ሕዝብ በማስደሰት (ማር. 12፡37) መሚሑ ሰውም እግዚአብሔርም (‘‘ጌታ’’ እና ‘‘ልጅ’’፥ ማቴ. 22፡45፤ ማር. 12፡37፤ ሉቃስ 20፡44) መሆኑን በብሉይ ኪዳን ከሰፈረው የእግዚአብሔር ቃል አረጋገጠ።

| (ማቴዎስ 23፡1-36 የቀጠለ) | (ማርቆስ 12፡38-40 የቀጠለ) | (ሉቃስ 20፡45-47 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| አያደርጉትምና እንደ<br>ሥራቸው አታድርጉ። 4<br>ከባድና አስቸጋሪ ሸክም<br>ተብትበው በሰው ትከሻ<br>ይጭናሉ፥ እነርሱ ግን<br>በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት<br>አይወዱም። | | |
| 5 ለሰውም እንዲታዩ<br>ሥራቸውን ሁሉ<br>ያደርጋሉ፤ ስለዚህ<br>አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ<br>ዘርፋንም ያስረዝማሉ፥ 6 | 40 የመበለቶችን ቤት<br>የሚበሉ ጸሎታቸውንም<br>በማስረዘም የሚያመካኙ<br>እነዚህ የባሰ ፍርድ<br>ይቀበላሉ። | 47 የመበለቶችን ቤት<br>የሚበሉ ጸሎታቸውንም<br>በማስረዘም የሚያመካኙ፥<br>እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ<br>አለ። |

በምሳም የከበሬታ ስፍራ፥ በምኵራብም የከበሬታ ወንበር፥ 7 በገበያም ሰላምታና፦
መምህር ሆይ መምህር ሆይ ተብለው እንዲጠሩ ይወዳሉ።

8 እናንተ ግን፦ መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለ ሆነ
እናንተም ሁላችሁ ወንድማማች ናችሁ። 9 አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና
በምድር ላይ ማንንም፦ አባት ብላችሁ አትጥሩ። 10 ሊቃችሁ አንድ እርሱም ክርስቶስ
ነውና፦ ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ። 11 ከእናንተም የሚበልጠው አገልጋያችሁ
ይሆናል። 12 ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፥ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ
ይላል።

13 እናንተ[12] ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት
ስለምትዘጉ፥ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።
14 እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን
ቤት ስለምትበሉ፥ ወዮላችሁ፤ ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ።

15 እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ
ስለምትዞሩ፥ በሆነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ
ስለምታደርጉት፥ ወዮላችሁ።

[11] (ማቴ. 23፡3) ኢየሱስ ሕግ አዋቂዎችንና ፈሪሳውያንን እንደ ግብዞች (ማቴ. 23፡13፥ 15፥ 23፥ 25፥ 27፥ 29)፥ "እንደዕውሮች መሪዎች" (ማቴ. 23፡16) የሚያወግዝበት ጊዜ ቢቃረብም፥ የሙሴን ሕግ የማስፈጸም ሥልጣናቸውን ተቀብሏል። ሕግን በታማኝነት እስካስተማሩ ድረስ ሰው ሊታዘዛቸው ይገባ ነበር። ልማዳቸው የሕግን ምንነት ከሳተ (ማቴ. 5፡21-48፥ ክፍል 54ሠ) ወይም የሕግን አስተምህሮ ከሻረ ግን (ማቴ. 15፡1-20፤ ማር. 7፡1-23፥ ቁጥር 77)፥ ትእዛዛቸው ሊከበር አይገባውም ነበር።

[12] (ማቴ. 23፡13) የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን በሥፍራው ቆይተው እነዚህን ቃላት የመስማት አለመስማታቸው ጉዳይ አከራካሪ ነው። ይሁን እንጂ ነበሩ የሚለው አመለካከት ያመዝናል። ምክንያቱም "ወዮላችሁ" የሚለው ቃል ("እናንተ") ማለትን የሚያመለክት ነው። ኢየሱስ ይህን ቃል በሚናገርበት ጊዜ ገና ቤተ መቅደስ ውስጥ ስለነበር፥ ሰዎቹ ቃሉን ሊሰሙ ከሚችሉበት ርቀት ላይ እንደሚሆኑ ይገመታል። ቤተ መቅደሱን ሁለት ጊዜ ከማጽዳቱ (ክፍል 31፥ 129ለ) ባሻገር የኢየሱስ ቁጣ ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ እዚህ ተገልጧል። እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ለእግዚአብሔር መንግሥት መብቃት አለመቻላቸው በዚህ አጋጣሚ ተመልክቷል።

(ማቴዎስ 23፡ 1-36 የቀጠለ)

16 እናንተ፡- ማንም በቤተ መቅደስ የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በቤተ
መቅደስ ወርቅ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል የምትሉ፥ ዕውሮች መሪዎች፥
ወዮላችሁ። 17 እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች፥ ማናቸው ይበልጣል? ወርቁ ነውን?
ወይስ ወርቁን የቀደሰው ቤተ መቅደስ? 18 ደግማችሁም፡- ማንም በመሠዊያው
የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በላዩ ባለው መባ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል
ትላላችሁ። 19 እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች፥ ማናቸው ይበልጣል? መባው ነውን?
ወይስ መባውን የሚቀድሰው መሠዊያው? 20 እንግዲህ በመሠዊያው የሚምለው
በእርሱና በእርሱ ላይ ባለው ሁሉ ይምላል፤ 21 በቤተ መቅደስም የሚምለው
በእርሱና በእርሱ በሚኖረው ይምላል፤ 22 በሰማይም የሚምለው በእግዚአብሔር
ዙፋንና በእርሱ ላይ በተቀመጠው ይምላል።

23 እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ከአዝሙድና ከእንስላል ከከሙንም
አሥራት ስለምታወጡ፥ ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንም፥ በሕግ ያለውን ዋና
ነገር ስለምትተዉ፥ ወዮላችሁ፤ ሌላውን ሳትተዉ ይህን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር።
24 እናንተ ዕውሮች መሪዎች፥ ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ።

25 እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በውስጡ ቅሚያና ስስት ሞልቶ ሳለ
የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለምታጠሩ፥ ወዮላችሁ። 26 አንተ ዕውር ፈሪሳዊ፥
ውጭው ደግሞ ጥሩ እንዲሆን አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጡን አጥራ።

27 እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጡ ግን
የሙታን አጥንት ርኵሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን
ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ። 28 እንዲሁ እናንተ ደግሞ በውጭ ለሰው እንደ ጻድቃን
ትታያላችሁ፥ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ዓመፀኝነት ሞልቶባችኋል።

29 እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ
የጻድቃንንም መቃብር ስለምታስጌጡና፡- 30 በአባቶቻችን ዘመን ኖረን በሆነስ
በነቢያት ደም ባልተባበርናቸውም ነበር ስለምትሉ፥ ወዮላችሁ። 31 እንግዲያስ
የነቢያት ገዳዮች ልጆች እንደሆናችሁ በራሳችሁ ላይ ትመሰክራላችሁ። 32 እናንተ
ደግሞ የአባቶቻችሁን መስፈሪያ ሙሉ።

33 እናንተ እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች፥ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ?
34 ስለዚህ፥ እነሆ፥ ነቢያትንና ጥበበኞችን ጻፎችንም ወደ እናንተ እልካለሁ፤
ከእነርሱም ትገድላላችሁ ትሰቅሉማላችሁ፥ ከእነርሱም በምኩራባችሁ ትገርፉላችሁ
ከከተማም ወደ ከተማ ታሳድዳላችሁ፤ 35 ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ
መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ
ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችሁ ዘንድ። 36
እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ በዚህ ትውልድ ላይ ይደርሳል።

---

[13] [ማቴ. 23፡39ሀ] ከመጀመሪያው ይልቅ በኢየሱስ ዳግም ምጽዓት ጊዜ እጅግ የበዙ እስራኤላውያን ኢየሱስን እንደ መሢሕ በደስታ ይቀበሉታል። ስለ ኢየሩሳሌም የተደረገ ይህ ማስጠንቀቂያ፥ ኢየሱስ ዳግም ምጽዓቱ ከኢየሩሳሌም ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ለደቀ መዛሙርቱ ሊነግራቸው ለፈለገው ነገር ዝግጅት ነበር (ክፍል 139ሀ)።

## ♦ ክፍል 137ለ. ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ማዘኑ

[ክፍል 113ለን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም፥ በመቅደሱ ውስጥ -

ማቴዎስ 23፡37-39

37 ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም። 38 እነሆ፥ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል። 39 እላችኋለሁና፥ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ[13] ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም። [መዝሙር 118፡26]

## ♦ ክፍል 138. አንዲት መበለት የነበራትን ሁሉ መስጠቷ

- ኢየሩሳሌም፥ በመቅደሱ ውስጥ -

ማርቆስ 12፡41-44

41 ኢየሱስም በመዝገብ አንጻር ተቀምጦ ሕዝቡ በመዝገብ ውስጥ ገንዘብ እንዴት እንዲጥሉ ያይ ነበር፤ ብዙ ባለ ጠጎችም ብዙ ይጥሉ ነበር፤ 42 አንዲትም ድሀ መበለት መጥታ አንድ ሳንቲም የሚያህሉ ሁለት ናስ ጣለች።

43 ደቀ መዛሙርቱንም ጠርቶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ በመዝገብ ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድሀ መበለት አብልጣ ጣለች፤ 44 ሁሉ ከትርፋቸው ጥለዋልና፥ ይህች[14] ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አላቸው።

ሉቃስ 21፡1-4

1 ዓይኑንም አንሥቶ መባቸውን በመዝገብ የሚጥሉ ባለ ጠጎችን አየ። 2 አንዲትም ድሀ መበለት ሁለት ሳንቲም በዚያ ስትጥል አየና፦

3 እውነት እላችኋለሁ፥ ይህች ድሀ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች፤ 4 እነዚህ ሁሉ ከትርፋቸው ወደ እግዚአብሔር መዝገብ ጥለዋልና፤ ይህች[14] ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አለ።

---

[14] [ማር. 12፡44፤ ሉቃስ 21፡4] ይህ የእውነተኛ ሃይማኖተኛነት ምሳሌ ነው። ከተበላሹ የሃይማኖት መሪዎች (ማቴ. 23፡23-24፥ ክፍል 137ሀ) አንጻር ስትታይ፥ ይህች ሴት በመሥዋዕትነቷ እንደተረጋገጠው ከልቧ ሰጠች።

# 11

# በክርስቶስ የሞት ዝግጅት ላይ የተነገሩ ትንቢቶች

## > የደብረ ዘይት ስብከት፥ ኢየሱስ ስለ ቤተ መቅደስና ስለ ዳግም ምጽአቱ በትንቢት ተናገረ <

### ♦ ክፍል 139ሀ. የስብከቱ አጀማመር

- ከመቅደሱ ወደ ደብረ ዘይት -

| ማቴዎስ 24፡1-3 | ማርቆስ 13፡1-4 | ሉቃስ 21፡5-7 |
|---|---|---|
| 1 ኢየሱስም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ። | 1 እርሱም ከመቅደስ ሲወጣ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፦ መምህር ሆይ፥ እንዴት ያሉ ድንጋይዎችና እንዴት ያሉ ሕንጻዎች እንደ ሆኑ እይ አለው። | 5 አንዳንዶቹም ስለ መቅደስ በመልካም ድንጋይና በተሰጠው ሽልማት እንዳጌጠ ሲነጋገሩ፦ ይህማ የምታዩት ሁሉ፥ 6 ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል አለ። |
| 2 እርሱ ግን መልሶ፦ ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ፥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው። | 2 ኢየሱስም መልሶ፦ እነዚህን ታላላቅ ሕንጻዎች ታያለህን? ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አለው። | |
| 3 እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፦ ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል?[15] የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት። | 3 በመቅደስም ትይዩ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ጴጥሮስና ያዕቆብ ዮሐንስም እንድርያስም፦ 4 ንገረን፥[15] ይህ መቼ ይሆናል? ይህስ ሁሉ ይፈጸም ዘንድ እንዳለው ምልክቱ ምንድር ነው? ብለው ለብቻቸው ጠየቁት። | 7 እነርሱም፦ መምህር ሆይ፥ እንግዲህ ይህ መቼ[15] ይሆናል? ይህስ ይሆን ዘንድ እንዳለው ምልክቱ ምንድር ነው? ብለው ጠየቁት። |

[15] [ማቴ. 24፡3፤ ማር. 13፡4፤ ሉቃስ 21፡7] ደቀ መዛሙርቱ ሦስት ጥያቄዎች የጠየቁ ይመስላል። የመጀመሪያው በ70 ዓ.ም. በሮማውያን ወታደሮች የተፈጸመውን የቤተ መቅደሱን መፍረስ የሚመለከት ነው (ማቴ. 24፡1-2፤ ማር. 13፡1-2፤ ሉቃስ 21፡5-6)። ሌላው የኢየሱስን ዳግም ምጽዓትና ከዚያ ጋር የተያያዘውን የዘመን ፍጻሜ ይመለከታል። እነዚህ ሁለት ክንውኖች ምንም እንኳ በአያሌ ዓመታት የተለያዩ ቢሆኑ፥ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ካለው እቅድ ጋር በቅርብ የተዛመዱ ናቸው። ከምልክቱ ጋር የተዛመደውና "ይህ መቼ ይሆናል?" የሚለው ሌላ ጥያቄ ምናልባት ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሚሆነው የቤተ መቅደሱ መፍረስ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። የቤተ መቅደሱ መፍረስ፥ መሢሑ ዘመኑን የመፈጸሙና መንግሥቱን በምድር ለመመሥረት የመምጣቱ ዋዜማ ነው በማለት ደቀ መዛሙርቱ አስበው ነበር። ኢየሱስም ቢሆን በሁለቱ ክንውኖች መካከል ዝምድና መኖሩን አላስተባበለም፤ ሁለቱን ስለሚለየው ረጅም ዘመንም በኋላ ባደረገው ንግግር የገለጠው ነገር የለም። ቃላቱን ከተናገረ ጥቂት ዓመታት በኋላ አንዳንድ ትንቢቶቹ ተፈጽመዋል (ለምሳሌ፥ ሉቃስ 21፡20፥ ክፍል 139ሐ)፤ ሌሎቹ ግን ገና የሚፈጸሙ ናቸው (ለምሳሌ፥ ማቴ. 24፡30፥ ክፍል 139መ)።

## ♦ ክፍል 139ለ. የምጥ መጀመሪያ

[ክፍል 70ለና 108ሀን ይመልከቱ]

- ደብረ ዘይት -

<u>ማቴዎስ</u> 24፡4-14

4 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡- ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። 5 ብዙዎች፡- እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። 6 ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው። 7 ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል፤ 8 እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር[16] መጀመሪያ ናቸው።

9 በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፥ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ። 10 በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤

<u>ማርቆስ</u> 13፡5-13

5 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ ይላቸው ጀመር፡- ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። 6 ብዙዎች፡- እኔ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፥ ብዙዎችንም ያስታሉ። 7 ጦርንም የጦርንም ወሬ በሰማችሁ ጊዜ አትደንግጡ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና፥ ነገር ግን መጨረሻው ገና ነው። 8 ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፤ በልዩ ልዩ ስፍራ የምድር መናወጥ ይሆናል፤ ራብ ይሆናል፤ እነዚህ የምጥ ጣር[16] መጀመሪያ ናቸው።

9 እናንተ ግን ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል በምኵራብም ትገረፋላችሁ ምስክርም ይሆንባቸው ዘንድ ስለ እኔ በገዥዎችና በነገሥታት ፊት ትቆማላችሁ።

<u>ሉቃስ</u> 21፡8-19

8 እንዲህም አለ፡- እንዳትስቱ ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች፡- እኔ ነኝ፥ ዘመኑም ቀርቦአል እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ እነርሱን ተከትላችሁ አትሂዱ። 9 ጦርንና ሁከትንም በሰማችሁ ጊዜ አትደንግጡ፤ ይህ አስቀድሞ ይሆን ዘንድ ግድ ነውና፥ ነገር ግን መጨረሻው ወዲያው አይሆንም።

10 በዚያን ጊዜ እንዲህ አላቸው፡- ሕዝብ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል፤ 11 ታላቅም የምድር መናወጥና በልዩ ልዩ ስፍራ ቸነፈር ራብም ይሆናል፤ የሚያስፈራም ነገር ከሰማይም ታላቅ ምልክት ይሆናል።

12 ከዚህም ሁሉ በፊት እጃቸውን በላያችሁ ይጭናሉ ያሳድዱአችሁማል፤ ስለ ስሜም ወደ ምኵራብና ወደ ወኅኒ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ ወደ ነገሥታትና ወደ ገዥዎችም ይወስዱአችኋል፤ 13

---

16 [ማቴ. 24፡8፤ ማር. 13፡8] “ምጥ” በመጽሐፍ ቅዱስ “የጌታ ቀን” የመጀመሪያ ክፍል የሆነውን የእስራኤል የፍዳ ዘመን ለመግለጥ ያገለገለ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው (ኢሳ. 13፡8፤ 26፡17-19፤ 66፡7-9፤ ኤር. 30፡7-8፤ ሚክ. 4፡9-10፤ 1ኛ ተሰ. 5፡3)። እየጨመረ የሚሄደው ይህ የሰው ልጆች የመከራ ዘመን፥ መሢሑ ዳግም ወደ ምድር በሚመጣበት ጊዜ በጣም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል።

| (ማቴዎስ 24፡4-14 የቀጠለ) | (ማርቆስ 13፡5-13 የቀጠለ) | (ሉቃስ 21፡8-19 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| | 10 አስቀድሞም ወንጌል ለአሕዛብ ሁሉ ይሰበክ ዘንድ ይገባል። 11 ሲጐትቱአችሁና አሳልፈው ሲሰጡአችሁም ምን እንድትናገሩ አስቀድማችሁ አትጨነቁ፥ ዳሩ ግን በዚያች ሰዓት የሚሰጣችሁን ተናገሩ፤ የሚነግረው መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ እናንተ አይደላችሁምና። 12 ወንድምም ወንድሙን አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፥ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ። ይገድሉአቸውማል፤ 13 በሁሉም ዘንድ ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ | ይህም ለምስክርነት ይሆንላችኋል። 14 ስለዚህ እንዴት እንድትመልሱ አስቀድማችሁ እንዳታስቡ በልባችሁ አኑሩት፤ 15 ወደረኞቻችሁ ሁሉ ሊቃወሙና ሊከራከሩ የማይችሉትን አፍና ጥበብ እሰጣችኋለሁና። 16 ወላጆችም ስንኳ ወንድሞችም ዘመዶችም ወዳጆችም አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ ከእናንተም አንዳንዱን ይገድላሉ፤ 17 በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ። 18 ከራሳችሁም አንዲት ጠጉር ስንኳ አትጠፋም፤ 19 በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ። |
| 11 ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ 12 ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች። 13 እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። 14 ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል። | እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። | |

## ♦ ክፍል 139ሐ. የጥፋት ርኩሰትና ተከታዩ ሥቃይ

[ክፍል 120ለን ይመልከቱ]

- ደብረ ዘይት -

<u>ማቴዎስ 24፡15-28</u>

15 እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት[17] በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥ [ዳንኤል 9፡27፥ 11፡31፥ 12፡11]

16 በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ፥ 17 በሰገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ፥ 18 በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ።

19 በዚያችም ወራት ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው። 20 ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ፤ 21 በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና። 22 እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ።

<u>ማርቆስ 13፡14-23</u>

14 ነገር ግን በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋት ርኵሰት በማይገባው ስፍራ ቆሞ ብታዩ [ዳንኤል 9፡27፥ 11፡31፥ 12፡11]፥[17] አንባቢው ያስተውል፥

በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች ይሽሹ፥ 15 በሰገነትም ያለ ወደ ቤት አይውረድ ከቤቱም አንዳች ይወስድ ዘንድ አይግባ፥ 16 በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ።

17 በዚያን ወራትም ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው። 18 ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት እንዳይሆን ጸልዩ፤ 19 በዚያን ወራት እግዚአብሔር ከፈጠረው ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያልሆነ ደግሞም የማይሆን የመከራ ዓይነት ይሆናልና። 20 ጌታስ ወራቶቹን ባያሳጥር፥ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም፤ ነገር ግን ስለ መረጣቸው ምርጦች ወራቶቹን አሳጠረ።

<u>ሉቃስ 21፡20-24</u>

20 ኢየሩሳሌም ግን በጭፍራ ተከባ ስታዩ በዚያን ጊዜ ጥፋትዋ እንደ ቀረበ እወቁ። 21 የዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራራዎች ይሽሹ፥ በመካከልዋም ያሉ ከእርስዋ ፈቀቅ ይበሉ፥ በገጠር ያሉም ወደ እርስዋ አይግቡ፤ 22 የተጻፈው ሁሉ እንዲፈጸም ይህ የበቀል ጊዜ ነውና። 23 በዚያን ወራት ለእርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው፤

[17] [ማቴ. 24፡15፤ ማር. 13፡14] ይህ ዳንኤል ስለ ሰባዎቹ ሳምንታት የተናገረው ትንቢት (ዳን. 9፡27) ያኔም ሆነ። ከኢየሱስ ጊዜ ጀምሮም አልተፈጸመም ነበር። ወደፊት የሚሆነው የሰባኛው ሳምንት ትንቢት አማካይ ጊዜ እንደመሆኑ፥ ይህ "የጥፋት ርኩሰት" የኢየሱስን መመለስ በግልጥ ከሚጠቁሙ ምልክቶች አንዱን ያመለክታል (ማቴ. 24፡3፥ ክፍል 139ሀ)።

**(ማቴዎስ 24፡15-28 የቀጠለ)**

23 በዚያን ጊዜ ማንም፡-
እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ
ወይም፡- ከዚያ አለ
ቢላችሁ አትመኑ፤ 24
ሐሰተኞች ክርስቶሶችና
ሐሰተኞች ነቢያት
ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ
የተመረጡትን እንኳ
እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ
ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።
25 እነሆ፥ አስቀድሜ
ነገርኋችሁ።

26 እንግዲህ፡- እነሆ፥
በበረሀ ነው ቢሉአችሁ፥
አትውጡ፤ እነሆ፥
በእልፍኝ ነው ቢሉአችሁ፥
አትመኑ፤ 27 መብረቅ
ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ
ምዕራብ እንደሚታይ፥
የሰው ልጅ መምጣት
እንዲሁ ይሆናልና፤ 28
በድን ወዳለበት በዚያ
አሞራዎች ይሰበሰባሉ።

**(ማርቆስ 13፡14-23 የቀጠለ)**

21 በዚያን ጊዜም
ማንም፡- እነሆ፥ ክርስቶስ
ከዚህ አለ፥ ወይም፡- እነሆ
፥ ከዚያ አለ ቢላችሁ
አትመኑ፤ 22 ሐሰተኞች
ክርስቶሶችና ሐሰተኞች
ነቢያት ይነሣሉና፥
ቢቻላቸውስ የተመረጡትን
እንኳ ያስቱ ዘንድ
ምልክትና ድንቅ
ያደርጋሉ። 23 እናንተ ግን
ተጠንቀቁ፤ እነሆ፥
አስቀድሜ ሁሉን
ነገርኋችሁ።

**(ሉቃስ 21፡20-24 የቀጠለ)**

ታላቅ ችግር በምድር
ላይ፥ በዚህም ሕዝብ ላይ
ቍጣ ይሆናልና፤

24 በሰይፍ ስለትም
ይወድቃሉ፤ ወደ አሕዛብ
ሁሉም ይማረካሉ፤
የአሕዛብም ዘመን
እስኪፈጸም ድረስ
ኢየሩሳሌም በአሕዛብ
የተረገጠች ትሆናለች።

## ♦ ክፍል 139መ. የሰው ልጅ መምጣት

[ክፍል 120ለን ይመልከቱ]

*- ደብረ ዘይት -*

<u>*ማቴዎስ* 24፡29-31</u>

29 ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው

“ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ”

[ኢሳይያስ 13፡10፥ 34፡4፤ ሕዝቅኤል 32፡7፤ ኢዮኤል 2፡10፥ 31፥ 3፡15]

30 የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ[18] ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም[18] በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ [ዳንኤል 7፡13] 31 መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ። [ኢሳይያስ 27፡13]

<u>*ማርቆስ* 13፡24-27</u>

24 በዚያን ወራት ግን ከዚያ መከራ በኋላ

“ፀሐይ ይጨልማል ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ 25 ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ።”

[ኢሳያይስ 13፡10፥ 34፡4፤ ሕዝቅኤል 32፡7፤ ኢዮኤል 2፡10፥ 31፥ 3፡15]

26 በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ[18] በብዙ ኃይልና ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል። [ዳንኤል 7፡13] 27 በዚያን ጊዜም መላእክትን ይልካል ከአራቱ ነፋሳትም ከምድር ዳርቻ እስከ ሰማይ ዳርቻ የተመረጡትን ይሰበስባቸዋል።

<u>*ሉቃስ* 21፡25-27</u>

25 በፀሐይና በጨረቃም በከዋክብትም ምልክት ይሆናል፤ በምድር ላይም አሕዛብ ከባሕሩና ከሞገዱም ድምፅ የተነሣ እያመነቱ ይጨነቃሉ፤ 26 ሰዎችም ከፍርሃትና በዓለም የሚመጣበትን ከመጠበቅ የተነሣ ይደክማሉ፤ የሰማያት ኃይላት ይናወጣሉና።

27 በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ[18] በኃይልና በብዙ ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል። [ዳንኤል 7፡13]

---

[18] [ማቴ. 24፡40፤ ማር. 13፡26፤ ሉቃስ 21፡27] “የሰው ልጅ” ወደምድር መመለስ የእስራኤልን ተስፋና ጉጉት ከዳር ያደርሰዋል። ዳግም ምጽዓቱ ከፍዳው በኋላ ወዲያውኑ በመከናወን (ማቴ. 24፡29)፥ የተበተኑ እስራኤላውያን ወደ ምድራቸው የመመለሻ ጊዜ ይሆናል (ማቴ. 24፡31፤ ማር. 13፡27)። ይህ የምድሪቱ ነጻ መሆን፥ በብሉይ ኪዳን ሁሉ የተደጋገመ የአይሁዳውያን የመጨረሻው ዘመን ተስፋ ነው (ዘዳ. 30፡3-4፤ ኢሳ. 11፡12፤ 27፡13፤ 56፡8፤ ኤር. 23፡3፤ 31፡8፤ ሕዝ. 11፡17፤ 20፡34፥ 41፤ 28፡25፤ 34፡13፤ ሮሜ 11፡26)።

[19] [ማቴ. 24፡33፤ ማር. 13፡29፤ ሉቃስ 21፡31] “ይህ ሁሉ” የተባሉት ነገሮች ኢየሱስ ቀደም ብሎ በዚህ ንግግሩ የገለጣቸውና “የምጥ ጣር” (ማቴ. 24፡8፤ ማር. 13፡9፤ ክፍል 139ለ) እና “የጥፋት ርኩሰት” (ማቴ. 24፡15፤ ማር. 13፡14፥ ክፍል 139ሐ) የመሳሰሉት ናቸው። እስራኤላውያን እነዚህ ነገሮች መከናወን መጀመራቸውን ሲመለከቱ “ቤዛችሁ ቀርቧልና” (ሉቃስ 21፡28)፥ እና “የእግዚአብሔር መንግሥት እንደቀረበች” (ሉቃስ 21፡31) የሚሉትን መልእክቶች ይገነዘባሉ። ይህን ብሔራዊ ነጻነት የሚያገኙት በሰው ልጅ መምጣት አማካይነት ነው (ክፍል 139መ)።

## ♦ ክፍል 139ሠ. ቅርብ፥ ነገር ግን መቼ መሆኑ ያልታወቀው ጊዜ ምልክቶች [ክፍል 120ለን ይመልከቱ]

- ደብረ ዘይት -

<u>ማቴዎስ</u> 24፡32-41

32 ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤ 33 እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ[19] ስታዩ በደጅ እንደ ቀረበ እወቁ። 34 እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። 35 ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።

36 ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም። 37 የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና። 38 በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥ [ዘፍጥረት 7፡7] 39 የጥፋት ውኃም መጥቶ

<u>ማርቆስ</u> 13፡28-32

28 ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤ 29 እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህን ሁሉ መሆኑን ስታዩ[19] ቀርቦ በደጅ እንደ ሆነ እወቁ። 30 እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። 31 ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።

32 ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም።

<u>ሉቃስ</u> 21፡28-33

28 ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቦአልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ።

29 ምሳሌንም ነገራቸው እንዲህ ሲል፦ በለስንና ዛፎችን ሁሉ እዩ፤ 30 ሲያቈጠቍጡ ተመልክታችሁ በጋ አሁን እንደ ቀረበ ራሳችሁ ታውቃላችሁ። 31 እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህ ሁሉ[19] መሆኑን ስታዩ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ቀረበች እወቁ።

32 እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። 33 ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።

---

20 ከአምስቱ ምሳሌዎች አንዱ ማርቆስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ሲጠቀስ (13፡34-36)፥ አራቱ ደግሞ ማቴዎስ ውስጥ ብቻ ነው የተነገሩት (24፡43፥ 45-51፤ 25፡1-12፥ 14-30)። በመጀመሪያው፥ በሁለተኛውና በአራተኛው ምሳሌዎች የተጠቀሰው ዋና ትምህርት ነቅቶ ስለመጠበቅ ነው።የሦስተኛውና የአምስተኛው ምሳሌዎች ትምህርት ደግሞ የአገልግሎት ታማኝነት የጌታን መምጣት በንቃት በመጠበቅ ይታጀባል የሚል ነው።

(ማቴዎስ 24፡32-41 የቀጠለ)

ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።
40 በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤ 41
ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች።

## ♦ ክፍል 139ሪ. ተግቶ መጠበቅንና ታማኝነትን የሚያስተምሩ አምስት ምሳሌዎች[20] [ክፍል 108ሐና 127ለን ይመልከቱ]

- ደብረ ዘይት -

ማቴዎስ 24፡42-25፡30

42 ጌታችሁ በምን ሰዓት
እንዲመጣ አታውቁምና
እንግዲህ ንቁ።

43 ያን ግን እወቁ፤
ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው

ማርቆስ 13፡33-37

33 ጊዜው መቼ እንዲሆን
አታውቁምና ተጠንቀቁ፤
ትጉ፤ ጸልዩም። 34 ቤቱን
ትቶ ወደ ሌላ አገር እንደ
ሄደ ሰው ነው፥ ለባሮቹም
ሥልጣን ለእያንዳንዱም
ሥራውን ሰጥቶ በረኛውን
እንዲተጋ አዘዘ።

35 እንግዲህ በማታ ቢሆን
ወይም በእኩለ ሌሊት ወይም
ዶሮ ሲጮኽ ወይም በማለዳ
ቢሆን ባለቤቱ መቼ
እንዲመጣ አታውቁምና 36
ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ
እንዳያገኛችሁ ስለዚህ ትጉ።
37 ለእናንተም የምነግራችሁ
ለሁሉ እላለሁ፤ ትጉ።

ሉቃስ 21፡34-36

34 ነገር ግን ልባችሁ
በመጠጥ ብዛትና በስካር
ስለ ትዳርም በማሰብ
እንዳይከብድ፥ ያ ቀንም
በድንገት እንዳይመጣባችሁ
ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ 35
በምድር ሁሉ ላይ
በሚቀመጡ ሁሉ እንደ
ወጥመድ
ይደርስባቸዋልና። 36
እንግዲህ ሊመጣ ካለው
ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፥
በሰው ልጅም ፊት
ለመቆም እንድትችሉ
ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ።

ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ ቤቱም ሊቈፈር ባልተወም ነበር። 44
ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት
ይመጣልና።

45 እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎች ላይ
የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው? 46 ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ
የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው፤ 47 እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ
ይሾመዋል። 48 ያ ክፉ ባሪያ ግን፦ ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥
49 ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥ 50 የዚያ
ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ 51 ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፥
እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

(ማቴዎስ 24:42-25:30 የቀጠለ)

1 በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ
የወጡ አሥር ቆነጃጅትን ትመስላለች። 2 ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች አምስቱም
ልባሞች ነበሩ። 3 ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙምና፤ 4
ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ። 5 ሙሽራውም በዘገየ
ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ።

6 እኩል ሌሊትም ሲሆን፦ እነሆ፥ ሙሽራው ይመጣል፥ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ የሚል ውካታ ሆነ።

7 በዚያን ጊዜ እነዚያ ቆነጃጅት ሁሉ ተነሡና መብራታቸውን አዘጋጁ። 8 ሰነፎቹም
ልባሞቹን፦ መብራታችን ሊጠፋብን ነው፤ ከዘይታችሁ ስጡን አሉአቸው።

9 ልባሞቹ ግን መልሰው፦ ምናልባት ለእኛና ለእናንተ ባይበቃስ፤ ይልቅስ ወደሚሸጡት ሄዳችሁ ለራሳችሁ ግዙ አሉአቸው።

10 ሊገዙም በሄዱ ጊዜ ሙሽራው መጣ፥ ተዘጋጅተው የነበሩትም ከእርሱ ጋር ወደ ሰርግ ገቡ፥ ደጁም ተዘጋ።

11 በኋላም ደግሞ የቀሩቱ ቈነጃጅት መጡና፦ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ፥ ክፈትልን አሉ።

12 እርሱ ግን መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ አላውቃችሁም አለ።

13 ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።

14 ወደ ሌላ አገር የሚሄድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ እንደ ሰጣቸው
እንዲሁ ይሆናልና፤ 15 ለእያንዳንዱ እንደ ዓቅሙ፥ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ
ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ አገር ወዲያው ሄደ። 16 አምስት መክሊትም
የተቀበለው ሄዶ ነገደበት ሌላም አምስት አተረፈ፤ 17 እንዲሁም ሁለት የተቀበለው
ሌላ ሁለት አተረፈ። 18 አንድ የተቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቈፈረና የጌታውን ገንዘብ
ቀበረ።

19 ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው። 20 አምስት
መክሊት የተቀበለውም ቀረበና ሌላ አምስት መክሊት አስረክቦ፦ ጌታ ሆይ፥ አምስት
መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ፥ ሌላ አምስት መክሊት አተረፍሁበት አለ።

21 ጌታውም፦ መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው።

22 ሁለት መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ፥ ሌላ ሁለት መክሊት አተረፍሁበት አለ።

23 ጌታውም፦ መልካም፥ አንተ በጎ፥ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፥ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው።

24 አንድ መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህባት
የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ 25
ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፤ እነሆ፥ መክሊትህ አለህ አለ።

---

[21] [ማቴ. 25፡31] የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ የሚቀመጥበት ዙፋን (ማቴ. 24፡30፤ ማር. 13፡26፤ ሉቃስ 21፡27፥ ክፍል 139መ)፥ በምድር ላይ ነው የሚገኘው። ይህ ዙፋን የአውራሽ አባቱ የዳዊት ነው (ሉቃስ 1፡32-33፥ ክፍል5)። እዚያ ላይ ሆኖ ከታላቁ የፍዳ ዘመን በተረፉት ላይ ይፈርዳል ("ታላቅ መከራ"፥ ማቴ. 24፡ 21-22፤ ማር. 13፡19-20፥ ክፍል 139ሐ፤ ማቴ. 24፡29፤ ማር. 13፡24፥ ክፍል 139መ)።

(ማቴዎስ 24:42-25:30 የቀጠለ)

26 ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው፦ አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ፥ ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ታውቃለህን? 27 ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፥ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር።

28 ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት አሥር መክሊትም ላለው ስጡት፤ 29 ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። 30 የማይጠቅመውንም ባሪያ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

## ♦ ክፍል 139ሰ. በሰው ልጅ መምጫ ጊዜ የሚኖር ፍርድ

- ደብረ ዘይት -

ማቴዎስ 25፥31-46

31 የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን[21] ይቀመጣል፤ 32 አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥ 33 በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።

34 ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። 35 ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ 36 ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና።

37 ጻድቃንም መልሰው ይሉታል፦ ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? 38 እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ? 39 ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?

40 ንጉሡም መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።

41 በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፦ እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ። 42 ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥ 43 ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና።

44 እነርሱ ደግሞ ይመልሱና፦ ጌታ ሆይ፥ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል።

45 ያን ጊዜ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል።

46 እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።

# > አሳልፎ የመስጠት ዝግጅቶች <

## ♦ ክፍል 140. *የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስን ለማሠርና ለመግደል ያቀዱት ሤራ*

- ደብረ ዘይት እና የሊቀ ካህናቱ ግቢ. -

| ማቴዎስ 26፥1-5 | ማርቆስ 14፥1-2 | ሉቃስ 22፥1-2 |
|---|---|---|
| 1 ኢየሱስም እነዚህን ቃሎች ሁሉ በፈጸመ ጊዜ፥ 2 ለደቀ መዛሙርቱ፦ ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁ፥ የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል አለ። | 1 ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካና የቂጣ በዓል ነበረ። | 1 ፋሲካም የሚባለው የቂጣ በዓል ቀረበ። |
| 3 በዚያን ጊዜ የካህናት አለቆች[22] የሕዝብም ሽማግሎች ቀያፋ በሚባለው በሊቀ ካህናቱ ግቢ ተሰበሰቡ፥ 4 ኢየሱስንም በተንኰል ሊያስይዙት ሊገድሉትም ተማከሩ፤ 5 ነገር ግን፦ በሕዝቡ ዘንድ ሁከት እንዳይነሣ በበዓል አይሁን አሉ። | የካህናት አለቆችም ጻፎችም[22] እንዴት አድርገው በተንኰል እንደሚይዙትና እንደሚገድሉት ይፈልጉ ነበር። 2 የሕዝብ ሁከት እንዳይሆን በበዓል አይሁን ይሉ ነበርና። | 2 የካህናት አለቆችና ጻፎችም[22] እንዴት እንዲያጠፉት ይፈልጉ ነበር፤ ሕዝቡን ይፈሩ ነበርና። |

22 [ማቴ. 26፡3፤ ማርቆስ 14፡1፤ ሉቃስ 22፡2] የካህናቱ አለቆች ከሦስት ቡድኖቻቸው መካከል ሁለቱን በመወከል ቀደም ሲል የተሰጡ ውሳኔዎችን ተግባራዊ የሚያደርጉበትን እቅድ ለማዘጋጀት በቀያፋ መሪነት ተሰበሰቡ (ዮሐ. 11፡53፥ ክፍል 119)። የካህናቱ አለቆች ኢየሱስ በሕዝቡ ዘንድ፥ በተለይም ከገሊላና ከፓርያ በመጡት ዘንድ ከነበረው ታላቅ ተወዳጅነት የተነሣ (ሉቃስ 21፡38፤ 22፡2)፥ በዓሉ እስኪያበቃና፥ እነዚህ ተጓገኞች ወደየመጡበት እስኪመለሱ ለመጠበቅ ወሰኑ (ማቴ. 26፡5፤ ማር. 14፡2)። ይሁን እንጂ ያልጠበቁትና የሚፈልጉት መልካም ነገር ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከአንዱ ስለደረሳቸው (ክፍል 142)፥ የድርጊታቸውን ጊዜ አፈጠኑት። ይህ ሁኔታ ኢየሱስን በስውር እንዲይዙት አስቻላቸው (ሉቃስ 22፡6፥ ክፍል 142፥ 153)። የእግዚአብሔር በግ መሰዋት በፋሲካ ዕለት እንጂ፥ ከዚያ በኋላ እንዳይሆን (ማቴ. 26፡2) አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተወሰነው ጊዜ በዚህ ሁኔታ ተጠበቀ።

## ♦ ክፍል 141. ማርያም ኢየሱስን ለቀብሩ ሽቶ መቀባቷ

[ክፍል 59ን ይመልከቱ]

- ቢታንያ፥ በለምጻሙ ስምዖን ቤት -

ማቴዎስ 26፥6-13

6 ኢየሱስም በቢታንያ
በለምጻሙ በስምዖን ቤት
ሳለ፥ 7 አንዲት ሴት
ዋጋው እጅግ የበዛ ሽቱ
የሞላው የአልባስጥሮስ
ብልቃጥ ይዛ ወደ እርሱ
ቀረበች በማዕድም
ተቀምጦ ሳለ በራሱ ላይ
አፈሰሰችው።

8 ደቀ መዛሙርቱም
ይህን አይተው ተቈጡና፦
ይህ ጥፋት ለምንድር ነው?
9 ይህ በብዙ ዋጋ ተሽጦ
ለድሆች ሊሰጥ ይቻል
ነበርና አሉ።

10 ኢየሱስም ይህን
አውቆ እንዲህ አላቸው፦
መልካም ሥራ
ሠርታልኛለችና ሴቲቱን
ስለ ምን
ታደክሙአታላችሁ? 11
ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ
ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን
ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር
አልኖርም፤ 12 እርስዋ
ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ
አፍስሳ ለመቃብሬ
አደረገች። 13 እውነት
እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል
በዓለም ሁሉ በማናቸውም
ስፍራ በሚሰበክበት እርስዋ
ያደረገችው ደግሞ
ለእርስዋ መታሰቢያ
እንዲሆን ይነገራል።

ማርቆስ 14፥3-9

3 እርሱም በቢታንያ
በለምጻሙ በስምዖን ቤት
በነበረ ጊዜ፥ በማዕድ
ተቀምጦ ሳለ፥ አንዲት ሴት
ዋጋው እጅግ የከበረ ጥሩ
ናርዶስ ሽቱ የመላበት
የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ ይዛ
መጣች፤ ቢልቃጡንም
ሰብራ በራሱ ላይ
አፈሰሰችው።

4 አንዳንዶችም፦ ይህ
የሽቱ ጥፋት ለምንድር ነው?
5 ይህ ሽቱ ከሦስት መቶ
ዲናር በሚበልጥ ዋጋ ተሽጦ
ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና
ብለው በራሳቸው ይቈጡ
ነበር፤ እርስዋንም ነቀፉአት።

6 ኢየሱስ ግን እንዲህ
አለ፦ ተዉአት፤ ስለ ምን
ታደክሙአታላችሁ?
መልካም ሥራ
ሠርታልኛለች። 7 ድሆች
ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር
ይኖራሉና፥ በማናቸውም
በወደዳችሁት ጊዜ መልካም
ልታደርጉላቸው
ትችላላችሁ፥ እኔ ግን
ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር
አልኖርም። 8 የተቻላትን
አደረገች፤ አስቀድማ
ለመቃብሬ ሥጋዬን
ቀባችው። 9 እውነት
እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል
በዓለሙ ሁሉ በሚሰበክበት
በማናቸውም ስፍራ፥ እርስዋ
ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ
መታሰቢያ ሊሆን ይነገራል።

ዮሐንስ 12፥2-8

2 በዚያም እራት
አደረጉለት፤ ማርታም
ታገለግል ነበር፤ አልዓዛር
ግን ከእርሱ ጋር
ከተቀመጡት አንዱ ነበረ።
3 ማርያምም ዋጋው
እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ
ሽቱ ንጥር ወስዳ
የኢየሱስን እግር ቀባች፤
በጠጕርዋም እግሩን
አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ
ሽቱ ሞላ።

4 ነገር ግን ከደቀ
መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ
ሊሰጠው ያለው የስምዖን
ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ፦
5 ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ
ዲናር ተሽጦ ለድሆች
ያልተሰጠ ስለ ምን ነው?
አለ። 6 ይህንም የተናገረ
ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ
ለድሆች ተገድዶላቸው
አይደለም፤ ከረጢትም
ይዞ በውስጡ ከሚገባው
ይወስድ ስለ ነበረ ነው።

7 ኢየሱስም፦
ለምቀበርበት ቀን
እንድትጠብቀው
ተውአት፤ 8 ድሆችስ
ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር
ይኖራሉና፥ እኔ ግን
ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር
አልኖርም አለ።

## ♦ ክፍል 142. ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት መስማማቱ

- ኢየሩሳሌም -

| <u>ማቴዎስ 26፡14-16</u> | <u>ማርቆስ 14፡10-11</u> | <u>ሉቃስ 22፡3-6</u> |
|---|---|---|
| 14 በዚያን ጊዜ የአስቆሮቱ ይሁዳ የሚባለው ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ወደ ካህናት አለቆች ሄዶ፡- 15 ምን ልትሰጡኝ ትወዳላችሁ እኔም አሳልፌ እሰጣችኋለሁ? እነርሱም ሠላሳ ብር መዘኑለት። 16 ከዚያችም ሰዓት ጀምሮ አሳልፎ ሊሰጠው ምቹ ጊዜ ይሻ ነበር። | 10 ከአሥራ ሁለቱም አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ ሊሰጠው ወደ ካህናት አለቆች ሄደ። 11 ሲሰሙም ደስ አላቸው ብርም ይሰጡት ዘንድ ተስፋ ሰጡት። በሚመች ጊዜም እንዴት አድርጎ አሳልፎ እንዲሰጠው ይፈልግ ነበር። | 3 ሰይጣንም[23] ከአሥራ ሁለቱ ቍጥር አንዱ በነበረው የአስቆሮቱ በሚባለው በይሁዳ ገባ፤ 4 ሄዶም እንዴት አሳልፎ እንዲሰጣቸው ከካህናት አለቆችና ከመቅደስ አዛዦች ጋር ተነጋገረ። 5 እነርሱም ደስ አላቸው፥ ገንዘብም ሊሰጡት ተዋዋሉ። 6 እሺም አለ፥ ሕዝብም በሌለበት አሳልፎ እንዲሰጣቸው ምቹ ጊዜ ይፈልግ ነበር። |

## > የመጨረሻው ማዕድ <

## ♦ ክፍል 143. የፋሲካ ማዕድ መሰናዶ

- ኢየሩሳሌም -

| <u>ማቴዎስ 26፡17-19</u> | <u>ማርቆስ 14፡12-16</u> | <u>ሉቃስ 22፡7-13</u> |
|---|---|---|
| 17 በቂጣው በዓል በመጀመሪያ ቀን ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፡- ፋሲካን[24] ትበላ ዘንድ ወዴት ልናሰናዳልህ ትወዳለህ አሉት። | 12 ፋሲካን በሚያርዱበት በቂጣ በዓል መጀመሪያ ቀን ደቀ መዛሙርቱ፡- ፋሲካን ትበላ ዘንድ ወዴት ሄደን ልናሰናዳ ትወዳለህ?[24] አሉት። | 7 ፋሲካንም ሊያርዱበት የሚገባው የቂጣ በዓል ደረሰ፤<br><br>8 ጴጥሮስንና ዮሐንስንም፡- ፋሲካን |

[23] [ሉቃስ 22፡3] ይሁዳ ይህን የጥፋት አቅጣጫ እንዲከተል ሰይጣን በምን ሁኔታ እንዳነሣሣው መጽሐፍ ቅዱስ አይገልጥም። ከብዙ ዓላማዎች በአንዱ ወይም ሁሉንም በያዘ ምክንያት ተነሣሥቶ ይሆናል። ምኞት አንዱ ምክንያት ይመስላል (ዮሐ. 12፡6፥ ክፍል 141)። እንደ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ለድሆች ያሰበ መስሎ ለመታየት ሳይሻም አልቀረም (ማቴ. 26፡8-9፤ ማር. 14፡4-5፥ ክፍል 141)። ምናልባትም በቅርቡ በወጣው ትእዛዝ መሠረት ኢየሱስ ያለበትን በመጠቆም (ዮሐ. 11፡57፥ ክፍል 128ሀ) የዜግነት ግዴታውን መወጣት እንዳለበት ተሰምቶት ይሆናል። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በክብር ከገባ በኋላ እንዲነግሥ (ማቴ. 21፡15-17፤ ሉቃስ 19፡39-40፥ ክፍል 128ለ)፥ በአይሁድና በርሱ መካከል አንዳች ስምምነት ባለመደረጉ ከሌሎቹ ደቀመዛሙርት ይልቅ ተበሳጭቶ ይሆናል። ምናልባትም በዚህ ድርጊቱ እንዲነግሥ ኢየሱስን የሚያስገድድ መስሎታል። ባለፉት ሦስት ዓመታት የተከናወኑትን ከተመለከተ በኋላ ድርጊቱ በምንም ሁኔታ ኢየሱስን ለሞት ያበቃዋል ብሎ አላሰበም (ክፍል 158)። ያም ሆነ ይህ ለድርጊቱ ያነሣሣው ራስ ወዳድነት ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ በሰይጣን ባልተመራ ነበር።

(ማቴዎስ 26፣17-19 የቀጠለ)

18 እርሱም፦ ወደ ከተማ ከእገሌ ዘንድ ሄዳችሁ፦

መምህር፦ ጊዜዬ ቀርቦአል፤ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ከአንተ ዘንድ ፋሲካን አደርጋለሁ ይላል በሉት አለ።

19 ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ ፋሲካንም አሰናዱ።

(ማርቆስ 14፣12-16 የቀጠለ)

13 ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ላከ እንዲህም አላቸው፦

ወደ ከተማ ሂዱ፥ ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰውም ይገናኛችኋል፤ 14 ተከተሉት፥ የሚገባበትንም የቤቱን ጌታ፦ መምህሩ፦ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን የምበላበት የእንግዳ ቤት ወዴት ነው? ይላል በሉት። 15 እርሱም በደርብ ላይ ያለውን የተሰናዳና የተነጠፈ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል፤

16 በዚያም አሰናዱልን። ደቀ መዛሙርቱም ወጡ ወደ ከተማም ሄደው እንዳላቸው አገኙ፥ ፋሲካንም አሰናዱ።

(ሉቃስ 22፣7-13 የቀጠለ)

እንድንበላ ሄዳችሁ አዘጋጁልን[24] ብሎ ላካቸው።

9 እነርሱም፦ ወዴት እናዘጋጅ ዘንድ ትወዳለህ? አሉት።

10 እርሱም አላቸው፦ እነሆ፥ ወደ ከተማ ስትገቡ ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል፤ ወደ ሚገባበት ቤት ተከተሉት፤ 11 ለባለቤቱም፦ መምህሩ፦ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን የምበላበት የእንግዳ ቤት ክፍል ወዴት ነው? ይልሃል በሉት፤ 12 ያም በደርብ ላይ ያለውን የተነጠፈ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል፤ በዚያም አሰናዱልን።

13 ሄደውም እንዳላቸው አገኙና ፋሲካን አሰናዱ።

## ♦ ክፍል 144. የፋሲካ ማዕድ መጀመርና፥ ታላቅ ሆኖ ስለመቆጠር በደቀ መዛሙርቱ መሐል የተፈጠረ ክርክር

[ክፍል 125ለን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

ማቴዎስ 26፣20

20 በመሸም ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር በማዕድ ተቀመጠ።

ማርቆስ 14፣17

17 በመሸም ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ጋር መጣ።

ሉቃስ 22፣14-16፥ 24-30

14 ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር በማዕድ ተቀመጠ። 15 እርሱም፦ ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን

[24] [ማቴ. 26፡17፤ ማር. 14፡12፤ ሉቃስ 22፡8] እነዚህ ዝግጅቶች የተደረጉት በሚያዝያ ወር ሐሙስ ዕለት (በዕብራውያን የቀን አቆጣጠር በኒሳን ወር አሥራ አራተኛው ቀን) ነው። በፋሲካው እራት ዝግጅት ወቅት፥ ከቀትር በኋላ በጊዜው ልማድ መሠረት ጠቦቶች ይሰውና በምሽት ይመገቧቸው ነበር።

(ሉቃስ 22፡ 14-16፥ 24-30 የቀጠለ)

ፋሲካ[25] ልበላ እጅግ እመኝ ነበር፤ 16 እላችኋለሁና፥ በእግዚአብሔር መንግሥት
እስኪፈጸም ድረስ፥ ወደ ፊት ከዚህ አልበላም አላቸው።

24 ደግሞም ማናቸውም ታላቅ ሆኖ እንዲቈጠር በመካከላቸው ክርክር ሆነ። 25
እንዲህም አላቸው፡- የአሕዛብ ነገሥታት ይገዙአቸዋል፥ በላያቸውም የሚሠለጥኑት
ቸርነት አድራጊዎች ይባላሉ። 26 እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፤ ነገር ግን ከእናንተ
ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፥ የሚገዛም እንደሚያገለግል ይሁን። 27
በማዕድ የተቀመጠ ወይስ የሚያገለግል ማናቸው ታላቅ ነው? የተቀመጠው
አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ። 28 ነገር ግን እናንተ
በፈተናዎቼ ከእኔ ጋር ጸንታችሁ የኖራችሁ ናችሁ፤ 29-30 አባቴ እኔን እንደ ሾመኝ
እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ፥ በአሥራ ሁለቱ በእስራኤል
ነገድ ስትፈርዱ በዙፋኖች ትቀመጡ ዘንድ ለመንግሥት እሾማችኋለሁ።

## ♦ ክፍል 145. የደቀ መዛሙርትን እግር ማጠብ

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

ዮሐንስ 13፡ 1-20

1 ኢየሱስም ከፋሲካ በዓል በፊት፥ ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደ
ደረሰ አውቆ፥ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ
ወደዳቸው።

2 እራትም ሲበሉ ዲያብሎስ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ በይሁዳ ልብ አሳልፎ
እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኋላ፥ 3 ኢየሱስ አብ ሁሉን በልጁ እንደ ሰጠው
ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሄድ አውቆ፥ 4 ከእራት
ተነሣ ልብሱንም አኖረ፥ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ፤ 5 በኋላም በመታጠቢያው
ውኃ ጨመረ፥ የደቀ መዛሙርቱንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበትም ማበሻ ጨርቅ
ሊያብስ ጀመረ።

6 ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ፤ እርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ አንተ የእኔን እግር
ታጥባለህን? አለው።

7 ኢየሱስም መልሶ፡- እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፥ በኋላ ግን
ታስተውለዋለህ አለው።

8 ጴጥሮስም፡- የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም አለው።

ኢየሱስም፡- ካላጠብሁህ፥ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም ብሎ መለሰለት።

9 ስምዖን ጴጥሮስም፡- ጌታ ሆይ፥ እጄንና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ
አይደለም አለው።

---

[25] [ሉቃስ 22፡ 15] ይህ “የመጨረሻው እራት” የፋሲካ ምግብ መሆኑን ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ በማያሻማ ሁኔታ ገልጠውታል። ይህ ማለት የፋሲካው ግብዣ የተደረገው በሚያዝያ ወር (ዘሌዋ. 23፡ 5)፥ ሐሙስ ምሽት ጸሐይ ከጠለቀች በኋላ ሆኖ፥ የወሩ አሥራ አራተኛ ቀን አብቅቶ አሥራ አምስተኛው የተጀመረበት ነበር። ወሩ በዕብራይስጥ ‘ኒሳን’ ሲባል፥ ይህም የመጀመሪያው ወር ነው።

[26] [ዮሐ. 13፡ 15] እራት በመበላት ላይ ሳለ ኢየሱስ ያደረገው ነገር ራስን እስከ መሥዋዕት የሚያደርስ ትህትናን ማሳየት ስለሆነ፥ ደቀ መዛሙርቱ ይህን ምሳሌ በመውረስ መምህራቸውን ለመምሰል ይችሉ ነበር (ዮሐ. 13፡ 14፥ 16-17፥ ክፍል 125ለ፥ 144)።

(ዮሐንስ 13፡1-20 የቀጠለ)

10 ኢየሱስም፦ የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም፥ ሁለንተናው ግን ንጹሕ ነው፤ እናንተም ንጹሐን ናችሁ፥ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም አለው። 11 አሳልፎ የሚሰጠውን ያውቅ ነበርና፤ ስለዚህ፦ ሁላችሁ ንጹሐን አይደላችሁም አለው።

12 እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንሥቶ ዳግመኛ ተቀመጠ፥ እንዲህም አላቸው፦ ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን? 13 እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ። 14 እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። 15 እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ[26] ሰጥቻችኋለሁና። 16 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም። መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም። 17 ይህን ብታውቁ፥ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ።

18 ስለ ሁላችሁ አልናገርም፤ እኔ የመረጥኋቸውን አውቃለሁ፤ ነገር ግን መጽሐፍ፦ እንጀራዬን የሚበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣብኝ ያለው ይፈጸም ዘንድ ነው።

19 በሆነ ጊዜ እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ ዘንድ፥ ከአሁን ጀምሬ አስቀድሞ ሳይሆን እነግራችኋለሁ። 20 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ማናቸውን የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።

## ♦ ክፍል 146. አሳልፎ ሰጪው መታወቁ

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

| ማቴዎስ 26፡21-25 | ማርቆስ 14፡18-21 | ሉቃስ 22፡21-23 | ዮሐንስ 13፡21-30 |
| --- | --- | --- | --- |
| 21 ሲበሉም፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል አለ። | 18 ተቀምጠውም ሲበሉ ኢየሱስ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ፥ እርሱም ከእኔ ጋር የሚበላው አሳልፎ ይሰጠኛል አለ። | 21 ነገር ግን አሳልፎ የሚሰጠኝ እጅ[27] እነሆ በማዕድ ከእኔ ጋር ናት። 22 የሰው ልጅስ እንደ ተወሰነው ይሄዳል፥ ነገር ግን አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት። 23 ከእነርሱም ይህን ሊያደርግ ያለው ማን እንደ ሆነ እርስ በርሳቸው ይጠያየቁ ጀመር። | 21 ኢየሱስ ይህን ብሎ በመንፈሱ ታወከ መስክሮም፦ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል አለ። |
| 22 እጅግም አዝነው እያንዳንዱ፦ ጌታ ሆይ፥ እኔ እሆንን? ይሉት ጀመር። 23 እርሱም መልሶ፦ ከእኔ ጋር | 19 እነርሱም ያዝኑ፥ እያንዳንዳቸውም፦ እኔ እሆንን? ይሉት ጀመር። 20 እርሱም መልሶ፦ ከአሥራ ሁለቱ[27] | | 22 ደቀ መዛሙርቱ ስለ ማን እንደ ተናገረ አመንትተው እርስ በርሳቸው ተያዩ። |

| (ማቴዎስ 26፥21-25 የቀጠለ) | (ማርቆስ 14፥18-21 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 13፥21-30 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| እጁን በወጭቱ ያጠለቀ፥27 እኔን አሳልፎ የሚሰጥ እርሱ ነው። 24 የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል፥ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር አለ። | አንዱ ከእኔ ጋር ወደ ወጭቱ እጁን የሚያጠልቀው ነው። 21 የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር አላቸው። | 23 ኢየሱስም ይወደው የነበረ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ በኢየሱስ ደረት ላይ ተጠጋ፤ 24 ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ እርሱን ጠቅሶ፦ ስለማን እንደ ተናገረ ንገረን አለው።<br>25 እርሱም በኢየሱስ ደረት እንዲህ ተጠግቶ፦ ጌታ ሆይ፥ ማን ነው? አለው።<br>26 ኢየሱስም፦27 እኔ ቍራሽ አጥቅሼ የምሰጠው እርሱ ነው ብሎ መለሰለት። ቍራሽም አጥቅሶ ለአስቆሮቱ ለስምዖን ልጅ ለይሁዳ ሰጠው። |
| 25 አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳም መልሶ፦ መምህር ሆይ፥ እኔ እሆንን?<br>አለ፤ አንተ አልህ አለው።27 | | 27 ቍራሽም ከተቀበለ በኋላ ያን ጊዜ ሰይጣን ገባበት።<br>እንግዲህ ኢየሱስ፦ የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ አለው። 28 ነገር ግን ከተቀመጡት ስለ ምን ይህን እንዳለው ማንም አላወቀም፤ 29 ይሁዳ ከረጢቱን የያዘ ስለ ሆነ፥ ኢየሱስ፦ ለበዓሉ የሚያስፈልገንን ግዛ፥ ወይም ለድሆች ምጽዋት እንዲሰጥ ያለው ለአንዳንዱ መስሎአቸው ነበርና። 30 እርሱም ቍራሹን ከተቀበለ በኋላ ወዲያው ወጣ፤ ሌሊትም ነበረ። |

## ♦ ክፍል 147. የጴጥሮስ ክህደት በቅድሚያ መነገሩ

[ክፍል 156ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

<u>ዮሐንስ 13፡31-36</u>

31 ከወጣም በኋላ ኢየሱስ እንዲ አለ፡- አሁን የሰው ልጅ ከበረ እግዚአብሔርም ስለ
እርሱ ከበረ፤ 32 እግዚአብሔር ስለ እርሱ የከበረ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ደግሞ እርሱን
ራሱን ያከብረዋል ወዲያውም ያከብረዋል።

33 ልጆች ሆይ፥ ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፤ ትፈልጉኛላችሁ፤ ለአይሁድም፡-
እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አይቻላችሁም እንዳልኋቸው፥ አሁን ለእናንተ
ደግሞ እላችኋለሁ።

34 እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ
ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ። 35 እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥
ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።

36 ስምዖን ጴጥሮስም፡- ጌታ ሆይ፥ ወዴት ትሄዳለህ? አለው። ኢየሱስም፡-
ወደምሄድበት አሁን ልትከተለኝ አትችልም፥ ነገር ግን በኋላ ትከተለኛለህ ብሎ
መለሰለት።

| <u>ማቴዎስ 26፡31-35</u> | <u>ማርቆስ 14፡27-31</u> | <u>ሉቃስ 22፡31-38</u> | <u>ዮሐንስ 13፡37-38</u> |
|---|---|---|---|
| 31 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ፡- በዚች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ፤ [ዘካርያስ 13፡7] ‘‘እረኛውን እመታለሁ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ’’ የሚል ተጽፎአልና፤ 32 ከተነሣሁ በኋላ ግን ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው። | 27 ኢየሱስም፡- በዚች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ፤ ‘‘እረኛዉን እመታለሁ በጎችም ይበተናሉ’’ የሚል ተጽፎአልና። [ዘካርያስ 13፡7] 28 ነገር ግን ከተነሣሁ በኋላ ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው። | 31 ጌታም፡- ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ 32 እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና አለ። | |

[27] [ማቴ. 26፡23፥ 25፤ ማር. 14፡20፤ ሉቃስ 22፡21፤ ዮሐ. 13፡26] ማርቆስና ሉቃስ አሳልፎ የሰጠውን በስም አልጠቀሱትም፤ ማቴዎስና ዮሐንስ ግን ማንነቱን ገልጠዋል። በሥፍራው የነበሩት ሌሎች ደቀ መዛሙርት አሳልፎ ሰጪው ይሁዳ ነው ብለው ያሰቡ አይመስሉም (ዮሐ. 13፡28)። ምክንያቱም ይሁዳ የአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት የተከበረ አባል ነበር። ገንዘብ ያዣቸው ይሁዳ ከመሆኑ ባሻገር (ዮሐ. 13፡29፤ 12፡6፥ ክፍል 141) በእነርሱ ስም ለድሆች የሚመፀውተውም እርሱ ነበር (ዮሐ. 13፡29፤ 12፡4-5፥ ክፍል 141)። በዚህ የጌታ እራት ላይም ከጌታ በስተቀኝ የተቀመጠው ሐዋርያው ዮሐንስ ሲሆን፥ በስተግራ የነበረው እርሱ በመሆኑ የክብር ሥፍራ ተሰጥቶት ነበር (ዮሐ. 13፡23፥ 26)። እንዲህ ያለ ክብር የነበረው ይሁዳ ጌታን አሳልፎ አይሰጥም በማለት ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ሳይከራከሩ አይቀርም።

| (ማቴዎስ 26፡31-35 የቀጠለ) | (ማርቆስ 14፡27-31 የቀጠለ) | (ሉቃስ 22፡31-38 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 13፡37-38 የቀጠለ) |
|---|---|---|---|
| 33 ጴጥሮስም መልሶ፡- ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም አለው። 34 ኢየሱስ፡- እውነት እልሃለሁ፥ በዚች ሌሊት ዶሮ[28] ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው። 35 ጴጥሮስ፡- ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚያስፈልገኝ ቢሆን፥ ከቶ አልክድህም አለው። ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ደግሞ እንደዚሁ አሉ። | 29 ጴጥሮስም፡- ሁሉም ቢሰናከሉ እኔ ግን ከቶ አልሰናከልም አለው። 30 ኢየሱስም፡- እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ በዚች ሌሊት ዶሮ[28] ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው። 31 እርሱም ቃሉን አበርትቶ፡- ከአንተ ጋር የምሞት እንኳ ቢሆን ከቶ አልክድህም አለ። ሁሉም ደግሞ እንደዚሁ አሉ። | 33 እርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ ወደ ወኅኒም ወደ ሞትም ከአንተ ጋር ለመሄድ የተዘጋጀሁ ነኝ አለው። 34 እርሱ ግን፡- ጴጥሮስ ሆይ፥ እልሃለሁ፥ እንዳታውቀኝ ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዛሬ ዶሮ[28] አይጮኽም አለው። 35 ደግሞም፡- ያለ ኮረጆና ያለ ከረጢት | 37 ጴጥሮስም፡- ጌታ ሆይ፥ አሁን ልከተልህ አለመቻሌ ስለ ምንድር ነው? ነፍሴን ስንኳ ስለ አንተ እሰጣለሁ አለው። 38 ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰለት፡- ነፍስህን ስለ እኔ ትሰጣለህን? እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዶሮ[28] አይጮኽም። |

ያለ ጫማም በላክኋችሁ ጊዜ፥ አንዳች ጐደለባችሁን? አላቸው።

እነርሱም፡- አንዳች እንኳ አሉ።

36 እርሱም፡- አሁን ግን ኮረጆ ያለው ከእርሱ ጋር ይውሰድ፥ ከረጢትም ያለው እንዲሁ፤ የሌለውም ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ። 37 እላችኋለሁና፥ ይህ፡- ከዓመፀኞች ጋር ተቈጠረ ተብሎ የተጻፈው [ኢሳይያስ 53፡12] በእኔ ሊፈጸም ግድ ነው፤ አዎን፥ ስለ እኔ የሚሆነው አሁን ይፈጸማልና አላቸው።

38 እነርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ እነሆ፥ በዚህ ሁለት ሰይፎች አሉ አሉት።

እርሱም፡- ይበቃል አላቸው።

[28] [ማቴ. 26፡34፤ ማር. 14፡30፤ ሉቃስ 22፡34፤ ዮሐ. 13፡38] ከእኩለ ሌሊት እስከ ለሊቱ 9 ሰዓት ድረስ ያለው ጊዜ "የዶሮ መጮኺያ" ይባል ነበር (ማር. 13፡35፥ ክፍል 139ረ)። ዶሮ በዚህ ሌሊት መጀመሪያና መጨረሻ ይጮሃል። በማርቆስ ዘገባ መሠረት ኢየሱስ በግልጥ የተናገረው ስለ ሁለተኛው የዶሮ ጩኸት ነው። ማቴዎስ፥ ሉቃስና ዮሐንስ ግን ትንቢቱን በአጠቃላይ ገለጣ እንደደጋገሙ፥ ማለት ስለ አንድ ጊዜ የዶሮ ጩኸት ማለት በሚገባ ስለሚታወቀው ስለ ሁለተኛው ብቻ መናገሩን ነው የዘገቡት። በሚቀጥለው ማለዳ፥ ከንጋት በፊት ጴጥሮስ ጌታውን ሦስት ጊዜ መካድ ነበረበት።

## ♦ ክፍል 148. የማዕዱ ማብቃት እና የጌታ እራት ሥርዓት መደንገግ

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

ማቴዎስ 26፡26-29

26 ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡- እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ።

27 ጽዋንም[29] አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፡- ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ 28 ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው። 29 ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም።

ማርቆስ 14፡22-25

22 ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ሰጣቸውና፡- እንካችሁ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ።

23 ጽዋንም[29] አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው፥ ሁሉም ከእርሱ ጠጡ።

24 እርሱም፡- ይህ ስለ ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው። 25 እውነት እላችኋለሁ፥ በእግዚአብሔር መንግሥት ከወይኑ ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ደግሞ አልጠጣውም አላቸው።

ሉቃስ 22፡17-20

17 ጽዋንም ተቀብሎ አመስግኖም፡- ይህን እንካችሁ በመካከላችሁም ተካፈሉት፤ 18 እላችኋለሁና፥ የእግዚአብሔር መንግሥት እስክትመጣ ድረስ ከአሁን ጀምሮ ከወይኑ ፍሬ አልጠጣም አለ።

19 እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ ቈርሶም ሰጣቸውና፡- ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።

20 እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፡- ይህ ጽዋ[29] ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው።

1 ቆሮንቶስ 11፡23-26

23 ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤

24 ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቈርሶም፡- እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።

25 እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ፡- ይህ ጽዋ[29] በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።

26 ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።

# > ከደርቡ እስከ ጌቴሴማኒ የተደረገ ጸሎትና ስብከት <

## ♦ ክፍል 149. ስለ ጌታ መድረሻ፥ ስለ አብ፥ እንዲሁም ስለ መንፈስ ቅዱስ የተነሡ ጥያቄዎች መልስ አገኙ

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

<u>ዮሐንስ 14፡1-31</u>

1 ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ።[30] 2 በአባቴ
ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ
እሄዳለሁና፤ 3 ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ
ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ። 4 ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ፥
መንገዱንም ታውቃላችሁ።

5 ቶማስም፦ ጌታ ሆይ፥ ወደምትሄድበት አናውቅም፤ እንዴትስ መንገዱን
እናውቃለን? አለው።

6 ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ
የለም። 7 እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁንም ጀምራችሁ
ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው።

8 ፊልጶስ፦ ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው።

9 ኢየሱስም አለው፦ አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር
አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ፦ አብን አሳየን ትላለህ?
10 እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል
ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል። 11
እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው
እመኑኝ። 12 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ
እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥ 13 እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤

---

[29] [ማቴ. 26፡27፤ ማር. 14፡23፤ ሉቃስ 22፡20፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡25] እንደ እንጀራ (ማቴ. 26፡26፤ ማር. 14፡22፤ ሉቃስ 22፡19፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡23)፥ *ይህ ጽዋ የአይሁዳውያን ባሕላዊ የፋሲካ ዝግጅትና ግብዣ አካል ነበር። ተጋባዦቹ በግብዣው ሰዓት አራት ጊዜ ሊያደርጉት ከሚገባ የጽዋ ማንሣት ሥርዓት ሦስተኛው ነበር። በባሕሉ መሠረት ሦስተኛው ጽዋ፥ እግዚአብሔር ዘጸዓት* 6፡6-7 *"ከተገዢነታቸውም አድናችኋለሁ፥ በተዘረጋ ክንድ በታላቅ ፍርድም እታደጋችኋለሁ" በማለት ለእስራኤል ከገባው አራት ተስፋዎች ከሦስተኛው ጋር ይዛመዳል። ለቤዛነት የፈሰሰው የኢየሱስ ደም ተምሳሌት ይሆናል (ማቴ.* 26፡28፤ ማር. 14፡24፤ ሉቃስ 22፡20፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡25]። *የመጨረሻው ጽዋ የእስራኤልን ወደ ምድሯ መመለስ ከሚመለከተው ከአራተኛው ተስፋ ጋር የሚዛመድ ሲሆን፥ የእግዚአብሔር መንግሥት* እስኪ.መሠረት ድረስ ኢየሱስ የሚያከናውነው አይሆንም (ማቴ. 26፡29፤ ማር. 14፡25)።

[30] [ዮሐ. 14፡1] *ይህ በሕማማት ሰሞን ማክሰኞ ዕለት የተደረገ ንግግር* (ክፍል 149-151)፥ *በደብረ ዘይት ተራራ ስብከቱ ጊዜ ሐሙስ ዕለት ለነዚሁ አድማጮች ይነገር ነበር* (139ሀ-139ሰ)። *ይሁን እንጂ አንዱ ከሌላው ፍጹም ይለያያል። ልዩነቱ ንግግሮቹ በተደረጉበት ዓላማ ውስጥ ነው ያለው። ማክሰኞ ዕለት በተደረገው ንግግር የቁምነገሩ ትኩረት፥ አድማጮቹ አባላት የሆኑበት የወደፊቱ የእስራኤል መንግሥት ጉዳይ ነው* (ክፍል 139ሀ)። *የሐሙሱ ንግግር ጉዳይ ደቀ መዛሙርቱና ሌሎች አማኞች ኢየሱስ በማይኖርበት ጊዜ* (ዮሐ. 13፡33፥ 36፥ ክፍል 147፤ ዮሐ. 16፡5-7፥ ክፍል 150ሐ) *የሚገኙበትን ሁኔታ የተመለከተ ነበር። ብዙዎቹ እስራኤላውያን ያልሆኑ ሁለተኛዎቹ አድማጮች የሚጠብቁት፥ ለእስራኤል መንግሥት መመሥረት የሚጨነቁት ከሚጠብቁት በጣም ይለያል።*

(ዮሐንስ 14፥1-31 የቀጠለ)

አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። 14 ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።

15-16 ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ 17 እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ። 18 ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ። 19 ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፤ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፤ እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ። 20 እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ። 21 ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ።

22 የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ፦ ጌታ ሆይ፥ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነው? አለው።

23 ኢየሱስም መለሰ አለውም፦ የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን። 24 የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።

25 ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ፤ 26 አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል። 27 ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም።

28 እኔ እሄዳለሁ ወደ እናንተም እመጣለሁ እንዳልኋችሁ ሰማችሁ። የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር። 29 ከሆነም በኋላ ታምኑ ዘንድ አሁን አስቀድሞ ሳይሆን። ነግሬአችኋለሁ። 30 ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም፥ የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣልና፤ በእኔ ላይም አንዳች የለውም፤ 31 ነገር ግን አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ፥ አብም እንዳዘዘኝ፥ እንዲሁ አደርጋለሁ።

ተነሡ፤ ከዚህ እንሂድ።

---

[31] [ዮሐ. 15፥1] ወይን ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እስራኤልን የሚወክል ምሳሌ መሆኑ በሚገባ ይታወቃል (መዝ. 80፥8፤ ኢሳ. 5፥1-7፤ ኤር. 2፥21፤ ሕዝ. 15፥1-8፤ 19፥10፤ ሆሴዕ10፥1)። ይሁን እንጂ በኢየሱስ የመጀመሪያ ምጽዓት የነበረ ትውልድ ጀርባውን ሰጠው። በመሆኑም እነዚያ ሕዝቦች "የእውነተኛው" ወይን ቅርንጫፍ አልነበሩም። የእውነተኛ የወይን ግንድ በሆነው በርሱ የሚኖር ብቻ ነው የርሱ ሊሆን የሚችለው (15፥4)። በዚህ መንፈሳዊ ግንኙነት ነበር ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ካረገ በኋላ ፍሬ ሊያፈሩ የቻሉት (ዮሐ. 15፥16)።

[32] [ዮሐ. 15፥18] ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ የመለየው ጊዜ በመቃረቡ፥ ተቃውሞን አስመልክቶ ይህን ቃል መናገር ነበረበት። እርሱ እስካለ ድረስ ስደቱ በርሱ እንጂ በነርሱ ላይ ስለማይሆን ቀደም ብሎ ይህን ቃል መናገሩ አስፈላጊ አልነበረም (ዮሐ. 16፥ 4ለ)። ከርሱ ማረግ በኋላ ይረዳቸው ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ ይኖርባቸዋል (ዮሐ. 15፥26-27)።

## ♦ ክፍል 150ሀ. የወይኑ ግንድና ቅርንጫፎቹ

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

ዮሐንስ 15፡1-17

1 እውነተኛ የወይን ግንድ[31] እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው። 2 ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል። 3 እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ፤ 4 በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም።

5 እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። 6 በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል ይደርቅማል፤ እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል፥ ያቃጥሉአቸውማል። 7 በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል። 8 ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከበራል።

9 አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ። 10 እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። 11 ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ። 12 እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። 13 ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። 14 እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ። 15 ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ አስታውቄአችኋለሁና። 16 እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ፥ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ። 17 እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ።

## ♦ ክፍል 150ለ. ከዓለም የሚነሣ ተቃውሞ

[ክፍል 54ሰ፥ 70ለና 145ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

ዮሐንስ 15፡18-16፡4

18 ዓለም[32] ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ። 19 ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል። 20 ባርያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ። እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው እንደ ሆኑ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ። 21 ዳሩ

[33] [ዮሐ. 16፡5] ይህ ቃል በመጀመሪያ ሲታይ በጴጥሮስ (ዮሐ. 13፡36፥ ክፍል 147) እና በቶማስ (ዮሐ. 14፡5፥ ክፍል 149) የቀረቡትን ጥያቄዎች በዝምታ ያለፋቸው ይመስላል። ኢየሱስ ይህን ቃል የተናገረው፥ ቀደም ሲል የተጠየቁት ጥያቄዎች የተሰነዘሩት፥ በእርግጥ እርሱ የሚሄድበትን ለማወቅ ጓጉተው ሳይሆን፥ ከርሱ መለየታቸው አስጨንቋቸው መሆኑን ለማመልከት ነበር። አሁን ግን ወደ አብ የሚመለስ ስለመሆኑ ስለገለጠላቸው፥ ስለዚያ ስፍራ ምንነት ብልህ በሆነ አቀራረብ መጠየቅ ነበረባቸው።

(ዮሐንስ 15፡18-16፡4 የቀጠለ)

ግን የላከኝን አያውቁምና ይህን ሁሉ ስለ ስሜ ያደርጉባችኋል። 22 እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም። 23 እኔን የሚጠላ አባቴን ደግሞ ይጠላል። 24 ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው ባላደረግሁ፥ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል ጠልተውማል። 25 ነገር ግን በሕጋቸው፦ በከንቱ ጠሉኝ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው። [መዝሙር 35፡19፥ 69፡4]

26 ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ 27 እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ።

1 እንዳትሰናከሉ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። 2 ከምኵራባቸው ያወጡአችኋል፤ ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል። 3 ይህንም የሚያደርጉባችሁ አብንና እኔን ስላላወቁ ነው። 4 ነገር ግን ጊዜው ሲደርስ እኔ እንደ ነገርኋችሁ ታስቡ ዘንድ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። ከእንናንተም ጋር ስለ ነበርሁ በመጀመሪያ ይህን አልነገርኋችሁም።

## ♦ ክፍል 150ሐ. የመንፈስ ቅዱስ መምጣትና አገልግሎቱ

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

ዮሐንስ 16፡5-15

5 አሁን ግን ወደ ላከኝ እሄዳለሁ ከእናንተም፦ ወዴት ትሄዳለህ? ብሎ የሚጠይቀኝ የለም።[33] 6 ነገር ግን ይህን ስለ ተናገርኋችሁ ኀዘን በልባችሁ ሞልቶአል። 7 እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ።[34] 8 እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤ 9-10 ስለ ኃጢአት፥ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም፥ ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ 11 ስለ ፍርድም፥ የዚህ ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው።

12 የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። 13 ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል። 14 እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና። 15 ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው፤ ስለዚህ፦ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልሁ።

---

34 [ዮሐ. 16፡7] የመንፈስ ቅዱስ (አጽናኙ) በበዓለ አምሳ ዕለት የሚጀምረውን አዲስ ዘመን ለማክበር መምጣት፥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አዲስ ምዕራፍን ያመለክታል። የመንፈስ ቅዱስ አዲሱ እንቅስቃሴ በአዲሱ ዘመን ከነበረው ልዩ ባሕርያቱ ውስጥ አንዱ ነበር። እዚህ ላይ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት መንታ መሆኑ ነው የተገለጠው፦ ለዓለም የሚሰጠው አገልግሎቱ (ዮሐ. 16፡7-11)፥ እና ለደቀ መዛሙርቱና በነርሱ ምስክርነት ለሚያምኑት አማኞች የሚሰጠው አገልግሎት (ዮሐ. 16፡12-15፤ ዮሐ 17፡20፥ ክፍል 151)።

## ♦ ክፍል 150መ. ስለ ጌታ ትንሣኤ ደስታ በቅድሚያ መነገሩ

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

ዮሐንስ 16፥16-22

16 ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁም፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና።

17 ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ እርስ በርሳቸው፦ ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁም፤ ደግሞ፦ ወደ አብ እሄዳለሁና የሚለን ይህ ምንድር ነው? ተባባሉ። 18 እንግዲህ፦ ጥቂት የሚለው ይህ ምንድር ነው? የሚናገረውን አናውቅም አሉ።

19 ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደ ወደዱ አውቆ እንዲህ አላቸው፦ ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁ ስላልሁ፥ ስለዚህ እርስ በርሳችሁ ትመራመራላችሁን? 20 እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እናንተ ታለቅሳላችሁ ሙሾም ታወጣላችሁ፥ ዓለም ግን ደስ ይለዋል፤ እናንተም ታዝናላችሁ፥ ነገር ግን ኀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል። 21 ሴት በምትወልድበት ጊዜ ወራትዋ ስለ ደረሰ ታዝናለች፤ ነገር ግን ሕፃን ከወለደች በኋላ፥ ሰው በዓለም ተወልዶአልና ስለ ደስታዋ መከራዋን ኋላ አታስበውም። 22 እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ፤ ነገር ግን እንደ ገና አያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል፥ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።

## ♦ ክፍል 150ሠ. የጸሎት መልስ ማግኘትና የሰላም ተስፋ

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

ዮሐንስ 16፥23-33

23 በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል። 24 እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።

25 ይህን በምሳሌ ነግሬአችኋለሁ፤ ነገር ግን ስለ አብ ለእናንተ በግልጥ የምናገርበት እንጂ ከዚያ ወዲያ በምሳሌ የማልናገርበት ሰዓት ይመጣል። 26 በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤ 27 እናንተ ስለ ወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እኔ እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና። 28 ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ።

29 ደቀ መዛሙርቱ፦ እነሆ፥ አሁን በግልጥ ትናገራለህ በምሳሌም ምንም አትነግርም። 30 ሁሉን እንድታውቅ ማንምም ሊጠይቅህ እንዳትፈልግ አሁን እናውቃለን፤ ስለዚህ ከእግዚአብሔር እንደ ወጣህ እናምናለን አሉት።

31 ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፦ አሁን ታምናላችሁን? 32 እነሆ፥ እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት የምትበታተኑበት እኔንም ለብቻዬ የምትተዉበት ሰዓት ይመጣል፥ አሁንም ደርሶአል፤ ነገር ግን አብ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም።

33 በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።

## ♦ ክፍል 151. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱና ለሚያምኑ ሁሉ መጸለዩ

- ኢየሩሳሌም፥ በደርብ ላይ ባለው አዳራሽ -

ዮሐንስ 17፡1-26

1-2 ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ወደ ሰማይ ዓይኖቹን አንሥና እንዲህ አለ፡-

"አባት ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአል፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ፥ በሥጋም ሁሉ ላይ
ሥልጣን እንደ ሰጠኸው፥ ለሰጠኸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ
ልጅህን አክብረው። 3 እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም
ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት። 4 እኔ ላደርገው
የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤ 5 አሁንም፥ አባት ሆይ፥ ዓለም
ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ።

6 ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገለጥሁላቸው። የአንተ ነበሩ ለእኔም
ሰጠሃቸው፤ 7 ቃልህንም ጠብቀዋል። የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ አሁን
ያውቃሉ፤ 8 የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፥ ከአንተም
ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ። 9 እኔ ስለ
እነዚህ እለምናለሁ፤ ስለ ዓለም አልለምንም ስለ ሰጠኸኝ እንጂ፤ የአንተ
ናቸውና፤ 10 የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተውም የእኔ ነው፤ እኔም ስለ
እነርሱ ከብሬአለሁ። 11 ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም፥ እነርሱም በዓለም
ናቸው፥ እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን
እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው። 12 ከእነርሱ ጋር በዓለም ሳለሁ
የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበር፤ ጠበቅኋቸውም መጽሐፉም
እንዲፈጸም ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም።

13 አሁንም ወደ አንተ እመጣለሁ፤ በእነርሱም ዘንድ ደስታዬ የተፈጸመ
እንዲሆንላቸው ይህን በዓለም እናገራለሁ። 14 እኔ ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔም
ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው። 15 ከክፉ
እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም። 16 እኔ ከዓለም
እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም። 17 በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት
ነው። 18 ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው፤ 19
እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ።

20-21 ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ
እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥
አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ
ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ። 22-23 እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤
እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን
ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም
መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል።

24 አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ
ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ።

25 ጻድቅ አባት ሆይ፥ ዓለም አላወቀህም፥ እኔ ግን አወቅሁህ እነዚህም አንተ
እንደ ላክኸኝ አወቁ፤ 26 እኔንም የወደድህባት ፍቅር በእነርሱ እንድትሆን እኔም
በእነርሱ፥ ስምህን አስታወቅኋቸው አስታውቃቸውማለሁ።"

## ♦ ክፍል 152. ኢየሱስ በጌቴሴማኒ የጸለያቸው ሦስት አስጨናቂ ጸሎቶች

- ደብረ ዘይት በሚገኘው ጌቴሴማኒ -

| ማቴዎስ 26፡30፥ 36-46 | ማርቆስ 14፡26፥ 32-42 | ሉቃስ 22፡39-46 | ዮሐንስ 18፡1 |
| --- | --- | --- | --- |
| 30 መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ። | 26 መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ። | 39 ወጥቶም እንደ ልማዱ ወደ ደብረ ዘይት ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም ደግሞ ተከተሉት። 40 ወደ ስፍራውም ደርሶ፦ | 1 ኢየሱስም ይህን ብሎ አትክልት ወዳለበት ስፍራ ወደ ቄድሮን ወንዝ ማዶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወጣ፤ እርሱም ደቀ መዛሙርቱም በዚያ ገቡ። |
| 36 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ጌቴሴማኒ ወደምትባል ስፍራ መጣ ደቀ መዛሙርቱንም፦ ወዲያ ሄጄ ስጸልይ ሳለ በዚህ ተቀመጡ አላቸው። 37 ጴጥሮስንም ሁለቱንም የዘብዴዎስን ልጆች ወስዶ ሊያዝን[35] ሊተክዝም ጀመር። 38 ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ቆዩ ከእኔም ጋር ትጉ አላቸው። | 32 ጌቴሴማኒ ወደምትባል ስፍራ መጡ፥ ደቀ መዛሙርቱንም፦ ስጸልይ ሳለሁ፥ በዚህ ተቀመጡ አላቸው። 33 ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ከእርሱ ጋር ወሰደ፤ ሊደነግጥም ሊተክዝም ጀመረና፦ 34 ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤[35] በዚህ ቈዩ ትጉም አላቸው። | ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ አላቸው። 41 ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም፦ አባት ሆይ፥ 42 ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ | |
| 39 ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ፦ አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ | 35 ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በምድርም ወድቆ፥ ቢቻልስ ቢሆን ሰዓቲቱ ከእርሱ እንድታልፍ ጸለየና፦ 36 አባ አባት ሆይ፥ ሁሉ | | |

[35] [ማቴ. 26፡37፤ ማር. 14፡33፤ ሉቃስ 22፡44] የኢየሱስ ሰቆቃ በዋናነት በአካላዊ ስቃይ ወይም ወዳጆቹና አብረውት የሚሠሩ ሰዎች ጥለውት ስለሚሄዱ የተፈጠረ አልነበረም። ከርሱ እንዲያልፍለት ሦስት ጊዜ የጸለየበት "ጽዋ" (ማቴ. 26፡39፥ 42፥ 44፤ ማር. 14፡36፥ 39፤ ሉቃስ 22፡42)፥ ማለት ከአብ መለየቱ (ማቴ. 27፡46፤ ማር. 15፡34፥ ክፍል 165) ነበር ዋናው ሰቆቃ። ይሁን እንጂ የአብ ፈቃድ ከሆነ፥ ነበርም፥ ያንንም ለመቀበል ፈቃደኛ ነበር (ሐዋ. 2፡22-23)።

(ማቴዎስ 26፡30፥ 36-46 የቀጠለ)

ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ።

40 ወደ ደቀ መዛሙርቱም
መጣ፤ ተኝተውም
አገኛቸውና ጴጥሮስን፦
እንዲሁም ከእኔ ጋር
አንዲት ሰዓት እንኳ
ልትተጉ አልቻላችሁምን?
41 ወደ ፈተና እንዳትገቡ
ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ
ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን
ደካማ ነው አለው።

42 ደግሞ ሁለተኛ ሄዶ
ጸለየና፦ አባቴ፥ ይህች ጽዋ
ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ
የማይቻል እንደ ሆነ፥
ፈቃድህ ትሁን አለ። 43
ደግሞም መጥቶ
ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ
ከብደው ነበርና ተኝተው
አገኛቸው። 44 ደግሞም
ትቶአቸው ሄደ፥ ሦስተኛም
ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ።

45 ከዚያ ወዲያ ወደ ደቀ
መዛሙርቱ መጥቶ፦
እንግዲህስ ተኙ ዕረፉም፤

(ማርቆስ 14፡26፥ 32-42 የቀጠለ)

ይቻልሃል፤ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን አለ።

37 መጣም ተኝተውም
አገኛቸው፥ ጴጥሮስንም፦
ስምዖን ሆይ፥ ተኝተሃልን?
አንዲት ሰዓትስንኳ
ልትተጋ አልቻልህምን?
38 ወደ ፈተና እንዳትገቡ
ትጉ ጸልዩም፤ መንፈስስ
ተዘጋጅታለች፥ ሥጋ ግን
ደካማ ነው አለው።

39 ደግሞም ሄዶ ያንኑ
ቃል ጸለየ።

40 ደግሞም መጥቶ
ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ
ከብደው ነበርና ተኝተው
አገኛቸው፥
የሚመልሱለትንም
አላወቁም።

41 ሦስተኛም መጥቶ፦
እንግዲህስ ተኙ ዕረፉም፤

(ሉቃስ 22፡39-46 የቀጠለ)

ፈቃድ አይሁን የአንተ
እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።
43 ከሰማይም መጥቶ
የሚያበረታ መልአክ
ታየው። 44 በፍርሃትም[35]
ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ
ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ
እንደሚወርድ እንደ ደም
ነጠብጣብ ነበረ።

45 ከጸሎትም ተነሥቶ
ወደ ደቀ መዛሙርቱ
መጣና ከኀዘን የተነሣ
ተኝተው ሲያገኛቸው፦ 46
ስለ ምን ትተኛላችሁ? ወደ
ፈተና እንዳትገቡ
ተነሥታችሁ ጸልዩ
አላቸው።

(ማቴዎስ 26፡30፥ 36-46 የቀጠለ)

እነሆ፥ ሰዓቲቱ ቀርባለች የሰው ልጅም በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል። 46 ተነሡ፥ እንሂድ፤ እነሆ፥ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል አላቸው።

(ማርቆስ 14፡26፥ 32-42 የቀጠለ)

ይበቃል፤ ሰዓቲቱ ደረሰች፤ እነሆ፥ የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል። 42 ተነሡ፥ እንሂድ፤ እነሆ፥ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል አላቸው።

# 12

# የክርስቶስ ሞት

## > አልፎ መሰጠትና እሥራት <

### ♦ ክፍል 153. ኢየሱስ አልፎ ተሰጠ፥ ታሠረ፥ ብቻውን ተተወ

- ጌቴሴማኒ -

| ማቴዎስ 26፡47-56 | ማርቆስ 14፡43-52 | ሉቃስ 22፡47-53 | ዮሐንስ 18፡2-12 |
|---|---|---|---|
| 47 ይህንም ገና ሲናገር፥ እነሆ፥ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ መጣ፥ ከእርሱም ጋር ብዙ ሕዝብ ሰይፍና ጐመድ ይዘው ከካህናት አለቆችና ከሕዝቡ ሽማግሎች ዘንድ መጡ። | 43 ወዲያውም ገና ሲናገር ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ መጣ፥ ከእርሱም ጋር ብዙ ሰዎች ሰይፍና ጐመድ ይዘው ከካህናት አለቆችና ከጻፎች ከሽማግሌዎችም ዘንድ መጡ። | 47 ገናም ሲናገር እነሆ፥ ሰዎች መጡ፤ ከአሥራ ሁለቱ አንዱም ይሁዳ የሚባለው ይቀድማቸው ነበር፥ | 2 ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ጊዜ ወደዚያ ስለ ተሰበሰቡ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ደግሞ ስፍራውን ያውቅ ነበር። 3 ስለዚህ ይሁዳ ጭፍሮችንና[36] ከካህናት አለቆች ከፈሪሳውያንም ሎሌዎችን ተቀብሎ በችቦና በፋና በጋሻ ጦርም ወደዚያ መጣ። |
| | | | 4 ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና፦ ማንን ትፈልጋላችሁ አላቸው። |
| | | | 5 የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት። |
| | | | ኢየሱስ፦ እኔ ነኝ አላቸው። አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ደግሞ ከእነርሱ ጋር |

[36] [ዮሐ. 18፡3] ኢየሱስን ለመግደል በነበራቸው እቅድ መሠረት ሊቀካህኑ፥ በካህናት አለቆችና በፈሪሳውያን ተወክለው የሮም ባለሥልጣናት ኢየሱስን በመያዝ እንዲተባበሯቸው ጠየቀ። ለአንድ ግዳጅ የሚሰባሰበውም መለስተኛ የሮማውያን ወታደር ብዛት ስድስት መቶ ነበር። ምንም እንኳን ሮማውያን አንድ እስረኛ ለመጠበቅ ብዙ ወታደሮች የሚያሰማሩ ቢሆንም (ሐዋ. 23፡23)፥ ኢየሱስን በመያዙ ጊዜ ግን ስድስት መቶ ወታደሮች ማሰማራታቸው ያጠራጥራል። በማቴዎስ 26፡47 ላይ ‘‘ብዙ ሕዝብ’’ ከሚለው፥ እንዲሁም ማርቆስና ሉቃስ ‘‘ብዙ ሰዎች’’ (ማር. 14፡43፤ ሉቃስ 22፡47)፥ ከሚሉት በመነሣት የምንረዳው የወታደሮቹ ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አለመሆኑን ነው።

(ማቴዎስ 26፡47-56 የቀጠለ)

48 አሳልፎ
የሚሰጠውም፦
የምስመው እርሱ
ነው፤ ያዙት ብሎ
ምልክት
ሰጥቶአቸው ነበር።
49 ወዲያውም ወደ
ኢየሱስ ቀረበና፦
መምህር ሆይ፥
ሰላም ለአንተ ይሁን
ብሎ ሳመው።

(ማርቆስ 14፡43-52 የቀጠለ)

44 አሳልፎ
የሚሰጠውም፦
የምስመው እርሱ
ነው፤ ያዙት
ተጠንቅቃችሁም
ውሰዱት ብሎ
ምልክት
ሰጥቶአቸው ነበር።
45 መጥቶም
ወዲያው ወደ እርሱ
ቀረበና፦

መምህር ሆይ፥
መምህር ሆይ፥
ብሎ ሳመው፤

(ሉቃስ 22፡47-53 የቀጠለ)

ሊስመውም ወደ
ኢየሱስ ቀረበ።
48 ኢየሱስ ግን፦
ይሁዳ ሆይ፥
በመሳም የሰውን
ልጅ አሳልፈህ
ትሰጣለህን?
አለው።

(ዮሐንስ 18፡2-12 የቀጠለ)

ቆሞ ነበር። 6
እንግዲህ፦ እኔ ነኝ
ባላቸው ጊዜ ወደ
ኋላ አፈግፍገው
በምድር ወደቁ።

7 ደግሞም፦ ማንን
ትፈልጋላችሁ? ብሎ
ጠየቃቸው።

እነርሱም፦
የናዝሬቱን ኢየሱስን
አሉት።

8 ኢየሱስ መለሰ፦
እኔ ነኝ አልኋችሁ፤
እንግዲህ እኔን
ትፈልጉ እንደ ሆ
ናችሁ እነዚህ ይሂዱ
ተዉአቸው አለ፤ 9
ይህም፦ ከእነዚህ
ከሰጠኸኝ አንዱን
ስንኳ አላጠፋሁም
ያለው ቃል ይፈጸም
ዘንድ ነው።

(ማቴዎስ 26፥47-56 የቀጠለ)

50 ኢየሱስም፦ ወዳጄ ሆይ፥ ለምን ነገር መጣህ? አለው።

በዚያን ጊዜ ቀረቡ
እጃቸውንም
በኢየሱስ ላይ
ጭነው ያዙት። 51
እነሆም፥ ከኢየሱስ
ጋር ከነበሩት አንዱ
እጁን ዘርግቶ
ሰይፉን መዘዘና
የሊቀ ካህናቱን ባሪያ
መትቶ ጆሮውን
ቈረጠው።

52 በዚያን ጊዜ
ኢየሱስ እንዲህ
አለው፦ ሰይፍ
የሚያነሡ ሁሉ
በሰይፍ ይጠፋሉና
ሰይፍህን ወደ
ስፍራው መልስ።
53 ወይስ አባቴን
እንድለምን እርሱም
አሁን ከአሥራ
ሁለት ጭፍሮች
የሚበዙ መላእክት
እንዲሰድልኝ
የማይቻል
ይመስልሃልን? 54
እንዲህ ከሆነስ፦
እንደዚህ ሊሆን
ይገባል የሚሉ
መጻሕፍት እንዴት
ይፈጸማሉ?

(ማርቆስ 14፥43-52 የቀጠለ)

46 እነርሱም እጃቸውን በእርሱ ላይ ጭነው ያዙት።

47 በአጠገብ ከቆሙት ግን አንዱ ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መታ ጆሮውንም ቈረጠ።

(ሉቃስ 22፥47-53 የቀጠለ)

49 በዙሪያውም የነበሩት የሚሆነውን ባዩ ጊዜ፦ ጌታ ሆይ፥ በሰይፍ እንምታቸውን? አሉት።

50 ከእነርሱም አንዱ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠው።

51 ኢየሱስ ግን መልሶ፦ ይህንስ ፍቀዱ አለ፤ ጆሮውንም ዳስሶ ፈወሰው።

(ዮሐንስ 18፥2-12 የቀጠለ)

10 ስምዖን ጴጥሮስም ሰይፍ ስለ ነበረው መዘዘው፥ የሊቀ ካህናቱንም ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠ፤ የባርያውም ስም ማልኮስ ነበረ።

11 ኢየሱስም ጴጥሮስን፦ ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን? አለው።

12 እንግዲህ የሻለቃው ጭፍሮቹ የአይሁድም ሎሌዎች ኢየሱስን ይዘው አሰሩት፥

(ማቴዎስ 26፡47-56 የቀጠለ)

55 በዚያን ሰዓት ኢየሱስ ለሕዝቡ፡- ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ ወጣችሁን? በመቅደስ ዕለት ዕለት እያስተማርሁ ከእናንተ ጋር ስቀመጥ ሳለሁ አልያዛችሁኝም። 56 ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነ የነቢያት መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ነው አለ። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ።

(ማርቆስ 14፡43-52 የቀጠለ)

48 ኢየሱስም መልሶ፡- ወንበዴ እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁን? 49 በመቅደስ ዕለት ዕለት እያስተማርሁ ከእናንተ ጋር ስኖር አልያዛችሁኝም፤ ነገር ግን መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ይህ ሆነ አላቸው። 50 ሁሉም ትተውት ሸሹ።

51 ዕርቃኑን በነጠላ የሸፈነ አንድ ጎበዝ ይከተለው ነበር፥ 52 ጎበዛዝቱም ያዙት፤ እርሱ ግን ነጠላውን ትቶ ዕራቁቱን ሸሸ።

(ሉቃስ 22፡47-53 የቀጠለ)

52 ኢየሱስም ወደ እርሱ ለመጡበት ለካህናት አለቆችና ለመቅደስ አዛዦች ለሽማግሌዎችም፡- ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ወጣችሁን? 53 በመቅደስ ዕለት ዕለት ከእናንተ ጋር ስሆን እጆቻችሁን አልዘረጋችሁብኝም፤ ይህ ግን ጊዜያችሁና የጨለማው ሥልጣን ነው አላቸው።

## > ፍርድ <

## ♦ ክፍል 154. በአይሁድ ዘንድ የመጀመሪያው ምዕራፍ፤ ኢየሱስ ሐና ፊት መቅረቡ

- ኢየሩሳሌም፥ በሐና ግቢ -

ዮሐንስ 18፡13-14፥ 19-23

13 አስቀድመውም ወደ ሐና ወሰዱት፤ በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ለነበረው ለቀያፋ አማቱ ነበርና። 14 ቀያፋም፡- አንድ ሰው ስለ ሕዝብ ይሞት ዘንድ ይሻላል ብሎ ለአይሁድ የመከራቸው ነበረ።

19 ሊቀ ካህናቱም ኢየሱስን ስለ ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው።

20 ኢየሱስም መልሶ፡- እኔ በግልጥ ለዓለም ተናገርሁ፤ አይሁድ ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኵራብና በመቅደስ እኔ ሁልጊዜ አስተማርሁ፥ በስውርም ምንም አልተናገርሁም። 21 ስለምን ትጠይቀኛለህ? ለእነርሱ የተናገርሁትን የሰሙትን ጠይቅ፤ እነሆ፥ እነዚህ እኔ የነገርሁትን ያውቃሉ አለው።

22 ይህንም ሲል በዚያ ቆሞ የነበረው ከሎሌዎች አንዱ፡- ለሊቀ ካህናቱ እንዲህ ትመልሳለህን? ብሎ ኢየሱስን በጥፊ መታው።

23 ኢየሱስም መልሶ፡- ክፉ ተናግሬ እንደ ሆንሁ ስለ ክፉ መስክር፤ መልካም ተናግሬ እንደ ሆንሁ ግን ስለ ምን ትመታኛለህ? አለው።

## ♦ ክፍል 155. ሁለተኛው ምዕራፍ በአይሁድ ዘንድ፥ ኢየሱስ ቀያፋ እና ሸንጎ ፊት መቅረቡ

- ኢየሩሳሌም፥ በቀያፋ ቤት -

| ማቴዎስ 26፡57፥ 59-68 | ማርቆስ 14፡53፤ 55-65 | ሉቃስ 22፡54ሀ፥ 63-65 | ዮሐንስ 18፡24 |
|---|---|---|---|
| 57 ኢየሱስን የያዙትም ጻፎችና ሽማግሎች ወደ ተከማቹበት ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት። | 53 ኢየሱስንም ወደ ሊቀ ካህናቱ[37] ወሰዱት፥ የካህናት አለቆችም ሁሉ ሽማግሌዎችም ጻፎችም ተሰበሰቡ። | 54ሀ ይዘውም ወሰዱት ወደ ሊቀ ካህናት ቤትም አገቡት፤ | 24 ስለዚህ ሐና እንደ ታሰረ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ሰደደው። |
| 59 የካህናት አለቆችና ሽማግሎች ሸንጎውም ሁሉ እንዲገድሉት በኢየሱስ ላይ የሐሰት ምስክር ይፈልጉ ነበር፥ አላገኙም፤ 60 ብዙም የሐሰት ምስክሮች ምንም ቢቀርቡ አላገኙም። | 55 የካህናት አለቆችም ሸንጎውም ሁሉ እንዲገድሉት በኢየሱስ ላይ ምስክር ይፈልጉ ነበር፥ አላገኙምም፤ 56 ብዙዎች በሐሰት ይመሰክሩበት ነበርና፥ ምስክርነታቸው ግን አልተስማማም። | | |
| 61 በኋላም ሁለት ቀርበው:- ይህ ሰው:- የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን | 57-58 ሰዎችም ተነሥተው:- እኔ ይህን በእጅ የተሠራውን ቤተ መቅደስ አፈርሰዋለሁ በሦስት ቀንም ሌላውን በእጅ | | |

37 [ማር. 14፡53] ማርቆስ በኢየሩሳሌሙ ሸንጎ የተሰበሰቡትን ሦስት ቡድኖች ይገልጣል። ይህ ሸንጎ ከፍተኛው የአይሁድ ችሎት ነው:-

1. "ሊቀካህናቱ" ይህ የቀድሞ ሊቀካህናትን (ምናልባትም ሐናን ይጨምር ይሆናል)፥ የቤተ መቅደስ ጠባቂዎችን አለቃ፥ አስተዳዳሪውንና ሦስቱን ገንዘብ ያዦች ያካትታል፤ 2. "ሽማግሌዎች" ኢየሩሳሌም ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ባለጸጎችና እውቅ ሰዎች፤ 3."ጸሐፎች" ወይም "የሕግ መምህራን" በአብዛኛው ከመካከለኛው የኅብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ።

የመጀመሪያዎቹ ሁለት ቡድኖች በአብዛኛው ሰዱቃውያንን ሲያካትቱ፥ ሦስተኛው ቡድን ደግሞ ፈሪሳውያንን ያጠቃልል ነበር። ሸንጎው በተለመደው ስፍራ ሳይሆን ቀያፋ ቤት ውስጥ በመሰብሰብ፥ በኢየሱስ ላይ ለመፍረድ ቀደም ሲል የነበረውን እቅድ ለመፈጸም መቻኮሉን አረጋገጠ (ማር. 14፡55፤ ማቴ. 26፡4፤ ማር. 14፡1፥ ክፍል 140)። የኢየሱስን መያዝና ፍርድ አስመልክቶ ለበለጠ ውይይት መጣጥፍ 12ን ይመልከቱ።

(ማቴዎስ 26፡57፥ 59-68 የቀጠለ)

ልሠራው እችላለሁ ብሎአል አሉ።

62 ሊቀ ካህናቱም ተነሥቶ፦ እነዚህ ለሚመሰክሩብህ አንድ ስንኳ አትመልስምን? አለው። 63 ኢየሱስ ግን ዝም አለ።

ሊቀ ካህናቱም፦ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሆንህ እንደ ሆነ እንድትነግረን በሕያው እግዚአብሔር አምልሃለሁ አለው።

64 ኢየሱስም፦ አንተ አልህ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለው። [መዝሙር 110፡1፤ ዳንኤል 7፡13]

65 በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀዶ፦ ተሳድቦአል እንግዲህ ወዲህ ምስክሮች ስለ ምን ያስፈልገናል? እነሆ፥ ስድቡን አሁን ሰምታችኋል፤ ምን ይመስላችኋል? አለ።

66 እነርሱም፦ ሞት ይገባዋል ብለው መለሱ።

67 በዚያን ጊዜ በፊቱ ተፉበት፤ ጐሰሙትም፥ ሌሎችም በጥፊ መትተው፦ ክርስቶስ ሆይ፥ በጥፊ የመታህ ማን ነው? 68 ትንቢት ተናገርልን አሉ።

(ማርቆስ 14፡53፥ 55-65 የቀጠለ)

ያልተሠራውን እሠራለሁ ሲል ሰማነው ብለው በሐሰት መሰከሩበት። 59 ምስክርነታቸውም እንዲሁ እንኳ አልተሰማማም።

60 ሊቀ ካህናቱም በመካከላቸው ተነሥቶ፦ አንዳች አትመልስምን? እነዚህስ በአንተ ላይ የሚመሰክሩብህ ምንድር ነው? ብሎ ኢየሱስን ጠየቀው። 61 እርሱ ግን ዝም አለ አንዳችም አልመለሰም።

ደግሞ ሊቀ ካህናቱ ጠየቀውና፦ የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን? አለው።

62 ኢየሱስም፦ እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ። [መዝሙር 110፡1፤ ዳንኤል 7፡13]

63 ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደና፦ ከእንግዲህ ወዲህ ምስክሮችን ምን ያስፈልገናል? 64 ስድቡን ሰማችሁ፤ ምን ይመስላችኋል? አለ።

እነርሱም ሁሉ፦ ሞት ይገባዋል ብለው ፈረዱበት። 65 አንዳንዶችም ይተፉበት ፊቱንም ሸፍነው ይጐስሙትና፦ ትንቢት ተናገር ይሉት ጀመር፤ ሎሌዎችም በጥፊ እየመቱ ወሰዱት።

(ሉቃስ 22፡54ሀ፥ 63-65 የቀጠለ)

63 ኢየሱስንም የያዙት ሰዎች ይዘብቱበትና ይደበድቡት ነበር፤ 64 ሸፍነውም ፊቱን ይመቱት ነበርና፦ በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገር እያሉ ይጠይቁት ነበር። 65 ሌላም ብዙ ነገር እየተሳደቡ በእርሱ ላይ ይናገሩ ነበር።

## ♦ ክፍል 156. የጴጥሮስ ክህደቶች

[ክፍል 147ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም፥ በቀያፋ ግቢ -

| ማቴዎስ 26፡58፥ 69-75 | ማርቆስ 14፡54፥ 66-72 | ሉቃስ 22፡54ለ-62 | ዮሐንስ 18፡15-18፥ 25-27 |
|---|---|---|---|
| 58 ጴጥሮስ ግን እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ድረስ ሩቅ ሆኖ ተከተለው፥ የነገሩንም ፍጻሜ ያይ ዘንድ ወደ ውስጥ ገብቶ | 54 ጴጥሮስም እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ውስጥ በሩቁ ተከተለው፥ | 54ለ ጴጥሮስም ርቆ ይከተለው ነበር። | 15 ስምዖን ጴጥሮስም ሌላውም ደቀ መዝሙር ኢየሱስን ተከተሉ። ያም ደቀ መዝሙር በሊቀ ካህናቱ[38] ዘንድ የታወቀ ነበረ፥ ወደ ሊቀ ካህናቱም ግቢ ከኢየሱስ ጋር ገባ፤ 16 ጴጥሮስ ግን በውጭ በበሩ ቆሞ ነበር። እንግዲህ በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀው ሌላው ደቀ መዝሙር ወጣ ለበረኛይቱም ነግሮ ጴጥሮስን አስገባው። 17 በረኛ የነበረችይቱም ገረድ ጴጥሮስን፦ አንተ ደግሞ ከዚህ ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን? አለችው። እርሱ፦ አይደለሁም አለ። |
| ከሎሌዎቹ ጋር ተቀመጠ። | ከሎሌዎችም ጋር ተቀምጦ እሳት ይሞቅ ነበር። | 55 በግቢ መካከልም እሳት አንድደው | 18 ብርድ ነበረና ባሮችና ሎሌዎች የፍም እሳት አንድደው ቆመው ይሞቁም ነበር፤ ጴጥሮስም ደግሞ |

38 [ዮሐ. 18፡15] እዚህና ቁጥር 16፥ 19፥ እንዲሁም 22 ውስጥ ዮሐንስ ሐናን "ሊቀ ካህናት" ይለዋል። 18፡13 (ክፍል 154) ላይ ግን ሊቀካህናቱ ቀያፋ ነው ይላል። የሚስቱ አባት ሐና በ15 ዓ.ም. ከተሻረ በኋላ፥ እርሱን ተክቶ በ18 ዓ.ም. በግልፅ ሊቀካህን የሆነው ቀያፋ ነው። ሐና ምንም እንኳ በሥልጣን ላይ ባይሆን ታላቅ ተጽእኖ ስለነበረው፥ ለሌሎቹ ቀደምት ሊቀካህናት የሚገባቸው ክብር ለርሱም ይሰጠው ነበር።

**(ማቴዎስ 26፥58፥ 69-75 የቀጠለ)**

69 ጴጥሮስም ከቤት ውጭ በአጥሩ ግቢ ተቀምጦ ነበር፤ አንዲት ገረድም ወደ እርሱ ቀርባ፦

አንተ ደግሞ ከገሊላው ከኢየሱስ ጋር ነበርህ አለችው።

70 እርሱ ግን፦ የምትዪውን አላውቀውም ብሎ በሁሉ ፊት ካደ።

71 ወደ በሩም ሲወጣ ሌላይቱ አየችውና በዚያ ላሉት፦ ይህ ደግሞ ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ጋር ነበረ አለች።

72 ዳግመኛም ሲምል፦ ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ካደ።

73 ጥቂትም ቈይተው በዚያ ቆመው የነበሩ ቀርበው ጴጥሮስን፦ አነጋገርህ ይገልጥሃልና በእውነት አንተ ደግሞ ከእነርሱ

**(ማርቆስ 14፥54፥ 66-72 የቀጠለ)**

66 ጴጥሮስም በግቢ ውስጥ ወደ ታች ሳለ ከሊቀ ካህናቱ ገረዶች አንዲቱ መጣች፥ 67 ጴጥሮስም እሳት ሲሞቅ አይታ ተመለከተችውና፦

አንተ ደግሞ ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ጋር ነበርህ አለችው።

68 እርሱ ግን፦ የምትዪውን አላውቅም አላስተውልምም ብሎ ካደ። ወደ ውጭም ወደ ደጅ ወጣ፤ ዶሮም ጮኸ።

69 ገረዲቱም አይታው በዚያ ለቆሙት፦ ይህም ከእነርሱ ወገን ነው ስትል ሁለተኛ ትነግራቸው ጀመር። 70 እርሱም ደግሞ ካደ።

ጥቂት ቈይተውም በዚያ የቆሙት ዳግመኛ ጴጥሮስን፦ የገሊላ ሰው ነህና ከእነርሱ ወገን በእውነት ነህ አሉት።

71 እርሱ ግን፦ ይህን የምትሉትን ሰው አላውቀውም ብሎ ይረገምና

**(ሉቃስ 22፥54ለ-62 የቀጠለ)**

በአንድነት ተቀምጠው ሳሉ ጴጥሮስ በመካከላቸው ተቀመጠ።

56 በብርሃኑም በኩል ተቀምጦ ሳለ አንዲት ገረድ አየችውና ትኵር ብላ፦ ይህ ደግሞ ከእርሱ ጋር ነበረ አለች።

57 እርሱ ግን፦ አንቺ ሴት፥ አላውቀውም ብሎ ካደ።

58 ከጥቂት ጊዜም በኋላ ሌላው አይቶት፦ አንተ ደግሞ ከእነርሱ ወገን ነህ አለው። ጴጥሮስ ግን፦ አንተ ሰው፥ እኔ አይደለሁም አለ።

59 አንድ ሰዓትም የሚያህል ቆይቶ ሌላው አስረግጦ፦ እርሱ የገሊላ ሰው ነውና በእውነት ይህ ደግሞ ከእርሱ ጋር ነበረ አለ።

60 ጴጥሮስ ግን፦ አንተ ሰው፥

**(ዮሐንስ 18፥15-18፥ 25-27 የቀጠለ)**

ከእነርሱ ጋር ቆሞ ይሞቅ ነበር።

25 ስምዖን ጴጥሮስም ቆሞ እሳት ይሞቅ ነበር። እንግዲህ፦ አንተ ደግሞ ከደቀመዛሙርቱ አይደለህምን? አሉት።

እርሱም፦ አይደለሁም ብሎ ካደ።

26 ጴጥሮስ ጆሮውን የቈረጠው ዘመድ የሆነ ከሊቀ ካህናቱ ባሮች አንዱ፦ በአትክልቱ ከእርሱ ጋር እኔ አይቼህ አልነበርሁምን? አለው።

27 ጴጥሮስም እንደ ገና ካደ፥ ወዲያውም ዶሮ ጮኸ።

(ማቴዎስ 26፡58፥ 69-75 የቀጠለ)

ወገን ነህ አሉት።

74 በዚያን ጊዜ፡- ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ሊራገምና ሊምል ጀመረ።

ወዲያውም ዶሮ ጮኸ። 75 ጴጥሮስም፡- ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው የኢየሱስ ቃል ትዝ አለው፤ ወደ ውጭም ወጥቶ መራራ ልቅሶ አለቀሰ።

(ማርቆስ 14፡54፥ 66-72 የቀጠለ)

ይምል ጀመር። ወዲያውም ዶሮ ሁለተኛ ጮኸ።

72 ጴጥሮስንም ኢየሱስ፡- ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው ቃል ትዝ አለው፤ ነገሩንም አስቦ አለቀሰ።

(ሉቃስ 22፡54ለ-62 የቀጠለ)

የምትለውን አላውቅም አለ። ያን ጊዜም ገና ሲናገር ዶሮ ጮኸ። 61 ጌታም ዘወር ብሎ ጴጥሮስን ተመለከተው፤ ጴጥሮስም፡- ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ እንዳለው የጌታ ቃል ትዝ አለው። 62 ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ።

## ♦ ክፍል 157. ሦስተኛው ምዕራፍ በአይሁድ ዘንድ፤ ኢየሱስ በሽማግሌዎች (በሸንጎው) ፊት

- ኢየሩሳሌም፥ የሸንጎው ቦታ -

ማቴዎስ 27፡1

1 ሲነጋም የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሎች ሁሉ ሊገድሉት በኢየሱስ ላይ ተማከሩ፤

ማርቆስ 15፡1ሀ

1ሀ ወዲያውም ማለዳ የካህናት አለቆች ከሽማግሌዎችና ከጻፎች ከሸንጎውም ሁሉ ጋር ከተማከሩ በኋላ፥

ሉቃስ 22፡66-71

66 በነጋም ጊዜ[39] የሕዝቡ ሽማግሌዎችና የካህናት አለቆች ጻፎችም ተሰብስበው ወደ ሸንጎአቸው ወሰዱትና 67 ክርስቶስ አንተ ነህን? ንገረን አሉት።

እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፡- ብነግራችሁ አታምኑም፤

68 ብጠይቅም አትመልሱልኝም አትፈቱኝምም። 69 ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ኃይል ቀኝ ይቀመጣል። [መዝሙር 110፡1]

70 ሁላቸውም፡- እንግዲያስ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህን? አሉት።

እርሱም፡- እኔ እንደ ሆንሁ እናንተ ትላላችሁ አላቸው።

71 እነርሱም፡- ራሳችን ከአፉ ሰምተናልና ከእንግዲህ ወዲህ ምን ምስክር ያስፈልገናል? አሉ።

---

39 [ሉቃስ 22፡66] የተለመደው የክርስቲያኖች ገለጣ በምሽት የተደረገ የትኛውም የአይሁድ ሸንጎ ውሳኔ ሕጋዊ አይደለም የሚል ነው። በመሆኑም ከጥቂት ሰዓታት በፊት የሰጠውን ሕገወጥ ፍርድ (ማቴ. 26፡66፤ ማር. 14፡64፥ ክፍል 155) ሕጋዊ ለማድረግ ሸንጎው እንደገና መሰብሰብ ነበረበት። ይሁን እንጂ የሕጋዊነ ጥያቄ አከራካሪና መልስ የማይገኝለት ነጥብ በመሆኑ መጣጥፍ 12 ውስጥ ተነሥቷል።

## ♦ ክፍል 158. የአስቆሮቱ ይሁዳ ጸጸትና ታንቆ መሞት

- በመቅደሱ ውስጥና የሸክላ ሠሪው መሬት -

| ማቴዎስ 27፡3-10 | የሐዋርያት ሥራ 1:18-19 |
|---|---|
| 3 በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደ ተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ፥ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሎች መልሶ፡- 4 ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ።<br>እነርሱ ግን፡- እኛስ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ አሉ።<br>5 ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ።[40] | |
| 6 የካህናት አለቆችም ብሩን አንሥተው፡- የደም ዋጋ ነውና ወደ መባ ልንጨምረው አልተፈቀደም አሉ። 7 ተማክረውም የሸክላ ሠሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት። 8 ስለዚህ ያ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ የደም መሬት ተባለ። 9 በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለው፡- ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን፥ የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ፥ 10 ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት። የሚል ተፈጸመ። [ዘካርያስ 11፡12-13፤ ኤርምያስ 18፡2፥ 32፡6-9] | 18 ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ፤[40]<br>19 በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ ሁሉ ታወቀ፤ ስለዚህም ያ መሬት በቋንቋቸው አኬልዳማ ተብሎ ተጠራ፥ እርሱም የደም መሬት ማለት ነው። |

## ♦ ክፍል 159. የመጀመሪያው ምዕራፍ በሮማውያን ፊት፥ ጲላጦስ ፊት

- ኢየሩሳሌም፥ በገዢው ግቢ (በሮም ገዥው ቤተ መንግሥት) -

| ማቴዎስ 27፡2፥ 11-14 | ማርቆስ 15፡1ለ-5 | ሉቃስ 23፡1-5 | ዮሐንስ 18፡28-38 |
|---|---|---|---|
| 2 አስረውም ወሰዱት፥ ለገዢው ለጴንጤናዊው ጲላጦስም አሳልፈው ሰጡት። | 1ለ ኢየሱስን አሳስረው ወሰዱትና ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት። | 1 ሁሉም በሞላው ተነሥተው ወደ ጲላጦስ ወሰዱትና፡- | 28 ኢየሱስንም ከቀያፋ ወደ ገዡ ግቢ ወሰዱት፤ ማለዳም ነበረ፤ እነርሱም የፋሲካ በግ ይበሉ ዘንድ እንጂ እንዳይረክሱ ወደ ገዡ ግቢ |
| | | 2 ይህ ሕዝባችንን ሲያጣምም | አልገቡም። 29 ስለዚህ ጲላጦስ ወደ |

| (ማቴዎስ 27፡2፥ 11-14 የቀጠለ) | (ማርቆስ 15፡1ለ-5 የቀጠለ) | (ሉቃስ 23፡1-5 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 18፡28-38 የቀጠለ) |
| --- | --- | --- | --- |
| | | ለቄሣርም ግብር እንዳይሰጥ ሲከለክል ደግሞም፡- እኔ ክርስቶስ ንጉሥ ነኝ ሲል አገኘነው ብለው ይከሱት ጀመር። | ውጭ ወደ እነርሱ ወጥቶ፡- ይህን ሰው ስለ ምን ትከሱታላችሁ አላቸው። 30 እነርሱም መልሰው፡- ይህስ ክፉ አድራጊ ባይሆን ወደ አንተ አሳልፈን ባልሰጠነውም ነበር አሉት። 31 ጲላጦስም፡- እናንተ ወስዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት አላቸው። አይሁድም፡- ለእኛስ ማንንም ልንገድል አልተፈቀደልንም አሉት፤ 32 ኢየሱስ በምን ዓይነት ሞት ሊሞት እንዳለው ሲያመለክት የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው። 33 ጲላጦስም እንደ ገና ወደ ገዡ ግቢ ገባና ኢየሱስን ጠርቶ፡- |
| 11 ኢየሱስም በገዢው ፊት ቆመ፤ ገዢውም፡- የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን? ብሎ ጠየቀው፤ | 2 ጲላጦስም፡- አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየቀው። | 3 ጲላጦስም፡- አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየቀው። | የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን? አለው። 34 ኢየሱስም መልሶ፡- አንተ ይህን የምትለው ከራስህ ነውን ወይስ ሌሎች ስለ እኔ ነገሩህን? አለው። |
| ኢየሱስም፡- አንተ አልህ አለው። | እርሱም፡- አንተ አልህ ብሎ መለሰለት። | እርሱም መልሶ፡- አንተ አልህ አለው። | |

40 [ማቴ. 27፡5፤ ሐዋ. 1፡18] የይሁዳን ሞት አስመልክቶ እነዚህን ሁለት ገለጣዎች ለማገናኘት ሲባል የተለመደው ጥያቄ የሚቀርብበት ምክንያት የለም። ይኸውም ይሁዳ አንድ ገደል ጫፍ ላይ ባለው ዛፍ ራሱን ሲሰቅል፥ የዛፉ ቅርንጫፍ ተገንጥሎ ወይም ገመዱ ተበጥሶ ከታች ከነበረው ሸለቆ ውስጥ ወድቋል የሚል ነው።

| (ማቴዎስ 27፡2፥ 11-14 የቀጠለ) | (ማርቆስ 15፡1ለ-5 የቀጠለ) | (ሉቃስ 23፡1-5 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 18፡28-38 የቀጠለ) |
|---|---|---|---|
| | | | 35 ጲላጦስ መልሶ:- እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ወገኖችህና የካህናት አለቆች ለእኔ አሳልፈው ሰጡህ፤ ምን አድርገሃል? አለው። 36 ኢየሱስም መልሶ:- መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ 41 መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው። 37 ጲላጦስም:- እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ:- እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው። |
| | | 4 ጲላጦስም ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ:- በዚህ ሰው አንድ በደል ስንኳ አላገኘሁበትም አለ። | 38 ጲላጦስ:- እውነት ምንድር ነው? አለው። ይህንም ብሎ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጥቶ:- እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም። |
| 12 የካህናት አለቆችም ሽማግሎችም ሲከሱት ምንም አልመለሰም። | 3 የካህናት አለቆችም ብዙ ያሳጡት ነበር፤ እርሱ ግን ምንም አልመለሰም። 4 ጲላጦስም ደግሞ:- | | |

| (ማቴዎስ 27፡2፥ 11-14 የቀጠለ) | (ማርቆስ 15፡1ለ-5 የቀጠለ) | (ሉቃስ 23፡1-5 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| 13 በዚያን ጊዜ ጲላጦስ፡- ስንት ያህል እንዲመሰክሩብህ አትሰማምን? አለው። 14 ገዢውም እጅግ እስኪደነቅ ድረስ አንዲት ቃል ስንኳ አልመለሰለትም። | አንዳች አትመልስምን? እነሆ፥ በስንት ነገር ያሳጡሃል ብሎ ጠየቀው። 5 ኢየሱስም ከዚያ በኋላ ጲላጦስ እስኪደነቅ ድረስ ምንም አልመለሰም። | 5 እነርሱ ግን አጽንተው፡- ከገሊላ ጀምሮ እስከዚህ ድረስ በይሁዳ ሁሉ እያስተማረ ሕዝቡን ያውካል አሉ። |

## ♦ ክፍል 160. ሁለተኛው ምዕራፍ በሮማውያን ፊት፥ በሄሮድስ ፊት

- ኢየሩሳሌም፥ በሄሮድስ አንቲጳስ ፊት -

ሉቃስ 23፡6-12

6 ጲላጦስ ግን፡- ገሊላ ሲሉ በሰማ ጊዜ፡- የገሊላ ሰው ነውን? ብሎ ጠየቀ፤ 7 ከሄሮድስም ግዛት[42] እንደ ሆነ ባወቀ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ሰደደው፤ እርሱ ደግሞ በዚያ ጊዜ በኢየሩሳሌም ነበረና።

8 ሄሮድስም ኢየሱስን ባየው ጊዜ እጅግ ደስ አለው፤ ስለ እርሱ ስለ ሰማ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሊያየው ይመኝ ነበርና፥ ምልክትም ሲያደርግ ሊያይ ተስፋ ያደርግ ነበር። 9 በብዙ ቃልም ጠየቀው፤ እርሱ ግን አንድ ስንኳ አልመለሰለትም። 10 የካህናት አለቆችና ጻፎችም አጽንተው ሲከሱት ቆመው ነበር። 11 ሄሮድስም ከሠራዊቱ ጋር ናቀው ዘበተበትም፥ የጌጥ ልብስም አልብሶ ወደ ጲላጦስ መልሶ ሰደደው። 12 ሄሮድስና ጲላጦስም በዚያን ቀን እርስ በርሳቸው ወዳጆች ሆኑ፥ ቀድሞ በመካከላቸው ጥል ነበረና።

---

[41] [ዮሐ. 18፡36] ኢየሱስ መንግሥቱ ምድራዊ መሠረት እንደሌለው ገለጠ። መንግሥቱ ምድራዊ ቢሆን ኖሮ፥ ባስፈለገው ጊዜ የሚጠቀምበት ሠራዊት ሊያደራጅ ይችል ነበር። ይሁን እንጂ፥ የርሱ መንግሥት በእግዚአብሔር ቃል እንደተገለጠው፥ አይሁድ የሚጠብቁትና መሲሑ የሚመሠርተው ምድራዊነትም ያለው (ዳን. 7፡13-14፥ 22-23፥ 27) መሆኑንም አልካደም። የርሱ መንግሥት በሮማውያን ባለሥልጣናት ላይ የሚያምጽ ስላልሆነ፥ ጲላጦስ ኢየሱስን ሊፈታው ፈቃደኛ ነበር (ሉቃስ 23፡4፤ ዮሐ. 18፡38)።

[42] [ሉቃስ 23፡7] ይህ ሰው በመጥምቁ ዮሐንስ ትምህርት ንስሐ በመግባት ፈንታ፥ አንገቱን ያስቀወ የገሊላና የፓርያ ገዢ ሄሮድስ አንቲጳስ (ክፍል 71ለ) ነው። አብዛኛው የኢየሱስ አገልግሎት ገሊላ ውስጥ ስለነበር፥ ጲላጦስ በአንድ ንጹህ ሰው ላይ ከመፍረድ የሚያድነውን መንገድ እንዳገኘ አሰበ። ሆኖም ሄሮድስ ኢየሱስን ጥፋተኛ ወይም ንጹሕ ሰው ነው በማለት ፍርድ አልሰጠም። ሉቃስ ከሄሮድስ ቤተሰብ ጋር ግንኙነት ስለነበረው (ሉቃስ 8፡3፥ ክፍል 60)፥ በሌሎች ወንጌሎች ውስጥ የሌለውን የፍርድ ሂደት ለመግለጥ ችሏል፤ ልክ ዮሐንስ ሐና ቤት ውስጥ ስለተደረገው ነገር ለመግለጥ እንደቻለ (ክፍል 154)።

## ♦ ክፍል 161. ሦስተኛው ምዕራፍ በሮማውያን ፊት፥ ጲላጦስ ፊት

- ኢየሩሳሌም፥ በገዢው ግቢ. -

| ማቴዎስ 27፡15-26 | ማርቆስ 15፡6-15 | ሉቃስ 23፡13-25 | ዮሐንስ 18፡39-19፡16 |
|---|---|---|---|
| 15 በዚያም በዓል ሕዝቡ የወደዱትን አንድ እስረኛ ሊፈታላቸው ለገዢው ልማድ ነበረው። 16 በዚያን ጊዜም በርባን[43] የሚባል በጣም የታወቀ እስረኛ ነበራቸው። | 6 በዚያም በዓል የለመኑትን አንድ እስረኛ ይፈታላቸው ነበር። 7 በዓመፅም ነፍስ ከገደሉት ከዓመፀኞች ጋር የታሰረ በርባን[43] የተባለ ነበረ። 8 ሕዝቡም ወጥተው እንደ ልማዱ ያደርግላቸው ዘንድ እየጮኹ ይለምኑት ጀመር። | | |
| | | 13 ጲላጦስም፥ የካህናትን አለቆችና መኳንንትን ሕዝቡንም በአንድነት ጠርቶ እንዲህ አላቸው፦ 14 ሕዝቡን ያጣምማል ብላችሁ ይህን ሰው ወደ እኔ አመጣችሁት፤ እነሆም፥ በፊታችሁ መርምሬ ከምትከሱበት ነገር አንድ በደል ስንኳ በዚህ ሰው አላገኘሁበትም። 15 ሄሮድስም ደግሞ ምንም አላገኘም፤ ወደ እኛ | 39 ነገር ግን በፋሲካ አንድ |

[43] [ማቴ. 27፡16፤ ማር. 15፡7፤ ሉቃስ 23፡19፤ ዮሐ. 18፡40] በርባን የሮማውያንን አገዛዝ ለማስወገድ ይሁዳ ውስጥ የሚታገለው ተቃዋሚ ንቅናቄ አባል ነበር። ምንም እንኳን ሌባና ነፍስ ገዳይ ቢሆን፥ የሮማውያንን አገዛዝ በማይወዱ አይሁዳውያን ዘንድ እንደ ጀግና ነበር የሚቆጠረው። በመሆኑም የተሰበሰበው ሕዝብ በርባን ይፈታለት ዘንድ እንዲጠይቅ ለማድረግ ሊቀካህናቱ ብዙም አልተቸገሩም (ማቴ. 27፡20፤ ማር. 15፡11)። መሪዎቹ ኢየሱስን የከሰሱበትን ዓይነት ወንጀል የፈጸመው ይህ ሰው እንዲፈታላቸው መጠየቃቸው ምጸት ነው (ሉቃስ 23፡2፥ ክፍል 159፤ ዮሐ. 19፡12)።

(ማቴዎስ 27፡ 15-26 የቀጠለ)

17 እንግዲህ እነርሱ ተሰብስበው ሳሉ ጲላጦስ፦ በርባንን ወይስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤ 18 በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።

19 እርሱም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ፦ ስለ እርሱ ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚያ ጻድቅ ሰው ምንም አታድርግ ብላ ላከችበት።

20 የካህናት አለቆችና ሽማግሎች ግን በርባንን እንዲለምኑ ኢየሱስን ግን እንዲያጠፉ ሕዝቡን አባበሉ።

21 ገዢውም መልሶ፦ ከሁለቱ ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤

(ማርቆስ 15፡ 6-15 የቀጠለ)

9 ጲላጦስም፦ የአይሁድን ንጉሥ እፈታላችሁ ዘንድ ትወዳላችሁን? ብሎ መለሰላቸው፤ 10 የካህናት አለቆች በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።

11 የካህናት አለቆች ግን በርባንን በእርሱ ፈንታ ይፈታላቸው ዘንድ ሕዝቡን አወኩአቸው።

(ሉቃስ 23፡ 13-25 የቀጠለ)

መልሶታልና፤ እነሆም፥ ለሞት የሚያደርሰው ምንም አላደረገም፤ 16-17 እንግዲያስ ቀጥቼ እፈታዋለሁ። በበዓሉ አንድ ይፈታላቸው ዘንድ ግድ ነበረና።

18 ሁላቸውም በአንድነት፦ ይህን አስወግድ፥ በርባንንም ፍታልን እያሉ ጮኹ፤ 19 እርሱም[43] ሁከትን

(ዮሐንስ 18፡ 39-19፡ 16 የቀጠለ)

ልፈታላችሁ ልማድ አላችሁ፤ እንግዲህ የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን? አላቸው።

40 ሁሉም ደግመው፦ በርባንን[43] እንጂ ይህን አይደለም እያሉ ጮኹ። በርባን ግን ወንበዴ ነበረ።

(ማቴዎስ 27፡ 15-26 የቀጠለ)

እነርሱም :- በርባንን አሉ።

22 ጲላጦስ :- ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው? አላቸው፤

ሁሉም:- ይሰቀል አሉ።

23 ገዢውም:- ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድር ነው? አለ፤

(ማርቆስ 15፡6-15 የቀጠለ)

12 ጲላጦስም ዳግመኛ መልሶ:- እንግዲህ የአይሁድ ንጉሥ የምትሉትን ምን ላደርገው ትወዳላችሁ? አላቸው።

13 እነርሱም ዳግመኛ:- ስቀለው እያሉ ጮኹ።

14 ጲላጦስም:-

(ሉቃስ 23፡ 13-25 የቀጠለ)

በከተማ አንሥቶ ሰውን ስለ ገደለ በወኅኒ ታስሮ ነበር።

20 ጲላጦስም ኢየሱስን ሊፈታ ወድዶ ዳግመኛ
ተናገራቸው፤ 21
ነገር ግን እነርሱ:- ስቀለው ስቀለው እያሉ ይጮኹ ነበር።

22 ሦስተኛም:- ምን ነው? ያደረገውስ ክፋት

(ዮሐንስ 18፡39- 19፡16 የቀጠለ)

19:1 በዚያን ጊዜም
ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ
ገረፈው። 2
ወታደሮችም ከእሾህ
አክሊል ጐንጕነው
በራሱ ላይ አኖሩ ቀይ
ልብስም አለበሱት፤ 3
እየቀረቡም :-
የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን ይሉት ነበር፤

4 በጥፊም ይመቱት
ነበር። ጲላጦስም
ደግሞ ወደ ውጭ
ወጥቶ:- እነሆ፥
አንዲት በደል ስንኳ
እንዳላገኘሁበት
ታውቁ ዘንድ እርሱን
ወደ ውጭ
አወጣላችኋለሁ
አላቸው። 5
ኢየሱስም የእሾህ
አክሊል ደፍቶ ቀይ
ልብስም ለብሶ ወደ
ውጭ ወጣ።

6 ጲላጦስም:- እነሆ ሰውዬው አላቸው። የካህናት አለቆችና ሎሌዎች ባዩትም ጊዜ:- ስቀለው ስቀለው እያሉ ጮኹ።

(የሐንስ 18፡39-19፡16
የቀጠለ)

ጲላጦስም፦ እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትምና እናንተ ወስዳችሁ ስቀሉት
አላቸው።

7 አይሁድም መልሰው፦ እኛ ሕግ አለን፥ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፥ ራሱን
የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአልና አሉት።

8 ስለዚህ ጲላጦስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እግጅ ፈራ፤ 9 ተመልሶም ወደ ገዥ ግቢ
ገባና ኢየሱስን፦ አንተ ከወዴት ነህ? አለው። ኢየሱስ ግን አንድ እንኳ
አልመለሰለትም። 10 ስለዚህ ጲላጦስ፦ አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ
ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው።

11 ኢየሱስም መልሶ፦ ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን
ባልነበረህም፤ ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው አለው።

12 ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ፤ ነገር ግን አይሁድ፦ ይህንስ ብትፈታው
የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሣር ተቃዋሚ ነው
እያሉ ጮኹ።

13 ጲላጦስም ይህን ነገር ሰምቶ ኢየሱስን ወደ ውጭ አወጣው፥ በዕብራይስጥም ገበታ
በተባለው ጸፍጸፍ በሚሉት ስፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ። 14 ለፋሲካም የማዘጋጀት
ቀን ነበረ፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤

አይሁድንም፦ እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው።

(ማቴዎስ 27፡15-26
የቀጠለ)

እነርሱ ግን፦ ይሰቀል እያሉ ጩኸት አበዙ።

24 ጲላጦስም ሁከት እንዲጀመር እንጂ አንዳች እንዳይረባ ባየ ጊዜ፥ ውኃ አንሥቶ፦ እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ።

25 ሕዝቡም ሁሉ መልሰው፦ ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ።

(ማርቆስ 15፡6-15
የቀጠለ)

ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድር ነው? አላቸው።

እነርሱ ግን፦ ስቀለው እያሉ ጩኸት አበዙ።

15 ጲላጦስም የሕዝቡን ፈቃድ

(ሉቃስ 23፡13-25
የቀጠለ)

ምንድር ነው? ለሞት የሚያደርሰው በደል አላገኘሁበትም፤ ስለዚህ ቀጥቼ እፈታዋለሁ አላቸው።

23 እነርሱ ግን እንዲሰቀል በታላቅ ድምፅ አጽንተው ለመኑት። የእነርሱ ጩኸትና የካህናት አለቆችም ቃል በረታ።

24 ጲላጦስም ልመናቸው እንዲሆን ንላቸው ፈረደበት።
25 ያንን

15 እነርሱ ግን፦ አስወግደው፥ አስወግደው፥ ስቀለው እያሉ ጮኹ።

ጲላጦስም፦ ንጉሣችሁን ልስቀለውን? አላቸው።

የካህናት አለቆችም፦ ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት።

| (ማቴዎስ 27፡15-26 የቀጠለ) | (ማርቆስ 15፡6-15 የቀጠለ) | (ሉቃስ 23፡13-25 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 18፡39-19፡16 የቀጠለ) |
|---|---|---|---|
| 26 በዚያን ጊዜ በርባንን ፈታላቸው፥ ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቀል አሳልፎ ሰጠ። | ሊያደርግ ወዶ በርባንን ፈታላቸው፥ ኢየሱስንም ገርፎ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠ። | የለመኑትንም፥ ስለ ሁከት ሰውንም ስለ መግደል በወኅኒ ታስሮ የነበረውን አስፈታላቸው፥ ኢየሱስን ግን ለፈቃዳቸው[44] አሳልፎ ሰጠው። | 16 ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።[44] |

# > ስቅለት <

## ♦ ክፍል 162. የሮማውያን ወታደሮች ፌዝ

- ኢየሩሳሌም፥ በገዢው ግቢ -

### ማቴዎስ 27፡27-30

27 በዚያን ጊዜ የገዢው ወታደሮች
ኢየሱስን ወደ ገዢው ግቢ ውስጥ ወሰዱት
ጭፍራውንም ሁሉ ወደ እርሱ አከማቹ።
28 ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ
አለበሱት፥ 29 ከእሾህም አክሊል
ጎንጉነው በራሱ ላይ፥ በቀኝ እጁም መቃ
አኖሩ፥ በፊቱም ተንበርክከው፦
የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥[45] ሰላም ለአንተ
ይሁን እያሉ ዘበቱበት፤ 30 ተፉበትም
መቃውንም ይዘው ራሱን መቱት።

### ማርቆስ 15፡16-19

16 ወታደሮችም ፕራይቶሪዮን ወደሚባል
ግቢ ውስጥ ወሰዱት፥ ጭፍራውንም ሁሉ
በአንድነት ጠሩ። 17 ቀይ ልብስም
አለበሱት፥ የእሾህ አክሊልም ጎንጉነው
ደፋበት፤ 18 የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥[45]
ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ እጅ ይነሱት
ጀመር፤ 19 ራሱንም በመቃ መቱት
ተፉበትም፥ ተንበርክከውም ሰገዱለት።

---

44 [ሉቃስ 23፡25፤ ዮሐ. 19፡16] በሉቃስ 23-24 "ልመናቸው እንዲሆንላቸው"፥ በዮሐንስ 19፡15 ውስጥ "አሳልፎ ሰጣቸው" የተባሉት፥ የካህናት አለቆች፥ መኳንንት እና ሕዝቡ ናቸው። ይሁን እንጂ አይሁዳውያን የሞት ፍርድ ለመፍረድ ሥልጣን አልነበራቸውም (ዮሐ. 18፡31፥ ክፍል 159)። ይህ ዓይነቱ ሥልጣን የነበራቸው ቢሆንም፥ የሞቱ ቅጣት የሚፈጸመው በድንጋይ በመውገር ነበር (ሐዋ. 7፡58-60)። ሉቃስና ዮሐንስ በግልጥ የሚናገሩት ጲላጦስ ኢየሱስን በስቅላት ይገድሉት ዘንድ ለሮማውያን ወታደሮች በመስጠት የአይሁድን ምኞት መፈጸሙን ነው(ሉቃስ 23፡36፤ ዮሐ. 19፡23፤ ክፍል 164)።

45 [ማቴ. 27፡29፤ ማር. 15፡18] በኢየሱስ ላይ ከተፈጸመው ማላገጥና ማንገላታት ይህ ሁለተኛው ነው። ጲላጦስ አይሁዳውያን ለኢየሱስ ይራሩለትና በዚያም ሳቢያ መፈታቱን ይጠይቁ ዘንድ ሊያነሣሣቸው በማሰብ (ዮሐ. 19፡1-5፥ ክፍል 161) ወታደሮቹ ኢየሱስን እንዲያንገላቱት የፈቀደ ይመስላል። በዚህኛው ክፍል ግን፥ በኢየሱስ ላይ ፍርድ እንደተሰጠ ወዲያውኑ ወታደሮቹ እጅግ በከፋ ሁኔታ ያላግጡበት ጀመር።

## ♦ ክፍል 163. ወደ ጎልጎታ ጉዞ

- ከገዢው ግቢ ወደ ጎልጎታ -

**ማቴዎስ 27፡31-34**

31 ከዘበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፥ ልብሱንም አለበሱት ሊሰቅሉትም ወሰዱት።

32 ሲወጡም ስምዖን የተባለው የቀሬናን ሰው አገኙ፤ እርሱንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት።[46]

**ማርቆስ 15፡20-23**

20 ከተዘባበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፥ ልብሱንም አለበሱት፥ ሊሰቅሉትም ወሰዱት።

21 አንድ መንገድ አላፊም የአሌክስንድሮስና የሩፎስ አባት ስምዖን የተባለ የቀሬና ሰው ከገጠር ሲመጣ መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት።[46]

**ሉቃስ 23፡26-33ሀ**

26 በወሰዱትም ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መስቀሉን[46] እንዲሸከም ጫኑበት። 27 ዋይ ዋይ ከሚሉና ሙሾ ከሚያወጡ ሴቶችና ከሕዝቡ እጅግ ብዙዎች ተከተሉት። 28-29 ኢየሱስ ግን ወደ እነርሱ ዘወር ብሎ እንዲህ አለ፦ እናንተ የኢየሩሳሌም ልጆች፥ ለእኔስ አታልቅሱልኝ፤ ዳሩ ግን፦ መካኖችና ያልወለዱ ማኅፀኖች ያላጠቡ ጡቶችም ብፁዓን ናቸው የሚሉበት ጊዜ እነሆ

**ዮሐንስ 19፡17**

17 ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፤ መስቀሉንም ተሸክሞ[46]

---

46 [ማቴ. 27፡32፤ ማር. 15፡21፤ ሉቃስ 23፡26፤ ዮሐ. 19፡17] እንደ ዮሐንስ አገላለጥ ከሆነ ኢየሱስ ከመነሻው ጀምሮ እስከጎልጎታ ድረስ መስቀሉን (ወይም የመስቀሉን አንድ ግንድ) ሳይሸከም አይቀርም። ይሁን እንጂ በእንቅልፍ እጦትና አሰቃቂ ግርፋት ሳቢያ በመዳከሙ፥ መስቀሉን ተሸክሞ ጉዞውን ሊፈጽም አልቻለም። ስለሆነም ነው በኢየሱስ ፈንታ መስቀሉን እንዲሸከም ወታደሮቹ የቀሬናው ስምኦንን ያስገደዱት። ጳውሎስ ሮሜ 16፡13 ውስጥ የሚጠቅሰውና ማርቆስ 15፡21 ውስጥ የተገለጠው ሩፎስ የዚሁ ስምኦን የተባለ ሰው ልጅ ሳይሆን አይቀርም።

| (ማቴዎስ 27፡31-34 የቀጠለ) | (ማርቆስ 15፡20-23 የቀጠለ) | (ሉቃስ 23፡26-33ሀ የቀጠለ) | (ዮሐንስ 19፡17 የቀጠለ) |
|---|---|---|---|
| | | ይመጣልና ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ።<br>30 በዚያን ጊዜ ተራራዎችን፡-<br>በላያችን ውደቁ፥ ኮረብቶችንም፡- ሰውሩን [ሆሴዕ 10፡8] ይሉ ዘንድ ይጀምራሉ፤ 31 በእርጥብ እንጨት እንዲህ የሚያደርጉ ከሆኑ፥ በደረቀውስ እንዴት ይሆን?<br>32 ሌሎችንም ሁለት ክፉ አድራጊዎች ደግሞ ከእርሱ ጋር ይገድሉ ዘንድ ወሰዱ። 33ሀ | |
| 33 ትርጓሜው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሆን ጎልጎታ ወደሚባለው ስፍራ በደረሱ ጊዜም፥ 34 በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት፤ ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም። | 22 ትርጓሜውም የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሆን ጎልጎታ ወደተባለ ስፍራ ወሰዱት። 23 ከርቤም የተቀላቀለበትን የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት፤ እርሱ ግን አልተቀበለም። | ቀራንዮም ወደሚባል ስፍራ በደረሱ ጊዜ፥ | በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ። |

## ♦ ክፍል 164. የመጀመሪያዎቹ ሦስት የስቅላት ሰዓታት

- ጎልጎታ -

**ማቴዎስ 27፡35-44**

35 ከሰቀሉትም
በኋላ ልብሱን ዕጣ
ጥለው ተካፈሉ፥
36 በዚያም
ተቀምጠው
ይጠብቁት ነበር።

**ማርቆስ 15፡24-32**

24 ሰቀሉትም፥
ልብሱንም ማን
ማን እንዲወስድ
ዕጣ ተጣጥለው
ተካፈሉ።

**ሉቃስ 23፡33ለ-43**

33ለ በዚያ እርሱን
ክፉ አድራጊዎ
ቹንም አንዱን
በቀኝ
ሁለተኛውንም
በግራ ሰቀሉ። 34
ኢየሱስም፡- አባት
ሆይ፤
የሚያደርጉትን
አያውቁምና ይቅር
በላቸው[47] አለ።
ልብሱንም
ተካፍለው ዕጣ
ተጣጣሉበት።

**ዮሐንስ 19፡18፥ 23-24፥ 19-22፥ 25-27**

18 በዚያም
ሰቀሉት፥ ከእርሱም
ጋር ሌሎች ሁለት፥
አንዱን በዚህ
አንዱን በዚያ
ኢየሱስንም
በመካከላቸው
ሰቀሉ።

23 ጭፍሮችም
ኢየሱስን በሰቀሉት
ጊዜ ልብሶቹን
ወስደው
ለእያንዳንዱ
ጭፍራ አንድ
ክፍል ሆኖ በአራት
ከፋፈሉት፤
እጀጠባቡን ደግሞ
ወሰዱ። እጀ
ጠባቡም ከላይ
ጀምሮ ወጥ ሆኖ
የተሠራ ነበረ እንጂ
የተሰፋ አልነበረም።

24 ስለዚህ እርስ
በርሳቸው፡-

ለማን እንዲሆን
በእርሱ ዕጣ
እንጣጣልበት እንጂ
አንቀደደው
ተባባሉ። ይህም፡-

“ልብሴን እርስ
በርሳቸው

---

[47] [ሉቃስ 23፡34] ይህ የይቅርታ ጸሎት ኢየሱስ መስቀል ላይ ሆኖ ከተናገረው ቃል የመጀመሪያው ነው። ሌሎቹ ንስሀ ለገባው ወንጀለኛ የተሰጠ ተስፋ (ሉቃስ 23፡43)፥ ስለእናቱ የተናገረው (ዮሐ. 19፡26-27)፥ ከአብ በመለየቱ ሳቢያ ያሰማው ጩኸት (ማቴ. 27፡46፤ ማር. 15፡34፥ ክፍል 165)፥ መጠማቱን መግለጡ (ዮሐ. 19፡28፥ ክፍል 165)፥ የፍጻሜው ድምጽ (ዮሐ. 19፡30፥ ክፍል 165) እና ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ ያሰማው ጩኸት (ሉቃስ 23፡46፥ ክፍል 165) ናቸው።

(ማቴዎስ 27፡35-44 የቀጠለ)

37 ይህ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነው የሚል[49] የክሱን ጽሕፈት ከራሱ በላይ አኖሩ። 38 በዚያን ጊዜ ሁለት ወንበዶች አንዱ በቀኝ አንዱም በግራ ከእርሱ ጋር ተሰቀሉ።

(ማርቆስ 15፡24-32 የቀጠለ)

25 በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት[48] ነበረ። 26 የክሱ ጽሕፈትም፡- የአይሁድ ንጉሥ[49] የሚል ተጽፎ ነበር። 27 ከእርሱም ጋር ሁለት ወንበዶች አንዱን በቀኙ አንዱንም በግራው ሰቀሉ። 28 መጽሐፍም፡- ከአመፀኞች ጋር ተቆጠረ ያለው ተፈጸመ።

(ሉቃስ 23፡33ለ-43 የቀጠለ)

38 ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው[49] ተብሎ በግሪክና በሮማይስጥ በዕብራይስጥም ፊደል የተጻፈ ጽሕፈት ደግሞ በእርሱ ላይ ነበረ።

(ዮሐንስ 19፡18፥ 23-24፥ 19-22፥ 25-27 የቀጠለ)

ተከፋፈሉ በእጀ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉበት”

የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው። ሳመዝሙር 22፡18]

19 ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው፤ ጽሕፈቱም፡-[49] የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበረ። 20 ኢየሱስም የተሰቀለበት ስፍራ ለከተማ ቅርብ ነበረና ከአይሁድ ብዙዎች ይህን ጽሕፈት አነበቡት፤ በዕብራይስጥና በሮማይስጥ በግሪክም ተጽፎ ነበር። 21 ስለዚህ የአይሁድ ካህናት አለቆች ጲላጦስን፡- እርሱ፡- የአይሁድ ንጉስ ነኝ እንዳለ እንጂ የአይሁድ ንጉሥ ብለህ አትጻፍ አሉት።

---

48 [ማር. 15፡25] ኢየሱስ በመስቀል ላይ የቆየበት ጊዜ ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ 9 ነበር። የመጨረሻዎቹ 3 ሰዓታት ከቀትር አንስቶ አካባቢው በጭለማ የተዋጠበት ስለነበር፥ ከሌሎቹ የተለዩ ናቸው (ማቴ. 27፡45፤ ማር. 15፡33፤ ሉቃስ 23፡44-45ሀ፥ ክፍል 165)።

49 [ማቴ. 27፡37፤ ማር. 15፡26፤ ሉቃስ 23፡38፤ ዮሐ. 19፡19] እያንዳንዱ ጸሐፊ የዚህን ጽሑፍ አንድ ክፍል ብቻ ነው ያሰፈረው። ሙሉው ጽሑፍ የተገኘው አራቱን መግለጫዎች ማለት “ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ፥ የአይሁድ ንጉሥ ነው” የሚሉትን በማገጣጠም ነው።

| (ማቴዎስ 27፡35-44 የቀጠለ) | (ማርቆስ 15፡24-32 የቀጠለ) | (ሉቃስ 23፡33ለ-43 የቀጠለ) | (ዮሐንስ 19፡18፥ 23-24፥ 19-22፥ 25-27 የቀጠለ) |
|---|---|---|---|
| | | | 22 ጲላጦስም፡- የጻፍሁትን ጽፌአለሁ ብሎ መለሰ። |
| 39 የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና፡- 40 ቤተ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራው፥ ራስህን አድን፤ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ አሉት። | 29 የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና፡- ዋ፥ ቤተ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራ፥ 30 ከመስቀል ወርደህ ራስህን አድን አሉ። | 35 ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር። | |
| 41 እንዲሁም ደግሞ የካህናት አለቆች ከጻፎችና ከሽማግሎች ጋር እየዘበቱበት እንዲህ አሉ፡- 42 ሌሎችን አዳነ፥ ራሱን ሊያድን አይችልም፤ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ፥ አሁን ከመስቀል ይውረድ እኛም እናምንበታለን። 43 በእግዚአብሔር ታምኖአል፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎአልና ከወደደውስ አሁን ያድነው። [መዝሙር 22፡8] | 31 እንዲሁም የካህናት አለቆች ደግሞ ከጻፎች ጋር እርስ በርሳቸው እየተዘባበቱ፡- ሌሎችን አዳነ፤ ራሱን ሊያድን አይችልም፤ 32 አይተን እናምን ዘንድ የእስራኤል ንጉሥ ክርስቶስ አሁን ከመስቀል ይውረድ አሉ። | መኳንንቱም ደግሞ፡- ሌሎችን አዳነ፤ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ ከሆነ፥ ራሱን ያድን እያሉ ያፌዙበት ነበር። 36 ጭፍሮችም ደግሞ ወደ እርሱ ቀርበው ሆምጣጤም አምጥተው፡- 37 አንተስ የአይሁድ ንጉሥ ከሆንህ፥ ራስህን አድን እያሉ ይዘብቱበት ነበር። | |
| 44 ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዴች ደግሞ ያንኑ እያሉ ይነቅፉት ነበር። | ከእርሱም ጋር የተሰቀሉት ይነቅፉት ነበር። | 39 ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም | |

(ሉቃስ 23፡33ለ-43 የቀጠለ)

አንዱ፡- አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው።
40 ሁለተኛው ግን መልሶ፡- አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን? 41 ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፉት አላደረገም ብሎ ገሠጸው።
42 ኢየሱስንም፡- ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው።
43 ኢየሱስም፡- እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።

(ዮሐንስ 19፡ 18፥ 23-24፥ 19-22፥ 25-27 የቀጠለ)

25 ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ። ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ፥ የእናቱም እኅት፥ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም፥ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር። 26 ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን፡- አንቺ ሴት፥ እነሆ ልጅሽ አላት። 27 ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን፡- እናትህ እነኋት አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።

## ♦ ክፍል 165. የመጨረሻዎቹ ሦስት የስቅለት ሰዓታት

-ጎልጎታ-

**ማቴዎስ 27፡45-50**

45 ከስድስት ሰዓትም ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ። 46 በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ?[50] ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም፦ አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው። [መዝሙር 22፡1]

47 በዚያም ከቆሙት ሰዎች ሰምተው፦ ይህስ ኤልያስን ይጠራል አሉ።

48 ወዲያውም ከእነርሱ አንዱ ሮጠ፤ ሰፍነግም ይዞ ሆምጣጤ ሞላበት፥ በመቃም አድርጎ አጠጣው። 49 ሌሎቹ ግን፦ ተው፥ ኤልያስ መጥቶ ያድነው እንደ ሆነ እንይ አሉ።

50 ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ።

**ማርቆስ 15፡33-37**

33 ስድስት ሰዓትም በሆነ ጊዜ፥ እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ። 34 በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ፥ ኤሎሄ፥ ላማ ሰበቅታኒ?[50] ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ? ማለት ነው። [መዝሙር 22፡1]

35 በዚያም ከቆሙት ሰዎች ሰምተው፦ እነሆ፥ ኤልያስን ይጠራል አሉ።

36 አንዱም ሮጦ ሆምጣጤ በሰፍነግ ሞላ በመቃም አድርጎ፦ ተዉ፤ ኤልያስ ሊያወርደው ይመጣ እንደ ሆነ እንይ እያለ አጠጣው።

37 ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ ነፍሱንም ሰጠ።

**ሉቃስ 23፡44፥ 46**

44 ስድስት ሰዓትም ያህል ነበረ፥ ጨለማም እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ሆነ፥ ፀሐይም ጨለመ፥

**ዮሐንስ 19፡28-30**

28 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ፦ ተጠማሁ አለ። 29 በዚያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ

---

50 [ማቴ. 27፡46፤ ማር. 15፡34] ይህ ሰሚ ያጣ የኢየሱስ ጩኸት ወደ ምድር የመጣበትንና የሞቱን ዋና ምክንያት፥ የሰው ልጆችን የኃጢአት ቅጣት መሸከም ያጠቃልላል። ኃጢአት ከቅዱስ እግዚአብሔር ስለሚለይ፥ ኢየሱስ ያን የመለየት ጊዜ በሞቱ መቀበል ነበረበት። ይህ ባይሆን ኖሮ፥ የኃጢአት ቅጣት ሊከፈል አይችልም ነበር።

(ሉቃስ 23፡44፥ 46 የቀጠለ)

46 ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ፡- አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። [መዝሙር 31፡5] ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።

(ዮሐንስ 19፡28-30 የቀጠለ)

ሞልተው በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት። 30 ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፡- ተፈጸመ አለ፥[51] ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።

## ♦ ክፍል 166. የኢየሱስ ሞት ምስክሮች

- መቅደስ እና ጎልጎታ-

ማቴዎስ 27፡51-56

51 እነሆም፥ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፥ ምድርም ተናወጠች፥ ዓለቶችም ተሰነጠቁ፤ 52 መቃብሮችም ተከፈቱ፥ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ፤ 53 ከትንሣኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ።

54 የመቶ አለቃም ከእርሱም ጋር ኢየሱስን የሚጠብቁ መናወጡንና የሆነውን ነገር አይተው፡- ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ ብለው እጅግ ፈሩ።

55 ኢየሱስን እያገለገሉ ከገሊላ የተከተሉት ብዙ

ማርቆስ 15፡38-41

38 የቤተ መቅደስም መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ።

39 በዚያም በአንጻሩ የቆመ የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ ነፍሱን እንደ ሰጠ[52] ባየ ጊዜ፡- ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ አለ።

40-41 ሴቶችም ደግሞ በሩቅ ሆነው ይመለከቱ ነበር፤

ሉቃስ 23፡ 45፥ 47-49

45 የቤተ መቅደስም መጋረጃ ከመካከሉ ተቀደደ።

47 የመቶ አለቃውም የሆነውን ነገር ባየ ጊዜ፡- ይህ ሰው በእውነት ጻድቅ ነበረ ብሎ እግዚአብሔርን

---

[51] [ዮሐ. 19፡30] እነዚህ ቃላት ወደ ኋላ በመመለስ ዮሐንስ 19፡28 ውስጥ "አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ" ከሚለው ጋር ይጣቀሳሉ። ቃሉ የሚያመለክቱትም አብ ኢየሱስ ይፈጽማቸው ዘንድ የሰጠውን ሁሉ ነው (ዮሐ. 17፡4፥ ክፍል 151፤ ዮሐ. 3፡35፥ ክፍል 33፤ ዮሐ. 13፡3፥ ክፍል 145)። የእግዚአብሔር ቃል ፍጻሜ በዚህ ተልእኮ ውስጥ ይካተታል (ዮሐ. 19፡28)፤ "የተፈጸመ" የሚለው ቃል የሚያመለክተውም ይህንኑ ነው።

[52] [ማር. 15፡39] የመቶ አለቃው ልቡ የተነካው በመሬቱ መንቀጥቀጥና ሌሎች ምልክቶች ብቻ (ማቴ. 27፡54) ሳይሆን፥ በኢየሱስ አሟሟት ሁኔታም ነበር። ኢየሱስ በሞቱ ጊዜ ድምጹን ጎላ አድርጎ ለመጮኽ ብርታት ማግኘቱን (ማቴ. 27፡50፤ ማር. 15፡37፤ ሉቃስ 23፡46፥ ክፍል 165) መመልከት፥ በስቅላት የሚቀጡ ወንጀለኞች በፍጹም ድካም የሚሞቱ መሆናቸውን ለሚያውቅ ሰው የሚያስደንቅ ነበር።

| (ማቴዎስ 27፡51-56 የቀጠለ) | (ማርቆስ 15፡38-41 የቀጠለ) | (ሉቃስ 23፡ 45፥ 47-49 የቀጠለ) |
|---|---|---|
| ሴቶች በሩቅ ሆነው ሲመለከቱ በዚያ ነበሩ፤ 56 ከእነርሱም መግደላዊት ማርያምና[53] የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም የዘብዴዎስም የልጆቹ እናት ነበሩ። | ከእነርሱም በገሊላ ሳለ ይከተሉትና ያገለግሉት የነበሩ መግደላዊት ማርያም[53] የታናሹ ያዕቆብና የዮሳም እናት ማርያም ሰሎሜም ነበሩ፥ ከእርሱም ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የወጡ ሌሎች ብዙዎች ሴቶች ነበሩ። | አከበረ። 48 ይህንም ለማየት ተከማችተው የነበሩ ሕዝብ ሁሉ፥ የሆነውን ባዩ ጊዜ፥ ደረታቸውን እየደቁ ተመለሱ። 49 የሚያውቁቱ ግን ሁሉ ከገሊላ የተከተሉት ሴቶችም[53] ይህን እያዩ በሩቅ ቆመው ነበር። |

## > ቀብር <

## ♦ ክፍል 167ሀ. የኢየሱስ ሞት መረጋገጥና አስከሬኑን መረካከብ

- ጎልጎታ እና የገገርው ግቢ -

<u>ዮሐንስ 19፡31-37</u>

31 አይሁድም የማዘጋጀት ቀን ስለ ሆነ ያ ሰንበት ትልቅ ነበረና ሥጋቸው በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር፥ ጭናቸውን ሰብረው እንዲያወርዱአቸው ጲላጦስን ለመኑት። 32 ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭን ሰበሩ፤ 33 ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤ 34 ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ። 35 ያየውም መስክሮአል፤ ምስክሩም እውነት ነው፤ እናንተም ደግሞ ታምኑ ዘንድ እርሱ እውነት እንዲናገር ያውቃል። 36 ይህ የሆነ፡- ከእርሱ አጥንት አይሰበርም የሚል የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው። [መዝሙር 34፡20] 37 ደግሞም ሌላው መጽሐፍ፡- የወጉትን ያዩታል ይላል። [ዘካርያስ 12፡10]

---

53 [ማቴ. 27፡56፤ ማር. 15፡40፤ ሉቃስ 23፡49] እነዚህ ሴቶች የወንጌልን ዋና ነገር የሚያጠናክሩ ክንውኖች የዓይን ምስክሮች ናቸው። ክንውኖቹም፥ የኢየሱስ ሞት (በዚህ ክፍል ማለት ነው)፥ መቀበሩ (ማቴ. 27፡61፤ ማር. 15፡47፤ ሉቃስ 23፡55፥ ክፍል 168)፥ ትንሣኤው (ማቴ. 28፡1፤ ማር. 16፡1፥ ክፍል 169) ናቸው። ይህን ጉዳይ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3-4 ውስጥ ከሰፈረው ቃል ጋር ያነጻጽሩ።

| ማቴዎስ 27፡57-59ሀ | ማርቆስ 15፡42-45 | ሉቃስ 23፡50-52 | ዮሐንስ 19፡38 |
|---|---|---|---|
| 57 በመሸም ጊዜ | 42 አሁንም በመሸ ጊዜ የሰንበት ዋዜማ የሆነ የማዘጋጀት ቀን ስለ ነበረ፥ | | |
| ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፥ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ። | የከበረ አማካሪ የሆነ የአርማትያስ ዮሴፍ መጣ፥ 43 እርሱም ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ ነበር። | 50 እነሆም፥ በጎና ጻድቅ ሰው የሸንጎ አማካሪም የሆነ ዮሴፍ የሚባል ሰው ነበረ። 51 ይህም በምክራቸውና በሥራቸው አልተባበረም ነበር። አርማትያስም ከምትባል ከአይሁድ ከተማ ሆኖ እርሱ ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ ነበር። | 38 ከዚህም በኋላ አይሁድን ስለ ፈራ በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበረ የአርማትያስ ዮሴፍ የኢየሱስን ሥጋ ሊወስድ ጲላጦስን ለመነ። |
| 58 ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። | ደፍሮም ወደ ጲላጦስ ገባና የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። 44 ጲላጦስም አሁኑን እንዴት ሞተ ብሎ ተደነቀ፥ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ቆይቶአልን? ብሎ ጠየቀው። 45 ከመቶ አለቃውም ተረድቶ | 52 ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። | |
| 59ሀ ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። | በድኑን ለዮሴፍ ሰጠው። | | ጲላጦስም ፈቀደለት። ስለዚህም መጥቶ የኢየሱስን ሥጋ ወሰደ። |

[54] [ማቴ. 27፡59፤ ዮሐ. 19፡39] ኢየሱስን በሕይወት ዘመኑ በግልጥ ሲከተሉት የነበሩት ደቀ መዛሙርት በመጨረሻ ሲሸሹ፥ እርሱ በሕይወት ሳለ እምነታቸውን በምስጢር ጠብቀው የነበሩት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ (ዮሐ. 19፡38፥ ክፍል 167ሀ) ግን ተገቢውን ቀብር ሊፈጽሙለት ገሀድ ወጡ።

## ♦ ክፍል 167ለ. የኢየሱስ አስከሬን መቃብር ውስጥ አረፈ

- በጎልጎታው የአትክልት ቦታ መቃብር -

| <u>ማቴዎስ 27፥59ለ-60</u> | <u>ማርቆስ 15፥46</u> | <u>ሉቃስ 23፥53-54</u> | <u>ዮሐንስ 19፥39-42</u> |
|---|---|---|---|
| | | | 39 ደግሞም አስቀድሞ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ[54] መቶ ንጥር የሚያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ መጣ። 40 የኢየሱስንም ሥጋ ወስደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት። |
| 59ለ ዮሴፍም[54] ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው፥ | 46 በፍታም ገዝቶ አውርዶም በበፍታ ከፈነው ከዓለትም በተወቀረ መቃብር አኖረው፥ | 53 አውርዶም በተልባ እግር ልብስ ከፈነው፥ ማንም ገና ባልተቀበረበት ከዓለትም በተወቀረ መቃብር አኖረው። | 41 በተሰቀለበትም ስፍራ አትክልት ነበረ፥ በአትክልቱም ማንም ገና ያልተቀበረበት አዲስ መቃብር ነበረ። |
| 60 ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው፥ በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ። | በመቃብሩ ደጃፍም ድንጋይ አንከባለለ። | 54 የመዘጋጀት ቀንም ነበረ፤ ሰንበትም ሊጀምር ነበረ። | 42 ስለዚህ መቃብሩ ቅርብ ነበረና ስለ አይሁድ ማዘጋጀት ቀን ኢየሱስን በዚያ አኖሩት። |

## ♦ ክፍል 168. መቃብሩን ሴቶች ተመለከቱት፥ በወታደሮችም ተጠበቀ

- ቢታንያ፥ ጎልጎታ፥ እና የገነርው ግቢ -

| <u>ማቴዎስ 27፥61-66</u> | <u>ማርቆስ 15፥47</u> | <u>ሉቃስ 23፥55-56</u> |
|---|---|---|
| 61 መግደላዊት ማርያምም ሁለተኛይቱም ማርያም በመቃብሩ አንጻር ተቀምጠው በዚያ ነበሩ። 62 በማግሥቱም ከመዘጋጀት በኋላ በሚሆነው ቀን፥ የካህናት | 47 መግደላዊትም ማርያም የዮሳም እናት ማርያም ወዴት እንዳኖሩት ይመለከቱ ነበር። | 55 ከገሊላም ከእርሱ ጋር የመጡት ሴቶች ተከትለው መቃብሩን ሥጋውንም እንዴት እንዳኖሩት አዩ። 56 ተመልሰውም ሽቱና ቅባት አዘጋጁ። በሰንበትም እንደ ትእዛዙ ዐረፉ። |

(ማቴዎስ 27፥61-66 የቀጠለ)

አለቆችና ፈሪሳውያን ወደ ጲላጦስ ተሰበሰቡና፦ 63 ጌታ ሆይ፥ ያ አሳች በሕይወቱ
ገና ሳለ፦ ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ እንዳለ ትዝ[55] አለን። 64 እንግዲህ ደቀ
መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁት ለሕዝቡም፦ ከሙታን ተነሣ
እንዳይሉ፥ የኋለኛይቱ ስሕተት ከፊተኛይቱ ይልቅ የከፋች ትሆናለችና መቃብሩ
እስከ ሦስተኛ ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ አሉት።

65 ጲላጦስም፦ ጠባቆች አሉአችሁ፤ ሄዳችሁ እንዳወቃችሁ አስጠብቁ አላቸው።
66 እነርሱም ሄደው ከጠባቆች ጋር ድንጋዩን አትመው መቃብሩን አስጠበቁ።

---

[55] [ማቴ. 27፥63] ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ስለ ትንሣኤው በግልጥ የነገራቸውን ሲዘነጉ (ክፍል 83፥ 88፤ 125ሀ)፥ ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን ግን በዘይቤያዊ አባባል የገለጠላቸውን መረዳታቸውና ማስታወሳቸውም የሚደንቅ ነው (ማቴ. 12፥40፥ ክፍል 62፤ ማቴ. 16፥4፥ ክፍል 80፤ ዮሐ. 2፥19-20፥ ክፍል 31)።

[56] [ማቴ. 28፥1፤ ማር. 16፥1] መቃብሩን በተለየ ሁኔታ የጎበኙት ሴቶች ቁጥር አይታወቅም። ስማቸው የተጠቀሰው እነዚህ ናቸው፦ መግደላዊት ማርያም (ማቴ. 28፥1፤ ማር. 16፥1፤ ሉቃስ 24፥10፥ ክፍል 172፤ ዮሐ. 20፥1፥ ክፍል 171)፥ የያዕቆብ እናት ወይም "ሌላይቱ ማርያም" (ማቴ. 28፥1፤ ማር. 16፥1፤ ሉቃስ 24፥10፥ ክፍል 172)፥ ሰሎሜ (ማር. 16፥1) እና ዮሐና (ሉቃስ 24፥10፥ ክፍል 172)። ስንት "ሌሎች" (ሉቃስ 24፥10፥ ክፍል 172) አብረዋቸው እንደነበሩ አልተነገረም።

# 13

# የክርስቶስ ትንሣኤና እርገት

## > ባዶው መቃብር <

### ♦ ክፍል 169. መቃብሩ በሴቶች ተጎበኘ

- ቢታንያና ጎልጎታ -

| ማቴዎስ 28፡1 | ማርቆስ 16፡1 |
|---|---|
| 1 በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና[56] ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ። | 1 ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም[56] የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ። |

### ♦ ክፍል 170. ድንጋዩ ተንከባለለ

- ጎልጎታ -

ማቴዎስ 28፡2-4

2 እነሆም፥ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ[57] ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። 3 መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። 4 ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ።

### ♦ ክፍል 171. ሴቶቹ ያገኙት ባዶ መቃብር ነው

- ጎልጎታ -

| ማቴዎስ 28፡5-8 | ማርቆስ 16፡2-8 | ሉቃስ 24፡1-8 | ዮሐንስ 20፡1 |
|---|---|---|---|
| | 2 ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን እጅግ በማለዳ ፀሐይ ከወጣ በኋላ[58] ወደ መቃብር መጡ። 3 እርስ በርሳቸውም፦ ድንጋዩን | 1 ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ። 2 ድንጋዩንም | 1 ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ[58] ማለዳ ወደ መቃብር መጣች ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች። |

---

[57] [ማቴ. 28፡2] ምናልባት የኢየሱስ ትንሣኤ፥ በዚህ "ታላቅ የምድር መናወጥ" ጊዜ ተከናውኖ ይሆናል። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገለጠው፥ ብዙ ጊዜ የምድር ነውጥ የመለኮትን ጉብኝት ያመለክታል (ማቴ. 27፡51፥ 54፥ ክፍል 166)። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከመቃብር ሲነሣ ማንም ስላላየው ትክክለኛውን ጊዜ ለመናገር አይቻልም። የትንሣኤው መጀመሪያ ምስክሮች (ሐዋ. 1፡22) ከተነሣ በኋላ ያዩት (ክፍል 173-174፥ 176፥ 178-184) ነበሩ። የመቃብሩን ድንጋይ እንዲያንከባልል መልአክ መምጣቱ፥ የተነሣው ኢየሱስ ከመቃብሩ እንዲወጣ ለማድረግ የታቀደ አልነበረም። ይህ አላስፈለገውም (ዮሐ. 20፡19፥ ክፍል 178)። የድንጋዩ መንከባለል ያስፈለገው ባዶውን መቃብር ምስክሮች ያዩ ዘንድ ነበር (ማር. 16፡5፤ ሉቃስ 24፡3፥ ክፍል 171፤ ዮሐ. 20፡5-8፥ ክፍል 172)።

(ማቴዎስ 28፡5-8 የቀጠለ)

5 መልአኩም መልሶ
ሴቶቹን አላቸው፡-
እናንተስ አትፍሩ
የተሰቀለውን ኢየሱስን
እንድትሹ አውቃለሁና፤ 6
እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና
በዚህ የለም፤ የተኛበትን
ስፍራ ኑና እዩ። 7
ፈጥናችሁም ሂዱና፡-
ከሙታን ተነሣ፥ እነሆም፥
ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል
በዚያም ታዩታላችሁ
ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ
ንገሩአቸው።

8 እነሆም፥ ነገርኋችሁ።
በፍርሃትና በታላቅ ደስታም
ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፥
ለደቀ መዛሙርቱም
ሊያወሩ ሮጡ።

(ማርቆስ 16፡2-8 የቀጠለ)

ከመቃብር ደጃፍ ማን ያንከ
ባልልልናል? ይባባሉ
ነበር፤

4 ድንጋዩ እጅግ ትልቅ
ነበርና፤ አሻቅበውም
አይተው ድንጋዩ ተንከባሎ
እንደ ነበር ተመለከቱ። 5
ወደ መቃብሩም ገብተው
ነጭ ልብስ የተጎናጸፈ
ጎልማሳ በቀኝ በኩል
ተቀምጦ አዩና ደነገጡ።

6 እርሱ ግን፡-
አትደንግጡ፤ የተሰቀለውን
የናዝሬቱን ኢየሱስን
ትፈልጋላችሁ፤
ተነሥቶአል፥ በዚህ የለም፤
እነሆ እርሱን ያኖሩበት
ስፍራ። 7 ነገር ግን ሄዳችሁ
ለደቀ መዛሙርቱ
ለጴጥሮስም፡- ወደ ገሊላ
ይቀድማችኋል፤ እንደ
ነገራችሁ በዚያ
ታዩታላችሁ ብላችሁ
ንገሩአቸው አላቸው።

8 መንቀጥቀጥና መደንገጥ
ይዞአቸው ነበርና ወጥተው
ከመቃብር ሸሹ፤ ይፈሩ
ነበርና ለማንም አንዳች
አልነገሩም። እነርሱም
ያዘዛቸውን ሁሉ
ለጴጥሮስና ከእርሱ ጋር
ላሉት በአጭሩ ተናገሩ።
ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ራሱ
ለዘላለም ድኅነት የሆነውን
የማይለወጠውን ቅዱስ
ወንጌል ከፀሐይ መውጫ
እስከ መጥለቂያው ድረስ
በእጃቸው ላከው።

(ሉቃስ 24፡1-8 የቀጠለ)

ከመቃብሩ ተንከባሎ
አገኙት፥ 3 ገብተውም
የጌታን የኢየሱስን ሥጋ
አላገኙም። 4 እነርሱም
በዚህ ሲያመነቱ፥ እነሆ፥
ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ
ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ
ቀረቡ፤ 5 ፈርተውም
ፊታቸውን ወደ ምድር
አቀርቅረው ሳሉ፥ እንዲህ
አሉአቸው፡- ሕያውን
ከሙታን መካከል ስለ ምን
ትፈልጋላችሁ?
ተነሥቶአል እንጂ በዚህ
የለም። 6-7 የሰው ልጅ
በኃጢአተኞች እጅ አልፎ
ሊሰጥና ሊሰቀል
በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ
ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ
ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ
አስቡ። 8 ቃሎቹንም
አሰቡ፥

## ♦ ክፍል 172. ጴጥሮስና ዮሐንስ ያገኙት ባዶ መቃብር ነው

- ጎልጎታ -

<u>ሉቃስ 24፡9-12</u>

9 ከመቃብሩም ተመልሰው ይህን ሁሉ
ለአሥራ አንዱና ለሌሎች ሁሉ
ነገሩአቸው።

10 ይህንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው
መግደላዊት ማርያምና ዮሐና የያዕቆብም
እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩት
ሌሎች ሴቶች ነበሩ። 11 ይህም ቃል
ቅዠት መስሎ ታያቸውና
አላመኑአቸውም። 12 ጴጥሮስ ግን
ተነሥቶ ወደ መቃብር ሮጠ፤ በዚያም
ዝቅ ብሎ ሲመለከት የተልባ እግር
ልብስን ብቻ አየ፤ በሆነውም ነገር
እየተደነቀ ወደ ቤቱ ሄደ።

<u>ዮሐንስ 20፡2-10</u>

2 እየሮጠችም ወደ ስምዖን ጴጥሮስና
ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው ወደ ሌላው
ደቀ መዝሙር መጥታ፡- ጌታን ከመቃብር
ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት
አናውቅም አለቻቸው።

3 ስለዚህ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር
ወጥተው ወደ መቃብሩ ሄዱ። 4 ሁለቱም
አብረው ሮጡ፤ ሌላው ደቀ መዝሙርም
ከጴጥሮስ ይልቅ ፈጥኖ ወደ ፊት ሮጠና
አስቀድሞ ከመቃብሩ ደረሰ፤ 5 ዝቅም ብሎ
ቢመለከት የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ
አየ፥ ነገር ግን አልገባም። 6 ስምዖን
ጴጥሮስም ተከትሎት መጣ ወደ
መቃብሩም ገባ፤ የተልባ እግሩን ልብስ
ተቀምጦ አየ፥ 7 ደግሞም በራሱ የነበረውን
ጨርቅ ለብቻው በአንድ ስፍራ ተጠምጥሞ
እንደ ነበረ እንጂ ከተልባ እግሩ ልብስ ጋር
ተቀምጦ እንዳልነበረ አየ። 8 በዚያን ጊዜ
አስቀድሞ ወደ መቃብር የመጣውም ሌላው
ደቀ መዝሙር ደግሞ ገባ፥ አየም፥
አመነም፤ 9 ከሙታን ይነሣ ዘንድ
እንዲገባው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል ገና
አላወቁም ነበርና።

10 ደቀ መዛሙርቱም ወደ ቤታቸው
ደግሞ ሄዱ።

[58] [ማር. 16፡2፤ ዮሐ. 20፡1] ማርቆስ 16፡2 ውስጥ "እጅግ በማለዳ" የሚለው ቃል ዮሐንስ 20፡1 ውስጥ "ገና ጨለማ ሳለ" ከሚለው ጋር አይቃረንም። ምናልባት መግደላዊት ማርያም ከሌሎቹ ቀድማ በመሮጥ፥ ዮሐንስ እንደገለጠው ጸሐይ ከመውጣቷ በፊት ደርሳ፥ ሌሎቹ ደግሞ ማርቆስ እንደገለጠው ጸሐይ ከወጣች በኋላ መቃብሩ ዘንድ ደርሰው ይሆናል። ሊሆን የሚችለው ሌላ ገለጣ፥ ሴቶቹ ወደ መቃብሩ ጉዞ የጀመሩት በምሽት ሳይሆን፥ መቃብሩ ዘንድ የደረሱት ጸሐይ ስትወጣ ነው የሚል ነው።

# > ከእርገት በኋላው መገለጥ <

## ♦ ክፍል 173. ለመግደላዊት ማርያም መታየት

- ጎልጎታ እና ኢየሩሳሌም -

ማርቆስ 16፡9-11[59]

9 ከሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን ማልዶ በተነሣ ጊዜ፥ አስቀድሞ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለመግደላዊት ማርያም ታየ።

10 እርስዋ ሄዳ ከእርሱ ጋር ሆነው ለነበሩት ሲያዝኑና ሲያለቅሱ ሳሉ

ዮሐንስ 20፡11-18

11 ማርያም ግን እያለቀሰች ከመቃብሩ በስተ ውጭ ቆማ ነበር። ስታለቅስም ወደ መቃብር ዝቅ ብላ ተመለከተች፤ 12 ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም በእግርጌ ተቀምጠው አየች።

13 እነርሱም፦ አንቺ ሴት፥ ስለ ምን ታለቅሻለሽ? አሉአት።

እርስዋም፦ ጌታዬን ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም አለቻቸው። 14 ይህንም ብላ ወደ ኋላ ዘወር ስትል ኢየሱስን ቆሞ አየችው፤ ኢየሱስም እንደ ሆነ አላወቀችም።

15 ኢየሱስም፦ አንቺ ሴት፥ ስለ ምን ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊያለሽ? አላት።

እርስዋም የአትክልት ጠባቂ መስሎአት፦ ጌታ ሆይ፥ አንተ ወስደኸው እንደ ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ እኔም እወስደዋለሁ አለችው።

16 ኢየሱስም፦ ማርያም አላት።

እርስዋ ዘወር ብላ በዕብራይስጥ፦ ረቡኒ አለችው፤ ትርጓሜውም፦ መምህር ሆይ ማለት ነው።

17 ኢየሱስም፦ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤[60] ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ፦ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።

[59] [ማር. 16፡9-20] በጣም ተአማኒነት ያላቸው ሁለቱ ቀደምት ጽሑፎች ማርቆስ 16፡9-20 ላይ የቀረቡት ጥቅሶች አይገኙባቸውም። ጥንታዊ አባቶችም ቢሆኑ እነዚህን ጥቅሶች አልጠቀሱም።

(ማርቆስ 16፡9-11 የቀጠለ)

አወራችላቸው፤ 11 እነርሱም ሕያው እንደ ሆነ ለእርስዋም እንደ ታያት ሲሰሙ አላመኑም።

(ዮሐንስ 20፡11-18 የቀጠለ)

18 መግደላዊት ማርያም መጥታ ጌታን እንዳየች ይህንም እንዳላት ለደቀ መዛሙርቱ ነገረች።

## ♦ ክፍል 174. ለሌሎች ሴቶች መታየት

- ኢየሩሳሌም -

ማቴዎስ 28፡9-10

9 እነሆም፥ ኢየሱስ አገኛቸውና፦ ደስ ይበላችሁ አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት። 10 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ፦ አትፍሩ፤ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ፥ በዚያም ያዩኛል አላቸው።

## ♦ ክፍል 175. ወታደሮች ለአይሁድ ባለሥልጣናት ያቀረቡት ሪፖርት

- ኢየሩሳሌም -

ማቴዎስ 28፡11-15

11 ሲሄዱም ሳሉ እነሆ፥ ከጠባቆቹ አንዳንድ ወደ ከተማ መጥተው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩ። 12 ከሽማግሌዎች ጋርም ተሰብስበው ተማከሩና ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋቸው፦ 13 እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ።[61] 14 ይህም በገዢው ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ፥ እኛ እናስረዳዋለን እናንተም ያለ ሥጋት እንድትሆኑ እናደርጋለን አሉአቸው። 15 እነርሱም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ አስተማሩአቸው አደረጉ። ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል።

---

60 [ዮሐ. 20፡17] ኢየሱስ ለማርያም ለመንገር የፈለገው፥ እንደ አልአዛር ወደ አሮጌው ሰውነት የማይመለስ መሆኑን ነበር (ዮሐ. 12፡2፥ ክፍል 141፤ ዮሐ. 12፡9፥ ክፍል 128ሀ)። ያኔ ከትንሣኤው በፊት የነበረው ገጽታ ሊቆይ የሚችለው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነበር፤ ምክንያቱም ወዲያውኑ ወደ አባቱ መመለስ ነበረበት (ክፍል 184፤ ዮሐ. 14፡2፥ ክፍል 149)። በመሆኑም ማርያም ያየችውን ሄዳ ለደቀ መዛሙርቱ እንድትነግር አዛዛት።

61 [ማቴ.28፡13] የዚህ በሸንጎው ግልጥ ስብሰባ የተፈጠረ ሐሰት ነገር (ማቴ. 28፡11-12) ባለፉት ጊዜያት በተከታታይነት በተከናወኑ ሁኔታዎች ሳቢያ የመጣ ተስፋ መቁረጥ ውጤት ነው። የመቃብሩን ድንጋይ ያንከባለሉት ደቀ መዛሙርቱ ቢሆኑ ኖሮ፥ ያን በሚያደርጉበት ጊዜ ድምጽ ስለሚሰማ ቢያንስ ከወታደሮቹ አንዱ ይነቃ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ ወታደሮቹ ተኝተው ከነበረ የኢየሱስን አስከሬን የወሰዱት ደቀ መዛሙርቱ እንደሆኑ በምን አወቁ? የመቃብሩን ባዶነት ምክንያት ለመግለጥ የሚደረገው ሙከራ ባለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ቢቀጥልም ውጤት አልባ ሆኗል። አሳማኙ ገለጣ እግዚአብሔር ኢየሱስን በኃይሉ ከሞት ማስነሣቱና ከመቃብሩ እንዲወጣ ማድረጉ ነው።

## ♦ ክፍል 176. ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ለነበሩት ሁለት ደቀ መዛሙርት መታየት

- ወደ ኤማሁስ ጉዞ መንገዱ ላይ -

**ማርቆስ 16፥12-13**

12 ከዚህም በኋላ ከእነርሱ ለሁለቱ ወደ ባላገር ሲሄዱ በመንገድ በሌላ መልክ ተገለጠ፤ 13 እነርሱም ሄደው ለሌሎቹ አወሩ፤ እነዚያንም ደግሞ አላመኑአቸውም።

**ሉቃስ 24፥13-32**

13 እነሆም፥ ከእነርሱ ሁለቱ በዚያ ቀን ከኢየሩሳሌም ስድሳ ምዕራፍ ያህል ወደሚርቅ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር ይሄዱ ነበር፤ 14 ስለዚህም ስለ ሆነው ነገር ሁሉ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር። 15 ሲነጋገሩና ሲመራመሩም፥ ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር፤ 16 ነገር ግን እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር።

17 እርሱም፦ "እየጠወለጋችሁ ስትሄዱ፥ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩአቸው እነዚህ ነገሮች ምንድር ናቸው?" አላቸው። 18 ቀለዮጳ የሚባልም አንዱ መልሶ፦ አንተ በኢየሩሳሌም እንግዳ ሆነህ ለብቻህ ትኖራለህን? በእነዚህ ቀኖች በዚያ የሆነውን ነገር አታውቅምን? አለው።

19 እርሱም፦ "ይህ ምንድር ነው?" አላቸው።

እነርሱም እንዲህ አሉት፦ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ፤ 20 እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ እንዲሆን አሳልፈው እንደ ሰጡትና እንደ ሰቀሉት ነው።
21 እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደ ሆነ ተስፋ አድርገን ነበር፤ ደግሞም ከዚህ ሁሉ ጋር ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው። 22 ደግሞም ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፤ 23 ሥጋውንም ባጡ ጊዜ፦ ሕያው ነው የሚሉ የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን ሲሉ መጥተው ነበር። 24 ከእኛም ጋር ከነበሩት ወደ መቃብር ሄደው ሴቶች እንደ ተናገሩት ሆኖ አገኙት፥ እርሱን ግን አላዩትም።

25 እርሱም፦ እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤ 26 ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው። 27 ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።

28 ወደሚሄዱበትም መንደር ቀረቡ፥ እርሱም ሩቅ የሚሄድ መሰላቸው። 29 እነርሱ፦ ከእኛ ጋር እደር፥ ማታ ቀርቦአልና ቀኑም ሊመሽ ጀምሮአል ብለው ግድ አሉት፤ ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ።

30 ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እንጀራውን አንሥቶ ባረከው፥ ቈርሶም ሰጣቸው፤ 31 ዓይናቸውም ተከፈተ፥ አወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ። 32 እርስ በርሳቸውም፦ በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን? ተባባሉ።

## ♦ ክፍል 177. ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ያዩትን ለሌሎቹ መንገራቸው

- ኢየሩሳሌም -

| ሉቃስ 24፡33-35 | 1 ቆሮንቶስ 15:5ሀ |
|---|---|
| 33-34 በዚያችም ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥ አሥራ አንዱና ከእነርሱ ጋር የነበሩትም፡- ጌታ በእውነት ተነሥቶአል ለስምዖንም[62] ታይቶአል እያሉ በአንድነት ተሰብስበው አገኙአቸው። 35 እነርሱም በመንገድ የሆነውን እንጀራውንም በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንደ ታወቀላቸው ተረኩላቸው። | 5ሀ ለኬፋም[62] ታየ . . . |

## ♦ ክፍል 178. ተሰብስበው ለነበሩ አሥር ደቀ መዛሙርት መታየት

[ክፍል 181ና 183ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም -

| ማርቆስ 16፡14 | ሉቃስ 24፡36-43 | ዮሐንስ 20፡19-25 |
|---|---|---|
| 14 ኋላም በማዕድ ተቀምጠው ሳሉ ለአሥራ አንዱ ተገለጠ፥ ተነሥቶም ያዩትን ስላላመኑአቸው አለማመናቸውንና የልባቸውን ጥንካሬ ነቀፈ። | 36 ይህንም ሲነጋገሩ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ፡-[63] ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። 37 ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ መንፈስም ያዩ መሰላቸው። 38 እርሱም፡- ስለ ምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? 39 እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው። 40 ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው። 41 | 19 ያም ቀን እርሱም ከሳምንቱ ፊተኛው በመሸ ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት፥ አይሁድን ስለ ፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ፥ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፡-[63] ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። |

[62] [ሉቃስ 24፡34፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡5ሀ] ለስምዖን ጴጥሮስ (ለኬፋ) በግል ታየ የሚለውን ምንም እንኳን ጳውሎስ በአንደኛ የቆሮንቶስ መልእክቱ ቢጠቅሰው፥ በአራቱ ወንጌሎች ግን አልተገለጠም። ይህ የሆነው ምናልባት ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ወደ ኤማሁስ ጉዞ ከመጀመራቸውና (ሉቃስ 24፡13፥ ክፍል 176) ነገር ግን አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ኢየሩሳሌም ውስጥ ከመሰብሰባቸው በፊት (ሉቃስ 24፡33) ይሆናል።

[63] [ሉቃስ 24፡36 ፤ዮሐ. 20፡19] ይህ ክፍል ስለ ኢየሱስ የትንሣኤ አካል ብዙ ይገልጣል። በዚህ ቁጥር ገለጣ መሠረት ኢየሱስ በተዘጋ በር ሊገባ ችሏል። ቁስሎቹ ይታዩ ነበር (ሉቃስ 24፡39፤ ዮሐ. 20፡20)። አካሉ ሊዳሰስ የሚችል ገላ ነበር (ሉቃስ 24፡39፤ ዮሐ. 20፡25፥ 27፥ ክፍል 178-179)። ሥጋና አጥንት ነበረው (ሉቃስ 24፡39)። እንደ ማንኛውም ሟች አካል ይመገብ ነበር (ሉቃስ 24፡43)።

(ሉቃስ 24፡36-43 የቀጠለ)

እነርሱም ከደስታ የተነሣ ገና ስላላመኑ ሲደነቁ ሳሉ፦ በዚህ አንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው። 42 እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራጭ፥ ከማር ወለላም ሰጡት፤ 43 ተቀብሎም በፊታቸው በላ።

(ዮሐንስ 20፡ 19-25 የቀጠለ)

20 ይህንም ብሎ እጆቹንም ጎኑንም አሳያቸው። ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው።

21 ኢየሱስም ዳግመኛ፦ ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው። 22 ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና፦ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። 23 ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።

24 ነገር ግን ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከእነርሱ ጋር አልነበረም። 25 ሌሎቹም ደቀ መዛሙርቱ፦ ጌታን አይተነዋል አሉት።

እርሱ ግን፦ የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው።

## ♦ ክፍል 179. ለአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት መታየት

- ኢየሩሳሌም -

ዮሐንስ 20፡26-31

26 ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው በውስጥ ነበሩ፥ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ፦ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው።

27 ከዚያም በኋላ ቶማስን፦ ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው።

28 ቶማስም፦ ጌታዬ አምላኬም[64] ብሎ መለሰለት።

29 ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።

30 ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤ 31 ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።

1 ቆሮንቶስ 15:5ለ

. . . በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ . . .

64 [ዮሐ. 20፡28] ቶማስ ተጠራጣሪነቱን ካስወገደ በኋላ ከሁሉ የላቀ ብርቱ ንስሐ አደረገ። ከዚያ ቀደም ሲል ኢየሱስ ማንንም እንደዚያ አልተናገረም። ቶማስ ኢየሱስን አምላክ ብሎ መጥራቱ ከአብ ጋር አስተካከለው (ዮሐ. 5፡23፥ ክፍል 49ሐ)።

## ♦ ክፍል 180. ዓሣ በማጥመድ ላይ ለነበሩ ሰባት ደቀ መዛሙርት መታየት

- በገሊላ ባሕር -

የሐንስ 21፡ 1-25

1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ገና
ተገለጠላቸው፤ 2 እንዲህም ተገለጠ። ስምዖን ጴጥሮስና ዲዲሞስ የሚባለው ቶማስ
ከገሊላ ቃና የሆነ ናትናኤልም የዘብዴዎስም ልጆች ከደቀ መዛሙርቱም ሌሎች ሁለት
በአንድነት ነበሩ። 3 ስምዖን ጴጥሮስ፡- ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ አላቸው። እነርሱም፡-
እኛም ከአንተ ጋር እንመጣለን አሉት። ወጥተውም ወደ ታንኳይቱ ገቡ በዚያችም
ሌሊት ምንም አላጠመዱም።

4 በነጋም ጊዜ ኢየሱስ በባሕር ዳር ቆመ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን
አላወቁም።

5 ኢየሱስም፡- ልጆች ሆይ፥ አንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው።

የለንም ብለው መለሱለት።

6 እርሱም፡- መረቡን በታንኳይቱ በስተ ቀኝ ጣሉት ታገኙማላችሁ አላቸው። ስለዚህ
ጣሉት፤ በዚህም ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ ሊጐትቱት አቃታቸው።

7 ኢየሱስ ይወደው የነበረውም ደቀ መዝሙር ጴጥሮስን፡- ጌታ እኮ ነው አለው።
ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን በሰማ ጊዜ ዕራቁቱን ነበረና ልብሱን ታጥቆ ወደ
ባሕር ራሱን ጣለ። 8 ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ግን ከምድር ሁለት መቶ ክንድ ያህል
እንጂ እጅግ አልራቁም ነበርና ዓሣ የሞላውን መረብ እየሳቡ በጀልባ መጡ። 9 ወደ
ምድርም በወጡ ጊዜ ፍምና ዓሣ በላዩ ተቀምጦ እንጀራም አዩ።

10 ኢየሱስም፡- አሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ አምጡ አላቸው።

11 ስምዖን ጴጥሮስም ወደ ጀልባይቱ ገብቶ መቶ አምሳ ሦስት ታላላቅ ዓሦች ሞልቶ
የነበረውን መረብ ወደ ምድር ጐተተ፤ ይህንም ያህል ብዙ ሲሆን መረቡ
አልተቀደደም። 12 ኢየሱስም፡- ኑ፥ ምሳ ብሉ አላቸው። ከደቀ መዛሙርቱ አንድ
ስንኳ፡- አንተ ማን ነህ? ብሎ ሊመረምረው የደፈረ አልነበረም፤ ጌታ መሆኑን
አውቀው ነበርና። 13 ኢየሱስም መጣና እንጀራ አንሥቶ ሰጣቸው፥ እንዲሁም
ዓሣውን። 14 ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጥላቸው ይህ
ሦስተኛው ጊዜ ነበረ።

15 ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ
ይልቅ ትወደኛለህን? አለው።

አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው።

ግልገሎቼን አሰማራ አለው።

16 ደግሞ ሁለተኛ፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው።

አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው።

17 ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው።

ሦስተኛ ጊዜ፡- የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው።

ሦስተኛ፡- ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና፡-

(የዮሐንስ 21፡ 1-25 የቀጠለ)

ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው።

ኢየሱስም፦ በጎቼን አሰማራ። 18 እውነት እውነት እልሃለሁ፥ አንተ ጕልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፥ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው። 19 በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ። ይህንም ብሎ፦ ተከተለኝ አለው።

20 ጴጥሮስም ዘወር ብሎ ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ሲከተለው አየ፤ እርሱም ደግሞ በእራት ጊዜ በደረቱ ተጠግቶ፦ ጌታ ሆይ፥ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው? ያለው ነበረ። 21 ጴጥሮስም ይህን አይቶ ኢየሱስን፦ ጌታ ሆይ፥ ይህስ እንዴት ይሆናል? አለው።

22 ኢየሱስም፦ እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ፥ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ አለው። 23 ስለዚህ፦ ያ ደቀ መዝሙር አይሞትም የሚለው ይህ ነገር ወደ ወንድሞች ወጣ፤ ነገር ግን ኢየሱስ፦ እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? አለው እንጂ አይሞትም አላለውም።

24 ስለ እነዚህም የመሰከረ ይህንንም ጽፎ ያለ ይህ ደቀ መዝሙር ነው፥ ምስክሩም እውነት እንደ ሆነ እናውቃለን።

25 ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል።

## ♦ ክፍል 181. በገሊላ ለአሥራ አንዱ መታየት

[ክፍል 178ና 183ን ይመልከቱ]

- ገሊላ በሚገኝ አንድ ተራራ -

| ማቴዎስ 28፡ 16-20 | ማርቆስ 16፡ 15-18 | 1 ቆሮንቶስ 15:6 |
| --- | --- | --- |
| 16 አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ ወዳዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ፥ 17 ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ የተጠራጠሩ ግን ነበሩ። 18 ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። 19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ | 15 እንዲህም አላቸው፦ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ። | 6 ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፤ |

(ማቴዎስ 28፡16-20 የቀጠለ)

እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት
አድርጓቸው፤ እነሆም፥ እኔ እስከ ዓለም
ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

(ማርቆስ 16፡15-18 የቀጠለ)

16 ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ
ግን ይፈረድበታል። 17 ያመኑትንም
እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ
አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ
ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥ 18
የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤
እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ
እነርሱም ይድናሉ።

## ♦ ክፍል 182. የኢየሱስ ወንድም ለሆነው ያዕቆብ መታየት

1 ቆሮንቶስ 15:7

7 ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ[66] ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ፤

## ♦ ክፍል 183. ኢየሩሳሌም ውስጥ ለደቀ መዛሙርቱ መታየት

[ክፍል 178ና 181ን ይመልከቱ]

- ኢየሩሳሌም -

ሉቃስ 24፡44-49

44 እርሱም፦ ከእናንተ ጋር ሳለሁ
በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም
ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ
ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው
አላቸው።
45 በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን
ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን
ከፈተላቸው፤ 46 እንዲህም አላቸው፦
ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም
ቀን ከሙታን ይነሣል፥ 47 በስሙም
ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም
ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ
እንዲሁ ተጽፎአል።

48 እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ።
49 እነሆም፥ አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ
እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል
እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ
ቆዩ።

የሐዋርያት ሥራ 1፡3-8

3 ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ
እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር
እየነገራቸው፥ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ
በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን
አሳያቸው። 4 ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ
ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፥ ነገር
ግን፦ ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን
የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ 5 ዮሐንስ በውኃ
አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን
በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ
አለ። 6 እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ፦ ጌታ
ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል
መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው
ጠየቁት። 7 እርሱም፦ አብ በገዛ ሥልጣኑ
ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ
ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ 8 ነገር
ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ
ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥
በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ
በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ
ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።

# > እርገቱ <

## ♦ ክፍል 184. የክርስቶስ የመጨረሻ በረከትና መለየት

- ከኢየሩሳሌም ወደ ደብረ ዘይት (ቢታንያ አጠገብ) -

**ማርቆስ 16፡19-20[59]**

19 ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ።

20 እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፥ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፥ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር።

**ሉቃስ 24፡50-53**

50 እስከ ቢታንያም አወጣቸው እጆቹንም አንሥቶ ባረካቸው። 51 ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም ዐረገ።

52 እነርሱም፤ ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥ 53 ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በመቅደስ[66] ኖሩ።

**የሐዋርያት ሥራ 1፡9-12**

9 ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው። 10 እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኵር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፤ 11 ደግሞም፡- የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው። 12 በዚያን ጊዜ ደብረ ዘይት ከሚባለው ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥ እርሱም ከኢየሩሳሌም የሰንበት መንገድ ያህል የራቀ ነው።

---

[65] [1ኛ ቆሮ. 15፡7] ይህ ሰው ምናልባት የኢየሱስ ግማሽ ወንድም የሆነው ያዕቆብ ሳይሆን አይቀርም። ይህ መገለጥ የሆነው መቼ እንደሆነ ባይታወቅም፥ መከናወኑ ግን እርግጥ ነው። ከኢየሱስ ሞት በፊት አማኝ ያልነበረው ያዕቆብ ከዚህ ሁኔታ በኋላ አማኝና የኢየሩሳሌሚ ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆነ። ከሞት የተነሣውን ኢየሱስን ማየቱ በእምነት ለመለወጡ ብቻ ሳይሆን፥ ለሐዋርያዊ ሹመቱ መሠረት ሆነ (ገላ. 1፡19)።

[66] [ሉቃስ 24፡53] ጥንታዊያኑ ክርስቲያኖች ከአሮጌው የቤተ መቅደስ ስግደት ነጻ መሆናቸውን የተረዱት ቀስ በቀስ ነበር (ዕብ. 8፡13)። ከኢየሱስ ማረግ በኋላ የሄዱት ወደሚያውቁት የስግደት ዓይነት ነው። ከዓመታት በኋላ ግን የቤተ መቅደሱ በ70 ዓ.ም. መፍረስ እንኳን ስግደታቸውን ሊያግደው ባልቻለበት ሁኔታ ግንዛቤያቸው አደገ።

# መጣጥፎች

# 1

# ወንጌላት የማዛመድ ሥራ መርሖችና ችግሮች

ወንጌላትን እያዛመዱ ማጥናት ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት። ስለተመሳሳይ ሁነቶች ያሉ መረጃዎች ሁሉ፥ ቃለ ልውውጦች ወይም ጭውውቶችና ንግግሮች አንድ ገጽ ላይ ጎን ለጎን ሰፍረዋል። ወንጌላት ውስጥ ያሉትና የተለያዩ ሁኔታዎችን የሚገልጡት ትረካዎች ሁሉ ሊሆኑ ይችላል ተብሎ በሚገመተው አኳኋን በቅደም ተከተል ተገልጠዋል። ስለሆነም አንባቢው ኢየሱስ ከመጸነሱ ጀምሮ ከትንሣኤ በኋላ እስከነበረው አገልግሎቱ ድረስ ስላለው የሕይወቱ ጉዞ ጠቅላላ ምልከታ ሊኖረው ይችላል። ይህ ለብዙ አንባቢያን ታላቅ ጥቅም ያለው አዲስ ልምምድ ይሆናል።

ይሁን እንጂ፥ ይህ ተዛምዶ ለመጀመሪያ ጊዜ በጥንቃቄ ሲነበብ፥ በተለይ የወንጌላቱን እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነትና እውነተኛነት ለተቀበለ ሰው ግር የሚያሰኝ ይሆን ይሆናል። ምንም እንኳን አራት ፍጹም ተመሳሳይነት የሌላቸው ወንጌላት የመኖራቸውን እውነት አንባቢያን ቢገነዘቡ፥ ብዙዎቹ የእውነቱን ምንነት አልመረመሩም። የወንጌላትን ተዛምዶ የሚያነብ ሰው ግን ልዩነቶቹን ልብ ማለቱ የግድ ነው። የኢየሱስ ገለጣዎች አንዳንዴ እንደሚለያዩ አንባቢው ይረዳል። አንድ ወንጌላዊ በአንድ ውይይት፥ አባባል ወይም ንግግር ላይ የሚያቀርበው ዘገባ ከሞላ ጎደል ሌላው ወንጌላዊ ከሚያቀርበው ይልቅ የተሟላ ይሆን ይሆናል። በገለጣው ሰዋሰዋዊ አወቃቀር ልዩነቶች ይኖሩ ይሆናል። አንዳንድ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ባላቸው ቃላት ሊተኩ፥ የግሦች አረባብ ሊቀየር፥ ስሞች በተውላጠ ስሞች ሊተኩ ይችላሉ። በገለጣ ቅደም ተከተል ረገድም ልዩነት ይኖር ይሆናል። በሚቀርበው ዘገባ የሚታየው ልዩነት አንዳንዴ እርስ በርሱ የሚቃረን ሊመስልም ይችላል። አልፎ አልፎም አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ አባባሎች በአገባባቸው መሠረት ሲታዩ፥ ፍጹም የማይገናኙ ሁኔታዎችን የሚያመለክቱ ይመስሉ ይሆናል። በማቴዎስና በሉቃስ በተመዘገቡት ብጹአን መካከል የጎሉ ልዩነቶች አሉ። ታዲያ የትኛው ዘገባ ነው ትክክሉ? ሁለቱም ትክክል ናቸው? የልዩነቶቹ ምክንያት እንዴት ነው የሚታወቀው?

በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው የኢየሱስን ተግባራት በሚያነብበት ጊዜ ተመሳሳይ ሁነቶች የተደረጉት በተለያዩ መንገዶች መሆኑን ይረዳል። ሁነቶቹ የተለያዩ ናቸው ወይስ ተመሳሳይ ሆነው ሳለ በተሳሳተ ሁኔታ ተመዘገቡ? አንድ ተመሳሳይ ለሆነ ነገር አንዳንዴ ሌላ ወንጌል ውስጥ በተለየ ሁኔታ ተመዝግቦ መገኘቱ፥ ሁኔታውን ይበልጥ አወሳስቦታል። አንዳንዴ ደግሞ ተመሳሳይ ለሆነ ነገር ብዙ የተለያዩ ዝርዝር ገለጣዎች ተሰጥተዋል። እነዚህ ዝርዝር ገለጣዎችም አንዳንዴ የልዩነት ሁኔታ ይታይባቸው ይሆናል። የወንጌላት ጸሐፊዎች ተመሳሳይ ሁኔታዎችን አለመመዝገባቸው ጥቂት አንባቢዎችን ያስደንቅ ይሆናል።

ከነዚህ ክስተቶች ሳቢያ የሚነሡ ጥያቄዎች ግልጥና ቁም ነገር ያዘሉ ናቸው። እነዚህ ክስተቶች የወንጌላትን ታሪክ እውነትነት ዝቅ ያደርጉታል? ታሪካዊ ተዓማኒነታቸውስ ዘላቂነት ያለው ነው? በወንጌል እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነትና ስሕተት አልባነት ላይ የሚያስከትሉት ጥያቄ ይኖራል? ወይስ ወንጌል እስትንፋሰ-

እግዚአብሔር ነው የሚለውን መሠረታዊ ግንዛቤ በማያወላውል ሁኔታ ያረጋግጣሉ? አንድ እርግጠኛ የሚመስል ነገር አለ፤ ይኸውም የወንጌል ዘጋቢዎች ትክክለኞች ባለመሆን፥ የተሳሳቱና የሚቃረኑ ነገሮችን በማቅረብ በደለኞች ሆነው ከተገኙ፥ የወንጌሉ ተአማኒነትና እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት ያጠራጥራል የሚለው ነው።

ወንጌላትን እያነጻጸሩ በማንበብ ጊዜ ለሚነሡ የተዛምዶ ችግሮች ሁሉ በነዚህ የግርጌ ማስታወሻዎች መልስ መስጠቱ የሚቻል ወይም የሚያስፈልግ አይደለም። የዚህ ተዛምዶ አዘጋጆች ግን ወንጌል ታሪካዊ እውነትነት ያለውና እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ለመሆኑ የጸና እምነት አላቸው። በዘገባ ወይም በመጻፍ ጊዜ አንዳንድ የተፈጥሮ እውቀት ደንቦች በሥራ ላይ ከዋሉ፥ ቃሉን በመፍታት ጊዜ ብዙዎቹ የተዛምዶ ችግሮች በበቂ ሁኔታ እንደሚፈቱም ያምናሉ። ቀሪዎቹ ችግሮች፥ ምንም እንኳ ቁርጥ ያለ መፍትሔ ለመስጠት ስለእነሱ ይበልጥ መረጃ ማግኘቱ የሚረዳ ቢሆን፥ ተገቢው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

የኢየሱስ ንግግሮች የተዘገቡበትን ሁኔታ በተመለከተ በተለይ አንዳንድ አጠቃላይ አመለካከቶች ተግባራዊ ይሆናሉ። ኢየሱስ በጊዜው የነበሩ ብዙ ሰዎች ያደርጉ እንደነበረው ሦስት ቋንቋዎችን ይናገር እንደነበር ይገመታል (መጣጥፍ 2ትን ይመልከቱ)። በብዙ ሁኔታ የአንድ ሰው ቃል ሲመዘገብ ያ ቃል የጽሑፉ መነሻ ከሆነው አረማውኛ (የሶርያ ቋንቋ) ወይም ከእብራይስጥ የተተረጎመ መሆኑ መረሳት የለበትም። በትርጉም ሥራ ጊዜ አንዳንድ ልዩነቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ በመተርጎም ጊዜ ቁርጥ ያለና የተወሰነ አሠራር ስለሌለው ልዩነቱ መኖሩም ተገቢ ነው። እንደውም ወንጌላውያን አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ የተናገረውን፥ ቃል በቃል አለመተርጎሙ ለዓላማቸው የሚስማማ መሆኑን ያምናሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸው ቁም ነገሮች ለታለሙለት አንባቢ በታማኝነት፥ በትክክልና በሚገባው ቋንቋ እስከተላለፉ ድረስ ይህ አባባላቸው ስህተት አይደለም። የኢየሱስ ንግግሮች ሲገለጡ አንዳንዴ የነጻ ትርጉም ዘዴ ሥራ ላይ ይውል ይሆናል። ይህ የሚሆነው ነጻ ትርጉም ዋናው ቋንቋ በሚነገርበት ጊዜ በምልክት፥ በእንቅስቃሴና በአገላለጥ የተባሉ ነገሮችን በመግለጥ ለመልእክቱ ኃይል ስለሚሰጠው ነው።

የኢየሱስን ንግግር በነጻ ትርጉም ቃል በቃል ከመተርጎም ሳቢያ ከሚመጡ ልዩነቶች ሌላ ልብ ሊባሉ የሚገባቸው ሌሎች ቁም ነገሮችም አሉ። ዘመናዊው የአጻጻፍ ዘዴ ቀጥተኛና እቻ ጥቅሶችን ለማመልከት በተለያዩ አሠራሮች ይጠቀማል። በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የሠፈሩ ቃላት የተናጋሪው ቀጥተኛ ንግግሮች ናቸው። ምንም እንኳ ጥቅሶቹ የዋናው ጥቅስ አካል ባይሆኑ እነሱን ግልጥ ለማድረግ በአቅራቢያው የተጨመሩ ቃላትን ለማመልከት ቅንፎች በአገልግሎት ላይ ውለዋል። ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ ወይም በተለያዩ ጊዜያት የተነገሩ ጥቅሶችን ለማመልከት ደግሞ በግርጌ ማስታወሻዎች መገልገል ያስፈልግ ይሆናል። የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ጸሐፊዎች ከነዚህ ምልክቶች አንዱ እንኳን አልነበሯቸውም። በመሆኑም ያልነበሩ ምልክቶችን እንደነበሩ ቆጥሮ ደረጃውን የጠበቀ ሥነ ጽሑፍ ከነሱ መጠበቅ ስሕተት ነው።

ከዚህም በላይ ዘመናዊው የጥቅስ ደንብ፥ የቃል ንግግሮችን በትክክል ለመመዝገብ መቅረጸ ድምጽ መጠቀም ያስፈልገው ይሆናል። ጥንታውያን ጸሐፍት መቅረጸ ድምፅ አልነበራቸውም። በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግን አሳጥሮ የመጻፍ

ጥበብ (አጭር ጽሕፈት) በስፋት በሥራ ላይ ውሎ ነበር። ነገሮችን በመዝገብ የመያዝ ልምድ የነበረው ቀራጩ ማቴዎስ ይህ እውቀት ይኖረው ይሆናል። የክርስቶስን ድርጊቶችና ንግግሮች መዝግቧል የሚል አሳብም አለ። ይህን በማድረግም የወንጌላት መዝጋቢዎችን ጨምሮ የቀድሞ ክርስቲያን ጸሐፊዎች ልምድ የሚገበዩበትን መነሻ ፈጥሯል። በወንጌላት መካከል ያለውን አስደናቂ ተዛምዶ ይህ ሁኔታ በከፊል ይገልጠዋል። ያም ቢባል አሠራሩ ልዩነቶችን ያጠፋል ማለት አይደለም። ምክንያቱም ከብዙ ሰዎች መካከል ይህ ልምድ የሚገኝበትን የመነሻ ባሕል የፈጠረ እርሱ ብቻ ነበር።

እነዚህን አጠቃላይ ግንዛቤዎች በአእምሮ በመያዝ ነው አንድ ሰው ኢየሱስ ወይም ሌሎች ሰዎች የተናገሯቸው ነገሮች፥ ትክክለኛነት ይጎድላቸዋል የሚሉትን የተለያዩ ንድፈ አሳቦች መመርመር የሚኖርበት። ይህ ተገቢ አባባል ነውን? በፍጹም አይደለም። ወንጌላት ትክክለኛነት የሚጎድላቸው ሊባሉ አይገባም። ምክንያቱም ተግባራዊ የሚሆኑና የወንጌላቱን ትክክለኛነት የሚያረጋግጡ ቢያንስ ሁለት አማራጮች አሉ።

1. አንደኛው መንገድ ጸሐፊዎቹ በኋለኛው ዘመን ከዳበረው ትክክለኛ የቃል ገለጣ ደረጃ ጋር የግድ መስማማት ወይም ያን መከተል ያልነበረባቸው መሆኑን መረዳት ነው። ይህ ገለጣ የኢየሱስን ንግግር ቃል በቃል በጽሑፍ ማስቀመጥን ሁልጊዜ እንደ ዋና ጉዳይ አይመለከትም። ይልቁንም የወንጌላውያኑ ቃላት ኢየሱስ የተናገራቸውን እውነቶች ይገልጣሉ? የሚለው ነው ዋናው ቁም ነገር። ኢየሱስ የተናገራቸውና በተለያዩ ወንጌላውያን የቀረቡት ገለጣዎች በትርጉማቸው አንዱ ከሌላው ይስማማሉ? የሚለውም ሌላ ጥያቄ ነው። መልሱ አዎ ከሆነ፥ የገለጣዎቹ ትክክለኛነት አያጠራጥርም።

በተግባር ሲታይ ይህን የመሰለው ሌሎች የተናገሩትን በቃል የመግለጡ ዘዴ አሁንም ይሠራበታል። በጥንቃቄ እስከተሠራበት ድረስ የተባለውን ነገር እውነተኛነት ማንም አይጠራጠርም። የሌላን ሰው ንግግር ቃል በቃል የመድገሙ ሁኔታ የተለመደ ወይም የሚቻል አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ቃላትን ወይም አንቀጽን ሁሉ ደግሞ መናገሩ አዳጋች ነው። አንድ ሰው ከአንድ ተራ ውይይት እንዲወጡ የሚጠብቃቸው ጠቃሚ ንግግሮች፥ ዋና አሳቦችን፥ ዋና ዋና ጉዳዮችን፥ ከአንዱ ጉዳይ ወደ ሌላው የሚደረገውን ሽግግር ጨምሮ የውይይቱ አጠቃላይ አቅጣጫ ናቸው። ምንም እንኳ የተለያዩ ገለጣዎች ከነዚህ ሁኔታዎች ጋር እንዲስማሙ የሚጠበቅ ቢሆን፥ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ሲገባ ግን የተናጋሪዎችን ስሜትና ዓላማ የሚያንጸባርቁ ልዩነቶች እንደሚኖሩ ይጠበቃል። በተራ ውይይት ወቅት የሌላን ሰው ንግግር የሚገልጥ አንድ ሰው፥ ሰዎችን ቢለውጥ፥ ስምን በተውላጠ ስም ቢቀይር ወይም ተገላቢጦሹን ቢያደርግ፥ የቃላቱን የጊዜ ገለጣ፥ የግሦችን ድምጸት ወይም ሁኔታ ለውጦ ቢያቀርብ፥ ተመሳሳይ ነገሮችን ቢተካ የንግግሩን እውነትነት መጠራጠር ተገቢ አይደለም። ቃላትን መምረጥ ጠቃሚ ቢሆንም፥ ለማለት የተፈለገ ነገር በተለያዩ መንገዶች ሊገለጥ ይችላል። የቃላት እስትንፋሰ እግዚአብሔር መሆን፥ እውነት የሚገለጠው በአንድ መንገድ ብቻ ነው ሊያሰኝ አይችልም። ይልቁንም መንፈስ ቅዱስ በሰዎች በኩል የተናገረውና ቃል በቃል የተገለጠው ንግግር እውነት መሆኑን ነው የሚያመለክተው።

2. በአንድ ንግግር ውስጥ የተለያዩ ገለጣዎች ቢኖሩም እንኳ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት የመከላከያው ሁለተኛ አማራጭ የሚመሠረተው፥ ገለጣዎቹ የኢየሱስና የሌሎቹ ሰዎች የቃል ንግግሮች ያሉባቸው በመሆናቸው ላይ ነው። ግሪክኛውን ቋንቋ በመጠቀም ጊዜ መነሻ የሆነው ምክንያት ይህ ይሆናል። የኢየሱስን አስተምህሮ በአጭር አጻጻፍ የመዘገቡ ሰዎች፥ ዋናዎቹን ቃላት ለመያዝ ሲሉ የተጠቀሙበት ዘዴ ይህ መሆኑ አያጠራጥርም። በተጨማሪም ከአይሁድ መካከል የሥለጠኑና ከፍተኛ የማስታወስ ችሎታ ያላቸው ሰዎች በጊዜው መኖራቸው ግንዛቤ ሊሰጠው ይገባል። እነዚህ ሰዎች በሃያኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት ምዕራባውያን ይልቅ ዝርዝር ጉዳዮችን የማስታወስ ችሎታ የነበራቸው መሆኑ በአጠቃላይ ታምኖበታል።

አጭር አጻጻፍንና ትውስታን ከመጠቀም ባሻገር፥ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃላት ወደ ሰዎች አእምሮ በማምጣት ያከናወነው ተግባርም ግንዛቤ ሊሰጠው ይገባል። ኢየሱስ ረዳት ስለሆነው መንፈስ ቅዱስ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ "አብ በስሜ የሚልከውን ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፥ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል" (ዮሐ. 14፡26)። መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላሉና በቃል ለተነገሩ ሌሎች ክፍሎች ምዝገባ ምሪት ከሰጠ፥ ለወንጌላትም ይህንኑ ማድረጉ እርግጥ ነው።

አንድ ሰው በዚህ መንገድ ቢጠቀም፥ በተመሳሳይ ዘገባዎች ወይም ውይይቶች መካከል ያሉ ልዩነቶች የተገለጡት፥ የትኛውም ወንጌል ቢሆን በአንድ ሁኔታ የተነገሩ ወይም የተከናወኑ ድርጊቶችን ሁሉ ያልመዘገበ መሆኑን በመረዳት መሆኑን ይገነዘባል። እንደውም ማንኛውም የተመሳሳይ ጉዳይ ቅንብር ያንድን ንግግር ወይም ውይይት ዝርዝር ነገር የመዘገበ መሆኑ አጠራጣሪ ነው። ክርስቶስ አንዳንድ ትምህርቶቹን በተለያዩ አጋጣሚዎች ጥቂቱ ለየት ባለ ሁኔታ የደጋገማቸው መሆኑ ጥርጥር የለውም። በአንድ አጋጣሚ ብቻም ቢሆን ይህን መደጋገም ተጠቅሞበት ይሆናል። በመሆኑም በተለያየ ሁኔታ በጥቂቱ የተገለጡ ተመሳሳይ ነገሮች ወይም ሁነቶች፥ በአንድ አጋጣሚ የተከናወኑና በተለያዩ መንገዶች የተገለጡ የአንድ ንግግር ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። እያንዳንዱም ጸሐፊ ለሱ የሚሆን ገለጣን እየመረጠ የዘገበ መሆኑን ያስረዳሉ። የዚህ አባባል ናሙና የሚሆነው ማቴዎስ፥ "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብጹዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና" (ማቴ. 5፡3) የሚለው ሲሆን፥ ይህንኑ አባባል ሉቃስ እንዲህ በማለት ገልጦታል፦ "እናንተ ድሆች ብጹዓን ናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ ነውና" (ሉቃስ 6፡20)። ኢየሱስ ይህን የብፁዕነት ቃል በተራራው ስብከቱ በተለያየ አቀራረብ ገልጦት ይሆናል። እንዲያ ከሆነ መጀመሪያ ስለ ሦስተኛ ቁጥር ወይም ሰው ተናገረ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ስለ ሁለተኛ ቁጥር (እናንተ ብሎ) ተናገረ፥ እና መንግሥተ ሰማያትን በሁለት አርእስት ጠቀሰው። በአንደኛው ንግግሩ ድኅነትን "በመንፈስ" በማለት ሲያብራራው፥ በሌላው ግን ይህን አላደረገም። በመሆኑም ከሁለቱ ወንጌላት የትኛውም ቢሆን ሙሉውን መልእክት እንዳልመዘገበ ስለምንረዳ፥ ይህ ገለጣ በጣም ይታመናል።

ስለ ሰናፍጭ ዛፍ የተነገረው ምሳሌ (ማቴ. 13፡32፤ ማር. 4፡32) ኢየሱስ በአንድ አጋጣሚ እንዴት አንድን ነገር ጥቂት ለየት ባለ መንገድ እንደደጋገመ ያመለክታል። በማቴዎስ ዘገባ መሠረት፥ የሰማይ ወፎች "በቅርንጫፎችዋ"

ይሰፍራሉ። በማርቆስ ዘገባ መሠረት ግን ወፎቹ "በጥላዋ" ይሰፍራሉ። ኢየሱስ የተናገረው የትኛውን ነው? ሁለቱንም ተናግሯል ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ አለ። እንደገና በማቴዎስ ገለጣ መሠረት በደብረዘይት ተራራ ስብከቱ ኢየሱስ ወደፊት የሚነሱ ሐሰተኞች "እኔ ክርስቶስ ነኝ" (ማቴ. 24፥5) እያሉ ይመጣሉ ማለቱን ነው የገለጠው። ማርቆስና ሉቃስ ግን ሐሰተኛው "እኔ ነኝ" የሚል መሆኑን እንደገለጠ ነው የጠቀሱት (ማር. 13፥6፤ ሉቃስ 21፥8)። ይህን የመሰሉ አነስተኛ ልዩነቶች ብዙ ናቸው።

በሌሎች ሥፍራዎች ያሉት ልዩነቶችም ቀላል አይደሉም። "ስለዚህ" (ማቴ. 13፥13) በሚለውና፥ "እንዳይሰረይላቸው" (ማር. 4፥12) በሚለው ቃላት መካከል ያለው ልዩነት ትርጉምን በተመለከተ የሚጠቁመው ሰፊ ነገር አለ። ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ የተናገረው ተቃዋሚዎቹ ቀድሞውኑ በመንፈስ ዕውሮች በመሆናቸው ነው ወይስ የታወሩ እንዲሆኑ? ምናልባት ሁለቱንም ይሆናል የተናገረው። በማቴዎስ ገለጣ፥ ቃላቱ የሚናገሩት ስለኢየሱስ ጠላቶች ሲሆን፥ በሌሎቹ ግን ስለ ደቀ መዛሙርቱ ነው። እዚህም የትርጉሙ ልዩነት የጎላ ነው። እንዲህ የጎሉ ልዩነቶች አዘውትረው ስለሚገጥሙ፥ መፍትሔያቸው ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በአንድ ምክንያት ተመሳሳይ መሠረታዊ እውነቶችን ደጋግሞ የተናገረ መሆኑን መረዳቱ ነው።

በዚህ መሠረት እንግዲህ የተመሳሳይ ጉዳዮች ገለጣ ትክክል አለመሆን መሠረታዊ ነገር አለመሆኑን ለማሳየት ከሁለቱ አማራጮች አንዱ ወይም ሁለቱ በጣምራ በቂ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ያሉን ኢየሱስ የተናገራቸው ትክክለኛ ቃላት ወይም አስተዋጽኦዎቹ ናቸው ብሎ በትክክል ለመናገር ያዳግታል። ከሁለቱም የሆነ ነው ያለን ብለን ለመናገር እንችል ይሆናል። ለቀረበው ቃል እውነተኛነት ጠቃሚው ጉዳይ፥ የተጻፈውን ነገር በመምራት ረገድ መንፈስ ቅዱስ የነበረውን ሚና መገንዘቡ ነው። ወንጌላት በብዙ ሁኔታዎች እርስ በርሳቸው ከመለያየት ይልቅ አንድ መሆናቸውን ከዚህ መገንዘቡ አያዳግትም።

በተለያየ ቅደም ተከተል በወንጌላውያን ስለቀረቡ ሁኔታዎች ታዲያ ምን ይባል? በመጀመሪያ በሁለት ሁኔታዎች መሠረት፥ ማለት በተወሰነ ክልልና በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲሁም ሁለቱን በብዙ ረገድ በማገናኘት አንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይቻላል። የገለጣዎቹ ዋና ነገሮች ከተለያዩ ግን የአንድ ክንውን ዘገባዎች ሆነው ሊወሰዱ አይገባም። ስለዚህ የቅደም ተከተል ልዩነት፥ በአንድ ወሳኝ ጊዜ የሆኑና የተለያዩ ሁነቶችን በዝርዝር የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ወንጌላት በቃላትም ሆነ በሁነት ያላቸውን በተመሳሳይ ቅደም ተከተል አለማቅረባቸው ችግር ሊሆን የሚችለው፥ ጸሐፊዎቹ አንድ ወጥ የሆነ የጊዜ ቅደም ተከተል መከተል ነበረባቸው የሚል አስተሳሰብ ሲኖር፥ ወይም የታሪኩን ቅደም ተከተል ሙሉ በሙሉ ጠብቀው እንደገና ያናጉታል የሚል እምነት ሲኖር ነው። የመጀመሪያው እምነት ተገቢ ያለመሆኑ ግልጥ ሲሆን፥ ሁለተኛው ሊሆን የሚችል አይደለም። ምንም እንኳ የቅደም ተከተል ቅንብር እጅጉን የሚጠበቅ ቢሆን፥ ለጥሩ ዘገባ ቅድመ ሁኔታ ሊሆን አይችልም። ጸሐፊዎቹ ወይም ደራሲዎቹ ለዓላማቸው የሚጠቅም መስሎ ከታያቸው፥ የሚጽፉትን ነገር በቅደም ተከተል ከማድረግ ይልቅ በጉዳዩ የማቀናበር ነጻነት አላቸው። ይህ ደራሲዎች የሚገለገሉበት ነጻነት፥ በወንጌላት ጽሑፍ ብዙ የቅደም

ተከተል ልዩነቶች ያስከትላል። ሁኔታው የወንጌላትን ጽሑፍ በቅደም ተከተል ለማዛመድ ለሚሻ ሰው ችግር ይፈጥርበታል። የትኛው ወንጌላዊ ነው ያን የቅደም ተከተል ሥርዓት ተከትሎ የጻፈ? አንድን ጊዜ ወይም ቦታ ሲጠቀስ የሚፈለገውን ነገር ይጠቁም ይሆናል፤ ሁሌ የሚሆን ግን አይደለም። ይሁን እንጂ ይህ የደራሲው ሳይሆን ጽሑፉን የሚያዛምደው ሰው ችግር ነው።

በመጨረሻም የወንጌላትን ተዛምዶ በጥንቃቄ የሚያነብ አንድ ሰው ሁነቶችን በመዘርዝር ጊዜ፥ በሁለት ወይም ሦስት ወንጌላውያን መካከል ልዩነት መኖሩን ልብ ይላል። ይህን የመሳሰሉትን ጥቂት የሁነት ምሳሌዎችን በመገንዘብ እውነት የሆነ ወይም የሚመስል ምንም ልዩነት ያለመኖሩንም ይረዳል። በብዙ ሁኔታ ይህ መፍትሔ ባይሆንም፥ መፍትሔውን ማግኘቱ ግን አይከብድም። አንዳንድ ጸሐፊዎች አንድን ነገር በሚተርኩበት ጊዜ የተባለውን፥ የሆነውንና ተከታታይ ሁኔታዎችን በመግለጥ ረገድ በብዙ ነጥቦች መለያየታቸው የሚሆንና ሊሆን የሚችል ነገር ነው።

ይህ እውነት በዕለት ተዕለት ልምምድ የተረጋገጠ ነው። በአንድ የጨዋታ ሜዳ የተለያየ አቅጣጫ አጫዋች ዳኞች የሚመደቡት የተለያዩ ነገሮችን ይመለከቱ ዘንድ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በጎዳና ማቋረጫዎች ላይ የተመደቡ ብልህና ረጋ ያሉ ተመልካቾች ስለ አንድ የተሽከርካሪ አደጋ የተመለከቱትን የሚገልጡት በተለያየ መንገድ ነው። በዚሁ አኳኋን በአንድ ስብሰባ ላይ የተገኙ ብቁዕ ጋዜጠኞች ስለ ጉባኤው በሚገልጡበት ጊዜ ዘገባቸው ይለያያል። ለምን? ምክንያቱም እያንዳንዱ ጋዜጠኛ የሚገልጠው እሱ ከተመለከተው አንጻር ወይም በተጠቀመበት የመረጃ ምንጭ ላይ በመመሥረት ስለሚሆን ነው። እያንዳንዱ ተራኪ የሚገልጠውን ነገር የሚያቀርበው፥ ከዓላማው ጋር በሚስማማ አኳኋን በማቀናበር ነው። አንደኛው ተመልካች የገለጠውን ሌላው በሁለቱም ወገን ሐሰት በማይታይበት ሁኔታ በዝምታ ያልፈው ይሆናል። በጣም የተቀራረበ ተመሳሳይነት ያላቸው ገለጣዎች ቢኖሩ ግን፥ በሥራው ግብረአበርነት ወይም አብሮነት መኖሩን የሚያስጠረጥር ሁኔታ ይፈጠራል።

ምንም እንኳን የወንጌላት ገለጣዎች ላይ ላዩን እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ቢመስሉ፥ ጸሐፊዎች ያቀረቧቸው የተለያዩ ምልከታዎችና ምርጫዎች እራሳቸው የትክክለኛነትና ተአማኒነት ምልክቶች ናቸው። በዚህ ምሳሌ መሠረት ተቃርኖዎቹ የሚመስሉ እንጂ በእርግጥ ያሉ አይደሉም። በጥንቃቄ መፈተሽ በጽሑፉ ውስጥ ያሉ የሚመስሉ ተቃርኖዎችን ለመፍታትና ገለጣዎቹን ለማዛመድ ይረዳል። አንድ ሰው ግልጥና አሳማኝ መፍትሔዎች የማይገኙላቸው የሚመስሉ ተቃርኖዎች ቢገጥሙት እንኳ ይህን ለመቀበል መገፋፋት የለበትም። የሚቃረኑ በሚመስሉ ገለጣዎች መካከል ያሉትን እውነተኛና ዋና ዋና ተዛምዶዎች ለማቅረብ የሚያስችል በቂ መግለጫ የለም።

እነዚህ ግንዛቤዎች፥ በወንጌላት ተዛምዶ ንጽጽር ጥናት ወቅት የሚገጥሙ ችግሮችን ሁሉ አያስወግዱም። ይሁን እንጂ ለሌላ ጉዳዮች ተገቢ እና እውነት እንደመሆናቸው፥ በወንጌላት ጥናትም ጠቃሚ መመሪያዎች ናቸው። አብዛኛዎቹን የማዛመድ ችግሮች በአጥጋቢ ሁኔታ ይፈታሉ። አጥጋቢ መረጃዊ መፍትሔ የሌላቸው ጉዳዮች ሲገጥሙ፥ ያልሆነ ትርጉም ለመስጠት ከመጣር ይልቅ ነገሩን እንዳለ መተው ይሻላል። የእጅ ጽሑፍ ወደ ሌላ በሚገለጥበት ጊዜ የጽሑፍ መዛባት ይፈጸም ይሆናል፤ ይህ የስሕተት ቀላል ምክንያት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋስ

እግዚአብሔር መሆኑን የሚያምን ተማሪ እግዚአብሔር ቃል ውስጥ ላለ ችግር ሁሉ መፍትሔ እንዲፈልግ ግዴታ የለበትም። ወንጌላት ተአማኒ መሆናቸው በተደጋጋሚ ከመረጋገጡ አንጻር፥ አንድ ሰው ወንጌላት እርስ በራሳቸው የሚቃረኑበትን መረጃ አቀርባለሁ ቢል አጉል ድፍረት አይሆንም? ታሪካዊ ገለጣዎች የሚይዙትን መረጃዎች መምረጡ የግድ አስፈላጊ ነው። የወንጌላት ጸሐፊዎች ታሪክ ሲዘግቡ አንድ ቀን፥ አንድ ሰው ጽሑፎቻቸውን ያዛምዳቸው ይሆናል ብለው እያሰቡ አልነበረም። ታሪካዊ ዘገባቸውን ለመጠራጠር ምንም የሚታመን ምክንያት የለንም። የዘገባ ዓላማቸው በጣም የተለያየ ነበር። በቀላሉ የተዛመዱ ታሪኮችን ለመጻፍ ቢፈልጉና፥ አድርገውት ቢሆን ኑሮ፥ የአሁኑን የማዛመድ ተግባር እጅግ ያቀሉት ነበር። ይህን ማድረጉ ግን መንፈስ ቅዱስ ከመራቸው አቅጣጫ ያዛባቸውና፥ የወንጌላትን የአጻጻፍ ባሕርይ እጅግ ይቀይረው ይሆናል። የወንጌላት ባሕርይም ይጠፋና የምሥራቹ ቃል ልዩ ልዩ ገለጣዎች ውጤት አልባ ይሆኑ ነበር።

# 2

# ኢየሱስ የተናገረባቸው ቋንቋዎች

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የኖሩ ፍልስጤማውያን ይጠቀሙበት የነበረውን ቋንቋ ለማጥናት ሞክረዋል። ኢየሱስ በመጀመሪያ የተናገራቸው ቋንቋዎች፥ እኛ ስለ ወንጌላት አጀማመር ባለን ታሪካዊ መረጃ አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ለምሳሌ ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት ቋንቋ አረማይክ[67] በመሆኑና ወንጌላት የአረማይክን ቃላትና አሳብ በመያዛቸው የወንጌልን እውነተኛነት ያረጋግጣል። በተቃራኒው ደግሞ ኢየሱስ ይናገር የነበረው በሴማዊ ቋንቋ አይደለም ቢባል፥ የቃሉን ሥልጣን ተዓማኒነት ያዛባዋል የሚል ክርክርም አልፎ አልፎ አለ።

የክርክሩ ሁኔታ ምንድነው? ላቲንኛ ፍልስጥኤም ውስጥ በቋንቋነት ማገልገሉ የተለመደ አልነበረም። ይህን ለማለት የሚያስደፍረው፥ የሮማውያን ወታደሮች ምድሪቱን ድል አደረጉ ማለት ላቲንኛ ድል አድርጓል ማለት ባለመሆኑ ነው። ታላቁ እስክንድር ከክርስቶስ ልደት በፊት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተቀዳጀውን ድል በመከተል፥ በግሪኮች ቋንቋና ባሕላዊ እንቅስቃሴ፥ ግሪክኛ ዋነኛው የጋራ መግለገያ ቋንቋ ሆኖ ነበር። የሮማውያን ወረራና ድልም የኀላ ለውጥ አላመጣበትም። በክርስቶስ ዘመን፥ ግሪክኛ በፍልስጥኤም ምድር የነበረው ጠቀሜታ ምን ነበር? ጥቂት የተማሩ ሰዎች የሚጠቀሙበት የባሕልና የንግድ ቋንቋ ነበር፥ ወይስ ተራውም ሰው የሚገለገልበት? ከምሁራን ውጭ ሌሎችም የሚገለገሉበት ከሆነ፥ አጠቃቀሙ ምን ያህል የሰፋ ነበር? የአረማውያን ቋንቋስ ብዙሃኑ ባጠቃላይ የሚገለገሉበት ነበር? ከመካከለኛው ዘመን ወዲህ ያለው አመለካከት፥ ወደ ባቢሎን ከተደረገው ፍልሰት አንስቶ የዕብራይስጥ ቋንቋ ቀስ በቀስ ሕልውናው አከተመና የአረማይክ ቋንቋ በአይሁዳውያን መካከል የዕለት ከዕለት መነጋገሪያ ሆነ የሚል ነው። ይሁን እንጂ የዕብራይስጥ ቋንቋ በእርግጥ ሕይወቱ አክትሞ፥ የአይሁድ ምሁራን የሚገለገሉበት የሃይማኖት ቋንቋ ሆኖ ነበር? ከነዚህ ሦስት ቋንቋዎች አንዱ የበላይነት ነበረው የሚለውን አሳብ የሚደግፉ ሰዎች አልጠፉም። ፍልስጥኤም ውስጥ በአንደኛው ክፍለ ዘመን አይሁዳውያን ሦስቱንም ቋንቋዎች ይገለገሉባቸው ነበር የሚሉ መረጃዎችም ተገኝተዋል።

በቅርቡ በከርሰ-ምድር ቁፋሮ የተገኘው መረጃ ይህን ችግር በመፍታት ረገድ ብዙ ረድቷል። የሙታን አፅም ማሳረፊያዎች ወይም መቃብሮች አንዳንዴ ጽሑፍ ይገኝባቸዋል። መቃብር ውስጥ ወይም ሃውልት ላይ ተጽፈው የተገኙ ቋንቋዎች ጥንት የነበሩ ሰዎች ይናገሯቸው የነበሩ ቋንቋዎች መሆናቸው ተገምቷል። የምድር ቁፋሮ ተመራማሪ የሆነ አንድ ግለሰብ ፍልስጥኤም ውስጥ ያሉትን የመቃብር ሥፍራዎች

---

[67] አረማይክ ጥንት አራም አሁን ደግሞ ሲሪያ የተባለችው ግዛት ቋንቋ ነበር። ቋንቋው ሴማዊ ሲሆን፥ ከዕብራውያን ቋንቋ ጋርም ይዛመዳል። ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓ.ዓ-500 ዓ.ም ድረስ በሶሪያ፥ በባቢሎን፥ በአሦርና በሜሶፖታሚያ የሚነገርም ቋንቋ ነበር። ፊደሎቹም ከዕብራውያን ፊደል ጋር ይመሳሰላሉ።

የብሉይ ኪዳን ግማሹ ክፍል የተጻፈው በአረማይክ ነበር። በአረማይክ የተጻፉ ሥነ-ጽሑፎች በምዕራብ ከግብፅ እስከ ሰሜን ካውካከስ ተራራዎች፥ በምስራቅ ህንድ፥ ቻይናና በደቡብ ዓረብ ውስጥ በሚገኘው ናባታ ግዛት ይገኙ ነበር። አረማይክ ከክርስቶስ ልደት በፊት 550- 450 ዓ.ዓ. ድረስ የፋርስ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ በመሆን አገልግሏል።

በመጠኑ መርምሮ፥ ከሞላ ጎደል በሦስቱም ቋንቋዎች በእኩልነት የተጻፉ መረጃዎችን አግኝቷል።

እነዚህ ሦስት ቋንቋዎች በጊዜው ስለመኖራቸው የቀረበው ይህ ማስረጃ፥ ሙት ባሕር አካባቢ ባሉት ዋሻዎች ውስጥ በተደረገው ቁፋሮ ተጠናክሯል። በዚህ "የደብዳቤዎች ዋሻ" ይጋል ያዲን የተባሉ ሰውና ተባባሪዎቻቸው ከአሥራ አምስት ያላነሱ ደብዳቤዎች አግኝተዋል። ከአርባ የበለጡ ጥንታዊ ውሎች እና ደረሰኞችም ሰብስበዋል። የእነዚህ ማስረጃዎች ዕድሜ፥ ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጨረሻ ዓመታት ባር-ኮክባ የተባለ አይሁዳዊ አመፅ እስካስነሣበት ከ132-135 ዓ.ም. ይደርሳል። ዋሻው ይህ ሰውና ተከታዮቹ ይደበቁበት የነበረ ይመስላል። ደብዳቤዎቹም ወታደራዊና የዕለት ተዕለት ጉዳዮችን የሚገልጡ ሳይሆኑ አይቀርም። ሦስቱ ማለት ግሪክኛ፥ ዕብራይስጥኛ እና አረማይክ ቋንቋዎች በደብዳቤዎቹና በተለያዩ የታሪክ ሰነዶች ውስጥ ተገኝተዋል። እነዚህ ሰዎች ምሁራን አልነበሩም። ቋንቋዎቹን መረዳታቸውና በነሱም መግለገላቸው፥ በፍልስጥኤም ምድር የነበሩ ሰዎች ባጠቃላይ በቋንቋዎቹ መጠቀማቸውን ያመለክታል። ይህ ሁኔታ የዕብራይስጥ ቋንቋ ለአይሁድ ምሁራን ብቻ አለመሆኑን፥ ግሪክኛ ደግሞ የንግድና የባሕል ቋንቋ ብቻ አለመሆኑን ያስገነዝባል። ከአረማውኛ ጋር ሁለቱ ቋንቋዎች ሰው ሁሉ ይጠቀምባቸው የነበሩ ቋንቋዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። ከዚህ በመነሣት ኢየሱስ በሦስቱም ቋንቋዎች በቀላሉ ይናገር ነበር ለማለት ይቻላል።

አድልኦ በሌለበት ሁኔታ ወንጌላትን ማጥናት፥ ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ ያለው የቋንቋ ሁኔታ ይህን የሚመስል መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል። ሮበርት ገንዳሪ የተባሉት ተመራማሪ በከርሰ-ምድር ቁፋሮ ያገኙትን መረጃና የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን በማዛመድ ሦስቱ ቋንቋዎች ያኔ ያገለግሉ እንደነበር አረጋግጠዋል። በግሪክኛ በተጻፉት ወንጌላት ውስጥ የሴም ቋንቋ ከሆነው አረማይክ ወይም ከዕብራይስጥ አባባሎች መገኘታቸው፥ የሴማዊው ቋንቋ በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበረችው ፍልስጥኤም ውስጥ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ውሏል ማለት አይደለም። በብዙ ቋንቋዎች በሚገለገሉ አካባቢዎች በአገላለጥና በቃላት አጠቃቀም ረገድ ቋንቋዎቹ አንዱ በሌላው ውስጥ የመወራረስ ሁኔታ ታይቶባቸዋል። ለምሳሌ በግሪክኛ በተተረጎመው ብሉይ ኪዳን ("ሰፕቱዋጂንት"[68]) ውስጥ፥ የሴማውያን አገላለጥ ዘይቤ በብዛት ይታይበታል። ይህ በጊዜው ተስፋፍቶ የነበረና በብዙ ቋንቋዎች የመጠቀም ልማድ፥ ፍልስጥኤም ውስጥ ይነገር በነበረው ግሪክኛ ላይ ከባድ ተጽእኖ አድርጓል። ግሪክኛ በሴም ቋንቋ ወደሚገለገሉ አካባቢዎች መግባቱ፥ ከዚያ ወዲህ በሥፍራው ይነገር የነበረው ግሪክኛ

---

68 የሰብዓው ሊቃውንት ትርጉም (ሰፕቱዋጂንት) በግሪክኛ ለተተረጎመው የዕብራውያን ብሉይ ኪዳን የተሰጠ ስም ነው። የዚህ ትርጉም እውነተኛ ታሪክ በትክክል አልታወቀም። በሙሴ የተጻፉት አምስት የኦሪት መጻሕፍት በመጀመሪያ የተተረጎሙት፥ ግብፅ ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ285-246 ዓ.ዓ. በነበረው ጊዜ ውስጥ ነበር። እንዲያ የተደረገው ግሪክኛ ተናጋሪ ለሆኑ አይሁዳውያን ጥቅም ነበር። ቀሪው የብሉይ ኪዳን ክፍል ከ117 ዓ.ዓ. በፊት ተተረጎመ። የአዋልድ መጻሕፍት ደግሞ ከ117 ዓ.ዓ. እስከ ክርስቶስ ልደት በነበረው ጊዜ የተተረጎመ መሆኑ ይታወቃል።

የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ትርጉም ሰፕቱዋጂንት በጣም የታወቀ ስለነበር፥ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች፥ በተለይም ሉቃስና ወደ ዕብራውያን መልእክት የጻፈው ግለሰብ ከዚያ ይጠቅሱ ነበር።

ሰፕቱዋጂንት በብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ይህም ዓረብኛን፥ ኮፕቲክን፥ የአርመን ቋንቋን፥ ላቲንኛን፥ ምናልባትም ግዕዝን ያጠቃልላል። ዛሬም በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብሉይ ኪዳን ውስጥ ዋነኛ የመገልገያ ቋንቋ ነው።

የሴምን ቋንቋ ዘይቤና አስተሳሰብ ዘዴዎችን የሚያንጸባርቅ መሆኑን ለመረዳት ምክንያት ይሆናል።

ወንጌላትና የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ፥ ክርስቶስ በምድር በተመላለሰበትና ባስተማረበት ጊዜ ግሪክኛ የጊዜው ቋንቋ መሆኑን ይበልጥ ያረጋግጣሉ። ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ሁለቱ፥ እንድርያስና ፊሊጶስ ስማቸው ግሪክኛ ነበር። ዮሐንስ 12፡20-23 ውስጥ ያለው ቃል ፊሊጶስ፥ እንድርያስና ኢየሱስ ግሪክኛ ይሰሙና ይናገሩ እንደነበር ያመለክታል። ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ዋና የነበረው ጴጥሮስ በዕብራይስጥ ስምዖን፥ በአረማይክ ኬፋ፥ እንዲሁም በግሪክ ጴጥሮስ በሚለው ስም ይጠራ ነበር። ጴጥሮስ፥ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ውስጥ እንደተመለከተው ለቆርኔሊዮስ ቤተሰብ የተናገረውና በስሙ የተሰየሙትን ሁለት መልእክቶች የጻፈው በግሪክኛ ሳይሆን አይቀርም። ያ ገሊላዊ ዓሳ አጥማጅ በግሪክኛ ስም መጠራቱ፥ ግሪክኛ መናገሩና መጻፉ፥ ዝቅተኛ ትምህርት ያላቸው ሰዎች እንኳ ያን ቋንቋ ሊገለገሉበት ይችሉ እንደነበር ያረጋግጣል። በግሪክኛ በተጻፈው የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ውስጥ ኢየሱስ የተለያዩ ሁለት ግሪክኛ ቃላት ተናግሯል። እነዚያም ስለ "ፍቅር" እና "መንጋውን" ስለመጠበቅ የሚገልጡ ነበሩ። ጴጥሮስም "ማወቅ" የሚለውን ቃል ለመግለጥ በሁለት የተለያዩ ቃላት ተጠቅሟል። እነዚህ ጥንድ ቃላት አረማይክና ዕብራይስጥ ውስጥ ልዩነታቸው ጎልቶ አይታይም። በግሪክኛ የተደረገው የቃላት ምልልስ ግን ልዩነት እንዳላቸው ያመለክታል። ስለሆነም በኢየሱስና በጴጥሮስ መካከል ይደረግ የነበረው የንግግር ልውውጥ በግሪክኛ ነበር ለማለት ይቻላል። እንዲሁም ማቴዎስ ወንጌል 16፡18 የተጠቀሱት 'ፔትራ' እና 'ጴጥሮስ' የሚሉት ቃላት ዕብራይስጥና አረማይክ ቋንቋ ውስጥ ልዩነታቸው አይታይም። በግሪክኛ በተደረገው ንግግር ግን ልዩነት እንዳላቸው በተሻለ ሁኔታ ይታያል። ኢየሱስ ግሪካዊት በሆነችው የሲሮፊኒቃዊት ሴት (ማርቆስ 7፡26)፥ ከሮማዊው መቶ አለቃና ከጲላጦስ ጋር የተነጋገረው በግሪክኛ እንደነበር ይገመታል። እስጢፋኖስ (ሐዋ.7) እና ያዕቆብ (ሐዋ.15) በንግግራቸው ከሰፕቱዋጂንት መጥቀሳቸው፥ በግሪክኛ ለመገልገላቸው የሚጠቀስ ማረጋገጫ ነው።

አረማይክ በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበረው የፍልስጥኤም ምድር ሕዝቡ ይናገረው የነበረ ቋንቋ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከዚያ ውጭ ባሉ ምንጮች ተረጋግጧል። ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁሉም የፍልስጥኤም ክልሎች ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያን ቋንቋ አረማይክ መሆኑ ይታወቃል። ወንጌላት ውስጥ የሚታዩት ሴማዊ የአገላለጥ ዘይቤዎች፥ ለዚህ እንደ አጠቃላይ ማረጋገጫ ተቆጥረዋል፤ ይህንንም ወንጌላት ውስጥ በብዛት በሚገኙት የአረማይክ ቃላትና ስሞች ለማየት ይቻላል። ክርስቶስ በዚህ ምድር በነበረ ጊዜ፥ አረማይክ ሕዝቡ የሚጠቀምበት ብቸኛ ቋንቋ ተደርጎ ይታሰብ ነበር። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችና (ዮሐ. 19፡20፤ ሐዋ. 21፡40፤ 22፡25፤ 26፡14)፥ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች 'ዕብራውያን' የሚለውን ቃል በሚጠቀሱበት ጊዜ፥ በእርግጥም 'አረማይክ' የሚለውን ቃል ማለታቸው ነው ብለው አንዳንዶች ያስባሉ።

አረማይክ ከወንጌላት ጋር ተዛምዶ ያለው መሆኑ፥ በፍልስጥኤም የነበሩ ሰዎች ሁሉ ይገለገሉበት የነበረ ብቸኛ ቋንቋ አያሰኘውም። ከዚህ በፊት በግሪክኛ ጥቂት ቃላት ከአረማይክ ቃል በቃል ተወስደዋል ተብሎ ይታሰብ ነበር። አሁን ግን ቢያንስ እነዚህ ጥቂት ቃላት በእርግጥም የአረማይክ ቃላት መሆናቸው ታውቋል (ማቴ. 27፡46፤ ማር. 5፡41፤ 7፡34፤ 14፡36፤ 15፡34)። ከነዚህም ጥቂቶቹ ደግሞ የዕብራይስጥ

ቃላት ነበሩ። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች፥ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ስለ ዕብራይስጥ ቋንቋ በሚጠቅሱበት ጊዜ የዕብራይስጥ ቋንቋን መጠቀማቸው ነበር። በተጨማሪም በዛ ጊዜ የነበሩ የአይሁድ ምሁራን በጽሑፋቸው ዕብራይስጥ ቋንቋን ይጠቀሙ እንደነበር ማረጋገጫ አለ። ይህ ቋንቋ ሙት ቋንቋም አልነበረም። በዚህ ፋንታ ቋንቋው ሕዝቡ የሚጠቀምበት፥ የተለመደ፥ አዳዲስ ቃላት የሚፈጠሩበትና የሕዝቡን የእለት ተእለት ኑሮ የሚገልጥ ቃላት ያለው ቋንቋ ይመስላል። በአይሁድ ምሁራን ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ የዕብራይስጥ ቋንቋ በውይይት መልክ ያገለግል ስለነበር፥ የውይይቱ ዋና ጉዳይ የዕለት ተዕለት ክንውኖችን ጭምር ያካተተ እንጂ ምሁራዊ ጉዳዮችን ብቻ የያዘ አልነበረም። ቁምራን በተባለው ዋሻ ውስጥ በተደረገው ምርምርም በዕብራይስጥኛ የተጻፉ ብዙ ሰነዶች ተገኝተዋል። እነዚህ ሰነዶች የያዟቸው ጉዳዮች በምሁራን ብቻ የተጻፉ ሳይሆኑ፥ በሌሎችም ተራ ሰዎች የተጻፉ ነበሩ። ስለሆነም ሰነዶቹን ማንኛውም ተራ ሰው ሊረዳቸው ይችል ነበር። አንዳንድ ሰዎች አረማይክ ቋንቋ ዕብራይስጥን እንደ ተራ የሕዝብ ቋንቋ ሙሉ በሙሉ በፍጥነት ተክቷል ብለን መጠብቅ የለብንም ብለው ይከራከራሉ። አረማይክ ከመነሻው በንግዱ እንቅስቃሴና በመንግሥት ሥልጣን ደረጃ የነበሩ የአይሁድ ማኅበረሰቦች ይናገሩት ነበር። ቀስ በቀስ የተራውና ያልተማረው ሕዝብ የመናገሪያና የጽሑፍ ቋንቋ ለመሆን በቃ። ዕብራይስጥኛ ግን የተራው ሕዝብ ቋንቋ ሆኖ ነው የኖረው። የመናገሪያ ቋንቋነቱ የመጨረሻ አደጋ የገጠመው፥ የአይሁድ አብዮታውያን ትግል ከ132-135 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት ድል ከተመታ በኋላ ነው።

ከዚያ ወዲህ ግሪክኛ፥ ዕብራይስጥ እና አረማይክ ቋንቋዎች ፍልስጥኤም ምድር ውስጥ ይኖሩ በነበሩ አይሁዳውያን ኢየሱስ እስከመጣ ድረስ የሚረዷቸውና የሚናገሯቸው ቋንቋዎች እንደነበሩ ይገመታል። ከሕዝቡ ስንቱ፥ የትኛውን ቋንቋ ይናገረው ነበር? የሚለውን መገመቱ ያዳግታል። ምናልባት ከነዚህ አንደኛው ቋንቋ ባንድ አካባቢ ከሌሎቹ ይበልጥ ተናጋሪ የነበረው ሊሆን ይችላል። በዚያም ሆነ በዚህ፥ ምድሪቱ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ነበረች። ኢየሱስ በሦስቱም ቋንቋዎች ይናገር ነበር ብሎ ለመናገርም ይቻላል። የዚህ እውነት ማረጋገጫዎችም ወንጌላት ውስጥ አሉ።

# 3

# የክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ቅደም ተከተል

የክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ቅደም ተከተል በሚጠናበት ጊዜ ጥርጣሬ የሚያጠላባቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ። ክርስቶስ የተወለደው በአንድ[69] ዓመተ ምሕረት መሆኑና የሞተው ደግሞ በሠላሳ ዓመተ ምሕረት መሆኑ ይገመታል። ይሁን እንጂ እነዚህ አጠቃላይ አሳቦች ናቸው። የክርስቶስን ልደት እንደመነሻ ነጥብ ለመጠቀም የሚፈልገው ጎርጎሪሳዊ የፈረንጆች የቀን አቆጣጠር ከታወቀበት ከ525 ዓ.ም. ጀምሮ ስሕተት ነበረበት። በእንግሊዝኛ "ኤ.ዲ." የሚለው ምሕፃረ ቃል የተገኘው በላቲንኛ "አኖዳሚኖ" ከሚለው ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም "ከክርስቶስ ልደት በኋላ" ማለት ነው። ነገር ግን በኋላ የተገኙት ማስረጃዎች እንደገለጡት ኢየሱስ የተወለደው ከአንድ ዓመተ ምሕረት በፊት ነበር።

ምንም እንኳን ቀናትን በተመለከተ ፍጹም እርግጠኛ መሆን የማይቻል ቢሆን፥ ኢየሱስ በምድር የኖረበትን ጊዜ በተመለከተ ግን ብዙ ለማለት ይቻላል። የበለጠ ዝርዝር መረጃ ለመስጠት ይቻል ዘንድ አንዳንድ የተመረጡ ሁነቶችና ገለጣዎች ለውይይት ይቀርባሉ።

## የታላቁ ሄሮድስ ሞት

በማቴዎስ ወንጌል 2፡1 እና በሉቃስ 1፡5 መሠረት ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ፥ ታላቁ ሄሮድስ የአይሁዳውያን ንጉሥ ነበር። በአንዳንድ ሌሎች ምንጮች እሁን እንደተገለጠው ደግሞ፥ ሄሮድስ የሞተው ከክርስቶስ ልደት አራት ዓመት ቀደም ብሎ ነበር። በአይሁድ አቆጣጠር የኒሳን ወር አንደኛው ቀን እንዳለፈ ማለት ነው። ኢየሱስ የተወለደው፥ ከዚያ ቀደም ሲል በነበሩት ሁለት ዓመታት ውስጥ መሆን አለበት። ምክንያቱም ሄሮድስ ኮከቡ የታየበትን ዘመን ከተረዳ በኋላ ነበር (ማቴ. 2፡7) ሁለት ዓመትና ከዚያ በታች የሆኑ ወንድ ሕፃናት ሁሉ እንዲገደሉ ትእዛዝ የሰጠው (ማቴ. 2፡16)። ስለዚህ ኢየሱስ የተወለደው፥ በ6 እና በ4 ዓመተ ዓለም መካከል መሆን አለበት።

## በአውግስጦስ ቄሣር ዘመን የተከናወነው የሕዝብ ቆጠራ

ሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 2፡1-2 ባለው ክፍል የተጻፈው ቃል ክርስቶስ የተወለደው በሮማዊው ገዥ በአውግስጦስ ቄሣር ግዛት ውስጥ መሆኑን ይገልጣል። ከዚሁ ጋር ምንም እንኳን አንዳንዶች ሉቃስ የሕዝብ ቆጠራው የተከናወነው ከዚህ ሰው አገዛዝ በፊት ያለ ቢመስላቸው፥ የክርስቶስ ልደት ሶሪያ ውስጥ ከነበረው ቄሬኔዎስ ከተባለው ሮማዊ ገዢ አስተዳደር ጋርም ሳያገናኘው አይቀርም። አውግስጦስ ቄሣር ከክርስቶስ ልደት በፊት 30 ዓመት ቀደም ብሎ በመጀመር እስከ 14 ዓ.ም. በዘለቀው የአገዛዝ ዘመኑ የሕዝብ ቆጠራ ሥርዓት አውጥቶ ነበር። ያንን ነው ሉቃስ በምዕራፍ 2፡1 ውስጥ የሚጠቅሰው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሚወለድበት ጊዜ ዮሴፍና ማርያም ወደ ቤተልሄም እንዲሄዱ ያደረጋቸው የሕዝብ ቆጠራ፥ ከሥርዓቶቹ አንዱና ቄሬኔዎስ ገዥ በነበረ ጊዜ የተከናወነ ነበር፤ (የሐዋርያት ሥራ 5፡37 የሚያመለክተው፥ ምናልባት በስድስት ዓመተ ምሕረት የተከናወነውንና ሁለተኛውን ቆጠራ ሳይሆን አይቀርም)።

---

[69] የተጠቀሱት ጊዜያት የተመለከቱት በአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ነው።

ቆጠራው በየአሥራ አራት ዓመቱ ይከናወን እንደነበር የተገኘው ማስረጃ ያረጋግጣል። አንድ ሰው ግብጽ ውስጥ ከተከናወነው ቆጠራ በመነሣት ወደኋላ ቢያሰላ፥ ከክርስቶስ ልደት ስምንት ዓመት ቀደም ብሎ የሕዝብ ቆጠራ ተከናውኖ እንደነበር ይረዳል። ፍልስጥኤምና ሶሪያ ውስጥ በጊዜው ተነሥቶ የነበረው ብጥብጥ የቆጠራውን ክንውን ለጥቂት ዓመታት ሳያዘገየው እንዳልቀረ ይገመታል።

ቄሬኔዎስ ቆጠራው በተከናወነበት በስድስት ዓመተ ምሕረት የሶሪያ ገዢ እንደነበር ይታወቃል። ነገር ግን ይህ ጊዜ ከኢየሱስ ልደት ጋር በሚገናዘብበት ጊዜ አሥር ዓመት ያህል ይዘገያል። ይሁን እንጂ፥ የጽሑፍ ግኝቶች እንዳረጋገጡት ቄሬኔዎስ ከክርስቶስ ልደት ስምንት ዓመት ያህል ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ፥ ሶሪያ ውስጥ በጋራ አገዛዝ ሳይሳተፍ አልቀረም። የዚህ ሰው የአገዛዝ ጊዜ አጋሩ የሆነውና ሴንቲዮስ ሳተርኒየስ የተባለው ሰው አገዛዝ ከክርስቶስ ልደት ስድስት ዓመት በፊት እስካከተመበት ጊዜ ድረስ ሳይራዘም አልቀረም።

## የጢባርዮስ ቄሣር አሥራ አምስተኛ ዓመት

ሉቃስ 3፡1 ውስጥ እንደተጠቀሰው፥ የጢባርዮስ ቄሣር አገዛዝ አሥራ አምስተኛ ዓመት መጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎቱን የጀመረበት ጊዜ ነበር። የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት የጀመረው ከኢየሱስ አገልግሎት ጥቂት ቀደም ብሎ በመሆኑ፥ የኢየሱስን የአገልግሎት ጊዜ ለመረዳት ይህን የጊዜ ቅደም ተከተል መገንዘቡ ይረዳል።

ይሁን እንጂ፥ የጢባርዮስ አገዛዝ ወቅት ሁለት ጅማሬዎች ስለነበሩት ይህን አሥራ አምስተኛ ዓመት ትክክለኛ ጊዜ መወሰኑ ብዙ ችግር አስከትሎ ነበር። ከአባቱ ሞት ቀደም ብሎ በአንድ ወቅት ከአባቱ ከአውግስጦስ ቄሣር ጋር በጋራ ገዢ ሆኖ ነበር። አውግስጦስ በ14 ዓ.ም. ከሞተ በኋላ ግን፥ የግዛቱ ሁሉ ጠቅላይ ገዢ ሆነ። ሉቃስ የሚጠቅሰው ቀደም ያለውን ጊዜ ከሆነ፥ የዮሐንስ ነቢያዊ አገልግሎት የተጀመረው በ26 ወይም በ27 ዓ.ም. ነው። የተናገረው ስለኋለኛው ጊዜ ከሆነ ግን አሥራ አምስተኛው ዓመት ምናልባት በ28 ወይም በ29 ዓ.ም. ነበር።

በጥንት ዘመን ከነበረው የቀናት ቀመር ጋር ሲነጻጸር ከነዚህ ሁለት ግምቶች የኋለኛው ትክክል ይመስላል። ወደፊት በዚህ ጥናት ከምናገናዝበው የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ ጋር ሲነጻጸር ግን፥ የመጀመሪያው አገላለጥ ትክክለኛነት ያደላል። በግልጥ ለመናገር፥ ኢየሱስ አገልግሎት የጀመረበትን ጊዜ በተመለከተ 26 ወይም 27 ዓ.ም. ከሉቃስ ገለጣ ጋር ይበልጥ ይስማማል።

## "ሠላሳ ዓመት ያህል ዕድሜ"

ሉቃስ በ3፡23 ውስጥ እንደሚገልጠው፥ ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎቱን በሚጀምርበት ጊዜ ዕድሜው "ሠላሳ ዓመት ያህል" ነበር። ምንም እንኳን ይህ አገላለጥ ከሃያ ስምንት እስከ ሠላሳ ሁለት ድረስ ያለውን ማንኛውንም ዕድሜ የሚያመለክት ቢሆን፥ በጊዜው የነበሩ ልማዶችና ሌሎች የኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ዝርዝር ጉዳዮች እንደሚያመለክቱት፥ ምድራዊ አገልግሎቱን የጀመረው፥ ከ29-31 ዓመት ባለው ዕድሜ ነበር። የኢየሱስን ዕድሜ በማስገንዘቡ ረገድ ይህን የተሻለ ገለጣ አድርጎ መቀበሉ ሉቃስ የነገሮችን ዝርዝር ቅደም ተከተል ለማቅረብ ካደረገው ጥረት ጋር ይስማማል (ሉቃስ 1፡5፤ 2፡1-2፤ 3፡1-2)።

ኢየሱስ የተወለደው በስድስት ዓመተ ዓለም ገደማ ነው ከተባለ፥ ሠላሳ ዓመት የሞላው በ25 ዓመተ ምሕረት ይሆናል። በአምስት ዓመተ ዓለም ነበር ከተባለ ደግሞ፥ ሠላሳ ዓመት የሞላው በ26 ዓመተ ምሕረት ነው። ሁለተኛው የልደት ቀን ትክክል ይመስላል፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ በስቅለት የሞተበት ጊዜ ከ30 ዓ.ም. በፊት ነበር ሊባል አይቻልም። "ኢየሱስ የተሰቀለበት ቀንና ዓመቱ" የሚለውን መጣጥፍ ገጽ 295 ላይ ይመልከቱ።

ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት የጀመረበትን ጊዜ ከ27 ዓ.ም. በኋላ በነበረው በማንኛውም ጊዜ ነው ማለቱ ያስቸግራል። ምክንያቱም ይህን ዕድሜ አስመልክቶ ሉቃስ ያቀረበውን ገለጣ ተቀባይነት ያሳጣዋል። ከዚህም ይልቅ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት አንድ ወይም ሁለት ዓመት ብቻ ካልሆነ አገልግሎቱን በ30 ዓ.ም. ሊፈጽም አይችልም። በተጨማሪም አገልግሎቱ እንዲሁ ከሚታሰበው ይበልጥ አራት ወይም አምስት ዓመት ያህል ካልተራዘመ፥ እስከ 33 ዓ.ም. ሊቆይ አይችልም። (ለተጨማሪ መረጃ መጣጥፍ 43 ይመልከቱ።)

## ቤተ መቅደስ የማደሻ አርባ ስድስት ዓመታት

113 ዮሐንስ 2፡20 ላይ እንደተመለከተው፥ የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ከአርባ ስድስት ዓመታት በፊት በሄሮድስ ስለተጀመረው የቤተ መቅደስ እድሳት ሥራ ጉዳይ ይጠቅሳሉ። የሚታደሰው ቤተ መቅደስ በዘሩባቤል የተገነባ ነበር። መንፈሳዊ ባልሆነው የታሪክ ዘገባ መሠረት ሄሮድስ እድሳቱን የጀመረው ከክርስቶስ ልደት 19 ወይም 20 ዓመታት ቀደም ብሎ ነበር። ስለ ቤተ መቅደሱ የእድሳት ሥራ ለኢየሱስ የተነገረው አገልግሎቱን በግልጥ ከጀመረ ወዲህ በሆነው የመጀመሪያ ፋሲካ ወቅት ነው። በመሆኑም "አርባ ስድስቱ ዓመት" ክርስቶስ አገልግሎት የጀመረበትን ዓመት የመገንዘቢያ ሌላ መንገድ ያቀርባል።

ይህ ሰፊ የቤተ መቅደስ ሥራ፥ ሄሮድስ ከክርስቶስ ልደት አራት ዓመት ቀደም ብሎ እስከሞተበት ጊዜ እንኳን አልተጠናቀቀም። አይሁዳውያን ዮሐንስ 2፡20 ውስጥ የተጠቀሰውን ቃል በተናገሩ ጊዜም ሥራው በመካሄድ ላይ ነበር። በ64 ዓ.ም. ነበር ሥራው የተጠናቀቀው።

ምንም እንኳን "ቤተ መቅደስ" እና "መሥራት" ወይም "ማነጽ" የሚሉትን ቃላት በተመለከተ አንዳንድ አለመግባባቶች ቢኖሩ፥ ግልጥና ለሁኔታው ግንዛቤ አጥጋቢ የሆነው ነገር፥ አይሁድ ያነጻጸሩ የነበረው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ መቅደሱን እሠራዋለሁ ባለው ሦስት ቀንና የእድሳቱ ሥራ የፈጀውን ረጅም ጊዜ መሆኑን መረዳቱ ነው (ዮሐ. 2፡19)።

ከ19 ወይም 20 ዓ.ዓ. ጀምሮ አርባ ስድስት ዓመት የሚቆጥር ሰው 26 ወይም 27 ዓ.ም. ላይ ደርሶ ይቆማል። ስለዚህ በኢየሱስ አገልግሎት ወቅት የመጀመሪያው ፋሲካ የተከበረው በ27 ዓ.ም. ጸደይ ውስጥ ነው።

## የኢየሱስ አገልግሎት ጊዜ እርዝማኔ

ክርስቶስ አገልግሎት የጀመረበት ጊዜ ከታወቀ፥ የተሰቀለበት ትክክለኛ ዕለት ይህ ነበር ከመባሉ በፊት የአገልግሎቱ ጊዜ እርዝማኔ መታወቅ አለበት።

አንዳንድ ሰዎች፥ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወንጌላት የሚጠቅሱት፥ በኢየሱስ አገግልግሎት ጊዜ አንድ የፋሲካ በዓል፥ ማለት በስቅላቱ ዋዜማ የተደረገውን ብቻ

መሆኑን (ማቴ. 26፡17-20፤ ማር. 14፡12-17፤ ሉቃስ 22፡7-16) መነሻ በማድረግ አገልግሎቱ አንድ ዓመት ብቻ ነበር ብለው ተከራክረዋል። የዮሐንስ ወንጌል ግን ይህን ግንዛቤ ይቃረናል። ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ከጀመረ በኋላ ያለፈባቸውን ፋሲካዎች በግልጥ ይጠቅሳቸዋል (ዮሐ. 2፡13፤ 6፡4፤ 11፡55)።

ሌሎቹ ደግሞ የአገልግሎቱ ጊዜ ከሁለት ዓመት አለፍ ያለ ነበር የሚለውን ደግፈዋል። እነዚህ ሰዎች ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተጠቀሱትን ሦስት የፋሲካ በዓላት የሁለቱ ዓመታት መነሻና መደምደሚያ እንደነበሩ ይገነዘባሉ። ይህ ንድፈ አሳብ ብዙ ጊዜ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አምስትና ስድስትን በማዟዟር አሠራር ላይ በመመሥረት ነው ትክክለኛነቱን የሚያስገነዝበው። ይሁን እንጂ ይህን እንደገና አስተካክሎ የማስላት አሠራር የሚደግፍ የጽሑፍ ማስረጃ ስለሌለ፥ ሁለት ዓመት የሚለው ጽንሰ-አሳብ ደካማ ነው።

114 የክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ከአራት ዓመት እልፍ ይላል የሚለውን ግንዛቤ ለማረጋገጥ የሚደረገው ሙከራ የሚመሠረተው በዮሐንስ ያልተጠቀሱትን ሁለት የፋሲካ በዓላት በመገመት ላይ ነው። ከነዚህ ተጨማሪ የፋሲካ በዓላት አንዱ ዮሐንስ 4፡35 ውስጥ የተጠቀሰው (ይህ ዮሐ. 2፡13 ውስጥ ከተጠቀሰው በዓል በኋላ ወቅቱ ክረምት መሆኑን ያመለክታል) እና ቀጥሎ በነበረው ክረምት የተከበረውን የድንኳን በዓል ያመለክት ይሆናል ተብሎ በተገመተው ማለት ዮሐንስ 5፡1 ውስጥ በተጠቀሰው በዓል መካከል የተከናወነው ነበር። ይህን ያልተጠቀሰ የፋሲካ በዓል እንደ ማስረጃ መጠቀሙ መላምታዊ ይመስላል። ሌላውን ተጨማሪ የፋሲካ በዓል እንደሆነ መቁጠሩም ጥሩ መሠረት የለውም። አንዳንዶች በዓሉን ከዮሐንስ 2፡13 በፊት፥ ሌሎቹ ደግሞ ዮሐንስ 6፡4 ውስጥ ከተጠቀሰው ፋሲካ በኋላ ያደርጉታል። በሁለቱም በኩል ቢሆን፥ አምስተኛ የፋሲካ በዓል ነበር ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አሳማኝ ማስረጃ የለም።

በሰፊው የታመነበት አሳብ የክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ከሦስት ዓመት ላቅ ያለ መሆኑ ነው። ኢየሱስ በዮሐንስ ከተጠመቀበት (ማቴ. 3፡1-17፤ ማር. 1፡9-11፤ ሉቃስ 3፡21-23ሀ) እስከ መጀመሪያው የፋሲካ በዓል (ዮሐ.2፡13) ድረስ የነበረው ጊዜ ብዙ ወራት ያለፉበት፥ እንዲሁም ኢየሱስ ገሊላና ይሁዳ ውስጥ የተዘዋወረበት ነበር። የመጀመሪያው አንድ ዓመት (በፋሲካ በዓላት መካከል የነበረው) አገልግሎቱም እንዲሁ ይሁዳና ገሊላ ውስጥ የነበረ ሲሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባልተጠቀሰ የፋሲካ በዓል ጊዜ አብቅቷል። ይህም የፋሲካ በዓል ኢየሱስ ዮሐንስ 4፡35 ውስጥ የተጠቀሰውን ቃል ከተናገረ ጥቂት ወራት በኋላና ዮሐንስ 5፡1 ውስጥ ከተጠቀሰው የድንኳን በዓል ስድስት ወር ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ የሆነ ነበር። የኢየሱስ አገልግሎት ሁለተኛ ዓመት በአብዛኛው ገሊላ ውስጥ ሲሆን፥ ዮሐ. 6፡4 ውስጥ በተጠቀሰው የፋሲካ በዓል ወቅት አብቅቷል። የመጨረሻውን የአገልግሎት ዓመት ያሳለፈው በአብዛኛው በገሊላ ዙሪያ፥ ይሁዳና ፖርያ ውስጥ ሲሆን፥ አገልግሎቱ የተጠናቀቀውም ዮሐንስ 11፡55 ውስጥ የተጠቀሰው የፋሲካ በዓል በተከበረ ጊዜ ነው።

እንግዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ጊዜ ከሦስት ዓመት ጥቂት አለፍ ያለ ነበር የሚለው አሳብ፥ በጠንካራ ማስረጃ የተረጋገጠና ግራ ከሚያጋባ ነገር የፀዳ ነው።

## ስቅላቱ

በመጣጥፍ 4 ውስጥ እንደተገለጠው፥ "ክርስቶስ የተሰቀለበት ቀንና ዓመት" ማለት ኒሳን የተባለው ሰባተኛ ወር አሥራ አራተኛ ቀን የፋሲካ በዓል የዋለው በአይሁድ የጊዜ ቀመር ሁለት ጊዜ ማለት በ26 ዓ.ም. እና በ36 ዓ.ም. ነው። ይህም ክርስቶስ የተሰቀለው በ30 ወይም 33 ዓ.ም. ነው ከሚሉ ሁለት አማራጭ ጊዜያት ላይ ያደርሰናል። ቀደም ሲል በዚህ የመጣጥፍ ክፍል የተደረሰበት ማጠቃለያ ከታመነበት፥ ክርስቶስ የተሰቀለው በ30 ዓ.ም. ነበር የሚለውን አማራጭ እንድንቀበል ያደርገናል።

## መደምደሚያ

የዚህ መጣጥፍ ማጠቃለያዎች ባለፉት ገለጣዎች የተነሡ ሌሎች ግምታዊ አማራጮችን ባካተተ ሁኔታ በሚከተለው ሰሌዳ በአጭሩ ይቀርባሉ።

| | |
|---|---|
| የክርስቶስ ልደት | 6 ዓ.ዓ. (በዓመቱ ማብቂያ) ወይም 5 ዓ.ዓ. (በዓመቱ መጀመሪያ) |
| የታላቁ ሄሮድስ ሞት | 4 ዓ.ዓ. (ከኒሳን 1 በኋላ ) |
| የጢባሪዮስ ቄሣር አገዛዝ መጀመር | 12 ዓ.ም. |
| የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት መጀመር | 26 ዓ.ም. (በዓመቱ መጀመሪያ) |
| የክርስቶስ አገልግሎት መጀመር | 26 ዓ.ም. (በዓመቱ አጋማሽ ወይም ፍጻሜ) |
| በክርስቶስ አገልግሎት ወቅት የመጀመሪያው ፋሲካ | 27 ዓ.ም. (ኒሳን 14) |
| በክርስቶስ አገልግሎት ወቅት ሁለተኛ ፋሲካ | 28 ዓ.ም. (ኒሳን 14) |
| በክርስቶስ አገልግሎት ወቅት ሦስተኛ ፋሲካ | 29 ዓ.ም. (ኒሳን 14) |
| የክርስቶስ መሰቀል | 30 ዓ.ም. (ኒሳን 14) |

ምንም እንኳን ችግሮች የሉትም ባይባል፥ ይህ የዕለታት ሰሌዳ ካከማቻቸው ብርቱ ማረጋገጫዎች የተነሣ ከሌሎች ማስረጃዎች የተሻለ መፍትሔ ያለው ይመስላል። በመሆኑም የወንጌላት ተማሪ የሆነ ሰው ኢየሱስ በምድር የኖረበትን፥ ያገለገለበትንና የሞተበትን ጊዜ በትክክል እንዲረዳ ያስችለዋል።

# 4

# ኢየሱስ የተሰቀለበት ቀንና ዓመት

ኢየሱስ የተሰቀለበትን ቀንና ወሩን፥ እንዲሁም ዓመቱን በእርግጠኛ መረዳቱ የክርስቶስን ምድራዊ ሕይወት ሰፊ ቅደም ተከተል ለመገንዘብ እጅግ ይጠቅማል። ወደሌሎች ከክርስቶስ ሕይወት ጋር ከሚዛመዱ የወንጌላት ቅደም ተከተላዊ ጉዳዮች ከመሻገራችን በፊት፥ ጥርት ላለ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ እነዚህ ሦስት ጉዳዮች በዚህ ጽሑፍ ይዳሰሳሉ። ሦስቱም የሚታዩት ከላይ በተቀመጡበት ቅደም ተከተል ሲሆን፥ በሚያመች አኳኋን ለየብቻቸው ይታያሉ።

## የሳምንቱ ዕለት

ቤተ ክርስቲያን በተለምዶ ኢየሱስ የሞተበት ዕለት አርብ እንደሆነ ትቆጥራለች። ይህን ግንዛቤ የሚሽር ጠንካራ ምክንያት አልቀረበም። ኢየሱስ አርብ ዕለት ነው የተሰቀለው የሚለውን ለማስተባበል በተደጋጋሚ የሚነሣው ተቃውሞ የሚነሣው፥ ማቴዎስ 12፡40 ውስጥ "ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት" የሚለውን ቃል በስሕተት በመገንዘብ፥ ኢየሱስ እያንዳንዳቸው ሃያ አራት ሰዓት ለሆኑ ሦስት ቀናት መቃብር ውስጥ ቆይቷል ከሚሉ ወገኖች ነው። ከዚህ ግንዛቤ በመነሣት፥ አንዳንዶች ከእሁድ ወደ ኋላ ይቆጥሩና የስቅለቱን ዕለት ወደ ሐሙስ ወይም ወደ ረቡዕ ይወስዱታል።

ይሁን እንጂ፥ ይህ ድምዳሜ ኢየሱስ የመዘጋጀት ወይም የሰንበት ዋዜማ በተባለው ቀን መሰቀሉን ከሚያስገነዝበው የአራቱ ወንጌላት የማያሻማ መግለጫ ጋር ይቃረናል (ማቴ. 27፡62፤ ማር. 15፡42፤ ሉቃስ 23፡54፤ ዮሐ. 19፡14፥ 31፥ 42)። ይህ የዝግጅት ዕለት ዛሬ እኛ አርብ ብለን የምንጠራው የሳምንት ዕለት ሲሆን፥ አይሁዳውያን ለሥርዓታቸው ማከናወኛ የለዩት ቀን ነው። "ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት" የሚለው ገለጣ በትክክል ከግንዛቤ ሲገባና ጊዜው ከሀያ አራት እስከ ሰባ ሁለት ሰዓት ሊደርስ እንደሚችል ሲታወቅ፥ ይህ የሚቃረን የሚመስል አሳብ ይወገዳል።

ኢየሱስ መቃብር ውስጥ የሚቆይበትን ጊዜ ሲተነብይ "በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት" በማለት ራሱን ከዮናስ ጋር አነጻጽሯል (ማቴ. 12፡40)። በዚህ ንግግሩ አንድን ነገር ሊገልጥ ከሚችልባቸው ብዙ መንገዶች አንዱን ብቻ መረጠ። አንድን ዕለት ለመጥቀስ የቀኑን ክፍልፋይ ብቻ መጥቀሱ በአይሁዳውያን ዘንድ የተለመደ ነገር ነበር (ዘፍጥ. 42፡17-18፤ 1ኛ ሳሙ. 30፡12-13፤ 1ኛ ነገሥ. 20፡29፤ 2ኛ ዜና. 10፡5፥ 12፤ አስቴር 4፡16፤ 5፡1)። ስለዚህ "ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት" የሚለው ቃል በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መካከል ሀያ አራት ሰዓታት ያላቸው ሦስት ቀናት አልፈዋል አያሰኝም። ነገር ግን ገለጣው "በሦስተኛው ቀን" ተነሣ የሚለው ቃል ሌላ አባባል ነው (ማቴ. 16፡21፤ 17፡23፤ 20፡19፤ 27፡64፤ ሉቃስ 9፡22፤ 18፡33፤ 24፡7፥ 21፥ 46፤ ሐዋ. 10፡40፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡4)፥ ወይም "ከሦስት ቀን በኋላ" (ማቴ. 26፡61፤ 27፡40፥ 63፤ ማር. 8፡31፤ 9፡31፤ 10፡34፤ 14፡58፤ 15፡29፤ ዮሐ. 2፡19-20)።

ከወንጌላት ገለጣ አኳያ ሲታይ እንግዲህ፥ ኢየሱስ አርብ ዕለት ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ሞቶ፥ በዚያኑ ዕለት ዘግየት ብሎ (ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት) ተቀበረ ብሎ ያለ ስጋት ለመናገር ይቻላል። መቃብር ውስጥ የቆየው የአርብን የተወሰነ ጊዜ (ፀሐይ እስክትጠልቅ)፥ ቀጥሎ የነበረውን ሙሉ ዕለት (ከአርብ ፀሐይ መጥለቅ እስከ ቅዳሜ

ፀሐይ መጥለቅ) እና የሦስተኛውን ቀን የተወሰነ ጊዜ (ከቅዳሜ ፀሐይ መጥለቅ እስከ እሁድ ማለዳ) ነበር። ከፀሐይ መጥለቅ እስከ ፀሐይ መጥለቅ ያለውን ጊዜ አንድ ቀን ብሎ የመቁጠሩ አሠራር ኢየሩሳሌም ውስጥ ሰዱቃውያን የሚከተሉት ነበር። ከፀሐይ መውጣት እስከ ፀሐይ መውጣት ያለውን ጊዜ እንደ አንድ ዕለት የመቁጠሩ አሠራርም ነበር። ነገር ግን ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ የሚለው አሠራር ይበልጥ ተቀባይነት ያገኘ ነው።

## የወሩ ዕለት

ክርስቶስ በአይሁዳውያን የቀን አቆጣጠር በየትኛው ዕለት እንደተሰቀለ በትክክል ማወቁ ተገቢ ነው። በአይሁዳውያን ሰባተኛ ወር (ኒሳን) በአሥራ አራተኛው ወይስ በአሥራ አምስተኛው ቀን ነው ክርስቶስ የተሰቀለው? የዮሐንስ ወንጌል ዕለቱ የወሩ የአሥራ አራተኛው ቀን ስለመሆኑ መነሻ የሚሆን አሳብ ሲኖረው፥ ሌሎቹ ወንጌላት ግን አሥራ አምስተኛው ቀን ነበር የሚሉ ይመስላሉ። ዮሐንስ በጌታ መሰቀል ዋዜማ የተከናወነው የእንጀራ መቁረስ ሥርዓት የፋሲካ እራት አልነበረም ሲል፥ የሌሎቹ ወንጌላት ፀሐፊዎች ግን ነበር ይላሉ።

ዮሐንስ 13፡1 ላይ የተጻፈው ቃል በክርስቶስ መሰቀል ዋዜማ የተከናወነው እራት "ከፋሲካ በዓል በፊት" እንደነበር ያስረዳል። በኢየሱስ ላይ የተፈረደበት "ፋሲካ በተዘጋጀ ቀን" መሆኑንም ይኸው የዮሐንስ ወንጌል ይገልጣል (ዮሐ. 19፡14)። የኢየሱስ ከሳሾች በጊዜው ገና የፋሲካ ምግብ እንዳልበሉ ዮሐንስ 18፡28 ውስጥ ተገልጧል። ዮሐንስ 13፡29 ውስጥ የተጻፈው ቃልም የይሁዳን ተልዕኮ በተመለከተ ሌሎቹ ሐዋርያት የነበራቸው ግንዛቤ፥ የፋሲካው ሥርዓት በሚቀጥለው ዕለት በመሆኑ ላይ የተመሠረተ እንደነበር ያስገነዝባል። የፋሲካ ምግብ መበላት የነበረበት በወሩ አሥራ አራተኛ ቀን ፍጻሜ ምሽትና፥ በአሥራ አምስተኛው ቀን መጀመሪያ ስለነበር (ዘሌዋ. 23፡5)፥ ዮሐንስ ኢየሱስ የሞተበትን ዕለት የወሩ (ኒሳን) አሥራ አራተኛው ቀን እንደሆነ አድርጎ ነው የተረዳው።

በጥያቄው ሌላ አቅጣጫ ሲታይ ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ በጌታ ሞት ዋዜማ የተከናወነውን የጌታ እራት ሥርዓት በወሩ አሥራ አራተኛ ቀን ማብቂያና በአሥራ አምስተኛው መጀመሪያ (ማቴ. 26፡17-20፤ ማር. 14፡12-17፤ ሉቃስ 22፡7-16) ላይ መሆኑን በግልጥ ያስረዳሉ። ሁኔታዎቹ የሚያመለክቱት፥ በእስራኤላውያን ዘንድ የሚታወቀውንና በወሩ አሥራ አራተኛ ቀን የሚከናወነውን የጠቦቶች መሥዋዕት፥ እንዲሁም በዚያው ዕለት ምሽት የሚቀርበውን ምግብ ነው።

ለዚህ እርስ በርሱ የሚጋጭ የሚመስል ነገር መፍትሔ ለመሻት የተለያዩ ሙከራዎች ተደርገዋል። አንዳንዶቹ የዮሐንስ ወንጌል የዘገበው ስሕተት እንደሆነና ሌሎቹ ወንጌላት ግን ትክክል እንደሆኑ ሲናገሩ፥ የቀሩት ደግሞ የዚህን ተቃራኒ አሳብ አቅርበዋል። ሌላው አሳብ ደግሞ የዮሐንስ ወንጌልም ሆነ ሌሎቹ ትክክል ናቸው፤ የሚያስፈልገው ነገር ትርጉሙን በማስማማት ወንጌላቱን ማዛመድ ይቻላል የሚል ነው።

ለዚህ ጉዳይ መፍትሔ የመስጫው የላቀ አሠራር፥ ክርስቶስ የሞተበትን ዕለት በተመለከተ ሁለቱም መንገዶች ትክክል መሆናቸውን መቀበል ነው። ይህ ይቻላል። ምክንያቱም፥ ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ የነበሩ አይሁዳውያን ቀናትን የመለያ ሁለት መንገዶች የነበሯቸው ይመስላል። እያንዳንዱን አዲስ ዕለት ከፀሐይ መጥለቂያ

በመጀመር ከሚታወቀው አሠራር በተጨማሪ፥ የአንዳንዶች መመሪያ ዕለትን የሚለየው ከፀሐይ መውጫ እስከ ጸሐይ መውጫ ባለው ጊዜ ነው። ከላይ የተጠቀሰው እያንዳንዱ የአቆጣጠር ባሕል ከብሉይ ኪዳን ድጋፍ አለው። የመጀመሪያው የዘፍጥረት 1፡5 እና ዘጸአት 12፡18፤ ሁለተኛው ዘፍጥረት 8፡22 እና 1ኛ ሳሙኤል 19፡11 በመሳሰሉት ይደገፋሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ የተገለገሉበትና፥ በማቴዎስ፥ በማርቆስና በሉቃስ የተገለጠው የቀን አቆጣጠር ሥርዓት፥ ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መውጫ ያለው ነው። ዮሐንስ ሁነቶችን የሚገልጣቸው ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ባለው የቀን አቆጣጠር ዘዴ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት አሠራሩ በጊዜው ይበልጥ ይታወቅ ስለነበር ነው (በዚህ መጣጥፍ "የሳምንቱ ዕለት" በሚለው ርዕስ ሥር የቀረበውን አሳብ ይመልከቱ)። ይህ የሚያመለክተው፥ በፈሪሳውያን (አንድ ቀን ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መውጫ ያለው ነው) በሚሉትና፥ በሰዱቃውያን (ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ) በሚሉት መካከል የልዩነት ነጥብ መኖሩን ነው።

ስለዚህ ከዮሐንስ ወንጌል በስተቀር፥ ሌሎቹ ኢየሱስ የፋሲካን እንጀራ የበላው በመሞቻው ዋዜማ መሆኑን ነው የሚገልጡት። አንድ ቀን ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መውጫ ያለው ጊዜ ነው የሚሉት ወገኖች ደግሞ የፋሲካ ጠቦቶች የታረዱት ከቀትር በኋላ ጥቂት ሰዓታት ቀደም ብሎ መሆኑን ይናገራሉ። በነሱ አባባል እርዱ የተከናወነው በወሩ (ኒሳን) በአሥራ አራተኛው ቀን፥ የፋሲካው እንጀራ በተበላበት ጊዜ ነው። የወሩ አሥራ አምስተኛ ቀን እስከሚቀጥለው ዕለት፥ ማለት አርብ ከማለዳው አሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ድረስ አልጀመረም።

ይሁን እንጂ ዮሐንስ ሁነቶችን የሚመለከታቸው ቤተ መቅደሱን ያዝዙ ከነበሩት ሰዱቃውያን አንጻር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው፥ ጠቦቶች ለፋሲካ በዓል በሚታረዱበት ሰዓት፥ ማለት በኒሳን በአሥራ አራተኛው ቀን ከሰዓት በኋላ ነበር። ይህ ዕለት ሐሙስ ፀሐይ ስትጠልቅ ጀምሮ አርብ ፀሐይ ስትጠልቅ ያበቃል። የፋሲካ ጠቦቶች የሚሰዉበት ትክክለኛ ጊዜ ይህ ነው። ነገር ግን የቤተ መቅደሱ ባለሥልጣናት ሌላ የቀን አቆጣጠር ከሚከተሉ ሰዎች ጋር በመስማማት ጠቦቶችን ሐሙስ ዕለት እንዲያርዱ ሳይፈቅዱላቸው አልቀሩም። ይህ ባይሆን ኑሮ የሚሰዉአቸውን እንስሳት ይዘው ለፋሲካው ዝግጅት በዓል በየዓመቱ የሚመጡትን ሰዎች በሚገባ ለማስተናገድ አይቻልም ነበር። የኢየሱስ ወንጀሮች የፋሲካ ምግብ ሳይበሉ የዘገዩበትን ምክንያት ይህ ልዩነት ያስረዳል (ዮሐ. 18፡28)። እነሱ በዓሉን አርብ ማታ ማለት ፀሐይ መግቢያ በሚጀምረው ኒሳን 15 ቀን ሊያደርጉ በመዘጋጀት ላይ ነበሩ።

ከላይ የቀረበው መፍትሔ ትክክል ከሆነ እንግዲህ፥ ኢየሱስ የሞተው (በጭፍን እንዲሁ ትክክል ነው ለማለት አይቻልም፤ ነገር ግን ከሌሎቹ አሳቦች ሁሉ የላቀ ማረጋገጫ የያዘ ይመስላል) አንድን ዕለት ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መውጫ ለሚቆጥሩት ኒሳን 15 ቀን ፥ ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ባለው ጊዜ ለሚያሰሉት ደግሞ ኒሳን 14 ነው።

## ዓመቱ

ኢየሱስ የሞተበትን ዕለት በመወሰኑ ረገድ የኮከብ ቆጠራው መስክ በተሻለ ይረዳል። የአይሁዳውያን የቀን አቆጣጠር በጨረቃ መውጣትና መጥለቅ ላይ የተመሠረተ ነበር። በመሆኑም የኢየሱስን ሞት አጠቃላይ ጊዜ ከአዲስ ጨረቃ መታየት

ጋር በማያያዝ፥ ኒሳን 14 (ከፀሐይ መጥለቅ እስከ ፀሐይ መጥለቅ ባለው ስሌት መሠረት) ከሐሙስ ፀሐይ መጥለቅ እስከ አርብ ፀሐይ መጥለቅ ድረስ ያለው ጊዜ የዋለበትን ዓመት ለመረዳት ይቻላል።

ኢየሱስ በ26 ዓ.ም. እና በ36 ዓ.ም. መካከል ባለው ጊዜ የተሰቀለ መሆኑ ይታወቃል። ይህ የሚባልበት ምክንያት ጊዜው ጲላጦስ የአካባቢው ገዢ የነበረበት በመሆኑ ነው (ዮሐ. 19፡15-16)። ውስብስብ የሆኑና በከዋክብት እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረቱ ስሌቶች እንደሚያስረዱት፥ በዚያ ዘመን ኒሳን 14 አርብ ዕለት የዋለው ሁለት ጊዜ፥ ማለት በ30 ዓ.ም. እና በ33 ዓ.ም. ነበር።

በ30 እና በ33 ዓ.ም. ነው ብሎ መወሰኑ ቀላል ነገር አይደለም። ምክንያቱም ጉዳዩ በብዙ መልኩ ከክርስቶስ ሕይወት ጋር የተያያዘ ቅደም ተከተላዊ ገጽታ አለው። መጨረሻ ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት አንዳንድ ነገሮች፥ ለምሳሌ የኢየሱስን ልደት አስመልክቶ "ጢባርዮስ ቄሣርም በነገሠ በአሥራ አምስተኛው ዓመት" (ሉቃስ 3፡1-2) የሚለው፥ "ሠላሳ ዓመት ያህል" "ሉቃስ 3፡23" የሚለው፥ ዮሐንስ ደግሞ "ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር" (ዮሐንስ 2፡20) የሚለውና ኢየሱስ ከሞተበት ዓመት ጋር የተያያዙ ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው። ቀጥሎ የሚቀርበው መጣጥፍ ይህን ጉዳይ በይበልጥ ያብራራዋል።

# 5

# የኢየሱስ ለምርመራ መቅረብ

ደቀ መዛሙርቱ ከሌላው ጊዜ ይልቅ ስለመጨረሻዎቹ የኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ብዙ መረጃዎችን ይሰጡ ነበር። በአጠቃላይ ሲታይ፥ ወንጌላት ስለመጨረሻው ሳምንት ጠለቅ ያለ ገለጣ ይሰጣሉ። በተለይ ስለ ኢየሱስ መያዝና ለፍርድ መቅረብ የገለጡት ጉዳይ አይሁዳውያንና የክርስቲያን ምሁራንን ለረጅም ጊዜ እንዲመሰጡ አድርጓቸው ነበር።

ደቀ መዛሙርቱ እውነተኛ መረጃዎች ስጥተውናል ብለን ካሰብን፥ እስከ ኢየሱስ መሰቀል ድረስ ያሉት ሁኔታዎች በሚከተሉት መንገዶች ተከናውነዋል ለማለት እንችላለን።

1. በመጨረሻው ሳምንት ሀሙስ ምሽት ደርብ ላይ ከነበረው አዳራሽ እስከ ጌቴሰማኒ የአትክልት ስፍራ ድረስ ከተደረገው ጉዞ በኋላ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ኢየሱስን አትክልቱ ውስጥ በጨለማ ተገናኘው። ይሁዳ ብቻውን አልነበረም። በአጠቃላይ የሸንጎው ተወካዮች፥ የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች፥ እንዲሁም ሁለት መቶ የሚሆኑ ሮማውያን ወታደሮች አብረውት እንደነበሩ ተገልጧል። የሚፈልጉት እሱን መሆኑን ቀድሞውን ኢየሱስ ያወቀ ቢሆንም፥ ይሁዳ በመሳም ለጠላቶቹ አሳልፎ ሰጠው። በዚህ አኳኋን ኢየሱስን ወሰዱት፤ አሠሩት።

ጴጥሮስ የኢየሱስን የመያዝ ሙከራ ለማገድ የሊቀካህናቱን አለቃ ጭፍራ ቀኝ ጆሮ በሰይፍ ቆረጠው። ኢየሱስ ግን ጴጥሮስን ስለ ድርጊቱ ገሰፀውና የጭፍራውን ማለት የማልኩስን ጆሮ በነበረበት መሰሰለት። ያ ያልተገባና ጀብደኛ የጴጥሮስ ድርጊት በኢየሱስ ከተገሰፀ በኋላ ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ጥለውት ሸሹ። ጴጥሮስ ሁኔታውን ከርቀት ለመከታተል ተመልሶ ነበር።

2. ኢየሱስ ወደ ቀድሞው ሊቀካህን ወደሃና ተወሰደ። በመጀመሪያው የአይሁዳውያን ምርመራ ክፍል በሃና በአጭሩ ተጠየቀ። ከዛም የሃና አማች ወደሆነው የጊዜው ሊቀካህን ወደ ቀያፋ ተላከ።

3. በቀያፋ ቤት ጉባኤው ለምሽት ውይይት ተሰብስቦ ነበር። ይህ ኢየሱስ የሚቀርብበት ሁለተኛው የአይሁዳውያን የምርመራ ክፍል ነበር። የዓይን ምስክሮች በኢየሱስ ላይ እንዲመሠክሩ ቢቀርቡም ከነሱ ሁለቱ እንኳን ቃላቸው አልተስማማም። ኢየሱስም ክሱን በዝምታ ተቃወመ። በመጨረሻም ከቀያፋ ጉትጎታ በኋላ ኢየሱስ መሢሕ፥ የእግዚአብሔር ልጅ፥ እንዲሁም የሰው ልጅ መሆኑን ገለጠ። ቀያፋም ይህን የኢየሱስ ገለጣ ስድብና ሞት የሚገባው አድርጎ ፈረደ። ጉባዔውም በፍርዱ ተስማማ፥ አፀናው፥ የአካል ስቃይም ያደርስበት ጀመር።

4. ሦስተኛው የአይሁዶች ምርመራ የተካሄደው በማግስቱ ጠዋት ነበር። ምንም እንኳን ባለፈው ምሽት ጉባኤ የተገኙት መጠነኛ ቢሆኑ የአሁኑ ስብሰባ ምልአተ ጉባኤ ነበር። ይሄኛውም ጉባኤ ያለፈውን ክስና ፍርድ አጸደቀ።

5. አሁን የኢየሱስ ምርመራ ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገሩ ነው። ምክንያቱም አይሁዳውያን ሰውን በሞት የመቅጣት ውሳኔ የማሳለፍ አጠቃላይ ሥልጣን አልነበራቸውም። ስለዚህ ኢየሱስ ለመጀመሪያው የሮማውያን ምርመራ ወደ ሮማዊው ገዥ ወደ ጲላጦስ ተወሰደ። ጉባኤው በኢየሱስ ላይ ያቀረባቸው ክሶች ሦስት ነበሩ። እነርሱም "ሕዝባችንን ያውካል፤ "ለቄሣር የሚከፈለውን ቀረጥ ይቃወማል፤ ራሱን የተቀባሁ ንጉሥ ነኝ ይላል" (ሉቃስ 23፡2) የሚሉ ናቸው።

6. ኢየሱስ ብዙ ሥራዎችን ያከናወነው ገሊላ ውስጥ መሆኑን በመጥቀስ ሁለተኛው ምርመራ ወደ ሄሮድስ አንቲጳስ ተመራ። ሄሮድስ ያኔ ኢየሩሳሌም ውስጥ ነበር። ጲላጦስ ኢየሱስን ወደ ሄሮድስ የላከው ምናልባት ችግሮችን ከራሱ ለማራቅ ወይም በሄድሮስ ዘንድ መወደድን ለማግኘት ሳይሆን አይቀርም። ሄሮድስ በኢየሱስ ላይ ለማሾፍና እሱን ለመጠየቅ ዕድል ቢያገኝም አልፈረደበትም። መልሶ ወደ ጲላጦስ ላከ።

7. ጉዳዩ ወደ ጲላጦስ ተመለሰና የሮማውያን ምርመራ ሦስተኛ ክፍል ተጀመረ። ጲላጦስ በኢየሱስ ላይ የቀረቡትን ክሶች ማየትና የኢየሱስን ንፁህነት በራሱ ውሳኔ ማረጋገጥ ጀመረ። ሄሮድስም ኢየሱስን ለሞት የሚያበቃ ጥፋት ያላገኘበት መሆኑን ተረዳ። ነገር ግን ጲላጦስ ስለ ኢየሱስ ንጹሕነት በነበረው እምነትና በአይሁዳውያን ኢየሱስን ለሞት አሳልፎ የመስጠት ፍላጎት ሁከት አሳቡ ሁለት ላይ ተከፈለ።

ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ይህን ውስብስብ ችግር ለመፍታት መፍትሔ መፈለግ ጀመረ። በነበረው ልማድ መሠረት የፋሲካ በዓልን ምክንያት በማድረግ አንድ አይሁዳዊ እስረኛ ይለቀቅ ነበር። ይህንኑ ዓመታዊ ምሕረት ለመጠየቅም ሕዝቡ ይሰበሰባል። በዚሁ መሠረት ሕዝቡ ከኢየሱስና አዋኪ ከነበረው ወንበዴ ከባራባስ የትኛውን ሊፈታላቸው እንደሚሹ ሊያስመርጣቸው ወሰነ። የአይሁድ መሪዎች በኢየሱስ ላይ ያላቸው ጥላቻ ምክንያት ቅናት መሆኑን ጲላጦስ አውቋል። ለዚህም ሕዝቡ ያለጥርጥር ከባራባስ ይልቅ ኢየሱስ እንዲለቀቅለት ስለሚፈልግ ያን በመፈጸም ጲላጦስ ከጉዳዩ የሚገላገል መስሎት ነበር። ጲላጦስ ግን ሕዝቡን ለአድማ የቀሰቀሱት ሊቀ ካሕናትና ሽማግሌዎች የማነሣሣት ጉልበት ያላቸው መሆኑን ወይም ባራባስ በሕዝቡ የሚወደድ መሆኑን አልተረዳም ነበር። ሕዝቡ በቀረበለት የምርጫ ዕድል መሠረት የኢየሱስን መሰቀልና የባራባስን መለቀቅ መረጠ። ጲላጦስ ሕዝቡን ለማግባባት ሙከራ ቢያደርግም ሁካታው እንዲጨምር አደረገ እንጂ የፈየደው ነገር አልነበረም። ኢየሱስን ሊፈታው ቢሞክርም፥ ያን ካደረገ ጲላጦስ የቄሳር ወዳጅ ሊሆን እንደማይችል በመግለጥ ሕዝቡ ወነጀሉት። ይህ ክስ የጲላጦስን የፖለቲካ አቋም የሚያወድመው ሊሆን ይችል ነበር። ይህን በመፍራትና ከእምነት ይልቅ ሥራን በማስቀደም ጥያቄያቸውን ለመቀበል ወሰነ። በንጹሑ ሰው ሞት ምክንያት ከሚመጣ ተጠያቂነት ለመዳን ተስፋ በማድረግም በሕዝቡ ፊት እጆቹን ታጥቦ ከኢየሱስ ደም ንጹሕ መሆኑን ገለጠ። በዚሁ መሠረት ባራባስ ተለቀቀ። ኢየሱስ ግን ተገርፎ እንደ አይሁዳውያን ፍላጎት በሮማውያን የሞት ቅጣት መሠረት እንዲሰቀል ለሮማውያን ወታደሮች ተሰጠ።

# 6

# የሄሮድስ ቤተሰብ

በታሪክ "ታላቁ ሄሮድስ" ተብሎ የሚታወቀውና ዘሩ መላውን ፍልስጥኤም ከ100 ዓመታት በላይ ገዝተዋል። በተለያዩ ምክንያቶች የዚህን ቤተሰብ የእርስ በእርስ ዝምድና ለማወቅ በጣም አዳጋች ነው። ለምሳሌ፥ 1. አብዛኛውን ጊዜ ተመሳሳይ ስምና ማዕረግ ይጠቀማሉ፤ 2. አንዳንድ ጊዜ ስማቸውንና ማዕረጋቸውን ይለውጣሉ ወይም የሚጨምሩበት ነገር አለ፤ 3. ቤተሰቡ እርስ በእርሱ ይጋባል።

አዲስ ኪዳን ውስጥ 11 የቤተሰቡ አባላት ተጠቅሰዋል። የእነዚህን ሰዎች የእርስ በእርስ ዝምድናና መጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱበትን ቦታ ለመግለጥ እንሞክራለን። ትውልዱን ይበልጥ ግልጥ ለማድረግ እያንዳንዱ ሰው ቁጥር ተሰጥቶታል። ለምሳሌ፥ 100 ቤት ቁጥር የተሰጣቸው ከመጀመሪያው ትውልድ ሲሆኑ፥ 200 ቤት ቁጥር የተሰጣቸው ደግሞ ከሁለተኛው ትውልድ የሆኑ ናቸው። (በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ስዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ።)

ታላቁ ሄሮድስ (#101) በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ሄሮድስ ወይም ንጉሥ ሄሮድስ" በመባልም የሚታወቅ ሲሆን፥ ከ37 ዓ.ዓ. እስከ 4 ዓ.ዓ. ድረስ ገዝቷል። በሮማውያን መሪዎች ዘንድ "የአይሁዶች ንጉሥ" የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል። የታላቁ ሄሮድስ የትውልድ ሥፍራ ከይሁዳ በስተደቡብ በኩል የሚገኘውና ኤዶምያስ የሚባለው ቦታ ነው። ይህ ቦታ መጀመሪያ የኤሳው ትውልድ በሆኑት ኤዶማውያን ተይዞ ነበር። ኤሳው የያዕቆብ ወንድም ነው። ኤዶምያስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው በማርቆስ 3፡8 ውስጥ ብቻ ነው።

ታላቁ ሄሮድስ ቢያንስ 10 ሚስቶችና ብዙ ልጆች ነበሩት። የታወቀውም በሕንፃ ሥራዎቹ ነው፡- ቤተ መቅደሱን አድሷል፥ የኢየሩሳሌምን ከፊል ግንብ ገንብቷል፥ እንዲሁም በቂሣርያና በሰማርያ ከተማዎች ላይ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች አከናውኗል።

ታላቁ ሄሮድስ በጭካኔ ሥራውም ይታወቃል። ቤተልሔም ውስጥ ሕፃናትን ማስገደሉ አይረሳም። ቢያንስ ሦስት ልጆቹን አስገድሏል። በሞት ጣር ተይዞ ሳለ ከብዙ መንደሮች የአይሁድ መሪዎች ተይዘው እንዲታሠሩ አድርጓል። በሚሞትበት ጊዜ የሚያለቅሱ ሰዎች ለመኖራቸው እርግጠኛ ለመሆንም እርሱ በሚሞትበት ጊዜ የታሠሩት መሪዎች እንዲገደሉ ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር። ሆኖም ከሞተ በኋላ ከሚስቶቹ መካከል አንደኛዋ ይህ ትእዛዝ እንዳይፈጸምና መሪዎቹ እንዲለቀቁ አድርጋለች። በመሆኑም ሄሮድስ በሞተ ጊዜ ሐዘን ሳይሆን ታላቅ ደስታ ነበር። (ታላቁ ሄሮድስ ማቴዎስ 2፡1-22 እና ሉቃስ 1፡5 ውስጥ ተጠቅሷል።)

ታላቁ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ አገሪቱ ለሦስት ልጆቹ ተከፋፈለች።

1. አንደኛው ልጁ አርኬላዎስ (#203) በይሁዳ ከ4 ዓ.ዓ. እስከ 6 ዓ.ም. ነግሦአል። በሕዝቡ ዘንድ የተጠላ በመሆኑ፥ የይሁዳና የሰማርያ መሪዎች ተቃውሟቸውን ለአውግስጦስ ቄሣር አሰምተው አርኬላዎስ ከሥልጣን እንዲወርድና በግዞት እንዲቀመጥ ተደርጓል። ([አርኬላዎስ ማቴዎስ 2፡22 ውስጥ ተጠቅሷል።)

2. ሄሮድስ አንቲጳስ (#202) በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ሄሮድስ"፥ "ንጉሥ ሄሮድስ" ወይም "የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስ" በመባልም የሚታወቅ

ሲሆን፥ የገሊላና የፖርያ ገዥ ነበር። ሄሮድስ አንቲጳስ በግንባታ ሥራው የታወቀ ነበር። ይህ ሥራው ገሊላ ባሕር አጠገብ ያለችውን የጥብርያዶስ ከተማ ግንባታን ያጠቃልላል። የመጀመሪያ ሚስቱ የንጉሥ ናባታ ልጅ ነበረች። እሷን ፈትቶ ሄሮድያዳ የተባለችውን የወንድሙን ልጅ በሚያገባበት ጊዜ ናባታ ጦሩን አሰባስቦ የሄሮድስ አንቲጳስን ጦር ደመሰሰ። በ39 ዓ.ም. ከሥልጣን ተወግዶ ፈረንሣይ በሚገኘው ጎል በግዞት ተቀመጠ።

ወንጌላት ውስጥ በሁለት ነገሮች የታወቀ ነው፦ 1. የመጥምቁ ዮሐንስን አንገት በመቁረጡ፤ 2. በኢየሱስ ፍርድ ላይ በመካፈሉ።

(ሄሮድስ አንቲጳስ በማቴ. 14፡1-6፤ ማር. 6፡14-22፤ ሉቃስ 3፡1፤ 19-20፤ 8፡3፤ 9፡7-9፤ 13፡31፤ 23፡7-15፤ ሐዋ. 4፡27፤ 13፡1 ውስጥ ተጠቅሷል።)

3. ፊልጶስ (#205) በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ፊልጶስ" ወይም "የአራተኛው ክፍል ገዥ ፊልጶስ" በመባል ይታወቃል። ከ4 ዓ.ዓ. እስከ 34 ዓ.ም. ድረስ ሰሜን ምሥራቅ ፍልስጥኤም ውስጥ በሚገኙ ብዙ ግዛቶች ላይ ገዥ ነበር። ሰሎሜ የምትባለውን የሄሮድያዳ የመጀመሪያ ባል ልጅ የሆነችውን የወንድሙን የልጅ ልጅ ነበር ያገባው። (ፊልጶስ ሉቃስ 3፡1 ውስጥ ተጠቅሷል።)

ሌላው የታላቁ ሄሮድስ ልጅ ሄሮድስ ፊልጶስ (#204) ነው። በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ፊልጶስ" በመባል ሲታወቅ፥ ሄሮድያዳ የምትባለው የወንድሙ ልጅ የመጀመሪያ ባል ነበር። ሕይወቱን ሙሉ የኖረው ሰላማዊ ዜጋ በመሆን ነበር (ሄሮድስ ፊልጶስ ማቴ. 14፡3፤ ማር. 6፡17፤ ሉቃስ 3፡19 ውስጥ ተጠቅሷል።)

ሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ (#301) በአዲስ ኪዳን "ሄሮድስ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ ነው። በ7 ዓ.ዓ. አባቱ አርስቶቡሎስ (#201) በታላቁ ሄሮድስ ከተገደለ በኋላ ወደ ሮም ተሰደደ። ለብዙ ዓመታት ሮም ውስጥ ወጣ ገባ በማለት ኖረ። በ36 ዓ.ም. ንጉሥ ጢባርዮስ አሳሰረው። ከአንድ ዓመት በኋላ ካሊጉላ በሚባለው አዲስ ንጉሥ ከእሥር ነጻ በመውጣት የሰሜን ምሥራቅ ፍልስጥኤም ገዢ እንዲሆን ተልኳል። በ39 ዓ.ም. ገሊላና ፖርያ ግዛቱ ውስጥ ተጨምረውለታል። በ41 ዓ.ም. ደግሞ ይሁዳና ሰማርያን እንዲቆጣጠር ተሰጥተውታል። ከልጆቹ ውስጥ አንዱ ወንድ ልጅና ሁለቱ ሴት ልጆቹ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰዋል። በ44 ዓ.ም. በ53 ዓመት ዕድሜው መሞቱ ሐዋርያት ሥራ 12፡1-24 ውስጥ ተጠቅሷል።

ሄሮድያዳ (#303) የአርስቶቡሎስ ሴት ልጅ፥ የሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ (#301) እህት ናት። በመጀመሪያ ሄሮድስ ፊልጶስ (#204) የሚባለውን አጎቷን ያገባች ሲሆን፥ በኋላም እሱን በመተው ሌላውን ሄሮድስ አንቲጳስ (#205) የሚባለውን አጎቷን አግብታለች። በሄሮድስ አንቲጳስ ፊት በመደነስ ለመጥምቁ ዮሐንስ ሞት ምክንያት የሆነችው፥ ምናልባት ሰሎሜ የምትባለው ልጇ ሳትሆን አትቀርም (ማቴ. 14፡3፥ 6፤ ማር. 6፡19)።

ሄሮድስ አግሪጳ 2ኛ (#401) በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ንጉሥ አግሪጳ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ የተወለደው በ27 ዓ.ም. ነበር። አባቱ በሞተ ጊዜ፥ የአባቱን ቦታ ለመተካት ያልደረሰ ወጣት ነበር። ሆኖም ከጊዜ በኋላ በንጉሥ ቀላውዴዎስ በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ ፍልስጥኤም ግዛት ተሰጠው። በ56 (በ54) ዓ.ም. ንጉሥ ኔሮ ግዛቱ ውስጥ ተጨማሪ መሬት ሰጠው።


ሄሮድስ አግሪጳ 2ኛ ከ66-70 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ አይሁዳውያን በሮም

ላይ ያነሡትን አመጽ ለመግታት ሞክሯል። ለዚህ ሥራውም ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ የሮም መንግሥት ተጨማሪ መሬት ሰጥቶታል። ሄሮድስ አግሪጳ 2ኛ የሞተው በ100 ዓ.ም. ነው (ሐዋ. 25፥13-26፥32)።

በርኒቄ (#402)፥ የሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ (#301) ልጅ፥ በ28 ዓ.ም. ተወለደች። የካልሲሱ ሄሮድስ (302) የተባለውን አጎቷን አገባች። በ48 ዓ.ም. ከሞተ በኋላ ሄሮድስ አግሪጳ 2ኛ የተባለው ወንድሟ ቅምጥ ሆነች። ከዚያም ሌላ ሰው አገባችና ይህን ሰው በመፍታት ወደ ወንድሟ ተመለሰች። በኋላም የንጉሥ ጥጦስና ቬስፓሲያን ቅምጥ ሆነች። ከወንድሟ ጋር ሳለች ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ቃለ ምልልስ አድርገዋል። ይህም በሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ 25-26 ተመዝግቧል።

ድሩሲላ (#403) የሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ (#301) ሌላ ሴት ልጁ ነበረች። የተወለደችው በ38 ዓ.ም. ሲሆን፥ የሶርያን ንጉሥ አግብታለች። በኋላም ንጉሡን በመተው ፊሊክስ የተባለውን የሮም ባለሥልጣን አገባች። ከእርሱ ጋር በመሆን በ57 (59) ዓ.ም. ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ተገናኝተዋል። ይህም በሐዋርያት ሥራ 24፥24 ተጠቅሷል።

ሰሎሜ (#404) የሄሮዲያዳ ልጅ ናት። ሄሮዲያዳ ሰሎሜን የወለደችው የመጀመሪያ ባሏ ከሆነው ከሄሮድስ ፊልጶስ (#204) ሲሆን፥ እሱም የታላቁ ሄሮድስ ልጅ ነው። በወንጌላት ባይጠቀስም በሄሮድስ ፊት በመደነስ ለመጥምቁ ዮሐንስ ሞት ምክንያት የሆነችው እሷ እንደነበረች ይገመታል። በኋላም የአራተኛው ክፍል ገዥ ፊልጶስ (#205) የተባለውን የእናቷን አጎት አግብታለች (ማቴ. 14፥1-12፤ ማር. 6፥14-29)።


የሄሮድስ የዘር ግንድ
ማርያምኔ 1ኛ
101 ታላቁ ሄሮድስ
የኢየሩሳሌም ክሊዎፓትራ
ማልቴስ
ማርያምኔ 2ኛ
201 አርስቶቡሎስ
202 ሄሮድስ አንቲጳስ
203 አርኬላዎስ
204 ሄሮድስ ፊልጶስ
205 ፊልጶስ፥ የአራተኛው ክፍል ገዥ
(2)
(1)
301 ሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ
302 የካልሲሱ ሄሮድስ
303 ሄሮድያዳ
401 ሄሮድስ አግሪጳ 2ኛ
403 ድሩሲላ
ፊሊክስ
402 በርኒቄ
404 ሰሎሜ
መግለጫ
ነጠላ መስመር የሚያሳየው የልጅና የወላጆችን ዝምድና ሲሆን፥ ድርቡ መስመር የሚያመለክተው ደግሞ የጋብቻ ግንኙነትን ነው።

# የጥቅሶች ማውጫ በቅደም ተከተል

| | | ማቴዎስ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ | ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
| 1 | 1-17 | 3 | 24 | 11 | 2-19 | 57 | 77 |
| 1 | 18-25 | 9 | 30 | 11 | 20-30 | 58 | 78 |
| 2 | 1-12 | 14 | 32 | 12 | 1-8 | 50 | 64 |
| 2 | 13-18 | 15 | 33 | 12 | 9-14 | 51 | 65 |
| 2 | 19-23 | 16 | 34 | 12 | 15-21 | 52 | 66 |
| 3 | 1-6 | 21 | 36 | 12 | 22-37 | 61 | 81 |
| 3 | 7-10 | 22 | 37 | 12 | 38-45 | 62 | 82 |
| 3 | 11-12 | 23 | 38 | 12 | 46-50 | 63 | 83 |
| 3 | 13-17 | 24 | 39 | 13 | 1-3ሀ | 64ሀ | 84 |
| 4 | 1-11 | 25 | 40 | 13 | 3ለ-23 | 64ለ | 84 |
| 4 | 12 | 34 | 47 | 13 | 24-30 | 64መ | 87 |
| 4 | 13-16 | 40 | 52 | 13 | 31-32 | 64ሠ | 88 |
| 4 | 17 | 37 | 50 | 13 | 33-35 | 64ረ | 88 |
| 4 | 18-22 | 41 | 52 | 13 | 36-43 | 64ሰ | 88 |
| 4 | 23-25 | 44 | 55 | 13 | 44 | 64ሸ | 89 |
| 5 | 1-2 | 54ሀ | 67 | 13 | 45-46 | 64ቀ | 89 |
| 5 | 3-12 | 54ለ | 68 | 13 | 47-50 | 64በ | 89 |
| 5 | 13-16 | 54ሐ | 69 | 13 | 51-53 | 64ተ | 89 |
| 5 | 17-20 | 54መ | 69 | 13 | 54-58 | 69 | 97 |
| 5 | 21-48 | 54ሠ | 69 | 14 | 1-2 | 71ሀ | 101 |
| 6 | 1-18 | 54ረ | 71 | 14 | 3-12 | 71ለ | 102 |
| 6 | 19-7:6 | 54ሰ | 72 | 14 | 13-14 | 72ለ | 104 |
| 7 | 7-27 | 54ሸ | 73 | 14 | 15-21 | 72ሐ | 105 |
| 7 | 28-8:1 | 54ቀ | 75 | 14 | 22-23 | 73 | 108 |
| 8 | 2-4 | 45 | 56 | 14 | 24-33 | 74 | 108 |
| 8 | 5-13 | 55 | 75 | 14 | 34-36 | 75 | 110 |
| 8 | 14-17 | 43 | 54 | 15 | 1-20 | 77 | 113? |
| 8 | 18 | 65 | 90 | 15 | 21-28 | 78 | 115 |
| 8 | 19-22 | 93 | 134 | 15 | 29-31 | 79ሀ | 116 |
| 8 | 23-27 | 65 | 90 | 15 | 32-38 | 79ለ | 117 |
| 8 | 28-34 | 66 | 91 | 15 | 39-16:4 | 80 | 118 |
| 9 | 1-8 | 46 | 57 | 16 | 5-12 | 81ሀ | 118 |
| 9 | 9 | 47ሀ | 59 | 16 | 13-20 | 82 | 120 |
| 9 | 10-13 | 47ለ | 59 | 16 | 21-26 | 83 | 122 |
| 9 | 14-17 | 48 | 60 | 16 | 27-28 | 84 | 123 |
| 9 | 18-26 | 67 | 93 | 17 | 1-8 | 85 | 123 |
| 9 | 27-34 | 68 | 96 | 17 | 9-13 | 86 | 125 |
| 9 | 35-38 | 70ሀ | 97 | 17 | 14-21 | 87 | 126 |
| 10 | 1-42 | 70ለ | 97 | 17 | 22-23 | 88 | 128 |
| 11 | 1 | 70ሐ | 101 | 17 | 24-27 | 89 | 129 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 18 | 1-5 | 90 | 129 |
| 18 | 6-14 | 91 | 130 |
| 18 | 15-35 | 92 | 133 |
| 19 | 1-12 | 122 | 172 |
| 19 | 13-15 | 123 | 173 |
| 19 | 16-30 | 124ሀ | 174 |
| 20 | 1-16 | 124ለ | 177 |
| 20 | 17-19 | 125ሀ | 178 |
| 20 | 20-28 | 125ለ | 179 |
| 20 | 29-34 | 126 | 180 |
| 21 | 1-11 | 128ለ | 184 |
| 21 | 12-13 | 129ለ | 189 |
| 21 | 14-17 | 128ለ | 184 |
| 21 | 18-19ሀ | 129ሀ | 188 |
| 21 | 19ለ-22 | 131 | 191 |
| 21 | 23-27 | 132ሀ | 193 |
| 21 | 28-22:14 | 132ለ | 194 |
| 22 | 15-22 | 133 | 197 |
| 22 | 23-33 | 134 | 199 |
| 22 | 34-40 | 135 | 200 |
| 22 | 41-46 | 136 | 201 |
| 23 | 1-36 | 137ሀ | 202 |
| 23 | 37-39 | 137ለ | 205 |
| 24 | 1-3 | 139ሀ | 206 |
| 24 | 4-14 | 139ለ | 207 |
| 24 | 15-28 | 139ሐ | 209 |
| 24 | 29-31 | 139መ | 211 |
| 24 | 32-41 | 139ሠ | 212 |
| 24 | 42-25:30 | 139ረ | 213 |
| 25 | 31-46 | 139ሰ | 215 |
| 26 | 1-5 | 140 | 216 |
| 26 | 6-13 | 141 | 217 |
| 26 | 14-16 | 142 | 218 |
| 26 | 17-19 | 143 | 218 |
| 26 | 20 | 144 | 219 |
| 26 | 21-25 | 146 | 221 |
| 26 | 26-29 | 148 | 225 |
| 26 | 30 | 152 | 232 |
| 26 | 31-35 | 147 | 223 |
| 26 | 36-46 | 152 | 232 |
| 26 | 47-56 | 153 | 235 |
| 26 | 57 | 155 | 239 |
| 26 | 58 | 156 | 241 |
| 26 | 59-68 | 155 | 239 |
| 26 | 69-75 | 156 | 241 |
| 27 | 1 | 157 | 243 |
| 27 | 2 | 159 | 244 |
| 27 | 3-10 | 158 | 244 |
| 27 | 11-14 | 159 | 244 |
| 27 | 15-26 | 161 | 248 |
| 27 | 27-30 | 162 | 252 |
| 27 | 31-34 | 163 | 253 |
| 27 | 35-44 | 164 | 255 |
| 27 | 45-50 | 165 | 259 |
| 27 | 51-56 | 166 | 260 |
| 27 | 57-58 | 167ሀ | 261 |
| 27 | 59-60 | 167ለ | 263 |
| 27 | 61-66 | 168 | 263 |
| 28 | 1 | 169 | 265 |
| 28 | 2-4 | 170 | 265 |
| 28 | 5-8 | 171 | 265 |
| 28 | 9-10 | 174 | 269 |
| 28 | 11-15 | 175 | 269 |
| 28 | 16-20 | 181 | 274 |

**ማርቆስ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | 1 | 20 | 36 |
| 1 | 2-6 | 21 | 36 |
| 1 | 7-8 | 23 | 38 |
| 1 | 9-11 | 24 | 39 |
| 1 | 12-13 | 25 | 40 |
| 1 | 14ሀ | 34 | 47 |
| 1 | 14ለ-15 | 37 | 50 |
| 1 | 16-20 | 41 | 52 |
| 1 | 21-28 | 42 | 53 |
| 1 | 29-34 | 43 | 54 |
| 1 | 35-39 | 44 | 55 |
| 1 | 40-45 | 45 | 56 |
| 2 | 1-12 | 46 | 57 |
| 2 | 13-14 | 47ሀ | 59 |
| 2 | 15-17 | 47ለ | 59 |
| 2 | 18-22 | 48 | 60 |
| 2 | 23-28 | 50 | 64 |
| 3 | 1-6 | 51 | 65 |
| 3 | 7-12 | 52 | 66 |
| 3 | 13-19 | 53 | 67 |
| 3 | 20-30 | 61 | 81 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ | ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | 31-35 | 63 | 83 | 11 | 12-14 | 129ሀ | 188 |
| 4 | 1-2 | 64ሀ | 84 | 11 | 15-18 | 129ለ | 189 |
| 4 | 3-25 | 64ለ | 84 | 11 | 19-26 | 131 | 191 |
| 4 | 26-29 | 64ሐ | 87 | 11 | 27-33 | 132ሀ | 193 |
| 4 | 30-32 | 64ሠ | 88 | 12 | 1-12 | 132ለ | 194 |
| 4 | 33-34 | 64ረ | 88 | 12 | 13-17 | 133 | 197 |
| 4 | 35-41 | 65 | 90 | 12 | 18-27 | 134 | 199 |
| 5 | 1-20 | 66 | 91 | 12 | 28-34 | 135 | 200 |
| 5 | 21-43 | 67 | 93 | 12 | 35-37 | 136 | 201 |
| 6 | 1-6ሀ | 69 | 97 | 12 | 38-40 | 137ሀ | 202 |
| 6 | 6ለ | 70ሀ | 98 | 12 | 41-44 | 138 | 205 |
| 6 | 7-11 | 70ለ | 98 | 13 | 1-4 | 139ሀ | 206 |
| 6 | 12-13 | 70ሐ | 101 | 13 | 5-13 | 139ለ | 207 |
| 6 | 14-16 | 71ሀ | 101 | 13 | 14-23 | 139ሐ | 209 |
| 6 | 17-29 | 71ለ | 102 | 13 | 24-27 | 139መ | 211 |
| 6 | 30 | 72ሀ | 104 | 13 | 28-32 | 139ሠ | 212 |
| 6 | 31-34 | 72ለ | 104 | 13 | 33-37 | 139ረ | 213 |
| 6 | 35-44 | 72ሐ | 105 | 14 | 1-2 | 140 | 216 |
| 6 | 45-46 | 73 | 108 | 14 | 3-9 | 141 | 217 |
| 6 | 47-52 | 74 | 108 | 14 | 10-11 | 142 | 218 |
| 6 | 53-56 | 75 | 110 | 14 | 12-16 | 143 | 218 |
| 7 | 1-23 | 77 | 113 | 14 | 17 | 144 | 219 |
| 7 | 24-30 | 78 | 115 | 14 | 18-21 | 146 | 221 |
| 7 | 31-37 | 79ሀ | 116 | 14 | 22-25 | 148 | 225 |
| 8 | 1-9ሀ | 79ለ | 117 | 14 | 26 | 152 | 232 |
| 8 | 9ለ-12 | 80 | 118 | 14 | 27-31 | 147 | 223 |
| 8 | 13-21 | 81ሀ | 118 | 14 | 32-42 | 152 | 232 |
| 8 | 22-26 | 81ለ | 119 | 14 | 43-52 | 153 | 235 |
| 8 | 27-30 | 82 | 120 | 14 | 53 | 155 | 239 |
| 8 | 31-37 | 83 | 122 | 14 | 54 | 156 | 241 |
| 8 | 38-9:1 | 84 | 123 | 14 | 55-65 | 155 | 239 |
| 9 | 2-8 | 85 | 123 | 14 | 66-72 | 156 | 241 |
| 9 | 9-13 | 86 | 125 | 15 | 1ሀ | 157 | 243 |
| 9 | 14-29 | 87 | 126 | 15 | 1ለ-5 | 159 | 244 |
| 9 | 30-32 | 88 | 128 | 15 | 6-15 | 161 | 248 |
| 9 | 33-37 | 90 | 129 | 15 | 16-19 | 162 | 252 |
| 9 | 38-50 | 91 | 130 | 15 | 20-23 | 163 | 253 |
| 10 | 1-12 | 122 | 172 | 15 | 24-32 | 164 | 255 |
| 10 | 13-16 | 123 | 173 | 15 | 33-37 | 165 | 259 |
| 10 | 17-31 | 124ሀ | 174 | 15 | 38-41 | 166 | 260 |
| 10 | 32-34 | 125ሀ | 178 | 15 | 42-45 | 167ሀ | 261 |
| 10 | 35-45 | 125ለ | 179 | 15 | 46 | 167ለ | 263 |
| 10 | 46-52 | 126 | 180 | 15 | 47 | 168 | 263 |
| 11 | 1-11 | 128ለ | 184 | 16 | 1 | 169 | 265 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 16 | 2-8 | 171 | 265 |
| 16 | 9-11 | 173 | 268 |
| 16 | 12-13 | 176 | 270 |
| 16 | 14 | 178 | 271 |
| 16 | 15-18 | 181 | 274 |
| 16 | 19-20 | 184 | 276 |
| ሉቃስ | | | |
| 1 | 1-4 | 1 | 23 |
| 1 | 5-25 | 4 | 26 |
| 1 | 26-38 | 5 | 27 |
| 1 | 39-45 | 6 | 27 |
| 1 | 46-56 | 7 | 28 |
| 1 | 57-66 | 8ሀ | 28 |
| 1 | 67-79 | 8ለ | 29 |
| 1 | 80 | 8ሐ | 29 |
| 2 | 1-7 | 9 | 30 |
| 2 | 8-20 | 11 | 31 |
| 2 | 21 | 12 | 31 |
| 2 | 22-38 | 13 | 31 |
| 2 | 39 | 16 | 34 |
| 2 | 40 | 17 | 34 |
| 2 | 41-50 | 18 | 34 |
| 2 | 51-52 | 19 | 35 |
| 3 | 1-2 | 20 | 36 |
| 3 | 3-6 | 21 | 36 |
| 3 | 7-14 | 22 | 37 |
| 3 | 15-18 | 23 | 38 |
| 3 | 19-20 | 34 | 47 |
| 3 | 21-23ሀ | 24 | 39 |
| 3 | 23ለ-38 | 3 | 24 |
| 4 | 1-13 | 25 | 40 |
| 4 | 14ሀ | 34 | 47 |
| 4 | 14ለ-15 | 37 | 50 |
| 4 | 16-31ሀ | 39 | 51 |
| 4 | 31ለ-37 | 42 | 53 |
| 4 | 38-41 | 43 | 54 |
| 4 | 42-44 | 44 | 55 |
| 5 | 1-11 | 41 | 52 |
| 5 | 12-16 | 45 | 56 |
| 5 | 17-26 | 46 | 57 |
| 5 | 27-28 | 47ሀ | 59 |
| 5 | 29-32 | 47ለ | 59 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 5 | 33-39 | 48 | 60 |
| 6 | 1-5 | 50 | 64 |
| 6 | 6-11 | 51 | 65 |
| 6 | 12-16 | 53 | 67 |
| 6 | 17-19 | 54ሀ | 67 |
| 6 | 20-26 | 54ለ | 68 |
| 6 | 27-30 | 54ሠ | 69 |
| 6 | 31 | 54ሸ | 73 |
| 6 | 32-36 | 54ሠ | 69 |
| 6 | 37-42 | 54ሰ | 72 |
| 6 | 43-49 | 54ሸ | 73 |
| 7 | 1-10 | 55 | 75 |
| 7 | 11-17 | 56 | 76 |
| 7 | 18-35 | 57 | 77 |
| 7 | 36-50 | 59 | 79 |
| 8 | 1-3 | 60 | 80 |
| 8 | 4 | 64ሀ | 84 |
| 8 | 5-18 | 64ለ | 84 |
| 8 | 19-21 | 63 | 83 |
| 8 | 22-25 | 65 | 90 |
| 8 | 26-39 | 66 | 91 |
| 8 | 40-56 | 67 | 93 |
| 9 | 1-5 | 70ለ | 98 |
| 9 | 6 | 70ሐ | 101 |
| 9 | 7-9 | 71ሀ | 101 |
| 9 | 10ሀ | 72ሀ | 104 |
| 9 | 10ለ-11 | 72ለ | 104 |
| 9 | 12-17 | 72ሐ | 105 |
| 9 | 18-21 | 82 | 120 |
| 9 | 22-25 | 83 | 122 |
| 9 | 26-27 | 84 | 123 |
| 9 | 28-36ሀ | 85 | 123 |
| 9 | 36ለ | 86 | 125 |
| 9 | 37-43ሀ | 87 | 126 |
| 9 | 43ለ-45 | 88 | 128 |
| 9 | 46-48 | 90 | 129 |
| 9 | 49-50 | 91 | 130 |
| 9 | 51-56 | 95 | 135 |
| 9 | 57-62 | 93 | 134 |
| 10 | 1-16 | 102ሀ | 146 |
| 10 | 17-24 | 102ለ | 147 |
| 10 | 25-37 | 103 | 147 |
| 10 | 38-42 | 104 | 148 |
| 11 | 1-13 | 105 | 149 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 11 | 14-36 | 106 | 150 |
| 11 | 37-54 | 107 | 151 |
| 12 | 1-12 | 108ሀ | 152 |
| 12 | 13-34 | 108ለ | 153 |
| 12 | 35-48 | 108ሐ | 154 |
| 12 | 49-53 | 108መ | 155 |
| 12 | 54-59 | 108ሠ | 155 |
| 13 | 1-9 | 109 | 156 |
| 13 | 10-21 | 110 | 156 |
| 13 | 22-30 | 113ሀ | 159 |
| 13 | 31-35 | 113ለ | 160 |
| 14 | 1-24 | 114 | 160 |
| 14 | 25-35 | 115 | 162 |
| 15 | 1-32 | 116 | 162 |
| 16 | 1-13 | 117ሀ | 164 |
| 16 | 14-31 | 117ለ | 165 |
| 17 | 1-10 | 117ሐ | 166 |
| 17 | 11-21 | 120ሀ | 170 |
| 17 | 22-37 | 120ለ | 170 |
| 18 | 1-14 | 121 | 171 |
| 18 | 15-17 | 123 | 173 |
| 18 | 18-30 | 124ሀ | 174 |
| 18 | 31-34 | 125ሀ | 178 |
| 18 | 35-43 | 126 | 180 |
| 19 | 1-10 | 127ሀ | 181 |
| 19 | 11-28 | 127ለ | 181 |
| 19 | 29-44 | 128ለ | 184 |
| 19 | 45-48 | 129ለ | 189 |
| 20 | 1-8 | 132ሀ | 193 |
| 20 | 9-19 | 132ለ | 194 |
| 20 | 20-26 | 133 | 197 |
| 20 | 27-40 | 134 | 199 |
| 20 | 41-44 | 136 | 201 |
| 20 | 45-47 | 137ሀ | 202 |
| 21 | 1-4 | 138 | 205 |
| 21 | 5-7 | 139ሀ | 206 |
| 21 | 8-19 | 139ለ | 207 |
| 21 | 20-24 | 139ሐ | 209 |
| 21 | 25-27 | 139መ | 211 |
| 21 | 28-33 | 139ሠ | 212 |
| 21 | 34-36 | 139ረ | 213 |
| 21 | 37-38 | 131 | 191 |
| 22 | 1-2 | 140 | 216 |
| 22 | 3-6 | 142 | 218 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 22 | 7-13 | 143 | 218 |
| 22 | 14-16 | 144 | 219 |
| 22 | 17-20 | 148 | 225 |
| 22 | 21-23 | 146 | 221 |
| 22 | 24-30 | 144 | 219 |
| 22 | 31-38 | 147 | 223 |
| 22 | 39-46 | 152 | 232 |
| 22 | 47-53 | 153 | 235 |
| 22 | 54ሀ | 155 | 239 |
| 22 | 54ለ-62 | 156 | 241 |
| 22 | 63-65 | 155 | 239 |
| 22 | 66-71 | 157 | 243 |
| 23 | 1-5 | 159 | 244 |
| 23 | 6-12 | 160 | 247 |
| 23 | 13-25 | 161 | 248 |
| 23 | 26-33ሀ | 163 | 253 |
| 23 | 33ለ-43 | 164 | 255 |
| 23 | 44 | 165 | 259 |
| 23 | 45 | 166 | 260 |
| 23 | 46 | 165 | 259 |
| 23 | 47-49 | 166 | 260 |
| 23 | 50-52 | 167ሀ | 261 |
| 23 | 53-54 | 167ለ | 263 |
| 23 | 55-56 | 168 | 263 |
| 24 | 1-8 | 171 | 265 |
| 24 | 9-12 | 172 | 267 |
| 24 | 13-32 | 176 | 270 |
| 24 | 33-35 | 177 | 271 |
| 24 | 36-43 | 178 | 271 |
| 24 | 44-49 | 183 | 275 |
| 24 | 50-53 | 184 | 276 |

**ዮሐንስ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | 1-18 | 2 | 23 |
| 1 | 19-28 | 26 | 41 |
| 1 | 29-34 | 27 | 42 |
| 1 | 35-52 | 28 | 43 |
| 2 | 1-11 | 29 | 44 |
| 2 | 12 | 30 | 44 |
| 2 | 13-22 | 31 | 44 |
| 2 | 23-25 | 32ሀ | 45 |
| 3 | 1-21 | 32ለ | 45 |
| 3 | 22-36 | 33 | 46 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 4 | 1-4 | 34 | 47 |
| 4 | 5-26 | 35ሀ | 47 |
| 4 | 27-38 | 35ለ | 49 |
| 4 | 39-42 | 35ሐ | 49 |
| 4 | 43-45 | 36 | 49 |
| 4 | 46-54 | 38 | 50 |
| 5 | 1-9 | 49ሀ | 62 |
| 5 | 10-18 | 49ለ | 62 |
| 5 | 19-47 | 49ሐ | 63 |
| 6 | 1-3 | 72ለ | 104 |
| 6 | 4-13 | 72ሐ | 105 |
| 6 | 14-15 | 73 | 108 |
| 6 | 16-21 | 74 | 108 |
| 6 | 22-59 | 76ሀ | 110 |
| 6 | 60-71 | 76ለ | 112 |
| 7 | 1 | 77 | 113 |
| 7 | 2-9 | 94 | 134 |
| 7 | 10 | 95 | 135 |
| 7 | 11-31 | 96ሀ | 136 |
| 7 | 32-52 | 96ለ | 137 |
| 7 | 53-8:11 | 97 | 138 |
| 8 | 12-20 | 98 | 139 |
| 8 | 21-30 | 99ሀ | 139 |
| 8 | 31-59 | 99ለ | 140 |
| 9 | 1-7 | 100ሀ | 141 |
| 9 | 8-12 | 100ለ | 142 |
| 9 | 13-34 | 100ሐ | 142 |
| 9 | 35-38 | 100መ | 144 |
| 9 | 39-41 | 100ሠ | 144 |
| 10 | 1-18 | 101ሀ | 144 |
| 10 | 19-21 | 101ለ | 145 |
| 10 | 22-39 | 111 | 157 |
| 10 | 40-42 | 112 | 159 |
| 11 | 1-16 | 118ሀ | 166 |
| 11 | 17-44 | 118ለ | 167 |
| 11 | 45-54 | 119 | 169 |
| 11 | 55-12:1 | 128ሀ | 183 |
| 12 | 2-8 | 141 | 217 |
| 12 | 9-11 | 128ሀ | 183 |
| 12 | 12-19 | 128ለ | 184 |
| 12 | 20-36ሀ | 130ሀ | 190 |
| 12 | 36ለ-50 | 130ለ | 191 |
| 13 | 1-20 | 145 | 220 |
| 13 | 21-30 | 146 | 221 |
| 13 | 31-38 | 147 | 223 |
| 14 | 1-31 | 149 | 226 |
| 15 | 1-17 | 150ሀ | 228 |
| 15 | 18-16:4 | 150ለ | 228 |
| 16 | 5-15 | 150ሐ | 229 |
| 16 | 16-22 | 150መ | 230 |
| 16 | 23-33 | 150ሠ | 230 |
| 17 | 1-26 | 151 | 231 |
| 18 | 1 | 152 | 232 |
| 18 | 2-12 | 153 | 235 |
| 18 | 13-14 | 154 | 238 |
| 18 | 15-18 | 156 | 241 |
| 18 | 19-23 | 154 | 238 |
| 18 | 24 | 155 | 239 |
| 18 | 25-27 | 156 | 241 |
| 18 | 28-38 | 159 | 244 |
| 18 | 39-19:16ሀ | 161 | 248 |
| 19 | 16ለ-17 | 163 | 253 |
| 19 | 18-27 | 164 | 255 |
| 19 | 28-30 | 165 | 259 |
| 19 | 31-38 | 167ሀ | 261 |
| 19 | 39-42 | 167ለ | 263 |
| 20 | 1 | 171 | 265 |
| 20 | 2-10 | 172 | 267 |
| 20 | 11-18 | 173 | 268 |
| 20 | 19-25 | 178 | 271 |
| 20 | 26-31 | 179 | 272 |
| 21 | 1-25 | 180 | 273 |

**የሐዋርያት ሥራ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | 3-8 | 183 | 275 |
| 1 | 9-12 | 184 | 276 |
| 1 | 18-19 | 158 | 244 |

**1ኛ ቆሮንቶስ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 11 | 23-26 | 148 | 225 |
| 15 | 5ሀ | 177 | 271 |
| 15 | 5ለ | 179 | 272 |
| 15 | 6 | 181 | 274 |
| 15 | 7 | 182 | 275 |

# መጣጥፎች

# 1

# ወንጌላት የማዛመድ ሥራ መርሖችና ችግሮች

ወንጌላትን እያዛመዱ ማጥናት ብዙ ጠቀሚታዎች አሉት። ስለተመሳሳይ ሁነቶች ያሉ መረጃዎች ሁሉ፥ ቃለ ልውውጦች ወይም ጭውውቶችና ንግግሮች አንድ ገጽ ላይ ጎን ለጎን ሰፍረዋል። ወንጌላት ውስጥ ያሉትና የተለያዩ ሁኔታዎችን የሚገልጡት ትረካዎች ሁሉ ሊሆኑ ይችላል ተብሎ በሚገመተው አኳኋን በቅደም ተከተል ተገልጠዋል። ስለሆነም አንባቢው ኢየሱስ ከመጸነሱ ጀምሮ ከትንሣኤ በኋላ እስከነበረው አገልግሎቱ ድረስ ስላለው የሕይወቱ ጉዞ ጠቅላላ ምልከታ ሊኖረው ይችላል። ይህ ለብዙ አንባቢያን ታላቅ ጥቅም ያለው አዲስ ልምምድ ይሆናል።

ይሁን እንጂ፥ ይህ ተዛምዶ ለመጀመሪያ ጊዜ በጥንቃቄ ሲነበብ፥ በተለይ የወንጌላቱን እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነትና እውነተኛነት ለተቀበለ ሰው ግር የሚያሰኝ ይሆን ይሆናል። ምንም እንኳን አራት ፍጹም ተመሳሳይነት የሌላቸው ወንጌላት የመኖራቸውን እውነት አንባቢያን ቢገነዘቡ፥ ብዙዎቹ የእውነቱን ምንነት አልመ ረመሩም። የወንጌላትን ተዛምዶ የሚያነብ ሰው ግን ልዩነቶቹን ልብ ማለቱ የግድ ነው። የኢየሱስ ገለጣዎች አንዳንዴ እንደሚለያዩ አንባቢው ይረዳል። አንድ ወንጌላዊ በአንድ ውይይት፥ አባባል ወይም ንግግር ላይ የሚያቀርበው ዘገባ ከሞላ ጎደል ሌላው ወንጌላዊ ከሚያቀርበው ይልቅ የተሟላ ይሆን ይሆናል። በገለጣው ሰዋሰዋዊ አወቃቀር ልዩነቶች ይኖሩ ይሆናል። አንዳንድ ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም ባላቸው ቃላት ሊተኩ፥ የግሦች አረባብ ሊቀየር፥ ስሞች በተውላጠ ስሞች ሊተኩ ይችላሉ። በገለጣ ቅደም ተከተል ረገድም ልዩነት ይኖር ይሆናል። በሚቀርበው ዘገባ የሚታየው ልዩነት አንዳንዴ እርስ በርሱ የሚቃረን ሊመስልም ይችላል። አልፎ አልፎም አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ አባባሎች በአገባባቸው መሠረት ሲታዩ፥ ፍጹም የማይገናኙ ሁኔታዎችን የሚያመለክቱ ይመስሉ ይሆናል። በማቴዎስና በሉቃስ በተመዘገቡት ብጹአን መካከል የጎሉ ልዩነቶች አሉ። ታዲያ የትኛው ዘገባ ነው ትክክሉ? ሁለቱም ትክክል ናቸው? የልዩነቶቹ ምክንያት እንዴት ነው የሚታወቀው?

በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው የኢየሱስን ተግባራት በሚያነብበት ጊዜ ተመሳሳይ ሁነቶች የተደረጉት በተለያዩ መንገዶች መሆኑን ይረዳል። ሁነቶቹ የተለያዩ ናቸው ወይስ ተመሳሳይ ሆነው ሳለ በተሳሳተ ሁኔታ ተመዘገቡ? አንድ ተመሳሳይ ለሆነ ነገር አንዳንዴ ሌላ ወንጌል ውስጥ በተለየ ሁኔታ ተመዝግቦ መገኘቱ፥ ሁኔታውን ይበልጥ አወሳስቦታል። አንዳንዴ ደግሞ ተመሳሳይ ለሆነ ነገር ብዙ የተለያዩ ዝርዝር ገለጣዎች ተሰጥተዋል። እነዚህ ዝርዝር ገለጣዎችም አንዳንዴ የልዩነት ሁኔታ ይታይባቸው ይሆናል። የወንጌላት ጸሐፊዎች ተመሳሳይ ሁኔታዎችን አለመመዝገባቸው ጥቂት አንባቢዎችን ያስደንቅ ይሆናል።

ከነዚህ ክስተቶች ሳቢያ የሚነሡ ጥያቄዎች ግልጥና ቁም ነገር ያዘሉ ናቸው። እነዚህ ክስተቶች የወንጌላትን ታሪክ እውነትነት ዝቅ ያደርጉታል? ታሪካዊ ተዓማኒነታቸውስ ዘላቂነት ያለው ነው? በወንጌል እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነትና ስሕተት አልባነት ላይ የሚያስከትሉት ጥያቄ ይኖራል? ወይስ ወንጌል እስትንፋሰ-

እግዚአብሔር ነው የሚለውን መሠረታዊ ግንዛቤ በማያወላውል ሁኔታ ያረጋግጣሉ? አንድ እርግጠኛ የሚመስል ነገር አለ፤ ይኼውም የወንጌል ዘጋቢዎች ትክክለኞች ባለመሆን፥ የተሳሳቱና የሚቃረኑ ነገሮችን በማቅረብ በደለኞች ሆነው ከተገኙ፥ የወንጌሉ ተአማኒነትና እስትንፋሰ-እግዚአብሔርነት ያጠራጥራል የሚለው ነው።

ወንጌላትን እያነጻጸሩ በማንበብ ጊዜ ለሚነሡ የተዛምዶ ችግሮች ሁሉ በነዚህ የግርጌ ማስታወሻዎች መልስ መስጠቱ የሚቻል ወይም የሚያስፈልግ አይደለም። የዚህ ተዛምዶ አዘጋጆች ግን ወንጌል ታሪካዊ እውነትነት ያለውና እስትንፋሰ-እግዚአብሔር ለመሆኑ የጸና እምነት አላቸው። በዘገባ ወይም በመጻፍ ጊዜ አንዳንድ የተፈጥሮ እውቀት ደንቦች በሥራ ላይ ከዋሉ፥ ቃሉን በመፍታት ጊዜ ብዙዎቹ የተዛምዶ ችግሮች በበቂ ሁኔታ እንደሚፈቱም ያምናሉ። ቀሪዎቹ ችግሮች፥ ምንም እንኳ ቁርጥ ያለ መፍትሔ ለመስጠት ስለእነሱ ይበልጥ መረጃ ማግኘቱ የሚረዳ ቢሆን፥ ተገቢው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል።

የኢየሱስ ንግግሮች የተዘገቡበትን ሁኔታ በተመለከተ በተለይ አንዳንድ አጠቃላይ አመለካከቶች ተግባራዊ ይሆናሉ። ኢየሱስ በጊዜው የነበሩ ብዙ ሰዎች ያደርጉ እንደነበረው ሦስት ቋንቋዎችን ይናገር እንደነበር ይገመታል (መጣጥፍ 2ትን ይመልከቱ)። በብዙ ሁኔታ የአንድ ሰው ቃል ሲመዘገብ ያ ቃል የጽሑፉ መነሻ ከሆነው አረማውኛ (የሶርያ ቋንቋ) ወይም ከእብራይስጥ የተተረጎመ መሆኑ መረሳት የለበትም። በትርጉም ሥራ ጊዜ አንዳንድ ልዩነቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ በመተርጎም ጊዜ ቁርጥ ያለና የተወሰነ አሠራር ስለሌለው ልዩነቱ መኖሩም ተገቢ ነው። እንደውም ወንጌላውያን አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ የተናገረውን፥ ቃል በቃል አለመተርጎሙ ለዓላማቸው የሚስማማ መሆኑን ያምናሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸው ቁም ነገሮች ለታለሙለት አንባቢ በታማኝነት፥ በትክክልና በሚገባው ቋንቋ እስከተላለፉ ድረስ ይህ አባባላቸው ስህተት አይደለም። የኢየሱስ ንግግሮች ሲገለጡ አንዳንዴ የነጻ ትርጉም ዘዴ ሥራ ላይ ይውል ይሆናል። ይህ የሚሆነው ነጻ ትርጉም ዋናው ቋንቋ በሚነገርበት ጊዜ በምልክት፥ በእንቅስቃሴና በአገላለጥ የተባሉ ነገሮችን በመግለጥ ለመልእክቱ ኃይል ስለሚሰጠው ነው።

የኢየሱስን ንግግር በነጻ ትርጉም ቃል በቃል ከመተርጎም ሳቢያ ከሚመጡ ልዩነቶች ሌላ ልብ ሊባሉ የሚገባቸው ሌሎች ቁም ነገሮችም አሉ። ዘመናዊው የአጻጻፍ ዘዴ ቀጥተኛና እቻ ጥቅሶችን ለማመልከት በተለያዩ አሠራሮች ይጠቀማል። በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የሠፈሩ ቃላት የተናጋሪው ቀጥተኛ ንግግሮች ናቸው። ምንም እንኳ ጥቅሶቹ የዋናው ጥቅስ አካል ባይሆኑ እነሱን ግልጥ ለማድረግ በአቅራቢያው የተጨመሩ ቃላትን ለማመልከት ቅንፎች በአገልግሎት ላይ ውለዋል። ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ ወይም በተለያዩ ጊዜያት የተነገሩ ጥቅሶችን ለማመልከት ደግሞ በግርጌ ማስታወሻዎች መገልገል ያስፈልግ ይሆናል። የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ጸሐፊዎች ከነዚህ ምልክቶች አንዱ እንኳን አልነበሯቸውም። በመሆኑም ያልነበሩ ምልክቶችን እንደነበሩ ቆጥሮ ደረጃውን የጠበቀ ሥነ ጽሑፍ ከነሱ መጠበቅ ስሕተት ነው።

ከዚህም በላይ ዘመናዊው የጥቅስ ደንብ፥ የቃል ንግግሮችን በትክክል ለመመዝገብ መቅረጸ ድምጽ መጠቀም ያስፈልገው ይሆናል። ጥንታውያን ጸሐፍት መቅረጸ ድምፅ አልነበራቸውም። በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ግን አሳጥሮ የመጻፍ

ጥበብ (አጭር ጽሕፈት) በስፋት በሥራ ላይ ውሎ ነበር። ነገሮችን በመዝገብ የመያዝ ልምድ የነበረው ቀራጩ ማቴዎስ ይህ እውቀት ይኖረው ይሆናል። የክርስቶስን ድርጊቶችና ንግግሮች መዝግቧል የሚል አሳብም አለ። ይህን በማድረግም የወንጌላት መዝጋቢዎችን ጨምሮ የቀድሞ ክርስቲያን ጸሐፊዎች ልምድ የሚገበዩበትን መነሻ ፈጥሯል። በወንጌላት መካከል ያለውን አስደናቂ ተዛምዶ ይህ ሁኔታ በከፊል ይገልጠዋል። ያም ቢባል አሠራሩ ልዩነቶችን ያጠፋል ማለት አይደለም። ምክንያቱም ከብዙ ሰዎች መካከል ይህ ልምድ የሚገኝበትን የመነሻ ባሕል የፈጠረ እርሱ ብቻ ነበር።

እነዚህን አጠቃላይ ግንዛቤዎች በአእምሮ በመያዝ ነው አንድ ሰው ኢየሱስ ወይም ሌሎች ሰዎች የተናገሯቸው ነገሮች፥ ትክክለኛነት ይጎድላቸዋል የሚሉትን የተለያዩ ንድፈ አሳቦች መመርመር የሚኖርበት። ይህ ተገቢ አባባል ነውን? በፍጹም አይደለም። ወንጌላት ትክክለኛነት የሚጎድላቸው ሊባሉ አይገባም። ምክንያቱም ተግባራዊ የሚሆኑና የወንጌላቱን ትክክለኛነት የሚያረጋግጡ ቢያንስ ሁለት አማራጮች አሉ።

1. አንደኛው መንገድ ጸሐፊዎቹ በኋለኛው ዘመን ከዳበረው ትክክለኛ የቃል ገለጣ ደረጃ ጋር የግድ መስማማት ወይም ያን መከተል ያልነበረባቸው መሆኑን መረዳት ነው። ይህ ገለጣ የኢየሱስን ንግግር ቃል በቃል በጽሑፍ ማስቀመጥን ሁልጊዜ እንደ ዋና ጉዳይ አይመለከትም። ይልቁንም የወንጌላውያኑ ቃላት ኢየሱስ የተናገ ራቸውን እውነቶች ይገልጣሉ? የሚለው ነው ዋናው ቁም ነገር። ኢየሱስ የተናገ ራቸውና በተለያዩ ወንጌላውያን የቀረቡት ገለጣዎች በትርጉማቸው አንዱ ከሌላው ይስማማሉ? የሚለውም ሌላ ጥያቄ ነው። መልሱ አዎ ከሆነ፥ የገለጣዎቹ ትክክለኛነት አያጠራጥርም።

በተግባር ሲታይ ይህን የመሰለው ሌሎች የተናገሩትን በቃል የመግለጡ ዘዴ አሁንም ይሠራበታል። በጥንቃቄ እስከተሠራበት ድረስ የተባለውን ነገር እውነተኛነት ማንም አይጠራጠርም። የሌላን ሰው ንግግር ቃል በቃል የመድገሙ ሁኔታ የተለመደ ወይም የሚቻል አይደለም። አንዳንድ ጊዜ ቃላትን ወይም አንቀጽን ሁሉ ደግሞ መናገሩ አዳጋች ነው። አንድ ሰው ከአንድ ተራ ውይይት እንዲወጡ የሚጠብቃቸው ጠቃሚ ንግግሮች፥ ዋና አሳቦችን፥ ዋና ዋና ጉዳዮችን፥ ከአንዱ ጉዳይ ወደ ሌላው የሚደረገውን ሽግግር ጨምሮ የውይይቱ አጠቃላይ አቅጣጫ ናቸው። ምንም እንኳ የተለያዩ ገለጣዎች ከነዚህ ሁኔታዎች ጋር እንዲስማሙ የሚጠበቅ ቢሆን፥ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ሲገባ ግን የተናጋሪዎችን ስሜትና ዓላማ የሚያንጸባርቁ ልዩነቶች እንደሚኖሩ ይጠበቃል። በተራ ውይይት ወቅት የሌላን ሰው ንግግር የሚገልጥ አንድ ሰው፥ ሰዎችን ቢለውጥ፥ ስምን በተውላጠ ስም ቢቀይር ወይም ተገላቢጦሹን ቢያደርግ፥ የቃላቱን የጊዜ ገለጣ፥ የግሦችን ድምጸት ወይም ሁኔታ ለውጦ ቢያቀርብ፥ ተመሳሳይ ነገሮችን ቢተካ የንግግሩን እውነትነት መጠራጠር ተገቢ አይደለም። ቃላትን መምረጥ ጠቃሚ ቢሆንም፥ ለማለት የተፈለገ ነገር በተለያዩ መንገዶች ሊገለጥ ይችላል። የቃላት እስትንፋስ እግዚአብሔር መሆን፥ እውነት የሚገለጠው በአንድ መንገድ ብቻ ነው ሊያሰኝ አይችልም። ይልቁንም መንፈስ ቅዱስ በሰዎች በኩል የተናገረውና ቃል በቃል የተገለጠው ንግግር እውነት መሆኑን ነው የሚያመለክተው።

2. በአንድ ንግግር ውስጥ የተለያዩ ገለጣዎች ቢኖሩም እንኳ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት የመከላከያው ሁለተኛ አማራጭ የሚመሠረተው፥ ገለጣዎቹ የኢየሱስና የሌሎቹ ሰዎች የቃል ንግግሮች ያሉባቸው በመሆናቸው ላይ ነው። ግሪክኛውን ቋንቋ በመጠቀም ጊዜ መነሻ የሆነው ምክንያት ይህ ይሆናል። የኢየሱስን አስተምህሮ በአጭር አጻጻፍ የመዘገቡ ሰዎች፥ ዋናዎቹን ቃላት ለመያዝ ሲሉ የተጠቀሙበት ዘዴ ይህ መሆኑ አያጠራጥርም። በተጨማሪም ከአይሁድ መካከል የሥለጠኑና ከፍተኛ የማስታወስ ችሎታ ያላቸው ሰዎች በጊዜው መኖራቸው ግንዛቤ ሊሰጠው ይገባል። እነዚህ ሰዎች በሃያኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩት ምዕራባውያን ይልቅ ዝርዝር ጉዳዮችን የማስታወስ ችሎታ የነበራቸው መሆኑ በአጠቃላይ ታምኖበታል።

አጭር አጻጻፍንና ትውስታን ከመጠቀም ባሻገር፥ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃላት ወደ ሰዎች አእምሮ በማምጣት ያከናወነው ተግባርም ግንዛቤ ሊሰጠው ይገባል። ኢየሱስ ረዳት ስለሆነው መንፈስ ቅዱስ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ ‘‘አብ በስሜ የሚልከውን ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፥ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል’’ (ዮሐ. 14፡26)። መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላሉና በቃል ለተነገሩ ሌሎች ክፍሎች ምዝገባ ምሪት ከሰጠ፥ ለወንጌላትም ይህንኑ ማድረጉ እርግጥ ነው።

አንድ ሰው በዚህ መንገድ ቢጠቀም፥ በተመሳሳይ ዘገባዎች ወይም ውይይቶች መካከል ያሉ ልዩነቶች የተገለጡት፥ የትኛውም ወንጌል ቢሆን በአንድ ሁኔታ የተነገሩ ወይም የተከናወኑ ድርጊቶችን ሁሉ ያልመዘገበ መሆኑን በመረዳት መሆኑን ይገነዘባል። እንደውም ማንኛውም የተመሳሳይ ጉዳይ ቅንብር ያንድን ንግግር ወይም ውይይት ዝርዝር ነገር የመዘገበ መሆኑ አጠራጣሪ ነው። ክርስቶስ አንዳንድ ትምህርቶቹን በተለያዩ አጋጣሚዎች ጥቂቱ ለየት ባለ ሁኔታ የደጋገማቸው መሆኑ ጥርጥር የለውም። በአንድ አጋጣሚ ብቻም ቢሆን ይህን መደጋገም ተጠቅሞበት ይሆናል። በመሆኑም በተለያየ ሁኔታ በጥቂቱ የተገለጡ ተመሳሳይ ነገሮች ወይም ሁነቶች፥ በአንድ አጋጣሚ የተከናወኑና በተለያዩ መንገዶች የተገለጡ የአንድ ንግግር ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። እያንዳንዱም ጸሐፊ ለሱ የሚሆን ገለጣን እየመረጠ የዘገበ መሆኑን ያስረዳሉ። የዚህ አባባል ናሙና የሚሆነው ማቴዎስ፥ ‘‘በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብጹዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና’’ (ማቴ. 5፡3) የሚለው ሲሆን፥ ይህንኑ አባባል ሉቃስ እንዲህ በማለት ገልጦታል፦ ‘‘እናንተ ድሆች ብጹዓን ናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ ነውና’’ (ሉቃስ 6፡20)። ኢየሱስ ይህን የብፁዕነት ቃል በተራራው ስብከቱ በተለያየ አቀራረብ ገልጦት ይሆናል። እንዲያ ከሆነ መጀመሪያ ስለ ሦስተኛ ቁጥር ወይም ሰው ተናገረ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ስለ ሁለተኛ ቁጥር (እናንተ ብሎ) ተናገረ፥ እና መንግሥተ ሰማያትን በሁለት አርእስት ጠቀሰው። በአንደኛው ንግግሩ ድኅነትን ‘‘በመንፈስ’’ በማለት ሲያብራራው፥ በሌላው ግን ይህን አላደረገም። በመሆኑም ከሁለቱ ወንጌላት የትኛውም ቢሆን ሙሉውን መልእክት እንዳልመዘገበ ስለምንረዳ፥ ይህ ገለጣ በጣም ይታመናል።

ስለ ሰናፍጭ ዛፍ የተነገረው ምሳሌ (ማቴ. 13፡32፤ ማር. 4፡32) ኢየሱስ በአንድ አጋጣሚ እንዴት አንድን ነገር ጥቂት ለየት ባለ መንገድ እንደደጋገመ ያመለክታል። በማቴዎስ ዘገባ መሠረት፥ የሰማይ ወፎች ‘‘በቅርንጫፎችዋ’’

ይሰፍራሉ። በማርቆስ ዘገባ መሠረት ግን ወፎቹ "በጥላዋ" ይሰፍራሉ። ኢየሱስ የተናገረው የትኛውን ነው? ሁለቱንም ተናግሯል ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ አለ። እንደገና በማቴዎስ ገለጣ መሠረት በደብረዘይት ተራራ ስብከቱ ኢየሱስ ወደፊት የሚነሱ ሐሰተኞች "እኔ ክርስቶስ ነኝ" (ማቴ. 24፥5) እያሉ ይመጣሉ ማለቱን ነው የገለጠው። ማርቆስና ሉቃስ ግን ሐሰተኛው "እኔ ነኝ" የሚል መሆኑን እንደገለጠ ነው የጠቀሱት (ማር. 13፥6፤ ሉቃስ 21፥8)። ይህን የመሰሉ አነስተኛ ልዩነቶች ብዙ ናቸው።

በሌሎች ሥፍራዎች ያሉት ልዩነቶችም ቀላል አይደሉም። "ስለዚህ" (ማቴ. 13፥13) በሚለውና፥ "እንዳይሰረይላቸው" (ማር. 4፥12) በሚለው ቃላት መካከል ያለው ልዩነት ትርጉምን በተመለከተ የሚጠቁመው ሰፊ ነገር አለ። ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ የተናገረው ተቃዋሚዎቹ ቀድሞውኑ በመንፈስ ዕውሮች በመሆናቸው ነው ወይስ የታወሩ እንዲሆኑ? ምናልባት ሁለቱንም ይሆናል የተናገረው። በማቴዎስ ገለጣ፥ ቃላቱ የሚናገሩት ስለኢየሱስ ጠላቶች ሲሆን፥ በሌሎቹ ግን ስለ ደቀ መዛሙርቱ ነው። እዚህም የትርጉሙ ልዩነት የጎላ ነው። እንዲህ የጎሉ ልዩነቶች አዘውትረው ስለሚገጥሙ፥ መፍትሔያቸው ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በአንድ ምክንያት ተመሳሳይ መሠረታዊ እውነቶችን ደጋግሞ የተናገረ መሆኑን መረዳቱ ነው።

በዚህ መሠረት እንግዲህ የተመሳሳይ ጉዳዮች ገለጣ ትክክል አለመሆን መሠረታዊ ነገር አለመሆኑን ለማሳየት ከሁለቱ አማራጮች አንዱ ወይም ሁለቱ በጣምራ በቂ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ያሉን ኢየሱስ የተናገራቸው ትክክለኛ ቃላት ወይም አስተዋጽኦዎቹ ናቸው ብሎ በትክክል ለመናገር ያዳግታል። ከሁለቱም የሆነ ነው ያለን ብለን ለመናገር እንችል ይሆናል። ለቀረበው ቃል እውነተኛነት ጠቃሚው ጉዳይ፥ የተጻፈውን ነገር በመምራት ረገድ መንፈስ ቅዱስ የነበረውን ሚና መገንዘቡ ነው። ወንጌላት በብዙ ሁኔታዎች እርስ በርሳቸው ከመለያየት ይልቅ አንድ መሆናቸውን ከዚህ መገንዘቡ አያዳግትም።

በተለያየ ቅደም ተከተል በወንጌላውያን ስለቀረቡ ሁኔታዎች ታዲያ ምን ይባል? በመጀመሪያ በሁለት ሁኔታዎች መሠረት፥ ማለት በተወሰነ ክልልና በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲሁም ሁለቱን በብዙ ረገድ በማገናኘት አንድ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይቻላል። የገለጣዎቹ ዋና ነገሮች ከተለያዩ ግን የአንድ ክንውን ዘገባዎች ሆነው ሊወሰዱ አይገባም። ስለዚህ የቅደም ተከተል ልዩነት፥ በአንድ ወሳኝ ጊዜ የሆኑና የተለያዩ ሁነቶችን በዝርዝር የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ወንጌላት በቃላትም ሆነ በሁነት ያላቸውን በተመሳሳይ ቅደም ተከተል አለማቅረባቸው ችግር ሊሆን የሚችለው፥ ጸሐፊዎቹ አንድ ወጥ የሆነ የጊዜ ቅደም ተከተል መከተል ነበረባቸው የሚል አስተሳሰብ ሲኖር፥ ወይም የታሪኩን ቅደም ተከተል ሙሉ በሙሉ ጠብቀው እንደገና ያናጉታል የሚል እምነት ሲኖር ነው። የመጀመሪያው እምነት ተገቢ ያለመሆኑ ግልጥ ሲሆን፥ ሁለተኛው ሊሆን የሚችል አይደለም። ምንም እንኳ የቅደም ተከተል ቅንብር እጅጉን የሚጠበቅ ቢሆን፥ ለጥሩ ዘገባ ቅድመ ሁኔታ ሊሆን አይችልም። ጸሐፊዎቹ ወይም ደራሲዎቹ ለዓላማቸው የሚጠቅም መስሎ ከታያቸው፥ የሚጽፉትን ነገር በቅደም ተከተል ከማድረግ ይልቅ በጉዳዩ የማቀናበር ነጻነት አላቸው። ይህ ደራሲዎች የሚገለገሉበት ነጻነት፥ በወንጌላት ጽሑፍ ብዙ የቅደም

ተከተል ልዩነቶች ያስከትላል። ሁኔታው የወንጌላትን ጽሑፍ በቅደም ተከተል ለማዛመድ ለሚሻ ሰው ችግር ይፈጥርበታል። የትኛው ወንጌላዊ ነው ያን የቅደም ተከተል ሥርዓት ተከትሎ የጻፈ? አንድን ጊዜ ወይም ቦታ ሲጠቀስ የሚፈለገውን ነገር ይጠቁም ይሆናል፤ ሁሌ የሚሆን ግን አይደለም። ይሁን እንጂ ይህ የደራሲው ሳይሆን ጽሑፉን የሚያዛምደው ሰው ችግር ነው።

በመጨረሻም የወንጌላትን ተዛምዶ በጥንቃቄ የሚያነብ አንድ ሰው ሁነቶችን በመዘርዝር ጊዜ፥ በሁለት ወይም ሦስት ወንጌላውያን መካከል ልዩነት መኖሩን ልብ ይላል። ይህን የመሳሰሉትን ጥቂት የሁነት ምሳሌዎችን በመገንዘብ እውነት የሆነ ወይም የሚመስል ምንም ልዩነት ያለመኖሩንም ይረዳል። በብዙ ሁኔታ ይህ መፍትሔ ባይሆንም፥ መፍትሔውን ማግኘቱ ግን አይከብድም። አንዳንድ ጸሐፊዎች አንድን ነገር በሚተርኩበት ጊዜ የተባለውን፥ የሆነውንና ተከታታይ ሁኔታዎችን በመግለጥ ረገድ በብዙ ነጥቦች መለያየታቸው የሚሆንና ሊሆን የሚችል ነገር ነው።

ይህ እውነት በዕለት ተዕለት ልምምድ የተረጋገጠ ነው። በአንድ የጨዋታ ሜዳ የተለያየ አቅጣጫ አጫዋች ዳኞች የሚመደቡት የተለያዩ ነገሮችን ይመለከቱ ዘንድ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በጎዳና ማቋረጫዎች ላይ የተመደቡ ብልህና ረጋ ያሉ ተመልካቾች ስለ አንድ የተሽከርካሪ አደጋ የተመለከቱትን የሚገልጡት በተለያየ መንገድ ነው። በዚሁ አኳኋን በአንድ ስብሰባ ላይ የተገኙ ብቁዕ ጋዜጠኞች ስለ ጉባኤው በሚገልጡበት ጊዜ ዘገባቸው ይለያያል። ለምን? ምክንያቱም እያንዳንዱ ጋዜጠኛ የሚገልጠው እሱ ከተመለከተው አንጻር ወይም በተጠቀመበት የመረጃ ምንጭ ላይ በመመሥረት ስለሚሆን ነው። እያንዳንዱ ተራኪ የሚገልጠውን ነገር የሚያቀርበው፥ ከዓላማው ጋር በሚስማማ አኳኋን በማቀናበር ነው። አንደኛው ተመልካች የገለጠውን ሌላው በሁለቱም ወገን ሐሰት በማይታይበት ሁኔታ በዝምታ ያልፈው ይሆናል። በጣም የተቀራረበ ተመሳሳይነት ያላቸው ገለጣዎች ቢኖሩ ግን፥ በሥራው ግብረአበርነት ወይም አብሮነት መኖሩን የሚያስጠረጥር ሁኔታ ይፈጠራል።

ምንም እንኳን የወንጌላት ገለጣዎች ላይ ላዩን እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ቢመስሉ፥ ጸሐፊዎች ያቀረቧቸው የተለያዩ ምልከታዎችና ምርጫዎች እራሳቸው የትክክለኛነትና ተአማኒነት ምልክቶች ናቸው። በዚህ ምሳሌ መሠረት ተቃርኖዎቹ የሚመስሉ እንጂ በእርግጥ ያሉ አይደሉም። በጥንቃቄ መፈተሽ በጽሑፉ ውስጥ ያሉ የሚመስሉ ተቃርኖዎችን ለመፍታትና ገለጣዎቹን ለማዛመድ ይረዳል። አንድ ሰው ግልጥና አሳማኝ መፍትሔዎች የማይገኙላቸው የሚመስሉ ተቃርኖዎች ቢገጥሙት እንኳ ይህን ለመቀበል መገፋፋት የለበትም። የሚቃረኑ በሚመስሉ ገለጣዎች መካከል ያሉትን እውነተኛና ዋና ዋና ተዛምዶዎች ለማቅረብ የሚያስችል በቂ መግለጫ የለም።

እነዚህ ግንዛቤዎች፥ በወንጌላት ተዛምዶ ንጽጽር ጥናት ወቅት የሚገጥሙ ችግሮችን ሁሉ አያስወግዱም። ይሁን እንጂ ለሌላ ጉዳዮች ተገቢ እና እውነት እንደመሆናቸው፥ በወንጌላት ጥናትም ጠቃሚ መመሪያዎች ናቸው። አብዛኛዎቹን የማዛመድ ችግሮች በአጥጋቢ ሁኔታ ይፈታሉ። አጥጋቢ መረጃዊ መፍትሔ የሌላቸው ጉዳዮች ሲገጥሙ፥ ያልሆነ ትርጉም ለመስጠት ከመጣር ይልቅ ነገሩን እንዳለ መተው ይሻላል። የእጅ ጽሑፍ ወደ ሌላ በሚገለጥበት ጊዜ የጽሑፍ መዛባት ይፈጸም ይሆናል፤ ይህ የስሕተት ቀላል ምክንያት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋሰ

እግዚአብሔር መሆኑን የሚያምን ተማሪ እግዚአብሔር ቃል ውስጥ ላለ ችግር ሁሉ መፍትሔ እንዲፈልግ ግዴታ የለበትም። ወንጌላት ተአማኒ መሆናቸው በተደጋጋሚ ከመረጋገጡ አንጻር፥ አንድ ሰው ወንጌላት እርስ በራሳቸው የሚቃረኑበትን መረጃ አቀርባለሁ ቢል አጉል ድፍረት አይሆንም? ታሪካዊ ገለጣዎች የሚይዙትን መረጃዎች መምረጡ የግድ አስፈላጊ ነው። የወንጌላት ጸሐፊዎች ታሪክ ሲዘግቡ አንድ ቀን፥ አንድ ሰው ጽሑፎቻቸውን ያዛምዳቸው ይሆናል ብለው እያሰቡ አልነበረም። ታሪካዊ ዘገባቸውን ለመጠራጠር ምንም የሚታመን ምክንያት የለንም። የዘገባ ዓላማቸው በጣም የተለያየ ነበር። በቀላሉ የተዛመዱ ታሪኮችን ለመጻፍ ቢፈልጉና፥ አድርገውት ቢሆን ኑሮ፥ የአሁኑን የማዛመድ ተግባር እጅግ ያቀሉት ነበር። ይህን ማድረጉ ግን መንፈስ ቅዱስ ከመራቸው አቅጣጫ ያዛባቸውና፥ የወንጌላትን የአጻጻፍ ባሕርይ እጅግ ይቀይረው ይሆናል። የወንጌላት ባሕርይም ይጠፋና የምሥራቹ ቃል ልዩ ልዩ ገለጣዎች ውጤት አልባ ይሆኑ ነበር።

# 2

# ኢየሱስ የተናገረባቸው ቋንቋዎች

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የኖሩ ፍልስጤማውያን ይጠቀሙበት የነበረውን ቋንቋ ለማጥናት ሞክረዋል። ኢየሱስ በመጀመሪያ የተናገራቸው ቋንቋዎች፥ እኛ ስለ ወንጌላት አጀማመር ባለን ታሪካዊ መረጃ አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ለምሳሌ ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት ቋንቋ አረማይክ[67] በመሆኑና ወንጌላት የአረማይክን ቃላትና አሳብ በመያዛቸው የወንጌልን እውነተኛነት ያረጋግጣል። በተቃራኒው ደግሞ ኢየሱስ ይናገር የነበረው በሴማዊ ቋንቋ አይደለም ቢባል፥ የቃሉን ሥልጣን ተዓማኒነት ያዛባዋል የሚል ክርክርም አልፎ አልፎ አለ።

የክርክሩ ሁኔታ ምንድነው? ላቲንኛ ፍልስጥኤም ውስጥ በቋንቋነት ማገልገሉ የተለመደ አልነበረም። ይህን ለማለት የሚያስደፍረው፥ የሮማውያን ወታደሮች ምድሪቱን ድል አደረጉ ማለት ላቲንኛ ድል አድርጓል ማለት ባለመሆኑ ነው። ታላቁ እስክንድር ከክርስቶስ ልደት በፊት በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተቀዳጀውን ድል በመከተል፥ በግሪኮች ቋንቋና ባሕላዊ እንቅስቃሴ፥ ግሪክኛ ዋነኛው የጋራ መገልገያ ቋንቋ ሆኖ ነበር። የሮማውያን ወረራና ድልም የጎላ ለውጥ አላመጣበትም። በክርስቶስ ዘመን፥ ግሪክኛ በፍልስጥኤም ምድር የነበረው ጠቀሜታ ምን ነበር? ጥቂት የተማሩ ሰዎች የሚጠቀሙበት የባሕልና የንግድ ቋንቋ ነበር፥ ወይስ ተራውም ሰው የሚገለገልበት? ከምሁራን ውጭ ሌሎችም የሚገለገሉበት ከሆነ፥ አጠቃቀሙ ምን ያህል የሰፋ ነበር? የአረማውያን ቋንቋስ ብዙሃኑ ባጠቃላይ የሚገለገሉበት ነበር? ከመካከለኛው ዘመን ወዲህ ያለው አመለካከት፥ ወደ ባቢሎን ከተደረገው ፍልሰት አንስቶ የዕብራይስጥ ቋንቋ ቀስ በቀስ ሕልውናው አክትመና የአረማይክ ቋንቋ በአይሁዳውያን መካከል የዕለት ከዕለት መነጋገሪያ ሆኖ የሚል ነው። ይሁን እንጂ የዕብራይስጥ ቋንቋ በእርግጥ ሕይወቱ አክትሞ፥ የአይሁድ ምሁራን የሚገለገሉበት የሃይማኖት ቋንቋ ሆኖ ነበር? ከነዚህ ሦስት ቋንቋዎች አንዱ የበላይነት ነበረው የሚለውን አሳብ የሚደግፉ ሰዎች አልጠፉም። ፍልስጥኤም ውስጥ በአንደኛው ክፍለ ዘመን አይሁዳውያን ሦስቱንም ቋንቋዎች ይገለገሉባቸው ነበር የሚሉ መረጃዎችም ተገኝተዋል።

በቅርቡ በከርሰ-ምድር ቁፋሮ የተገኘው መረጃ ይህን ችግር በመፍታት ረገድ ብዙ ረድቷል። የሙታን አፅም ማሳረፊያዎች ወይም መቃብሮች አንዳንዴ ጽሑፍ ይገኝባቸዋል። መቃብር ውስጥ ወይም ሃውልት ላይ ተጽፈው የተገኙ ቋንቋዎች ጥንት የነበሩ ሰዎች ይናገሯቸው የነበሩ ቋንቋዎች መሆናቸው ተገምቷል። የምድር ቁፋሮ ተመራማሪ የሆነ አንድ ግለሰብ ፍልስጥኤም ውስጥ ያሉትን የመቃብር ሥፍራዎች

---

[67] አረማይክ ጥንት አራም አሁን ደግሞ ሲሪያ የተባለችው ግዛት ቋንቋ ነበር። ቋንቋው ሴማዊ ሲሆን፥ ከዕብራውያን ቋንቋ ጋርም ይዛመዳል። ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓ.ዓ-500 ዓ.ም ድረስ በሶሪያ፥ በባቢሎን፥ በአሦርና በሜሶፖታሚያ የሚነገርም ቋንቋ ነበር። ፊደሎቹም ከዕብራውያን ፊደል ጋር ይመሳሰላሉ።

የብሉይ ኪዳን ግማሹ ክፍል የተጻፈው በአረማይክ ነበር። በአረማይክ የተጻፉ ሥነ-ጽሑፎች በምዕራብ ከግብፅ እስከ ሰሜን ካውካከስ ተራራዎች፥ በምስራቅ ህንድ፥ ቻይናና በደቡብ ዓረብ ውስጥ በሚገኘው ናባታ ግዛት ይገኙ ነበር። አረማይክ ከክርስቶስ ልደት በፊት 550- 450 ዓ.ዓ. ድረስ የፋርስ የመንግሥት የሥራ ቋንቋ በመሆን አገልግሏል።

በመጠኑ መርምሮ፥ ከሞላ ጎደል በሦስቱም ቋንቋዎች በእኩልነት የተጻፉ መረጃዎችን አግኝቷል።

እነዚህ ሦስት ቋንቋዎች በጊዜው ስለመኖራቸው የቀረበው ይህ ማስረጃ፥ ሙት ባሕር አካባቢ ባሉት ዋሻዎች ውስጥ በተደረገው ቁፋሮ ተጠናክሯል። በዚህ "የደብዳቤዎች ዋሻ" ይጋል ያዲን የተባሉ ሰውና ተባባሪዎቻቸው ከአሥራ አምስት ያላነሱ ደብዳቤዎች አግኝተዋል። ከአርባ የበለጡ ጥንታዊ ውሎች እና ደረሰኞችም ሰብስበዋል። የእነዚህ ማስረጃዎች ዕድሜ፥ ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጨረሻ ዓመታት ባር-ኮክባ የተባለ አይሁዳዊ አመፅ እስካስነሣበት ከ132-135 ዓ.ም. ይደርሳል። ዋሻው ይህ ሰውና ተከታዮቹ ይደበቁበት የነበረ ይመስላል። ደብዳቤዎቹም ወታደራዊና የዕለት ተዕለት ጉዳዮችን የሚገልጡ ሳይሆኑ አይቀርም። ሦስቱ ማለት ግሪክኛ፥ ዕብራይስጥኛ እና አረማይክ ቋንቋዎች በደብዳቤዎቹና በተለያዩ የታሪክ ሰነዶች ውስጥ ተገኝተዋል። እነዚህ ሰዎች ምሁራን አልነበሩም። ቋንቋዎቹን መረዳታቸውና በነሱም መገልገላቸው፥ በፍልስጥኤም ምድር የነበሩ ሰዎች ባጠቃላይ በቋንቋዎቹ መጠቀማቸውን ያመለክታል። ይህ ሁኔታ የዕብራይስጥ ቋንቋ ለአይሁድ ምሁራን ብቻ አለመሆኑን፥ ግሪክኛ ደግሞ የንግድና የባሕል ቋንቋ ብቻ አለመሆኑን ያስገነዝባል። ከአረማውኛ ጋር ሁለቱ ቋንቋዎች ሰው ሁሉ ይጠቀምባቸው የነበሩ ቋንቋዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። ከዚህ በመነሣት ኢየሱስ በሦስቱም ቋንቋዎች በቀላሉ ይናገር ነበር ለማለት ይቻላል።

አድልኦ በሌለበት ሁኔታ ወንጌላትን ማጥናት፥ ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ ያለው የቋንቋ ሁኔታ ይህን የሚመስል መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል። ሮበርት ገንዳሪ የተባሉት ተመራማሪ በከርሰ-ምድር ቁፋሮ ያገኙትን መረጃና የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን በማዛመድ ሦስቱ ቋንቋዎች ያኔ ያገለግሉ እንደነበር አረጋግጠዋል። በግሪክኛ በተጻፉት ወንጌላት ውስጥ የሴም ቋንቋ ከሆነው አረማይክ ወይም ከዕብራይስጥ አባባሎች መገኘታቸው፥ የሴማዊው ቋንቋ በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበረችው ፍልስጥኤም ውስጥ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ውሏል ማለት አይደለም። በብዙ ቋንቋዎች በሚገለገሉ አካባቢዎች በአገላለጥና በቃላት አጠቃቀም ረገድ ቋንቋዎቹ አንዱ በሌላው ውስጥ የመወራረስ ሁኔታ ታይቶባቸዋል። ለምሳሌ በግሪክኛ በተተረጎመው ብሉይ ኪዳን ("ሰፕቱዋጂንት"[68]) ውስጥ፥ የሴማውያን አገላለጥ ዘይቤ በብዛት ይታይበታል። ይህ በጊዜው ተስፋፍቶ የነበረና በብዙ ቋንቋዎች የመጠቀም ልማድ፥ ፍልስጥኤም ውስጥ ይነገር በነበረው ግሪክኛ ላይ ከባድ ተጽእኖ አድርጓል። ግሪክኛ በሴም ቋንቋ ወደሚገለገሉ አካባቢዎች መግባቱ፥ ከዚያ ወዲህ በሥፍራው ይነገር የነበረው ግሪክኛ

---

68 የሰብዓው ሊቃውንት ትርጉም (ሰፕቱዋጂንት) በግሪክኛ ለተተረጎመው የዕብራውያን ብሉይ ኪዳን የተሰጠ ስም ነው። የዚህ ትርጉም እውነተኛ ታሪክ በትክክል አልታወቀም። በሙሴ የተጻፉት አምስት የኦሪት መጻሕፍት በመጀመሪያ የተተረጎሙት፥ ግብፅ ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ285-246 ዓ.ዓ. በነበረው ጊዜ ውስጥ ነበር። እንዲያ የተደረገው ግሪክኛ ተናጋሪ ለሆኑ አይሁዳውያን ጥቅም ነበር። ቀሪው የብሉይ ኪዳን ክፍል ከ117 ዓ.ዓ. በፊት ተተረጎመ። የአዋልድ መጻሕፍት ደግሞ ከ117 ዓ.ዓ. እስከ ክርስቶስ ልደት በነበረው ጊዜ የተተረጎመ መሆኑ ይታወቃል።

የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ትርጉም ሰፕቱዋጂንት በጣም የታወቀ ስለነበር፥ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች፥ በተለይም ሉቃስና ወደ ዕብራውያን መልእክት የጻፈው ግለሰብ ከዚያ ይጠቅሱ ነበር።

ሰፕቱዋጂንት በብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። ይህም ዓረብኛን፥ ኮፕቲክን፥ የአርመን ቋንቋን፥ ላቲንኛን፥ ምናልባትም ግዕዝን ያጠቃልላል። ዛሬም በግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ብሉይ ኪዳን ውስጥ ዋነኛ የመገልገያ ቋንቋ ነው።

የሴምን ቋንቋ ዘይቤና አስተሳሰብ ዘዴዎችን የሚያንጸባርቅ መሆኑን ለመረዳት ምክንያት ይሆናል።

ወንጌላትና የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ፥ ክርስቶስ በምድር በተመላለሰበትና ባስተማረበት ጊዜ ግሪክኛ የጊዜው ቋንቋ መሆኑን ይበልጥ ያረጋግጣሉ። ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ሁለቱ፥ እንድርያስና ፊሊጶስ ስማቸው ግሪክኛ ነበር። ዮሐንስ 12፡20-23 ውስጥ ያለው ቃል ፊሊጶስ፥ እንድርያስና ኢየሱስ ግሪክኛ ይሰሙና ይናገሩ እንደነበር ያመለክታል። ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ዋና የነበረው ጴጥሮስ በዕብራይስጥ ስምዖን፥ በአረማይክ ኬፋ፥ እንዲሁም በግሪክ ጴጥሮስ በሚለው ስም ይጠራ ነበር። ጴጥሮስ፥ ሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10 ውስጥ እንደተመለከተው ለቆርነሊዮስ ቤተሰብ የተናገረውና በስሙ የተሰየሙትን ሁለት መልእክቶች የጻፈው በግሪክኛ ሳይሆን አይቀርም። ያ ገሊላዊ ዓሳ አጥማጅ በግሪክኛ ስም መጠራቱ፥ ግሪክኛ መናገሩና መጻፉ፥ ዝቅተኛ ትምህርት ያላቸው ሰዎች እንኳ ያን ቋንቋ ሊገለገሉበት ይችሉ እንደነበር ያረጋግጣል። በግሪክኛ በተጻፈው የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 21 ውስጥ ኢየሱስ የተለያዩ ሁለት ግሪክኛ ቃላት ተናግሯል። እነዚያም ስለ "ፍቅር" እና "መንጋውን" ስለመጠበቅ የሚገልጡ ነበሩ። ጴጥሮስም "ማወቅ" የሚለውን ቃል ለመግለጥ በሁለት የተለያዩ ቃላት ተጠቅሟል። እነዚህ ጥንድ ቃላት አረማይክና ዕብራይስጥ ውስጥ ልዩነታቸው ጎልቶ አይታይም። በግሪክኛ የተደረገው የቃላት ምልልስ ግን ልዩነት እንዳላቸው ያመለክታል። ስለሆነም በኢየሱስና በጴጥሮስ መካከል ይደረግ የነበረው የንግግር ልውውጥ በግሪክኛ ነበር ለማለት ይቻላል። እንዲሁም ማቴዎስ ወንጌል 16፡18 የተጠቀሱት 'ፔትራ' እና 'ጴጥሮስ' የሚሉት ቃላት ዕብራይስጥና አረማይክ ቋንቋ ውስጥ ልዩነታቸው አይታይም። በግሪክኛ በተደረገው ንግግር ግን ልዩነት እንዳላቸው በተሻለ ሁኔታ ይታያል። ኢየሱስ ግሪካዊት በሆነችው የሲሮፊኒቃዊት ሴት (ማርቆስ 7፡26)፥ ከሮማዊው መቶ አለቃና ከጲላጦስ ጋር የተነጋገረው በግሪክኛ እንደነበር ይገመታል። እስጢፋኖስ (ሐዋ.7) እና ያዕቆብ (ሐዋ.15) በንግግራቸው ከስፕቱዋጀንት መጥቀሳቸው፥ በግሪክኛ ለመገልገላቸው የሚጠቀስ ማረጋገጫ ነው።

አረማይክ በአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበረው የፍልስጥኤም ምድር ሕዝቡ ይናገረው የነበረ ቋንቋ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ከዚያ ውጭ ባሉ ምንጮች ተረጋግጧል። ከክርስቶስ ልደት በፊት በሁሉም የፍልስጥኤም ክልሎች ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያን ቋንቋ አረማይክ መሆኑ ይታወቃል። ወንጌላት ውስጥ የሚታዩት ሴማዊ የአገላለጥ ዘይቤዎች፥ ለዚህ እንደ አጠቃላይ ማረጋገጫ ተቆጥረዋል፤ ይህንንም ወንጌላት ውስጥ በብዛት በሚገኙት የአረማይክ ቃላትና ስሞች ለማየት ይቻላል። ክርስቶስ በዚህ ምድር በነበረ ጊዜ፥ አረማይክ ሕዝቡ የሚጠቀምበት ብቸኛ ቋንቋ ተደርጎ ይታሰብ ነበር። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችና (ዮሐ. 19፡20፤ ሐዋ. 21፡40፤ 22፡25፤ 26፡14)፥ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች 'ዕብራውያን' የሚለውን ቃል በሚጠቅሱበት ጊዜ፥ በእርግጥም 'አረማይክ' የሚለውን ቃል ማለታቸው ነው ብለው አንዳንዶች ያስባሉ።

አረማይክ ከወንጌላት ጋር ተዛምዶ ያለው መሆኑ፥ በፍልስጥኤም የነበሩ ሰዎች ሁሉ ይገለገሉበት የነበረ ብቸኛ ቋንቋ አያሰኘውም። ከዚህ በፊት በግሪክኛ ጥቂት ቃላት ከአረማይክ ቃል በቃል ተወስደዋል ተብሎ ይታሰብ ነበር። አሁን ግን ቢያንስ እነዚህ ጥቂት ቃላት በእርግጥም የአረማይክ ቃላት መሆናቸው ታውቋል (ማቴ. 27፡46፤ ማር. 5፡41፤ 7፡34፤ 14፡36፤ 15፡34)። ከነዚህም ጥቂቶቹ ደግሞ የዕብራይስጥ

ቃላት ነበሩ። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች፥ ወይም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ስለ ዕብራይስጥ ቋንቋ በሚጠቅሱበት ጊዜ የዕብራይስጥ ቋንቋን መጠቀማቸው ነበር። በተጨማሪም በዛ ጊዜ የነበሩ የአይሁድ ምሁራን በጽሑፋቸው ዕብራይስጥ ቋንቋን ይጠቀሙ እንደነበር ማረጋገጫ አለ። ይህ ቋንቋ ሙት ቋንቋም አልነበረም። በዚህ ፋንታ ቋንቋው ሕዝቡ የሚጠቀምበት፥ የተለመደ፥ አዳዲስ ቃላት የሚፈጠሩበትና የሕዝቡን የእለት ተእለት ኑሮ የሚገልጥ ቃላት ያለው ቋንቋ ይመስላል። በአይሁድ ምሁራን ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ የዕብራይስጥ ቋንቋ በውይይት መልክ ያገለግል ስለነበር፥ የውይይቱ ዋና ጉዳይ የዕለት ተዕለት ክንውኖችን ጭምር ያካተተ እንጂ ምሁራዊ ጉዳዮችን ብቻ የያዘ አልነበረም። ቁምራን በተባለው ዋሻ ውስጥ በተደረገው ምርምርም በዕብራይስጥኛ የተጻፉ ብዙ ሰነዶች ተገኝተዋል። እነዚህ ሰነዶች የያዟቸው ጉዳዮች በምሁራን ብቻ የተጻፉ ሳይሆኑ፥ በሌሎችም ተራ ሰዎች የተጻፉ ነበሩ። ስለሆነም ሰነዶቹን ማንኛውም ተራ ሰው ሊረዳቸው ይችል ነበር። አንዳንድ ሰዎች አረማይክ ቋንቋ ዕብራይስጥን እንደ ተራ የሕዝብ ቋንቋ ሙሉ በሙሉ በፍጥነት ተክቷል ብለን መጠብቅ የለብንም ብለው ይከራከራሉ። አረማይክ ከመነሻው በንግዱ እንቅስቃሴና በመንግሥት ሥልጣን ደረጃ የነበሩ የአይሁድ ማኅበረሰቦች ይናገሩት ነበር። ቀስ በቀስ የተራውና ያልተማረው ሕዝብ የመናገሪያና የጽሑፍ ቋንቋ ለመሆን በቃ። ዕብራይስጥኛ ግን የተራው ሕዝብ ቋንቋ ሆኖ ነው የኖረው። የመናገሪያ ቋንቋነቱ የመጨረሻ አደጋ የገጠመው፥ የአይሁድ አብዮታውያን ትግል ከ132-135 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት ድል ከተመታ በኋላ ነው።

ከዚያ ወዲህ ግሪክኛ፥ ዕብራይስጥ እና አረማይክ ቋንቋዎች ፍልስጥኤም ምድር ውስጥ ይኖሩ በነበሩ አይሁዳውያን ኢየሱስ እስከመጣ ድረስ የሚረዷቸውና የሚናገሯቸው ቋንቋዎች እንደነበሩ ይገመታል። ከሕዝቡ ስንቱ፥ የትኛውን ቋንቋ ይናገረው ነበር? የሚለውን መገመቱ ያዳግታል። ምናልባት ከነዚህ አንደኛው ቋንቋ ባንድ አካባቢ ከሌሎቹ ይበልጥ ተናጋሪ የነበረው ሊሆን ይችላል። በዚያም ሆነ በዚህ፥ ምድሪቱ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባት ነበረች። ኢየሱስ በሦስቱም ቋንቋዎች ይናገር ነበር ብሎ ለመናገርም ይቻላል። የዚህ እውነት ማረጋገጫዎችም ወንጌላት ውስጥ አሉ።

# 3

# የክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ቅደም ተከተል

የክርስቶስ ምድራዊ ሕይወት ቅደም ተከተል በሚጠናበት ጊዜ ጥርጣሬ የሚያጠላባቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ። ክርስቶስ የተወለደው በአንድ[69] ዓመተ ምሕረት መሆኑና የሞተው ደግሞ በሠላሳ ዓመተ ምሕረት መሆኑ ይገመታል። ይሁን እንጂ እነዚህ አጠቃላይ አሳቦች ናቸው። የክርስቶስን ልደት እንደመነሻ ነጥብ ለመጠቀም የሚፈልገው ጎርጎሪሳዊ የፈረንጆች የቀን አቆጣጠር ከታወቀበት ከ525 ዓ.ም. ጀምሮ ስሕተት ነበረበት። በእንግሊዝኛ ‘‘ኤ.ዲ.’’ የሚለው ምሕፃረ ቃል የተገኘው በላቲንኛ ‘‘አኖዳሚኖ’’ ከሚለው ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም ‘‘ከክርስቶስ ልደት በኋላ’’ ማለት ነው። ነገር ግን በኋላ የተገኙት ማስረጃዎች እንደገለጡት ኢየሱስ የተወለደው ከአንድ ዓመተ ምሕረት በፊት ነበር።

ምንም እንኳን ቀናትን በተመለከተ ፍጹም እርግጠኛ መሆን የማይቻል ቢሆን፥ ኢየሱስ በምድር የኖረበትን ጊዜ በተመለከተ ግን ብዙ ለማለት ይቻላል። የበለጠ ዝርዝር መረጃ ለመስጠት ይቻል ዘንድ አንዳንድ የተመረጡ ሁነቶችና ገለጣዎች ለውይይት ይቀርባሉ።

## የታላቁ ሄሮድስ ሞት

በማቴዎስ ወንጌል 2፡1 እና በሉቃስ 1፡5 መሠረት ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ፥ ታላቁ ሄሮድስ የአይሁዳውያን ንጉሥ ነበር። በአንዳንድ ሌሎች ምንጮች አሁን እንደተገለጠው ደግሞ፥ ሄሮድስ የሞተው ከክርስቶስ ልደት አራት ዓመት ቀደም ብሎ ነበር። በአይሁድ አቆጣጠር የኒሳን ወር አንደኛው ቀን እንዳለፈ ማለት ነው። ኢየሱስ የተወለደው፥ ከዚያ ቀደም ሲል በነበሩት ሁለት ዓመታት ውስጥ መሆን አለበት። ምክንያቱም ሄሮድስ ኮከቡ የታየበትን ዘመን ከተረዳ በኋላ ነበር (ማቴ. 2፡7) ሁለት ዓመትና ከዚያ በታች የሆኑ ወንድ ሕፃናት ሁሉ እንዲገደሉ ትእዛዝ የሰጠው (ማቴ. 2፡16)። ስለዚህ ኢየሱስ የተወለደው፥ በ6 እና በ4 ዓመተ ዓለም መካከል መሆን አለበት።

## በአውግስጦስ ቄሣር ዘመን የተከናወነው የሕዝብ ቆጠራ

ሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 2፡1-2 ባለው ክፍል የተጻፈው ቃል ክርስቶስ የተወለደው በሮማዊው ገዥ በአውግስጦስ ቄሣር ግዛት ውስጥ መሆኑን ይገልጣል። ከዚሁ ጋር ምንም እንኳን አንዳንዶች ሉቃስ የሕዝብ ቆጠራው የተከናወነው ከዚህ ሰው አገዛዝ በፊት ያለ ቢመስላቸው፥ የክርስቶስ ልደት ሶሪያ ውስጥ ከነበረው ቄሬኔዎስ ከተባለው ሮማዊ ገዢ አስተዳደር ጋርም ሳያገናኘው አይቀርም። አውግስጦስ ቄሣር ከክርስቶስ ልደት በፊት 30 ዓመት ቀደም ብሎ በመጀመር እስከ 14 ዓ.ም. በዘለቀው የአገዛዝ ዘመኑ የሕዝብ ቆጠራ ሥርዓት አውጥቶ ነበር። ያንን ነው ሉቃስ በምዕራፍ 2፡1 ውስጥ የሚጠቅሰው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሚወለድበት ጊዜ ዮሴፍና ማርያም ወደ ቤተልሄም እንዲሄዱ ያደረጋቸው የሕዝብ ቆጠራ፥ ከሥርዓቶቹ አንዱና ቄሬኔዎስ ገዥ በነበረ ጊዜ የተከናወነ ነበር፤ (የሐዋርያት ሥራ 5፡37 የሚያመለክተው፥ ምናልባት በስድስት ዓመተ ምሕረት የተከናወነውንና ሁለተኛውን ቆጠራ ሳይሆን አይቀርም)።

---

69 የተጠቀሱት ጊዜያት የተመለከቱት በአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ነው።

ቆጠራው በየአሥራ አራት ዓመቱ ይከናወን እንደነበር የተገኘው ማስረጃ ያረጋግጣል። አንድ ሰው ግብጽ ውስጥ ከተከናወነው ቆጠራ በመነሣት ወደኋላ ቢያሰላ፥ ከክርስቶስ ልደት ስምንት ዓመት ቀደም ብሎ የሕዝብ ቆጠራ ተከናውኖ እንደነበር ይረዳል። ፍልስጥኤምና ሶሪያ ውስጥ በጊዜው ተነሥቶ የነበረው ብጥብጥ የቆጠራውን ክንውን ለጥቂት ዓመታት ሳያዘገየው እንዳልቀረ ይገመታል።

ቄሬኔዎስ ቆጠራው በተከናወነበት በስድስት ዓመተ ምሕረት የሶሪያ ገዢ እንደነበር ይታወቃል። ነገር ግን ይህ ጊዜ ከኢየሱስ ልደት ጋር በሚገናዘብበት ጊዜ አሥር ዓመት ያህል ይዘገያል። ይሁን እንጂ፥ የጽሑፍ ግኝቶች እንዳረጋገጡት ቄሬኔዎስ ከክርስቶስ ልደት ስምንት ዓመት ያህል ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ፥ ሶሪያ ውስጥ በጋራ አገዛዝ ሳይሳተፍ አልቀረም። የዚህ ሰው የአገዛዝ ጊዜ አጋሩ የሆነውና ሴንቲዮስ ሳተርኒየስ የተባለው ሰው አገዛዝ ከክርስቶስ ልደት ስድስት ዓመት በፊት እስካከተመበት ጊዜ ድረስ ሳይራዘም አልቀረም።

## የጢባርዮስ ቄሣር አሥራ አምስተኛ ዓመት

ሉቃስ 3፡1 ውስጥ እንደተጠቀሰው፥ የጢባርዮስ ቄሣር አገዛዝ አሥራ አምስተኛ ዓመት መጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎቱን የጀመረበት ጊዜ ነበር። የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት የጀመረው ከኢየሱስ አገልግሎት ጥቂት ቀደም ብሎ በመሆኑ፥ የኢየሱስን የአገልግሎት ጊዜ ለመረዳት ይህን የጊዜ ቅደም ተከተል መገንዘቡ ይረዳል።

ይሁን እንጂ፥ የጢባርዮስ አገዛዝ ወቅት ሁለት ጅማሬዎች ስለነበሩት ይህን አሥራ አምስተኛ ዓመት ትክክለኛ ጊዜ መወሰኑ ብዙ ችግር አስከትሎ ነበር። ከአባቱ ሞት ቀደም ብሎ በአንድ ወቅት ከአባቱ ከአውግስጦስ ቄሣር ጋር በጋራ ገዢ ሆኖ ነበር። አውግስጦስ በ14 ዓ.ም. ከሞተ በኋላ ግን፥ የግዛቱ ሁሉ ጠቅላይ ገዢ ሆነ። ሉቃስ የሚጠቅሰው ቀደም ያለውን ጊዜ ከሆነ፥ የዮሐንስ ነቢያዊ አገልግሎት የተጀመረው በ26 ወይም በ27 ዓ.ም. ነው። የተናገረው ስለኋለኛው ጊዜ ከሆነ ግን አሥራ አምስተኛው ዓመት ምናልባት በ28 ወይም በ29 ዓ.ም. ነበር።

በጥንት ዘመን ከነበረው የቀናት ቀመር ጋር ሲነጻጸር ከነዚህ ሁለት ግምቶች የኋለኛው ትክክል ይመስላል። ወደፊት በዚህ ጥናት ከምናገናዝበው የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ ጋር ሲነጻጸር ግን፥ የመጀመሪያው አገላለጥ ትክክለኛነት ያደላል። በግልጥ ለመናገር፥ ኢየሱስ አገልግሎት የጀመረበትን ጊዜ በተመለከተ 26 ወይም 27 ዓ.ም. ከሉቃስ ገለጣ ጋር ይበልጥ ይስማማል።

## "ሠላሳ ዓመት ያህል ዕድሜ"

ሉቃስ በ3፡23 ውስጥ እንደሚገልጠው፥ ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎቱን በሚጀምርበት ጊዜ ዕድሜው "ሠላሳ ዓመት ያህል" ነበር። ምንም እንኳን ይህ አገላለጥ ከሃያ ስምንት እስከ ሠላሳ ሁለት ድረስ ያለውን ማንኛውንም ዕድሜ የሚያመለክት ቢሆን፥ በጊዜው የነበሩ ልማዶችና ሌሎች የኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ዝርዝር ጉዳዮች እንደሚያመለክቱት፥ ምድራዊ አገልግሎቱን የጀመረው፥ ከ29-31 ዓመት ባለው ዕድሜ ነበር። የኢየሱስን ዕድሜ በማስገንዘቡ ረገድ ይህን የተሻለ ገለጣ አድርጎ መቀበሉ ሉቃስ የነገሮችን ዝርዝር ቅደም ተከተል ለማቅረብ ካደረገው ጥረት ጋር ይስማማል (ሉቃስ 1፡5፤ 2፡1-2፤ 3፡1-2)።

ኢየሱስ የተወለደው በስድስት ዓመተ ዓለም ገደማ ነው ከተባለ፥ ሠላሳ ዓመት የሞላው በ25 ዓመተ ምሕረት ይሆናል። በአምስት ዓመተ ዓለም ነበር ከተባለ ደግሞ፥ ሠላሳ ዓመት የሞላው በ26 ዓመተ ምሕረት ነው። ሁለተኛው የልደት ቀን ትክክል ይመስላል፤ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ በስቅለት የሞተበት ጊዜ ከ30 ዓ.ም. በፊት ነበር ሊባል አይቻልም። "ኢየሱስ የተሰቀለበት ቀንና ዓመቱ" የሚለውን መጣጥፍ ገጽ 295 ላይ ይመልከቱ።

ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት የጀመረበትን ጊዜ ከ27 ዓ.ም. በኋላ በነበረው በማንኛውም ጊዜ ነው ማለቱ ያስቸግራል። ምክንያቱም ይህን ዕድሜ አስመልክቶ ሉቃስ ያቀረበውን ገለጣ ተቀባይነት ያሳጣዋል። ከዚህም ይልቅ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት አንድ ወይም ሁለት ዓመት ብቻ ካልሆነ አገልግሎቱን በ30 ዓ.ም. ሊፈጽም አይችልም። በተጨማሪም አገልግሎቱ እንዲሁ ከሚታሰበው ይበልጥ አራት ወይም አምስት ዓመት ያህል ካልተራዘመ፥ እስከ 33 ዓ.ም. ሊቆይ አይችልም። (ለተጨማሪ መረጃ መጣጥፍ 43 ይመልከቱ።)

## ቤተ መቅደስ የማደሻ አርባ ስድስት ዓመታት

113 ዮሐንስ 2፡20 ላይ እንደተመለከተው፥ የኢየሱስ ተቃዋሚዎች ከአርባ ስድስት ዓመታት በፊት በሄሮድስ ስለተጀመረው የቤተ መቅደስ እድሳት ሥራ ጉዳይ ይጠቅሳሉ። የሚታደሰው ቤተ መቅደስ በዘሩባቤል የተገነባ ነበር። መንፈሳዊ ባልሆነው የታሪክ ዘገባ መሠረት ሄሮድስ እድሳቱን የጀመረው ከክርስቶስ ልደት 19 ወይም 20 ዓመታት ቀደም ብሎ ነበር። ስለ ቤተ መቅደሱ የእድሳት ሥራ ለኢየሱስ የተነገረው አገልግሎቱን በግልጥ ከጀመረ ወዲህ በሆነው የመጀመሪያ ፋሲካ ወቅት ነው። በመሆኑም "አርባ ስድስቱ ዓመት" ክርስቶስ አገልግሎት የጀመረበትን ዓመት የመገንዘቢያ ሌላ መንገድ ያቀርባል።

ይህ ሰፊ የቤተ መቅደስ ሥራ፥ ሄሮድስ ከክርስቶስ ልደት አራት ዓመት ቀደም ብሎ እስከሞተበት ጊዜ እንኳን አልተጠናቀቀም። አይሁዳውያን ዮሐንስ 2፡20 ውስጥ የተጠቀሰውን ቃል በተናገሩ ጊዜም ሥራው በመካሄድ ላይ ነበር። በ64 ዓ.ም. ነበር ሥራው የተጠናቀቀው።

ምንም እንኳን "ቤተ መቅደስ" እና "መሥራት" ወይም "ማነጽ" የሚሉትን ቃላት በተመለከተ አንዳንድ አለመግባባቶች ቢኖሩ፥ ግልጥና ለሁኔታው ግንዛቤ አጥጋቢ የሆነው ነገር፥ አይሁድ ያነጻጽሩ የነበረው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ መቅደሱን እሠራዋለሁ ባለው ሦስት ቀንና የእድሳቱ ሥራ የፈጀውን ረጅም ጊዜ መሆኑን መረዳቱ ነው (ዮሐ. 2፡19)።

ከ19 ወይም 20 ዓ.ዓ. ጀምሮ አርባ ስድስት ዓመት የሚቆጥር ሰው 26 ወይም 27 ዓ.ም. ላይ ደርሶ ይቆማል። ስለዚህ በኢየሱስ አገልግሎት ወቅት የመጀመሪያው ፋሲካ የተከበረው በ27 ዓ.ም. ጸደይ ውስጥ ነው።

## የኢየሱስ አገልግሎት ጊዜ እርዝማኔ

ክርስቶስ አገልግሎት የጀመረበት ጊዜ ከታወቀ፥ የተሰቀለበት ትክክለኛ ዕለት ይህ ነበር ከመባሉ በፊት የአገልግሎቱ ጊዜ እርዝማኔ መታወቅ አለበት።

አንዳንድ ሰዎች፥ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወንጌላት የሚጠቅሱት፥ በኢየሱስ አገግልግሎት ጊዜ አንድ የፋሲካ በዓል፥ ማለት በስቅላቱ ዋዜማ የተደረገውን ብቻ

መሆኑን (ማቴ. 26፡17-20፤ ማር. 14፡12-17፤ ሉቃስ 22፡7-16) መነሻ በማድረግ አገልግሎቱ አንድ ዓመት ብቻ ነበር ብለው ተከራክረዋል። የዮሐንስ ወንጌል ግን ይህን ግንዛቤ ይቃረናል። ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ከጀመረ በኋላ ያለፈባቸውን ፋሲካዎች በግልጥ ይጠቅሳቸዋል (ዮሐ. 2፡13፤ 6፡4፤ 11፡55)።

ሌሎቹ ደግሞ የአገልግሎቱ ጊዜ ከሁለት ዓመት አለፍ ያለ ነበር የሚለውን ደግፈዋል። እነዚህ ሰዎች ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተጠቀሱትን ሦስት የፋሲካ በዓላት የሁለቱ ዓመታት መነሻና መደምደሚያ እንደነበሩ ይገነዘባሉ። ይህ ንድፈ አሳብ ብዙ ጊዜ የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አምስትና ስድስትን በማዟዟር አሠራር ላይ በመመሥረት ነው ትክክለኛነቱን የሚያስገነዝበው። ይሁን እንጂ ይህን እንደገና አስተካክሎ የማስላት አሠራር የሚደግፍ የጽሑፍ ማስረጃ ስለሌለ፥ ሁለት ዓመት የሚለው ጽንሰ-አሳብ ደካማ ነው።

114 የክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ከአራት ዓመት እልፍ ይላል የሚለውን ግንዛቤ ለማረጋገጥ የሚደረገው ሙከራ የሚመሠረተው በዮሐንስ ያልተጠቀሱትን ሁለት የፋሲካ በዓላት በመገመት ላይ ነው። ከነዚህ ተጨማሪ የፋሲካ በዓላት አንዱ ዮሐንስ 4፡35 ውስጥ የተጠቀሰው (ይህ ዮሐ. 2፡13 ውስጥ ከተጠቀሰው በዓል በኋላ ወቅቱ ክረምት መሆኑን ያመለክታል) እና ቀጥሎ በነበረው ክረምት የተከበረውን የድንኳን በዓል ያመለክት ይሆናል ተብሎ በተገመተው ማለት ዮሐንስ 5፡1 ውስጥ በተጠቀሰው በዓል መካከል የተከናወነው ነበር። ይህን ያልተጠቀሰ የፋሲካ በዓል እንደ ማስረጃ መጠቀሙ መላምታዊ ይመስላል። ሌላውን ተጨማሪ የፋሲካ በዓል እንደሆነ መቁጠሩም ጥሩ መሠረት የለውም። አንዳንዶች በዓሉን ከዮሐንስ 2፡13 በፊት፥ ሌሎቹ ደግሞ ዮሐንስ 6፡4 ውስጥ ከተጠቀሰው ፋሲካ በኋላ ያደርጉታል። በሁለቱም በኩል ቢሆን፥ አምስተኛ የፋሲካ በዓል ነበር ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አሳማኝ ማስረጃ የለም።

በሰፊው የታመነበት አሳብ የክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ከሦስት ዓመት ላቅ ያለ መሆኑ ነው። ኢየሱስ በዮሐንስ ከተጠመቀበት (ማቴ. 3፡1-17፤ ማር. 1፡9-11፤ ሉቃስ 3፡21-23ሀ) እስከ መጀመሪያው የፋሲካ በዓል (ዮሐ.2፡13) ድረስ የነበረው ጊዜ ብዙ ወራት ያለፉበት፥ እንዲሁም ኢየሱስ ገሊላና ይሁዳ ውስጥ የተዘዋወረበት ነበር። የመጀመሪያው አንድ ዓመት (በፋሲካ በዓላት መካከል የነበረው) አገልግሎቱም እንዲሁ ይሁዳና ገሊላ ውስጥ የነበረ ሲሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባልተጠቀሰ የፋሲካ በዓል ጊዜ አብቅቷል። ይህም የፋሲካ በዓል ኢየሱስ ዮሐንስ 4፡35 ውስጥ የተጠቀሰውን ቃል ከተናገረ ጥቂት ወራት በኋላና ዮሐንስ 5፡1 ውስጥ ከተጠቀሰው የድንኳን በዓል ስድስት ወር ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ የሆነ ነበር። የኢየሱስ አገልግሎት ሁለተኛ ዓመት በአብዛኛው ገሊላ ውስጥ ሲሆን፥ ዮሐ. 6፡4 ውስጥ በተጠቀሰው የፋሲካ በዓል ወቅት አብቅቷል። የመጨረሻውን የአገልግሎት ዓመት ያሳለፈው በአብዛኛው በገሊላ ዙሪያ፥ ይሁዳና ፖርያ ውስጥ ሲሆን፥ አገልግሎቱ የተጠናቀቀውም ዮሐንስ 11፡55 ውስጥ የተጠቀሰው የፋሲካ በዓል በተከበረ ጊዜ ነው።

እንግዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ጊዜ ከሦስት ዓመት ጥቂት አለፍ ያለ ነበር የሚለው አሳብ፥ በጠንካራ ማስረጃ የተረጋገጠና ግራ ከሚያጋባ ነገር የፀዳ ነው።

## ስቅላቱ

በመጣጥፍ 4 ውስጥ እንደተገለጠው፥ ‘‘ክርስቶስ የተሰቀለበት ቀንና ዓመት’’ ማለት ኒሳን የተባለው ሰባተኛ ወር አሥራ አራተኛ ቀን የፋሲካ በዓል የዋለው በአይሁድ የጊዜ ቀመር ሁለት ጊዜ ማለት በ26 ዓ.ም. እና በ36 ዓ.ም. ነው። ይህም ክርስቶስ የተሰቀለው በ30 ወይም 33 ዓ.ም. ነው ከሚሉ ሁለት አማራጭ ጊዜያት ላይ ያደርሰናል። ቀደም ሲል በዚህ የመጣጥፍ ክፍል የተደረሰበት ማጠቃለያ ከታመነበት፥ ክርስቶስ የተሰቀለው በ30 ዓ.ም. ነበር የሚለውን አማራጭ እንድንቀበል ያደርገናል።

## መደምደሚያ

የዚህ መጣጥፍ ማጠቃለያዎች ባለፉት ገለጣዎች የተነሡ ሌሎች ግምታዊ አማራጮችን ባካተተ ሁኔታ በሚከተለው ሰሌዳ በአጭሩ ይቀርባሉ።

| | |
|---|---|
| የክርስቶስ ልደት | 6 ዓ.ዓ. (በዓመቱ ማብቂያ) ወይም<br>5 ዓ.ዓ. (በዓመቱ መጀመሪያ) |
| የታላቁ ሄሮድስ ሞት | 4 ዓ.ዓ. (ከኒሳን 1 በኋላ ) |
| የጢባሪዮስ ቄሣር አገዛዝ መጀመር | 12 ዓ.ም. |
| የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት መጀመር | 26 ዓ.ም. (በዓመቱ መጀመሪያ) |
| የክርስቶስ አገልግሎት መጀመር | 26 ዓ.ም. (በዓመቱ አጋማሽ ወይም ፍጻሜ) |
| በክርስቶስ አገልግሎት ወቅት የመጀመሪያው ፋሲካ | 27 ዓ.ም. (ኒሳን 14) |
| በክርስቶስ አገልግሎት ወቅት ሁለተኛ ፋሲካ | 28 ዓ.ም. (ኒሳን 14) |
| በክርስቶስ አገልግሎት ወቅት ሦስተኛ ፋሲካ | 29 ዓ.ም. (ኒሳን 14) |
| የክርስቶስ መሰቀል | 30 ዓ.ም. (ኒሳን 14) |

ምንም እንኳን ችግሮች የሉትም ባይባል፥ ይህ የዕለታት ሰሌዳ ካከማቻቸው ብርቱ ማረጋገጫዎች የተነሣ ከሌሎች ማስረጃዎች የተሻለ መፍትሔ ያለው ይመስላል። በመሆኑም የወንጌላት ተማሪ የሆነ ሰው ኢየሱስ በምድር የኖረበትን፥ ያገለገለበትንና የሞተበትን ጊዜ በትክክል እንዲረዳ ያስችለዋል።

# 4

# ኢየሱስ የተሰቀለበት ቀንና ዓመት

ኢየሱስ የተሰቀለበትን ቀንና ወሩን፥ እንዲሁም ዓመቱን በእርግጠኛ መረዳቱ የክርስቶስን ምድራዊ ሕይወት ሰፊ ቅደም ተከተል ለመገንዘብ እጅግ ይጠቅማል። ወደሌሎች ከክርስቶስ ሕይወት ጋር ከሚዛመዱ የወንጌላት ቅደም ተከተላዊ ጉዳዮች ከመሻገራችን በፊት፥ ጥርት ላለ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ እነዚህ ሦስት ጉዳዮች በዚህ ጽሑፍ ይዳሰሳሉ። ሦስቱም የሚታዩት ከላይ በተቀመጡበት ቅደም ተከተል ሲሆን፥ በሚያመች አኳኋን ለየብቻቸው ይታያሉ።

## የሳምንቱ ዕለት

ቤተ ክርስቲያን በተለምዶ ኢየሱስ የሞተበት ዕለት አርብ እንደሆነ ትቆጥራለች። ይህን ግንዛቤ የሚሽር ጠንካራ ምክንያት አልቀረበም። ኢየሱስ አርብ ዕለት ነው የተሰቀለው የሚለውን ለማስተባበል በተደጋጋሚ የሚነሣው ተቃውሞ የሚነሣው፥ ማቴዎስ 12፡40 ውስጥ “ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት” የሚለውን ቃል በስሕተት በመገንዘብ፥ ኢየሱስ እያንዳንዳቸው ሃያ አራት ሰዓት ለሆኑ ሦስት ቀናት መቃብር ውስጥ ቆይቷል ከሚሉ ወገኖች ነው። ከዚህ ግንዛቤ በመነሣት፥ አንዳንዶች ከእሁድ ወደ ኋላ ይቆጥሩና የስቅለቱን ዕለት ወደ ሐሙስ ወይም ወደ ረቡዕ ይወስዱታል።

ይሁን እንጂ፥ ይህ ድምዳሜ ኢየሱስ የመዘጋጀት ወይም የሰንበት ዋዜማ በተባለው ቀን መሰቀሉን ከሚያስገነዝበው የአራቱ ወንጌላት የማያሻማ መግለጫ ጋር ይቃረናል (ማቴ. 27፡62፤ ማር. 15፡42፤ ሉቃስ 23፡54፤ ዮሐ. 19፡14፥ 31፥ 42)። ይህ የዝግጅት ዕለት ዛሬ እኛ አርብ ብለን የምንጠራው የሳምንት ዕለት ሲሆን፥ አይሁዳውያን ለሥርዓታቸው ማከናወኛ የለዩት ቀን ነው። “ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት” የሚለው ገለጣ በትክክል ከግንዛቤ ሲገባና ጊዜው ከሀያ አራት እስከ ሰባ ሁለት ሰዓት ሊደርስ እንደሚችል ሲታወቅ፥ ይህ የሚቃረን የሚመስል አሳብ ይወገዳል።

ኢየሱስ መቃብር ውስጥ የሚቆይበትን ጊዜ ሲተነብይ “በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት” በማለት ራሱን ከዮናስ ጋር አነጻጽሯል (ማቴ. 12፡40)። በዚህ ንግግሩ አንድን ነገር ሊገልጥ ከሚችልባቸው ብዙ መንገዶች አንዱን ብቻ መረጠ። አንድን ዕለት ለመጥቀስ የቀኑን ክፍልፋይ ብቻ መጥቀሱ በአይሁዳውያን ዘንድ የተለመደ ነገር ነበር (ዘፍጥ. 42፡17-18፤ 1ኛ ሳሙ. 30፡12-13፤ 1ኛ ነገሥ. 20፡29፤ 2ኛ ዜና. 10፡5፥ 12፤ አስቴር 4፡16፤ 5፡1)። ስለዚህ “ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት” የሚለው ቃል በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ መካከል ሀያ አራት ሰዓታት ያላቸው ሦስት ቀናት አልፈዋል አያሰኝም። ነገር ግን ገለጣው “በሦስተኛው ቀን” ተነሣ የሚለው ቃል ሌላ አባባል ነው (ማቴ. 16፡21፤ 17፡23፤ 20፡19፤ 27፡64፤ ሉቃስ 9፡22፤ 18፡33፤ 24፡7፥ 21፥ 46፤ ሐዋ. 10፡40፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡4)፥ ወይም “ከሦስት ቀን በኋላ ” (ማቴ. 26፡61፤ 27፡40፥ 63፤ ማር. 8፡31፤ 9፡31፤ 10፡34፤ 14፡58፤ 15፡29፤ ዮሐ. 2፡19-20)።

ከወንጌላት ገለጣ አኳያ ሲታይ እንግዲህ፥ ኢየሱስ አርብ ዕለት ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ሞቶ፥ በዚያኑ ዕለት ዘግየት ብሎ (ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት) ተቀበረ ብሎ ያለ ስጋት ለመናገር ይቻላል። መቃብር ውስጥ የቆየው የአርብን የተወሰነ ጊዜ (ፀሐይ እስክትጠልቅ)፥ ቀጥሎ የነበረውን ሙሉ ዕለት (ከአርብ ፀሐይ መጥለቅ እስከ ቅዳሜ

ፀሐይ መጥለቅ) እና የሦስተኛውን ቀን የተወሰነ ጊዜ (ከቅዳሜ ፀሐይ መጥለቅ እስከ እሁድ ማለዳ) ነበር። ከፀሐይ መጥለቅ እስከ ፀሐይ መጥለቅ ያለውን ጊዜ አንድ ቀን ብሎ የመቁጠሩ አሠራር ኢየሩሳሌም ውስጥ ሰዱቃውያን የሚከተሉት ነበር። ከፀሐይ መውጣት እስከ ፀሐይ መውጣት ያለውን ጊዜ እንደ አንድ ዕለት የመቁጠሩ አሠራርም ነበር። ነገር ግን ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ የሚለው አሠራር ይበልጥ ተቀባይነት ያገኘ ነው።

## የወሩ ዕለት

ክርስቶስ በአይሁዳውያን የቀን አቆጣጠር በየትኛው ዕለት እንደተሰቀለ በትክክል ማወቁ ተገቢ ነው። በአይሁዳውያን ሰባተኛ ወር (ኒሳን) በአሥራ አራተኛው ወይስ በአሥራ አምስተኛው ቀን ነው ክርስቶስ የተሰቀለው? የዮሐንስ ወንጌል ዕለቱ የወሩ የአሥራ አራተኛው ቀን ስለመሆኑ መነሻ የሚሆን አሳብ ሲኖረው፥ ሌሎቹ ወንጌላት ግን አሥራ አምስተኛው ቀን ነበር የሚሉ ይመስላሉ። ዮሐንስ በጌታ መሰቀል ዋዜማ የተከናወነው የእንጀራ መቊረስ ሥርዓት የፋሲካ እራት አልነበረም ሲል፥ የሌሎቹ ወንጌላት ፀሐፊዎች ግን ነበር ይላሉ።

ዮሐንስ 13፡1 ላይ የተጻፈው ቃል በክርስቶስ መሰቀል ዋዜማ የተከናወነው እራት "ከፋሲካ በዓል በፊት" እንደነበር ያስረዳል። በኢየሱስ ላይ የተፈረደበት "ፋሲካ በተዘጋጀ ቀን" መሆኑንም ይኸው የዮሐንስ ወንጌል ይገልጣል (ዮሐ. 19፡14)። የኢየሱስ ከሳሾች በጊዜው ገና የፋሲካ ምግብ እንዳልበሉ ዮሐንስ 18፡28 ውስጥ ተገልጧል። ዮሐንስ 13፡29 ውስጥ የተጻፈው ቃልም የይሁዳን ተልዕኮ በተመለከተ ሌሎቹ ሐዋርያት የነበራቸው ግንዛቤ፥ የፋሲካው ሥርዓት በሚቀጥለው ዕለት በመሆኑ ላይ የተመሠረተ እንደነበር ያስገነዝባል። የፋሲካ ምግብ መበላት የነበረበት በወሩ አሥራ አራተኛ ቀን ፍጻሜ ምሽትና፥ በአሥራ አምስተኛው ቀን መጀመሪያ ስለነበር (ዘሌዋ. 23፡5)፥ ዮሐንስ ኢየሱስ የሞተበትን ዕለት የወሩ (ኒሳን) አሥራ አራተኛው ቀን እንደሆነ አድርጎ ነው የተረዳው።

በጥያቄው ሌላ አቅጣጫ ሲታይ ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ በጌታ ሞት ዋዜማ የተከናወነውን የጌታ እራት ሥርዓት በወሩ አሥራ አራተኛ ቀን ማብቂያና በአሥራ አምስተኛው መጀመሪያ (ማቴ. 26፡17-20፤ ማር. 14፡12-17፤ ሉቃስ 22፡7-16) ላይ መሆኑን በግልጥ ያስረዳሉ። ሁኔታዎቹ የሚያመለክቱት፥ በእስራኤላውያን ዘንድ የሚታወቀውንና በወሩ አሥራ አራተኛ ቀን የሚከናወነውን የጠቦቶች መሥዋዕት፥ እንዲሁም በዚያው ዕለት ምሽት የሚቀርበውን ምግብ ነው።

ለዚህ እርስ በርሱ የሚጋጭ የሚመስል ነገር መፍትሔ ለመሻት የተለያዩ ሙከራዎች ተደርገዋል። አንዳንዶቹ የዮሐንስ ወንጌል የዘገበው ስሕተት እንደሆነና ሌሎቹ ወንጌላት ግን ትክክል እንደሆኑ ሲናገሩ፥ የቀሩት ደግሞ የዚህን ተቃራኒ አሳብ አቅርበዋል። ሌላው አሳብ ደግሞ የዮሐንስ ወንጌልም ሆነ ሌሎቹ ትክክል ናቸው፤ የሚያስፈልገው ነገር ትርጉሙን በማስማማት ወንጌላቱን ማዛመድ ይቻላል የሚል ነው።

ለዚህ ጉዳይ መፍትሔ የመስጫው የላቀ አሠራር፥ ክርስቶስ የሞተበትን ዕለት በተመለከተ ሁለቱም መንገዶች ትክክል መሆናቸውን መቀበል ነው። ይህ ይቻላል። ምክንያቱም፥ ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ የነበሩ አይሁዳውያን ቀናትን የመለያ ሁለት መንገዶች የነበሯቸው ይመስላል። እያንዳንዱን አዲስ ዕለት ከፀሐይ መጥለቂያ

በመጀመር ከሚታወቀው አሠራር በተጨማሪ፥ የአንዳንዶች መመሪያ ዕለትን የሚለየው ከፀሐይ መውጫ እስከ ጸሐይ መውጫ ባለው ጊዜ ነው። ከላይ የተጠቀሰው እያንዳንዱ የአቆጣጠር ባሕል ከብሉይ ኪዳን ድጋፍ አለው። የመጀመሪያው የዘፍጥረት 1፡5 እና ዘጸአት 12፡18፤ ሁለተኛው ዘፍጥረት 8፡22 እና 1ኛ ሳሙኤል 19፡11 በመሳሰሉት ይደገፋሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስና ደቀ መዛሙርቱ የተገለገሉበትና፥ በማቴዎስ፥ በማርቆስና በሉቃስ የተገለጠው የቀን አቆጣጠር ሥርዓት፥ ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መውጫ ያለው ነው። ዮሐንስ ሁነቶችን የሚገልጣቸው ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ባለው የቀን አቆጣጠር ዘዴ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት አሠራሩ በጊዜው ይበልጥ ይታወቅ ስለነበር ነው (በዚህ መጣጥፍ "የሳምንቱ ዕለት" በሚለው ርዕስ ሥር የቀረበውን አሳብ ይመልከቱ)። ይህ የሚያመለክተው፥ በፈሪሳውያን (አንድ ቀን ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መውጫ ያለው ነው) በሚሉትና፥ በሰዱቃውያን (ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ) በሚሉት መካከል የልዩነት ነጥብ መኖሩን ነው።

ስለዚህ ከዮሐንስ ወንጌል በስተቀር፥ ሌሎቹ ኢየሱስ የፋሲካን እንጀራ የበላው በመሞቻው ዋዜማ መሆኑን ነው የሚገልጡት። አንድ ቀን ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መውጫ ያለው ጊዜ ነው የሚሉት ወገኖች ደግሞ የፋሲካ ጠቦቶች የታረዱት ከቀትር በኋላ ጥቂት ሰዓታት ቀደም ብሎ መሆኑን ይናገራሉ። በነሱ አባባል እርዱ የተከናወነው በወሩ (ኒሳን) በአሥራ አራተኛው ቀን፥ የፋሲካው እንጀራ በተበላበት ጊዜ ነው። የወሩ አሥራ አምስተኛ ቀን እስከሚቀጥለው ዕለት፥ ማለት አርብ ከማለዳው አሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ድረስ አልጀመረም።

ይሁን እንጂ ዮሐንስ ሁነቶችን የሚመለከታቸው ቤተ መቅደሱን ያዝዙ ከነበሩት ሰዱቃውያን አንጻር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው፥ ጠቦቶች ለፋሲካ በዓል በሚታረዱበት ሰዓት፥ ማለት በኒሳን በአሥራ አራተኛው ቀን ከሰዓት በኋላ ነበር። ይህ ዕለት ሐሙስ ፀሐይ ስትጠልቅ ጀምሮ አርብ ፀሐይ ስትጠልቅ ያበቃል። የፋሲካ ጠቦቶች የሚሰዉበት ትክክለኛ ጊዜ ይህ ነው። ነገር ግን የቤተ መቅደሱ ባለሥልጣናት ሌላ የቀን አቆጣጠር ከሚከተሉ ሰዎች ጋር በመስማማት ጠቦቶችን ሐሙስ ዕለት እንዲያርዱ ሳይፈቅዱላቸው አልቀሩም። ይህ ባይሆን ኑሮ የሚሰዉአቸውን እንስሳት ይዘው ለፋሲካው ዝግጅት በዓል በየዓመቱ የሚመጡትን ሰዎች በሚገባ ለማስተናገድ አይቻልም ነበር። የኢየሱስ ወንጀዮች የፋሲካ ምግብ ሳይበሉ የዘገዩበትን ምክንያት ይህ ልዩነት ያስረዳል (ዮሐ. 18፡28)። እነሱ በዓሉን አርብ ማታ ማለት ፀሐይ መግቢያ በሚጀምረው ኒሳን 15 ቀን ሊያደርጉ በመዘጋጀት ላይ ነበሩ።

ከላይ የቀረበው መፍትሔ ትክክል ከሆነ እንግዲህ፥ ኢየሱስ የሞተው (በጭፍን እንዲሁ ትክክል ነው ለማለት አይቻልም፤ ነገር ግን ከሌሎቹ አሳቦች ሁሉ የላቀ ማረጋገጫ የያዘ ይመስላል) አንድን ዕለት ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መውጫ ለሚቆጥሩት ኒሳን 15 ቀን ፥ ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ባለው ጊዜ ለሚያሰሉት ደግሞ ኒሳን 14 ነው።

## ዓመቱ

ኢየሱስ የሞተበትን ዕለት በመወሰኑ ረገድ የኮከብ ቆጠራው መስከ በተሻለ ይረዳል። የአይሁዳውያን የቀን አቆጣጠር በጨረቃ መውጣትና መጥለቅ ላይ የተመሠረተ ነበር። በመሆኑም የኢየሱስን ሞት አጠቃላይ ጊዜ ከአዲስ ጨረቃ መታየት

ጋር በማያያዝ፥ ኒሳን 14 (ከፀሐይ መጥለቅ እስከ ፀሐይ መጥለቅ ባለው ስሌት መሠረት) ከሐሙስ ፀሐይ መጥለቅ እስከ አርብ ፀሐይ መጥለቅ ድረስ ያለው ጊዜ የዋለበትን ዓመት ለመረዳት ይቻላል።

ኢየሱስ በ26 ዓ.ም. እና በ36 ዓ.ም. መካከል ባለው ጊዜ የተሰቀለ መሆኑ ይታወቃል። ይህ የሚባልበት ምክንያት ጊዜው ጲላጦስ የአካባቢው ገዢ የነበረበት በመሆኑ ነው (ዮሐ. 19፡15-16)። ውስብስብ የሆኑና በከዋክብት እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረቱ ስሌቶች እንደሚያስረዱት፥ በዚያ ዘመን ኒሳን 14 አርብ ዕለት የዋለው ሁለት ጊዜ፥ ማለት በ30 ዓ.ም. እና በ33 ዓ.ም. ነበር።

በ30 እና በ33 ዓ.ም. ነው ብሎ መወሰኑ ቀላል ነገር አይደለም። ምክንያቱም ጉዳዩ በብዙ መልኩ ከክርስቶስ ሕይወት ጋር የተያያዘ ቅደም ተከተላዊ ገጽታ አለው። መጨረሻ ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት አንዳንድ ነገሮች፥ ለምሳሌ የኢየሱስን ልደት አስመልክቶ "ጢባርዮስ ቄሣርም በነገሠ በአሥራ አምስተኛው ዓመት" (ሉቃስ 3፡1-2) የሚለው፥ "ሠላሳ ዓመት ያህል" "ሉቃስ 3፡23" የሚለው፥ ዮሐንስ ደግሞ "ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር" (ዮሐንስ 2፡20) የሚለውና ኢየሱስ ከሞተበት ዓመት ጋር የተያያዙ ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው። ቀጥሎ የሚቀርበው መጣጥፍ ይህን ጉዳይ በይበልጥ ያብራራዋል።

# 5

# የኢየሱስ ለምርመራ መቅረብ

ደቀ መዛሙርቱ ከሌላው ጊዜ ይልቅ ስለመጨረሻዎቹ የኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት ብዙ መረጃዎችን ይሰጡ ነበር። በአጠቃላይ ሲታይ፥ ወንጌላት ስለመጨረሻው ሳምንት ጠለቅ ያለ ገለጣ ይሰጣሉ። በተለይ ስለ ኢየሱስ መያዝና ለፍርድ መቅረብ የገለጡት ጉዳይ አይሁዳውያንና የክርስቲያን ምሁራንን ለረጅም ጊዜ እንዲመሰጡ አድርጓቸው ነበር።

ደቀ መዛሙርቱ እውነተኛ መረጃዎች ሰጥተውናል ብለን ካሰብን፥ እስከ ኢየሱስ መሰቀል ድረስ ያሉት ሁኔታዎች በሚከተሉት መንገዶች ተከናውነዋል ለማለት እንችላለን።

1. በመጨረሻው ሳምንት ሀሙስ ምሽት ደርብ ላይ ከነበረው አዳራሽ እስከ ጌቴሰማኒ የአትክልት ስፍራ ድረስ ከተደረገው ጉዞ በኋላ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ኢየሱስን አትክልቱ ውስጥ በጨለማ ተገናኘው። ይሁዳ ብቻውን አልነበረም። በአጠቃላይ የሸንጎው ተወካዮች፥ የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች፥ እንዲሁም ሁለት መቶ የሚሆኑ ሮማውያን ወታደሮች አብረውት እንደነበሩ ተገልጧል። የሚፈልጉት እሱን መሆኑን ቀድሞውን ኢየሱስ ያወቀ ቢሆንም፥ ይሁዳ በመሳም ለጠላቶቹ አሳልፎ ሰጠው። በዚህ አኳኋን ኢየሱስን ወሰዱት፤ አሠሩት።

ጴጥሮስ የኢየሱስን የመያዝ ሙከራ ለማገድ የሊቀካህናቱን አለቃ ጭፍራ ቀኝ ጆሮ በሰይፍ ቆረጠው። ኢየሱስ ግን ጴጥሮስን ስለ ድርጊቱ ገስፀውና የጭፍራውን ማለት የማልኩስን ጆሮ በነበረበት መሰሰለት። ያ ያልተገባና ጀብደኛ የጴጥሮስ ድርጊት በኢየሱስ ከተገሰፀ በኋላ ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ጥለውት ሸሹ። ጴጥሮስ ሁኔታውን ከርቀት ለመከታተል ተመልሶ ነበር።

2. ኢየሱስ ወደ ቀድሞው ሊቀካህን ወደሃና ተወሰደ። በመጀመሪያው የአይሁዳውያን ምርመራ ክፍል በሃና በአጭሩ ተጠየቀ። ከዛም የሃና አማች ወደሆነው የጊዜው ሊቀካህን ወደ ቀያፋ ተላከ።

3. በቀያፋ ቤት ጉባኤው ለምሽት ውይይት ተሰብስቦ ነበር። ይህ ኢየሱስ የሚቀርብበት ሁለተኛው የአይሁዳውያን የምርመራ ክፍል ነበር። የዓይን ምስክሮች በኢየሱስ ላይ እንዲመሠክሩ ቢቀርቡም ከነሱ ሁለቱ እንኳን ቃላቸው አልተስማማም። ኢየሱስም ክሱን በዝምታ ተቃወመ። በመጨረሻም ከቀያፋ ጉትጎታ በኋላ ኢየሱስ መሢሕ፥ የእግዚአብሔር ልጅ፥ እንዲሁም የሰው ልጅ መሆኑን ገለጠ። ቀያፋም ይህን የኢየሱስ ገለጣ ስድብና ሞት የሚገባው አድርጎ ፈረደ። ጉባዔውም በፍርዱ ተስማማ፥ አፀፋው፥ የአካል ስቃይም ያደርስበት ጀመር።

4. ሦስተኛው የአይሁዶች ምርመራ የተካሄደው በማግስቱ ጠዋት ነበር። ምንም እንኳን ባለፈው ምሽት ጉባኤ የተገኙት መጠነኛ ቢሆኑ የአሁኑ ስብሰባ ምልአተ ጉባኤ ነበር። ይሄኛውም ጉባኤ ያለፈውን ክስና ፍርድ አጸደቀ።

5. አሁን የኢየሱስ ምርመራ ወደ አዲስ ምዕራፍ መሸጋገሩ ነው። ምክንያቱም አይሁዳውያን ሰውን በሞት የመቅጣት ውሳኔ የማሳለፍ አጠቃላይ ሥልጣን አልነበራቸውም። ስለዚህ ኢየሱስ ለመጀመሪያው የሮማውያን ምርመራ ወደ ሮማዊው ገዥ ወደ ጲላጦስ ተወሰደ። ጉባኤው በኢየሱስ ላይ ያቀረባቸው ክሶች ሦስት ነበሩ። እነርሱም "ሕዝባችንን ያውካል፤ "ለቄሣር የሚከፈለውን ቀረጥ ይቃወማል፤ ራሱን የተቀባሁ ንጉሥ ነኝ ይላል" (ሉቃስ 23፡2) የሚሉ ናቸው።

6. ኢየሱስ ብዙ ሥራዎችን ያከናወነው ገሊላ ውስጥ መሆኑን በመጥቀስ ሁለተኛው ምርመራ ወደ ሄሮድስ አንቲጳስ ተመራ። ሄሮድስ ያኔ ኢየሩሳሌም ውስጥ ነበር። ጲላጦስ ኢየሱስን ወደ ሄሮድስ የላከው ምናልባት ችግሮችን ከራሱ ለማራቅ ወይም በሄድሮስ ዘንድ መወደድን ለማግኘት ሳይሆን አይቀርም። ሄሮድስ በኢየሱስ ላይ ለማሾፍና እሱን ለመጠየቅ ዕድል ቢያገኝም አልፈረደበትም። መልሶ ወደ ጲላጦስ ላከ።

7. ጉዳዩ ወደ ጲላጦስ ተመለሰና የሮማውያን ምርመራ ሦስተኛ ክፍል ተጀመረ። ጲላጦስ በኢየሱስ ላይ የቀረቡትን ክሶች ማየትና የኢየሱስን ንፁህነት በራሱ ውሳኔ ማረጋገጥ ጀመረ። ሄሮድስም ኢየሱስን ለሞት የሚያበቃ ጥፋት ያላገኘበት መሆኑን ተረዳ። ነገር ግን ጲላጦስ ስለ ኢየሱስ ንጹሕነት በነበረው እምነትና በአይሁዳውያን ኢየሱስን ለሞት አሳልፎ የመስጠት ፍላጎት ሁከት አሳቡ ሁለት ላይ ተከፈለ።

ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ይህን ውስብስብ ችግር ለመፍታት መፍትሔ መፈለግ ጀመረ። በነበረው ልማድ መሠረት የፋሲካ በዓልን ምክንያት በማድረግ አንድ አይሁዳዊ እስረኛ ይለቀቅ ነበር። ይህንኑ ዓመታዊ ምሕረት ለመጠየቅም ሕዝቡ ይሰበሰባል። በዚሁ መሠረት ሕዝቡ ከኢየሱስና አዋኪ ከነበረው ወንበዴ ከባራባስ የትኛውን ሊፈታላቸው እንደሚሹ ሊያስመርጣቸው ወሰነ። የአይሁድ መሪዎች በኢየሱስ ላይ ያላቸው ጥላቻ ምክንያት ቅናት መሆኑን ጲላጦስ አውቋል። ለዚህም ሕዝቡ ያለጥርጥር ከባራባስ ይልቅ ኢየሱስ እንዲለቀቅለት ስለሚፈልግ ያን በመፈጸም ጲላጦስ ከጉዳዩ የሚገላገል መስሎት ነበር። ጲላጦስ ግን ሕዝቡን ለአድማ የቀሰቀሱት ሊቀ ካሕናትና ሽማግሌዎች የማነሣሣት ጉልበት ያላቸው መሆኑን ወይም ባራባስ በሕዝቡ የሚወደድ መሆኑን አልተረዳም ነበር። ሕዝቡ በቀረበለት የምርጫ ዕድል መሠረት የኢየሱስን መሰቀልና የባራባስን መለቀቅ መረጠ። ጲላጦስ ሕዝቡን ለማግባባት ሙከራ ቢያደርግም ሁካታው እንዲጨምር አደረገ እንጂ የፈየደው ነገር አልነበረም። ኢየሱስን ሊፈታው ቢሞክርም፥ ያን ካደረገ ጲላጦስ የቄሳር ወዳጅ ሊሆን እንደማይችል በመግለጥ ሕዝቡ ወነጀሉት። ይህ ክስ የጲላጦስን የፖለቲካ አቋም የሚያወድመው ሊሆን ይችል ነበር። ይህን በመፍራትና ከእምነት ይልቅ ሥራን በማስቀደም ጥያቄያቸውን ለመቀበል ወሰነ። በንጹሑ ሰው ሞት ምክንያት ከሚመጣ ተጠያቂነት ለመዳን ተስፋ በማድረግም በሕዝቡ ፊት እጆቹን ታጥቦ ከኢየሱስ ደም ንጹሕ መሆኑን ገለጠ። በዚሁ መሠረት ባራባስ ተለቀቀ። ኢየሱስ ግን ተገርፎ እንደ አይሁዳውያን ፍላጎት በሮማውያን የሞት ቅጣት መሠረት እንዲሰቀል ለሮማውያን ወታደሮች ተሰጠ።

# 6

# የሄሮድስ ቤተሰብ

በታሪክ "ታላቁ ሄሮድስ" ተብሎ የሚታወቀውና ዘሩ መላውን ፍልስጥኤም ከ100 ዓመታት በላይ ገዝተዋል። በተለያዩ ምክንያቶች የዚህን ቤተሰብ የእርስ በእርስ ዝምድና ለማወቅ በጣም አዳጋች ነው። ለምሳሌ፥ 1. አብዛኛውን ጊዜ ተመሳሳይ ስምና ማዕረግ ይጠቀማሉ፤ 2. አንዳንድ ጊዜ ስማቸውንና ማዕረጋቸውን ይለውጣሉ ወይም የሚጨምሩበት ነገር አለ፤ 3. ቤተሰቡ እርስ በእርሱ ይጋባል።

አዲስ ኪዳን ውስጥ 11 የቤተሰቡ አባላት ተጠቅሰዋል። የእነዚህን ሰዎች የእርስ በእርስ ዝምድናና መጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱበትን ቦታ ለመግለጥ እንሞክራለን። ትውልዱን ይበልጥ ግልጥ ለማድረግ እያንዳንዱ ሰው ቁጥር ተሰጥቶታል። ለምሳሌ፥ 100 ቤት ቁጥር የተሰጣቸው ከመጀመሪያው ትውልድ ሲሆኑ፥ 200 ቤት ቁጥር የተሰጣቸው ደግሞ ከሁለተኛው ትውልድ የሆኑ ናቸው። (በዚህ ጽሑፍ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ስዕላዊ መግለጫ ይመልከቱ።)

ታላቁ ሄሮድስ (#101) በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ሄሮድስ ወይም ንጉሥ ሄሮድስ" በመባልም የሚታወቅ ሲሆን፥ ከ37 ዓ.ዓ. እስከ 4 ዓ.ዓ. ድረስ ገዝቷል። በሮማውያን መሪዎች ዘንድ "የአይሁዶች ንጉሥ" የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል። የታላቁ ሄሮድስ የትውልድ ሥፍራ ከይሁዳ በስተደቡብ በኩል የሚገኘውና ኤዶምያስ የሚባለው ቦታ ነው። ይህ ቦታ መጀመሪያ የኤሳው ትውልድ በሆኑት ኤዶማውያን ተይዞ ነበር። ኤሳው የያዕቆብ ወንድም ነው። ኤዶምያስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው በማርቆስ 3፡8 ውስጥ ብቻ ነው።

ታላቁ ሄሮድስ ቢያንስ 10 ሚስቶችና ብዙ ልጆች ነበሩት። የታወቀውም በሕንፃ ሥራዎቹ ነው፦ ቤተ መቅደሱን አድሷል፥ የኢየሩሳሌምን ከፊል ግንብ ገንብቷል፥ እንዲሁም በቂሣርያና በሰማርያ ከተማዎች ላይ የተለያዩ የግንባታ ሥራዎች አከናውኗል።

ታላቁ ሄሮድስ በጭካኔ ሥራውም ይታወቃል። ቤተልሔም ውስጥ ሕፃናትን ማስገደሉ አይረሳም። ቢያንስ ሦስት ልጆቹን አስገድሏል። በሞት ጣር ተይዞ ሳለ ከብዙ መንደሮች የአይሁድ መሪዎች ተይዘው እንዲታሠሩ አድርጓል። በሚሞትበት ጊዜ የሚያለቅሱ ሰዎች ለመኖራቸው እርግጠኛ ለመሆንም እርሱ በሚሞትበት ጊዜ የታሠሩት መሪዎች እንዲገደሉ ትእዛዝ ሰጥቶ ነበር። ሆኖም ከሞተ በኋላ ከሚስቶቹ መካከል አንደኛዋ ይህ ትእዛዝ እንዳይፈጸምና መሪዎቹ እንዲለቀቁ አድርጋለች። በመሆኑም ሄሮድስ በሞተ ጊዜ ሐዘን ሳይሆን ታላቅ ደስታ ነበር። (ታላቁ ሄሮድስ ማቴዎስ 2፡1-22 እና ሉቃስ 1፡5 ውስጥ ተጠቅሷል።)

ታላቁ ሄሮድስ ከሞተ በኋላ አገሪቱ ለሦስት ልጆቹ ተከፋፈለች።

1. አንደኛው ልጁ አርኬላዎስ (#203) በይሁዳ ከ4 ዓ.ዓ. እስከ 6 ዓ.ም. ነግሦአል። በሕዝቡ ዘንድ የተጠላ በመሆኑ፥ የይሁዳና የሰማርያ መሪዎች ተቃውሟቸውን ለአውግስጦስ ቄሣር አሰምተው አርኬላዎስ ከሥልጣን እንዲወርድና በግዞት እንዲቀመጥ ተደርጓል። ([አርኬላዎስ ማቴዎስ 2፡22 ውስጥ ተጠቅሷል።)

2. ሄሮድስ አንቲጳስ (#202) በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ሄሮድስ"፥ "ንጉሥ ሄሮድስ" ወይም "የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስ" በመባልም የሚታወቅ

ሲሆን፥ የገሊላና የፖርያ ገዥ ነበር። ሄሮድስ አንቲጳስ በግንባታ ሥራው የታወቀ ነበር። ይህ ሥራው ገሊላ ባሕር አጠገብ ያለችውን የጥብርያዶስ ከተማ ግንባታን ያጠቃልላል። የመጀመሪያ ሚስቱ የንጉሥ ናባታ ልጅ ነበረች። እሷን ፈትቶ ሄሮድያዳ የተባለችውን የወንድሙን ልጅ በሚያገባበት ጊዜ ናባታ ጦሩን አሰባስቦ የሄሮድስ አንቲጳስን ጦር ደመሰሰ። በ39 ዓ.ም. ከሥልጣን ተወግዶ ፈረንሣይ በሚገኘው ጎል በግዞት ተቀመጠ።

ወንጌላት ውስጥ በሁለት ነገሮች የታወቀ ነው፦ 1. የመጥምቁ ዮሐንስን አንገት በመቁረጡ፤ 2. በኢየሱስ ፍርድ ላይ በመካፈሉ።

(ሄሮድስ አንቲጳስ በማቴ. 14፡1-6፤ ማር. 6፡14-22፤ ሉቃስ 3፡1፤ 19-20፤ 8፡3፤ 9፡7-9፤ 13፡31፤ 23፡7-15፤ ሐዋ. 4፡27፤ 13፡1 ውስጥ ተጠቅሷል።)

3. ፊልጶስ (#205) በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ፊልጶስ" ወይም "የአራተኛው ክፍል ገዥ ፊልጶስ" በመባል ይታወቃል። ከ4 ዓ.ዓ. እስከ 34 ዓ.ም. ድረስ ሰሜን ምሥራቅ ፍልስጥኤም ውስጥ በሚገኙ ብዙ ግዛቶች ላይ ገዥ ነበር። ሰሎሜ የምትባለውን የሄሮድያዳ የመጀመሪያ ባል ልጅ የሆነችውን የወንድሙን የልጅ ልጅ ነበር ያገባው። (ፊልጶስ ሉቃስ 3፡1 ውስጥ ተጠቅሷል።)

ሌላው የታላቁ ሄሮድስ ልጅ ሄሮድስ ፊልጶስ (#204) ነው። በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ፊልጶስ" በመባል ሲታወቅ፥ ሄሮድያዳ የምትባለው የወንድሙ ልጅ የመጀመሪያ ባል ነበር። ሕይወቱን ሙሉ የኖረው ሰላማዊ ዜጋ በመሆን ነበር (ሄሮድስ ፊልጶስ ማቴ. 14፡3፤ ማር. 6፡17፤ ሉቃስ 3፡19 ውስጥ ተጠቅሷል።)

ሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ (#301) በአዲስ ኪዳን "ሄሮድስ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ ነው። በ7 ዓ.ዓ. አባቱ አርስቶቡሎስ (#201) በታላቁ ሄሮድስ ከተገደለ በኋላ ወደ ሮም ተሰደደ። ለብዙ ዓመታት ሮም ውስጥ ወጣ ገባ በማለት ኖረ። በ36 ዓ.ም. ንጉሥ ጢባርዮስ አሳሰረው። ከአንድ ዓመት በኋላ ካሊጉላ በሚባለው አዲስ ንጉሥ ከእሥር ነጻ በመውጣት የሰሜን ምሥራቅ ፍልስጥኤም ገዢ እንዲሆን ተልኳል። በ39 ዓ.ም. ገሊላና ፖርያ ግዛቱ ውስጥ ተጨምረውለታል። በ41 ዓ.ም. ደግሞ ይሁዳና ሰማርያን እንዲቆጣጠር ተሰጥተውታል። ከልጆቹ ውስጥ አንዱ ወንድ ልጅና ሁለቱ ሴት ልጆቹ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰዋል። በ44 ዓ.ም. በ53 ዓመት ዕድሜው መሞቱ ሐዋርያት ሥራ 12፡1-24 ውስጥ ተጠቅሷል።

ሄሮድያዳ (#303) የአርስቶቡሎስ ሴት ልጅ፥ የሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ (#301) እህት ናት። በመጀመሪያ ሄሮድስ ፊልጶስ (#204) የሚባለውን አጎቷን ያገባች ሲሆን፥ በኋላም እሱን በመተው ሌላውን ሄሮድስ አንቲጳስ (#205) የሚባለውን አጎቷን አግብታለች። በሄሮድስ አንቲጳስ ፊት በመደነስ ለመጥምቁ ዮሐንስ ሞት ምክንያት የሆነችው፥ ምናልባት ሰሎሜ የምትባለው ልጇ ሳትሆን አትቀርም (ማቴ. 14፡3፥ 6፤ ማር. 6፡19)።

ሄሮድስ አግሪጳ 2ኛ (#401) በአማርኛው አዲስ ኪዳን "ንጉሥ አግሪጳ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን፥ የተወለደው በ27 ዓ.ም. ነበር። አባቱ በሞተ ጊዜ፥ የአባቱን ቦታ ለመተካት ያልደረሰ ወጣት ነበር። ሆኖም ከጊዜ በኋላ በንጉሥ ቀላውዴዎስ በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ ፍልስጥኤም ግዛት ተሰጠው። በ56 (በ54) ዓ.ም. ንጉሥ ኔሮ ግዛቱ ውስጥ ተጨማሪ መሬት ሰጠው።

ሄሮድስ አግሪጳ 2ኛ ከ66-70 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ አይሁዳውያን በሮም


ላይ ያነሡትን አመጽ ለመግታት ሞክሯል። ለዚህ ሥራውም ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ የሮም መንግሥት ተጨማሪ መሬት ሰጥቶታል። ሄሮድስ አግሪጳ 2ኛ የሞተው በ100 ዓ.ም. ነው (ሐዋ. 25፡13-26፡32)።

በርኒቄ (#402)፥ የሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ (#301) ልጅ፥ በ28 ዓ.ም. ተወለደች። የካልሲሱ ሄሮድስ (302) የተባለውን አጎቷን አገባች። በ48 ዓ.ም. ከሞተ በኋላ ሄሮድስ አግሪጳ 2ኛ የተባለው ወንድሟ ቅምጥ ሆነች። ከዚያም ሌላ ሰው አገባችና ይህን ሰው በመፍታት ወደ ወንድሟ ተመለሰች። በኋላም የንጉሥ ጥጦስና ቬስፓሲያን ቅምጥ ሆነች። ከወንድሟ ጋር ሳለች ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ቃለ ምልልስ አድርገዋል። ይህም በሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ 25-26 ተመዝግቧል።

ድሩሲላ (#403) የሄሮድስ አግሪጳ 1ኛ (#301) ሌላ ሴት ልጁ ነበረች። የተወለደችው በ38 ዓ.ም. ሲሆን፥ የሶርያን ንጉሥ አግብታለች። በኋላም ንጉሡን በመተው ፊሊክስ የተባለውን የሮም ባለሥልጣን አገባች። ከእርሱ ጋር በመሆን በ57 (59) ዓ.ም. ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ተገናኝተዋል። ይህም በሐዋርያት ሥራ 24፡24 ተጠቅሷል።

ሰሎሜ (#404) የሄሮዲያዳ ልጅ ናት። ሄሮዲያዳ ሰሎሜን የወለደችው የመጀመሪያ ባሏ ከሆነው ከሄሮድስ ፊልጶስ (#204) ሲሆን፥ እሱም የታላቁ ሄሮድስ ልጅ ነው። በወንጌላት ባይጠቀስም በሄሮድስ ፊት በመደነስ ለመጥምቁ ዮሐንስ ሞት ምክንያት የሆነችው እሷ እንደነበረች ይገመታል። በኋላም የአራተኛው ክፍል ገዥ ፊልጶስ (#205) የተባለውን የእናቷን አጎት አግብታለች (ማቴ. 14፡1-12፤ ማር. 6፡14-29)።

# የሄሮድስ የዘር ግንድ



# የጥቅሶች ማውጫ በቅደም ተከተል


| | | ማቴዎስ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ | ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
| 1 | 1-17 | 3 | 24 | 11 | 2-19 | 57 | 77 |
| 1 | 18-25 | 9 | 30 | 11 | 20-30 | 58 | 78 |
| 2 | 1-12 | 14 | 32 | 12 | 1-8 | 50 | 64 |
| 2 | 13-18 | 15 | 33 | 12 | 9-14 | 51 | 65 |
| 2 | 19-23 | 16 | 34 | 12 | 15-21 | 52 | 66 |
| 3 | 1-6 | 21 | 36 | 12 | 22-37 | 61 | 81 |
| 3 | 7-10 | 22 | 37 | 12 | 38-45 | 62 | 82 |
| 3 | 11-12 | 23 | 38 | 12 | 46-50 | 63 | 83 |
| 3 | 13-17 | 24 | 39 | 13 | 1-3ሀ | 64ሀ | 84 |
| 4 | 1-11 | 25 | 40 | 13 | 3ለ-23 | 64ለ | 84 |
| 4 | 12 | 34 | 47 | 13 | 24-30 | 64መ | 87 |
| 4 | 13-16 | 40 | 52 | 13 | 31-32 | 64ሠ | 88 |
| 4 | 17 | 37 | 50 | 13 | 33-35 | 64ረ | 88 |
| 4 | 18-22 | 41 | 52 | 13 | 36-43 | 64ሰ | 88 |
| 4 | 23-25 | 44 | 55 | 13 | 44 | 64ሸ | 89 |
| 5 | 1-2 | 54ሀ | 67 | 13 | 45-46 | 64ቀ | 89 |
| 5 | 3-12 | 54ለ | 68 | 13 | 47-50 | 64በ | 89 |
| 5 | 13-16 | 54ሐ | 69 | 13 | 51-53 | 64ተ | 89 |
| 5 | 17-20 | 54መ | 69 | 13 | 54-58 | 69 | 97 |
| 5 | 21-48 | 54ሠ | 69 | 14 | 1-2 | 71ሀ | 101 |
| 6 | 1-18 | 54ረ | 71 | 14 | 3-12 | 71ለ | 102 |
| 6 | 19-7:6 | 54ሰ | 72 | 14 | 13-14 | 72ለ | 104 |
| 7 | 7-27 | 54ሸ | 73 | 14 | 15-21 | 72ሐ | 105 |
| 7 | 28-8:1 | 54ቀ | 75 | 14 | 22-23 | 73 | 108 |
| 8 | 2-4 | 45 | 56 | 14 | 24-33 | 74 | 108 |
| 8 | 5-13 | 55 | 75 | 14 | 34-36 | 75 | 110 |
| 8 | 14-17 | 43 | 54 | 15 | 1-20 | 77 | 113? |
| 8 | 18 | 65 | 90 | 15 | 21-28 | 78 | 115 |
| 8 | 19-22 | 93 | 134 | 15 | 29-31 | 79ሀ | 116 |
| 8 | 23-27 | 65 | 90 | 15 | 32-38 | 79ለ | 117 |
| 8 | 28-34 | 66 | 91 | 15 | 39-16:4 | 80 | 118 |
| 9 | 1-8 | 46 | 57 | 16 | 5-12 | 81ሀ | 118 |
| 9 | 9 | 47ሀ | 59 | 16 | 13-20 | 82 | 120 |
| 9 | 10-13 | 47ለ | 59 | 16 | 21-26 | 83 | 122 |
| 9 | 14-17 | 48 | 60 | 16 | 27-28 | 84 | 123 |
| 9 | 18-26 | 67 | 93 | 17 | 1-8 | 85 | 123 |
| 9 | 27-34 | 68 | 96 | 17 | 9-13 | 86 | 125 |
| 9 | 35-38 | 70ሀ | 97 | 17 | 14-21 | 87 | 126 |
| 10 | 1-42 | 70ለ | 97 | 17 | 22-23 | 88 | 128 |
| 11 | 1 | 70ሐ | 101 | 17 | 24-27 | 89 | 129 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 18 | 1-5 | 90 | 129 |
| 18 | 6-14 | 91 | 130 |
| 18 | 15-35 | 92 | 133 |
| 19 | 1-12 | 122 | 172 |
| 19 | 13-15 | 123 | 173 |
| 19 | 16-30 | 124ሀ | 174 |
| 20 | 1-16 | 124ለ | 177 |
| 20 | 17-19 | 125ሀ | 178 |
| 20 | 20-28 | 125ለ | 179 |
| 20 | 29-34 | 126 | 180 |
| 21 | 1-11 | 128ለ | 184 |
| 21 | 12-13 | 129ለ | 189 |
| 21 | 14-17 | 128ለ | 184 |
| 21 | 18-19ሀ | 129ሀ | 188 |
| 21 | 19ለ-22 | 131 | 191 |
| 21 | 23-27 | 132ሀ | 193 |
| 21 | 28-22:14 | 132ለ | 194 |
| 22 | 15-22 | 133 | 197 |
| 22 | 23-33 | 134 | 199 |
| 22 | 34-40 | 135 | 200 |
| 22 | 41-46 | 136 | 201 |
| 23 | 1-36 | 137ሀ | 202 |
| 23 | 37-39 | 137ለ | 205 |
| 24 | 1-3 | 139ሀ | 206 |
| 24 | 4-14 | 139ለ | 207 |
| 24 | 15-28 | 139ሐ | 209 |
| 24 | 29-31 | 139መ | 211 |
| 24 | 32-41 | 139ሠ | 212 |
| 24 | 42-25:30 | 139ረ | 213 |
| 25 | 31-46 | 139ሰ | 215 |
| 26 | 1-5 | 140 | 216 |
| 26 | 6-13 | 141 | 217 |
| 26 | 14-16 | 142 | 218 |
| 26 | 17-19 | 143 | 218 |
| 26 | 20 | 144 | 219 |
| 26 | 21-25 | 146 | 221 |
| 26 | 26-29 | 148 | 225 |
| 26 | 30 | 152 | 232 |
| 26 | 31-35 | 147 | 223 |
| 26 | 36-46 | 152 | 232 |
| 26 | 47-56 | 153 | 235 |
| 26 | 57 | 155 | 239 |
| 26 | 58 | 156 | 241 |
| 26 | 59-68 | 155 | 239 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 26 | 69-75 | 156 | 241 |
| 27 | 1 | 157 | 243 |
| 27 | 2 | 159 | 244 |
| 27 | 3-10 | 158 | 244 |
| 27 | 11-14 | 159 | 244 |
| 27 | 15-26 | 161 | 248 |
| 27 | 27-30 | 162 | 252 |
| 27 | 31-34 | 163 | 253 |
| 27 | 35-44 | 164 | 255 |
| 27 | 45-50 | 165 | 259 |
| 27 | 51-56 | 166 | 260 |
| 27 | 57-58 | 167ሀ | 261 |
| 27 | 59-60 | 167ለ | 263 |
| 27 | 61-66 | 168 | 263 |
| 28 | 1 | 169 | 265 |
| 28 | 2-4 | 170 | 265 |
| 28 | 5-8 | 171 | 265 |
| 28 | 9-10 | 174 | 269 |
| 28 | 11-15 | 175 | 269 |
| 28 | 16-20 | 181 | 274 |

**ማርቆስ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | 1 | 20 | 36 |
| 1 | 2-6 | 21 | 36 |
| 1 | 7-8 | 23 | 38 |
| 1 | 9-11 | 24 | 39 |
| 1 | 12-13 | 25 | 40 |
| 1 | 14ሀ | 34 | 47 |
| 1 | 14ለ-15 | 37 | 50 |
| 1 | 16-20 | 41 | 52 |
| 1 | 21-28 | 42 | 53 |
| 1 | 29-34 | 43 | 54 |
| 1 | 35-39 | 44 | 55 |
| 1 | 40-45 | 45 | 56 |
| 2 | 1-12 | 46 | 57 |
| 2 | 13-14 | 47ሀ | 59 |
| 2 | 15-17 | 47ለ | 59 |
| 2 | 18-22 | 48 | 60 |
| 2 | 23-28 | 50 | 64 |
| 3 | 1-6 | 51 | 65 |
| 3 | 7-12 | 52 | 66 |
| 3 | 13-19 | 53 | 67 |
| 3 | 20-30 | 61 | 81 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ | ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | 31-35 | 63 | 83 | 11 | 12-14 | 129ሀ | 188 |
| 4 | 1-2 | 64ሀ | 84 | 11 | 15-18 | 129ለ | 189 |
| 4 | 3-25 | 64ለ | 84 | 11 | 19-26 | 131 | 191 |
| 4 | 26-29 | 64ሐ | 87 | 11 | 27-33 | 132ሀ | 193 |
| 4 | 30-32 | 64ሠ | 88 | 12 | 1-12 | 132ለ | 194 |
| 4 | 33-34 | 64ረ | 88 | 12 | 13-17 | 133 | 197 |
| 4 | 35-41 | 65 | 90 | 12 | 18-27 | 134 | 199 |
| 5 | 1-20 | 66 | 91 | 12 | 28-34 | 135 | 200 |
| 5 | 21-43 | 67 | 93 | 12 | 35-37 | 136 | 201 |
| 6 | 1-6ሀ | 69 | 97 | 12 | 38-40 | 137ሀ | 202 |
| 6 | 6ለ | 70ሀ | 98 | 12 | 41-44 | 138 | 205 |
| 6 | 7-11 | 70ለ | 98 | 13 | 1-4 | 139ሀ | 206 |
| 6 | 12-13 | 70ሐ | 101 | 13 | 5-13 | 139ለ | 207 |
| 6 | 14-16 | 71ሀ | 101 | 13 | 14-23 | 139ሐ | 209 |
| 6 | 17-29 | 71ለ | 102 | 13 | 24-27 | 139መ | 211 |
| 6 | 30 | 72ሀ | 104 | 13 | 28-32 | 139ሠ | 212 |
| 6 | 31-34 | 72ለ | 104 | 13 | 33-37 | 139ረ | 213 |
| 6 | 35-44 | 72ሐ | 105 | 14 | 1-2 | 140 | 216 |
| 6 | 45-46 | 73 | 108 | 14 | 3-9 | 141 | 217 |
| 6 | 47-52 | 74 | 108 | 14 | 10-11 | 142 | 218 |
| 6 | 53-56 | 75 | 110 | 14 | 12-16 | 143 | 218 |
| 7 | 1-23 | 77 | 113 | 14 | 17 | 144 | 219 |
| 7 | 24-30 | 78 | 115 | 14 | 18-21 | 146 | 221 |
| 7 | 31-37 | 79ሀ | 116 | 14 | 22-25 | 148 | 225 |
| 8 | 1-9ሀ | 79ለ | 117 | 14 | 26 | 152 | 232 |
| 8 | 9ለ-12 | 80 | 118 | 14 | 27-31 | 147 | 223 |
| 8 | 13-21 | 81ሀ | 118 | 14 | 32-42 | 152 | 232 |
| 8 | 22-26 | 81ለ | 119 | 14 | 43-52 | 153 | 235 |
| 8 | 27-30 | 82 | 120 | 14 | 53 | 155 | 239 |
| 8 | 31-37 | 83 | 122 | 14 | 54 | 156 | 241 |
| 8 | 38-9:1 | 84 | 123 | 14 | 55-65 | 155 | 239 |
| 9 | 2-8 | 85 | 123 | 14 | 66-72 | 156 | 241 |
| 9 | 9-13 | 86 | 125 | 15 | 1ሀ | 157 | 243 |
| 9 | 14-29 | 87 | 126 | 15 | 1ለ-5 | 159 | 244 |
| 9 | 30-32 | 88 | 128 | 15 | 6-15 | 161 | 248 |
| 9 | 33-37 | 90 | 129 | 15 | 16-19 | 162 | 252 |
| 9 | 38-50 | 91 | 130 | 15 | 20-23 | 163 | 253 |
| 10 | 1-12 | 122 | 172 | 15 | 24-32 | 164 | 255 |
| 10 | 13-16 | 123 | 173 | 15 | 33-37 | 165 | 259 |
| 10 | 17-31 | 124ሀ | 174 | 15 | 38-41 | 166 | 260 |
| 10 | 32-34 | 125ሀ | 178 | 15 | 42-45 | 167ሀ | 261 |
| 10 | 35-45 | 125ለ | 179 | 15 | 46 | 167ለ | 263 |
| 10 | 46-52 | 126 | 180 | 15 | 47 | 168 | 263 |
| 11 | 1-11 | 128ለ | 184 | 16 | 1 | 169 | 265 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 16 | 2-8 | 171 | 265 |
| 16 | 9-11 | 173 | 268 |
| 16 | 12-13 | 176 | 270 |
| 16 | 14 | 178 | 271 |
| 16 | 15-18 | 181 | 274 |
| 16 | 19-20 | 184 | 276 |

**ሉቃስ**

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 1 | 1-4 | 1 | 23 |
| 1 | 5-25 | 4 | 26 |
| 1 | 26-38 | 5 | 27 |
| 1 | 39-45 | 6 | 27 |
| 1 | 46-56 | 7 | 28 |
| 1 | 57-66 | 8**ሀ** | 28 |
| 1 | 67-79 | 8**ለ** | 29 |
| 1 | 80 | 8**ሐ** | 29 |
| 2 | 1-7 | 9 | 30 |
| 2 | 8-20 | 11 | 31 |
| 2 | 21 | 12 | 31 |
| 2 | 22-38 | 13 | 31 |
| 2 | 39 | 16 | 34 |
| 2 | 40 | 17 | 34 |
| 2 | 41-50 | 18 | 34 |
| 2 | 51-52 | 19 | 35 |
| 3 | 1-2 | 20 | 36 |
| 3 | 3-6 | 21 | 36 |
| 3 | 7-14 | 22 | 37 |
| 3 | 15-18 | 23 | 38 |
| 3 | 19-20 | 34 | 47 |
| 3 | 21-23**ሀ** | 24 | 39 |
| 3 | 23**ለ**-38 | 3 | 24 |
| 4 | 1-13 | 25 | 40 |
| 4 | 14**ሀ** | 34 | 47 |
| 4 | 14**ለ**-15 | 37 | 50 |
| 4 | 16-31**ሀ** | 39 | 51 |
| 4 | 31**ለ**-37 | 42 | 53 |
| 4 | 38-41 | 43 | 54 |
| 4 | 42-44 | 44 | 55 |
| 5 | 1-11 | 41 | 52 |
| 5 | 12-16 | 45 | 56 |
| 5 | 17-26 | 46 | 57 |
| 5 | 27-28 | 47**ሀ** | 59 |
| 5 | 29-32 | 47**ለ** | 59 |
| 5 | 33-39 | 48 | 60 |
| 6 | 1-5 | 50 | 64 |
| 6 | 6-11 | 51 | 65 |
| 6 | 12-16 | 53 | 67 |
| 6 | 17-19 | 54**ሀ** | 67 |
| 6 | 20-26 | 54**ለ** | 68 |
| 6 | 27-30 | 54**ሠ** | 69 |
| 6 | 31 | 54**ሽ** | 73 |
| 6 | 32-36 | 54**ሠ** | 69 |
| 6 | 37-42 | 54**ሰ** | 72 |
| 6 | 43-49 | 54**ሽ** | 73 |
| 7 | 1-10 | 55 | 75 |
| 7 | 11-17 | 56 | 76 |
| 7 | 18-35 | 57 | 77 |
| 7 | 36-50 | 59 | 79 |
| 8 | 1-3 | 60 | 80 |
| 8 | 4 | 64**ሀ** | 84 |
| 8 | 5-18 | 64**ለ** | 84 |
| 8 | 19-21 | 63 | 83 |
| 8 | 22-25 | 65 | 90 |
| 8 | 26-39 | 66 | 91 |
| 8 | 40-56 | 67 | 93 |
| 9 | 1-5 | 70**ለ** | 98 |
| 9 | 6 | 70**ሐ** | 101 |
| 9 | 7-9 | 71**ሀ** | 101 |
| 9 | 10**ሀ** | 72**ሀ** | 104 |
| 9 | 10**ለ**-11 | 72**ለ** | 104 |
| 9 | 12-17 | 72**ሐ** | 105 |
| 9 | 18-21 | 82 | 120 |
| 9 | 22-25 | 83 | 122 |
| 9 | 26-27 | 84 | 123 |
| 9 | 28-36**ሀ** | 85 | 123 |
| 9 | 36**ለ** | 86 | 125 |
| 9 | 37-43**ሀ** | 87 | 126 |
| 9 | 43**ለ**-45 | 88 | 128 |
| 9 | 46-48 | 90 | 129 |
| 9 | 49-50 | 91 | 130 |
| 9 | 51-56 | 95 | 135 |
| 9 | 57-62 | 93 | 134 |
| 10 | 1-16 | 102**ሀ** | 146 |
| 10 | 17-24 | 102**ለ** | 147 |
| 10 | 25-37 | 103 | 147 |
| 10 | 38-42 | 104 | 148 |
| 11 | 1-13 | 105 | 149 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 11 | 14-36 | 106 | 150 |
| 11 | 37-54 | 107 | 151 |
| 12 | 1-12 | 108ሀ | 152 |
| 12 | 13-34 | 108ለ | 153 |
| 12 | 35-48 | 108ሐ | 154 |
| 12 | 49-53 | 108መ | 155 |
| 12 | 54-59 | 108ሠ | 155 |
| 13 | 1-9 | 109 | 156 |
| 13 | 10-21 | 110 | 156 |
| 13 | 22-30 | 113ሀ | 159 |
| 13 | 31-35 | 113ለ | 160 |
| 14 | 1-24 | 114 | 160 |
| 14 | 25-35 | 115 | 162 |
| 15 | 1-32 | 116 | 162 |
| 16 | 1-13 | 117ሀ | 164 |
| 16 | 14-31 | 117ለ | 165 |
| 17 | 1-10 | 117ሐ | 166 |
| 17 | 11-21 | 120ሀ | 170 |
| 17 | 22-37 | 120ለ | 170 |
| 18 | 1-14 | 121 | 171 |
| 18 | 15-17 | 123 | 173 |
| 18 | 18-30 | 124ሀ | 174 |
| 18 | 31-34 | 125ሀ | 178 |
| 18 | 35-43 | 126 | 180 |
| 19 | 1-10 | 127ሀ | 181 |
| 19 | 11-28 | 127ለ | 181 |
| 19 | 29-44 | 128ለ | 184 |
| 19 | 45-48 | 129ለ | 189 |
| 20 | 1-8 | 132ሀ | 193 |
| 20 | 9-19 | 132ለ | 194 |
| 20 | 20-26 | 133 | 197 |
| 20 | 27-40 | 134 | 199 |
| 20 | 41-44 | 136 | 201 |
| 20 | 45-47 | 137ሀ | 202 |
| 21 | 1-4 | 138 | 205 |
| 21 | 5-7 | 139ሀ | 206 |
| 21 | 8-19 | 139ለ | 207 |
| 21 | 20-24 | 139ሐ | 209 |
| 21 | 25-27 | 139መ | 211 |
| 21 | 28-33 | 139ሠ | 212 |
| 21 | 34-36 | 139ረ | 213 |
| 21 | 37-38 | 131 | 191 |
| 22 | 1-2 | 140 | 216 |
| 22 | 3-6 | 142 | 218 |
| 22 | 7-13 | 143 | 218 |
| 22 | 14-16 | 144 | 219 |
| 22 | 17-20 | 148 | 225 |
| 22 | 21-23 | 146 | 221 |
| 22 | 24-30 | 144 | 219 |
| 22 | 31-38 | 147 | 223 |
| 22 | 39-46 | 152 | 232 |
| 22 | 47-53 | 153 | 235 |
| 22 | 54ሀ | 155 | 239 |
| 22 | 54ለ-62 | 156 | 241 |
| 22 | 63-65 | 155 | 239 |
| 22 | 66-71 | 157 | 243 |
| 23 | 1-5 | 159 | 244 |
| 23 | 6-12 | 160 | 247 |
| 23 | 13-25 | 161 | 248 |
| 23 | 26-33ሀ | 163 | 253 |
| 23 | 33ለ-43 | 164 | 255 |
| 23 | 44 | 165 | 259 |
| 23 | 45 | 166 | 260 |
| 23 | 46 | 165 | 259 |
| 23 | 47-49 | 166 | 260 |
| 23 | 50-52 | 167ሀ | 261 |
| 23 | 53-54 | 167ለ | 263 |
| 23 | 55-56 | 168 | 263 |
| 24 | 1-8 | 171 | 265 |
| 24 | 9-12 | 172 | 267 |
| 24 | 13-32 | 176 | 270 |
| 24 | 33-35 | 177 | 271 |
| 24 | 36-43 | 178 | 271 |
| 24 | 44-49 | 183 | 275 |
| 24 | 50-53 | 184 | 276 |


### ዮሐንስ


| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 1 | 1-18 | 2 | 23 |
| 1 | 19-28 | 26 | 41 |
| 1 | 29-34 | 27 | 42 |
| 1 | 35-52 | 28 | 43 |
| 2 | 1-11 | 29 | 44 |
| 2 | 12 | 30 | 44 |
| 2 | 13-22 | 31 | 44 |
| 2 | 23-25 | 32ሀ | 45 |
| 3 | 1-21 | 32ለ | 45 |
| 3 | 22-36 | 33 | 46 |

| ምዕራፍ | ቁጥር | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 4 | 1-4 | 34 | 47 |
| 4 | 5-26 | 35ሀ | 47 |
| 4 | 27-38 | 35ለ | 49 |
| 4 | 39-42 | 35ሐ | 49 |
| 4 | 43-45 | 36 | 49 |
| 4 | 46-54 | 38 | 50 |
| 5 | 1-9 | 49ሀ | 62 |
| 5 | 10-18 | 49ለ | 62 |
| 5 | 19-47 | 49ሐ | 63 |
| 6 | 1-3 | 72ለ | 104 |
| 6 | 4-13 | 72ሐ | 105 |
| 6 | 14-15 | 73 | 108 |
| 6 | 16-21 | 74 | 108 |
| 6 | 22-59 | 76ሀ | 110 |
| 6 | 60-71 | 76ለ | 112 |
| 7 | 1 | 77 | 113 |
| 7 | 2-9 | 94 | 134 |
| 7 | 10 | 95 | 135 |
| 7 | 11-31 | 96ሀ | 136 |
| 7 | 32-52 | 96ለ | 137 |
| 7 | 53-8:11 | 97 | 138 |
| 8 | 12-20 | 98 | 139 |
| 8 | 21-30 | 99ሀ | 139 |
| 8 | 31-59 | 99ለ | 140 |
| 9 | 1-7 | 100ሀ | 141 |
| 9 | 8-12 | 100ለ | 142 |
| 9 | 13-34 | 100ሐ | 142 |
| 9 | 35-38 | 100መ | 144 |
| 9 | 39-41 | 100ሠ | 144 |
| 10 | 1-18 | 101ሀ | 144 |
| 10 | 19-21 | 101ለ | 145 |
| 10 | 22-39 | 111 | 157 |
| 10 | 40-42 | 112 | 159 |
| 11 | 1-16 | 118ሀ | 166 |
| 11 | 17-44 | 118ለ | 167 |
| 11 | 45-54 | 119 | 169 |
| 11 | 55-12:1 | 128ሀ | 183 |
| 12 | 2-8 | 141 | 217 |
| 12 | 9-11 | 128ሀ | 183 |
| 12 | 12-19 | 128ለ | 184 |
| 12 | 20-36ሀ | 130ሀ | 190 |
| 12 | 36ለ-50 | 130ለ | 191 |
| 13 | 1-20 | 145 | 220 |
| 13 | 21-30 | 146 | 221 |
| 13 | 31-38 | 147 | 223 |
| 14 | 1-31 | 149 | 226 |
| 15 | 1-17 | 150ሀ | 228 |
| 15 | 18-16:4 | 150ለ | 228 |
| 16 | 5-15 | 150ሐ | 229 |
| 16 | 16-22 | 150መ | 230 |
| 16 | 23-33 | 150ሠ | 230 |
| 17 | 1-26 | 151 | 231 |
| 18 | 1 | 152 | 232 |
| 18 | 2-12 | 153 | 235 |
| 18 | 13-14 | 154 | 238 |
| 18 | 15-18 | 156 | 241 |
| 18 | 19-23 | 154 | 238 |
| 18 | 24 | 155 | 239 |
| 18 | 25-27 | 156 | 241 |
| 18 | 28-38 | 159 | 244 |
| 18 | 39-19:16ሀ | 161 | 248 |
| 19 | 16ለ-17 | 163 | 253 |
| 19 | 18-27 | 164 | 255 |
| 19 | 28-30 | 165 | 259 |
| 19 | 31-38 | 167ሀ | 261 |
| 19 | 39-42 | 167ለ | 263 |
| 20 | 1 | 171 | 265 |
| 20 | 2-10 | 172 | 267 |
| 20 | 11-18 | 173 | 268 |
| 20 | 19-25 | 178 | 271 |
| 20 | 26-31 | 179 | 272 |
| 21 | 1-25 | 180 | 273 |


## የሐዋርያት ሥራ


| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | 3-8 | 183 | 275 |
| 1 | 9-12 | 184 | 276 |
| 1 | 18-19 | 158 | 244 |


## 1ኛ ቆሮንቶስ


| | | | |
|---|---|---|---|
| 11 | 23-26 | 148 | 225 |
| 15 | 5ሀ | 177 | 271 |
| 15 | 5ለ | 179 | 272 |
| 15 | 6 | 181 | 274 |
| 15 | 7 | 182 | 275 |